# ማዕበል

## የአብዮቱ ማግሥት



ከብርሃኑ ዘርይሁን

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ማዕበል

## የአብዮቱ ማግሥት

ታሪክ ቀመስ ልበ ወለድ

ከብርሃኑ ዘርይሁን

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ማውጫ

ምዕራፍ አንድ....................................................3
ምዕራፍ ሁለት.................................................... 31
ምዕራፍ ሦስት....................................................65
ምዕራፍ አራት....................................................108
ምዕራፍ አምስት....................................................154
ምዕራፍ ስድስት....................................................193
ምዕራፍ ሰባት....................................................218
ስለደራሲው በጥቂቱ .................................................... 268

# ምዕራፍ አንድ

ማስረሻ ከአማኑኤል ሆስፒታል በር ሲወጣ ያጋጠመው የአዲስ አበባ ሕይወት ብዙ ዘመን ታውሮ ዐይኑ ድንገት እንደ በራ ሰው ልቡናውን የሚያጥበረብር ሆነበት። በሆስፒታሉ በቆየበት ጊዜ ብዙ የተለወጠ ሁናቴ ውጪ እንደሚጠብቀው ግምት ነበረው። አልፎ አልፎ ከራዲዮ እንደ ሰማው ከጋዜጣው እንዳነበበው፥ ሆስፒታል ያስገቡት ጓደኞቹ ከስንት አንድ ጊዜ ሲያመቻቸው ሊጠይቁት ሲመጡ እንዳጭወቱት ትልልቅ ፋብሪካዎችና የገንዘብ ድርጅቶች በመንግሥት መወረሳቸውን የገጠር መሬት፥ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የሕዝብ ንብረት ሆኖ ጭሰኛና ምሪተኛ መቅረቱን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የሚባል መመሪያ መታወጁን ያውቅ ነበር።

የውይይት ክበቦች መቋቋሚያ ዐዋጅ እንደ ወጣም ጤንነታቸው በመጠኑ የተመለሰውና በፖለቲካ ወይም በባለ ሥልጣኖች ተቀናቃኝነት አማኑኤል ሆስፒታል እንዲገቡ የተደረጉ ከሞላ ጐደል ደህና ሥራ የነበራቸው ጥቂት ታካሚዎች፥ የወይይት ክበብ ለመመሥረት ሞክረው ነበር። እነዚህ ጥቂቶች ታካሚዎች - ማስረሻን ጨምሮ - ተሳሰቡና አንድ ጸሐፊና አንድ ደንብ አርቃቂ ኮሚቴ መረጡ። በመጀመርያው ሳምንት፥ ደንቡ በንባብ ተሰምቶ ጸደቀ። በሁለተኛው ሳምንት እነዚህ ጥቂት ታካሚዎች የመጀመርያውን ውይይት አካሄዱ። በተከታዩ ሳምንት ግን፥ ጥቂት ሰዎች ለብቻቸው ስብሰባ የሚያደርጉ መሆናቸው ወሬው ተዳርሶ ኖሮ፥ ውይይት በጥሞና ያደርጉ የማይችለው ሁሉ ተከማቸና ትርምስ ተፈጠረ። ተናጋሪና አድማጭ ሳይለይ፥ አርእስት - ጉዳይ ሳይወሰን፥ ሁካታ ብቻ ሆነ። ከነዚህም አልፎ፥ ሰደብከኝ መብቴን ነካህ፥ በሚል ሰበብ ውይይቱ ወደ አንባጓሮ አዘነበለ። በተለይ በሁለት ታካሚዎች መካከል የተነሣው ክርክር የተሰበሰበውን ታካሚ ከሁለት ከፍሎ ስላፋጠጠው አደገኛ ሁናቴ ከመፈጠሩ በፊት የሐኪም ቤቱ ሠራተኞችና ዘበኞች መሐል ገብተው ስብሰባውን በመበተን አበረዱት። ውይይቱ ከዚያ በኋላ አልቀጠለም።

በምትኩ ከሦስተኛና ከማገገሚያ ክፍሎች የሚፈልጉ ራዲዮና ጋዜጣ ማስገባት የሚችሉ መሆናቸው ተነግሮ የአብዮቱ ሂደት እንደ ተቻለ በዜና ማሰራጫዎች እንዲከታተሉ ተደረገ።

ማስረጃ የአእምሮ ጤንነቱ ያም ባይሆን የአእምሮ ሚዛናዊ አስተሳሰቡ ተመልሶለት፥ የት ቦታ እዳዘቀጠ የተገነዘበው ያን ጊዜ ነበር። ከዚያም በኋላ፥

ጓደኞቹ አልፎ አልፎ በሚያመጡለት ጋዜጣና መጻሕፍት አማካይነት የአብዮቱን ሂደት ለመከታተል ሲሞክር ቆይቶ ነበር።

...... የሆስፒታሉን ግቢ ወጥቶ እህል በረንዳ ወደሚያዘልቀው ጐዳና ሲገባ ያጋጠመው ሁናቴ ግን ከጠበቀው ውጭ ሆነበት። የቆርቆሮ አጥር፣ የግቢ በር፥ የቤት ግድግዳ የግንብ አጥር ሁሉ ልዩ ልዩ ጽሑፍ ተልቅልቆበታል። «ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ለዘለዓለም ይኑር » ከሚለው አጠገብ፤ «ፋሽስታዊ ደርግ ይውደም » የሚል በቀይ ቀለም ተጽፏል። «ሐቀኛ ወጣቶች ከሰፊው ሕዝብ እየተማሩ መልሰው ያስተምራሉ » የሚለው ቀጥሎ ያለው «ዘመቻው ፋሺዝምን በገጠር ለማስፋፋት ነው » ይላል።

-ግልገል ፋሺስቶች ይደመሰሳሉ!

-ባንዳ ምሁራን በጭቁን ሕዝብ ክንድ ይደቆሳሉ!

-የአድኃሪያን መንፈራገጥ ለማላላጥ!

-ብሕሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን የሚቃወሙ ይውደሙ!

የጽሑፉ ሐሳቦች መምታታት የአጻጻፍ መዘበራረቅ መደራረብና መለያየት በአብዛኛው

መሞነጫጨር ለማስረሻ አማኑኤሎች ቀለምና ብሩሽ ተሰቷቸው በከተማው ተለቀውበት ያደሩ መስሎ ታየው። ጥቅማቸው ከተነካባቸው መኳንንት መሳፍንትና የቀድሞ ባለሥልጣኖች ሌላ የደርግን ሥልጣን መያዝና የሚወስደውንም እርምጃ ሁሉ የሚቃወም ቡድን በኅቡዕ ጓደኞቹ አንድ ቀን ሊጠይቁት መጥተው ሳለ እንደ ዋዛ በሹክሹክታ ነግረውት ነበር። አዲስ አበባን እንደዚህ በጽሑፍ እስከ ማላበስ ይደርሳሉ ብሎ ግን አላሰበም ነበር። እንደ የካቲት ሥልታን በባዶ ሜዳ መዋለሉ እየተደገመ ይሆን? የሚል ጥያቄ በአእምሮው መጣ። ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ማስረሻ ቀደም ብሎ ፈቃድ እየጠየቀ አለ መውጣቱ ትንሽ ቆጨው። አሁን እንደዚህ ድንገተኛ ዱብ ዕዳ አይሆንበትም ነበር። በፈቃድ ለመውጥት ያልፈለገበት፥ ባንድ በኩል የሚያውቀው ሰው እንዳያጋጥመው በማፈር ሲሆን በሌላ በኩል ወይ ድኜ እንድያየን እወጣለሁ፥ ወይ ከዚሁ ቀልጨ እቀራለሁ በሚል እልህ ጭምር ነበር። አሁን ታዲያ፥ ሁለቱም አጉል ስህተት መስሎ ተሰማው። የፈሰሰ ውሀ አይታፈስ እንዲሉ ስላለፈው ምንም ነገር ማድረግ ስለማይቻል እንዳመጣበት የአሁኑን መጋፈጥ ግድ ሆነበት።

ማስረሻ፥ ወትሮም ማርካቶን አይወደውም። አዲሱን የህል በረንዳ አልፎ ወደ መሐል አዲስ ከተማ መግባት ሲጀምር ከአማኑኤል ሆስፒታል ይበልጥ ተተራመሰበት፥ ተበደላለቀበት። «አይ ማርካቶ » የሚለው የጸጋዬ ገብረ መድኅን ግጥም ትዝ አለው።

.... የኡኡታው የጡሩምባው የጩኸቱ የፊሻው ሣግ

የሠው የመኪና የከብት፣ የፍግ የቁሳቁስ ትንፋግ

ሲገፋተር ሲመዠረጥ፥ ላቦት ለላቦት ሲላላግ

ትንፋሽ ለትንፋሽ ሲማማግ

አባ ሸብሩ ማርካቶ ያለውን በገፍ አጣጥቶ

የሌለውን ከሌለበት አስጐልጉሎ አስወጥጦ

ስንቱን ከዳር ዳር አዛምቶ

በግድም በውድ አስማምቶ

አገርን ካገር አካትቶ

ሁሉን አቅፍ ባይ ማርካቶ......

የአሁኑ የማርካቶ ትርምስና ሸብር ግን የንግድ ልውውጥ የገበያ እንቅስቃሴ የኪስ አውላቂዎች ግርግር ብቻ አልነበረም። በሰው ሁሉ ላይ ሌላ ስሜት፥ ሌላ አስጨናቂ ጉዳይ መስፈኑ በግልጽ ያስታውቅ ነበር። ከፊሉ ከኋላው ጦረኛ እንደ መጣበት እየተገለጠ እግሬ አውጪኝ የሚሸሽ ይመስላል። አንዳንዱ አንዳች አሰቃቂና አጸያፊ ነገር እንዳጋጠመው ግንባሩን ደፍቶ ፊቱን ጨፍግጎ ላመል ያህል የጐሪጥ እያጨለገ ያሰግራል። ሌላው ገበያ መውጣቱን ለማስመስከር ይመስል የያዘውን ዕቃ አንቀርፍፎ እያሳየ ዐይኑን አፍጥጦ፥ ጥርሱን በጥርሱ ነክሶ ሲራመድ የደነበረ እንስሳ ይመስላል። በዚህ መካከል ነብር ገዳይ፣ ዝሆን ገዳይ፣ አንበሳ ገዳይ የሚያስንቀውና አዲሱ የጃፓን ማበጠሪያ ቀርቶ የመንዝ መንሽ ሊገባበት የማይደፍረው የሚመስል «አፍሮ » የተሸከሙ ወጣቶች ሦስት አራት ሆነው እየተንጐራደዱ አላፊ አግዳሚውን ይገረምማሉ። ይገላምጣሉ። ለለአንዳንዱ ፈገግታ አደፋፋሪ ገጽታ ያሳዩታል። ሌላውን በአስተያየታቸው አፈር ድቤ ያስገቡታል። አቀርቅሮ መሮጥ እስኪ.ቃጣው ድረስ።

ማስረሻ ይህንን ሁሉ በአጭር ጊዜ ሲያስተውል፥ ቀፈፈው። በቀይ በአረንጓዴ በወይን ጠጅ እንደ ተለቀለቀው ግድግዳና አጥር ሰውም ሁሉ በድንገት ተለዋወጠበት። አልዳነም? ወይስ ሌላው ሁሉ እንደርሱ ሁኗል ማለት ነው? ሁለቱም ግምት አልጣመውም። ዙሮ - ዙሮ - ያው ነው። እርሱ ተሽሎት ከዚያ የሚያየውን ሰው ሁሉ አእምሮ ይህ አብዮት አናውጦት ከሆነ ትንሽ ቆይቶ እርሱም መቀላቀሉ ሳይቀር ነው። በሰው መካከል ከኖረ የወቅቱ ስሜት ይጋባበታል - ወይ መምሰል ግድ ይሆንበታል። ከዚህ ውጪ ሊሆን የሚችልበት ምንም መንገድ እንደሌለ ተሰማው።

ወደ ሰፊው የዕብድ አደባባይ ከመግባት በዚያው በጠባቡ በዕብዶች ሆስፒታል መቆየቱ ይሻላል?

ከማያውቁት መልአከ የሚያውቁት ሰይጣን ተብሎ የለ? የሚል ሐሳብ መጣበት። ግን የመጣው ቢመጣ ተመልሶ እንደማይገባ ይሰማው ነበር። ከአንድ ወር በፊት የወሰነው ጉዳይ ነበር። ይህ ዕድል እንደዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚገጥመው በጊዜው ስንኳ እርግጠኛ አልነበረም። ጥያቄውን ያቀረበው በንዴት ስሜት ነበር። አሁን መልሶ ሲታወሰው ስለ ውሳኔው ግራ ገባው......

.....አንድ ቀን ከአንድ በሽተኛ ጋር በቆርኪ ዳማ ሲጫወቱ ከሄደ በኋላ እየመለሰ ከተባለ በኋላ እየፈረ፥ ሁለት ሦስት ጊዜ ሄዶ በር ከከፈተ በኋላ፥ «አይ! እንደ ገና! እንደ ገና! እያለ ቢያስቸግረው ማስረሻ ብሽቅ ብሎ «ወትሮውንስ ከዕብድ ጋር! » ሲል ጨዋታውን አቋረጠ።

«ከአስመሳይ ተራማጅ እንደሚባለው ከዐውቆ አበድ እንደኔ ያለው እውነተኛ በሽተኛ ይሻላል » ሲል በፌዝ መለሰለት።

«ምን ማለትህ ነው?« ባንድ በኩል ከሌሎች የተሻለ ጤነኛ መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ በተሰጠው ስያሜ ማስረሻ አልተቆጣም። እንዲያውም በአጠያየቁ እንደ መኩራራት ብሎ ነበር።

«የማናውቅህ መሰለህ? » በሽተኛው ከንፈሩን ለጥጦ በግልምጫ መልክ አስተዋለው።

«ምኑን? » ማስረሻ አሁንም እንደ ተኩራራ ነበር።

«መሽሽግህን ነዋ! »

«ከምን ነው ደሞ የምሸሸገው? » ማስረሻ ነገሩ ስላልገባውና የዕብድ እንቆቅልሽ ስለ ሆነበት መሣቅ ቃጣው።

«ከደርግ ነዋ! »

«እንዴት? »

«አንተኑ እንጠይቅህ እንጂ! ምንም በሽተኛ ብንሆንኮ እስከዚህም አእምሮዋችንን ጨርሰን ያልሳትን አለን። እንሰማለን። እናያለን። ታዲያ አንተ የልጅ ጉግሣ ካቢኔ አባል አልነበርኩም ትላላህ? »

«ብሆንስ? » ነገሩ አሁን ማስረሻን ጥቂት እያናደደው ሄደ።

«በዕብደት ስም ከዚህ ተደብቀህ ባታመልጥ ኖሮ እስከ አሁን ድረስ ከጌታህ ጋር አብረህ ዘለዓለማዊ ሐኪም ቤት ወርደህ ነበራ! ያም ባይሆን ይህ አይቀርልህም ነበር። » በእስራት መልክ ክንዶቹን አጣምሮ አፈዘበት። «ስለዚህ ከእኛው ጋር እኛኑ መስለህ ትኖራለህ። »

አማኑኤል የገባው ከቅጣት ለማምለጥ ነው ተብሎ ተወርቶበት ከሆነ ሐሰት መሆኑን ተከራክሮ ለማሳመን ከጀለውና «ከምድረ በሽተኛ ጋር ምን አዳረቀኝ! » ሲል መልሶ ተወው ከአማኑኤል ለመውጣት ቅንጣት የማይፈራ መሆኑን ያሳያቸዋል! «ኩስ በእግርህ መርገጥ በጣትህ እየጠነቆልክ በአፍንጫህ ስታሸት ከዚህ ሕይወትህን ታሳልፋለህ! እኔ ደሞ - » ንግግሩን ሳይጨርስ ወደ ሆስፒታሉ ቢሮ ሄደ።

ጤንነታቸው ተሻሽሏል የተባሉት በሽተኞች ዋናውን ሐኪም በቀላሉ የማነጋገር መብት አላቸው።

«ዶክተር ሕይወቴን ከዚህ እንደዚህ መጨረስ አለብኝ? ምንድን ነው የኔ ተስፋ? » ሲል ማስረሻ ባልወጣለት ንዴት ጫን ጫን እየተነፈሰ ጠየቀ።

«እውነቱን ለመናገር በእርግጠኛነት ለመመለስ በጣም አስቸጋሪ ነው። » ዶክተሩ ማስረሻን በአዘኔታ አስተዋለው። «የሕይወትና የሞት ጉዳይ፥ የጤንነትና የበሽታ ጉዳይ፥ እንደ ሒሳብ ሁለትና ሁለት ብለን በእርግጠኝነት መልስ የምንሰጥበት አይደለም። የቃላት ጉዳይ ብቻ አይደለም። ውስብስብ ነው። ገና በመዳሰስ፥ በመዳበስ ላይ የምንገኝበት ምሥጢር ነው። ለምሳሌ ጡንቻው ግርማ ቸሩን የመሰለው ስንኳን ሕመም ጥይት የማይጥለው የሚመስለው በትንሽ ብርድ ድንገት ድብን ሲል እናያለን። ሌላው ደግሞ በቃው ተብሎ የከፈን

ጨርቅ ተገዝቶ ሲጠበቅ ሕክምናም ሳይደረግለት ከመቃብር የወጣ ዐፅም መስሎ እንደ ገና ነፍስ ዘርቶ፥ በማናውቀው ምሥጢር ጤንነቱን አግኝቶ ብዙ ዓመት ይኖራል።

«ግን የአካልና የአንጐል ሕመም አንድ ዓይነት ስላልሆነ ጥያቄየ አልተመለሰልኝም » አለ ማስረሻ እንደ ዋዛ።

«ያው ነው። እንደዚያውም አንጐል ከሁሉም የበለጠ ገና ውስብስብ ምሥጢር ነው። ሐኪሞች ስለ አንጐል የሚያውቁት በጣም ጥቂት ነው። በውቅያኖስ ምሥጢር ውስጥ የጠበታ ያህል። ስለዚህ፥ እንደ አካል ሁሉ ስለ አእምሮ ጤንነትና በሽታም ከቶ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። አንጐሉ እንደ አለት የማይናወጽ ይመስል የነበረውና የረጋ ባሕርይ ያለው ሰው ባልታወቀ ምክንያት ድንገት ጨርቁን ሲጥል እናያለን። ወይም ደግሞ፥ ሆስፒታል ሲመጣ ሰው ከአውሬ መለየት እስኪያቅተው ድረስ አእምሮውን ፍጹም ስቶ የነበረው በሽተኛ እንደ ተአምር በሚቆጠር ሁናቴ ጤንነቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሲመለስለት እናያለን። በሕክምና ዓለም እንደ ሒሳብ የማይሰሉ ብዙ ነገሮች ያጋጥሙናል። ስለዚህም ነው፥ ሐኪሞች እስከ መጨረሻው ድረስ ተስፋ የማይቆርጡት ወይም እርግጠኞች የማይሆኑት። ጥያቄህን የመለስኩህ መስለኝ። » ሐኪሙ በማበረታታት ሁናቴ ማስረሻን ትክ ብሎ ተመለከተው።

«በአጠቃላይ አዎ! በተለይ እኔን በሚመለከት ረገድ ግን አሁንም አልተመለሰልኝም። »

«የአንተም ቢሆን ከአጠቃላዩ መልስ የተለየ ሊሆን አይችልም። » ዶክተሩ ሲጋራ አውጥቶ የራሱን ከማቀጣጠሉ በፊት ማስረሻን ጋበዘው። «ሕክምናውን በሚመለከት ረገድ ከእንግዲህ እስከዚህም የምናክለው ነገር የለም። ከአሁን ቀደም እንደ ነገርኩህ መሠረታዊና ጠንቀኛ የሆነ የአንጐል ሕመም አልነበረብህም። የለብህም። በአራዳው አነጋገር » ዶክተሩ ሌባ ጣቱን ከጭንቅላቱ ላይ እንደ ማዞር አደረገ፥ «ዋናው ብሎንህ አልወለቀም። ወይም ሽቦው አልተበጠሰም። በሽታህ ከሕይወት ለመሸሽ መሞከር ነበር። ምን ማለት ነው ባንድ በኩል የእንጀራ አባትህ ጉዳይ ከሕሊናህን በወቀሳ ሲያሠቃየው ከእርሱ ጋር የሚስትህ በደል ሲያሳርርህ መንፈስህ ሁለቱንም መሸከም ሲያቅተው፥ የሚያስብ አእምሮህ ሁሉንም ነገር ለመርሳት፥ የሆነውን ነገር ሁሉ እንዳልሆነ ለመቁጠር፥ ከኤሊ ቅርፊት የጠጠረ ምሽግ ሠርቶ ወደ ውስጥ ገባ። መጠጡ ይህንን ምሽግ የገነባህበት አንዱ መሣሪያህ ነበር። ሰውነትህ ሲደክም፥

ሕሊናህ እንደ ፈለገው አእምሮህ አብሮ አንቀላፋ። ሳተ። በሌላ አነጋገር የደረሰብህ በሽታ፥ አዳኝም የለም ጠመንጃም የለም ብላ ጭንቅላቷን አሸዋ ውስጥ እንደ ቀበረችው ሰጐን ውሳኔ ዓይነት ነበር።

«እና እኔ ከተደበቅሁበት አሸዋ፥ ወይም ቅርፊት ወጥቻለሁ? አልወጣሁም? » ሲል ማስረሻ ጠየቀ።

«ምን እናውቃለን! » ዶክተሩ ጥያቄውን ለማቃለል እንደ መቀለድ ቃጣው። «እኛ ራስክን ከቀበርክበት አሸዋ ወይም ከመሸግህበት ቅርፊት በግድ ፈርቅቀን ልናወጣው አንችልም። ማድረግም የለብንም። ያደረግነው ተደብቀህ መሽገህ ዘለዓለም መኖር እንደማትችል የመስኮቱን ጭላንጭል ማሳየት ብቻ ነው። በማኅበራዊ ሠራተኖች በኩል ጭላንጭሉን አይተሃል። በአልኮልና በምግብ እጦት ምክንያት የደረሰብህ የአካል ድካምህ በመጠኑ ተመልሷል። አሁን እንግዲህ ራስህ መጣር አለብህ። »

«አሁንም ጥያቄው አልተመለሰልኝም። ድኛለሁ? አልዳንኩም? እርግጠኛ መልስ! » ማስረሻ እንደ መብሸቅ እየቃጣው በዶክተሩ ላይ አፈጠጠ።

«ሒሳብ አይደለም ብየሃለሁ። »

«እና? »

«ከዚህ በኋላ የራስህ ጉዳይ ነው። »

«ከፈለግሁ ምንም ጊዜ መውጣት እችላለሁ ማለት ነው? » ማስረሻ ዶክተሩን አፍጥጦ ተመለከተው።

«እችላለሁ? » ማስረሻ ፍርጥም አድርጐ መልሶ ጠየቀ። የበሽተኛው አሽሙር ሲታሰበው እንደ ገና በሸቀ።

ዶክተሩ ወዲያውኑ መልስ አልሰጠም። የሚያስብ፥ የሚያመነታ መሰለ።

«እችላለሁ ወይ! » ማስረሻ በማፋጠጥ ጥርሱን አገጠጠ።

ዶክተሩ መነጽሩን አነሣና የአፍንጫ መዋረጃውንና የዐይኖቹን መጋጠሚያ ፈተገ።

«ትችላለህ። ግን ራስህም አስብበት » አለ የታከተ በሚመስል ድምፅ።

«አመሰግናለሁ! » ማስረሻ ተፈናጥሮ ከቢሮው ወጣ።

ከሆስፒታሉ ልውጣ? ወይስ ከዚሁ ልቆይ? - በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ማስረሻ ለብዙ ጊዜ ከራሱ ጋር ተሟገተ። ጥያቄው፥ ሐኪሙ እንዳለው፥ መቆየቱ የሕክምና ለውጥ ማምጣቱና አለማምጣቱ ብቻ አልነበረም። ለጊዜው የተሻለው መሆኑን አምኖ ተቀብሏል። ከወጣ በኋላ እንደ ገና ተመልሶ ያው ቢሆንስ?

## ፪

ለሥጋቱ ብዙ ምክንያቶች ነበሩት። ሥራ የለውም። እንዴት ይኖራል? አማኑኤል መግባቱ ሥራ እንዳይዝ እንቅፋት ሳይሆንበት ይቀራል? ወይንስ ሊደብቀው ነው? ከደበቀውስ ከፊተኛው ሥራው ያውም ከከፍተኛ ሹመት የተፈናቀለበትን ምክንያት እንዴት ያስረዳል? እርግጥ በሌላ ዓይነት ሕመም ሊያሳብብ ይችላል። ግን በአብዮቱ ትንቅንቆሽ ምክንያት ቁጥጥሩ ጥብቅ እየሆነ መሄዱን ስምቷል። የሐኪም ማስረጃ ወረቀት ይጠየቅ ይሆናል። ከየት አባቱ ያመጣል? ሌላም ሥጋት አብሮ ይታሰበዋል። የመኖሪያ ቤት ነገር። ይኖርበት የነበረው ቤት ሌላ ሰው እንደ ተከራየው ጓደኞቹ አይተው ነግረውታል። የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ከሆነ ወዲህ ደግሞ ቤት የሚያከራየው መንግሥትና ቀበሌ ነው። ተራው ሁለት ሦስት ዓመት ያስጠብቃል ይባላል። ጓደኞቹ ካላስጠጉት በስተቀር ሌላ መግቢያ የለውም። እርግጥ አፍ አውጥተው እምቢ አይሉት ይሆናል። ከልብ ፈቃደኞች ስለ መሆናቸው ግን እርግጠኛ አይደለም።

የተደቀኑበት አማራጮች በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ።

ባንድ በኩል ሥራ የለውም፥ መኖሪያ ቤት የለውም። ከውጪኛው ዓለም የሚጠብቀው ጨለማ ዕድል፥ ቢቻል አዝን ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች እንደሚባለው፥ ለችርቻሮ፥ ስለ ቀድሞው ጓደኝነት ብለው ከረዱት ጓደኞቹ ዘንድ ሳይፈለጉት እንደ መዥገር ተጣብቆ የኑሮዋቸው፥ የሕይወታቸው ሸክም መሆን ነው። የሕይወት አጋጣሚ ከእርሱ ጋር ያገናኛቸውን ቀን እየረገሙ፥ እሱንም በሆዳቸው እየተራገሙ፥ ምናልባትም ይሉኝታ የሚባል ፈሊጥ አለና፥ ብሽቀታቸውን በሆዳቸው እያፈኑ እስከ ተወሰነ ጊዜ ይችሉት ይሆናል። እስከ መቼ? አንድ ወር? ሁለት ወር? ቀነ ቀጠሮው ልዩነት አያመጣም። አንደኛ በእነርሱ መሰላቸት ሕይወት ውስጥ ዘወትር መኖር አለእብት። ከዚህም በቀር አንድ ቀን፥ «ማስረሻ እናዝናለን፤ እኛ የተቻለንን ረድተንሃል። ግን ኑሮ እየ

ተወደደ ሄደ። ማንም ደግሞ ራሱን መቻል እንጂ አንዱ ሌላውን ይዞ መስመጥ የለበትም። ስለዚህ......ስለዚህ...... » ውጣልን ለማለት ድፍረቱ አንሷቸው ወይም ያው ይሉኝታው ይዟቸው በጥላቻ ይመለከቱት ይሆናል። ከዚህ የባሰ ደግሞ ከመጀመሪያውኑ በረንዳ እየተኛ፥ አላፊ አግዳሚውን ምፅዋት መለመን ነው።

በአንጻሩ ደግሞ አሁን የሚገኝበት ዓለም አለ። እንደ ስሙ አማኑኤል ሆስፒታል በመሠረቱ ሆስፒታል ነው። ይዳኑም አይዳኑም ይሻላቸውም ይባስባቸውም የአእምሮ በሽተኞች እንደ ነገሩ ሕክምና የሚያገኙበት ነው። ነገር ግን፥ ክቡር ፍጡር የሆነው ሰው ወደ አውሬ ደረጃ ዝቅ ብሎ የሚገኝበት፥ አእምሮው ደህና ለሚያስብ መኖር ቀርቶ ማየቱ፥ ሰው መሆንን እስኪጠላ የሚያሳቅቅበት ሥፍራ ነው።

ጠቅላላው የሆስፒታሉ ግቢ፥ እንደ በሽተኞቹ ዓይነት በሦስት ደረጃ የተከፈለ ነው። ከሁሉም የተሻለው እነ ማስረሻ ያሉበት ሦስተኛው ደረጃ ቢሆንም፥ በዚህም ክፍል ሲጋራ ስጠን እያሉ ጉብኝን የሚያስቸግሩ፥ ከጊዜ ጊዘ እየሳቱ የሚቀባጥሩ አገግመዋል ከተባሉ በኋላ ድንገት እያገረሸባቸው ጸጥታ የሚያውኩ ወይም ከቀን ቀን ከሳምንት ሳምንት ከወር ወር በዝምታ ተውጠው ሌላውን ኀዘን ላይ የሚጥሉ ሞልተውበታል።

ሁለተኛ ደረጃ አስቂኝ እየመሰለ፥ በሐዘኔታ አንጀት የሚያኮማትር ትርኢት የሰፈነበት ክፍል ነው። በዚህ ክፍል የሚገኙት ልብሳቸውን አይጣሉ እንጂ የአእምሮ ግንዛቢያቸውን ጨርሶ ያጡ ናቸው። በአርባ ዓመቱ እንደ አምስት ዓመት ሕፃን የሚኮላተፈው አለ። ያገኘውን ሁሉ ዕብድ እያለ የሚያሽሟጥጥ፥ ቀኑን ሙሉ በስንጥር ጥርሱን የሚነቅሰው ቀኑን ሙሉ እንደ ቅዘት ልጅዋን ስትጠራ የምትውለው ቀኑን ሙሉ ዝንብ እያደነ የሚገድለው አሉ። አብዛኞቹ የአእምሮ ግንዛቤያቸውን መልሶ የማግኘት ተስፋ የላቸውም። በቅዠት ዓለማቸው ውስጥ እንደ ሰመጡ ዕድሜያቸውን ይጨርሳሉ።

ከሁሉም የከፋው ግን የአንደኛው ደረጃ ክፍል ነው። ይኸኛው በመጠኑ የሚለያዩ ሁለት ክፍሎች አሉት። በስተምዕራቡ በኩል ያለው ክፍል፥ አእምሮዋቸው ተቃውሶ ወንጀል የፈጸሙ ወይም አሰቃቂ ወንጀል ከፈጸሙ በኋላ አእምሮዋቸው ጨርሶ የተቃወሰ በዚያው በአራዳው ቋንቋ ‹ዋናው ብሎናቸው የወለቀ› አደገኛ የሚባሉት በሽተኞች የሚገኙበት ክንፍ ነው። (ልጁን አርዶ የቀበረው አባት፥ ደመኛውን ገድሎ ደሙን ሲጋት የተያዘው በቀለኛ፥ የሕፃናት ሕይወት የሚያስገብረው ቃልቻ) ሕይወት የማጥፋት ዝንባሌ ያለው

አደገኛ በሽተኛ በዚህ ክፍል ይገኛል። አብዛኞቹ በሽተኞች በእግር ብረት ይታሰራሉ። እግር ብረቱ ሲቅጨለጨል ገና ከሩቅ ይሰማል። የዚሁ ክፍል ሌላ ክንፍ ፈጽሞ የመዳን ተስፋ የሌላቸው፥ የአእምሮ ግንዛቤያቸው ከአራዊት ደረጃ ያልተሻለ በሽተኞች የሚገኙበት ነው። ሁሉም ከእናታቸው ሆድ እንደ ወጡ ዕርቃነ ሥጋቸውን ናቸው። አንዳንዱ አልጋውን ትቶ ከአልጋው ሥር ይንከባለላል። አንዳንዱ በወለሉ ላይ ተፈነጋግሏል። ወይም ኩምትር ብሎ ተቀምጧል። እንደ ወጋግራ ቀኑን ሙሉ ከአንድ ሥፍራ ተገትሮ የሚውል በሽተኛም አለ። ከቤቱ ውጪ ዕርቃናቸውን ከአፈር ላይ ሲንከባለሉ የሚውሉት ብዙ ናቸው።

ማስረሻ እንደ መሻል ብሎት በግቢው ውስጥ ሲዘዋወር ይህንን ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ተመለከተ የተሰማው ድንጋጤ ይህ ነው አይባልም። ዐይኑን ማመን ነበር ያቃተው። ልብሳቸውን ጥለው፥ በየአደባባዩ ዕርቃናቸውን የሚያዘወትሩ አልፎ አግዳሚውን የሚያስበረግጉ የአእምሮ በሽተኞች ከዚያ በፊትም ደጋግሞ አይቷል። ነገር ግን፥ በብረት ውስጥ እንደ ታጐተ ከብት ብዙዎቹን በአንድ ግቢ ውስጥ ሲመለከታቸው ይህ ነው የማይባል ስሜት ከእግር እስከ ራሱ ነዘረው። ልክ ኮረንቲ እንደ ጨበጠ ያህል። ሌላ ጊዜ በተቻለ መጠን ከዚያ ክፍል ራሱን ቢያርቅም ትርኢቱ ከአእምሮው ውስጥ ሊደበዝዝ አልቻለም። እንደ ቀን ብርሃን ቁልጭ ብለው በሐሳቡ በታዩት ቁጥር መላ ሰውነቱ በፍርሃት እንደ መንቀጥቀጥ ይላል። እሱም ቢሆን እንደዚያ ከመሆን ያመለጠው ለጥቂት ነው። ምናልባት የተረፈው ከሽረሪት ድር በማይወፍር ልዩነት ይሆናል። ሲያስበው ይሰቀጥጠዋል።

ሁለት ዓመት ያህል የኖረበት ዓለም ይህንን የመሰለ ነበር።

አሁን ደግሞ፥ በፊት የነበረበትና ሁለት ዓመት የተለየው ሕይወቱ ምን ዓይነት እንደሚሆን ጨርሶ ወደማያውቅበት ከውጪኛው ጨለማ ዓለም፣ ተመልሶ መግባት እንዲችል በሩ ተከፍቶለታል።

የትኛው ይሻላል?

የሚያሰቅቀው ሰው መሆንን የሚያስጠላው የአማኑኤል ሆስፒታል ዓለም? ወይስ ምናልባት ለማኝና የበረንዳ አዳሪ ሊሆን የሚችልበት የውጪኛው ጨለማ የችጋር ዓለም?

ማስረሻ ከሁለት አንዱን መምረጥ በጣም ከባድ ሆነበት። ምሽት፥ ደብዛዛው የኤሌክትሪክ መብራት ዐይኑን ከጣሪያው ላይ ተክሎ ቀን ግቢውንና

በሽተኞችን ሁሉ ሲቃኝ፥ ሁለቱን ዓለማት እያነጻጸረ ለመምረጥ ሲጨነቅ፥ ሲጠበብ ሰነበተ።

በመጨረሻ ከውሳኔ ላይ እንዲደርስ የረዱት ሁለት ምክንያቶች ነበሩ። አንደኛው ከርካሳ ቦልስዋገኑ ነበረች። ለጊዜው የት እንደ ደረሰች አልታወቀም። በኪራይ ይኖርበት ከነበረው ግቢ እንደሌለች ጓደኞቹ ከመንፈቅ በፊት ሄደው አይተው ነግረውታል። አዲሶቹ ተከራዮችም፥ እነርሱ ሲገቡ መኪና የሚባል ነገር በግቢው እንዳልነበረ ተናግረዋል። አራዳ ጊዮርጊስ አጠገብ ከሚገኘው የትራፊ ፖሊስ ጽሕፈት ቤትም ሄደው እንደሌለች አረጋግጠዋል። ሌባ ወስዶ ሱማሌ ተራ ቅርጫ አስገብቶ ካልጨረሳት በስተቀር እንደ መርፌ ተሠውራ አትቀርም። ብትገኝም የሚጠራጠረው የትራፊክ አደጋው ጉዳይ ካለቀለት ቢሸጣት ሥራ እስኪያገኝ ድረስ የሚግደረደርበት ዋጋ ታወጣለታለች። የሚጠረጥረው አደጋ ለእስራት የሚያደርሰው ከሆነ ደግሞ ወህኒ ቤት ከአማኑኤል አይብስም። እንዲያውም ከሆነ ደግሞ ወህኒ ቤት ከአማኑኤል አይብስም። እንዲያውም በአንድ ፊቱ ይሻለዋል። አይለምን በረንዳ አይተኛ።

ሌላው ምክንያት ዘለቃ ናት። ስለ ዘለቃ ያለው ስሜት በየጊዜው የሚለዋወጥ፥ በትክክል ሊረዳው የማይችል ምስቅልቅል ነው ነው። በመጀመሪያ እንደ ቆላ ቁስል መላ ሰውነቱን የሚጠዘጥዝ መራር ጥላቻና በቀል ነበር። አእምሮው እንድ ተመለሰለት ከዚህ አሰቃቂ በሽታ የጣለችው ተጠያቂ ወንጀለኛ ርስዋን ብቻ አድርጐ በመውሰድ በዓለም ላይ የመጨረሻ ምኞቱ አንገቷን ፈጥርቆ የመጨረሻ እስትንፋስዋ ሕቅ ብላ ስትወጣ ማየት ሆኖ ተሰማው። ሁለት መዳፉን ጨብጦ የሚጠላት ይሕወት በሐሳቡ ሲጥ ብላ ስትጠፋ ያየበት ጊዜ ነበርና። ፍጥርቅ። ጸጥ። ዝልፍልፍ።

እያደር ግን የሚያሠቃይ የጥላቻና የበቀል ቁስሉ እየሻረ እንደ ጠባሳ ድንዛዜ ተተካበት። የጥላቻም፤ የፍቅርም፥ የትዝታም ስሜት የሌለበት። እየ ቆየ ደግሞ የደነዘዘ ጠባሳው የሕይወት ደም እየተዘዋወረበት ሄደ። በጥላቻም ይሁን በናፍቆት ዘለቃን የማየት ፍላጐት እያገረሸበት ሄደ። በሠራችው ተጸጽታ ፍቅራቸውን አድሳ ያሳለፉትን ትዝታ እንደ ገና መልሳ፥ «ማስረሻ እንደምን አለህልኝ? » ስትል የምትጠይቀው እየመሰለው እንደ ጓደኞቹ እሑድ በመጣ ቁጥር በጉጉት ጠበቃት። ሳምንታት ወራት፥ አለፉ። ጓደኞቹ እንዳመቻቸው ከወርም ከሁለት ወርም አንድ ጊዜ ይጠይቁታል። ዘለቃ ግን ብቅ አላለችም። እንደጠበቃት ቀረች። ስለ ዘለቃ ያለው ስሜት እያመረቀዘ ሄደ። ልትጠይቀው ባለመምጣቷ ይናደዳል። ግን ንዴቱ የጥላቻ ይሁን የናፍቆት በትክክል

አይታወቅም። ዶክተሩ መውጣት ትችላለህ ባለው ጊዜ በዚህ ዓይነት ስሜት ላይ ነበር። የዶክተሩ መልስ የስሜት ቁስሉን ይበልጥ አባባሰበት።

እንዴት እንደ ሆነች ማየት እፈልጋለሁ! - ይላል ብቻውን።

-ስለኔ ያላት ስሜት ምን ይሆን? - ማወቅ እፈልጋለሁ።

-በአገኘኋት ጊዜ ምን ይሰማኛል? - ራሱን ይጠይቃል።

-ኑሮዋስ ለመሆኑ እንዴት ነው?

-ለመጀመሪያ ጊዜ ስንገናኝ ሁናቴያችን እንዴት ይሆን?

ውጤቱን ለማወቅ በጣም ይጓጓል።

ለመውጣት ከወሰነ በኋላ ደግሞ መዋል ማደር አልፈለገም። «ነገ መውጣት እፈልጋለሁ » አለ ዶክተሩን።

«እርግጠኛ ነህ? »

«አዎ? » አለ ማስረጃ ፍርጥም ብሎ።

«እኔ በመውጣትህ እስማማለሁ። ግና ሌላው ቢቀር ጓደኞችህ እስኪመጡ ብትጠብቅ አይሻልም? »

«ራሴን ካልቻልኩ፥ አልዳንኩም ማለት ነው! »

«እንዳልክ። »

በበነጋው ጓዙን ጠቅልሎ ያማኑኤል «ጓደኞቹን » ተሰነባብቶ ወጣ.....

የተጋፈጠው የውጪኛው ዓለም ግን ከአሰበው፥ ከጠበቀው የተለየ ሲሆንበት የባሰውን ተደናገረ። ተሳሳተ? ‹ቢሆንም የመጣው - ይምጣ አልመለስም› ሲል ጥርሱን ነክሶ መንገዱን ቀጠለ። ከአማኑኤል የባሰ የመሰለበትን የውጪኛውን ዓለም ትርምስ አንድ ዋና ምክንያት ለማወቅ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም።

## ፫

ማስረሻ የእህል በረንዳን ተሻግሮ፥ አዲስ የሚሠራውን የአውቶብስ መናኸሪያ አልፎ ወደ እስላም መስጊድ ሲያመራ፥ የሕዝቡ ትርምስና መገላመጥ እየባሰበት ሄደ። እሱም፥ የእሥጋም እየተገረመም ጉዞውን ቀጥሎ ከአባ ኮራን ሠፈርና ከገበያ አዳራሽ የሚመጡት መንገዶች ከሚጋጠሙበት መስቀለኛ አጠገብ ሲደርስ ብዙ ሰዎች ዳር - ዳሩን ተከማችተው አንድ ነገር በሩቁ ሲመለከቱ አገኘ። የሰዎቹ ሁሉ ዐይን ያረፈው ‹ምርጥ የጨሊያ ቅቤ› የሚል ሰሌዳ ከተለጠፈበት መደብር በር አጠገብ ነው። አንዳንዱ ላመል ያህል ከንፈሩን በአዘኔታ ይመጥጣል። አንዳንዱ በቅሬታ ይሁን በትዝብት ራሱን እንደ መነቅነቅ ያደርጋል። የርካታና የንቀት ስሜት ከፊቱ ላይ የሚነበብበትም አልታጣም። ከአውራ ጐዳናው ደቡባዊ ዳርቻ በኩል ይጓዙ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ሰው በብዛት ከተሰበሰበት ሥፍራ ሲደርሱ ቆም ብለው ላንዳፍታ ይመለከቱና በአጠገቡ ለማለፍ የፈሩ ይመስል ወደ ማዶ መንገዱን አቋርጠው በተቻኰለ አረማመድ ጉዞዋቸውን ይቀጥላሉ።

ማስረሻ እንደ ሌሎቹ መንገዱን አቋርጦ ለማለፍ ከከጀለው በኋላ የማውቅ ፍላጐት ስቦት እንደ ሌሎቹ ቆም ብሎ በትኩረት ተመለከተ። የሁሉም ዐይን ያረፈው ከእግረኛው መንገድ ላይ በወደቀው ሰው ላይ ነበር። ግራ እጁ በጭንቅላቱ በኩል ወደ እስላም መስጊድ አግጣጫ ተዘርግቷል። አድን ነገር ለማውጣት የሞከረ ይመስል ቀኝ እጁ ከለበሰው ጃኬት ሥር ወደ ብብቱ ተከቷል። እግሮቹ ፊትና ኋላ ተዘርግተዋል። ከሸሚዙና ከጃኬቱ የዘለቀው ፈሳሽ ደም በብብቱ ወርዶ አስፋልቱ ላይ ኵለል ማለት ጀምሮአል። ገና ሠላሳ ዓመት ያልደፈነ ወጣት መሆኑ ከሩቅ ያስታውቃል።

«ምን ሆኖ ነው? » ሲል ማስረሻ ጠየቀ ጠቅላላው ሁናቴ እንደ አንድ ነገር እየሰቀጠጠው።

ጥያቄው የቀረበለት ሰው በመገረም እንደ ጅል ተመለከተው። «እንደምታየው ነው። ምን ትጠይቃለህ? »

ማስረሻ በሰውየው ፍርጥም መልስ ግራ እንደ መጋባት አለና «ማለቴ በጠራራ ፀሐይ - መንገድ ላይ ደፍቶት እንደዚሁ ሄደ? » አጠያየቁ ራሱንም አስደነቀው። ከአፉ እንደ መጣለት ነበር።

«ሂድና ጠይቀው! » ሰውየው ከእግር እስከ ራሱ ገርምሞት ከአጠገቡ ዘወር አለ።

«አልሞተ እንደሆነኮ ምናለበት ሐኪም ቤት በአስቸኳይ ቢወስድ ይተርፍ ይሆናል » ሲል በተጨነቀ አንደበት አጠገቡ ለቆመው ሌላ ሰው ሐሳቡን ሰነዘረ። ሰውየው ትከሻውን ነቀነቀ።

ማስረሻ የሚያየውንና የሚሰማውን ማመን አቃተው። በግለሰብ ደረጃ አንዳንድ ሰዎች ግዴለሽም ጨካኝም ሊሆኑ ይችላሉ። የማያውቁት የማይተዋወቁት ቀርቶ የቅርብ ግንኙነት ባላቸው ግለሰቦች መካከልም ይህ ሁናቴ በየጊዜው የታየና የተለመደ ነው። እርሱ ራሱ፥ ያሳደገው አባቱ የጣዕረ ሞት ጥሪ ሲልክበት ከዛሬ ነገ ሲል የጭካኔም ባይሆን የግዴለሽነት በደል ፈጽሟል። ይህም እስከ አሁን ሕሊናውን በጸጸት ይቧጥጠዋል። እንደ ራሱ ያምናት የነበረችው ሚስቱ ዘለቃም ብትሆን ባልገባው ምክንያት ባዶ ቤት ጥላው ሄዳለች። ይህ ጭካኔ ነው ይባላል። የረሳቸው የዘነጋቸው የተዋቸው የቀድሞ ጓደኞቹ ደግሞ ደርሰውለት አትርፈውለታል። ግን ይህ ምን ይባላል?

በጥይት የተመታ ቁስለኛ ወይም የሞተ አስከሬን ሊሆን ይችላል። መንደር ዳር ወድቋል። በብዙ መቶ የሚቆጠር ሰው ይመለከተዋል። አንድ ሰው ሲራመድ ቢያደናቅፈው ስንኳ «አይዞህ » ብሎ መደገፍ አለ። ከዚያ ሁሉ ሰው መካከል ግን አንዱም አንድ ነገር ለማድረግ አልቃጣም።

የለም፤ ይህ የአንዳንድ ሰዎች ግዴለሽነት አይደለም። ማስረሻ ከሰዎቹ ፊት ላይ እንዳነበበው ጥቅል ጥላቻ ነው። ድምር ፍርሀትም ነው። ሊገባው አልቻለም።

የቀትር ፀሐይ ግንባር ግንባሩን እየመታው ማስረሻ ፈዝዞ ቆመ። ከአራቱም ማዕዘን የሚተላለፉት ተሽከርካሪዎች ዙሪያውን ከብቦ የሚመለከተውን ሕዝብ አርምሞ በየጊዜው ያደፈርሱታል። ከማዶ የገበያ አዳራሽና የአካባቢው ውካታ፥ አጥር ለመስበር እንደሚፈልግ ኃይል እየተመመ ይገፋል። በሰፈሩ የቆዳ ገበያና በዕርድ ቆሻሻ የታደሙ አሞሮች ከላይ ያንዣብባሉ። በዚህ መካከል ከማዶው መስጊድ «አላሁ አክበር አላሁ አክበር! አሽሀዱ አላህ ኢለላህ » የሚለው የዙህር ጥሪ አየሩን ሰንጥቆ አስተጋባ። «ላኢላህ ኢለላህ » ብሎ ሳይጨርስ ሌላ ጩኸት ተደባለቀበት።

«ወይኔ - ወይኔ! ልጄ! እኔ ደፋ ልበል - እኔ ድፍት ለበልልህ - እሪሪ! እሪሪ! » በዕድሜ ጠና ያሉ አንዲት ሴት እጃቸውን እያወናጨፉና ነጠላቸውን እያራገቡ

ከአባ ኮራን ሠፈር በኩል ተንደርድረው በመምጣት ከተዘረረው ወጣት ላይ ተደፉ። የልብ ትርታውን የሚያዳምጡ ይመስል ፊታቸውን ከደረቱ ላይ ለጥፈው ላንዳፍታ ዝም ካሉ በኋላ እንደገና እሪታቸውን አደባለቁት። «ኡ! ኡ! - ኡ! ያገር ያለህ! የመንግሥት ያለህ! ልጄን ገደሉት። እኔ ከንበል ልበልልህ! አንድዬ - አንድዬ - አቆላማጬ - አዛኜ! » ቀና ሲሉ ፊታቸው በደም ተእልቅልቆ ነበር። እንባቸው ከደሙ ጋር እየተቀላቀለ እየበረዘውና ቀጭን መስኖ እየሠራ ሲወርድ በሩቅ ዙሪያ የቆመውን ሰው በትዝብት አስተዋሉት። ፊታቸውን በለቀለቀው ደም ላይ የተሲአት የፀሐይ ጨረር አርፎ ሲያንጸባርቅ ለማስረሻ አንድ ዓይነት የሚቃጠል ችቦ፥ አንድ ዓይነት የእሳት አለሎ መስሎ ታየው። በሥቃይ የሚቃጠል በጭንቀት የሚቃጠል በልጅ ፍቅር የሚቃጠል እንደ ሻማ ነዶ የሚያልቅ። አንዱ በሌላው ሰብአዊ ፍቅር መንደድ። እሳት። ዐይኑን ጨፈነ።

የዙህሩ ጥሪ ቆመ።

የተሽከርካሪዎች ድምፅም ተገታ። ሌላ ድምፅ አስተጋባ።

«ከዚህ ሁሉ ሰው መካከል አንገትህን የሚያቀናው ጠፋ? እኔ ልደፋልህ! ሰው የለም እ? - ጀግና የለም እ! ኧረ ኧረ አገሬ እንዲህ ሆነች? የጨካኝ አገር! የፈሪ አገር? ለጭንቅ እይሚደፍር ለጀግና የሚደርስ ጠፋ! ዝም ብሎ የሚያይ ፈሪ? ራሱን የራሱን ሕይወት ብቻ የሚወድ ነፍሰ - ንፉግ - አገሬ ይህን አፈራች? ውይ? ውይ! መጥኔ - መጥኔ - ልጄስ - እንደኮራ በማተቡ እንደ ጠና - ምናባቱ - »

ማስረሻ ዐይኑን ከድኖ ድምፅ ሳይሆን የሚሰማው የሥቃይ ጥሪ የአሳደገው አባቱ፥ የሙሄ ሆነበት። «በሥጋ ባልወልድህም፥ ልጄ ነህ፥ በነፍሴ ድረስልኝ » የሚለው የጭንቀቱ ጥሪ መጣበት። ከሠርጉ ቀን ለልመና ቁሞ ያየው የሠቀቀን መልኩ አፈጠጠበት። በየመጠለያ ጣቢያው ያጋጠመው የጣዕር ገጽታ ተደቀነበት።

ሳይታወቀው ወደ አናትና ልጁ አመራ። ከመድረሱ በፊት ግን አንድ ላንድሮቨር ጡሩንባውን እያደባለቀ መጥቶ ቀጥ ሲል፥ ሰዉ በየአግጣጫው መበተን ጀመረ። አውቶማቲክ መሣሪያ የያዙ ሰዎች መኪናው በጥድፊያ ወርደው፣ የወደቀውን ወጣት የሳንሳ ተሸከመው ሴትየዋን ደግፈው በመጡበት ፍጥነት ሄዱ። አካባቢው ወዲአይው ጭር አለ።

ማስረሻ ያየው የሰማው የደረሰው ነገር ሁሉ ሕልም መስሎ ተሰማው። መዳኑን ተጠራጠረ። ለነገሩማ መርካቶ እንኳን ገመምተኛ ጤነኛም አእምሮ

የሚያዞር አይደል። «እኔ የሚያስፈልገኝ ደሞ ጸጥታና እርጋታ ነው » አለ በሐሳቡ። ጥቂት ተራምዶ ሰይቸንቶ ለመሳፈር ቆም እንዳለ አንዲት ዘናጭ መቶ ሃያ አራት ትንሽ ፈቀቅ ብላ ቆመች። ጥቁር «የኤር ፎርስ » መነጥር ያደረገው ወጣት ሹፌር ወጣና ከኪዎስክ ዊንስተን ሲጋራ ገዝቶ ተመለሰ። መኪናዋ እሱ ከቆመበት ስትደርስ ማስረሻ እጁን ዘረጋ።

«የት ነው? »

«ካዛንቺስ » ሲል ማስረሻ አፉ እንዳመጣለት መለሰ። እይት እንደሚሄድ ገና አልወሰነም ነበር። ጓደኞቹ ሊጠይቁት ሲመጡ ለሲጋራ መግዣ ከሚሰጡት ገንዘብ ተጠራቅሞ የተረፈ ከሃያ ብር በላይ ከኪሱ አለ። ለጊዜው ለአንድ ሁለት ቀን ሆቴል ማረፊያ ይበቃዋል። የነገው ደግሞ ነገ ሲመጣ ይታያል።

ባለ ሰይቼንቶው የፊተኛው በር ከፈተና አስገባው። ተጨማሪ ዋጋ አለመጠየቁ ማስረሻን ግርም አለው። ከመርካቶ እስከ ካዛንቺስ በስሙኒ የሚሄድበት ጊዜ ከመጣ ይህ ለውጥ በእርግጥ ተአምረኛ ነው ሲል በሆዱ አሰበ። «ስሙኒ ነው አይደል? » ሲል እንደ ዋዛ ጠየቀ። እንዲያው ለማወቅ ያህል።

ሹፌሩ ላመል ያህል ዘወር ብሎ አሽሙር አዘል ፈገግታ አሳየው። «ከዚህ ፒያሳ ከፒያሳ አራት ኪሎ ከአራት ኪሎ ካዛንቺስ ሦስት መናኸሪያ ነው በመሠረቱ። ለዘመድ ግን አጣጥፈን እንደ አንድ እንቆጥረዋለን።

ማስረሻ ዝምድናቸው ባይገባውም «አመሰግናለሁ » አለ። ይህ ሁሉ ሊሆን ከኋላ የተቀመጠው ሌላ ተሳፋሪ፥ ከፊት ለፊቱ ጋዜጣ ዘርግቶ የሚያነብ ይመስላል። ለምን ባለሰይቸንቶው ተሳፋሪ እንደ ልብ በሚገኝበት አግጣጫ እንደማይሄድ ማስረሻ እየገረመው በካቴድራል ትምህርት ቤት በኩል አቆራርጠው በቸርችል ጐዳና ወርደው ወደ ተረት ሠፈር ሲታጠፉ ከኋላ የተቀመጠው ተሳፋሪ ጋዜጣውን የማጣፈፍና ጉሮሮውን የመጥረግ ድምፅ አሰማ። ማስረሻ እንደ ዋዛ ዘወር አለ። ዐይን ለዐይን ተጋጩ። ማስረሻ መጀመሪያ እርግጠኛ ባይሆንም መርፌ እንደ ወጋው በድንጋጤ ስቅጥጥ አለ። ለቅጽበት ተፋጠጡ። እሱ ነው? አይደለም? ቢሆንስ? የአጋጣሚ ጉዳይ ነው። ፊቱን መለስ አደረገ።

«ስለ ሰውየው በጣም ተጨንቀህ ነበር? ታውቀዋለህ እንዴ? » የሚል ጥያቄ ከኋላው መጣበት።

«የትኛውን ሰውዬ? » ሲል ማስረሻ ያልገባው መስሎ ጠየቀ። ከአደጋው ሥፍራ ‹ማን ገደለው? ማነው? እያለ ማስረሻ ሲጠይቀው ገርምሞት ከአጠገቡ የተሠወረው ሰው ለመሆኑ ግን አሁን እርግጠኛ ነበር።

«ከዚያ ወድቆ የነበረው ነዋ! »

«ኧረ የት አውቄው! »

«ታዲያ ምን አመራመረህ? »

«እንዲያው ነገሩ አስደንቆኝ። » ማስረሻ ነገሩን በማቃለል ትከሻውን ነቅነቅ አደርገ።

«ምን ነገር? » ሲል የሰይቸንቶው ሹፌር ቀበል አደረገ።

«ማለቴ - ማለቴ - » ማስረሻ አሁንም የበለጠ ግራ ተጋባ «ሰው መንገድ ዳር ቀድቆ መቸም ዝም ማለት አይቻልም። ሕይወት - እኮ ነው መቸስ። የሰው ሕይወት። » የተሠቃየችው የሙሔ ሕይወት በሓሳቡ ታየችው።

«ወንጀለኛ አይቀጣ ወራዳ ሕይወት ሕዝብን ከሚበክል አይወገድ ነው የምትለው? » የኋለኛው ተሳፋሪ አነጋገር ጥያቄ ሳይሆን ቁጣ መሰል ነበር።

ማስረሻ ሥጋት ገባው። «ወንጀለኛ ይሁን አይሁን እኔ ምን ዐውቄ! ወድቆ ስላየሁት አዲስ ነገር ሆኖብኝ ነው እንጂ! »

ሁሉም ዝም ብለው፥ ሰይቸንቶው በንግድ ማተሚያ ቤት ታጥፎ በንግሥት ዘውዲቱ ሆስፒታል በር ዘለቀና ወደ ብሔራዊ ቤተ መንግሥት አመራ። ማስረሻ አግጣጫው ካዛንቺስ የሚያዘልቅ መሆኑን ቢያውቅም ሰውነቱን ቀፈፈውና «ከዚህ ልውረድ፤ በቃኝ » ሲል ጠየቀ።

«ካዛንቺስ - እኮ ገና ነው። »

«ዐውቃለሁ ግን ግድ የለም ከዚህ በኋላ በእግሬ እሄዳለሁ። »

«ከዚህ ነው እንዴ ሠፈርህ? » ሲል ሹፌሩ ጠየቀው በዐይኑ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትን እያመለከተ።

አሽሙሩ ማስረሻን ጥቂት አናደደው። «ነፋስ እየተቀበልኩ በእግሬ ማዝገም እችላለሁ ብዬ ነው። »

«ሐሩር ፀሐይ እንጂ አሁን የሽርሽር ሰዓት አይደለም። » ሲባል ማስረሻ ሥጋቱ አየለበት።

ይባስ ብሎ ደግሞ ከኋላ የተቀመጠው ተሳፋሪ «እስቲ ሲጋራ » ብሎ ሹፌሩን ሲጠይቀውና ሹፌሩም የመኪናዋን ኪስ ሲከፍት የማስረሻ ዐይን ምን በመሰለ ኮልት ሽጉጥ ላይ ዐረፈ። እንዲያውም በአኳኋኑ ሆን ብሎ ማስረሻ ማሳየት የፈለገ ይመስላል። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ፤ «ቋ! - ቋ! - ቋ! » የሚል ድምፅ ሰማ። ከኋላ የተቀመጠው ሰው ጥይቱ የወጣ ሽጉጥ ቃታ መሳቡ ነበር። አሁን የማስረሻ ስጋት ወደ ጭንቀትና ፍርሃት ተሸጋገረ። ወንበዴዎች ናቸው? አንዳንድ ሰይቸንቶ ነጅዎችና ተሳፋሪ መሳይ ተባባሪዎች በተለይ በምሽት ሴቶችንና ሽማግሌዎችን ወደ ገፈርሳና ወደ ሾላ እየወሰዱ እንደሚዘርፉ ሰምቶ ነበር። ወይስ የጸጥታ አስከባሪዎች ይሆኑ? ሰይቸንቶም ሌላም የጭነትና የማመላለሻ ተሽከርካሪዎች እንደሚይዙ ይነገራል። ታዲያ እሱን በምን ጠረጠሩት? እንደዚህ ካለው ወጥመድ ውስጥ ምን እግር ጣለው?

«ከዚህ እወርዳለሁ! » አለ አንድ ጊዜ ባለሥልጣን የነበረበትን የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት መሥሪያ ቤትን እንዳለፈ። ያልተደናገጠ ለመምሰል ሞከረ።

«ግዴለም ከምትፈልገው ቤት በራፍ ድረስ አደርስሃለሁ። »

«ከዚህ ይበቃኛል። »

«ቤተ መዛግብቱ ላይ ከዚህ ይበቃኛል ብለህ ነበር። እዚህም እንደዚሁ። የምትወርድበትን ትክክለኛ አድራሻ ለመንገር ምነው ፈራህ? » ሲል ነጂው በማሽሟጠጥ ጠየቀው።

«ምን አስፈራኝ። ከፈለግሁበት የትም መውረድ አልችልም እንዴ? ምነው ሰው ለዚህ ነጻነት ያለው መሰለኝ። »

«ልክ ነህ » አለ ነጂው በመስማማት ዓይነት ራሱን እያወዛወዘ። «ብሔራዊ ቤተ መዛግብት መውረድ ስትፈልግ በእርግጥ የምትፈልገው አድራሻ ነው ወይ? አሁንኮ ሰው ያለበት አልመሰለኝም። »

ቋ - ቋ - ቋ -! የሚለው ድምፅ አሁንም ከጆሮ ግንዱ በኩል አስተጋባበት። «ቂጡ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ እንደ ልቡ አይጮህም እንዲሉ ምክንያት ይኖረዋል! »

«ምንም ቁስል የለብኝም። » ማስረሻ አነጋገሩን ፍርጥም ሊያደርግ ቢሞክርም ድምፁ ተሰበረበት።

«ታዲያ ምን አስፈራህ? »

»ምን ፈራሁ? »

«የምትሄድበትን ትክክለኛ አድራሻ ለመንገር ወይም ለማሳየት። »

አሁን ጥያቄ መሆኑ ቀርቶ የሁለቱ ቅብብሎሽ ሆነበት።

«መናገር ባልፈልግስ መብት የለኝም? »

«መብት? መብት አልክ? ቀበሌ ጠይቆህ እንደ ፈለገ አሽቆጥቁጦህ አያውቅም? » ነጂው ከት አለበት።

ማስረሻ አሁን ነገሩ የገባው መስለው። ቀበሌዎች መሆን አለባቸው። ስለ ሥልጣናቸውና ስለ ተግባራቸው በጋዜጣም በራዲዮም በመጠኑ ተረድቷል። ‹ግን በፈለጉት ጊዜ በፈለጉበት ቦታ ማንንም ሰው መመርመር ይችላሉ ማለት ነው?› ሲል ለራሱ ሐሳብ ጥያቄ አቀረበ። «ፈጽሞ » ሲል መለሰላቸው።

«እንዴት? »

«አግኝቻቸው፤ አግኝተውኝ አያውቁማ! »

«ከቀበሌ መደበቅ ራሱ ወንጀል መሆኑን አታውቅም? »

«የመደበቅ ጉዳይ አይደለም! » ማስረሻ አሁን ደፈር ብሎ መናገሩ ተመለሰለት።

ይህ ሁሉ ሲሆን ካዛንቺስን አልፈው በአስመራ መንገድ ጉዞ ቀጥለው ነበር።

«እህስ? »

«ቀበሌ ውስጥ አድራሻ አልነበረኝማ። »

ግራ የተጋቡ በመምሰል ሁለቱ ጠያቂዎች በጐድን ተያዩ።

«ከክፍለ ሀገር መጥተህ ነው ማለት ነው? »

«ኧረ ከዚሁ ነኝ! »

«ታዲያ ዕፀ መሠውር አለህ ቀበሌ የማያውቅህ? »

«የኀቡዕነት መብት የተሰጠው ባንዳ ይሆናላ! » ሲል ነጂው ቀበል አደረገ።

መገናኛን አልፈው ወደ ፊያት ፋብሪካና ከዚያም አልፎ ወደ ሚገኘው የተንጣለለ ሜዳ ሲታጠፉበት ማስረጃ መቻል አቃተው። «እንዴ? ኧረ የት ነው የምትወስዱኝ » አለ ጭንቀት ባሰለለው ድምፅ።

«የምትወርድበትን ትክክለኛ አድራሻ አንተ ባታውቅ እኛ ልናሳይህ ነዋ? » የሚል ኮስታራ መልስ አገኘ።

«ከኔ ምንድን ነው የምትፈልጉት? ምንም የሠራሁት ነገር የለም። »

«ቀበሌ የማያውቅህ ቀበሌ የማታቅ መመርመር ያለብህ ሰው ትመስለናለህ። »

«ምክንያት አለዋ! » ማስረሻ በቀጠነ ድምፅ ጮኸ።

«ምን ምክንያት? »

ማስረሻ ጥርሱን ነክሶ ዐይኑን ጨፍኖ ለአንዳፍታ ተወጠረ። ከዚያም፥ ከሆዱ ፈንድቶ የወጣ በሚመስል ድምፅ «አማኑኤል ነበርኳ! » አለ።

ነጂው ፍሬን እንደ መያዝ አደረገና ዝርፊያ ለመከላከል ይመስል በቀኝ የመኪናዋን ኪስ ጋረድ አድርጎ ወደ ኋላ መለስ ብሎ «እእ? ምን ይመስልሃል? » ሲል ጠየቀ። ከኋላ የተቀመጠው ተሳፋሪ ከት ብሎ ሣቀ።

«እህ ምን ያሥቅሃል? » ሲል ነጂው መልሶ ጠየቀው።

«የተረቱን ነገር አስታወሰኝ! » ተሳፋሪው የሽጉጡን መዘውር ፈልቅቆ ጥይቶ ማጉረሱ ለማስረሻ ይታወቀው ነበር። ባያይም መሰለው። «እና ማጣፊያው ሲያጥራቸው ዕብድ እየሆኑ ቢቀርቡ አይገርመኝም። » የኋለኛው ተሳፋሪ አሁንም እንደ ገና ተንከተከተ። «ታሪኩን አልሰማህ እንደ ሆነ ልንገርህ። ትምህርት ይሆንሃል ለወደፊቱ። ከዚህ ከአገራችን ውስጥ ለሥልጣን የሚሻሙ መሳፍንት ጦርነት ገጠሙና ዓለም ቁና ሆነች አሉ። ትሰማለህ? » አለና ከኋላ የተቀመጠው ተሳፋሪ በሽጉጡ አፈ ምዝ የማስረሻን የትከሻ መጋጠሚያ ነካ ነካ አደረገው። ማስረሻ የብረት ቅዝቃዜና የባሩድ ትኩሳት ባንድነት ተሰማው፤ ምንም ሳይሆን።

«እያዳመጥኩ ነው! » አለ በጩኸት።

«ታዲያ እንደምታውቀው በጦር ሜዳ በትግል ሜዳ አንዱ ወገን መሸነፉ የማይቀር ነው። እንደ ራስ አሊና እንደ ደጃዝማች ውቤ ጦርነት ሁለቱም ማሸነፋቸውንና መሸነፋቸውን ሳያውቁት በየፊናቸው ካልሸሹ በስተቀር። ታዲያ በዚህ ጦርነት የተሸነፈው ወገን ግማሹ በጦር ሜዳ ሲወድቅ፥ ግማሹ ሲማረክ አንዱ መግቢያ መውጫ ማጣቱን ያይና ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ጭንቅ ነውና፥ ባዶ በሆነው መንደር አንዱ ቤት ገብቶ ጉሽጉሽ ይበረብርና ቀሚስና ነጠላ ለባብሶ መውጣት ነዋ! »

«እሺ። ከዚያ በኋላስ? » ሲል ነጂው በማዳነቅ ጠየቀ።

የኋለኛው ተሳፋሪ አሁንም እንደ መሣቅ ቃጣው። «ከዚያም ከድል አድራጊው ወገን አንዱ ያገኘውና ‹ቁም አንተ!› ይለዋል። ‹ኧረ እኔ ሴት ነኝ! ከምኑም የለሁበት› ሲል ድምፁን አቅጥኖ ይመልሳል። ያኛው ገጽታውንና ቁመናውን ከላይ እስከ ታች በማስተዋል ይጠራጠርና ቀሚሱን ገለብ ሲያደርገው ጉዱ እንድ ቀትር እባብ ተንዘልፎ መገኘት! »

ነጂው ከልቡ አሥቆት «እሺ! » ሲል በድጋሚ ጠየቀ።

የኋለኛው ተሳፍሪ በፌዝ ሣቅ በአፍንጫው ተንፈስ ተንፈስ አለና «ታዲያ ይህ ምንድን ነው? » ሲል አፈጠጠበት በጐራዴው እየጠቆመ። ምን መልስ ሰጠ መሰላችሁ? ቁልቁል ተመለከተና ‹ሰማይና ምድር ይፍረድብኝ ካለ ዛሬ አይቸው አላውቅም› አለ ይባላል። እና አሁንም መሬት ከሥራቸው ስተከዳቸውና የሚገቡበት ሲያጡ ዕብድ እየመሰሉ ቢቀርቡ አይደንቀኝም። »

ማስረሻ አንጀቱ በብሽቀት ሲኮማተር የጉንጬ ጡንቻ ሲንቀጠቀጥ ተሰማው። መርካቶ እንዳየው ወጣት መንገድ ዳር መደፋት አልፈለገም። «በእርግጥ ታምሜ አማኑኤል ሆስፒታል ነበርኩ። ባታምኑ ይኸው » ዶክተሩ የሰጠውን የምስክር ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ዘረጋላቸው።

እንደ ዋአ አዩለትና መልሰው ሰጡት። «ይህ'ንኳ ፋይዳ የለውም! » ተባለ።

«ለምን? » ማስረሻ በጭንቀት ጠየቀ።

«ስንኳን የሆስፒታል ምስክር ወረቀት ሌላም ማግኘት ይቻላል። ሁሉ በጄ - ሁሉ በደጄ ሆኖአል። »

«ከእኔ እምትፈልጉት ምንድን ነው? » ማስረሻ ለቅሶ እየከጀለው ድምፁ ተንጫረረበት። «ስለ ምን እንደምትናገሩ አይገባኝም። እኔ ግን ያሳላፍኩትን መከራና ሥቃይ የማውቀው ራሴ ነኝ።

«ንገረን እንስማዋ! » አለው ነጂው የማስረሻ ሠቀቀን እወንት ይሁን የማስመሰል ሳላላወቁ ለማስጨረስ ያህል።

ጉሮሮውን እየ ተናነቀውና እንደ አሮጌ ሸክላ ድምፁ እየተሰባበረ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የደረሰበትን ሁሉ ተናዘዘላቸው። «ብታምኑም ባታምኑኝም ይኸው ነው » ብሎ ሲጨርስ የሁለቱም አስተያየት ለወጥ አለ።

«እውነትም መከራ አይተሃል » አለው ነጂው ለጀመሪያ ጊዜ የአዘኔታ ፈገግታ እያሳየው። የነገራቸውን አመነውት ነበር። መንፈሱን ቀለለው። «እና አሁን የምትሄድበት የለህም ማለት ነው? » ሲል ጠየቀው - ተሳፋሪው።

ማስረሻ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ።

«ከእኛ ዘንድ ልታርፍ ትችላለህ » አለው ከኋላ የተቀመጠው ተሳፋሪ።

«ግዴለም አላስቸግራችሁም። »

«ምንም ችግር የለበትም። ብዙ ማረፊያ ቤቶች አሉን። »

መኪናውን ፈልጐ ማግኘት ሥራም ፈልጐ መያዝ እንዳለበት ነገራቸው።

«ግዴለም በእሱም ቢሆን እንረዳሃለን። ካስፈለገም ሁናቴውን አጣርተን እንደዚህ የበደለችህን ያችን ሚስትህን ተገቢ ቅጣቷን እንሰጥልሃለን። ደግሞ አትርሳ የልጅ ጉግሣ ሹሞች ሁሉ ተቀፍድደዋል። ምን በወጣህ። እኛ አስፈላጊውን ሽፋን ልንሰጥህ እንችላለን » አሉት።

ከዚያ ሁሉ ጭንቀትና ግራ መጋባት በኋላ መንፈሱን ስለ ታከተው በመስማማት ዝም አለ።

በአንደኛው ጭንቅላት ውስጥ ዕቅድ እየወጣለት መሆኑን ማስረጃ አላወቀም ነበር።

# ፬

ለማስረሻ ነገሩ ሁሉ የባሰ እንቆቅልሽ እየሆነበት ሄደ።

ሁለቱ ጐረምሶች በመጀመሪያ በመናኽሪያ ሆቴል ምሳውን ካበሉት በኋላ የእንደራሴን ሆቴል አልፈው በጠመዝማዛ ኮረኮንች መንገድ በቆርቆሮ ከታጠረ ግቢ ገቡ። ሰው የሚኖርበት አይመስልም። ጭር ያለ ነው። አንድ ጊዜ በረጅሙ ሁለት ጊዜ በአጭሩ የተነፋውን የመኪና ጥሩምባ ድምፅ ሰምቶ የግቢውን በር የከፈተላቸው ኮፍያውን እስከ አፍንጫው የደፋ አንድ ወጣት ነበር። ውናው ቤት የልስኑ ወረቀት ተላልጦ ያገጠጠ ማድ ቤቱ ግድግዳው ዘመም ብሎ ብሩ የወላለቀ ነው። ሲገቡ የታፈገ የቀለምና የሲጋራ ጢስ ተሰማው። ብዙ ክፍል አለው። «ከዚህ አርፈህ መቆየት ትችላለህ » አሉት አንዱን ክፍል ከፍተው እየመሩት። «መጸዳጃ ቤቱ ደግሞ እዚያ ነው » ነጂው በጣቱ አመለከተው። ክፍሉ ተነጥሮ የማያውቅ የሚመስል አንድ አልጋና አንድ ወንበር ብቻ አለው።

ሰፈሩ ለወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት እምብዛም ሩቅ ባለ መሆኑ ‹ያቺ ጉደኛ እንዴት እንደ ሆነች እስቲ ቀስ ብዬ እሰልላለሁ!› የሚል ሐሳብ መጣበት። ግን አእምሮውን ድንገት ያነበቡበት ይመስል «የሚያስፈልግህ ነገር ቢኖር እሱን ጠይቀው » አለው አንደኛው በር የከፈተውን ወጣት እያመለከተ። «ካለበለዚያ ግን እኛ ስናስማማበት ውጭ ባትወጣ ደግ ነው። » የንግግሩ ቃና ምክር ሳይሆን ማስጠንቀቂያ ነበር።

ከሰዓት በኋላ ቀኑን ሙሉ ግቢው ሰው ዝር ሳይልበት ጭር ብሎ ብቻውን ከአልጋው ላይ ተጋድሞ ምን ዕድል እንደሚጠብቀው ሲያሰላስል ዋለ። በር የከፈተው ወጣት ስንኳን የት እንደ ገባ ዐላወቀም። ከዚህ አስፈሪ የእንቆቅልሽ ሁኔታ ሹልክ ብሎ ለማምለጥ አንድ ሁለት ጊዜ ከጀለውና መርካቶ የወደቀው ወጣት፤ በሰይቸንቶ ውስጥ «ቋ! ቋ! » ያለው ኮልት ታስቦት መላ ሰውነቱ እንደ መንዘፍዘፍ አለበትና መልሶ ተወው።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ እንደ ቀኑ አንድ ረጅምና ሁለት አጭር የመኪና ጡሩምባ ድምፅ ተሰማ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሰይቸንቶው ነጂ የክፍሉን በር ከፍቶ ገባና መኖሩን ለማረጋገጥ ይመስል ዐይኑን ብልቅጥ አድርጐ ተመለከተ። «እንደ ምን ዋልክ? » አለው።

«እኔስ ደህና ነኝ። ግን እስከ መቸ ነው እንደዚህ የምቆየው? » ሲል በመማጠን አኳኋን ጠየቀ።

«ምን አጣደፈህ? ከአማኑኤል አይብስ፤ ይልቅስ መብራት ስታበራ መስኮቱን መዝጋት አትርሳ » አለና ራሱ ዘጋው። የክፍሉን በር ከውጭ ሳብ አርጐ ዘግቶበት ሄደ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሌላ አውቶሞቢል ጡሩምባ አስተጋባ። በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት እየተከታተለም የሰዎች ኮቴ ሰማ። የቤቱ ሳንቃ በአብዛኛው ሲረግጡት ሲጢጥ ሲጢጥ የሚል ነበር።

መልሶ ጸጥ አለ። ማስረሻ ጆሮውን አቅንቶ ለማዳመጥ ሞከረ። ከሰፈር ውሻ ጩኸት በቀር ምንም ዓይነት የሰው ድምፅ አልቻለም። ብቻውን በዝምታ ተውጦ ጠበቀ።

ነገር ግን ሁሉት ክፍል አልፎ አምስት ሰዎች ስለ እርሱ በመወያየት ላይ ነበሩ......

«......አስቸኳይ ስብሰባ እንድናደርግ ያስፈለገበት ምክንያት ያልተለመደ ነገር ስለ ተሠራ ምክንያቱን ለመረዳት ነው » አለ የኮሚቴው መሪ፥ ማስረሻን ወደ አመጡት ወጣቶች እያመለከተ፡ አሁን ትንሽ የተረጋጋ ይምሰል እንጂ መጀመሪያ በቴሌፎን ሲነገረው በጣም ተናድዶ ነበር። ‹ከመሠረቱ ግን ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ተፈጽሟል ባይ ነኝ። አንደኛ እሱው ራሱ ከነገራችሁ በስተቀር፥ ይህ ሰው ማን ይሁን ማን እርግጠኞች አይደላችሁም። ሁለተኛ፥ ገና በሕዋስ ደረጃ ስንኳ ተመልምሎ ያላበቃ ሰው በቀጥታ ከዚህ ድረስ መምጣታችሁ ‹የቀጣናውን አካል› ከከፍተኛ አደጋ ላይ መጣል ነው። ሦስተኛ አማኑኤል መቆየቱ እውነትም ከሆነ፥ አሁንም ጤነኛ ላይሆን ይችላል። ታዲያ ፓርቲያችን መታገያ እንጂ ሆስፒታል ወይም ጠባይ ማረሚያ አይደለም። ይህ የእኔ አስተያየት ነው። ለምን እንዲህ እንዳደረጋችሁ ግን እናንተው ንገሩኝ።

«ብዙም ትንታኔ የለንም » አለ አንደኛው ተጠያቂ ጓደኛውን እየተመለከተ። «እርግጥ በሁለተኛው ነጥብ ስሕተተኞች ነን። እዚህ መምጣት አልነበረብንም። በተለይ እኔ፣ እንዴት የሚጠቅም መሣሪያ ሊሆን እንደሚችል ብቻ ሲታየኝ ይህንን ዘነጋሁት። በሕዋስ ደረጃ ግንኙነት ለመፍጠር ጊዜም ደግሞ አልነበረም። እሱ ደግሞ ተጣደፈብን። »

«በሀገሪቱ የደረሰውን ሁሉ ያልተከታተለ የደርግን ተግባር የማያውቅ የአማኑኤል ሆስፒታል ትኩስ ምሩቅ ምን ዓይነት ጠቃሚ መሣሪያ እንደሚሆን - ይቅርታ አድርጉልኝና - እኔ አይታየኝም » አለ ሌላው የኮሚቴ አባል።

«እኔ ደሞ ድንገት ቦግ ብሎ የታየኝ እሱ ነው። »

«እንዴት? »

«አንደኛ - አንደኛ » አለ ቀን ከሰይቸንቶው ኋላ ተቀምጦ የነበረው ወጣት ረገጥ ባለ አነጋገር። «ባንዶች አልደረሱበትም። መርዛቸውን አልቀመሰም አላሸተተም ማለት ነው። ይህ ጥሩ ነገር ይመስለኛል። ከዚህም ከዚያም ላካክፎ ‹የቱ ነው ልክ› እያለ ከሚጠራጠር መናፍቅ.......። ሁለተኛ አማኑኤል ሆስፒታል የቆየ በሽተኛ ለመሆኑ የምስክር ወርቀት አለው። እርግጥ አሁን ወደ ኅብረተሰቡ ለመመለስ ይችላል ብሏል፣ ዶክተሩ። ግን እንገ አንድ ነገር እንዲፈጸም ብናዘውና ቢያዝ ከፓርቲያችን ጋር ምንም ግንኙነት ሳይኖረው ሕመሙ እንደገና አገርሽቶበት በግል የሠራው ለማስመሰል ይቻላል። ስለ ደርግ ተግባር ግን ማስረዳት የእኛ ተግባር ይመስለኛል። እኔ እንደዚህ ነው የሚታየኝ። »

«እንዳልከው በባንዶች ያልተበከለ ያልተለከፈ ያልተነካካ ከሆነ ስለ ጠቃሚነቱ አስተያየትህን እቀበላለሁ። ግና የተናገረው እውነት ለመሆኑ በምን እናረጋግጣለን? » ሲል የኮሚቴው መሪ ጠየቀ።

«በወንጀል ምርመራና በፍርድ አሠራር ከሆነ ጥያቄህ ልክ ነው። እቀበላለሁ። ግን አሁን የምናካሂደው ትግል እንደዚህ እንደማይሠራ ታውቃለህ። የማንን ልብ ማን ያውቀዋል? ግን መቆጣጠር አለብን። ይህ ግልጽ ነው። »

«ማስረጃም ባይኖረን ለማመን ደግሞ አንድ መነሻ መኖር አለበት » ሲል አንዱ ተናገረ።

«እርግጥ! » አለ የሰይቸንቶ ተሳፋሪ መስሎ የመጣው ጎልማሳ። «መነሳው ግን እኔ ነኝ። አሥራ አምስት ዓመት በማስተማር ኑሬአለሁ። ተማሪ ሲኮርጅ ሲዋሽ እውነቱን ሲናገር ከፊቱ ላይ ማንበብ ችያለሁ ባይ ነኝ። እና በእኔ ግምት ሰውየው ስለ ራሱ የተናገረው ታሪክ እውነት ነው። ከጀርባውም ቢሆን ስሜቱን ለመገንዘብ ችያለሁ። የሀገሪቱን የጊዜውን ሁናቴ የማያውቅ ገባሪ ባይሆን ኖሮ፥ ቅጣት ስለ ተፈጸመበት የቀበሌ መርስኔሪ እንደዚያ ባልጠየቀ ነበር። » በአመላለሱ የረታ መሆኑን ለማሳወቅ አራቱንም በየተራ ተመለከተቻቸው። በአስተማሪነት እስከ ጠረፍ ድረስ በክፍለ ሀገሩ ብዙ ስለ ተዘዋወረ በ67 ላይ በጅማ ከተማ በተካሄደው የኢትዮጵያ መምህራን ጉባዔ ላይ የክፍለ ሀገር ተወካይ ሆኖ በመካፈል አንድ ወር ያህል ታሥሮ ስለ ተፈታ ስለ ትግልም ሆነ ስለ ኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁናቴ ከአራቱም የበለጠ የሚያውቅ መስሎ ይሰማዋል። በዚህም ምክንያት የኮሚቴው መሪ ከበላይ አካል ተሹሞ ወይም

ተመርጦ የመጣበት ባይሆን ኖሮ፥ የቀጣናውን ኮሚቴ መምራት ያለብኝ እኔ ነኝ ባይ ነው። እርግጥ ዲሲፕሊን በማክበር ይህንን ምኞቱን በገሃድ አጋልጦት አያውቅም። የሚትርው ችሎታውን ሌሎቹ የኮሚቴ አባሎች እንዲያውቁለት ማድረግ ብቻ ነው። ከዚያ የበላይ አካል ይገነዘበኛል የሚል ተስፋ አለው። የኮሚቴው መሪ በበኩሉ ይህን ምኞቱን የገነዘበ ቢሆንም እባብ ለእባብ ይተያየል በካብ እንዲሉ በግልጽ በመቋቋም ፈንታ የሚጠልፈው በስላች ነበር።

«ይህንንኳ የምስክር ወረቀት የማታቀርብበት የሳይኮሎጂ ዶክተርነትህ ይመስለኛል። እሺ እሱም ይሁን። ስለ ሰውየው ያለህን አስተያየት እንቀበለው። አሁን ጥያቄው ምን እናድርገው ነው። የዚህ ኮሚቴ አባል ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው። »

«ዐውቃለሁ። ከዚህ ማምጣታችንኮ ስሕተት ነው ብያለሁ። »

«ኢ.አ.ወ.ሊ. ሊሆንም አይችልም። ወጣት አይደለም። ተማሪም አይደለም » ሲል ሌላው የኮሚቴ አባል ለጠቀ።

«በዲሞክራቲክ ፍሮንት ውስጥም እስከዚህ ሊጠቅም አይችልም። »

«ቀሚስ አልብሰን ኢ.አ.ሴ.ሊ. እንመድበዋ! »

«ለቀልድ ጊዜ አለው። እሱን እንተወውና በጥሞና እናስብበት » ሲል የኮሚቴው መሪ ተኮሳተረ።

ብዙ ሐሳቦች ቀረቡ። ክርክርና አማራጭ ተደረገባቸው። በመጨረሻ «ዘርፍ ውስጥ የአንድ መሥሪያ ቤት ሕዋስ ተመረጠለት።

ሌላው ከባድ ክርክር ስለ ቀጣናው ጣቢያ መጋለጥ ጉዳይ ነበር። «ሰውየው በየትኛውም ክፍል ቢሆን በሕዋስ ደረጃ ይመደብ። ግን በባንዶች ተወናብዶ ቢከዳ ይህ ደግሞ ከቅብር ጊዜ ወዲህ ተደጋግሞ የደረሰ ነው ወይም ድንገት ተይዞ በምርመራ ቢያምን በቀጥታ ይህንን የቀጣና ጣቢያ አያጋልጥም ወይ? ከባድ የዲስፕሊን ስሕተት የምለው ይህንን ነው። ፓርቲያችንን ከአደጋ ላይ የሚጥል » አለ የኮሚቴው መሪ እርግጥ አድርጐ በድጋሚ። «እና ይህንንስ አደጋ እንዴት እናየዋለን። »?

አስተማሪው አሁንም መልሱን አቀረበ። «ይህንን ሥፍራ አስንጠቀምበት ከዓመት በላይ ሊሆን ነው። አንተ ራስህ ደጋግመህ እንዳልከውም ረጅም ጊዜ ስለ ተጠቀምንበት ለመጋለጥ ያለው ዕድል በጣም ከፍተኛ ሆኗል። ቀበሌዎችም

ዐይናቸውን ሳያተኩሩበት የቀረ አይመስለኝም። ጆሮ ጠቢያቸውን እንድ አሸዋ በየሡፈሩ በትነውታል። ስንወጣ - ስንገባ እነማን ናቸው? ምንድን ናቸው? ማለታቸው አይቀርም። ስለዚህ ሰውየውን አመጣነውም አላመጣነውም ይህንን ሡፈር በአጭር ጊዜ መለወጣችን የማይቀር ነበር። አሁንም ሳንውል ሳናድር መለወጥ አለብን። ከዚያ በኋላ፣ ቢያዝ ቢከዳ ቢመራ ማንንም አያገኝም።

«የበላይ አካል ቤት እስኪያስፈላልግ ጊዜ እንዳይወስድ ነው ሥጋቴ። »

«እኔ ችግር ያለ አይመስለኝም » አለ አስተማሪው «ቤት መለወጥ የሚፈልግ ሞልቷል። ሌላው ቢቀር ሱፐር ማርኬት መስተዋት ላይ የሚለጠፈውን ማስታወቂያ መመልከት ይበቃል። ቤቶችና ከተማ ልማት ሚኒስትር ያሉትስ ምን ይሠራሉ? »

«በቀረቡት ሐሳቦች ሁላችሁም የምትስማሙ ከሆነ ሪፖርቱን ለበላይ አካል አስተላልፋለሁ » አለ የኮሚቴው መሪ። በአወንታ አራቱም ራሳቸውን አወዛወዙ።

ስብሰባው ከተበተነ በኋላ ማስረሻ ምን ማድረግ እንዳለበት ሰይቾንቶ ነጂው ነገረው። «በወረቀት ላይ አታሰፍረውም፤ በጭንቅላትህ ውስጥ ግን በሚገባ መዝግበህ ያዘው። አንድ አነስተኛ ስሕተት አንተንም ሌሎችንም አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል » አለው በማበከር ሌባ ጣቱን እያጣቀሰ። «ነገ ጧት ቁርስህን ከበላህ በኋላ የትም መብላት ትችላለህ፤ ፍል ውሀ ትሄዳለህ። ልብ አድርግ። አሮጌው ፍል ውሀ አይደለም። አዲሱ ነው። መኪኖች ከሚቆሙበት መግቢያ በር ላይ፤ ፎጣ፤ የውስጥ ልብስ የግር ሹራብና ሳሙና የሚሸጡ ሱቅ በደረቴዎች አሉ። ይህንን በሚገባ ያዘው። ቡናማ የከፋይ ጃኬት የለበሰና ከካኪ ኮፍያው ሥር ሰማያዊ እስክሪፕቶ የሰካው ሱቅ በደረቴ ቀርቦ ይፈለጋሉ? ሲል እንድትገዛ አረንጓዴ ፎጣ ይዘረጋልሃል። አልገዛም በለው። እንደገና ጥቁር የእግር ሹራብ ያሳይሃል። ዋጋውን ጠይቀው። ሦስት ብር ከአሥር ሣንቲም ልብ በል ሦስት ብር ከአሥር ሳንቲም ይልሃል። አንተ ግን ሁለት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም - ሁለት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም ብለው። ይህ የመገናኛ ኮድህ ነው። ሥራ ስለ መያዝህም ሆነ ስለ ሌላውም ነገር እሱ አስፈላጊውን ይፈጽምልሃል። ወይም ምን ማድረግ እንዳለብህ ይነግርሃል። ገባህ?

መመሪያው ግልጽ ይሁን እንጂ ለማስረሻ ሕይወቱ በሚያስፈራ ምሥጢራዊ የጨለማ አዘቅት ውስጥ ድንገት የሰመጠ ሆኖ ተሰማው። «ከዚህ

ሁሉ እንቆቅልሽ፣ ምናለ ብትተውኝና እንደምሆነው ብሆን? » አለ በጭንቀት ድምፁ እየተሰባበረ።

«ምንም እንቆቅልሽ የለበትም። አትፍራ። ትግል ነው። ይበልጥ እየተዳህ ስትሄድ ደግሞ ልጓም የማይገታው ፈረስ ልሁን የምትለው አንተው ራስህ ትሆናለህ። ዋናው ነገር ወለም ዘለም አለ ማለት ነው። ይህ አደገኛ ነው። በተረፈ መልካም ዕድል።

«እንዲህ አርጐም ዕድል የለ? » አለ ማስረሻ በሩ ሲዘጋ ብቻውን።

ማስረሻ ዕረፍት የሌለው ሌሊት አሳለፈ። እስከ ሌሊት ድረስ እንቅልፍ በዐይኑ ዝር አላለም። ከጣሪያው ኮርኒስ ጋር ተፋጥጦ የሚያስበውን ሳይውቀው በሐሳብ ብቻ ተጨነቀ። በኋላ እንደ ምንም ሽልብ ቢያደርገውም አንድ ጊዜ የውሾች ጩኸት አንድ ጊዜ የጣሪያውን ቆርቆሮ የሚያንኳኳው ነፋስ ብዙ ጊዜ ደግሞ የመኝታው ትኋንና ቁንጫ እያባነነ አስቸገረው። ከንጋቱ ላይ ትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ የወሰደው እንቅልፍ ስንኳ አስፈሪና አሰቃቂ ቅዠት የሞላበት ነበር።

ጧት በጠራው የበጋ ሰማይ ላይ ደማቅ ፀሐይ ሰፈነች። ነፋሻማ የሆነ ቀላል አየርም የአዲስ አበባ ከተማን አጠናች። ለሥራም ለፍቅርም ለሽርሽርም የአየሩ ጠባይ ተስማሚና አስደሳች ነበር። ለማስረሻ ግን በዚያ ብራ ጧት፣ በዚያ ደማቅ ጨረር፣ በዚያ ነፋሻ አየር ሕይወት አስፈሪ ጨለማ ሁሉም የአካባቢ ዓለም ድብዝብዝ ጭጋግ ሆኖ ታየው። በዚህ መካከል ግን እንደ እጅ ባትሪ ጮራ በአእምሮው ውስጥ አንድ ነጥብ ይታየው ነበር - ዘለቃ።

ማስረሻ ይሙትም ይኑር ወደማያውቀው እንቆቅልሽ ሕይወት ውስጥ ከመስመጡ በፊት ዘለቃ በምን ሁናቴ እንደምትገኝ ለአንድ አፍታ ያህል ለማየት ብቻ ብርቱ ጉጉት ተቀሰቀሰበት። ምን እንደሚፈይድለት ራሱም አልገባውም። እንዲሁም አሰኘው።

እንደ ተነገረው ወደ ፍል ውሀ በመሄድ ፈንታ በደመ ነፍስ እግሩ እየሳበው ወደ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ታጠፈ። ከዚያም ከአንድ አጥር ግጥ ተከልሎ ቁሞ በግቢው በር ላይ ዐይኑን ተከለ። ዘለቃ ወደ ሥራ ስትሄድ ለማየት ነው። ሲያያት ምን እንደሚያደርግ ራሱም ገና አላወቀም። ለእርሱ እንደ ብዙ ሰዓት የረዘሙ ጥቂት ደቂቃዎች ከጠበቀ በኋላ የግቢው በር በዘበኛ ተከፈተ። ማስረሻ ዐይኑን ብልጥጥ አደረገ። አንድ ትልቅ ፋሚሊ ፔጆ ወጣና በአጠገቡ ሲያልፍ ከማፍጠጡ የተነሣ ትዕይንቱ ስለ ደበዘዘበት ዐይኑን ጭፍን ክፍት አድርጐ አስተዋለ። አሽከርካሪው፥ የእስላም ኮፍያ ያደረገ አንድ ወፍራም ሰው ነበር።

የማርካቶ ነጋዴ ይመስላል። ማናዬ አለመሆኑን እርግጠኛ ነው። የማርካቶ ነጋዴ ቀየሩ? የሚል ግምት አደረበትና ግብዝነታቸውን ስለሚያውቅ ተጠራጠረ። አሁንም ጠበቀ። ግን በሩ አልተከፈተም። ሌላ አውቶሞቢል አልወጣም። በአቅራቢያው ወደሚገኝ ኪዎስክ ጐራ አለና ሲጋራ ገዝቶ ከቀጣጠለ በኋላ እንደ ዋዛ ጠየቀ «ያ ግቢ የወይዘሮ ዘርፈሽዋል አይደለም እንዴ? »

«ዱሮ ነበር። »

«አሁንስ? »

«አሁንማ ሌሎች ሰዎች ናቸው ያሉበት » አለ የኪዎስኩ ነጋዴ በጥርጣሬ እያስተዋለው።

«እነ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የት ሄዱ? »

«እኔ ሠርቶ አዳሪ ደሀ። ምን ዐውቃለሁ » ሲል የዕቃ መደርደሪያውን የሚያራግፍ ይመስል ጀርባውን ለማስረሻ ሰጠ። ጥርጣሬውና ሥጋቱ ከፊቱ ላይ የነበብ ነበር።

ማስረሻ የዘለቃን ሁናቴ የማወቅ ፍላጐቱ የበለጠ ገፋፋውና ቀድሞ እንደሚያስታውሰው የሕዝብ ቴሌፎን ካለበት ቡና ቤት ሄዶ መሥሪያ ቤትዋ ደወለ። የለችም። የት ሄደች? ከለቀቀች ቆይታለች። ሥራ ከለወጠች የት ነው? ምኑንም የሚያውቅ የለም ፡

የፈለገውን ባለማወቁ በሸቀ። በሌላ በኩል ደግሞ «እናታቸውን! ይኼኔ አድኃሪያን ተብለው ዓለም በቃኝ ወይም እንጦርጦስ ወርደዋል። ዋጋቸው ነው! » የሚል በደሉን የሚያጽናና ሐሳብ ይዞ ወደ ተነገረው የእንቆቅልሽ ዓለም ተጓዘ.....

# ምዕራፍ ሁለት

ማስረሻ እንደ ተመኘው ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ዘለቃ ከሰማዩም ሆነ ከምድሩም እንጦርጦስ አይውረዱ እንጂ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ወልደው ከብደው ተከብረው ስንት ዘመን የኖሩበትን ግቢ ያስለቀቃቸው የዚሁ ፍራቻ ነበር።

የኃዘን ቁስልን ጊዜ ይሽረዋል እንዲሉ፣ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከማናዬ ሞት በኋላ እየተጽናኑ ሄደው፣ እያደርም እንደ ቀድሞው ዘወትር አልጋቸውን

የሚያሞቅላቸው ሰው ባያስቀምጡም መቸም የተፈጥሮ ፍላጎት ነውና አብዮት የሚባል የጊዜው መጥፎ ዕድል አቆራኝቷቸው ከሚጐበኙዋቸውና ከሚያዩዋቸው አንዳንድ ወንዶች ጋር አልፎ አልፎ ሲወዛወዙ እየረሱትም ሄደው የሥልሳ ስምንትን ዓመተ ምህረት መጨረሻ እየረሱትም ሄደው ዘጠኝን ዘመን የተቀበሉት ከቀን ቀን ስሜታቸው ደስ እያለው ነበር።

ለዚህም ስሜታቸው ብዙ ምክንያቶች ነበሩ። አንደኛው ምክንያት የካርቱም የራዲዮ ብሮባጋንዳ ብሮባጋንዳ ሆኖ አለመቅረቱ ነው። እንደሚሰሙት ከሆነ በጣሊያን ጊዜ አርበኞች ተሹመውበት እስከነበረው እስከ ቴፒ ጠረፍ ድረስ የደርግ ተቃዋሚ እየገፋ መጥቷል። የወልቃይት ጠገዴ፣ የአርማጭሆ የአዳኝ አገር የጫቆ የቋራ የወንድ ሁሉ ተነቅንቆ ለኢ.ድ.ህ እየገባ ነው። ጐንደርን ለመያዝ ምንም የሚያግድ ነገር አይኖርም። በጐንደር ከተማ የደርግ ደጋፊ የነበሩት ጥቂት ሰዎች ጨንቋቸው ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ናቸው አሉ። ጐንደር ላይ ሆኖ የቀድሞውን መንግሥት እንደ ገና ማወጅ ነው። እንዲያውም እንደ ቀድሞዎቹ ነገሥታት አልጋ ወራሽ ጐንደር ፋሲል ግንብ ላይ የአባታአቸውን ዘውድ ቢጭኑ የበለጠ ያምራል። ታሪክም ይታደሳል። ከዚያም ወሎም ጐጃምም ወዲያው መገበሩ የማይቀር ነው። አሁንስ ቢሆን ለደርጉ ዝም ያለው መች ከልቡ ነበር። ቢቸግረው እንጂ። በአዲስ አበባ ከተማም ቢሆን ለደርግ ሲያቶስቱስ የነበረው ሁሉ ጭንቅ እየያዘው ሄዷል። ዘመቻ አቋርጦ የተመለሰው ተማሪና መምህር ከተማውን በቁጥጥሩ ሥር አውሎ ሣር ቅጠሉ ድንጋይ አፈሩ ሁሉ «ኢ.ህ.አ.ፓ » የሚል ቃል የሚተፋ ይመስላል። አንድ ጊዜ ለደርግ ቁመናል የሚሉ የቀበሌ መሪዎች ሁሉ ዛሬ አንገታቸውን ማቀርቀር ይዘዋል። ደፍረው አይናገሩም። አካሄዳቸው ሳይቀር ሹልክ ሹልክ ነው። አንድ ቀን ጧት የቤታቸው በርና አጥሩ ሁሉ በቀይ ቀለም «ደርግ ይወድማል። ባንዳ ይደመሰሳል። ኢ.ህ.አ.ፓ. ያሸንፋል » የሚል ጽሑፍ ተእልቅልቆበት ሲያገኙ «ግቢዬን አሽእብረቁልኝ አይደል እንዴ? ወቸው ጉድ መቆየት ደግ ይህንንም አየን? » እያሉ ተፍነከነኩ።

«ጊዜ ያመጣው አይደል? መቸስ ይሁና! » እያሉ በሚያቃልሉት መጠን የሰማንያ ብር ሙክት ታርዶ ሸንጥ ብልት ተወራርዶ ጠላ ተጠምቆ ጠጅ ተጥሎ ውስኪ ተከፍቶ ቄጤማ ተጐዝጉዞ የአዲስ ዓመት መብቻ የተቀበሉት በዚህ ዓይነት ስሜት ነበር። ደስ - ደስ እያላቸው አነጉት።

ከሁለት ዓመት በፊት ክረምቱን እንደዚሁ ትርምስ ነበር። ልጅ ጉግሣ ወታደሩ ሌላው ከዚያም በራዲዮና በጋዜጣ የመሳፍንቱን የመኳንንቱን ስም

ማጥፋቱ ቀጥሎ መስከረም ሁለት ቀን ያልታሰበው ዱብ ዕዳ። የተቀበሉት ከሰሎሞን ሐረግ የመጡት፥ ፀሐዩ ንጉሠ ነገሥት ከሥልጣን ወረዱ ተብሎ ታወጀ። ጆሮ እማይሰማው ጉድ የለ! ከሁለት ዓመት በኋላ አሁንም ደርግና ደጋፊዎቹ ሁሉ ከረምቱን ሙሉ እንደዚያው ጊዜ በየመንገዱ በየአደባባዩ በየሠፈሩ በየቤቱ ተመሳሳይ መዓት ሲወርድባቸው ከረመ፤ በሁለተኛው ዓመት «የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥትና የዚህም መንግሥት አባሎች ዛሬ መስከረም 2 ቀን 1969 ዓ.ም ጀምሮ የተወገዱ መሆኑን በእነርሱም ቦታ...... » የሚለውን የራዲዮ ድምፅ በሐሳባቸው ያዳምጡና ከዚህ በኋላ ያለውን ማለም ጥቂት ግራ ይገባቸዋል።

«ሰዎቻቸው እንደሆኑ ገና ጐንደርም አልተቃረቡ። አሁን ከተማውንና ደርግን ፈጥርቀው የያዙት ከዚህም ከዚያም የተጠራቀሙ ወጣቶች ናቸው። የኢ.ህ.አ.ፓ.ዎቹ ነገር ለወይዘሮ ዘርፈሽዋል እምብዛም አይገባቸውም። እንዲያውም በአንዳንድ ሥፍራ ከደርግም ብሰው ጠጅ ቤት ወፍጮ ቤት፣ ጋሪ ለመውረስ ሞክረው ነበር ይባላል። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ለዚህ ጥርጣሬ የራሳቸውን መጽናኛ መልስ ያገኙለታል። ደርግ ዝመቱ ብሎ በግድ መቸም ልጆች ናቸውና መካሪ ዘካሪ ተቆጪ ሲያጡ ነው። «ሰዎቹ » መጥተው በትረ ሥልጣኑን ይያዙ እንጂ የተሳሳተውን ያርሙታል፤ የጐበጠውን ያቀኑታል። ወትሮውንም ተዘናግተው ተበለጡ እንጂ ምን ይሳናቸዋል?

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ይህንን እያለሙ ዐውደ ዓመቱን ውለው በቀላቸውን አሟጥጦ የሚያወጣላቸው ይመስል በኈልተኛው ዓመት የዕለቱ ዕለት የጠበቁት ዐዋጅ ሳይነገር ቀረ። ግን በፊት «ዝጉልኝ አያደንቁረን » ያላሉትን ያህል አሁን ጆሮዋቸውን ከራዲዮ ላይ መትከላቸው አልቀረም ነበር። ሳምንት ሳይሞላ ከተመኙት የተገላቢጦሽ የሆነ ነገር ሰሙ።

ኢ.ህ.አ.ፓ እና ደጋፊዎቹ በየግድግዳው በየበሩ፥ በየአጥሩ በሚጻፈው ውግዘት፣ ታች ታቹን በሚበተን ወረቀት፥ በቃል ከሰው ሰው በሚተላለፍ መልእክትና ሌላም ቅስቀሳ ለሚያካሂዱት ዘመቻ አጸፋው ለመጀመሪያ ጊዜ በዜና ማሰራጫዎች ተከፈተ። «በአብዮት የሚነግዱ ፀረ - ሕዝቦች ሲጋለጡ » በሚል አርእስት የተሰጠው መግለጫ የሚያስፈራራ ኃይለ ቃል ባይኖርበትም የኢ.ህ.አ.ፓን ፀረ - ሕዝብነት በአጠቃላይ የሚያወሳ ነበር። ወይዘሮ ዘርፈሽዋልም፥ ነገሩን አክብደው አልተመለከቱትም ነበር። «ጀመሩ እንግዲህ ያንን ልፍለፋቸውን። አገር ዝንተ ዓለም በራዲዮ ብቻ ይገዛ መሰላቸው? እንግዲያው በከተማውም መድረሻ አጥተዋል » ሲሉ አቃለሉት። የዘለቃና

የሌሎችም አስተያየት ተመሳሳይ ነበር። በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሞሰብ ቤት ማታ ማታ የሚገናኙት እነ ኮሎኔል ደመላሽና እነ ፊታውራሪ ወርቃለማሁ፥ እነ ነጋድራስ አገኘሁ፥ ጥብሱን በዊስኪ እያወራረዱ «እንግዲህ ማጣፊያው ሲያጥር መቀበጣጠር ነው » በማለት ተሣለቁ።

ከሁለት ቀን በኋላ እንደዚሁ «ፀረ ሕዝብ ሁሉ በጭቁን ጫማ ሥር እንደ ድመት ያለቅሳል » በሚል አርእስት ሌላ መግለጫ ወጣ። ከፊተኛው ከረር ያለ ነበር። «ምነው ይህንን ራዲዮ አፉን ቢዘጉት ግድግዳና አጥሩን ሁሉ ከመለቅለቅ ይልቅ? ራዲዮ ጣቢያውን ጭምር አይይዙትም? ምን ይጠብቃሉ? » በማለት በመጠኑ በስጨት አሉ።

ለአንድ ሳምንት ያህል፥ የዜና ማሰራጫው ዘመቻ ጋብ ብሎ፣ የበሠፈሩ የወረቀት ብተናው የወሬው የግድግዳው ጽሑፍ ሥራ ተፋፍሞ ሲቆይ የወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ የዘለቃና በየጊዜው የሚገናኙት ‹ወገኖቻቸው› ስሜት ተንሰራርቶ ቆየ። ዘለቃ አሁንም አጥብቃ ከያዘችው የመረጃ ኃላፊ ወጃችዋ ዘንድ አንዳንድ ጥቆማዎች አምጥታለች። አሁን አሁን ብዙ ጊዜ ቤታቸው አይመጣም። ሥራ የበዛበት ወይም የተጠነቀቀ ይመስላል። ባልታሰበ ሰዓት ቴሌፎን ይደውልላታል። ባልታሰበ ቦታ ተቃጥረው ይለያያሉ። በእነዚህ ግንኙነቶች ወቅት ጣል ጣል ከሚያደርገው አነጋገር እንዳቀነባበረችው አንድ ዓይነት ለውጥ የሚመጣ ይመስላል።

-ምን ዓይነት ለውጥ? - ሲል ኮሎኔል ደመላሽ ጠየቃት።

«በእውነት አላውቅም » ትላለች፥ በሁሉም ላይ ዐይኗን አፍጥጣ። «እሱም አይናገርም። ዘግቶታል። እንደ ገባኝ ከሆነ በአጠቃላይ የሚለው፥ አለ አይደለ? ሞቅ ብሎት ሲቆጣ - ያበጠ ይፈንዳ - እንደዚህ ሊቀጥል አይችልም። ይለይ እንጂ አልሆነም - እንግዲህ እንደዚህ ነው ነገሩ። የሚፈነዳ ነገር አለ፥ የሚለይ ነገር አለ ማለት ነው። ምናልባትም በመካከላቸ።

«በመካከላቸውማ ያው ሁልጊዜ የምንሰማው ነው። »

«ማንኛውም ይሆን አሁን ደሞ? » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንደ ዋዛ ጠየቁ።

«እኔ የምሠጋው ትሻልን ፈትቸ ትብስን አገባሁ እንደ ሚባለው እንዳይሆን ነው » አሉ ፊታውራሪ ወርቃለማሁ።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኋላ ጭውውታቸውን የተኩስ ድምፅ አቋረጠው።

ጧ! - ጧ! - ጧ! - ጧ! - ትርምስ! አለ የአውቶማቲክ መሣሪያ።

ዷ! - ዷ! - ዷ! ጠመንጃ ተተካ።

ቡም! የቦምብ ድምፅ የሚመስል ታከለ። መልሶ አውቶማቲክ ተንጣጣ።

ሁሉም ጆሮዋቸውን አሹለው አዳመጡ። ወይዘሮ ዘርፈሻል ግን ከተቀመጡበት ደንደርድረው ከደመላሽ ጐን ተጠጉ። ደመላሽ «አይዞት - አይዞት » ሲል በክንዱ እንደ ማቀፍ ብሎ እያደፋፈረ ነጋድራ አገኘሁን ተመለከተ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ማናዬ ከሞተ ወዲህ ነጋድራስ ጠጋ - ጠጋ እያሏቸው ሄደው ነበር። ብዙ ምሽት ሌሎች ወደየቤታቸው ሲሄዱ እርሳቸው ለብቻ ወደ ኋላ ቀርተዋል። በጭንቀት ጊዜ ወደ ነጋዴው ሳይሆን ወደ ወታደር በመጠጋታቸው ደመላሽ ኩራት ቢጤ ተሰማው። ነጋድራስ ደስ አላላቸውም። ስሜታችውን ዋጥ አደረጉና «የት ይሆን ደሞ? » ሲሉ ማንንም ሳይሆን በደፈናው ጠየቁ።

«ከዚያው መከእኛ ግቢ ይሆናላ! » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከደመላሽ ጐን እንደ ተጠጉ።

ደመላሽ ራሱን ነቀነቀና የወይዘሮ ዘርፈሽዋልን ክንድ እየ ደባበሰ «የለም! አይደለም። አግጣጫው ወደ ባቡር ጣቢያ ገደማ ነው » አለ ጆሮውን ወደ አንድ በኩል ዘንበል አድርጎ ችሎታውን በመተማመን አኳኋን።

ምሽቱ መልሶ ጸጥ እርጭ አለ። ሰዎቹ ወደ የቤታቸው ለመግባት እየተሰናበቱና እየተሰነባበቱ ሲነሡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከተል አሉና «ደመላሽ አንተማ ቆይ እንጂ ቤት አድርሰኝ። ዘለቃ የለች በእንደዚህ ያለ ሁከት ጊዜ ከዚሁ አድራለሁ እንጂ ብቻዬን ንክች አላደርጋትም » ሲሉ ተናገሩ።

«ሹፌሩስ? » ሲል ደመላሽ ጠየቃቸው።

«የዛሬ ጊዜ ሠራተኛ ደሞ ምኑ ይታመናል? በነሱ ብሷል። »

«እሺ በመኪናዬ እከተላችኋለሁ » ደመላሽ ወደ ኋላ ሲቀር ነጋድራስ አገኘሁ ለጨረፍታ በትዝብት ተመልክተውት ወጡ፡

ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት ሲደርሱ ዘለቃ አልገባችም ነበር። «ባዶ ቤት ጥለኸኝ ልትሄድ ነው? » ሲሉ በቀልድ ተኮሳተሩበት። ዘለቃ ለስድስት ሰዓት አሥር ደቂቃ ያህል ሲቀር መጣች። ደመላሽ ሰዓት እላፊ ከመሙላቱ በፊት ቤቱ ሊደርስ የማይችል ስለ ነበር እዚያው አደረ።

# ፪

የምሽቱ ተኩስ በጆሮው ከሰማው ሰው በተጨማሪ በበነጋው ባሉ ቧልታ እንደ ቋያ እሳት በቅጽበት እየ ተዛመተ ከነፋስ ስልክ እስከ እንጦጦ፥ ከኮልፌ፣ እስከ ኮተቤ ከተማውን አዳረሰው። አንዱ ከተነገረው ሲቀጥል ሲጨምር ሌላው በመላ ምት ሲፈጥር ከሰው ሰው ሲባዛ ሲራባ ወሬው ሥፍር ቁጥር የሌለው ዓይነት ሆነ።

-ምንድን ነው የሆነው እባክህ? ትክክለኛውን ወሬ አግኝተሃል፡ - ሲል አንዱ

በጉጉት ይጠይቃል።

-ፓህ! ኧረ ተወኝ! እርስ በርሳቸው ተጨፋጨፉ በማዳነቅ መዳፉን እንደ ሰይፍ ይለጋል።

-ሰማህ? ኢ.ህ.አ.ፓ. እኮ ሦስቱን እሸከም አደረገች! በማጋነን መዳፍ ይሰየፋል።

-እነማንን?

-ሊቃነ መናበርት።

የባሰበት አንዳንዱ ለወሬ ሞትኩ ደግሞ፣ «ጉድ አይደለም? » ሲል ዐይኑን በአድናቆት በልጥጦ ያጋጠመውን ጓደኛውን ይጠይቃል።

-ምኑ?

-የትናንቱ ምሽት።

-ትናንት ምሽት ምን ሆነ?

-ትናንት ምሽት ምን ሆነ? ድብልቅልቅ ተኩስ ነዋ!

-የት? –

-አልታወቀም።

-እና ምን ሆነ?

-የሆነውንስ እኔ እንጃ! ብቻ! ብቻ! ነገሩ ከባድ መሆን አለበት።

በዕለቱ የሚደርሰውን ነገር ለማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ በዚህ ቀውጢ ጊዜ የወሬ አቀባባዩና ተቀባዩ ሁሉ የተለያየ ስሜት አለው። ዐመል ሆኖበት በመንደር ከተፈሳችው አንሥቶ በአገርና በዓለም አካባቢ የሆነውን ሁሉ አነፍንፎ መልሶ ዐዋቂነቱን የሚገልጽ አለ። እስከዚህም ሳይጓጓ የመጣለትን ወሬ የሚቀበል፣ ግን ጥቂት ሳይጨምርና ሳይቀምም ለሌላ መንገር የማይሆንለት ደግሞ አለ። በአብዮቱ ከዚህ ወይም ከዚያ ወገን የተሰለፉትና ውጤት በቀጥታ የሚመለከታቸው ደግሞ አሉ። ይህ ሁሉ ወሬውን ሲያጠያይቅ፣ ሲያናፍስና ሲያራግብ ዋለ።

የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ‹ወገኖችም› የሆነው ነገር በትክክል ለማወቅ በየፊናቸው ሲያጠያይቁና ሲያመራምሩ ዋሉ። በዚህ አካባቢ ራሱን እንደ አለቃ ድርጐ የሚቆጥረው ኮሎኔል ደመላሽ በተለይ ከፍተኛ ጥረት አደረገ። አሁንም አባል ከሆነበት ክብር ዘበኛ ክበብ ሄደ። የዘወትር የመረጃ መሥመሩን አላገኘም። ከሌሎች ጋር እንደ ዋዛ ጣል - ጣል ያደረገው ጥያቄም የሚያረካ መልስ አላስገኘለትም። በጦር ሠራዊት መኰንኖችና በፖሊስ ክበብም እንደዚሁ። የደላላና የጡረተኛ መናኸሪያ የሆኑትን በአድዋ አደባባይ የላየን ባርና ትንሿ ቡና ቤትም በማርካቶ ቃኘው ሻለቃ ቡና ቤት በአራት ኪሎ ብርሃንና ሰላም ቡና ቤት አንሥቶ መደዳዎቹን አዳረሰ። በአጠቃላይ ሊያገኝ የቻለው ፍንጭ ከሁለት ምክትል ሊቃነ መናብርት በአንዱ ምናልባትም በተቀዳሚው ምክትል ሊቀ መንበር ላይ አደጋ መጣሉን ነው። የአደጋው ውቴትስ? በእርግጠኛነት የሚመልስ አልተገኘም።

ኮሎኔል ደመላሽ በመጨረሻ ላይ ቢቸግረው፥ ማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ቴሌፎን ደወለ። አንዳንድ ምሽት ሲገናኙ እየጋበዘው የተዋወቀው፣ ከዚያም በኋላ በተደጋጋሚ ተገናኝተው አንዳንድ መረጃዎችን ለነገረውና እንደ ግምቱም ኢ.ህ.አ.ፓ. የመሰለውን ጋዜጠኛ በመሥሪያ ቤቱ የቴሌፎን ማዞሪያ ጠየቀ።

-ሀሎ!

-ሀሎ! ጓድ ገነነ?

-ገነነ የለም።

«የት ሄደ? » ሲል ደመላሽ አለዝቦ ጠየቀ።

በፊትም ቢሆን ጓድ የሚለው ቅጽል የጨመረበት ሆን ብሎ እስኪያረጋግጥ ድረስ የትርጉም ሽሚያውን በሁለቱም በኩል ክፍት ለማድረግ ነበር። «እኔ እንኳ » የሚል መልስ አገኘ። «ዛሬ ሥራ ይገባል? » ሲል እንደገና ጠየቀ።

«ሊገባም ላይገባም ይችላል። አላውቅም » ሲል ሌላው ጋዜጠኛ ድርቅ ባለ አነጋገር መለሰለት። ያልነገረው ግን ደመላሽ የሚፈልገው ጋዜጠኛ የዚያን ቀን ከሰዓት በኋላ በሥራ ገበታው ላይ እንዳለ በጸጥታ አስከባሪዎች መወሰዱን ነው።

ደመላሽ ትንሽ አቅማማና ለስለስ ባለ አንደበት «አይ! መቸም በስም የማውቀው እሱን ስለሆነ ነው እንጂ ጉዳዩ ሁላችሁንም የሚመለከት ነው። አየህ ወንድም! በአሁኑ ጊዜ ሕዝቡን ሲጨነቅ የምታበረታቱት ግራ ሲገባው የምታስረዱት እናንተው ናችሁ። በእውነቱ ኃላፊነታችሁ በጣም - በጣም ከባድ ነው። እምቸም በዚህ ዘመን እናንተ ባትኖሩ ኖሮ ሁላችንም ድንብርብራችን ወጥቶ ነበር። እና፥ አሁንም ትናንት በተሰማው ተኩስ ሕዝቡ ተረብሿል። ተጨንቋል፤ እና የሆነውን ልትነግሩት ልታስረዱት ይገባ ይመስለኛል » አለውና፥ በመጨረሻ እንድ ዋዛ «ለመሆኑ ትናንት ማምሻውን ምንድን ነው የሆነው? » ሲል ጠየቀ።

«የሆነውን ማታ ትደርሱበታላችሁ » በማለት ጋዜጠኛው ቴሌፎኑን ከጆሮው ላይ ዘጋበት።

ፍርጥም ያለው የጋዜጠኛው አነጋገር የደስታ ይሁን የንዴት ኮሎኔል ደመላሽ እርግጠኛ ሊሆን አልቻለም። ግን፥ በሁለቱም በኩል እርሱ እንደሚመኘው ተረጐመው። ደስ ብሎት ለማስመሰል የተኮሳተረ ከሆነ የደርግ ተቃዋሚ ወገን ነው። ከየትኛውም ክፍል ይሁን። የተናደደ ከሆነ ደጋፊ ነው ማለት ነው። ስለዚህም የተባለው አደጋ በእርግጥ ደርሷል ከሚል ውሳኔ ላይ ደረሰ።

ማምሻውን እንደተለመደው ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ‹ከሀገር ምግብ ቤት› ተገናኙ። እያንዳንዱ በበኩሉ ያገኘውንና «መረጃ » የሚለውን ወሬ አሰማ። ዋናው የተጠበቀው ከዘለቃ ነበር። ግን የረባ ነገር አላመጥችም። እርግጥ ትናንት ሙሉውን ምሽት ከመረጃ ወዳጅዋ ጋር አብራ ነበረች። ራታቸውን ኢትዮጵያ ሆቴል በሉ። ለአጭር የዳንስ ጨዋታ ዋቢ ሸበሌ ሄዱ። ከዚያም ለግል ጨዋታ እስከ አምስት ሰዓት ተኩል ሆቴል ደ. አፍሪክ አመሹ። በዚህ ጊዜ ሁሉ አንድ ጊዜ የሚያስብ ሌላ ጊዜ በራሱ ከራሱ ጋር የረካ የሚመስል ከመሆኑ በስተቀር እንደ ወትሮ አመሉ እየተንጿረጿረ አዲስ ፍንጭ አልሰጣትም። ምናልባት አዲስ

የተገነዘበችው ሁናቴ ቢኖር፣ ካለወትሮው በየገባበት ሆቴል ሁሉ ሆን ብሎ ለመታየት የፈልገ መምሰሉ ነው። በበር ከፋቹ ከእንግዳ ተቀባዩ ከአስተናባሪው ጋር ሆነ ብሎ ሰላምታ ይለዋወጣል። በሆቴሉ ውስጥ የሚያውቀው ሰው እንዳለ በዐይኑ ፈልጐ እጁን ያወዛውዛል። የተለመደ ቢሆንም ሰዓት መመልከቱ ጥቂት የበዛ ነበር። «ግን አንድ አዲስ ነገር ለመኖሩ እርግጠኛ ነኝ። ስትል ደመደመች። ይህንን የተጠራጠረ አልነበረም።

ለሁሉም የራዲዮና የቴሌቪዥኑን ፕሮግራም ጊዜ ጠበቁ። በመካከሉ፣ መጠጡም፣ ምግቡም ቀረበ። ሁሉም ከሞሰቡ ዙሪያ ከተሰብሰቡ በኋላ «እንዴ ዛሬ ነጋድራስ የት ቀሩ? » ስትል ዘለቃ ጠየቀች። ስለ ትናንቱ መጠነኛ ትርኢት ምንም አታውቅም ነበር።

«አይ መቸስ ያ ሪሃቸው ተነሥቶባቸው ይሆናላ! » ሲል ኮሎኔል ደመላሽ በፌስ መለሰ።

ነጋድራስ አገኘሁ አለመምጣታቸው በጀ።

ወይዘሮ ዘርፈሻ ከልጅነታቸው ጀምሮ ያደጉበት የይሉኝታ ስሜታቸውን ጥለው ጥብሱንም፣ ቁርጡንም፣ ጥሬና ለብለብ ክትፎውንም ወጡንም፣ እንጀራውንም እንዲያው በአጠቃላይ በሞሰብ ላይ ያለውን የምግብ ዓይነት እንደ አውራ ጐዳናው አፈር ገፊ መኪና በኮሎኔል ደመላሽ በኩል ሲከምሩት በሞሰቡ ዙሪያ ሌሎች ሰዎች መኖራቸው ሳት እያላቸው ከዚያ ክምር በዚያ መዳፋቸው ዛቅ አድርገው ማጉረስ ሲቃጣቸው፣ ከዘለቃ አንሥቶ ሌሎቹ ሁሉ መታዘባቸውን ለመደበቅ ቢሞክሩም ደመላሽ ራሱ ኃፍረት ተሰማው።

«ብሉ እንጂ! አይጣፍጥም እንዴ! » ይላሉ ክምሩን ወደ ደመላሽ እየቆለሉ።

«ኧረ ይጣፍጣል! እየበላን ነው » ይልና ደመላሽሽ ክምሩን ንዶ ወደ መሐል ይገፋዋል።

ይህ ድርጊቱ ቢደጋገምባቸው ፊታውራሪ ወርቃለማሁ «ኧረ እባካችሁ እንብላበት! የሰነፍ ውድማ ይመስል ለምን በከንቱ ታንገዋልሉታላችሁ? » ሲሉ ቀለዱ።

የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሁለት ሰዓት ላይ ሲጀምር ሁሉም ጸት ብለውና ነቅተው ጠበቁ።

የዕለቱ ዋና - ዋና ዜና ሳይጨረስ «ሊሆን አይችልም! ከቶ ሊሆን አይችልም! » ሲል ኮሎኔል ደመላሽ ጮህ ብሎ ተናገረ፣ የሚያየውንና የሚሰማውን ማመን አቅቶት። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት አድርባቸ የነበረው ተስፋ እፍ እንደ ተባለ ሻማ ድንገት ድርግም ብሎ አሁን አንጀታቸው እርር ድብን እያለ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር ትናንት ምሽት ስለተጣለባቸው አደጋ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጡ ተመለከቱ። ዋናውና ሁለተኛው ምክትል ሊቃነ መናብርት ከጐናቸው ተቀምጠዋል። አንደኛው ሙከራ የተደረገው በቀድሞው የብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ አካባቢ መሆኑንና በአንዲት የበረደች ጥይት እግራቸውን ከመምታታቸው በቀር በደህና ሁናቴ የሚገኙ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ «....በእውነቱ እኔ አንድ ሰው ነኝ። የእኔ መኖርና አለመኖር የተቃጣውን ወይም የተቀጣጠለውን የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ አብዮታዊ ሰደድ የሚያቆም አይደለም......አንድ ነገር ከዚህ ላይ ላስገነዝብ የምወደው አቦት ከተቀጣጠለ አንድ ሰው ወይም ጭቁን አብዮታውያንን በመግደል አብዮትን ለመቀልበስ አለመቻሉን ነው..... » ብለው መግለጫቸውን ሳይጨርሱ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንደ ተናደ ቋጥኝ ያንን ሰውነታቸውን እያንከባለሉ ሄደው ቴሌቪዥኑን ዘጉት።

ሁሉም ለአንዳፍታ በአርምሞ አቀረቀሩ። የሐሳብና የትካዜ ሠራቂያን ወሰዷቸው። «ኤጭ ኤዲያ » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ድንገት ብንን ብለውና ሌሎችንም አባንነው። «ያንን ሁሉ መዓት ጥይት አዝንቦ እንዴት ይስታል? »

«ለጊዜው እሱ ባይለው ነው » ሲሉ ፊታውራሪ መለሱ።

«እንደሱ አይበሉ አዎ ደሞ። አድንዌ እንደ ሰው ጊዜ አይቶ የሚከዳ አይደለም። አስቀይምነውም እንደ ሆነ እስከ አሁን የተቀጣነው ይበቃዋል። ኧረ ወንድ ተኳሽ ጠፍቶ! » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በምሬት ተናገሩ።

«ልጆቹ ከሆኑ የልምድ ጉዳይ ልሆን ስለሚችል አይፈረድባቸውም » አለ ኮሎኔል ደመላሽ።

«ምነው? የቀድሞ ልጆች ስንት ቁም ነገር ይሠሩ አልነበረም? ገና አሥራ አምስት ዓመት የማይሞላቸው » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የደመላሽን አነጋገር የነቀፉ እንዳይመስላቸው አንደበታቸውን አለዝበው፣ «ሐሞቱ ነው እንጂ - ሐሞቱ ነው የጠፋው። »

«ልምምድ ቢሆን ይጠቅማል፣ ያስፈልጋል። » ፍርጥም አድርጎ ደገመው።

«ኮስታራ ሐሞትም። ኮስታራ ሐሞትም! » ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አጉመተመቱ።

ከብሽቀታቸው የተነሣ የሚነጋገሩበት ሐሳብ ጠፍቶባቸው ሁሉም በድንገት ዝም አሉ። ከዚያም ወዲያው (ያለ ወትሮዋቸው) ኮሎኔል ደመላሽ በጊዜ ወደ ቤቱ ለመሄድ ሲነሣ ፊታውራሪ ወርቃለማሁም ተከተሉ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋልም ደመላሽ እስከ ቤታቸው እንዲሸኛቸው ለመጠየቅ ከጀሉና ሁናቴውን አይተው መልሰው ተውት። ከደጃዝማች ገሠሠ ወዲህ ወንድ መፍራት ሲሉ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አዳር አይበሉት አደሩ። መጥፎ ቅዠት በተለይ ከሥልሳ ሰባት ወዲህ ብዙ ጊዜ ያውካቸዋል። እንደዚህ ሌሊት ግን የቁ ሥቃይ አይተው አያውቁም። ከሁሉም የከፋው ሰው ሲጠራባቸው ስንኳ የሚሰቀጥጣቸው ከአራዊት ሁሉ የሚጠሉት የእባብ ቅዠት ነበር። እንደ ቅጥራን በጠቆረና በወፈረ ውሀ ውስጥ ሰምጠው ትንፋሽ ለማግኘት የሚወራጩ ይመስላቸዋል። ውሀው የሞላበት የራሳቸው ቤት ሆኖ ይታያቸዋል። የውሀው መጠን ወደ ጣሪያው ከፍ እያለ ሲሄድ አንገታቸውን ብቅ ለማድረግ ሲደፍቁ፣ በጣሪያው ኮርኒስ ቀዳዳ በኩል ሁለት ዐይኑና ምላሱ እንደ ሻማ የሚንቀለቀል እባባ ጭንቅላቱን ብቅ ያደርጋል። ከእርሱ ለመሸሽ በተጋገረው ጥቁር ውሀ ውስት ቢወራጩ - ቢወራጩ ስንዝር መንቀሳቀስ አይሆንላቸውም። እባቡ ግን ጅራቱ ከኮርኒሱ ቀዳዳ ጨርሶ ሳይወጣ እንደ ሐረግ - ሬሳ እየተሳበ እየረዘመ ቅርንጫፉ እየተራባ ውሀ የሞላውን ክፍል ያዳርሰዋል። ከዚያም ሰውነት ላይ መጠቅለል ሲጀምር ለመጮህ ይሞክሩና ድምፅ አልወጣቸው ብሎ በእንቅልፍ ልባቸው ሲያቃትቱ ብንን ይላሉ። የነቁት ግን በራሳቸው ሳይሆን ጨኸታቸውን ስምታ ዘለቃ ስለ ቀሰቀሰቻቸው ነበር። መላ ሰውነታቸው በላብ ተዘፍቋል።

«ምን ሆንሽ እማዬ? አቃዠሽ እንዴ? »

«ኧረ ምን ቅዠት! ገሃነመሳት መግባት እንጂ በስማም ወልደ መንፈስ ቅዱስ። በደልኩህ። ጌታዬ » በሚንቀጠቀጥ እጃቸው አማተቡ።

«ኧረ እስቲ ዛሬስ ከዚሁ ተኚልኝ ልጄ። »

ከዚህ በኋላ ዐይናቸው ጣሪያው ላይ ባረፈ ቁጥር ቤቱ አስጠላቸው። ቀፈፋቸው። እንዲለቁት ያደርጋቸው ምክንያት ግን ይህ ብቻ አልነበረም።

# ፫

ከአዲሱ ዓመት መባቻ ላይ አንሥቶ ከአንድ ወገን በዜና ማሰራጫዎች ከሌላው ወገን፥ በተባራሪ ጽሑፎችና በአጥር ላይ መፈክሮች ሲካሄድ የቆየው የፕሮፓጋንዳ ፍልሚያ እያደር እየተባባሰበት ሄደ። ያልተዳረሰው ግድግዳ በርና አስፋልት ሳይቀር ቀለም እየተለቀለቀበት ያድራል። መፈክር፥ ውግዘት፣ ዛቻ፣ ስሽብ ወረቀት በየሰፈሩ ይበተናል። ከእጅ እጅ ይተላለፋል። ቀይ ባንዲራ በኤሌክትሪክና ቴሌፎን ሽቦ ላይ ጧት ጧት ተንጠልጥሎ ይገኛል። ‹ባንዳነት› ለሚጠረጠረው ወይም እስካሁን ወገን ባለመለየቱ እንዲታረም ለሚፈለገው አጫጭር የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች ይደርሳሉ። ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፣ ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ደግሞ የምክር የማሳሰቢያ የማስጠንቀቂያ መግለጫዎች እየተከታተሉ ይወጣሉ።

-ባለሥልጣን ኮርቻ የቋመጡ ንኡስ ከበርቴዎች እንደ ተመኙ ይቀራሉ።

-ሐቀኛ ወዝ አደሮች ጥቅማቸው በተነካ የቀኝ ክንፍ ንኡስ ከበርቴዎች አይወናበዱም።

አንደኛ ምክትል ሊቀ መንበሩ በተሞከረባቸው ግድያ እርሳቸውን በመደገፍና፣ ሙከራውን በመቃወም ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ በአብዮት አደባባይ ተደረገ። በየክፍላተ ሀገርም እንደዚሁ። ሐተታ ግጥም በጋዜጣው በራዲዮው ይጕርፋል። በዚህ ሁሉ መካከል አዲስ አበባ ከተማ ምጣድ ሆኖ በፕሮፓጋንዳ እሳት የተንገበገበች መሰለች። ብዙ ሰዎች ይህንን የፕሮፓጋንዳ ወይም የቃላት ጦርነት መቻል አቃታቸው። ያለመዱት ሁናቴ ነበር። በኅብረተሰቡ ታሪክ የሰሙት ከመለኮት የተቀበሉት ገዢዎች የሥልጣን ፉክክራቸውን እርስ በርሳቸው በሥውር ወይም በተወሰነ ጦር ሜዳ መፈጸማቸውን ነበር። በሕይወታቸውም የሚያውቁት ሹም ሽር ከተከናወነ በኋላ መገለጹን ነበር የታኅሣሡ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ስንኳ ከሆነ በኋላ ታወጀ። ሲሸነፍ ባለየበት በሥልሳ ስድስት ስንኳ ይህንን የመሰለ ግልጽ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት አልታየም ነበር። ወገን ለይቶ ከሚቆራቆሰው በቀር ብዙው ሰው ነገሩ ግራ ሆነበት። መረዳት ብቻ ሳይሆን መቻልም አቃተው። ውጥረት ጭንቀት የመንፈስ መረበሽ ሰፈነ። «ምናልባት ሰላም ባይነሱን » ይላል የትኛውም ወገን መሆኑን ሳይለይ። ይህንን አሸባሪ የፕሮፓጋንዳ መዓት ላለመስማትና ላለማየት፤ ዐይኑን መጨፈን ጆሮውን መከደን ይቃጣዋል። ችግሩ ሕይወት ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ

በዚህ ዓይነት ሊመራ አይችልም። ወደደም ጠላ፣ ማንም ሰው ዙሪያውን አካባቢውን ማየትና መስማት ግድ ይሆንበታል።

ጦርነቱ ግን በቃላት ብቻ ተወስኖ አልቀረም። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ወደ ዱላ ተሸጋገረ።

ወገን የለዩት ወጣቶች ተማሪዎች አልፎ አልፎ ቦዘኔዎች በየመንደሩ በየ ሠፈሩ እየ ተፈላለጉ መተናነቅ ያዙ። የአንዱ ወንገ ሦስት አራት ሆነው የሌላውን ወገን ብቻውን ያገኙት እንደሆነ ወደ አንድ ሠዋራ ሥፍራ ሳብ አድርገው ከሳማ ግርፊያ እስከ እርግጫ አቋሙን እርም ብሎ እኪተው «አሩን ያስበሉታል »። ከሰፈር ውጪ ታፍነው ገፈርሳ ሾላና የካ ጫካ ድረስ እየተወሰዱ ሕይወታቸው እንደ ሸረሪት በቀጠነ ድር ተንጠልጥላ እስክትተርፍ ድረስ ተወቅተው ታሽተው ተቀጥቅጠው የተጣሉ ወጣቶች ብዙ ናቸው። እንደ ምንም ከሰፈራቸው ተመልሰው ቁስላቸውንና ጥቃታቸውን እየጠገኑ ሲያገግሙ በቀላቸውን አብረው ያረግዛሉ። ከቤታቸው እንደወጡ ሳይመለሱ የቀሩም አሉ። የሆኑትን የሚያውቅ የለም። የመከላከል አቅም አንሷቸው የሾላና የገፈርሳ ጅብ ተቀራምቶአቸው ይሆናል። በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶች እንደዚሁ በውይይት ክበብ ጊዜ አቋማቸውን በግልጽ ያሳዩ ሠራተኞች ማምሻውን እየተጠለፉ «በአብዮታዊ የፍርድ መድረክ » «በሕዝባዊ ሸንጐ ፊት » እየቀረቡ ከጥፊ እስከ ግርፋት የመታረሚያ ቅጣታቸውን ተቀብለዋል። ግማሾቹ ወደ ተማረኩበት ወገን አምነው ገቡ። ግማሾቹ ደግሞ ቅጣታቸውን ተቀብለው ከወጡ በኋላ የበለጠ አመፁ - በሚቃወሙት ወገን ላይ።

አሁንም ነገሩ እብዚህ አልቆመም። ወደ አመረረ የተኩስ ፍልሚያ ተሸጋገረ። በመጀመሪያ ሲጀመር፤ ፀሐይ ሳትጠልቅ ሰው በበዛበት በሚተላለፍበት በሰንጋ ተራ አካባቢ አንድ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት የክፍል ኃላፊ በአውቶሞቢሉ ውስጥ እንዳለ በሽጉጥ ተገደለ። ወሬው በዜና ማሰራጫዎች ተነገረ። እንደ አዝማሚያው ሰዉ ተደሰተ ተናደደ፣ ግራ ተጋባ። ግድያውን በማስመልከት ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ «የአንድ ቆራጥ ታጋይ የደም ጠብታ በሺህ ፀረ - ሕዝብ ሕይወት ትመነዘራለች » የሚል ከባድ መግለጫ ወጣ። በተከታዮቹ ቀናትና ሳምንታት ሕይወት መመንዘሩን የቀጠለው ግን ተቃዋሚው ክፍል ሆነ። የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ባልደረቦች ናቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ሁለት ወጣቶች አንደኛው ፒያሳ ከቡና ቤት በራፍ ሌላ ካዛንቺስ ከመኖሪያ ቤቱ አጠገብ ተገድሎ ሁለት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች እንደዚሁ መንገድ ዳር በጥይት

ወደቁ። በፖለቲካ ትምህርት ቤት ላይ ከባድ የፈንጅ አደጋ ተጥሎ፤ ንብረት ጠፋ። በሰዎችም ላይ ጉዳት ደረሰ። እንደ ክራር ጅማት የከረረ ጭንቀትና ፍራቻ ሰፈነ። ሰዎች የገዛ ጥላቸውን ሳይቀር መፍራት ጀመሩ። በተለይ ከሁሉም የባሰው ውጥረት ሁለቱም ወገኖች መድረክ በተጋሩበት በከተማ ቀበሌ ማኅበራት ውስጥ ነበር። ከሞላ ጐደል ስለሚተዋወቁ እባብ - ለእባብ ይተያያል በካብ እንዲሉ፣ ሁሉም በየበኩሉ ያደባ ገባ። ላለመቀደም። ላለመበለጥ። ላለመበላት.....

በዚህ መካከል ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በኋላ አጣጥመው መብላታቸው ሳይቀር ዶሮ ሲታረድ ዐይናቸውን መለስ እንደሚያደርጉት ሁሉ ግድያው ትንሽ ቢቀፋቸውም በደርግ ውድቀት እርግጠኛነት እየተሰማቸው ሄደ። ምኞታችው አንሠራራ። የቆሬ መሬታቸውን ትራክተር ሲያገላብጠው ስለ ውለታቸው አድአ የጤፍ ዝዋይ የቦሎቄ ከፋ የቡና ተጨማሪ መሬት ሲሰጣቸው እህሉ በትሬንታ እየተጫነ ብሩ በሻንታ እየታጨቀ ሲመጣላቸው መጥፎ ቅዠት ከአሣቃያቸው ወዲህ ቀፋፊ የሆነባቸውን ይህንን ቤት አፍርሰው ቦሌ «ከጨዋዎቹ » ሰፈር ምን የመሰለ ቪላ ሠርተው ሲገቡ በሐሳብ ይታያችው ጀመር።

ዕድል እንደ ጥንት ሰፈርዋ ፊቷን ለመመለስዋ እንደ ተጨማሪ ማረጋገጫ የቆጠሩት ሌላም አንድ ጉዳይ ተሳካ።

ዘለቃ በመጀመሪያ፣ በኋላ ከውርደት ጋር የተገለለውን ትልቅ ባለሥልጣን ቀጥሎ የጸጥታ ክፍል ኃላፊውን ወዳጅነት በመያዝ ብዙ ፍላጐቷን እንጂ፣ መሥሪያ ቤቷ አልተመቻትም ነበር። ያለፈተና በጓዳ በር ያስቀጠራት ማን እንደ ነበር የሚያውቁ አንዳንድ ሠራተኞች ሹም ኳንቱል በቁጥጥር ሥስር እንደ ዋለ ወዲያውኑ «የቀድሞ ባለሥልጣኖች ዕቁባቶችም ትኩረት ይደረግባቸው » የሚል ወረቀት እየበተኑና ወሬ እየነዙ የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፈቱባት። ከጊዜ በኋላ ይህ እየተራባ ሄዶ ሳለ መለስተኛው ፕሮግራም ታውጆ የውይይት ክበቦች ተቋቋሙ። ብዙዎቹ የውይይት ክበቦች የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ወይም የአብዮት ሂደት መስተማሪያ በመሆን ፈንታ የሠራተኛ አቤቱታና በደል የሚቀርብባቸው አለቃና ምንዝር የሚነታረኩባቸው መደኮች ሲሆኑ በዘለቃም ላይ ዘመቻው እንደገና በተዘዋዋሪ ተቀሰቀሰ ፡

አንድ ተራ ታይፒስት እጅዋን ስታነሣ ንግግርዋን አብራ ትቀጥላለች።

-ጥያቄ አለኝ።

-ጠይቂያ!

-እኔ የምጠይቀው ልዩ ጸሐፊ ስለሚባሉት ነው። አብዮታችን ሁሉም እኩል እንዲሆን ነው ተብሏል። ታዲያ አንዳንዶቹ የሚሆኑትና ልዩ ደሞዝ የሚያገኙት ለምንድን ነው? - ጭብጨባውና ሁካታው ያስተጋባል።

-እኔም ጥያቄ አለኝ - የመዝገብ ቤት ሠራተኛ እጁን ያነሣል።

እንዲናገር ይፈቀድለታል ፡

-ይህ አብዮት የመጣው ለጭቁኖች ነው ተብሏል። ግን እኛ ጭቁኖች ችሎታችንና አገልግሎታችን ሳይናስ አሁንም ከስብስቴ ዘመን ደሞዛችን ሳንወጣ አንዳንድ የቀድሞ ባለሥልጣኖች ቅምጦች ግን ሳይሠሩ ወፍራም ደሞዝ ይዝቃሉ። አብዮቱ ይህንን እንዴት ይመለከተዋል? ነው የእኔ ጥያቄ » - ድብልቅልቅ ባለ ጭብጨባና ፉጨት በተቀላቀለበት ሁካታ ይታጀባል።

በዚህ ላይ ደግሞ በሰው ልጅ ክብርና እኩልነት የሚያምኑ፤ የፊውዳል ትዕቢታቸውና ኩራታቸው አሁንም ያልደረበ.... ሲል ሌላው ቀበል ያደርጋል። አሁንም ጭብጨባና ሁካታ ይነጉዳል።

የዚህ ዓይነት ውርፋት ለሦስት የውይይት ሳምንታት ያህል ቀጠለ። እርግጥ ስም አልተጠቀሰም። ግን በአስተያየት፤ በግልምጫ በሹክሹክታ እነማንን ለመንካት እንደሆነ ግልጽ ነበር። ውይይቱ የሚረባረበው ዘለቃን ጨምሮ በሦስት ሴት ጸሐፊዎችና በአንድ የዕቃ ግዢ ክፍል ወንድ ኃላፊ ላይ ነበር።

ዘለቃ የመረጃ ሠራተኛ ለሆነው ወዳጅዋ ነግራ የሚያስቸግሩዋትን ሰዎች ልክ ማስገባት ትችል ነበር። ከጅሏትም ነበር። ነገር ግን ስታስበው አጉል የችኮላ ስሜት ሆኖ ታያት። በጥቂቶቹ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ብታስወስድ የቀሩት ሠራተኞች ዝንቧን እሺ እንዳማይሉ ብታውቅም በጥላቻ ዐይን መታየቷ ስንኳ አስፈላጊ አልመሰላትም። እንደዚሁም የውይይት ክበብቡን አመራር የያዙት ኢ.ህ.አ.ፓዎች ንትርኩንና ዘእልፋውን ስለሚያበረታቱ ከእነርሱ ጋር መቃቃር ብልህነት መስሎ አልታያትም። ከሥራ መቅረቱ ደግሞ ፈሪነት ሆነባት። ይህንን ሁሉ አውርዳ አውጥታ በመጀመሪያ ሥራ ለመቀየር ከዚያም ያስቸገሩዋትን ቀስ በቀስ ለመቅጣት ወሰነች።

ሥራ ፍለጋ ብዙም ሳንከራተት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዳጋጣሚ ቀናት። አጋጣሚውን የቀለበችው ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ነበር። ለመስቀል በዓል ዳንስ ይዟት የሚሄደው አልፎ አልፎ አብራው የምትወጣው አንድ የግል ኩባንያ የሽያጭ ኃላፊ ነበር። ከዚያ ቀደም ሲል ተቃጥሮዋቸው ከነበረው ጓደኞቹ ጋር ለስድስት

አንድ ጠረጴዛ ያዙ። አንድ ወንድና አብራቸው ያለችው ሴት የውጭ አገር ሰዎች ናቸው። ሴትዮዋ ኩፍኝ እንደ ጠቀጠቀው ፊቷ ጥቁር ነጠብጣብ የበዛበት ‹የኖርዲክ› ዘር የምትመስል የገረጣች ነጭ ናት። ወንድዬው ጥቁር አፍሪቃዊ ነው። ሌሎቹ ሁለት ኢትዮጵያውያን ናቸው። ስድስቱ በመካከላቸው አንድ ሙሉ ውስኪ አወረዱ። በአብዛኛው ጠረጴዛ እንደዚሁ ነበር።

እንደየምርጫው እንደየፍላጐቱ እንደየጨዳራው አቅም በየዓይነቱ የሚቀርበው ምግብ በዊስኪ በወይን ጠጅ በቢራ እየተወራረደ በመካከሉ በሸበሌዎች ባንድ አጃቢነት ዳንሱ ይቀልጣል። ለምግቡም ለመጠጡም ለዳንሱም የተወሰነ ጊዜ አልነበረውም። የጐረሰውን ሳይውጥ ተነሥቶ የሚሰበቅ አለ። ችሎታውን ለማስመስከር ይመስል ብርጭቆውን በአንድ እጁ እንደ ጨበጠ የሚያረግድ አለ። ብቻውን የሚውረገረግ አለ። «ይቅርታ! » ብሎ በመደነስ ላይ ያለች የሴት ጓደኛን መጠየቅና መቀበል የተለመደ ተራ ነገር ነው።

የዳንሱን ዓይነት የውዝዋዜ ሥርዓት የሚከተለው ከስንት አንድ ነው። አብዛኛው ግን እንደ መሰለው የቅኝቱን ፍጥነት ለመከተል ይሞክራል። በዝግታ ፈሰሰ - ፈሰሰ ሽክርክር ሽምድምድ። በአማካይ ፍጥነት እሽክም - እሽክም እሽክም - ክም - ወልገድገድ። በማኰብኰብ ሲክ - ሲክ - ሲክ - ድንቅፍ ድንቅፍ፡ በኩብኩባ ምት እንክት - እንክት - እንክት - ክት ድንቅፍቅፍ። በስብቅ ምት ወለም - ዘለም - ሰበር - ሰካ ቻቻ - ወለጠም - ወልጠም - ወልጠም፤ ስብቅብቅ። ዝልፍልፍ፤ ውልግድግድ።

ከዚያ ያለው ሰው ሁሉ እስከ እነሴት ጓደኛው አሥራ አምስት ብር ከፍሎ የገባው ስሜቱ እንደ መራው ለመደሰት ነበር። ሁሉም ፈለጉ ተደሰቱ።

ምግብና መጠጥ እንደ ተፈለገ እየገባ፣ በዚያም ሰውነትንና አእምሮን እያሚሚቀ ዐይን - ለዐይን ሲሥራረቅ ሆድ ለሆድ ሲፈላለግ ትንፋሽ ለትንፋሽ ሲተፋፈግ ጠረን ለጠረን ሲቀላቀል ገላ ለገላ ሲተካከክ፣ የስሜት እንፋሎት ሲተላለፍ የሚያስደስተው የማያስደስተው የሁሉም ምርጫ ሲዋሐድ ሁሉም የዘወትር እሱነቱን ሳይሆን ሌላ ሆነ፤ ሌላ ዓለም ውስጥ ገባ። በዚያ አዳራሽ ውስጥ የአብዮት ትግል ውጥረት ጣጣ - ምንጣጣ የለም። የሚነካው ቢኖር መዝገቡን ከበሩ ውጭ ትቶ የገባ ይመስላል። ትናንት እንዳልነበረ ነገ የራሱ ጉዳይ እንደ ሆነ ከዚያ አዳራሽ ውስጥ ሌላ ዓለም እንደ ሌለ፥ ሁሉም ያችን ጊዜ ለመኖር የወሰነ ይመስል ነበር።

የእነዘለቃ ገበታም ቢሆን ከዚሁ አጠቃላይ ስሜት የተለየ አልነበረም። እየጠጡ በሉ። እየበሉ ደነሱ። አንድ ጠርሙስ ዊስኪ ጨርሰው ሌላ አስወሰዱ። እንደ ሌሎቹ ሁሉ የሴት ጓደኞች እየተለዋወጡ ዳንስ መጫወቻቸውን ቀጠሉ። ልውውጡ በመደበኛው ዳንስ ብቻ ሳይወሰን እየቆየ ተለዋውጦ ወደ መዳራቱም አመራ። ዳንሱን ጨርሰው ሲመለሱ በአንድነት ይቀመጡና በሲጋራ ጢስ በሽቶ መዓዛ ስሜትና መጠጥ ከሚሟቀው ገላ በሚወጣ ሙቀት ታፍነው እየቆዩ ቡዝዝ ድብዝዝ በሚል ዐይን እየታዩ ይፈታተጋሉ። ይተሻሻሉ። እንደ መተቃቀፍም ይላሉ።

የዘለቃ ጓደኛ ዳንሱንም መዳራቱንም ወደ ነጭዋ ሴት ጋር እያመዘነ ሲሄድ ሴትዮዋም ዳንሱን ከጨረሱ በኋላ እንደ ሙቻ ከጐኑ ተጣብቃ ስትቀር ዘለቃም ከአፍሪቃዊው ጋር እየተጐዳኘች ሄደች። ሁለተኛውን ጠርሙስ ዊስኪ ሲገባደድ አስተውለው ሌሎች ሁለቱ - ሴትና ወንድ - ኢትዮጵያውያን ወጪው ከብዶባቸውም ይሁን የነገሩ አዝማሚያ ስላላማራቸው «መጣን » ብለው ወጥተው በዚያው ቀሩ።

ትንሽ ቆየት ብሎ ሰዓት እላፊው ገና ሳይቃረብ ነጭዋ ሴትዮ ቤቴ ካልሄድኩ ብላ አስቸገረች። ሰዓት እላፊም ቢደርስ ኖሮ በልዩ ቅናሽ ዋጋ ክፍል ተዘጋጅቶ ነበር።

«ለምን ነው የምትሄጂው? » ሲል ያመጣት ጓደኛዋ በእንግሊዝኛ ጠየቃት።

«ፈለግሁዋ! » እንደርሱ ቁጣ ባይሆንም እርሷም ኮስተር ለማለት ሞከረች።

«እኔ ደግሞ ለመቆየትና ለመደሰት እፈልጋለሁ። »

«ማንም አልከለከለሽ። መሄድ ትችያለሽ። »

«እንዳመጣኸኝ አድርሰኝ! »

ይህንን ንግግር የሚለዋወጡት ከዳንስ እንደ ተመለሱ እሷ ከዘለቃ ጓደኛ ጋር ትከሻ ለትከሻ ገጥማ አፍሪቃዊ ዘለቃን ከጐኑ አስቀምጦ ጀርባዋን በአንድ እጁ እየደባበሰ ነበር።

«ያመጣሁሽኮ ልንደሰት ነው እንጂ አምጣኝ ውሰደኝ እያልሽ ዘሮችሽ ለዘመናት እንዳደረጉት አሁንም እንደሚያደርጉት ልታዥኝ አይደለም። ገባሽ? »

«ምን? አንተ አስቀያሚ በሬ! » በመጠጥ የቦዘዘ ሰውነቷን እንደማኮማተር እያለች ብርጭቆ የምትወረውርበት ይመስል ቃጣች። ግን አላደረገችውም።

«ታውቂያለሽ? አንቺ ደግሞ አሮጊት ሸርሙጣ ነሽ! » ሲል ጥርሱን አግጥጦ መለሰላት።

ዐይኑዋም አፍንጫዋም አፏም በአንድነት የፈነዳ ይመስል ፈሳሹም ጩኸቱም ተቀላቅሎ ሲገነፍል «ምን? ምን? እያለች ፊቷን በመሐረም ሸፍና ለመነሣት ስትሞክር ተንገዳገደች።

ሴትየዋ እንዳትወድቅ በማዘን ሳይሆን በጠረጴዛቸው ዙሪያ ያለው ሰው ሁሉ እንዳይዘባበትባቸው ዘለቃ ወዲያውን ፈጠን ብላ በመደገፍ ወደ መጸዳጃ ቤቱ አደረሰቻት። ስትመለስ ዐይኗና አፍንጫዋ በርበሬ እንደ መሰለ ቢሆንም ስሜቷን ለመቆጣጠር ችላ ነበር።

«ሁለት እግር የሌለኝ አይምሰልህ! አመሰግናለሁ » አለችው ፍርጥም ባለ አነጋገር። ለመሄድ ካቦርቷንና ቦርሳዋን አነሣች።

ያመጣት ጓደኛ «የራስሽ ጉዳይ ነው » በሚል አኳኋን ትከሻውን ነቀነቀ።

«ለምን እኔ አላደርሳትም? » ሲል የዘለቃ ጓደኛ ተነሣ በአስታራቂ መልክ ሰውየውን እየተመለከተ።

«ችግር ካልሆነብህ እኔ ግዴለኝም። »

«አሁን እመለሳለሁ! » አላት፥ ዘለቃን።

ግን አልተመለሰም።

በአንድ ጠረጴዛ ሁለት ብቻቸውን ቀርተው ደነሱ ተሻሹ ከሁለተኛው ጠርሙስ የቀረውን ዊስኪም ብቻቸውን ተያያዙት። በዚህ ጊዜ፥ ሰውየው የት እንደሚሠራና የምን ክፍል ኃላፊ እንደ ሆነ ዐውቃ ነበር። የነገሮቹ አካሄድ ወዲያው በአእምሮዋ ይነደፍ ጀመር። የማዳራቱን መብት በሰፊው ለቀቀችለት። እንዲያውም አጸፋውን በመመለስ አደፋፈረችው።

ከምሽቱ አምስት ሰዓት በኋላ ሊገነፍል የተቃረበው ስሜቱን መቋቋም አልቻለም። «እንሂድ! » አለ ከውጥረቱ የተነሣ ሊፈነዳ በመሰለ አነጋገር።

«የት? » አለችው ዘለቃ በማቆላመጥና በመደባበስ።

«እኔ ቤት! »

«ደስ ይለኝ ነበር። ግን ሰዓት እላፊው እየተቃረበ ነው። »

«ከዚህ - ከዚህ - ከዚህም ክፍል መያዝ እንችላለን። »

ሰውነቱን መደባበሷን ሳትተው፥ ከቁልምጫ ፈገግታ ጋር ራስዋን በአሉታ ነቀነቀች። ሰውዬውን፥ ወይም የፍቅር ጨዋታ ማሳረጊያውን ጠልታ አይደለም። እንዲያውም የእርሷም ስሜት ወደ መወጠሩ ተቃርቦ ነበር። ነገር ግን እዚያው በዚያው በቀላሉ የሰውየውን ፈቃድ መፈጸም እርሷ ላሰበችው ነገር ምናልባት መሣሪያ የሚያሳጥት መስሎ ታያት። በዚያን ምሽት የሚፈጽሙት ግንኙነት ሰውየውን እጅ ተፍንጅ ማርኮ ለማስቀረት ያስችል ይሆናል። ወይም ደግሞ የመጀመሪያ ስሜቱን ከተወጣ በኋላ ስለ እርሷ፥ አስተሳሰቡን ሊቀይር ወይም ችላ ሊላት ይችላል። አይታወቅም። ስለዚህ፥ ገና ጦርነት ሲጀመር በመጀመሪያው ዙር እጅዋን መስጠት አልፈለገችም። እንደ ከብት የሚላስ ጨው እያሳየች ጥቂት ጊዜ መሳብ የተሻለ መስሎ ታያት።

«አንቺም እንደዚያች አሮጊት ነጭ ሽርሙጣ በጥቁርነቴ ትንቂኛለሽ ማለት ነው። እንትኔን - እንትኔን - ግን - » ሲል ዐይኑን አጉረጠረጠ።

«አይደለም። አይደለም። እኔም - እኔም እንዳንተ ጥቁር አይደለሁም እንዴ! » አለች ዘለቃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እጥረቷን በዳበሳ በዳሰሳ በዐይን ቁልምጫ እያሟላች። «እኔ ከአንተ ጋር መደሰት የምፈልገው፥ ለረጅም ጊዜ ነው። አንድ ሰዓት ቀርቶ ሙሉ ቀን አይበቃንም። አሁን ግን ሰዓት እላፊ ደርሷል። በሽተኛ የሆነች እናት ስላለችኝ መሄድ አለብኝ። እርግጥ በአምስት ደቂቃ ውስጥ ፈቃድህን ልፈጽም እችላለሁ። ግን፥ እኔ ስላንተ ባለኝ ስሜት ባጭር ጊዜ አያረካኝም፤ ካላረካኝ ደግሞ ያበሳጨኛል። » በቁልምጫ ፈገግታ አጠበችው።

«ባንድ በኩል ልክ ነሽ » አለ አላስችል ብሎት በእቅፉ ይዞ እየጨመቃት። አድራሻ ተለዋውጠው በጭንቅ ተለያዩ።

በሳምንቱ ውስጥ ሰውየው በሚሠራበት ድርጅት ፈተና ወሰደች። በሁለተኛው ሳምንት በኮንትራት መልክ ተቀጠረች። የመረጃ ክፍል ኃላፊ የሆነው የቀየ ወዳጅዋና በአዲሱ መካከል ጊዜዋን ደልድላ ማካፈል አላስቸገራትም።

«ለምን አሥር ጊዜ ኮንትራት አይሆንም? ይሄ መንግስትስ ቢሆን ማንን ቋሚ አደረገና? እንደ ፈለገ አይደል በየቀኑ ሠራተኛውን ሁሉ የሚያባርረው? የሚሾመው? የሚሽረው? » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል። «ኧረ እቴ በአሁኑ ጊዜ ለወር ስንኳ ለማይበቃ ደሞዝ ተብዬ ከእነርሱ ጋር ከመጨመላለቅ እንዲህ አንድ ፊቱን መለያየቱ በማን ዕድል። አንድዬ ፊቱን ቢመስል ነው እንጂ።

በልጃቸው ሥራ ይህ ነው የማይባል ኩራት ተሰማቸው።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ባይዘከሩትም ግብር፣ ባያስገቡትም ዱሮ ከበዓላት ሁሉ የማያዳንቁት ሐምሌ አሥራ ስድስትን ነበር። «ኤድያ፣ ለጀመሪያውኑ ባይወልዱ መቸ ይነግሡ ነበር? ቀብቶ የፈጠራቸው ስለሆነ ቁም እንገሩ ተፈጥረው ወደ ዓለም የመጡበት ጊዜ ነው » ብለው መከራከር ይወዱ ነበር። ለአድናቆታቸው ግን ሌላ የራሳቸው ምክንያት ነበር። ዕድሜያቸውን በትክክል ባይናገሩም እርሳቸውም የተወለዱት ሐምሌ አሥራ ሰባት ነበር። ስለዚህ፣ የፈጣሪ ቅባት እርሳቸውም በመጠኑ ያወዛዛቸው መስሎ ይሰማቸዋል። «አሆሆ! ለተአምር እኮ ነው። አሁን እስቲ ይታያችሁ። የእኔ እናት ምጥ ትንሽ ፈጠን ቢል፥ ወይን ደግሞ የልዕልት የሺመቤት ምጥ ላመል ያህል ዘግት ቢል በአንድ ቀን መወለዳችን እኮ ነበር! አይገርምም የፈጣሪ ነገር! » ይሉ ነበር፥ እየተፍነከነኩ።

እየለመለመ በሄደ ተስፋቸው ሳቢያ ዘንድሮ ግን ማክበር ያሰኛቸው ጥቅምት ሃያ ሦስትን ነበር።

ምን የመሰለ የፍየል ሙክት አሳርደው ሙሉ ጠርሙስ ዊስኪ አወረዱ።

«ምነው ዛሬ ልደትዎ ነው እንዴ? ለመሆኑ ወደ ሥልሳው ተጠጋዎት እንዴ? » ሲሉ ነጋድራስ በአሽሙር ነኩዋቸው የቅናት ብሽቀታቸውን ለመወጣት።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግን ዛሬ ቁጣ አላሰኛቸውም ነበር። «በአሞሌ ጨው የለመዱት ቁትር የማንበብ አመልዎ እስኪሞቱ ድረስ አይለቅዎትም። መቃብር ውስጥስ ሆነው፥ አንድ ሁለት ስንት ነው? እያሉ ስንት ነው እያሉ? ሳይቀባጥሩ ይቀራሉ? » ሲሉ በበኩላቸው አሾፉ። ነጋድራስ አገኘሁ ንግድ የጀመሩት በአሞሌ ጨው ነበር ይባላል።

«የእኔን ጨው ባይበሉ አልጫ ሆነው ቀርተው ነበር። »

«ማ? እኔ ዘርፏ? ተፈጥሮዬ የጨው ነው! »

ነጋድራስ በማሾፍ ከትከት ብለው ሣቁ። ጭውውታቸው ሌሎችንም ፈገግ አስደረጋቸው።

«ኧረ እንዲያው እኔም ልጠይቅ። ውስኪ የወረደበት ምን አዲስ ነገር ተገኘ »? አሉ ፊታውራሪ ወርቃለማሁ።

«ረሱት? ወይ ፈታውራሪ፣ እውነትም እየጃጁ ሄደዋል » ሲሉ መለሱ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የገበታውን ምግብ በየሰዎቹ ፊት እያሰናዱ።

«የዘውድ በዓል! »

«ወትሮማ ሻምፓኙ ነበር የሚንዶቀዶቅበት። »

«ሰው ሁሉ በረሳው ጊዜ አሁን ውለታዎን ማን ይከፍለኛል ብለው ነው የሚያዘክሩት? » ሲሉ አሁንም ነጋድራስ እገኘሁ ተነኮሱ።

«ኤጭ ነጋዴ ብቻ ነው ዘወትር ትርፉን የሚያስበው። እኔ እንደሆንኩ ለጌታዬ ክብር ለመስጠት ነው። »

«አሁን ተሰጠ አልተሰጠ ምን ዋጋ አለው። ክብሩን እንዳይቀበሉ የሉ! »

«ማን ነው ያለ? የጠላት ወሬ ነው። እነሱ ለፈፉ እንጂ አላየን። ደግሞስ ቢሆን መንፈሳቸው ሁልጊዜ አለ። »

በዚህ ዓይነት ስሜት ውስጥ እንዳሉ ነበር፣ በሁለት ሰዓት ላይ ራዲዮው የተከፈተው። በመጀመሪያ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መግለጫ የሚታጀብበት የተለመደው ወታደራዊ ማርሽ ሲሰማ ሁሉም ጆሮዋቸውን አቆበቆቡ።

«ኤጭ! ያንኑ ስድባቸውን ሊያዋርዱት ነው እንግዲህ » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል።

«አድኃሪዎች አብዮቱን ለመቀልበስ ሲፍጨረጨሩ አብዮታውያን እጃቸውን አጥፈው አይቀመጡም - ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተሰጠ መግለጫ » ሲል በርቱዕ አንደበቱ የታወቀ ራዲዮ ተናጋሪ ጀመረ።

«ሰው እንዲያው መርዶ መናገና መሳደብ አይሰለቸውም » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል መለሱለት።

......የአብዮቱ ባለቤት የሆንከው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! በተባበረ ክንዳቸው ማንቁርትህን አንቀው የግፍ ግፍ ሲዶልቱበህ የነበሩትን ኢምፔሪያሊዝምን ፊውዳሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ከጫንቃህ አውርደህ ክብርህንና ነጻነትህን ለማረጋገጥ ለአያሌ ዓመታት ከእነዚህ ጣምራ ጠላቶችህ ጋር ትንቅንቅ ገጥመሃል...... »

አማርኛውን ሳይቀር እኮ ነው ያበላሹት። አሁን ማ - ይሙት ለሰው ጣምራ ይባላል። ለጦር እንጂ » ሲሉ ተቀበሉ ፊታውራሪ ወርቃለማሁ የሚናገሩት ጠፍቷቸው።

ረጅሙ መግለጫ በዚያ በሚሰለቅና በሚንጐደጐድ አንደበት ቀጠለ።...... ኢ.ህ.አ.ፓዎች በተራማጅና ሳይንሣዊ ሶሺያሊዝምን ሙጥኝ ብለው በተማጸኑ ቃላት ይሸፋፍኑ እንጂ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ በወሰዱዋቸው አቋሞች በሙሉ ከመሳፍንቱና ከኢምፔሪያሊስት አሳዳሪዎች አንድ ናችው..... በአብዮትህ ላይ እስከተሰለፉ ድረስ አንተም በተራህ በእነሱ ላይ መሰለፍ ነው......

«ፖህ! » ሲል ደመላሽ ምራቁን ቱፍ ማለት ቃጣው። «እነሱ ከማንም ጋር ሲሻረኩስ? ደሞ ውሸት ነው! »

«እኔኮ » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አሁንም መግለጫውን የተለመደው አድርገው በማቃለል፥ «እስቲ ማን ይሙት የጨዋ የመሳፍንት የመኳንንት ዘር መሆን የሚያሰድብ ነው? አሆሆ የእህል ዘመን እንውሰድ ምርጥ የስንዴ ዘር የአጃ ዘር፥ የማኛ ጤፍ ዘር፥ ሙሬ ሙጃ፥ አራሙቻ ስሚዛ፥ እንክርዳድ ካሆነ ተብሎ ይሰደባል? »

«ምርጥ ዘር ሲሉ ምን ማለትዎ ነው? » ነጋድራስ አገኘሁ አሁንም ነጥብ አግኝተው እየተነኰሱ፣ «አሁን እርስዎ እንደ ሚሉት ምርጥ ዘር የሚባል የመሳፍንት የመኳንንት ዘር አለ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል? ከገረዱ ከአሽከሩ ያልተነካካ? ከዚያም - ከዚያም ያልተዳቀለ? ከዚያም ከዚያም ከጥቁርም ከምኑም ከምናምኑም ያልተካለሰ? ቅድም እንዳሉት ምርጥ ዘርነት እኮ አሞሌ ጨው አለ መሸጥ፣ እህል በኩንታል አለ መስፈር ጋሪ ቆዳ አለ መቁጠር ነው ይመስለኛል። በዚህም አልፎ መኳንንትም መሆን አለ። እርስዎ ግን ሌላውን ሁሉ ትተው ስለ አሞሌ ጨው ይተርካሉ። »

«እኔ ቧልተኛ ተራኪ አይደለሁም። ሐቁን ነው እቅጩን ነው ሁልጊዜ የምናገረው። መተረከማ የነጋዴ ሙያ ነው በዚህ ወርዶ በዚህ ወጥቶ ማለቱ። »

«እስቲ ሁላችሁም ምናምንቴ አቲካራችሁን አቁሙ! » ሲል ደመላሽ ክፍሉን ሁሉ በሚቆጣጠር ደንፊ አንደበት አዘዘ።

ጸጥ ሲሉ መግለጫው ቀጠለ.... በዚህም መሠረት አብዮቱን ከቅልበሳ ለማዳን በኢ.ህ.አ.ፓ ቀንደኛ ጠላቶችሁ ላይ በሰፊው ሕዝብ ላይ በሸረቡት ወንጀል ውሳኔ ተሰጥቷል....

አድማጮች አቀብቁበው ውሳኔውን ሲጠባበቁ አሁንም ወንጀላቸውን የሚዘረዝር ሐተታ ቀጠለ። ይህንኑ ውንብድናውን በመቀጠል..... የመጨረሻውን መንፈራገጥ ሲያደርጉ በመለዮ ለባሹ መተባበር ባደገው አሰሳ..... የተባሉት ሲገደሉ......«እጅ አልሰጥም ብለዋል! ለምን አይናገረውም? » ሲል ኮሎኔል ደመላሽ ደነፋ።

«እስቲ ቆየ እንሰማበት። መቸም - መች እንደዚህ ያለ ዘመን በፍካሬ እየሱስም አልተጠቀሰም። » ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሰውነታቸው እየተነፋ ሲጎድል ፊኛ ይመስሉ ነበር።

..... ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ሃያ ሦስት ሰዎች ላይ የማያወላውል አብዮታዊ እርምጃ በመውሰድ በቀረበባቸው የነፍስ ግድያ የፀረ - ሕዝብና የፀረ - አብዮት ወንጀል ክስ አጥጋቢ በመሆኑ ማስረጃዎች ተደግፎ በልዩ ጦር ፍርድ ቤት አንደኛ ወንጀል ችሎት ቀርቦ በሁሉም ላይ የሞት ፍርድ ተወስኖ ይህ ውሳኔም ለርዕሰ ብሔሩ ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ ቅጣቱ ተፈጽሞባቸዋል።

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

«ዝጉልኝ! ዝጉልኝ! » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አንባረቁ፤ የጣሪያው ቀለም ቅርፊት የሚረግፍ እስኪመስል ድረስ።

ነጋድራስ አገኘሁና ፊታውራሪ ወርቃለማሁ እንደ ጋለበ ፈረስ ትንፋሻቸው፥ አፍና አፍንጫቸውን እየቀደደ የፈነዳ መሰለ።

ኮሎኔል ደመላሽ መጠነኛ ካራቴ በተለማመደ ፍርጥም ቡጢው ጠረጴዛውን ሲደልቀው በመጠጥ ብርጭቆው አንዳንዱ ተከነበለ። የተረፈውና ሌላው ዕቃ ሁሉ ተንኳኳ።

ላንዳፍታ ቤቱ በሙሉ ጸጥ፣ ርጭ አለ። የሰዎች ትንፋሽ ሳይቀር ቀጥ ያለ መሰለ። አንጀት የሚያኮማትር ንዴት መላ ሰውነት የሚያጠጥር ብሽቀት ሰፈነ። በዚህ መካከል ዘለቃ አፍሪካዊ ወዳጅዋ (ወንድ በተለይ በስቅላት ሲገደል ለመጨረሻ ጊዜ ወሲብ ይሰማዋል) ያላት ታወሳትና ሣቋን እንደ ነጐድጓድ አደባለቀችው።

ምክንያቷን የጠየቃት አልነበረም።

ጭውውቱ እንደገና ሳይቀጥል ሁሉም በዝምታ እንደ ተዋጡ ሌሎቹ ወደየቤታቸው ለመሄድ ሲነሡ ኮሎኔል ደመላሽ ብቻ ወደ ኋላ ቀረ። ከዚያ በፊት

ሁለት ሦስት ቀን ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት ያደረው በመጀመሪያ እርሳቸው በአስተያየታቸውና በአነጋገራቸው አባብለውት በበኩሉ ትንሽ ከተግደረደረ በኋላ ነበር። አሁን ግን ቀስፎ የያዘውን ንዴቱን ለማብረድ የሚስቱን ለስላሳና ረቂቅ ሰውነት ሳይሆን እንደ ወደል አህያ የደለበው የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቋጥኝ ገላ አሰኘው።

ነጋድራስ አገኘሁ በበኩላቸው ከደርግ የዱብ ዕዳ መግለጫ ሌላ የባሰውን የተከኑት በወይዘሮ ዘርፈሽዋልና በኰሎኔል ደመላሽ ነበር። ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጋር እንደ ጐረምሳ እፍ - እፍ ያለ እንደ ዕድሜያቸው ሙዝዝ ያለ ፍቅር ይዟቸው በደመላሽ ቀንተው አይደለም። ወትሮውንም ስለ ገንዘብ እንጂ ስለ ፍቅር ደንታ የላቸውም። ሚስት እንኳ አይቀመጥላቸውም። በየጊዜው እንዳገቡ እንደ ፈቱ ነው። እንደ አባትና ልጅ እስከዚህም የማይቀራረቡ በየእናቶቻቸው የተበታተኑ ሦስት ልጆች አሏቸው። ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጋር ያላቸው ግንኙነትም የተፈጥሮ ስሜትን ከማርካት ልምድ የጠለቀ አልነበረም። ለብርድ ለሙቀት ለፍትጊያ ለዐመል መውጫ ያህል ብቻ ነበር። እንዲያውም የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ድብልብል ገላ ከሰባው ገላቸው የሚወጣው ላብ ከሚቀቡት ሽቶ ጋር ሲዋሐድ የሚሰጠው ጠረን ትንፋሻቸውን ከሌሎች ሴቶች ጋር ሲያነጻጽሩት እስከዚህም አስደሳች ሆኖ አላገኙትም ነበር። ታዲያ አሁን በደመላሽ መቀየራቸው ከፍተኛ ውርደት ሆኖ ተሰማቸው።

«እኔ አገኘሁ ነኝ ባጣ ቆየኝ! ግርንድ ወዲላ! » አሉ ከአልጋቸው ላይ በጀርባቸው ተጋድመው ከጣሪውያው ጋር በመፋጠጥ። «ከእሱ በምን ሳንስ ነው? እንደሷው ድቡልቡልና ሸካራ ስላልሆንኩ ነው? ተወደድኩ ብለህ ተፍነከንከሃል። እንደ ሎሚ መጥጣ ትጥልሃለች። እኔ ሆንኩ ማንንም አልለማመጥም። ኩሩ ነኝ..... » ግን ሐሳባቸው በኩሩነቱ ሊረጋላቸው አልቻለም። የበቀል ስሜት ሰፍኖባቸው በኩሩበቱ ሊረጋላቸው አልቻለም። የበቀል ስሜት ሰፍኖባቸው በምን ዓይነት እንደሚበቀሉት ብቻቸውን ከራሳቸው ጋር ይነጋገር ጀመር።

......አሁን ቴሌፎን ደውዬ ሙልጭ አድርጌ ልስደባት? የለም - የለም - ለስድብ የርስዋ ምላስ አይቻል። ምን ዓይነትስ ስድብ ቁጥኝ ሰውነቷን ዘልቆ ይገባና? ነገ ቀን ሄጄ በዱላ ባገላብጣትስ? ይህም አይሆንም። መቸም ሴት ወንድን ባታሸንፍም - ከጠብደል ጋር ምን አታገለኝ! በቤት መሰብሰብ። የለም - የለም ቅሌት ነው ትርፉ። ከሆነስ እርሱን መጠርጠሩን ነበር እንጂ! ወዳጁ ነኝ! ደሞ ያውቃል። እርግጠኛም ባይሆን መጠርጠሩን ብዙ ጊዜ በአሽሙር

ገልጾታል። ታዲያ እንዲህ ያለውን ምን ይሉታል? የመጨረሻው ቀላል ወራዳ። ከዚያው ከአለበቱ ስልክ ደውዬ አንተ ልክስክስ የእኔን፥ ትራፊ ነው የምትመገበው ብለውስ? ነገረኛ ፖሊስ መልስ አይቸግረውም ይሆናል። አንተም የማናዬ ትራፊ ተመጋቢ ነበርክ። ያውም አደግድገህ ተሽቆጥቁጠህ አሁን ስተተፉ ጊዜ ያጣ ወሬ ነው ቢለኝስ? ከሆነስ አይቀር አይለምደኝም እስኪል ድረስ ማንቆራጠጥ ነበር። ግን ዱላው ሲአይቅትወ ፖሊስ ጣቢያ ነው የሚሮጠው እንደ ለመደው። ምን አጓተተኝ ከእሱ ጋር......

ነጋድራስ አገኘሁ አማራጩን ሁሉ አንሥተው ጥለው ሲያልቅባቸው ጥቂት አሰቡና ሌላ የበቀል ዘዴ ተከሰተላቸው።.... በእሱ ቤት መንጠቁ አይደል? እኔስ የእሱን ሚስት ጨርቋን ጥላ መሄድ እስኪቀራት ድረስ ሲወጣ ሲገባ ዐይንህን ላፈር እስክትለው ድረስ በአከንፍለትስ?....ነጋድራስ በፍቅር ጨርቅ ማስጣል መቻላቸውን እንደ መጠራጠር ቃጣቸውና ምክንያቱን ለጣሪያው ነገሩት.....መልኳ ደህና ሆኖ እንዲያው ዐይን ዐፋር ቢጤ ናት። በፖሊስ አሠራሩ ቅስሟን ሰብሮት ቀና ብላ ልታየው ስንኳ ትፈራለች። ልቧም ቢከጅለኝ ስሜትም ቢኖራት አትደርፍም - ኤድያ! አትረባም - ስለዚህ ሁሉንም ነገር ንቆ መተው ነው። አሁን ሲመናቀሩ እርስ በርሳቸው እህ? ፊታውራሪ ወርቃለማሁስ ምን ያልፈኛል ብለው ሳይገቡበት ይቀራሉ? እና - እና - ዝም ብሎ ማየት ነው.....

ውጤቱን ዝም ብሎ ለማየት ዐይናቸውን ከድነው ለመተኛት ሞከሩ። ግን ዐይናቸውን ቢጨፍኑ ገልተው ጣራ ጣራውን ቢያዩ፥ ለመርሳት ቢሞክሩ የሁለቱ ግንኙነት ትርኢትና ድምፅ፣ በዐይነ ሕሊና እንደ ራዲዮ ድምፅ በጆሮዋቸው እየመጣ አስቸገራቸው። ስለ እርሳቸው ሲጨዋወቱ ድምፁ በእዝነ ልቦናቸው ጐልቶ ተሰማቸ።

-እስቲ ያ ሽማግሌ የጨው ነጋዴ እንዴት ነበር?

ይላል ኮሎኔል ደመላሽ።

-ኤጭ እቴ! ምን አመጣው እሱን አሁን!

-ውሽታም ተኝቶሽ የለም?

-ኤጭ!

-መልሱ እኮ ኤጭ አይደለም። እንዴት ነበር ነው ያልኩት!

-ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ!

-ታዲያ ጣፊያ ከሆነ ከጀመሪያውኑ ለምን?

«እኔ ነኝ ጣፊያ! » ሲሉ ነጋድራስ አገኘሁ ከተኙበት ተፈናጥረው ተነሡ። በእዝነ ልቦቸው የሰሙት በገሐድ የተነገረ ይመስል አልቻሉትም። ጥርሳቸውን አፋጩ። ሰዓታቸውን ተመለከቱ። አምስት ሰዓት ተኩል ሆኗል። ቀጥሎ ዐይናቸውን ከቴሌፎኑ ጭንቅላት ላይ ሲያርፍ ሌላ ዘዴ ብልጭ አለላቸው።

«.....እንደምን ሰነብትሽ ቆንጅት! ከእንቅልፍሽ ቀሰቀስኩሽ መሰለኝ! » ነጋድራስ ድምፃቸውን ለማረጋጋት ሞከሩ። «አሁንማኮ መተያየት ጠፋ! ልጆቹ ሁሉ ደህና? እሰይ?! እሰይ! ዋናው ነገር በሕይወት መቆየቱ ነው። ለመሆኑ ደመላሽ ገብቷል? »

የአሉታ መልስ ሲያገኙ «ምነው? በጤናው ነው እስከ አሁን? ሰዓት እላፊ አይደርስበትም እንዴ? » በመገረምና በማሳበቅ ቃና።

«ያ መከረኛ ከራንበላና ካርታ ሲጫዋእት ከመሸበት ከዚያው ከክበባቸው ያድራል » ስትል በቅርቡ ሁለት ሦስት ቀን ደመላሽ የሰጣትን ምክንያት አስተጋባች።

«አሄሄ! ከዚያ ከእነርሱ ክበብ መድረስ ከቻለ ቤቱ አይቀርበውም ነበር? »

«ምን ማለትዎ ነው? አልገባኝም። »

«አሄሄ! ዛሬ ጊኤ ስለ ሌላው ሰው ቀርቶ ስለ ራሳችንስ ምን ይገባናል ብለሽ ነው ቆንጅት። » በፌዝ እንደ መሣቅ አሉ።

«አሁንም ነገርዎ አልገባኝም። »

«እኔ ምን ነገር አለኝ ብለሽ? በይ ተውይው ደህና እደሪ እኔ እንኳ የደወልኩት ቤት መግባቱን ለማረጋገጥ ነበር። »

«ደህናም አይደል እንዴ? » አነጋገርዎ የሥጋት ቅና ነበረበት።

«ደህና ነው - ኧረ ደህና ነው። አብረን ነው ያመሸነው ለመሆኑ ውጭ ብዙ ጊዜ ያድራል እንዴ? መቼም በአሁኑ ጊዜ አስተማማኝ ስፍራ እምብዛም ስለሆነ ቤት ተከቶ ማደሩ ነው የሚሻለው ብዬ ነው። እከሌ ምከሪው አለኝ ብለሽ አትንገሪው እንጂ፣ የሱን ጋግርታም ጠባይ ከኔ የበለጠ አንቺ ታውቂው የለ! - ብትመከሪው አይከፋም። »

«እሱስ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አልፎ - ልፎ ነው » ስትል ቆንጆት መለሰች፤ ለመናገር ላንዳፍታ ተቆጥባ ከቆየች በኋላ በሁለት ጓደኝነት መልሳ በመዘናጋት «ከጓደኞቹ ጋር ሲጨዋወት ብስጭቱ ትንሽ ይቀልለታል በማለት እኔም ብዙ ልጫነው አልፈልግም። ታዲያ ይህም ሆኖ ዛሬ መቸም፣ ማን - ማንም አይታመንምና የቀድሞ የሥራ ጓደኞቹ ናቸው ብሎ በመጠጥ ሞቅታ እንዲያው አንዳንድ ነገር እንዳይዘባርቅ መሥጋቴ አልቀረም። »

«አዬ! ለሱ ግዴለሽም አታስቢ። ቅድም እንደ ነገርኩሽ እንደ ዛሬው አልፎ አልፎ አብረን ነው የምናመሽው። ቤቱ ደሞ በዚህ አይጠረጠርም። የአሁኑ ጊዜ ነገር ቢነሣ እንደ እንቆቆ ነው የሚያንገሸግሸው። » ነጋድራስ አገኘሁ የነገራቸው አካሄድ አስቀድሞ ያውጠነጠኑትና ያቀዱት ይመስል እየተሳካ መጣላቸው። ከጨው ንግድ አልፈውና ገና መክበር ጀምረው ከደህና ሰው ከደህና ቦታ መዋል ሲለማመዱ በብሔራዊ ቲያትር ያዩት የኦቴሎ ቲአትር በሐሳባቸው ታያቸው። ያን ጊዜም ቢሆን የኢያጎን ብልጠት አድንቀዋል። አሁን ደግሞ የብልጠቱ የዘዴው ጠቃሚነት የበለጠ አስደነቃቸው። «ስለዚህ አታስቢ ግዴለሽም የእኛው ሰው ናቸው » አሉ።

«አሁንምኮ የሚሉት አልገባኝም። ማን ናቸው እሳቸው? » ደመላሽ ስለ ማምሸቱም ሆነ ማደሩ ከነጋራት ምክንያት ጋር ፈጽሞ የተለየ በመሆኑ ግራ ገባት።

«ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት ነዋ! አልነገረሽም እንዴ? »

«እሱንስ ዐውቃለሁ » አለች የደመላሽ ሚስት የማታውቅ መሆንዋን ድንገት መግለጡ ቆጠብ አድርጋ በመያዝ። ወዲያው ግን የማወቅ ጉጉት ሳባትና «ታዲያኮ መሶብ ቤት ምኑ ላይ ያድረዋል ብለው ነው? ያው ከበቡ ነው የሚሄደው እንጂ » ስትል በማስተባበል ተናገረች።

«እንዴ ምን የመሰለ ቪላ መኖሪያ ቤት እኮ እላቸው። ያማ ለንግድ ነው። ታዲያ አንዳንድ ቀን ሲመሽባቸውና ጸጥታቸውንም ሲፈሩት ደምላሽዬ ሸኘኝ ይሉታል። እንዲህ አይምሰልሽ። የሥጋ ዝምድና አይኑራቸው እንጂ ልክ እንደ እናታቸው ልጅ ነው የሚንሰፈሰፉለት። ማለቴ ልብሽ ሌላ ነገር እንዳይጠራጠር ብዬ ነው። ለነገሩማ ቢሆንስ በዚህ ቀውጢ ቀን፥ ስንት ከባድ ጉዳይ ሞልቶ ተርፎ እንደዚህ ስላለው አላፊና ፋይዳ ቢስ ነገር መቸ ማሰብ ይገባናል - እና የገባም እንደ ሆነ በማይረባ ነገር አታስቸግሪው - በይ ደህና እደሪልኝ። » ነጋድራስ አገኘሁ፣ የነገራቸው ዘይቤና ዳር ዳርታ ቅንጣት ጥርጣሬ ሳይዘራባት

እንደማይቀር ተማመኑ። የጥርጣሪ ዘርም በጊዜው በቅላ ማደጓ አይቀርም። ቅንጣት ዘራቸውን ከተፈላጊው ቦታ ላይ ከጣሉ በኋላ ንዴቱ ቀለል አለላቸው።

በእርግጥም ዘርዋ በቅላ ከማፍራትዋ በፊት ረዘም ያለ ጊዜ ማለፍና፣ የደመላሽ ሚስትም ብዙ ሌሊቶች እያሰላሰለች ብቻዋን ማደር ነበረባት።

## ፬

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም ጧት ከቤታቸው ሲወጡ የግቢው በር በመፈክር ተለቅልቆ አገኙት። «ኢ.ህ.አ.ፓ. በጭቁኖች ክንድ ይደቆሳል - ኢ.ዲ.ህ. ይወድማል፤ ኢ.ዲ.ህንና ግልገል ልጁን ኢ.ህ.አፓን ሰፊው ጭቁን ሕዝብ ይደመስሳቸዋል - ሞት ለኢ.ህ.አ.ፓና ለኢ.አ.ዲ.ዩ. - የጭዉን አብዮት ወደ ማጥቃት ይሸጋገራል። » የሚያስገርመው፣ መፈክሮቹ የተጻፉት ከውጭ በኩል ብቻ ሳይሆን ከውስጥም በኩል ጭምር ነበር። የብረት በሩ አልበቃ ብሎ የድንጋዩ አጥር ጭምር ተዥጎርጉሯል።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ደመላሽ ሲያበረታታቸው ያደረ ቢሆንም የማታው መግለጫ ሰቀቀን ከአእምሮዋቸው ጨርሶ ያልጠፋ ስለ ነበር መፈክሩን ሲመለከቱ መላ ሰውነታቸው ተናወጠ። በራዲዮ እንደ ተነገረው መግለጫ የመፈክሮቹ ዛቻ ድምፅ አውጥቶ በጆሮዋቸው ላይ አቃጨለ። በበሩና በአጥሩ ላይ የተሰባጠረው የጽሑፍ ሐረግ በሕልማቸው እንዳዩት እባባ እየተጥመለመለና እየተሳበ በሰውነታቸው ላይ የተጠመጠመባቸው መሰላቸው።

«በሏ! በሏ! መኻታ ቤቴ ድረስ ገተው እስኪቧርቁና እስኪለቀልቁ ድረስ ዝም ብላችሁ ተመልከቷቸው! » ብለው ለመጮህና ተናነቃቸው። ግን፣ ደመላሽ በጧት ወጥቶ ነበርና ሁነኛ ወንድ በሌለበት ማንንም ምኑንም በማያምኑበት ከቤት ገረድና ከአሽከር ጋር የመፋለም ውርደት፥ ከዚያም አልፎ - አዎ! ከዚያም አልፎ - ሕይወታቸውን በፈተና ላይ መጣላቸው እንደ ልጓም ገታቸውና ስሜታቸውን ተወጥረው ቻሉት - የሚፈነዱ እስኪመስላቸው ድረስ።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቅድስት ገብተው ትንሽ እንደ ቆዩ ከወንድ ጋር ማደራቸው ትውስ አላቸው። እንደ ደንቡ ከሆነ ረክሰዋልና የማኅሌቱንም በር መርገጥ አይገባቸውም ነበር። ወይዘሮ ዘርፈሽዋልም ረክሰው ቅድስት ሲገቡ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አልነበረም። ግን አሁን «ከሰው ስሕተት ከብረት ዝገት

አይጠፋም ቢሆንም የልቤን ንጽሕና መቸም አንተ ታውቀዋለህ። ሥጋ እንደ ሆነ ፈራሽ - በስባሽ - ነው » ብለው ይቅርታ በመጠየቅ ፈንታ «የእኛ ጥቃቅን ጉድ ምን ዋጋ አለው። ተፈርቶ ተከብሮ የኖረውን የጨዋና የጌታ ዘር ሁሉ እንደ ምናምንቴ አመድ ላይ ጥለው ያረከሱትን ያዋረዱትን ከሐዲዎች መቅጣት ነበር እንጂ » አሉ በምጸት ከራሳቸው ጋር።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በቅዳሴው ጊዜ ሁሉ ልባቸው ከሁለት የተከፈለ ነበር። ሙሉ ልባቸውን በጸሎት ለማጥመድ ይሞክሩና፣ አቡነ ዘበሰማያት ጨርሰው ጸሎት እግዚእትነ ማርያም ሲደርሱ፣ ምሬታቸው ድንገት ቱግ ይልባቸዋል። «ወቸው ጉድ! የማንም መጫወቻ እንሁን! ግዴለም! ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ እንደ ተባለው አንድ ቀን መግቢያ ቀዳዳ ይጠፋቸዋል » ይላሉ በሆዳቸው ጸሎቱን አቋርጠው። ጆሮዋቸውን አቅንተው ለጥቂት ጊዜ ቅዳሴውን ያዳምጡና ወዲያው ድንገት ንዴታቸው ገንፍሎባቸው ምኑንም ነገር ይማይሰሙና የማያዩ ይሆናል። «ምን ሁኑ እኮ ነው ይሄ ሁሉ ድንፋታና ውርጅብኝ! ሰው በአገር አይቀመጥ ነው! ግዴለም እንተያያለን። » ውስጠ ሰውነታቸው ይወራቻል። ‹ተንስኡ ለጸሎትና› ‹እግዚኦ› ሲባል መቀበል ይጀምሩና በመካከሉ ጥርሳቸውን ያፋጫሉ።

በዚህ አኳኋን ቅዳሴውን አስጨርሰው፣ ‹ሁሩ በሰላም› እንደ ተባለ፥ እምነት ስንኳ ሳይቀበሉ ወደ ወይዘሮ ሸዋዬ ቤት አመሩ።

ማዕበል በሚያናውጸው ባሕር መካከል እንዳለ ደሴት የወይዘሮ ሸዋዬ ግቢ አሁንም ጸጥታና እርጋታ እንደ ሰፈነበት ነው። የግቢያቸውን አጥር አንድም የመፈክር ጽሑፍ አልነካውም። የመንደር ሰው የመንደር ወጣት በልምጫም ሆነ በቃላት ‹አድኀሪና ኢ.ዲ.ዩ› ብሎ አልደፈራቸውም። የግቢያቸው ከከተማው ዳርቻና ገለልተኛ መሆኑ ለዚህ በጣም ረድቷቸዋል። ወይዘሮ ሸዋዬ ራሳቸው ደግሞ ሁኔታውን የያዙት በከፍተኛ ጥንቃቄና በዘዴ ነበር።

አብዛኛው የሠፈሩ ነዋሪ ሕዝብ፣ በየጊዜው የሚለዋወጥ አዲስ መጥ ተከራይ ሳይሆን የየራሱን ቤት ሠርቶ የሚኖር ስለ ነበር በዕድርም በጉርብትናም ይተዋወቃል። ብዙዎቹ እንዲያውም ቦታውን የገዙት ከወይዘሮ ሸዋዬ ነበር። እንደ አጋጣሚ ሆኖ በአከፋፈል ብዙዎቹን አላስቸገሩዋቸውም ነበር። የሩቅ ጭሰኛ አስጥለው ቢያስገርፉ «ዛሬ ከሚያወጣ የቅርብ ጉረቤት ጋር ግን ሆድ ለሆድ አለመሽካከር » ነው የሚል ዘይቤ ነበራቸው። አብዮቱ ዙሪያቸውን እየተጋጋለባቸው መሄድ ከጀመረ ወዲህ ደግሞ የታመመ መጠየቅና ኀዘን

መድረስ ለወለደች የአራስ ጥሪ ቢጤ መላክ ሥራዬ ብለው ያዙት። ሌላው ቀርቶ አንድ የሠፈር ልጅ እባለባበሱ ተጐሳቁሎ ያዩት እንደ ሆነ አስጠርተው «አንተን የሚያህል ጐረምሳ ሰነፍ! » ሲሉ እንደ አሳቢ እናት ከገሠጹትና ስለ ወላጆቹ ጤንነት ከጠየቁት በኋላ ለሳሙና ብለው ረከስከስ ያለ ልብስ ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ ይሰጡታል። ከብዙዎቹ የቀበሌ ተመራጮች ጋርም እንደዚሁ ሰምና ወርቅ እየሆኑ ሄደው ነበር። አብዛኞቹ ከቀድሞ ጀምሮ የሚያውቋቸው ከዚያም ሠፈር ተወልደው ያደጉ ናቸው። አሁን ከመንገድ ያገኙት እንደ ሆነ፣ «ደህና ነህ ልጄ! ኧረ ምነው ልጄ ብንጠያየቅ። አባትህ የልብ ወዳጄ ነበር። ታዲያ እናንተ - እናንተ ባላችሁበት ቡና የሚያጣጣኝ ልጣ! » ይሉታል።

«ኧረ እጠይቃለሁ ይላል። »

«ታዲያ አሁን የማትመጣ! »

«ሌላ ቀን እሜቴ! »

«ከልብ ካለቀሱ ዕንባ አይገድም ተብሏል። ዘመድ ለመጠየቅ ቀጠሮ አያስፈልገውም። እንደ ተገኘ ነው። ከአሁኑ የተሻለ ጊዜም የለ። እናንተ ባታምኑበትም እሱ በፈቃዱ እንው ያጋጠመን። » በአውቶሞቢላቸው መስተዋት ጠጋ ብለው በሹክሹክታ «ጥሩ የማር ጠጅ አለች። የሚጠጣ አጥታ ልትደርቅብኝ ነው። በል ግባ ይልቅስ! » ሲሉ በቀልድ ይኮሳተሩበታል። ሳይታወቅ ይሉኝታ ስቦት ግብዣውን ይቀበላል።

ጠጁ ተደጋግሞ ሰውነት ሲዝናና ጨዋታውን እንደ ፈለጉ ይመሩታል።

«ለመሆኑ የእህል ገበያ እንዴት ነው? »

«አሄሄ! እሜቴ፥ የታለና! ጤፍና ስንዴማ ጨርሶ አይገኝም። »

«አዎ! እኔ በያው ሰሞን ትንሽ እህል ባስፈልግ፥ ባስፈልግ አጥቸ ከጐጃም አስመጣሁ። እኔኮ ያልገባኝ እህሉን ምን ዋጠው! »

«ምን እናውቃለን። »

«አንተ የሚቸግርህ ከሆነ ከእኔ ትንሽ ውሰድ! »

«ኧረ ምን አስቸገረዎት እሜቴ! »

«ምን ችግር እለበት። ያስመጣሁት ከአሥር ኩንታል በላይ ነው። በዚህ ዕድሜዬ፥ ዛሬ እሞት ነገ እሞት ዐላውቀው። የተረፈውን እስከበላሁ ዕድሜ

ከሰጠኝ ይበቃኛል። ደሞስ ሶሺያሊዝም የምትሉት በችግር ጊዜ መተሳሰብ መሆኑ አይደል? » ሰውዬው እሽታውንም እምቢታውንም አረጋግጦ ሳይገልጽ አሽከር ይታዘዝና እህሉ በጆንያ ተሰናድቶ ከውጭ እንዲቆይ ይደረጋል።

ሰውዬው ተሰናብቶ ሲወጣ «በኋላ ያምጣልህ? ወይስ አሁን አብሮ ያድርሰው? » ሲባል ይጠየቃል።

«ኧረ ምንም አያስፈልግም እሜቴ! እንደ ምንም አፈላልጌ እሸምታለሁ። »

«በቅርብ እያለ የሩቅ ድካም ካሰኘህ የኔን ዝምድና የኔን ወዳጅነት ባትሻው ነው ማለት ነው። »

«ኧረ እንደሱ አይደለም! »

«እህሣ! »

«እሺ ዋጋው ምን ያህል ነው? » ገንዘብ ቢኖርም ባይኖርም በመግደደር ኪስ እንደ መፈተሽ ይደረጋል።

«ምነው ሸዋ! እንደ ነጋዴ አስሊ አረከኝ እንዴ! ግዴለም እህሉን ስታገኝ ትመልስልኛለህ። »

ግን ይረሳሳና ወይ ሳይመች ይቀርና አይመለስም።

ወይዘሮ ሸዋዬ እንደዚህ የሚያደርጉት፥ ስውዬውን አስቀድመው አጥንተውና አስጠንተው በገንዘብም፥ በዐመልም ያለበትን ድክመት ከአረጋገጡ በኋላ ነው። በዚህ አኳኋን ብዙዎቹ የቀበሌ ሹማምንት፥ በጤፍ በስንዴ፥ በጥራጥሬ፥ በሽሮ እህል፥ በቅቤ በዘይት በበርበሬ ስጦታ፥ የወይዘሮ ሸዋዬ ባለ ውለታ ሆኑ።

«እንጀራህን በባሕር ውስጥ ጣል። ከጊዜ በኋላ ታገኘዋለህ » የሚለውን የመጽሐፍ ጥቅስ በሆዳቸው እያሰላሰሉ እንዳሰቡትም ዋጋቸውን ለማግኘት ረጅም ጊዜ አልወሰደባቸውም። መሰሎቻቸው፥ እኩዮቻቸው ሲፈረጥጡ፥ አብዮቱን አምነው የተቀበሉ አገር ወዳድ ተባሉ። እንዲያውም ከዚህ አልፎ በቀድሞው መንግሥት ባያመቻቸው ነው እንጂ እንደነ ራስ እምሩ ቤተሰቦች የሶሺያሊስት ዝንባሌ አላቸው የሚል ወሬ ሥር ሥሩን ይነፍስላቸው ጀመር። የአድአው የጤፍ፥ የከፋው የቡና፥ የጨርጨሩ የደን መሬት፥ በአዲስ አበባ የነበራቸው ቦታና የሚከራይ ቤት በአርሲ እየፈነቀሉ ያስነሡት ጭሰኛ ታሪክ ተረሳ።

ሌላውን ሥራቸውን የሚያካሂዱት ደግሞ፥ ከዚህ በበለጠ ጥንቃቄና ዘዴ ነበር። ወደ መጀመሪያው ገደማ፥ አዝማሪ ቁሞ ቃልቻ ተሰይሞ በቤታቸው ብዙ ሰው ሲሰበሰብ እንዳላመሸ ሁሉ የሚሸፍተው እንዲሸፍት፥ ከገር የሚወጣው እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ በከተማ ውስጥ ያሉት የሚገናኙበት ቦታና ሁናቴ እንደ ሐረግ ተጠቃቅሶ ከተዘረጋ በኋላ፥ ‹የወገን› ሰው ያለ ቀጠሮ ከቤታቸው እንዳይመጣ ወሰኑ። ጉዳይ ያለው አስቀድሞ ቴሌፎን ይደውላል። ወይም አልባሌ የሆነ ሰው ይላካል። ጠጉረ ልውጥ ሰው ወይም አዲስ ነገር እንደ ሌለ ሠፈሩ በአጠቃላይ ዐይን እንዲጐበኝ ተደርጎ ከዚያ የቀጠሮው ሰዓት ይነገረዋል። ከቀጠሮው ሰዓት ቀደም ሲል አንድ ታማኝ የቤተሰብ ልጅ ከአስፋልቱ ወደ ቤታቸው መታጠፊያ ላይ እንደ ዋዛ እየተጫወተ ይጠብቃል። በቀጠሮው መሠረት ሁሉም ነገር ደህና ከሆነ በቀልድ ትርፊከኛ እጁን ዘርግቶ ይመራዋል። በልዩ እክል ምክንያት ቀጠርዎው መሰረዝ ካለበት ኮረኮንቹን መግቢያ ሆን ብሎ በዝግታ ያቋርጣል። መልእክቱ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው የሚለወጥ ነው።

በዚህ አኳኋን ወይዘሮ ሸዋዬ የሠፈሩን እምነትና አክብሮት አገኙ። ጥርጣሬ የሚሰማቸው ምናልባት አንዳንድ ቢኖሩም ከንቱ ቅያሜ ከማትረፍ በቀር የሚያምናቸው እንደማያገኙ ስለሚያውቁ ለመግለጽ አይደፍሩም ነበር።

በወይዘሮ ዘፈርሸዋል ድንገተኛ አመጣጥ ጥንቃቄያቸው የተጣሰባቸው ወይዘሮ ሸዋዬ እንደ መቆጣት ብለው «ምነው ደህናም አይደለሽ? ለምን አስቀድመሽ አልደወልሽም? ወይም ሰው አላክሽም? ይኸን አጉል መዝረክረክ ተይ አላልኩም? » ሲሉ ጠየቁ።

«ቤተ ክርስቲያን እንደ ቆየሁ ተቻኩዬ ዘነጋሁትና በቀጥታ መጣሁ። ምክር እንድትሰጪኝ ብዬ » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሸዋል። ከዚያም ወይዘሮ ሸዋዬ እንደ ግል ዙፋናቸው ከሚቆጥሩት ፎቴ ላይ ተቀምጠው በማስተዋል እያዳመጧቸው ወይዘሮ ዘርፈሸዋል፥ ከዚያ አሰቃቂ ሕልም ጊዘ አንሥቶ እያደረባቸው የሄደውን ጭንቀትና ሥጋት አዋዩዋቸው።

«ጊዜውማ መቸም የመከራ፥ የጭንቅ ነው። እስኪያልፍ ድረስ። ታዲያ ስለ በረገግን፣ አጉል ስለ ተርበተበትን የምንጨምረው የምንቀንሰው ነገር የለም። ጤንነታችንን እንጎዳለን እንጂ። እና፥ ረጋ ማለት ነው። ክፉ ቀን ተጐንብሶ ይታለፋል ብለዋል ሲዳማዎች ሲተርቱ » ሲሉ ወይዘሮ ሸዋዬ አበረታቱ።

«የፍራትና የመርበትበት ጉዳይኮ አይደለም ሸዋዬ፥ ታውቂኝ የለ? ታዲያ አሁን ያንን የመሰለ አሰቃቂ ሕልም ምን ትይዋለሽ? »

«አይ መቸም ሕልም እንደ ፈቸው ነው ተብሏል። ያም ባይሆን ከመሠረቱ እባብ በምቀኛ የሚተረጐም ነው። እነዚህ የተነሡብን ምቀኞች አይደሉም ታዲያ? እና፥ ይኸው ነው፤ ሌላ ነገር የለውም። » ወይዘሮ ሸዋዬ አሁን የዘርፈሸዋልን ነገር ሲያዳምጡ የመጀመሪያ ቁጣ ቢጤያቸው እየተለሳለሰ ሄደ።

«ግን ነገሩ ሁላ ቀፈፈኝ! »

«ኤጭ! ምነው ሸዋ! ቀፈፈኝ፣ ሰለቸኝ በቃኝ! ብሎ ነገር የለም። መቻል ነው። አንዳንድ ጊዜ መቃጠልም ጭምር አለ። ሼክ ጂብሪል ካልተቃጠለ ሻማ አይበራም ብለዋል። በእነሱ ቋንቋ፥ ካልታገልን ደግሞ እንደዚሁ ሆነን መቅረት ነው። ማሸነፍ አንችልም። እንዲያው ያ ሰውዬሽ ከሞተ በኋላ ሆደ ባሻ ሆንሽ ልበል? »

«ወቸ ጉድ! - ምኑን ከምኑ አያያዝሽው እቴ! አሁንም አልተረዳሽኝም ልበል? » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሸዋል ጥቂት እንደ መከፋት በማለት። «አንቺ እንዳልሽው ትግል ነውና ለሌሎች ወገኖቻችን አብርተን ብንቃጠልማ ምን ቸገረኝ እበር። ሳናበራ ብንቃጠልስ? ነው የኔ ፍራቻ። ይህማ ከንቱ አመድ መሆን ነው። እና ቀፈፈኝ ስልሽ የምናደርገው ጥረት ሳይሆን ቤቱ ሠፈሩ ነው። ልጆጆቹ እንደ ሆነ ሠፈሩን ሙሉ በሙሉ ግዛታቸው አድርገው ነው የሚፈነጩበት። ዘፈን ሳይቀር ወጥቶበታል። ‹ባምቢስን ማን ባሻገረኝ፥ ባምቢስን ማን ባሻገረኝ ካዛቺስ ጉዳይ ነበረ› የሚል። የለውጡ ወገን ነኝ የደርግ ወገን ነኝ የሚል ሁሉ በካዛንቺስ መግቢያ መውጫ እያጣነው። ታዲያ ልጆቹ የልጅ ነገር ነውና አቅማቸውን ዐያውቁም። ታዲያ ትናንት በራዲዮ እንደ ተነገረው፥ ደርግ ለልጆቹ ሲል መላ ካዛንቺስን ድንገት ቢደበድበውስ? ከዚያ ያለነው ሁሉ አብረን ማለቃችን አይደል? ይሄን ነው ቀፈፈኝ ያልኩሽ? »

«ታዲያ መልቀቅ ነዋ! » አሉ ወይዘሮ ሸዋዬ የእርኩም አፍ የመሰለ አፍንጫቸውን በጣታቸው እየጠቀሱ።

«ምክር እንድትሰጭኝ የመጣሁትም ለእሱ እኮ ነው እሱን ሸጬ ሌላ ቤት መግዛት እችላለሁ ወይ? »

«መሸጡንማ እንኳን ካዛንቺስ ሌላስ ቦታ ቢሆን በአሁኑ የቤት ውድነት ገዢ መቸ ይታጣል! ግን ችግሩ፣ ሸያጭ በሕግ በከተማ ልማት በሚሉት በሕግ ካልጸደቀ አንቺ ሌላ ቤት ለመግዛት ሆነ ለመሥራት አትችዪም። አንድ ሰው ከአንድ ቤት በላይ አይኖረውም አይደል የሚሉት? ታዲያ ችግሩ፥ ይህ የሕግ

ፍቃድ የሚሉትን ለማግኘት ጥቂት ጊዜ ይወስድ ይሆናል። ምስክር ይላሉ። በጋዜጣ ይውጣ የሚሉት ነገር ሁሉ እምጥተዋል አሉ። »

«ታዲያ ምን ትመርከሪኛለሽ? »

ወይዘሮ ሽዋዬ አንጫቸውን በጣታቸው እየጠቀሙ ጥቂት አሰቡ። ያቀረቡትና ሁለቱ በአጭሩ ተመካክረው የተስማሙበት ዘዴ ቀላል ነበር።

ቤት መግዛት የሚፈልግ ሞልቷል። በተለይ ደግሞ በጨው በድርና ማግ፥ በጨርቃ ጨርቅ፥ በእህል በጥራጥሬ የጦፈ ንግድና በሌላም ኮንትሮባንድ አብዮቱ ሰማይ ያወጣቸው አዳዲስ ነጋዴዎች ገንዘባቸውን የሚጥሉበት አጥተዋል። ብዙዎቹ ከደላላነት ከኪዎስክ ንግድ በቅርብ ጊዜ የወጡ ናቸው። አሁን የሚነጋገሩት ግን በሙቶ ሺህ ብር ቤት ነው። እንደዚህ የመሰሉት ካዛንቺስ ቤት ከነግቢው አግኝተው ዐይናቸውን አያሹም። ለጊዜው ችግር የሚሆነው የሕጋዊ ፈቃዱ ዝውውር ነው። ነገር ግን ከሚገዛው ሰው ጋር በዋጋው ከተስማሙና ሰውዬው የሚታመን ከሆነ፥ ገንዘቡን በሙሉም ከፈለ አልከፈለ ገብቶ ሊቀመጥበት ይችላል። ምክንያቱም ቤቱ ባዶውን ከተዘጋ ኪራይ ፈላጊውም የሠፈር ደላላውና ጠቋሚውም ባለቤት የለውም ብሎ በመንግሥት ሊያስይዘው ይችላል። ከዚያ በኋላ ይቀልጣል ፡

ስለዚህ የሚገዛ ታማኝ ሰው ከተገኘ፥ ዕለቱን ቤቱን ለርሱ አስረክበው ዘርፈሽዋል ለጊዜው በመሶብ ቤቱ ተቻችለው ቢቆዩ ሌላው፥ ችግር ሁሉ በጊዜው ይፈታል ማለት ነው።

ወይዘሮ ሽዋዬ በሰዎቻቸው አማካይነት ያብዮት ጊዜ ያነሣው ነጋዴ፥ ገዢ ለማግኘት ብዙ ቀን አልፈጀባቸውም።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ‹በጨዋዎች› ሠፈር በቦሌ፥ ቤት እስኪገዙ ወይም እስኪሠሩ ለጊዜው በሞሰብ ቤታቸው ወዲያውኑ ተጠቃለው ገቡ።

ማስረሻ ከአማኑኤል ወጥቶ የቀድሞው አማቱን ግቢ ሲቃኝ አዲስ ነዋሪዎች ያጋጠምው ከዚሁ በኋላ ነበር።

# ምዕራፍ ሦስት

ካሣሁን ከእርሱ በፊት እነ አይዋ ደሴ የሚስቱ የዘይኔ አባት ሙሔና ሌሎችም የቆሬ መንደረተኞች እንዳደረጉት ሁሉ ከመንደሩ መሐል ላይ ከሚገኘው የግራር ዛፍ ሥር ተቀምጦ ዐይኑን እስከ ቻለ ደረስ ቀዬውን ከቃኘ በኋላ፥ እርካታና ሐሳብ በተቀላቀለበት ስሜት ከበድ አድርጎ ተነፈሰ።

ከፊት ለፊቱና ከአባባቢው የሚያየው ነገር ከሞላ ጐደል የሚያረካ ነበር። የአሸተው ለአጨዳ የደረሰው የታጨደው እንደ አብዛኛው የወሎ ክፍል ሁሉ የዘንድሮው የቆሬ መራ የጥጋብ ዘመን ነው ባያሰኝም ውብ ነው። ከየስደቱና ከየመጠለያው ተመልሶ፥ ስልሣ ሰባትን እንደ ምንም የዘለቀውና ያገባደደው ገበሬ ያ እልቂት ያ ችግር እየታወሰው ግንቦትና ሰኔን ሳይታክት ሳይሰለች አረሰ። ቆፈረ። ጐለጐለ። ከሆዱ የቆጠባትን ዘር ለመሬት አደራ ሰጠ። ወዙን ለመሬት አጠጣ። ጣሙንና ድካሙን ከገመሰው ከኮተኮተው አፈር ጋር አዋሐደ በሥራ አማካይነት ሰውና ተፈጥሮ ቃል ኪዳን ተጋቡ።

ሰኔን ይዞ እስከ ሐምሌ መጀመሪያ ገዳማ፥ ተፈጥሮ የቃል ኪዳን ድርሻዋን ማሟላት ጀመረች። እንፋሎት የተሸከሙ ደመናዎች በሙብረቅ ጨረር እየተመሩ በነጐድጓድ ድምፅ እየታጀቡ ከአገር፥ አገር በማዳረስ መሬትን በጠል አራሱዋት ዳመናው በንኖ የዳመና ግላጭ ፀሐይ እየተተካች ርጥበት በሙቀት ሲተንን መሬት በማኅፀንዋ ውስጥ ሕይወት መፀነስ ቀጠለች። ፅንሱ የዕድገት ጊዜውን ጠብቆ በየማሳው በየዳገቱ በየሸለቆው ብቅ ብቅ አለ። እያደር መሬትን አረንጓዴ አለበሳት። በዚህ ዓይነት፥ የአዝመራ ቡቃያ በቆሬና በሌሎችም ቀበሌዎች አምሮ ሰምሮ እንደ ወጣ ሐምሌ፥ አጋማሽ ላይ ደመና ጉብኝቱን ድንገት አቁረጠ። በምትኩ ደረቅ ነፋስ ከምሥራቅ በኩል እየመጣ ልምላሜውን ይገርፈው ጀመር ያለ አንዳች ዳመና ግርዶሽ በጠራው ሰማይ ላይ የተሠየመችው የሐምሌ ፀሐይ ቡቃያውን ያለ ማቋረጥ ስትለበልበው ሰነበተች። የገበሬም ወዝ አብሮ ተለበለበ። ቡቃያው እንደ መጠውለግ ሲል የገበሬ ተስፋ ጠወለገ። የቆሬውንም ሆነ ሌላውን የምሥራቅ ወሎ ገበሬ ሥጋት ያባባሰው በምዕራብ ወሎ፣ በዋግ በላስታ በዋድላ ደላንታና በቦርና ልብ አቅልት ከተባለው አሠቃቂ በሽታ ገር ከበልጉ ወራት ጀምሮ ድርቅ የመግባቱ ወሬ ነበር።

የሁለት ዓመት እሸት ሳይበለት ያ ዓመት እንደ ገና ሊመጣ? ምነው እንዲህ ተፈጥሮ ለገመ?

አንዳንዱ እንደ አለፈው ጊዜ ሞት ከቤት ታዞ ሳይመጣ ለማምለጥ ልቡ የተነሣሣ። ከስደት ተመልሶ ስደት።

ካሣሁን የቆሬ ገበሬዎች ቀበሌ ማኅበር ሊቀ መንበር በመሆኑ ተስፋ የቆረጠውን ማጽናናት መበርገግ የቃጣውን ማረጋጋት ነበረበት።

«ለሁሉም ነገር መታገሥ እንው እኮ የሚሻለው » ይላክ ካሣሁን፥ በዕድሜ ከእርሱ የሚበልጡት ብዙዎቹ አዛውንት ብዙ ፈተናና መከራ በትዕግሥት ያሳለፉ የትዕግሥት አስተማሪዎች መሆናቸውን እያወቀ።

«ብንታገሥ ምን ይገኛል? » የሚል ጥያቄ ይቀርባል።

«እኔ ዝናሙ በቅርቡ መልሶ የሚጥል ነው የሚመስለኝ እና ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም። »

«ከዚህ ፀሐይና ሙቀት በኋላ ቢጥልስ ምን ፋይዳ አለው? ወይ አንበጣ ነው የሚስበው ወይ ተባይ ነው የሚያፈላው። »

«ለዚህ ሁላ መድኃኒት አለ ይባላል። መንግሥትን እንጠይቃለን እንዲረዳን? ሲል ይመልሳል ካሣሁን።

«ኧረ ኤዲያልኝ! ተባዩ እህሉን ድምጥማጡን የሚያጠፋ በሦስት አራት ቀን። ገና አዲስ አበባ ተልኮ ተመክሮበት ተዘክሮበት እስኪሆን ድረስ ምኑ ይተርፋል። ለዚያውስ ቢሆን ለንዳድ እያሉ የሚረጩት መድኃኒትም በየቤታችን ትኋንና ቁንጫ ነው ያፈላብን » የሚል መልስ ያገኛል።

«እስቲ መጀመሪያ አዝመራው ይትረፍና በመድኃኒቱ ምክንያት ትኋን ያስቸግረን። አይሻልም? ደሞ እኛ ሰነፍ ካልሆነ በእሳትም እየለበለብን በፍል ውሀም እየረጨን ልናጠፋው የምንችል ይመስለኛል። » ካሣሁንን መልስ አንዳንድ ሰዎች በታከተ ሣቅ ቢጤ ያደንቁለታል። ብዙዎቹ ግን ርሳቸውን እየነቀነቁ ስደታቸውን ያስባሉ።

ነገር ግን እባብ ያላየ በልጥ ይበረግጋል እንደሚባለው ሆኖ ነው እንጂ ገበሬው የተደናገጠበት ጉዳት ሳይወርድ አለፈ።

ጠፍቶ የሰነበተው ደመና ባሕር ማዶ በመሻገር ከውቅያኖስ ተመለሰ። ቀሪውን ሐምሌና መላ ነሐሴን ያለ ማቋረጥ በልግሥና አወረደው።

ዝናሙ ከበድ ያለ ስለ ነበር መፈልፈል የጀመረውን ተባይ መርጨትም ሳያስፈልግ በእንጭጩ አጠፋው። አዝመራው መልሶ ሲለመልም የገበሬ ተስፋ አብሮ ለመለመ።

የቆሬና የአካባቢው ገበሬዎች የስልሣ ዘጠኝ አዲስ ዓመት የተቀበሉት ከሞላ ጐደል ከሥጋትና ከጭንቀት በተቀላቀለ ስሜት ነበር። ስለሚያገኙት ምርት እርግጠኛ እየሆኑ ሲሄዱ ደግሞ ሁሉም በየበኩሉ ለመጨረሻው ክፉ ቀን ያስቀመጠውን ጥሪት በማዋጣት አንዲት የአረጀት ላም ገዝተው ቅርጫ ተካፈሉ።

አሁን ካሣሁን ከግራሩ ዛፍ ሥር ተቀምጦ በሐሳብ የተጠመደበት ነገር ብቅ ማለት የጀመረው ያን ጊዜ ነበር.....

.....ወግ ልማዱ እንዳይቀር ከቅርጫው መደብ ዙሪያ ሰንበርና ምላስ እየተቀማመሰ፥ የቤት አረቄ ፉት እየተባለ ጨዋታ ሲሟሟቅ የማኅበራቸው ጉዳይ እንደ ዋዛ ተነሣ ቀድሞ የከበርቴ የትራክተር እርሻ የነበረው መሬት ላይ መሬት ያለነበራቸው ወይም የጠበባቸው ሰዎች ከሌላ ቀበሌና አካባቢ መጥተው ማረስ ጀምረው ስለ ነበር፥ የጐጆቹ ብዛት ወደ ሃያ ደርሶ የቆሬ መንደር ሞቅ ሞቅ ብላ ነበር።

«የደርግ መንግሥት የገበሬ ማኅበር የሚባለውን የሚፈልገው ለራሱ ሲል ነው የሚባለው እንዴት ነው? » ሲል ከልካይ የተባለው አዲስ ከመጡት ጐረምሳ ገበሬዎች አንዱ ጠየቀ።

«ምንድን ነው የሚባለው? » ሲል ካሣሁን መልሶ ጠየቀ። ጥያቄው በተለይ ለእርሱ የተሰነዘረ አልነበረም። እንደ ሌሎቹ እርሱም ወሬውን የሰማ ቢሆንም አጠያየቁ በገበሬው ማኅበር ሊቀ መንበርነቱ ለማስተባበል እንዲመቸው ነበር።

«እህላችንን ሁሉ መንግሥት ነው የሚወስደው አሉ። »

«ሁላውን ከወሰደማ ከወትሮዎቹ ምን ተሻለ! » ሲል ተገኝ የተባለው ሌላ አዲስ መጥ ቀበል አደረገ።

«ውሸት ነው! አድኃሪያን የሚባሉት የሚያስወሩት ወሬ ብቻ ነው » አለ ካሣሁን ፍርጥም ብሎ።

«ወሬ ብቻ ነው እንዳይባልማ ይኸው መንግሥት በየከተማው እንደ ነጋዴ ሚዛን አቁሞ እህል ሲሸምት እየታየ አይደል! » ሲል በዕድሜ ጠና ያለ ሌላ አዲስ መጥ ገበሬ መለሰለት።

«በገንዘብ መግዛት ሌላ መውሰድ ሌላ። ገንዘብ ከፍሎ የሚገዛ ከሆነ እኛ ምን አስጨነቀን። ለግብርም ለልብስም ለሌላም ነገር ከሆዳችን ቀንሰን መሸጣችን አይቀር » ሲል ከበደ ተከራከረ። ከበደ የቀበሌው ማኅበር ምክትል ሊቀ መንበር ነው።

«እሱን አይዶል የጠላነው? »

«ምኑን? » ካሣሁን ግራ ገባው።

«ለመንግሥት መሸጡን። »

«በምን ምህኛት? »

«እሱ ዋጋ ሰብሮ በወሰነው ነው አሉ የሚገዛው? »

«አይዴለም » አለ ሌላ አዲስ ተናጋሪ «ምህኛቱም በገበሬዎች ማኅበር እህሉን ከጐተራው አውጥቶ ይወስድበታል። ነጋዴ የሚገዛበትን ዋጋ ሳይሆን እነሱ ሰብረው የወሰኑትን ከፍለው። ታዲያ ይሄ ምን ይበጀናል? »

የመጀመሪያው ለጠቅ አደረገ «ኧረ ይኸ ብቻም አይደለ። እኛ ገበሬዎች ብንፈልግም ባንፈልግም፥ የምንበላው ቢኖርም ባይኖርም መንግሥት የሚፈልገውን ያህል መስጠት አለብን ነው የሚባለው። »

«ዛዲያ ምን ተሻለ? » ሲል እንደ ገለልተኛ ያዳምጥ የነበረ ገበሬ ጠየቀ።

«ማኅበሩን ማፍረስ ነዋ » ሲል በመጀመሪያ የማኅበሩን ጉዳይ ያነሣው ከልካይ ርግጥ አድርጐ መለሰ።

«ማንኛችንም እንደ ፈለገን መቸም - መች ማኅበር አይፈርስም መሰለኝ። »

«ከፈለግን ለምን አይፈርስም! እኛ አይዴል ያቋቋምነው? » ጣት ተቀስሮ ጩኸት አስተጋባ።

ካሣሁን ስለ ማኅበራችን ከጥቂቶቹም ሆነ ብዙዎቹ ይህንን የመሰለ ብርቱ ተቃውሞ ሲሰማ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር። ብዙ ሆነው መተባበራቸውም አዲስ ነገር ሆነበት። «እሱማ ነው ግን፥ ነገሩ እንዲህ ነው » አለ በማስረዳት አኳኋን። «እኛን ማኅበር አንድናቋቁም ያደረጉን ዘማቾች በጣፉልና እኛም እሺ ባልነው

ደንብ መሠረት የማኅበራችን ትልቅ ጉዳይ ሁሉ የሚለየው ሁሉ አባል ተጠርቶ ጉባዔ ተቀምጦ፥ ተመክሮበት ተዘክሮበት ነው። እኔንም አንዴ መርጣችሁኛል። መንግሥም ዐውቆታል። ይህንን ደንብ እጠብቃለሁ። እንዲከበርም አስደርጋለሁ። »

«ግና የፈለግነው ከማኅበሩ ብንወጣስ? »

«እሱማ አይከለከልም መሰለኝ። » ካሣሁን በመልሱ እርግጠኛ አልሆነም።

«እንዲያማ ከሆነ፥ ከያ በኋላ ማኅበሩ ለመንግሥት እህል በተሰበረ ዋጋ እንድሸጥ ወይም በሌላ ነገር አያስገድደንም ማለት ነው » የሚል አስተያየት ቀረበ።

«ይችላል። ምህኛቱም በቀበሌው ማኅበር ክልል ውስጥ ለሚሆነው ነገር ሁሉ፥ ኃላፊ ተጠሪ ነውና » አለ ካሣሁን ተኮሳትሮ።

«እንዴ! ለመሆኑ አንተ ከእኛው ወገን ነህ ወይስ የደርግ ሹም? » አለ ከልካይ በአሽሙር።

«እንዳንተ ያለው አይጠይቀኝም! »

«እኔ ምንድን ነኝ አንተ! »

ካሣሁና ከልካይ ከተቀመጡበት በመፈናጠር ተነሥተው ለመደባደብ ተፋጠጡ። ነገሩ ቢያመር ለመገላገል ወይም ሚና ለመለየት ሌሎችም አብረው ተነሡ።

«ምን መሆናችሁ ነው! ነውርም አይደል? » ሲሉ አንደኛው አዛውንት ገሠጹ።

«ለምን ይሰድበኛል! » አለ ከልካይ ዐይኑን አጉረጥጦ። «የደርግ አሽከር ስላልሆንኩ ነው እንዴ! » አሽከር የሚለውን ቃል የመጨረሻ አሳፋሪና ነውረኛ ቅላጼ ሰጠው።

«ማነው የደርግ አሽከር! እኔ ካሣሁን የማንም አሽከር አይደለሁም! » ለመማታት ተንደረደረ።ከመሃል የገቡት ገፍትረው አራራቁዋቸው። ደግነቱ ሰነብርና ምላሱን የሚመትሩት በሸንበቆ ሥንጥር ስለ ነበር፥ አደገኛ የካራ መሣሪያ በሁለትም እጅ አልገባም ነበር።

ከካሣሁን ኋላ ቆም ብሎ የቆየው ከበደ ወደ ፊት መጥቶ! ሁለቱንም አፈጠጠባቸው። «እውነትም ምን እየሆናችሁ ነው የቆየ የግል ጠብ እንዳላችሁ ሌላ ነገር ነው። ስለ ማኅበራችን ግን ሁለታችሁ በተለይ እንዲህ የምትኋኋኑበት ምህኛት የለም። እኔም የማኅበሩ ሹም ነኝ። ሌሎችም አሉ። በሚገባ አላገለገላችሁም እኛ አንፈልጋችሁም የሚባል ከሆነ፥ ስብሰባ ተጠርቶ ሁሉም በተገኙበት ጥፋታችን ተገልጾ ብቻ የምሻር እንደሆነ እንሻርና ሌሎች ይመረጣሉ። ለሁሉም ጐልታችሁ ወይም ከዚህ ያለነው የምንወስነው ጉዳይ አይደለም። ስንት ነን? ሃያ ስንኳ አንሞላም። አሁን ግን በበዓል ምድር በሰላም እንዋል እስቲ » ሲል ኮስተር ብሎ ተናገረ።

«አዎ እንጂ! »

»አዎ ከብደ እውነቱን ነው ጃል - ለፍቅር ነው የተሰበሰብነው! » አሉ አዛውንቶቹ በመቀባበል።

ካሣሁን በጥያፌ ከልካይን ገላምጦ ከአጠገቡ ገለል አለ።

ከልካይም ቢሆን በጠቡ ለጊዜው መብረድ አልተከፋም። ድፈረት ባያንሰውም፥ ሰውነቱ ኮስማና ቢጤ ነው። አንድ ለአንድ በትግል ሆነ በዱላ ካሣሁንን እንደማይችለው አሳምሮ ያውቅ ነበር። ወገን ለይቶ ማበር ከመጣ ደግሞ ልብ - ለልብ ከሚተዋወቁት ከአንድ አራቱ በስተቀር ስለ ሌሎቹ አሰላለፍ እርግጠኛ አልነበረም። የፈለገው ነገሩን ለመቀስቀስ ነበር። አሁን ጭሮታል። «እኔኮ አምባጓሮ ፈልጌ አይደለም። ስለ ማኅበራችንም ስለ እኛም በማሰብ ነው። አሁንም ስብሰባ ተጠርቶ በሚገባ እንነጋገርበት » አለ ራሱን ቅን አሳቢና ሰላማዊ በማድረግ አኳኋን የጆቹን መዳፎች ወደ ላይ ገልብጦ በመዘርጋት።

«ይጠራል ይጠራል! ማን የሚፈራ አለ መሰለህ! » ሲል ካሣሁን በሩቅ ጮኸ።

«የሚያስፈራማ ነገር የለም » አለ ከልካይ በሰላ ፌዝ ቀስ አድርጎ።

«ግና መሾም እንጂ መሻር አያስደስትም። »

«የሚሻረው የሚሾመው ያን ጊዜ ይታያል። »

«እሱማ ነው። »

የስብሰባው ቀን ከዚያው በዚያው ተወሰነ....

አሁን ካሣሁን ከግራሩ ሥር ተቀምጦ ቀየውን እያስተዋለ የሚያስበው ከሁለት ቀን በኋላ ስለሚደረገው ስለዚሁ ስብሰባ ነበር። ንዴትም ሥጋትም የተቀላቀለበት ነበር።

## ፪

የቆሬ ገበሬዎች የቀበሌ ማኅበርን ያደራጁት ዘማቾች ከመጀመሪያው እንደ መረጡት፥ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሰበሰበው በፊት የትራክተር እርሻ የእህል መጋዘንና ዕቃ ቤት በነበረው ትልቅ የቆርቆሮ ዛኒጋባ ቤት ውስጥ ነው። ክርስቲያኑ ከቤተ ክርስቲያን እንደ ወጣ ቤቱ ሳይደርስ፥ እስላሙ የጧት እስባሁን እንደ ጨረሰ ዐረፍ ብሎ ሳይዝናና ወደ ስብሰባው ያመራ ጀመር። ከረፋዱ ላይ፣ አብዛኛው አባል በዛኒጋባው ዙሪያ በውስጥ በአካባቢው ጥላ ሥር ተሰበሰበ። የማኅበሩ ሹማምንት ለማሴር ሳይሆን እንዲያው ሁናቴውን ለመገምገም ያህል በአንድነት ተከማችተው ያስተውሉና ይጫወቱ ጀመር። «ዛሬ ሰው የሉ በግዝት የወጣ አልመሰለም እንዴ? » አለ ካሣሁን በመገረም።

በዐይን ግምት በተከለለው ሃያ ጋሻ መሬት ውስጥ የገበሬ ቀበሌ ማኅበር ያቋቋሙት አባሎች ብዛት ወደ መቶ አሥራ አምስት ነው። ከእነዚህ መካከል ለጠቅላላ ስብሰባ የሚወጡት ከሰባ በልጠው አያውቁም ነበር። አሁን ግን ወደ መቶ ይደርሳሉ። የቀበሌው ሕፃናት በአካባቢው ተሰባስበው ይጫወታሉ።

ከበደ የካሣሁን ክንድ ሳብ አደረገና፣ «እንግባና ፍርዳችንን እንቀበል እንጂ » አለው።

«ምን ወንጀል ሠርተናል? » ሲል ካሣሁን መለሰ፤ ጥቂት ተኮሳትሮ።

«መምሬ ወልደ ሰንበት እንደሚሉት ጻድቃንም እኮ ለፍርድ ይቀርባሉ። ወንጀለኞች ብቻ አይደሉም። »

«ለሁሉም እስቲ ልናይ አይደል! »

በካሣሁን እየተመሩ የማኅበሩ ሹማምንት ወደ ስብሰባው ሲገቡ ጫጫታው ጋብ አለ። የተቀመጠውም ጥግ ይዞ የቆመውም ሁሉ በዐይኑ ተከተላቸው። የሹማምንቱ መድረክ ወነብርም፤ ጠረጴዛም የለውም። ግን ለስብሰባ እንዲያመች የዛኒጋባው አንድ ጥግ እንደ መደብ ከፍ ብሎ ተደልድሎ

ለመቀመጫ የሚያገለግሉ ትልልቅ ድንጋዮች ተደርድረውበታል። ዘማቾች ነበሩ እንዲህ አድርገው የሠሩት።

ሌሎቹ ሲቀመጡ ካሣሁን እንደ ቆመ ቀረ። ከአንዳንዱ ሹክሹክታ በቀር ጭውውቱን አሁን አብቅተዋል። ከውጭ ብቻ የልጆች ድምፅና የከብቶች ጩኸት አልፎ አልፎ ይሰማል። ካሣሁን ጸጥታውን የበለጠ ለማረጋገጥ ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራረገና «እንደምን አደራችሁ? » ሲል ሰላምታ አቀረበ። አጸፋው አስተጋባ። «ዛሬ የተሰበሰብነው አንዳንድ አባሎች ቅሬታ አለን ብለው በጠየቁት መሠረት አለ ማኅበራችን እኛ ቅሬታ አለን ብለው በጠየቁት መሠረት አለ ማኅበራችን እኛ የመረጣችሁ የሠራነው ስሕተት ቢኖር ለመነጋገርና ለማረም ነው » ሲል ንግግሩን ቀጠለ። «እንዲያውም ከመሠረቱ ማኅበር ኢያስፈልግም የሚሉ እንዳሉም ተረድተናል። ምህኛታቸውን ይንገሩንና እንመክርበታለን። ግን የሚወሰነው እነርሱ በፈለጉት ሳይሆን አብዛኖቻችን በተስማማንበት ነው። » ካሣሁን ለፍልሚያ በመገበዝ ዓይነት ዐይኑን በከልካይ ላይ ተከለ።

ከልካይም ለፍልሚያ ጥሪው ተነሣ። «የማኅበራችን ሊቀ መንበር ይህንን ዕድል ስለ ሰጠኸኝ በጣም - በጣም አመሰግናለሁ። ከልቤ! » አለ በመዳፉ ደረቱን እየዳበሰ በፌዝ ቃና፤ «አዎ ማኅበራችን አልተስማማንም ካሉት ሰዎች መካከል አንዱ እኔ ነኝ። ግን እኔ ብቻ ደግሞ አይደለሁም። ብዙዎች ነን። »

«ስለ ሌሎቹ የሚያገባህ የለም። ስላንተ ብቻ ተናገር ሌሎቹ ስለ ራሳቸው ራሳቸው ይናገራሉ » ሲል ከበደ በድንገት ተነሥቶ ቆመ። ሁካታ አስተጋባ።

«ሥነ ሥርዓት! አንተም ብትሆን በሊቀ መንበሩ ቦታ ተተክተህ መናገር የለብህም! » አለ ከልካ ጮህ ብሎ። በሐሳቡ። የሚስማሙ አውካኩ።

«ሥነ - ሥርዓት! ሥነ - ሥርዓት! ስብሰባ እንጂ ሁሉም የሚንጫጫበት ገበያ አይደለም! » በማለት ካሣሁን በግሣጼ መልክ ተናገረ።

«ሥነ - ሥርዓት አስከብራ! » አለ ከልካይ እንደገና።

ካሣሁን ንዴቱ ጉግ አለበት። ጠረጴዛ የሚደበድብ ይመስል እጁን አነሣና መልሶ አወረደው። «አንተም ብትሆን ሥነ - ሥርዓት ካላከበርክ ከስብሰባው አወጣሃለሁ » ሲል ካሣሁን ዐይኑን አጉረጠረጠበት። ግን የንዴት ስሜት ሆኖበት ነው እንጂ ከልካይ ከከበደ የባሰ ሥነ - ሥርዓት ጉድለት እንዳላደረገ ይታወቀው ነበር። እንዲያውም ከልካይ ከከበደ ላይ የሰጠው ማፋረሻ ሐሳብ ዘማቾች እንደ ነገሩት ነው። ካሣሁን በሐሳብ ተውጦ ከልካይን አስተዋለው።

ካሁን ቀደም ብዙ ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ ስለ ከልካይ ማንነትና ምንነት ከሐሳቡ ጋር ተጠያየቀ። ከየት መጣ? እንዴትስ ለምንስ መጣ?

ከልካይ ወደ ቆሬ የመጣው ከስምንት ወር በፊት ነበር። ራሱ እንደ ተናገረው ከሆነ፣ ዱሮ በየጁ በመቀናጆ እያረሰ ይኖር ነበር። ነገር ግን እያደር በሚያገኘው ምርት መተዳደር ስላልቻለ ወልድያ ከተማ ገብቶ በሽቀላ ይኖር ጀመር። ባላባቱና አስገባሪው ሁሉ ሰፋፊ መሬቱን ተነጥቆ ድሀ ገበሬ መሬት እንደ ልቡ የሚያገኝበት ጊዜ ሲመጣ ደግሞ፥ ከእርሻ ተፈናቅለው በከተማ ይንከራተቱ እንደ ነበሩ መሰሎቹ እንደገና ወደ ግብርና ለመመለስ ቆሬ መጥቶ ሰፈረ። ይዞ የመጣው አንድ በሬና አንድ አህያ ነበር። እንደርሱ አንድ በሬ ካለው ጋር እያቀናጀ ሲያደርስ ከርሟል። ሚስትም ቤተሰብም የለውም። የሚኖረው ዕጣ ነፍሱን ነው፤ ሚስት እንደ ነበረውና ግና ሳይወልዱ በችግረኝነቱ ምክንያት ጥላው እንደ ሄደች ይናገራል።

ይህ ታሪኩ እውነት ይሁን አይሁን ያረጋገጠ የለም። በተቻለው መጠን ታታሪ ከመሆኑ በቀር የእጅና እግሩ አለ መርገፍ የአንደበቱ መቀላጠፍ በግብርና የኖረ ገጠሬ አያስመስለውም።

ካሣሁን ይህንን በመታዘብ ስለ ከልካይ ምንነት ጥርጣሬ ካደረገበት ቆይቷል። ግን እንዲያው በደፈናው ለጥርጣሬ ያህል እንደ ዋዛ ነበር። ለማጣራት እስከዚህም አላሰበበትም። አልተጨነቀበትም። አሁን ማኅበሩን በሚመለከት እንደዚህ ሲፋጠጠው ከነከነው። መልሱም ከፊቱ ላይ የሚያገኝ ይመስል ትኩር ብሎ አየው። የካሣሁንን ትኩረት ተገነዘቡት ሌሎች ሰዎችም ዘወር ገልመጥ እያሉ ከልካይን አዩት።

«አዎ! ስብሰባ እንዲደረግና ስለ ማኅበራችን ዕድል እንድንነጋገር ከጠየቁት አንዱ እኔ ነኝ » ሲል ከልካይ እንደገና ብድግ ብሎ ንግግሩን ቀጠለ። «እኔ ማኅበርተኛ የሆንኩት በቅርቡ ቢሆንም በዚሁ አጭር ጊዜ ውስጥ አንድ ነገር መገንዘብ ችያለሁ። ብዙዎቻችሁም እንደኔው ሳትገነዘቡት አልቀራችሁም። ይኸውም ማኅበራችን ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን ነው። እንዲያውም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ በዝቷል። » የመስማማትና የማስተባበል ድምፅ ባንድነት ተመመ። ከልካይ ግን፥ ቅንጣት አልተሸበረም። «እንዴት ማለት ደግ ነው። አንድ ጠቦት ጠፋ ‹ተሰበሰቡ› አንድ መንግሥት አንድ ዐዋጅ አስነገረ ‹ተሰብሰቡ› የተረፈን ነገር ቢኖር ለማይረባ ነገር ሁሉ ነጋ ጠባ ስንሰበሰብ የሥራ ጊዜያችንን ማባከን ብቻ ነው። ስለዚህ....... »

ንግግሩን ሳይጨርስ ካሣሁን ጣቱን ቀስሮ አቋረጠው። «ውሸት ነው! በአብዛኛው የምንሰበሰበው በበዓል ቀን ነው። የሥራ ጊዜ አላበከንም። »

«በበዓል ቀንም ቢሆን ብዙ ጉዳይ ይፈጸማል። የሩቅ ዘመድ ይጠየቃል። »

«ዘመድ እንዳለህ አላውቅም ነበር! » አለ ካሣሁን በማፌዝ አኳኋን።

«እሱ የራሴ ጉዳይ ነው። ለሁሉም ነገሬን አልጨረስኩም » በማለት ከልካይ ቀጠለ።

«ስለዚህም ይህች ባቄላ ያደረች እንደ ሆነ አትቆረጠምም እንደሚባለው ይህ ማኅበራችን ወደ ፊት ጉዳቱ እየባሰ ከመሄዱ በፊት አፍርሶ እኛም እንድ ወትሮውአችን መኖሩ የተሻለ ይመስለኛል። እስቲ ስታስቡት ትርፉ ምንድን ነው? ሹማምንቱ እንደሁ ሹም - ነን እያሉ የሚኩራሩበትና እንዘጥ እንዘጥ የሚሉበት ከመሆኑ በተቀር። »

የሣቅም የተግሣጽም ሁካታ አስተጋባ።

«እርጋታ! እርጋታ! » አለ ካሣሁን በጩኸት።

ርዝማኔያቸውና ቅጥነታቸው ምሰሶ የመሰለ፥ ላመል ያህል እንኳ ጠጉር የሌለበት ጭንቅላታቸው እንደ ቅቤ ቅል ያወለወለ ጉንጫቸው ተሰርጉዶ አገጫቸው የሾለ አንድ አዛውንት ድንገት ብድግ ብለው ቆሙ። በሚያበሩ ልም ዐይኖቻቸው ሰውን ሁሉ ኮስተር ብለው አስተዋሉት።

«አይዋ ይመር የሚናገሩት ነገር አለ? » ሲል ካሣሁን በአክብሮት ጠየቃቸው። ጸጥታው ድንገት ሰፈነ።

«አዎ - አዎ እንጂ » ሲሉ ንግግራቸውን ጀመሩ። ድምፃቸው እንደ ቁመናቸው የቀጠነ ሳይሆን እንደ ነጋሪት ይተማል። ወፍራም ሆኖ ሳይሻክር እንደ ወንዝ ሙላት ይወርዳል። «ይኸ ልጅ የተናገረውን ሰማን። ማኅበራችን ይፍረስ ነው የሚለው። አመጣጡ በቅርብ ጊዜ ቢሆንም፥ እንዳለውም ማኅበራችን እስከ አሁን አልጠቀመን ይሆናል። ግን፥ ማኅበር ኅብረት ማለት ነው። ኅብረት ደግሞ መልካም ነው። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ኅምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለኅምሳ ሰው ግን ጌጡ ነው ተብሏል። ማኅበር፥ ሰንበቴ ደቦ፥ ይኸ ሁሉ የመጣው ለመተሳሰብ ለመረዳዳት ነው። እናንተ ልጅ ቢጤዎች ይኸንን ችላ እያላችሁት ሄዳችኋል። በተለይ ለደሃ ለገበሬ፥ ኅብረት ነው ኃይሉ። አሁን በቅርቡ ሃቻምናና አምና ስንኳ ያ - ወንበዴ ሁሉ እንዲያ የተጫወተብን ኅብረት

ባይኖረን ነው። እስኪበቃው መታን። ታዲያ አሁንም እንዲያው ዝም ብለን ማኅበራችንን ይፍረስ ከማለት ይልቅ እንዴት ሊበጅን ይቻልል? ብለን እንመካከር። እስቲ ካሣሁን አንተ ሸዋ ደርሰህ መተሃል። ከዘማቾች ጓደኞችህ ጋርም ብዙ ጊዜ አብረህ ቆይተሃል። መቸም ይህ ማኅበር እንዲቋቋም ሲደረግ ስለ ፋይዳው የምታውቀው ነገር ሳይኖር አይቀርም። ሹም አድርገን የመረጥንህም ስለዚህ ነበር። የምትነግረን ነገር ካለ ንገረን! » አቶ ይመር ያንን ቁመናቸውን በራሱ በሚሰበሰብ መጫና አስመስለው ሲቀመጡ የአድናቆት ጭብጨባና ሁካታ ተከተለ።

ካሣሁንም የአክብሮት ፈገግታ አሳዩ። ፈገግታው ለራሱም ጭምር ነበር። አቶ ይመር በአካባቢው የተከበሩ የታፈሩ ስለ ሆኑ ነገራቸው ከባድ ሚዛን ይኖረዋል። ስብሰባውን እነ ከልካይ እንደ ፈለጉ ሊፈነጩበት አይችሉም። ቢሞክሩም ብዙው ሰው በግልጽ መቃወሙ አይቀርም። ከዚህ ጊዜ በፊት አቶ ይመር ስለ ማኅበሩ ምን አስተያየት እንዳላቸው እርግጠኛ አልነበረም። በዕድሜ የገፉ ሰዎች አዲስ ነገር ለመቀበል ያዳግታቸዋል ሲሉ ዘማች ጓደኞቹ ነግረውት ነበርና። እርግጥ አሁንም ቢሆን ማኅበሩን በዱሮው የኅብረት ጠቃሚነት እንጂ ከለውጡ አንጻር አልተመለከቱት ይሆናል። ግናስ ማንኛችንስ መች እርግጠኛ ነን? የሚል አስተሳሰብ አብሮ መጣበት። አዎ ራሱ ስለ ለውጥ የሚያውቀው በፊት ተማሪዎች ጓደኞቹ፥ በኋላም ዘማቾቹ እንደ ነገሩት ነው። እንደ ተባለውም ብዙ ነገር ደርሷል። ገባርነት ጭሰኝነት፥ ቀርቷል። የምስለኔ የጭቃ ሹም ትእዛዝ አብቅቷል። ማኅበሩም አጀማመሩ መልካም ነው። ለወደፊትስ አብቅቷል። ማኅበሩም አጀማመሩ መልካም ነው። ለወደፊቱስ ይኸ ለውጥ ሁሉ ምንድን ነው ውጤቱ? ማን ያውቃል? እንደ አዝመራ ነው። አዝመራ ይታረሳል ይዘራል፥ ከዚያስ ዝናም አለ ይመጣል አይመጣም ኩትኳቶ - ሌላም ሌላም።

ካሣሁን በእነ ከልካይ ሙከራ ያልተሸበረ መሆኑን ለመግለጽ ፈገግታ እያሳየ በዚያ ዛኒጋባ ቤት ውስጥ ተሰብስቦ የርሱን መልስ የሚጠባበቀውን ሰው ፊት ሁሉ አንድ በአንድ ሲመለከት ብዙ ዓይነት ሐሳብ መጣበት። በአዲስ አበባ ፖሊስ ጣቢያ እሥር ቤት የቆየበት ጊዜ ትዝ አለው። ማታ ማታ ግማሹ እሥረኛ እፈታለሁ እያለ ራሱን በተስፋ ያሞኛል። ግማሹ ምርመራ እገባለሁ እያለ ራሱን ያስጨንቃል። ከወሎ ተሰደው መጥተው ለገዳዲ ሰፍረው በነበረ ጊዜ፥ የቀድሞው መንግሥት ባለሥልጣን መጥቶ ሲያነጋግራቸው ግማሹ አጉል ተስፋ አድሮበት ነበር። ግማሹም ሳይረዳ በርግጎ ነበር። ከዚያ በፊት ደግሞ በዳገታማ ሚካኤል አፈርሳታ ጊዜ በተመሳሳይ ሁናቴ እንደዚሁ፥ ተስፋና ጥርጣሬ፥

እምነትና ጭንቀት ነበር። ታዲያ ሁሉም እንዳሰበው አይሆንም። ታዲያ እንደዚህ ያለ ጊዜ በሕይወትና በዕድሜ ተፈትኖ እልህን ንዴት የሌለበት አስተያየት የሚሰጥ አዛውንት ከስሕተትና ከጉዳት እንደሚያድን አይቷል። አሁንም አይዋ ይመር ይህንን መንገድ ከፍተዋል። በዚያው መከተል እንዳለበት ተሰማው።

«እኔ መቼም እንደምታውቁኝ በዕድሜም በዕውቀትም የእናንተው ታናሽ ነኝ » ሲል ከአባቱም በኋላም ከሙሔ ፊት እንደሚያደርገው አንገቱን በአክብሮት ቀልበስ አደረገ። «በመሠረቱ ዋናውን ነገር ሁሉ የሁላችን መካሪ አባት የሆኑት አይዋ ይመር ጨርሰውታል። » ሳይታወቀው አሁንም በድጋሚ ለሁሉም በአክብሮት እጅ እንደሚነሣ አንገቱን ደፍቶ አነሣ። የዝንብ በረራ የሚሰማ እስኪመስል ድረስ ፍጹም ጸጥታ ሰፈነ። ከውጭ በግድግዳው ቀዳዳ ሁሉ ዐይናቸው አጨልገው ከውስጥ የሚሆነውን ሁሉ ለመከታተል ይሞክሩ የነበሩት ልጆች ሳይቀሩ ትንፋሻቸውን ዋጡ። «እና የሞቱት እነ አይዋ ደሴ እነ አባባ ሙሔ - » የትዝታ ኃዘን ትንሽ ተናነቀው፥ «ሕይወታችሁን አሁንም ለእኛ ሲል ያርዝመውና በሕይወት ያላችሁት፣ እነ አይዋ ይመር ከአያቶቻችሁ ከአባቶቻችሁ ከራሳችሁ እንዲያው በጠቅላላው ከሀገራችሁ የብዙ ዘመን ሕይወት የወረሳችሁት ዕውቀት ብልሃት፣ ይኸ ነው የእኛ ዋናው ቁም ነገር። ከዚህ ተነሥተን እኛ የምናክለው ቅንጣት ነው። ዛዲያን፥ አይዋ ይመር በጠየቁን መሠረት ስለ ማኅበራችን ጠቀሜታ እኔ አሁን የምናረገው ከዚህም፥ የሰማሁትን ነው። እወነቱን ለመናገር ይኸ ነው ብዬ እርግቱን አላውቀውም። » ከዚያም በምርት ዘር፥ በማዳበሪያ በተባይ ማጥፊያ መድኃኒት እንዲያም ሲል በመኪና ማረሻና በሌላውም ነገር ሁሉ የገበሬ ማኅበር ከመንግሥት ሊያገኘው ስለሚችለው ርዳታ ከዘማቾች ጓደኞቹ የተረዳውን የወሬ ወሬ የሰማውን ለእኩል ሰዓት ያህል ተናገረ።

እንደ ጨረሰ፣ «ላማለኝ በሰማይ ወተትዋንም አላይ » የሚል ፌዝ ከተቃዋሚዎቹ ወገን ተወረወረበት፤ በሁካታ ታጅቦ። አንጀቱ በንዴት ሲቋጠር ተሰማው። አንድ ጠጣር ነገር ከሆዱእ ውስጥ ተላወሰበት። ተንደርድሮ ሂዶ የአንዳቸውን አንገት መፈጥረቅ አሰኘው። ግን፥ ጉሮሮው እየተናነቀው ስሜቱን ገታ። ሐሳባቸው በነገር እየጐነተሉ በማብሸቅ ጥፋት እንዲሠራ ለማድረግ መሆኑን ዐውቆት ነበር። አንዱ ያናደደውም ይህ ተንኰላቸው ነው።

ግን፥ ብዙም ሳይቆይ ንዴቱን በርድ የሚያደርግ መልስ ከሌላ ጥግ በኩል ተሰነዘረለት። «ይኸ ስንኳ ከቁም ነገራችን ውጭ የሆነ አጉል ቧልት ነው። አንተስ ቢሆን ሂደህ ሳታየው ሰማይ መኖሩን ታምን የለ? ታዲያ ሂደህ ሳታይ፣ ሳትመለስ

ሰማይ መኖሩን ካመንክ ዘንዳ ላም በሰማይ የማይኖርበትስ ምን ምህኛት አለና። »

«ሁለቱን ምን አመሳሰለው፣ ያ የፈጣሪ ሥራ፣ ይኸ የሰው። »

ካሣሁን በእነ ከልካይ አሽሙር ላይ የተሰጠው መልስ በሌላ መልስ ከመሻሩ፣ በፊት «እስቲ እንደማመጥ ሥነ ሥርዓት! » ሲል የፌዙን፣ ልውውጥ አቋረጠው። «ስለ ማኅበራችን ጥቅምና ጉዳት ስለ ሥራው፣ መሠራትም ስላለበት ከብዙዎቹ የቀረበውን አስተያየት አዳምጠናል። ከመጀመሪያው ከእነ አቶ ከልካይ የቀረበው ሐሳብም ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለ ሚበልጥ ይፍረስልን የሚል ነው። አይዋ ይመር ደግሞ የተናገሩትን ቁም ነገር ሁላችንም ሰምታችሁታል። እና፣አሁን ተጨማሪ አስተያየት ከሌለ፥ በደንባችን መሠረት ይፍረስ ወይም አይፍረስ የሚለውን በድምፅ ብልጫ እንወስናለን። »

ከልካይ ወዲያው ነቃ። የብዙዎቹን ስሜት ከነካው ከአቶ ይመር ንግግር በኋላ፥ ስለ ማኅበሩ ምርጫ ማድረግ በጭራሽ ሊያዋጣ አይችልም። ለእነ ካሣሁን ነው የሚበጀው። ዞር ዞር ብሎ ‹ወገኖቹን› በዐይኑ ጠቃቅሳቸውና፥ ለመናገር እጁን አነሣ።

«አቶ ይመር እንደ መከሩን ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል እንዳይሆን የማኅበሩን መፍረስ ለመወሰን መጣደፋችን መልካም አይመስለኝም። »

ካሣሁንና ሌሎቹ በመገረም ተመለከቱት።

«ማኅበር እንደሚጠቅመን ሁላችንም ስለምናውቅ፥ ይልቁንስ ማኅበራችን ጠንክሮ ጥሩ እንዲሠራ በአያሌው ብንመካከርበት መልካም ይመስለኛል። »

«እንዲያ ነው እንጂ! »

«የምንፈልገው እሱኑ አይደል? » ሲል ካሣሁን ተስማማ።

ብዙዎቹ ገበሬዎች፥ ጉዳይ የሰላምና የስምምነት መልክ የያዘ ስለ መሰላቸው እየተነሡ ስለ ኅብረት ረጃጅም አስተያየት ያወርዱ ጀመር። አንዳንዱ ንግግር ማለቂያ ያለው አይመስልም።

በዚህ ዓይነት ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ያለ አድናች ውሳኔ ስብሰባው እንዳይበተን ከልካይ ስለ ሠጋና፥ ዘዴ መመካከርም ስላለበት «ብዙ ጠቃሚ አስተያየት ሰማን። መልካም ነው። አሁን ደግሞ ማኅበራችንን እንዴት ለእኛው የሚጠቅምና የሚስማማ እናድርገው? በሚለው ጉዳይ ላይ እንማከርበት። ከዚያ

በፊት ግንረጅም ጊዜ ተቀምጠን በመቆየታችን የአንዳንዶቻችን ሰውነት ሳይደነዝዝ አልቀረምና ትንሽ ወጣ ብለን ተናፍሰን ብንመለስ? » የሚል ሐሳብ አቀረበ ፡

እምቢ የማይባል ጥያቄ ነበር።

ከልካይ ከጥቂት ጓደኖቹ ጋር የሚጸዳዳ መስሎ ወደ አንድ ዛፍ ጥግ ሲሄድ ከበደ በዐይኑ እየተከተለው፥ «ሐሳባቸው ምን ይመስልሃል በመነቅነቅ መለሰለት።

«እኔ እንጃ! » አለ በጥርጣሬ አስተያየት።

ሁሉም፥ ተጸዳድቶ ተናፍሶ ተንፍሶ በአዳራሹ ውስጥ እንደ ተሰበሰበ ከሁሉ በፊት እጁን አንሥቶ ለመናገር የቆመው ከልካይ ሳይሆን፥ ጐረቤቱ የሆነ ጐረምሳ ቢጤ ገበሬ ነበር። «በመሠረቱ እኔ ስንኳ አዲስ ሐሳብ የለኝም » ሲል ጀመረ። «ሁሉንም ሌሎቹ ተናግረው ጨርሰውታል። በእርግጥም ኅብረትን የመሰለ ነገር የለም። ማኅበር ደግሞ ያው የኅብረት አንዱ መንገድ ነው። አሁን እኛ ያቋቋምነው የገበሬ ማኅበር ኅብረት ግን መቸም አዲስ ነገር ነው። ያቋቋመውም ያው መንግሥት ነው። ያልጠረጠረ ተመነጠረ፤ ተብሏልና ዛዲያ መጠራጠሩ ከፉ አይመስለኝም። አሁን በወሬ ወሬ ስንሰማ መንግሥት ብዙ ነገር ሊያደርግ ነው ይባላል። እህላችንን ሁሉ ይወስዳል ይባላል። አይቶ ደግሞ የሁሉንም እህል ከመውሰዱ ሌላ ከብትም ንብረትም ሚስትም ልጅም የአንድነት ያደርጋል ይባላል። ሶሺያሊዝም የሚባለው እንዲህ ነው የሚሉት። መቸም እንዲህ ያለ ነገር ከባድ ነው። » ሁካታውና ጉምጉምታው ጋብ እስኪል ንግግሩን አቋርጦ ቆየ። «እና፤ ለይህም ሲሉ ነው የገበሬ ማኅበርን ያቋቋሙት ይባላል። »

«ሥነ ሥርዓት - ሥነ ሥርዓት! » ብሎ ከበደ ራሱ ከሥስነ ሥርዓት ውጭ ተነሣ። ያገደው አልነበረም። «እኛ የምንነጋገረው ስለ ማኅበራችን፥ ስለ አሁኑ። ወሬን ምን አመጣው? ባለፉት ዓመታት ስንት ዓይነት ወሬ ሰምተናል። ደግሞም መንግሥት በዐዋጅ አቋቋመው ብሎ መጥላቱ ትክክል አይደለም። »

«አዎ - » ሲል ካሣሁ ለጠቀ።

«ገባርነት ጭሰኝነት ቀርቶ ይህንን መሬት አርሰን እንድንበላ የተደረገው በመንግሥት ዐዋጅ አይደለም? ይህንንም እምቢ እንበላ! » የደጋፊ ጭብጨባ አገኘ።

የመጀመሪያ ተናጋሪ ጭብጨባውና ሁካታው ጋብ እስኪል በትዕግሥት ጠበቀና ተተካ፣ «አልጨረስኩትም እንጂ ወደ አይዋ ከበደ ቁም ነገር ልመጣ ነእብርኮ። የመሬቱ ዐዋጅ መልካም ነው። ማኅበር ማቋቋሙ መልካም ነው። እንደሚወራው ወደ ፊት የሚመጣ ጠንቅ እንዳለው ደግሞ አናውቅም። በእውነት ወሬው ብዙ ነው። ታዲያ ቅዠት ተፈርቶ ሳይተኙ አያድሩም ይባላል። ስለይህም ገና ይህ ይመጣል፣ ይህ ሊደርስ ይችላል ብለን ማኅበራችንን ማፍረሱ አጉል ነው። አቶ ከልካይ ይህ ሐሳብ ካለው አይዋ ይመር እንዳሉት ተሳስቷል። ግና ደግሞ፥ ያልተረጠረ ተመነጠረ ነው። ስለዚህም አዲሱ የለውጥ መንግሥት እኛ የማንፈልገውን ለእኛ የማይበጀንን እኛን የሚጐዳንን ነገር በማኅበራችን በኩል የሚሠራ እንደ ሆነ እኛን መስለው እኛን ሁነው ከእኛ ጋር ተስማምተው እምቢ የሚሉን የማኅበሩ ሹማምንት ካሉን ችግር የለበትም። ማኅበር አለልና። ኅብረት አለልና። ይኸው ነው » ብሎ ተቀመጠ።

ካሣሁን የነገሩን አዝማሚያ ለማወቅ «እና አሁን የምታቀርበው ሐሳብ ምን መሆኑ ነው? » ሲል ጠየቀ።

ለዕረፍት ወጥተው በነእብረ ጊዜ ከልካይ ሹክ ያለውን የሚያስተጋባው ተናጋሪ ለጊዜው ግራ የተጋባ በመምሰል «እኔ? እኔ? ከሆነማ፥ ማኅበራችን ሳይፈርስ እንደሚወራው ሥጋታችንን ደሞ ጨርሶ ለማስወገድ መጥፎ ነገር ቢመጣ ከእኛው ጋር የሚሆኑ ሹማምንት እንምረጥ። እኔ በበኩሌ አሁን ያሉት ከነ ካሣሁን - ሌሎችም እንዲህ ናቸው፥ እንዲህ አድርገውናል ማለቴ አይደለም። እኔ ማናቸውም አላስከፉኝም። ታዲያ በዚህ ያለነው ሁሉ ወይ መልሰን እንምረጣቸው፤ ጥርጣሬ ያለውም ካለ ሌላ ነገር ነው። ከእንግዲህ ዓመት ተነፈቅ ሆኗቸዋልና አዲስ ምርጫ እናድርግ ነው የምለው። » እጅ እንደ መንሣት ብሎ ተቀመጠ።

ካሣሁን አሁን የነገሩን አካሄድ አረጋገጠ። መጀመሪያ ማኅበሩን ማፍረስ ፈለጉ። ምናልባትም እነርሱ እንደሚፈልጉት መልሰው ለማቋቋም። ይህ የማይሆንላቸው መሆኑን ከስብሰባው መንፈስ ሲገነዘቡ ደግሞ አዲስ ምርጫ እንዲደረግ ጠየቁ። አሁንም ማኅበሩን እንደሚፈልጉት ለማደራጀትና ለመምራት ግን ለምን? ስለሚለው ጥያቄ እርግጠኛ ለማደራጀትና ለመምራት። ግን ለምን? ስለሚለው ጥያቄ እርግጠኛ መልስ የለውም። በመጠኑ ከዚህም ከዚያም የሰማውና የተገነዘበው ነገር አለ። የመንግሥት ሥልጣናቸውን፥ የመሬት ባላባትነታቸውን ስላጡ ሸፍተው በየሥፍራው እየተዋጉ ከተሸነፉት መኳንንት በቀር፣ አዲሱን የለውጥ መንግሥት የሚቃወሙ፥ ከተማሩትም ከተማሪዎችም

መካከል አንዳንዶቹ መነሣታቸው በሰፊው ይወራል። እንዲያውም አሲምባ ከሚባል የትግሬ አምባ ላይ ቆይተው አሁን ወደ ወሎ ዘልቀዋል ይባላል። ሁለቱም ለውጥ የሚፈልጉ ከሆነ በምን ምክንያት እንደሚጣሉ በትክክል ሊረዳው አልቻለም። የሚያውቀውና ሕሊናውን የሚመራው ግማሾቹ በየፈፋው ወድቀው የቀሩት ሌሎችም ወደየመጡበት የተመለሱት ዘማች ጓደኞቹ ስለ ነጻነት፥ ስለ እኩልነት ያስተማሩት ነው። በእርሱ ላይ የተጫነ ከባድ አደራ ሆኖ የሚሰማው፥ እነዚያ ጐተራ በዝባዦች እንዳይመለሱ በሽምግልና ዕድሜው መሆነኛ ተራራ ላይ የተዋደቀው የሚስቱ አባት ሙሔ የኢትዮጵያን ነጻነት ስለ ማስከበር መሬት አርሶ አፈር ገምሶ ስለ ማደር በመጨረሻ እስትንፋሱ የነገረው ነው። አዲሱ መንግሥትም በየጊዜው የሚናገረው ስለዚህ ነው። ስለዚህ በዚህ ሁሉ የመጣበት በራሱ ዐይን የመጣ ማለት ነው። እስከ መጨረሻ ይተናነቀዋል። ሌላ ነገር አይታየውም።

«እና አሁን ምን ይሁን ነው የምትለው? » ሲል ጠየቀ፥ ጥርሱን በንዴት እያፋጨ።

«ምርጫ እናድርግ! »

«እንዴ ማኅበሩ ይፍረስ! እንዴ ሹማምንት ይለወጡ ያው አይደለም! » ሚስቱን መቆጣጠር አቃተው።

«አይደለም » አለ ሌላ ረጋ ያለ አንደበት።

«ያው ነው! »

የድምፅ ትርምስ ሲነሣ ከበደ ልብሱን ጐትቶ አስቀመጠው።

«እስቲ ለሁሉም ታገሥ! »

«ምን እታገሠዋለሁ! ይህንን በጥባጭ ሁላ! » አለ ጥርሱን አጋጥሞ እየገፋ በሚወጣ የንዴት ትንፋሹ መካከል።

«ለሁሉም ነገር እርጋታ ነው » አሉ አቶ ይመር አሁንም አጠና አካላታቸውን ቀጥ አድርገው። «የበፊቱን ሐሳብ ተቃውሜዋለሁ። ካስፈለገ አዲስ ሹም እንምረጥ መባሉን ግን ክፋት አላይበትም። »

ካሣሁን የባሰውን አረረ። «እሺ እንምረ! » አለ የንዴት ሲቃውን ለመግታት እየታገለ። «ግን ምርጫ እንዲሆን የምትጠይቁ እንዳላችሁ ሁሉ ማኅበሩ እንዳለ

እንዲቆይ የሚፈልጉ ደሞ ሞልተዋል። ስለይህ መጀመሪያ ይኸ ጉዳይ ይወሰን። »

«ልክ አይዴለም። »

«እንዴት? ካሣሁን ንዴቱ ነገር መተንተን አላስቻለውም።

«በደንቡ መሠረት። »

«ምንድን ነው ደንቡ? » ካሣሁን በማመናጨቅ ጠየቀ።

ግራ በተጋቡት የማኅበሩ አባላት ሹክሹክታ መካከል ከልካይ ብድግ አለና «እህህህ! » አለ፥ «እኔ እንደሚመስለኝ አንድም ሆነ ሁለት ሰው ከጠየቀ በቂ ነው። አብዛኛው ሰው እናንተው እንድትቆዩ የሚፈልግ ከሆነ መልሶ እናንተኑ ይመርጣል። ካልፈለገም አዲስ ይመርጣል። የምትፈሩት ይህንን ካልሆነ በተቀር ምርጫ ስለ መደረጉ በምርጫ ይወስን ማለት ትክክል አልመሰለኝም። በግድ እንቆያለን አንለወጥም ካላችሁ ደግሞ መቾስ! - » ትከሻውን ነቀነቀ።

«እንደሱ ያለ የለም! ካሣሁን አቋረጠው። «እሺ አሁኑኑ ምርጫው ይደረጋል። ለእጩነት የምታቀርቡዋቸውን ሰዎች ስም መጥራት ትችላላችሁ » አለ ጥርሱን ማፋጨት እየቃጣው።

አሁንም ከልካይ በነገር ጠለፈው። «እንደሱ አይዴለም አቶ ካሣሁን! » አለው በማሽሟጠጥ ከፍነሩን ወደ አንድ ወገን ጠመም አድርጐ።

«ምን ፈለግህ ደግሞ አሁን! » ንዴቱ እየባሰበት ሄደ። አልቻለውም።

«የእኔ መፈለግና አለመፈለግ አይደለም። የዴንቡ ጉዳይ ነው። እናንተ የምትለውጡት ሹማምንት ከእሱ ሆናችሁ ምርጫውን ልታስደርጉ አትችሉም። እናንተን ባለማመን ሳይሆን ዴንቡ አልመሰለኝም። ሌላ ቦታ ሲደረግ እንዳየሁት እናንተ ትወርዱና፥ ከማኅበሩ አባሎች መካከል ጥቂት ሰዎች ተሠይመው ምርጫው ይደረጋል። ምርጫውን የሚያስፈጽሙት እነዚህ ለዚሁ ተብሎ አዲስ የተሠየሙት ናቸው። »

ካሣሁን በሙብሸቁ ትዕግሥት ነሥቶት ምርጫውን የሚያስፈጽሙት ሰዎች ገና ሳይሠየሙ እየተንደረደረ ከመድረኩ ወረደ። እነ ከልካይ በአጋጣሚው ለመጠቀም ጊዜ አላጠፉም። እርስ እብርሳቸው እየተጠራጠሩ፥ መድረኩን ለመረከብ አንድ አራት ሆነው ተነሡ።

በነገሩ የነቃው ከበደ ነእብር። «ቆዩ እንጂ የት ነው ሩጫው! » አለ ከበደ በአንገት ተነሥቶ ገፍትሮ የሚመልሳቸው ይመስል የእጆቹን መዳፍ ወደ ፊት ዘርግቶ። «እኔም ሲደረግ እንዳየሁት የሚያመርጡት ሰዎችም መመረጥ አለባቸው። »

«ተመርጠናል! »

«ማን መረጣችሁ? » ካሣሁን ተንኮላቸውን መቋቋም የሚችለው በአጉል ቁጣ ሳይሆን በትዕግሥት መሆኑን ተገነዘበ።

ግራ በመጋባት ለጥቂት ጊዜ ያህል ጉባዔው በሁካታ ሲተራመስ ከቆየ በኋላ አስመራጭ የሚሆኑት ሰዎች አንድ በአንድ በትክክል እንዲመረጡ የሚለው ድምፅ እያየለ በመሄዱ እነ ከልካይ መቀበል ግድ ሆነባቸው። ካሣሁን እንደ ገና መድረኩን ያዘ።

አንድ ጊዜ አንዱ የጠራውን ስም ሌሎች ሲቃወሙ አንድ ጊዜ ቆጠራው ልክ አይደለም ሲባል ብዙ ጊዜ ጫጫታው በዝቶ መደማመጥ ሲጠፋ ካሣሁን ሥነ ሥርዓቱን በትዕግሥት ማስከበር እንዳለበት ሲታወቀው ንዴቱ እየሸነፈው የአስመራጭዎቹ ምርጫ ብቻ ከአንድ ሰዓት በላይ ፈጀ።

በመጨረሻ አንድ የእነ ከልካይ ወገን መሆኑ በግልጽ የሚያስታውቅ አንድ ደግሞ ከነ ካሣሁን፥ ወገን ከዚያም በስንት ውጣ ውረድ አይዋ ይመር ምርጫውን እንዲመሩ ተመረጡ። እሳቸው ደጋግመው እምቢ ቢሉም እንኳ በዕድሜም፥ በረጋ አስተያየትም በአባሎቹ ተቀባይነትም፥ ሁለቱም ወገኖች አጥብቀው ያዟቸው። ሁለቱም ከአንዳችን በኩል ይሆናሉ ካለያም በትትክል ይበይናሉ ነበር ሐሳባቸው። ከሁለቱም በኩል ገለልተኛ ሆነው የተቆጠሩት እሳቸው ነበሩ። ሊቀ መንበርነቱን ያዙ። ሚዛኑ እንዳያጋድል።

ግን ከሁለቱም በኩል የሚመጣው የነገር እንቆቅልሽ ሊገባቸው አልቻለም። «ሥነ ሥርዓት » ሲባሉ፥ ያንን አጠና ቁመናቸውን የዛኒጋባውን ጣሪያ የሚነካ ይመስል ይለጥጡና፥ «አስመርጥ ብላችሁኛል! አስመርጣለሁ! ዝም በሉ » እያሉ ሲገሥጹ ሁለቱም ወገኖች ሳይወዱ በግድ ትክክለኛ የምርጫ ሥነ ሥርዓት ይሁን አይሁን ትእዛዛቸውን እየተቀበሉ መሄድ ጀመሩ። ከሁለቱም ወገን ምክርና የሥነ ሥርዓት እርማት እየቀረበ ሁለቱ ባልደረቦቻቸው እየረዱዋቸው ለእያንዳንዱ የሹመት ቦታ እጩዎች እየተጠቆሙ ምርጫው ቀጠለ።

ካሣሁን አሁንም ለሊቀ መንበርነት ተጠቆመ። ከልካይን በዐይኑ ገርምሞ እጅ ነሥቶ ተቀበለ። የከልካይ ስም ተጠራ።

«ይህንን ከፍተኛ አደራ ልትጥሉብኝ ስላሰባችሁ በጣም አመሰግናለሁ። እኔ ከፈቃዳችሁ አልወጣም። ለሹመት ለሽልማት ስል እምነታችሁን አሳልፌ አልሰጥም። በእኔ በኩል ማኅበራችን የእኛው ለእኛው እንጂ የማንም የውጭ ትእዛዝ ተቀባይና ፈጻሚ እንደማይሆን ቃል እገባላችኋለሁ » አለ። አነጋገሩ ተመርጦ እንዳበቃ ያህል ነበር። ካሣሁን በበኩሉ እንደዚህ ያለ ንግግር ባለማድረጉ ቆጨው። «ምን ዓይነት ቡዳ አጋጠመኝ ባካችሁ » አሁን ይኸ ማ - ይሙት ባላገር ነው? » አለ በሆዱ በነገር መበለጡን ማመን ግድ ሆነበት።

በሁለቱ እጩዎች ላይ ድምፅ ሊሰጥ ሲል፤ ‹አይዋ ከበደም ለሊቀ መንበርነት እንዲቀርቡ እጠይቃለሁ » የሚል ድምፅ ከኋላ ተሰማ። ከበደ ዘወር ብሎ ተመለከተ ሐሳቡን ያቀረበው ከወደነከልካይ በኩል የሆነ ሰው ነበር ግራ ገባው።

«እኔም ሐሳቡን እደግፈዋለሁ » አለ ከልካይ።

ከበደ የባሰውን ግራ ተጋባ በእርግጥ እኔን ፈልገው ነው? ወይስ ሆን ብለው ከካሣሁን ጋር ለመቀያየም? የሚል ጥራጥሬ በሐሳቡ መጣ። አእምሮውን ያነበበ ይመስል ካሣሁንም በትዝብት እኳኋን ተመለከተው።

«ይቅርታ ይደረግልኝ እኔ ሐሳቡን አልቀበለእውም። ችሎታውም የለኝም። የተጠሩት ሁለቱ ይበቃሉ » አለ ተነሥቶ።

«እኛ ትችላለህ ብለን ስንፈልግ ማገልገል አለብህ በማለት ከልካይ ተናገረ።

«አልችልም ብያለሁ አልችልም! በግድ ተመረጡ የሚል ደንባችን ውስጥም የለ! » ሲል ከበደ ፍርጥም አድርጎ መለሰ።

ከልካይ በጥላቻ ዐይኑን አፈጠጠበት። ንዴቱ ከፊቱ ላይ በግልጽ ይነበብ ነበር። ከበደን በእጩነት ያቀረቡት የምርጫ ድምፅ ለመከፋፈል ነበር። ከልካይ የደጋፊዎቹን ድምፅ በአንድነት የሚያገኝ ሲሆን በእጩነት ከቀረበ ግን፥ ለካሣሁን ብቻ ይሆን ከነበረው ድምፅ ቀንሶ ከበደ መውሰድ አይቀርም ነበር ምክንያቱም በነባሮችና በዕድሜ ገፋ ባሉት ነዋሪዎች ዘንድ ከካሣሁን ያላነሰ ተቀባይነት ከበደ ነበረውና። በከበደ እምቢታ ይህ ዘዴያቸው ከሸፈ።

ይህም ሆኖ የሁለቱ ምርጫ ውድድር ልብ ማንጠልጠሉ አልቀረም። «ካሣሁን ሊቀ መንበር ይሁን የምትሉ እጃችሁን አንሡ! » ተባለ። ሲቆጠር አርባ ስምንት ሆነ። «ከልካይ ይሁን የምትሉ » ሲባል አሁንም አርባ ስምንት ሆነ። አቶ ይመር ተናገሩ። ሰዉ ተተረማመሰ። ካሣሁን ተከነ። ተሳስሮ እንደሆነ እንደገና ይቆጠር ተባለ። ያው ሆነ። ለዚህም ለዚያም እጃቸውን ያላነሡ ቢኖሩ እንዲመርጡ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ ሁለተኛ ምርጫ ተካሄደ። ኀምሳ ሁለት ለኀምሳ ሁለት ሆኑ።

ነገሩ አንዳንዶችን አሳቃቸው። «ተናንቀው አንላቀቅም ካሉ ሁለቱንም ሊቀ መንበር ማድረግ ነው » ሲል አንዱ ቀለደ።

በስብሰውባው ላይ ከተገኙት መካከል ድምፅ ሳይሰጡ የቀሩት አቶ ይመር ብቻ ነበሩ። ባለፉት ሁለት ምርጫዎች «እርስዎጅኮ እጅዎን አላነሡም » ሲባሉ «እኔማ ዳኛ ማለት ነኝ፣ እናንተው ትበቃላችሁ » በማለት አልፈው ነበር።

«እንደሚታየኝ ከሆነ ነገሩ እንዲያልቅ አይዋ ይመር ከኍልቱ አንዱን መምረጥ ግድ ሊሆንብዎ ነው። ካለበለዚያ በቀጠሮ አሳድረን እንደ ገና መጨቃጨቅ ይመጣል » ሲል ከበደ አፋጠጣቸው።

አይዋ ይመር ዐይናቸውን ከደን አድርገው በሐሳብ ተዋጡ። ከሌሎቹ ጋር ተቀላቅለው መርጠው ቢሆን ኖሮ የእሳቸው ድምፅ ብቻ ለእንደዚህ ወሳኝ ሆኖ ባልታየ ነበር። ዝምብ ሲበር የሚሰማ እስኪመስል ድረስ ሁሉም ሰው አፍጥጦ ጸጥ ብሎ ጠበቃቸው። ዐይናቸውን ገለጥ አደረጉና የሚያብረቀርቅ ጭንቅላታቸውን በሌባ ጣታቸው እየጠቃቀሱ አንድ ጊዜ ወደ ከልካይ አንድ ጊዜ ወደ ካሣሁን ተመለከቱ። ካሣሁን ዐይኑን ሰበር አደረገ። ለሊቀ መንበርነት ይህንን ያህል በመጨነቁ ራሱን ታዘበው። ጥቃቱን ጠልቶት ነው? ሹመቱን ፍለጎት? ስሜቱን የገዛው የትኛው እንደሆነ ካሣሁን መለየት አልቻለም። የሚያውቀው ልቡ ተንጠልጥሎ መጠበቁን ነው።

በተለይ ለካሣሁን አንድ ዓመት ከሚመስል ረጅም ጊዜ በኋላ «አንተም ምረጥ ነው የምትሉኝ? » ሲሉ አቶ ይመር ጠየቁ። የአስተጋባው የአወንታ ድምፅ የምርጫ ጭንቀታቸውን አላቀለለላቸውም። ካሣሁንን ከከልካይ ረዘም ላለ ጊዜ ያውቁታል። ቅን ነው፣ ታማኝ ነው። ቤተ ዘመዶቹ እነ ሙሔ እነ አልጣሽ፥ ከዚያም በፊት በዳገታማ ሚካኤል የቀሩት በዘር ዘራቸው ሁሉም መልካም ሰዎች እበሩ። ከማያውቁት መላክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላ እንደሚባለው ከሆነ ካሣሁን የሚያውቁት ሰይጣን ሳይሆን የሚያውቁት መላክ ነው ከሚያውቁት

መላክ ሌላ ምን ይመርጧል? ከልካይ ደግሞ ዘር ምንዝሩን ምንጩን የማያውቁት አዲስ መጥ ነው። ግን እንደ ተገነዘቡት ብልህ ነገር ወዋቂ፥ አንደበተኛና ትጉህም ነው። በዚህ ችሎታው ማኅበራቸው በብዙ ረገድ እንዲጠቅማቸው ማድረግ የሚችል ይመስላል። ካሣሁን መሬት የሰጠው አዲስ መንግሥት እንደ አማቹ እንደ ሙሔ በሙሉ ልቡ አምኖ እሱ ያለው የአምላክ ቃል ነው የሚል ሲመስል ከልካይ ደግሞ ጥያቄ ያቀርባል፤ ይጠራጠራል። ይህም የሚከፋ ነገር አይደለም። በተለይ ደግሞ የገበሬ ማኅበር የተቋቋመው ሶሺያሊዝም በሚባለው አስተዳደር ሚስትንም ልጅንም ቤትንም እንዲያው ምኑንም - ምኑንም ነገር ሁሉ የኅብረት ለማድረግ ነው እየተባለ የዳር ዳርታ ሲወራ ሰምትዋል። ይህ እንኳን በውናቸው በሕልማቸው ሲደርስ ማየት ያማይፈልጉት ነገር ነው። ታዲያ አሁን በሁለቱ ሰዎች መካከል የትኛው ይሻላል ተብሎ ይመረጣል? ካሣሁንን መምረጥ አጉል ይሉኝታ ከልካይን መተካት ወረተኛነት ይሆን? ይመር ተጨነቁ ተጠበቡ። የሕሊና ፍርዳቸው ከሁለት አግጣጫ ተወተረ። «እና አንተም ምረጥ ነው የምትሉኝ? » ሲሉ ለሦስተኛ ጊዜ በመጠየቅ ዐይናቸውን ወደ ሁለቱም ተፎካካሪዎች ወረወሩ። ካሣሁን ጭንቀታቸው ያሳፈረው ይመስል አንገቱን ደፍቶ በሣር ቢጤ የወለሉን አፈር ይነቅሳል። ከልካይ ትኩር ብሎ ይመለከታቸዋል። አስተያየቱ የትምክህት ምልክት ነበረበት። - ዋ! እስቲ የሚል ዛቻ ዓይነት። አልወደዱትም። «መምረጥ አለብህ ካላችሁ እንግዲህ » አሉ አንገታቸውን ወደ ፊት ሰገግ አድርገው «እኔ ካሣሁንን መርጫለሁ። »

አሁንም ቢሆን እነ ከልካይ መሸነፋቸውን አልተቀበሉም። «እንግዲያው አሁን ሁሉም ሰው እጁን አንሥቶ ይምረጥና ተቆጥሮ ይወሰን » የሚል ሐሳብ ቀረበ። ከደጋፊው ይልቅ የተቃዋሚው ድምፅ አይሎ ተሰማ - ይኸም በዛ! - የምን መመናቸክ ነው! ከዚህ ውለን ልናድር ነው!...... አጉል ግፊታቸው ስሕተት መሆኑን እነ ከልካይ ወዲያው አገኙት። እንደ ገና ምርጫ ተደርጐ ሲቆተር ኀምሳ ስድስት ለአርባ ስምንት ሆነ። እንዲያውም አሁን የአቶ ይመር መምረጥ አላፈለገም። ከዚህ በኋላ የከልካይ ወገኖች መጋፋት ስላልፈለጉ የሌሎቹ ሹማምንት ምርጫ ያለ ብዙ ውጣ ውረድ ተካሄደ።

ስብሰባው አብቅቶ ሰው ሲበተን፥ ፀሐይ ወደ ምዕራብ ተደፍታ የቆሬን፥ ቀበሌ በደረቱ ሥር ያቀፈ የሚመስለው ተራራ ጥላውን መዘርጋት ጀምሮ ነበር።

ሰው ሁሉ በየአግጣጫው ተበታትኖ ከበደና ካሣሁን ብቻቸውን አንድ ጊዜ ጐን ለጐን ሌላ ጊዜ ፊትና ኋላ እየሆኑ ወደ ቤታቸው ሲሄዱ፥ ካሣሁን የያዘውን

ስንጥር ድንገር ጣል አደረገና «ለምን አልመረጥም አልክ አይዋ ከበደ? እኔ እንዳልቀየምህ ብለህ ነው? አንተም ብትመረጥኮ ያው ነበር » አለው።

ወዲያው መልስ አልሰጠውም። ሁለቱም በአርምሞ ጥቂት ከተጓዙ በኋላ «አንተም ሆነ እኔ ተመረጥን ያው ነው። እኔ ግን እንግዲህ እያረጀሁ መሄዴን አትርሳ። ውጣ ውረዱን አልችለውም። በዚህ ላይ ደግሞ የአባትህ ውለታ አለብኝ። አይዋ ሙሔ ባይወልዱህም አባትህ ማለት ናቸው። ስለይህ አደራ እንዳሉኝ ትቃትህ ጥቃቴ ነው። ታዲያ ምንስ ቢሆን - » ንግግሩን ሳይጨርስ ወደሱ ቤት የምታመራውን የእግር ፈር ታጠፈና ተለየው።

ካሣሁን ጦሙን እንደ ዋለ እህል ለመቅመስ በቀጥታ ወደ ጐጆው አልገባም። ወይም መምጣቱን በጥሪና በሰላምታ ድምፅ አላስታወቀም። የራሱ ሰውነት እንደ ጭነት ከብዶት የሚያራግፍ ይመስል፣ ከጐጆው ታዛ ሥር ካለ ትልቅ ድንጋይ ላይ ተዘረገፈና በሰፊው ተነፈሰ። ከዚያም ፊቱን በሁለት መዳፉ ላይ አስደግፎ የቆሬን ዳገትና ሸለቆ ከዳር እስከ ዳር ቃኘ። በዚች ቦታ ስንት ሰው አልቋል። በዚች ሥፍራ ስንት ግፍና በደል ተፈጽሟል። ወደ ፊትስ? እነ ከልካይ ምን ማድረግ ነው የሚፈልጉት? አሁን አሸነፎአቸዋል። በአጠቃላይ ከተመረጡት አሥራ አምስት የማኅበሩ ሹማምንት መካከል ስምንት ያህሉ ካሣሁንን የሚደግፉ ሲሆኑ፥ ከከልካይ ‹ወገን› የገቡት ሦስት ብቻ ናቸው። የቀሩት ከዚህም ከዚያም ያልሆኑ ናቸው።

ግን እንደ መጀመሪያ ንዴቱ አሁን ድሉ አላረካውም የዳመና ጓል ለመንጠቅ ተሸቀዳድሞ ቀድሞ ደርሶ የማይጨበጥ ዳመና እንደ መዳሰስ ያህል ሆኖ ተሰማው። እንደ ሆዱ ስሜቱ ባዶ ሆነበት።

«ገብተህ እህል አትቀምስም? ወይንስ ከዚያው ላምጣልህ » አለችው ቀደም ብላ ከጐጆው ውስጥ ምግብ ስታዘጋጅ የቆየችው ዘኔ።

ሌላ ሐሳብ ድንገት ነዘረው። እነ ከልካይ ሆን ብለው በእርሱና በማኅበሩ ላይ ተነሥተው ከሆነ እንዲህ በቀላሉ አይተውትም። ገና ብዙ ይፈታተኑታል። ምናልባት አደጋ ሊጥሉበትም ይሞክሩ ይሆናል። ታዲያ በእንደዚህ የፈተና ጊዜ ቤተሰን አብሮ ከማስጨነቅ፥ እንደ ልብ ወጣ - ገባ ዘወር - ዘወር ማለት እንዲቻል ብቻ መሆን የተሻለ ነው። ትዳራቸው እንደ ሆነ ለስም ያህል እንጂ ከወደቀው መንግሥት ባተረፈው ቅርስ ምክንያት የወንድነትና የባልነትወጉም መፈጸም ከተወ ብዙ ጊዜ አልፎታል። ‹ታዲያ እሷን እንደ መበለት ከእኔ ጋር

አስሬ የማስቀምጥስ ምን ምህኛት አለኝ። በዚህ ላይ ደግሞ ጣጣ ውስጥ መጨመር› አለ ከሐሳቡ ጋር።

«ካሣ ግባ እንጂ!« አለችው እንደገና ወጥታ።

ዘመዶችሽ ዘንዳ ሂደሽ ዐረፍ ብለሽ ብትከርሚ ምን ይመስልሻል ዘይን? ሲል ጠየቃት።

«የትኞቹ  ዘመዶቼ? » በመገረም አስተዋለችው። በሐሳብ ተውጦ ዘንግቶ ነው እንጂ የቅርብ ዘመዶችዋ ሁሉ በችግሩ ጊዜ ያለቁት አልቀዋል። የተረፉትም የት እንደ ደረሱ አይታወቅም።

«ጉበዜም በምሕረት ገብቷል እኮ አሉ » አላት ካሣሁን።

«ወሬ ሰማን እንጂ የት እንዳለ አልታወቀ። »

«አይዋ ሙሔ ያደገው የእንጀራ ልጅ ወንድማችሁስ? አንድ ጊዜ ተሹሞ ነበር ተብሏል። »

«ዛሬ ምንድን ነው የምትቀባጥረው? ማስረሻን ፈለጋ አዲስ አበባ ልሄድ። አባበም በጣም ችግር ቢጠናብን ምንተፍረቱን ደብዳቤ ጥፎለት ብጣሽ ወረቀት መልስ አልላከለትም። እና ዘመድ ጥየቃ ብዬ ማስረሻ ዘንዳ ሂጂ ነው የምትለኝ? ሆሆሆ! » አለች በመገረም።

«ይልቅስ ግባና እህል ቅመስ። »

## ፫

ማስረሻ የቢሮውን በር ሲከፍትና ቴሌፎኑ ሲያቃጭል አንድ ሆነ። ሰዓቱን ለቅጽበት ተመለከተ። ለሥራ መግቢያው ሰዓት አምስት ደቂቃ ጉዳይ ነው። «አ! እሱ መሆን አለበት » አለ በሆዱ። ‹እሱ› የሚለው ድርጅት የሕዋስ መሪውን ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚደውለው ወይ ከሥራ ሰዓት ቀደም ብሎ ወይ ከሥራ ሰዓት በኋላ ዘግየት ብሎ ነው። ራሱ በሰዓት ሥራ መግባት ስላለበትና በሕዝብ ቴሌፎን ስለሚደውል ይሆን? ወይስ ማስረሻ ቢሮ ሌላ ሠራተኛ የማይኖርበትን ጊዜ በመምረጥ? ወይንስ ደግሞ ማስረሻ ብዙም የሚሄድበት ሥፍራና የሚገናኘው ሰው ባለመኖሩ ብዙ ጊዜ ቀደም ብሎ መግባትና ዘግየት ብሎ መውጣት ማዘውተሩን በማወቅ አመች ጊዜ ነው ብሎ? ማስረሻ መልሱን

ለማወቅ ማንንም ጠይቆ አያውቅም። መጠየቅ አይገባውም። የድርጅቱን የአሠራር ምክንያት መጠየቅ ለጠላት መጋለጥ ነው። ዐውቆ ከሆነ ከሐዲነት፥ ባለማወቅ ከሆነ ቸልተኝነት። ሁለቱም ያስጠይቃል። በዲሲፕሊን።

«ሃሎ! »

«ሃሎ። »

የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ በቀየረው የድምፅ ቃና ስንኳ ማን መሆኑን ወዲያውኑ ዐወቀ። ግን ምን ጊዜም ጥንቃቄው መጠበቅ አለበት። ዲሲፕሊን። የድርጅቱ ደህንነት።

«ማን ልበል? » የሚል ኮስታራ ጥይቄ ከሕዋሱ መሪ ተሰነዘረ።

«አልፋ! » ሲል መለሰ። አልፋ የማስረሻ የኮድ ስም ነው።

«መብረቅ። »

«እሺ » ሲል ማስረሻ መብሸቁን ውጦ ትእዛዝ ተጠባበቀ።

«ዛሬ በአንድ ሰዓት ላይ ውይይት አለን » አለው።

«ዛሬ? ዛሬ ቀጠሮ ነበረብኝ! » ማስረሻ አሁንም ቅሬታውን ለመዋጥ ሞከረ።

«ትግላችን ከማንኛው ጉዳይ እንደሚቀድም አውቅ የለ? »

«እሱስ ነው። እና የት ነው የምንገናኘው? ሲል ማስረሻን ጠየቀ።

«ሳንሱሲ » ብሎ መለሰለት። ይህም የሥፍራው ሌላ የኮድ ስም ነበር።

«ሰዓት ይከበር። ጥንቃቄ ይደረግ። »

ማስረሻ በዕለቱ ቀጠሮ አልነበረውም። ግን በድርጅቱ በኩል የተዋወቃት ታፈሱ እሺ እምቢ ማለቱና ባያውቅም ወይ ራስ ሆቴል ለቢራ ወይም ለገሀር ምግብ ራት ፍንፍኔ ሊጋብዛት አስቦ ነበር። አሁን ግን ይህ መሰረዝ አለበት ማለት ነው። ነገ ደግሞ ራሱ ሐሳቡን ሊቀይር ይቻላል። ማን ያውቃል? የዛሬ ሐሳቡን የዛሬ ሕልውናውን ግን ለድርጅቱ መሥዋዕት ማቅረብ ግድ ሆኖበታል።

ለትግል ቅድሚያ!

ለድርጅት ቅድሚያ!

ዲሲፕሊን!

ይህ ሁሉ ግን ለምን ለማን እንደሆነ በትክክል ገና ሊገባው አልቻለም። ባልገባው አዙሪት ውስጥ ግን ተጠምዷል። እንዴት? ማስረሻ የቴሌፎኑን ጭንቅላት እንዳስቀመጠ አሁንም ለስንተኛ ጊዜ ሂደቱን በሐሳቡ ውስጥ እንደ ሲኒማ በማጠንጠን ለመረዳት ሞከረ......

እርግጥ ከአማኑኤል ሆስፒታል እንደ ወጣ ተጠልፎ ሲወሰድ ብቻ ሳይሆን የደረሰበት - ነገር - እንደ ስለላ ፊልም አስቃቂ ነበር። በኋላ ግን አስቀድሞ እንደ ሠጋው አልሆነም። የፍል ውሀው ‹አገናኙ› በሰጠው መመሪያ መሠረት በሳምንት ውስጥ መገናኛ ሚኒስቴር ሥር በተጠለለ አንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ የአንድ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ተቀጠረ። በእርግጥም የትምህርት ደረጃው ለቦታው በቂ ነበር። ይህም ሆኖ ግን፥ በደንቡ መሠረት ሌላ ተወዳዳሪ ቢኖር እንዲቀርብ ማስታወቂያ አልወጣም። ፈተናም አልተደረገም። ደሞዙ ትቶት እንደ ወጣው የምክትል ሚኒስትር ደሞዝ ባይሆንም ‹የባለ ሙያ› ደረጃ እንዲይዝ ተደርጎለታል። ከተሟላ የቢሮ ዕቃ ጋር ደህና ቢሮ ተሰጥቶታል። እርሱ በኃላፊነት ከሚመለከታቸው በርከት ያሉ ሠራተኞች በስተቀር ልዩ ጸሐፊም አለው። ችግር ሆኖበት የቆየው የመኖሪያ ቤት ችግር ነበር። ይህንኑም ቢሆን የሚስማማውን ዓይነት ቤት ለጊዜው ማግኘት አልቻለም እንጂ ቅድሚያ እንዲሰጠው ተደርጎ ነበር። ከፈለገም በአንድ ትልቅ ቪላ ውስጥ ከሌሎች ሰዎች ጋር በደባልነት መቀመጥ እንደሚችል ተነግሮት ነበር። ማስረሻ ግን የሚሰማው ቤት እስኪገኝ ድረስ ዐመሉን ለብቻው ራሱ ችሎ በሆቴል መቆየቱን መረጠ።

ከሥራ አያያዙ ቅልጥፍና ይበልጥ ያስደነቀው የአውቶሞቢሉ አገኛኘት ነበር። እስከ አሁንም አድራሻቸውን ያላወቀው አማኑኤል ሆስፒታል ያስገቡት ጓደኖቹ የነገሩት ቢሆንም ዕሱ ስለ ተመኘ በተአምር ተከስታ የሚያገኛት ይመስል ዱሮ ተከራይቶ ይኖር ወደ ነበረበት ቤት ሄዶ መጀመሪያ በቀዳዳ አሾልቆ ቀጥሎ ገረድ ዕቃ ለመግዛት ስትወጣ በሩ ሲከፈት በደንብ አድርጐ ከአረጋገጠ በኋላ ሱማሌ ተራ ቅርጫ ገብታ ምኑም - ምኗም አይተርፍም ሲል ለጥቂት ቀናት ያህል ተስፋ ቆርጦ ትቶት ነበር። ግን ሥራ መያዙንና ቤት ማግኘቱን ይከታተልለት ለነበረው ‹ተወካይ› ነገሩን እንደ ዋዛ አነሣለት።

«ቀልላ ነው » አለው ተወካዩ «የተገጣጠመ ቁም አካል ካላት ከአዲስ አበባ ቀርቶ ከኢትዮጵያ ቀርቶ ከሰማይ ብትወጣ እናመጣታለን። » የማስረሻን ፍላጎት ለመፈጸም ሳይሆን ‹የድርጅቱን› ኃያልነት ለማሳየትና የማስረሻንም የወደፊት ፍጹም ታዛዥነት ለማረጋገጥ ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ አልነበረም። «እና በሕይወት ካለች እናመጣታለን። መቃብር ማለት ሱማሌ ተራ ነው። መኪና

እንደ ሕንድ መካነ መቃብር ተበታትኖ ተቀጣጥሎ ድራሹ የሚጠፋበት። ይህ ካልሆነ ግን መኪናህ ከፊትህ ቁጭ ትላለች። ይህም የሚያሳየው በየትም ቦታ በየትም ጊዜ፥ ድርጅታችን ምን ያህል ኃይል ያለው መሆኑን ነው። እስቲ መኪና ጠፋብኝ ብለህ ለመንግሥት አመልከትና መልሱን የዛሬ ኀምሳ ዓመት ድረስ ጠብቅ። እወራረዳእልሁ በፈለግኸው!

«ኧረ ምን አወራረደኝ! ነገሩን አነሣሁት እንጂ ኧረ አልፈልጋትም። ግዴም አይደለችም » ሲል ማሰረሻ ዘጋ።

በሦስተኛው ቀን ግን አውቶሞቢሉ ከመሥሪያ ቤት ግቢ ድረስ መጣችለት። የግቢው ዘበኛ ቁልፉን ሲሰጠው ማስረሻ ዐይኑን ማመን አቃተው። ቀለሟ ጥቂት ደብዝዟል እንጂ ታርጋዋም ሌላ - ሌላዋም እሷው ነች። ‹እንዳሉት በተአምር ከሕዋው መዘዙዋት ልበል?› ሲል በመገረም ራሱን ጠየቀ።

ነገር ግን ተአምር የሌለበት ብዙም ውስብስብ ፍለጋ ያልተካሄደበት ቀላል ነበር። ‹ድርጅቱ› ለሥራ እንቅስቃሴ ተሽከርካሪ ብበዛት ያስፈልገዋል። ትግልና እንቅስቃሴ እንቅስቃሴና ተሽከርካሪ ወይም ሌላ የመገናኛ ዘዴ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። በዚህም መሠረት ከመጀመሪያው አንሥቶ ከፍተኛ የተሽከርካሪ ስምሪትና የሥራ ጠባያቸውም የማያቋርጥ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጋቸውን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በቁጥጥር ሥር ለማዋል ተሞክሯል። እያደረ ግን መስኩ እየቀነሰ እየጠበበም ሄደ፤ ብዙዎቹ የተነቃባቸው ወይም የተጠቆመባቸው መሆኑን ሲያውቁ ኀቡዕ መግባታቸው ተሽከርካሪ በማቅረብ የሚሰጡት አገልግሎት እየተቋረጠ ሄደ። በዚህም ምክንያት ‹አካላት› ሁሉ ተሽከርካሪ የሚያገኙበትን መንገድ እንዲፈልጉ ከበላይ ትእዛዝ ተላልፎ ነበር። አንደኛው መንገድ በልዩ ልዩ ምክንያት በየመሥሪያ ቤቱ በየፖሊስ ጣቢያውና በየፍርድ ቤቱ የቆሙትን ተሽከርካሪዎች መዝግቦ በአስፈላጊ ጊዜ በእጅ እንዲገቡ ማድረግ ነበር። ከተመዘገቡት አንድዋ የማስረሻ አውቶሞቢል ነበረች።

የማስረሻ አውቶሞቢል ከኢ.ህ.አ.ፓ መዝገብ ውስጥ የገባችው በፍርድ ቤት ሙግት በኩል አድርጋ ነበር።

ማስረሻ ሆስፒታል ከገባ በኋላ የቤቱ ባለቤት «አቶ ማስረሻ ሙሔ የተባሉ ሰው የአምስት ወር የቤት ኪራይ ሳይከፍሉ በድንገት ስለ ተሰወሩብኝ በግቢዬ የምትገኘው ቮልስዋገን አውቶሞቢላቸው በሐራጅ ተሸጣ ውዝፉ ኪራይ እንዲከፈለኝ በማክበር አመለክታለሁ » ሲሉ ለአውራጃው ፍርድ ቤት

ማመልከቻ አስገቡ። ነገር ግን ሰውዬው ሳንቲም የማይወጣቸው ስስታም ስለሆኑ በተለመደው ‹የሥነ ሥርዓት› ዘዴ ጉዳዩ ተጓተተባቸው። በመጀመሪያ ማስረሻ እንዲቀርብ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ ላይ መውጣት ነበረበት። ብዙ ወራት አለፉ። ከዚያ ከሁለት ቀጠሮ በኋላ ማስረሻ ቤታቸውን ተከራይቶት ለመኖሩ ምስክር ያቅርቡ ተባለ። ይህ ስንኳ ችግር አልሆነባቸውም። ከስንት ውጣ ውረድ ከስንት ቀጠሮ በሁላ ማስረሻ እንደሌለ ተቆጥሮ አውቶሞቢሏ በሐራጅ ተሸጣ ዕዳቸው እንዲከፈላቸው ተፈረደላቸው። ለፍርድ አፈጻጸሙ አሁን ብዙ ከተጉላሉ በኋላ የሐራጁ ቀን ሲቃረብ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ያደረገው ዐዋጅ ወጣ። ሰውዬው ቀደም ሲል በነበራቸው የሱካር በሽታ ላይ የገጠሩ መሬት ዐዋጅ ጨጓራቸውን አቃጥሎት በዚያ ላይ ደም ብዛትም ጉበትም ታክሎበት ሕመማቸው ተወሳስቦና ተደራርቦ ጥቂት ቀን በሆስፒታል ከአጣጣሩ በኋላ እንዲያውን አንቀላፉት። ከቤት ከአሉት ሌላ ዲቃላው ልጅ ወፈ - ሰማይ መስሎ መጣ። የተለመደው ንብረት ማስከበርና ሙግት ቀጠለ። ወራሾቹ የተመደበው ንብረት ማስከበርና የሚያውቁት ነገር ስላልነበረ በፍርድ ቤት ተረስታ ቀረች። በኋላ የሚፈልጋት እስኪመጣ.....

ጠያቂ ቢመጣ ደብዛውን ለማጥፋት መጀመሪያ አውቶሞቢሉን የሚመለከው ፋይል ከአካባቢው ተወገደ። ከዚያም ዘበኛ ዐይኑ በማያማትርበት ተላላኪ ከወዲያው ወዲህ በሚዘዋወርበት ባለ ጉዳይ በሚተረማመስበት ዳኞች ችሎት በተሰየሙበት ግቢ ውስጥ ባትሪ ተሞልቶ የተነፈሰ ጐማ ተሠርቶ የሞተር ዘይት ተጨምሮበ አውቶሞቢሏን ተነድታ ስትወጣ ማንም የጠየቀ አልነበረም።

‹በተአምራዊ ቅጽበት› መገኘታኘቷን ለማረጋገጥ ያህል የመጀመሪአይው ቀን ቁልፉ ተሰጠው እንጂ፥ ራሱ ብቻ የሚጠቀምባት የራሱ አውቶሚቢል አልሆነችም። ግማሽ ቀን ይዟት እንደ ሆነ ሦስት አራት ቀን አያያትም። አንዳንድ ጊዜ እኩል ሰዓት ያህል ከርሱ ጋር አትቆይም። ቴሌፎን ይደወልና «ቁልፉን ከመኪናዋ ጋር ተው » ይባላል። ተላላኪ ይገባና «አንድ ሰው የመኪና ቁልፍ ይጠይቃል » ይለዋል።

የሚሰጠው ምክንያት ‹ለድርጅት ሥራ ትፈለጋለች› የሚል ነው። ‹ግን ማንም ጐረምሳ የአነዳድ መማሪያ ሳያደርጋት ይቀራል?› የሚል ጥያቄ በሐሳቡ ሳይመጣ አልቀረም። ይህም ሆኖ አውቶሞቢሏን ከነጭራሹ ወስደው እሱን ለብቻው ቢተውት በመረጠ ነበር። ምርጫው አልተሰጠውም።

ከአማኑኤል ሆስፒታል ወጥቶ ሥራ ይዞ፥ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአንድ የሕዋስ አካል ውስጥ መመደቡ ተነገረው። በኋላ እየቆየ እንደ ተገነዘበው የተመደበበት ክፍል ‹ኢንስቲቱሽናል› ይባላል። ይኸውም በአብዛኛው የመንግሥትና መንግሥት ነክ የሆኑትን ሠራተኞች እየመለመለ የሚያሰባስብ ነው። ‹በኢንስቲቱሽናል› መዋቅር ውስጥ ሕዋስ የመጨረሻው ዝቅተኛ አካል ነው። ግን፥ በሠራተኛ ደረጃ ብዙ እንቅስቃሴ የሚካሄደው በዚህ ደረጃ ነው።

ማስረሻ በተመደበበት ሕዋስ ውስጥ ከእርሱ ጋር አምስት አባሎች አሉ። አንዱ እንደርሱው በመገናኛ ሚኒስቴር ክልል ውስጥ የትራንስፖርት ክፍል አባል ነው። ሁለተኛው «ትግል ከትምህርት ይቀድማል » በሚለው የድርጅቱ ልፈፋ፥ ሦስተኛ ዓመቱ ከዩኒቨርሲቲ አቋርጦ በዚሁ መሥሪያ ቤት በመዝገብ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ ነው። ሦስተኛው በቴሌ ኦፕሬተሮች ክፍል መለስተኛ ኃላፊ ሆኖ የምትሠራ ሴት ናት። ታፈሱ ትባላለች።

ማስረሻ በመጀመሪያ ቀን ስብሰባው ገና ዐይኑ ሲያርፍበት ያደረበት ስሜት፥ «አሁን ይህች ደግሞ ከዚህ ጣጣ ውስጥ ምን አገባት? ወይስ ከቤት እመቤትነት እንደኔው ተጠልፋ ነው? » የሚል ነበር። መልሱን ከገላዋ ላይ የሚያነበው ይመስል ትኩር ብሎ ተመለከታት። ታፈሱ ሁለተናዋ የሴት አይሉት የወንድ ልዩ ቅርጽ አላት። የባትዋና የክንድዋ ጡንቻ የላጋር ጉምሩክ ዕቃ ተሸካሚዎችን ያስንቃል። ከጉልበታኡአ ላይ እየጋጨ ዝቅ ሲል ወደ ጐንና ወደ ጐን የተንሠራፋ ባቷ፣ ስትራመድ ወደ አራት ማዕዘን ቅርጽ የተጠጋው ትከሻዋና ደረቷ የግርማ ቸሩ ጅምናስቲክ ቅኝት ያስመስላታል። ቦርጭ ግን የላትም። ጠቅላላው የአካልዋ ግዝፈ፥ የሥጋ ውፍረት ሳይሆን የአጥንት ድጉሰትና የጡንቻ ጥጥረት ነው። ፊቷም ቢሆን ከሌላው አካልዋ የተለየ አይደለም። አገጭዋ እንደ ትከሻዋ ወደ አራት ማዕዘን ይጠጋል። ግንባርዋ እንደ በሬ ሰፊ ነው። አፍንጫዋ ደፍጠጥ ያለ ነው። ስትሥቅ የከንፈርዋ ጠርዝ ጆሮ ግንድዋን ይስማል። በመካከሉ ግጥግጥ ብሎ የሚወጣው ፍልጥ ፍልጥ የሚያካክል ጥርስ ነው። በጉራማይሌ ንቅሳቷ ላይ የጥርሷ ንጣት ከሚያስደስት ይልቅ ያስደነግጣል። ቅላት መልክ አይፈጅም እንደሚባለው ከሆነ ደማቅ ቀይ ናት። ግን ሁሉንም የሚያከክሱላት ጸጉርዋና ዐይንዋ ናቸው። እንደ ዋዛ እሁለት ጉንጉን የምትለቀው ዞማ ጸጉርዋ ከሽንጧ ይደርሳል። እግርዋን አምቦትርፋ ጉልበቷን እያጋጨች ስትራመድ፥ ሆን ብላ ራሷን ላመል ያህል አንገቷን ሰበቅ በማድረግ ጉንጉን ጸጉሩዋን ታወዛውዘዋለች። ከሁሉም ይልቅ ባሕርይዋን የሚያንጸባርቁ የሚመስሉት ዐይኖቿ ናቸው። በዚህ ሰፊ ግንባርዋ ሥር ተራርቀው የተተከሉ ልም ናቸው። ግን አካባቢዎቻቸውን

በአድናቆት የሚቃኙ ፈገግ ስትል የሚሥቁ፥ ስትሥቅ በደስታ የሚጨፍኑ የሚመስሉ ዓይነት ናቸው። ሰፊ ግንባርዋ አራት መዕዘን አገጭዋ ፍልጥ ጥርሶቿ የሚሥቁ ዐይኖቿ ከ24 በላይ ከሆነው ዕድሜዋ ጋር ተደምሮ በተመልካች ዘንድ የየዋህነትና የቅንነት ስሜትን ያሳድራሉ።

ማስረሻ አትኩሮ ሲያስተውላት ታፈሱ፣ በአእምሮው የመጣውን ጥያቄ ያነበበች ይመስል «መቼም ሰው ከማያውቀው ሰው መካከል ድንገት ሲገኝ ይደናገረዋል። ግራ ይገባዋል። ‹እነዚህ ሁሉ ምንድን ናቸው?› ይላል። ግን ዕውቂያና ልደት አንድ ቀን ነው ተብሏል፥ በአባአቶቻችን። ሰው ገበያ ላይ ይገናኛል። ቤተ ክርስቲያን፥ ዝክር ማኀበር፥ ይሰበሰባል። ይኸ ደሞ፥ አዲስ ዓይነት ስብሰባ ነው። ስለዚህ እየቆዩ መተዋወቅ፥ እየቆዩ መለማመድ ስላለ አትደንግጥ። የተለያዩ የማይተዋወቁ ሰዎችን የሚያሰባስብ የሚያገናኛቸው ደግሞ አንድ ዓላማ ነው » አለችው።

ማስረሻ የነገረችውን ማመን ሞከረ። ግን አልቻለም። ሳምንታዊ ውይይት በምንም ዓይነት የሚለመድ ሆኖ አላገኘውም። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኋላም በእንግሊዝ አገር እንደሚያውቀው ክርክር የለበትም። የተለያዩ ሐሳቦች በአንድ መድረክ ላይ ቀርበው አይፋጩም። አይረታቱም። ስለ ‹ንዑስ ከበርቴ ሶሺያሊዝም› ስለ ‹ሦስተኛው ዓለም ፋሽዝም› ስለ «ደርግ » «ስለ ኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የአርነት ንቅናቄ » «ስለ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት » «ስለ ዲሞክራሲያ ጥያቄና » ስለ ሌሎችም ልዩ ልዩ ጉዳዮች በዲሞክራሲና በኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን ተበታኝ ወረቀቶች ላይ የሚገለጹትን ወይም ደግሞ «የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም - ጠይቅ » «የቻይና አብዮት » በሚልና በሌሎችም አርእስቶች «ኮከብ አሳታሚ » ያሳተማቸውን መጣጥፎች፥ የሕዋሱ ተጠሪ ወይ እሱ የሚጠይቀው ያነባል። ሌሎች ያዳምጣሉ። ንባቡ ከአለቀ በኋላ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። ጥያቄው ግን የተነገረውን በሙሉ ልብ ተቀብሎ የበለጠ ለመረዳት እንጂ በመጠራጠርና በመከራከር ዓይነት መሆን የለበትም። ይህ ጠያቂውን ያስጠርጥራል። በባንዳነት፤ በሰርጎ ገብነት። የዚህ ቅጣት ደግሞ እጅግ ከባድ ነው። የድርጅቱ ልዩ ልዩ ክንፍ አባሎች ሁሉ ማንበብና ማጥናት የሚፈቀድላቸው ከበላይ አካል የሚመጣላቸውን ወይም የሚመረጥላቸውን ብቻ ነው።

ማስረሻ በሦስት ጥናት ላይ ከተገኘ በኋላ ነገሩ ትንሽ ከነከነውና «ለመሆኑ እነርሱ ምንድን ነው የሚሉት? » ሲል እንደ ዋዛ ጠየቀ።

«ስለ ምኑ? » የሚል ጥያቄ መልሶ ቀረበለት።

«ስለ ያዙት አቋም የሚያቀርቡት ምክንያት መኖር አለበት » አለ ማስረሻ በፈራ ተባ።

«የፋሽስት አገልጋይ ባንዳ አቋም የለውም! » መልሱ የተሰጠው በቁጣ ዓይነት ነበር።

ማስረሻ ግን አሁንም ጥያቄውን አላቆመም። ዱሮ በብዙ የውይይት መድረክ ላይ ተካፍሎ ስለ ነበር እንደ ጋሪ ፈረስ ዝም ብሎ መነዳቱን አልወደደውም። «ስለ ባንዳነታቸው የሚደረድሩትን ምክንያት ብናውቀውኮ የእኛን አቋም ለማጠናከር የሚረዳ ይመስለኛል » አለ ረጋ፥ ለስለስ ባለ አንደበት።

«የእኛ አቋም ምን ጊዜም ጠንካራ ነው! ደግሞ የመርዝን ጐጅነት ለማወቅና የግድ መርዝ መጠጣት አያስፈልግም። ባንዶች መርዞች ናቸው። ለመሞት ካልተፈለገ በስተቀር መርዝን በሩቅ ነው! » ሲል የሕዋሱ አለቃ ደነፋበት።

ለማብሸቅ ያህል፥ ‹መድኃኒትምኮ መርዝ ነው፤ መርዝም መድኃኒት ነው፤ መርዝም መድኃኒት ነው› ሲል ቃጣውና አፉን እንዲዘጋ ታፈሱ በዐይንዋ ስታስጠነቅቀው አየና ተወው። ከዚያ በኋላ ጥያቄም አስተያየትም አያቀርብም።

ከውይይቱ የገደል ማሚቶ ዓይነት መሆን ይበልጥ፥ ማስረሻን የሚያስጠላውና የሚያናድደው የሕዋሱ መሪ ነው። ማስረሻ በመልክና በስም ቀደም ሲል አሳምሮ ያውቀዋል። ደረበ የተባለ ታዋቂ ተዋናይ ነው። በኢትዮጵያ አሉ ከሚባሉት ምርጦች አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል። ከቲአትር አፍቃሪዎች የሚያደንቁት ሞልተዋል። ምናልባት እንደ ፈረንጆቹ የሲኒማ ተዋንያን የሚያመልኩትም ይኖሩ ይሆናል። ለማስረሻ ግን ቀድሞውንም በሩቅ መጥላቱ የሚያስደስተው ሰው ቢኖር ደረበ ነው። ይቀልዳል። ኮሜዲ ቲአትርም ይሠራል። ግን ቀልዱም ኮሜዲውም አያስቀውም። በትራጄዲ ባሕርይ የሚጫወተውም አያሳዝነውም። መድረክ ላይ ስንት ጊዜ፥ በስንት ዓይነት ባሕርይ አይቶታል። ምኑም - ምኑም አይጥመውም ነበር። ‹ደረበ ከማለት ‹ደበረ› ቢሉት አይሻልም ነበር?› ብሎ ነበር ከራሱ ጋር። አሁን በቅርብ ሲገናኘው ደግሞ ‹ከመደበር› አልፎ የእኩይ ምሳሌ ሆኖ ታየው። ምናልባት ከመልኩ ሊሆን ይችላል። ሞላላው አገጩ፥ ጠኔ እንደ ያዘው ወደ አንድ በኩል የተጣመመ ነው። እንደ ክራንቻ ወደ ኋላ እየሸሸ፥ እንደ ፍየል ከአፈጠጠ ግንባሩ ሥር ሽልት

እብሆነ ሽፋሉና ቅንብዱ መካከል የተበለጠጠ እንደ ግርሽ የቀላው ዐይኑ ሥጋ ደዌ ያደረበት ያስመስለዋል።

ግን ማስረሻ እንዲጠላው ያደረገው ይህ መልከ ጥፉነት አይደለም። ሁናቴው ነው። አነጋገሩ ነው። በተናገረ ቁጥር ሌሎች በአናገሩት ቁጥር፥ ጣቱን እያፋጨ ሣቅ አይሉት አድናቆት ፌዝ፥ አይሉት ቀልድ፥ እንደ ፈረስ፥ ሃሃ! ሃሃ! ሃ! ማለት ያዘወትርራል። ማስረሻ ይህን ሁናቴውን ሲያስተውል፥ በጸጋዬ ገብረ መድህን ‹እናት ዓለም ጠኑ› ቲአትር ያለውን የገራፊ ገብረየስ ባሕርይ ያስታውሰዋል። ቲአትሩን በመድረክ ላይ አላየውም። ግን አማኑኤል ሆስፒታል በነበረበት ወቅት፥ ‹ሀሁ በስድስት ወር› እና ‹እናት ዓለም ጠኑ› በአንድ ጥራዝ የታተሙበትን መጽሐፍ ጓደኞቹ አምጥተውለት አንብቦት ነበር። የገራፊ ገብረይስ እንደ ሞሼ እንዳያን አንድ ዐይኑን በጥቁር እራፊ ጨርቅ ሸፍኖ ጅራፉን እንደ ጨበጠ አብሮ ታትሞ ነበር። ለማስረሻ የሁለት ተፈጥሮ ተመሳሳይ ሆኖ ታየው። ያ ሰው በመግረፍ ይደሰታል። ይሣለቃል። ደረበ ደግሞ በሕይወት ያሾፋል። በሰው ጭንቀት ይቀልዳል። እንደ ገብረየስ ያሽካካል። ገብረየስ አሁንም አሁንም ጅራፉን እንደሚያጮክ፥ ደረበም ጣቱን ያፋጫል። ሌላው ቀርቶ፥ የድርጅት ሥራውን በተውኔት መልክ የያዘው ይመስላል።

ማስረሻ አልፎ አልፎ ሳይወድቅ ዘለቃ በሐሳቡ ስትመጣበት ከደረበ ጋር በማነጻጸር፥ የሁለቱ ሕይወት ቢጋጠም ምን ዓይነት ገቢረ እኩይ ይፈጠር ይሆን? ሲል የተገረመበት ጊዜ አለ……

በአንድ ሰዓት ለአስቸኳይ ሰብሰባ የያዘው፤ ይኸው ደረበ ነበር።

‹ከአማኑኤል እንቅብ ወደ አብዮት ምጣድ፤ ምን ዓይነት ዕድል ነው? ሲል በሐሳቡ ራሱን ነቀነቀ።

## ፬

በቀጠሮው ሰዓት ኪዳኔ በየነ ሕንፃ ውስጥ በአንድ ክፍል ተሰበሰቡ። ክፍልዋ በኪራይነት የተያዘችው ኢፒድ በሚሠራ አንድ ሰው ስም ይሁን እንጂ፥ ለስብሰባና ለመገናኛ የሚጠቀሙባት ብዙ ሰዎች ናቸው። እንዲያውም ተከራይው በአዲስ አበባ ከተማ የለም። ክፍሏም አንድ ፍራሽና አንድ አልጋ፥ ከአንድ መናኛ ጠረጴዛና ከአምስት የእንጨት ወንበሮች በስተቀር፥ ሌላ የቤት

ዕቃ የለባትም። በክፍሉ የሚጠቀሙት የሕዋስ ወይም የሌላ አካል መሪዎች የበሩን ቁልፍ የሚያስቀምጡበት አንድ ሥውር ቦታ አለ።

ደረበ ከሌሎቹ ቀደም ብሎ ገብቶ ጠበቃቸው።

«ሃሃሃ! ታዲያስ እንዴት ነው የትግል ሕይወት? » አለ ዐይኑን እያብለጠለጠና ጣቱን እያፋጨ። መስል የሰጠው የለም። በጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጠው ዝም ብለው ተመለከቱት። «ዛሬ የተሰበሰብነው፥ ለጥናት ሳይሆን አዲስ መመሪያ ስለ ወጣ ለከፍተኛ ጉዳይ ነው። » ሲጋራ እየወጣ ተቀጣጠለ። ሥጋትና ጭንቀት በሁሉም ፊት ላይ ይነበባል።

«ከመካከላችን ምልምል እስኳድ እንድናወጣ ታዘናል። »

«ምን? » አሉ ሦስቱ በአንድነት፣ ከማስረሻ በቀር። ማስረሻ ግን ነገሩ አልገባውም ነበር።

«ሃሃሃ! ምን የሚያስደነግጥ ነገር አለው? ለትግል ነው የተነሣነው » ሲል ደረበ መለሰ።

«ግን'ኮ እስኳድ መመልመል ኢንስቲቱሽንን አይመለከትም፤ ይመለከታል እንዴ? » ስትል ታፈሱ ጠየቀች።

«አዎ! እስከ አሁን አልነበረም። አሁን ግን ትግላችን እየተፋፈመ ሄዶ የመጨረሻውን የማጥቃት እርምጃ የምንወስድበት ወቅት ስለሆነ፥ ከፓርቲውም ከወጣቶች ሊግም፥ ከኢንስቲቱሽንም ከሴቶች ሊግም ሳይቀር እስኳድ በብዛት ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል » ሲል መለሰላት።

«ለመሆኑ እስኳድ፥ ምልምል ምንድ ነው? » ማስረሻ አንገቱን አቀርቅሮ ጠየቀ።

«አሃሃሃ! እስካሁን እስኳድ ምን እንደ ሆነ አታውቅም! አሃሃሃ! የድርጅታችን የአጥቂና የመከላከያ ኃይል ነው! አሃሃሃ! አንድ መንግሥት የጦር ኃይል እንዳለው ሁሉ፥ ለአንድ ፓርቲም አንዱ ዋናው ክፍል የኃይል ክንዱ ነው - አሃሃሃ! »

«እስኳድነትኮ የሰውነት አቋምን የሚጠይቅ ይመስለኛል። »

«ፈቃደኛ የመሆን ጉዳይም አለ። »

«እኔ እንደምገምተው ከሆነ ማንም እስኳድ መሆን የሚችል አይመስለኝም። »

የጥያቄአቸው መቀባበል ደረበን እስከዚህም አላደናገረውም። «ልክ - ልክ ናችሁ » አለ እርግጥ ባለ አነጋገር። «አሃሃሃ! በእርግጥም እስኳድ ለመሆን ጠንካራ ሰውነት አስፈላጊ ነው። ግን እየዞርን ጡንቻ አንለምንም። ጡንቻቸውን እኛው፣ እንፈጥረዋለን ባይ ነኝ! አሃሃሃ! ‹እንዴት?› የሚለውን ጥያቄ በወታደርነት የሚሠለጥነውና ለውጊያ የሚበቃው በመጀመሪያ ወታደርነት ከገባ በኋላ ነው። ፈቃደኛ የመሆኑ ጉዳይ ነው የሚያጠያይቅ አይመስለኝም። ለድርጅታችን ግዳጅ ፈቃደኛ እየሆነው ገና አባል ስንሆን ይመስለኛል! አይደለም እንዴ? አሃሃሃ! » መስል የሰጠው ባይኖር መልስም ሳይጠብቅ ንግግሩን ቀጠለ። ‹እና ከመሠረቱ እንደ አዲስ እንገር የሚያስገርማችሁ ወይም የሚያቅበጠብጣችሁ ምክንያት አልታየኝም። የትም ይሁን መቸ ተነሡ ሲባል መነሣት ብቻ ነው። በተለይ አንቺ ደግሞ » ታፈሱን በማሽሟጠጥ ተመልክቷት «ካለኔ ነውጠኛ የለም ባይ ነበርሽ። አሁን ግን ምን እንደ ነካሽ አላውቅም። ምነው ስሜትሽ እንደ ሳንባ ለሰለሰብኝ? »

«የመነካት የመለሳለስ ጉዳይ አይደለም። ጠይቆ ለመረዳት ነው። ቆራጡና ፈሪው በኋላ ይለያል። » ታፈሱ ያንን ልም ዐይኗን አጮልኃ ከፈርዋን ጠርዝ እስከ ጆሮ ግንዷ በማድረስ የፌዝ ጥርስ አሳየችው።

«አሃሃሃ! ልክ ነሽ! » ትንሽ በሚንቀጠቀጥ እጁ አዲስ ሲጋራ እያቀጣጠለ፥ ያደሙበት ይመስል ሁሉንም፣ በብልጥጥ ዐይኑ ቃኛቸው። «አስረዳሻለሁ፥ አስረዳችኋለሁ። ከመሠረቱ ከበላይ አካል የመጣ ግዳጅ ያለ ጥያቄ፥ ያለ ምንም ምርጫ መፈጸም ነበረበት። ቅድም እንዳልኩት ለድርጅታችን ግዳጅና ትእዛዝ ሕይወታችንን የሰጠነው ዐውቀን ፈቅደን በልዩ ልዩ ክንፎች አባል ስንሆን ነው። አሃሃሃ! አይደለም እንዴ? »

ሌሎቹ በመሰላቸው ከማዳመጥ በተቀር አሁንም መልስ የሰጠው የለም።

«በእኔ አስተያየት ግን፥ አሁን የመጣውን መመሪያ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እናሟላዋለን ባይ ነኝ! አሃሃ! »

‹ማይ ፉት ዲሞክራሲያዊ› አለ ማስረሻ በሆዱ፥ ከብሽቀት የተነሣ አስተሳሰቡን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ወስዶበት፥ ‹እንዲህ አርጎም ዲሞክራሲ የለ! በዲሞክራሲያዊ መንገድ ፈቃዴ ምርጫዬ ተጠይቆ ነው ከዚህ ጣጣ የገባሁት?› በቃል ግን ትንፋሽ አልወጣውም። ደረበን ቀና ብሎም አላየውም።

ክፍሉ አሁን በሲጋራ ጢስ እየታፈነ መሄድ ጀምሮ ነበር የደረበ ዐይን በዚያው መጠን ቅላቱ እየደመቀ ሄዷል። ሌሊት ሌሊት በየኤሌክትሪክና በየቴሌፎን ሽቦ ላይ ተንጠልጥለው የሚገኙትን ቀይ ጨርቆች እስኪመስል ድረስ። «በመሠረቱ እኔ ለእስኳድ የመረጥኩትን ሰው ለበላይ አካል ማስተላለፍ እችል ነበር። »

ሦስቱም ትንፋሻቸው በአፍንጫቸው ፉጨት መስሎ ሲወጣ ተሰማ።

«አዎ! ከዚህ ሕዋስ ለእስኳድም ሆነ ለምልምል የሆነውን መርጬ ለበላይ የማስተላለፍ ሙሉ ሥልጣን አለኝ። » ደረበ ድምፁን ልክ መድረክ ላይ ያለ አስመሰለው። «ግን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ነው የምንወስነው። »

«በምን ዓይነት ዲሞክራሲያዊ? » ማስረሻ አንገቱን እንዳቀረቀረ ሳይታወቀው ጥያቄው ከአፉ ወጣበት።

«አሃሃሃ! አይዞህ አትፍራ! እኩል ዲሞክራሲያዊ ዕድል ነው የሚደርስህ! በመካከላችን ዕጣ እናወጣለን። »

«አንተም ዕጣ ትገባለህ? » ታፈሱ በፌዝ አኳኋን ጠየቀች።

«ብገባ ደስ ይለኝ ነበር። »

«እና? »

«በዚህ ሕዋስ ውስጥ የእኔን እስኳድ መግባት የሚወስነው የበላይ አካል ነው። ግባ አልተባልኩም። »

«እና፥ የተፈረደብን እኛ ብቻ ነን! » አሁንም የሰላ ፌዝ የሰነዘረችው ታፈሱ ነበረች።

«ትግላችን ፍርጃ አይደለም! ለድል ነው! ምን ነክቶሻል አንቺ! ለንትርክ ጊዜ የለንም። ዕጣውን በወረቀት ጽፈን እናወጣለን። ከፈለጋችሁ የኔም ስም ይጻፍ። በኋላ የበላይ አካል መስማማት አለበት እንጂ። »

«ኧረ ምን ያስፈልጋል? እኛው እንበቃለን። »

ደረበ የፌዙን አነጋገር ያልሰማ በመምሰል ወረቀት እየበጣጠሰ ይጠቀልል ገባ። ሁሉም፥ ትንፋሻቸው ከከንፈራቸው ላይ ተንጠልጥሎ የቆመ መስለው ጠበቁ።

አንድ ሰው ሎተሪ ይገዛል። ጥቂት ብሮች ይከስራል። ወይም ከስንት ሺህ ሕዝብ መካከል፥ ከሆነ ጐጆ የሚያስቀልስ ካለበለዚያ ለተወሰነ ጊዜ ከሞዴል ስድት ነጻ የሚያወጣ ዕድል ይደርሰዋል። እንደ ዋዛ የሚጠቀለሉት እነዚያ ወረቀቶች ግን የሰውን ሕይወት የሚወስኑ ነበሩ። ደረበ ብጥስጣሽ ወረቀቶቹን ሲያድበለብል እየተመለከቱ እንደ ድቅድቅ ጨለማ ሁሉንም የዋጣቸው ስሜት፥ ፍርሃት አይሉት ጭንቀት ልዩ ነበር። እስኳድ መሆን ምን እንደሚያስከትል ማስረሻ፥ ከጥያቄዎቹና ከመልሶቹ በመጠኑ ገብቶታል። ወታደር ቀመስ ሥራ። የጦር መሣሪያ መግደል፣ መግደል። ማርካቶ ቅቤ ተራ አጠገብ በተደፋው ወጣት ቦታ ራሱን አየው። ‹አዎ! የደርጉ ወገንም እጁ በሱ አልጨበጠም። ይመታል፥ ይደፋል።› ግን መሞቱን እስከዚህም አልፈራውም። በዙ ጊዜ ስለ አሟሟት በሐሳቡ እንደ ተመራው በሚያሠቃይ በሽታ እየማቀቁ ከማለቅ ይኸኛው የተሻለ ነው። በሽጉጥ በቆሰለ ጊዜ እንደ ተሰማው ጥይቱ አካሉን በስቶ ሲገባ ለቅጽበት ይነዝራል። ከዚያም ቀስ በቀስ እድነ ሰመመን ይወስዳል። ፍጻሜው ከሆነ አበቃ። ሥቃይ የለም። ፀፀት የለም። በአንጻሩ ደግሞ ራሱን በገዳይ ቦታ ሆኖ አየው። እንዲገደል በተጠቆመው ላይ ሽጉጡን ሲያነጣጥር። ከዚያም መጥፎ ይሁን ጥሩ ቅን ይሁን እኩይ የማያውቀውን ሕይወት ለመቅጨት ቃታውን የሚስብበት ጊዜ እንደ ብዙ ዓመት ረዝሞ ተሰማው። ‹አዎ! የሰው ሕይወት እንደ ሻማ እፍ አይባልም። የሰው ሕይወት ክቡር ነው። ከአመለጠ አይገኝም። ያንን ሕይወት ከአጠፉ በኋላም እንደ ማርካቶው ይፋጠጡታል። ይፋረዱታል። አዎ!› አለ ማስረሻ በሐሳቡ ‹መሞት ቅጽበት ነው። መግደል ግን ሺህ ዓመት ነው።›

ታፈሱ የሐሳቡን ሰቀቀን ያነበበች ይመስል የዕጣውን ወረቀት ትታ ብላ ተመለከተችው። እሱ ግን ከውስጥ ሐሳቡ በስተቀር የውጭው ምኑም አይታየውም ነበር።

«አሃሃሃ! እሺ ይኸው » አለ ደረበ ብጥስጣሽ ወረቀቶን እንደ አተር አድበልብሎ ከአበቃ በኋላ እጁን ወደ ታፈሱ በመዘርጋት።

«ምንድን ነው? » ስትል ጠየቀች።

«ዕጣውን የምታጭው አንቺ ነሽ! አሃሃሃ! »

«ለምን? »

«ሴት ስለ ሆንሽ። »

«ሥነ ሥርዓት! የወንድ ትምክህተኝነትህን የድርጅት ዲስፕሊን አይቀበለውም። »

«አሃሃ! እታረማለሁ! » ጣቱን አፋጨ። «ግን ዕጣውን አንቺ እንድታወጪ የተፈለገው ስለሌለሽበት ነው። እኔ ግን የበላይ አካላ የሚፈቅድ ከሆነ፥ ለሁላችንም ሞራል ለመስጠት ያህል ራሴን አስገብቻለሁ። »

«እኔ ለምን የለሁበትም? » ታፈሱ ያንን ከንፈርዋን ለጥጣ ተኮሳተረች።

«ትክክለኛ ጥያቄ ነው። ስለ ሴቶች እስኳድ መመልመል ከበላይ የመጣው መመሪያ ግልጽ አይደለም። እንደማውቀው ከሆነ ከአሁኑ በፊት አልገቡም። ስለዚህ በእኔ ውሳኔ ለጊዜው አውጥቼሻለሁ። ሲያስፈልግና መመሪያ ሲመጣ አንቺም ትገቢያለሽ። አዝኘልሽ አይምሰልሽ። »

«ዐውቃለሁ። »

«መጀመሪያ ዕጣ - ዕጣ ለባለ ዕጣ በይ! አሃሃ! ዕጣ - ዕጣ - ለባለ ዕጣ። »

ታፈሱ ወረቀቶቹን ከእጇ መንጨቅ አደረገችና በመዳፍዋ ውስጥ አንቀረቀበቻቸው። የሁሉም ዐይን በተከደነው መዳፍዋ ላይ አነጣጠረ። ዘረጋችው። እንደ ዳቦ ቆሎ በተድበለበሉ አራት ወረቀቶች ላይ ስምንት ዐይኖች ተተከሉ። ደረበ ጣቱን አፋጨ «አሃሃ! ዕጣውን እኔ ላውጣው ወይስ መሳብ የሚፈልግ አለ! » መልስ የሰጠው የለም። «እንግዲያው እንደ ፈረደብኝ እኔ ነኝ ማለት ነው። » አንዷን ድብልብል ብጣሽ ወረቀት አነሣና ቀስ ብሎ ሲዘረጋጋ የሁሉም ዐይን የጣቱን እንቅስቃሴ ተከተለ። ደረበ ትልቅ ስጦታ እንደሚያበረክት ወረቀቷን ከጠረጴዛው ላይ አስቀመጣትና በአድናቆት ተመለከታት «አሃሃ! የመጀመሪያው ዕጣ ለማስረሻ ሙሔ፥ እንኳን ደስ አለህ ለእስኳድ በመብቃትህ! አሃሃ! » ደረበ የዘጋለትን እጅ ማስረሻ አላየም። ሌላ ዓለም ውስጥ ነበር።

«አሁን የሚወጣው ዕጣ ደግሞ የተጠባባቂው ምልምል ይሆናል። » አሁንም አንድ ጥቅል አነሣና በእርጋታ ዘረጋጋው። «ይሄ ዕጣ ደግሞ ለአስጨናቂ ደርሷል። መልካም ዕድል ከዚህ በኋላ የቀረውን ማውጣት አያስፈልገንም። ሁለት ሰው ነው የሚመረጥ የነበረው። ዕድለኞች አግኝተዋል » ሲል ከታፈሱ መዳፍ የቀሩትን ጥቅል ብጣሾች ወሰደና ብጥቅጥቅ አድርጎ ጣላቸው።

ለአምስ ደቂቃ ያህል ማንም አልተናገረም። ከየሰው አፍንጫ የሲጋራ ጢስ ብቻ እየተንጐለጐለ ወጣ።

«በቃ፤ ይኸው አይደለም? » ሲል አስጨናቂ ከወንበሩ ተነሣ።

«ከእኔ በኩልም ሆነ ከሌላ አካል የሁለታችሁ መመሪያ በቅርቡ ይደርሳችኋል። ለዛሬ ይኸው ነው » አለ ደረበ የክፍሉ ውጥረት እሱንም በመጠኑ እየተሰማው።

ከቀብር መልስ እንደሚሰናበት ልቅሶ ደራሽ ደረበን በጐሪጥ በመመልከት ሁሉም ተራ በተራ ተከታትለው ወጡ። ወንበሩ በአጣብቂኝ የያዘው ይመስል ደረበን የጐሪጥ አይቶ በመጨረሻ የወጣው ማስረሻ ነበር።

# ፳

ታፈሱ ሰይቸንቶ፥ የምትጠብቅ መስላ ከአምባሳደር ቲአትር መግቢያ አጠገብ ቆየችው። «ከእንግዲህ ሰይቸንቶ በቀላሉ የምታገኝም አይመስለኝም። ይልቅስ በእግርሽ ብታዘግሚ ይሻላል » አላት ማስረሻ።

«የኔም ሐሳብ እሱው ነው። የምትሸኘኝ ከሆነ አለችው። »

«ደስ እያለኝ። »

«የማይመሽብህ ከሆነ። »

«እስኳድ ተሁኖ ጨለማ ፈርቶ እንግዲህ መች ይሆናል። » ማስረሻ ነገሩን ያቃለለው ለመምሰል ያጋደለ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ። በፌዝ አኳኋን ከት ብላ ሣቀች - ታፈሱ።

«ምነው? » ሲል ጠየቃት።

«እንዲያው ነገሩ ሁሉ እያስገረመኝ። »

«ለእኔስ ከመገረም በላይ ሆኖብኛል። »

የፖሊስ ጋራዥን እንዳለፉ ታፈሱ ወደ ቀኝ እየታጠፈች እግዜር ይስጥልኝ። ከዚህ ነው ሠፈሬ » አለችው። ለመሰናበት እጁን ሲሰረጋለት ለጠቅ አደረገችና «ለምን እራት አትበላም? ቤት ያፈራውን » ስትል ጠየቀችው።

«ይመሽብኛል። »

«እስኳድ ሆኖ ሌሊትም ግዳጅ መወጣት አለ። ከአሁኑ ተለማመደው እንጂ። » አሁንም በፌዝ እንደ መሣቅ ቃጣት።

«ምንድን ነው ይህንን ያህል! አንድ ሕይወት ብቻ ነው ያለኝ። » ማስረሻ በውስጡ እንደ ቋጥኝ የከበደውን ስሜት በአነጋገሩ አቃልሎ ለማቅረብ መሞከሩ ነበር።

«አንድ ሕይወት ብቻ መሆኑ ነው ከፋቱ። ትርፍማ ቢኖር ማን ቸግሮት። »

«ትርፍ አልፈግም። » ማስረሻ ያጋደለ ትከሻውን ነቅነቅ አድርጎ ከጐንዋ መራመዱን ቀጠለ።

ታፈሱ፥ በዕቃ በተጣበበች የጭቃ ቤት ውስጥ ከእናቷ ጋር ነው የምትኖረው። እናትዋ ከሰላምታ በስተቀር ነገር ሳያበዙ ራት አቅርበውላቸው ወደ ጓዳቸው ገቡ። ብቻቸውን እንደ ቀሩ፥ ሁለቱም በየሐሳባቸው የተጠመዱ ይመስል ዝም ብለው እንጀራውን መቀነጣጠብ ቀጠሉ። ግን ማስረሻ እንጀራውን ቆርሶ በላ ቁጥር ትርኩ ብላ ስታስተውለው ብዙ ጊዜ ዐይን ለዐይን ተጋጩ። ከእርሱ የምትፈልገው ነገር አለ ይሆን? በሴቶች አጥማችነት ስለሚሠራ ልዩ ልዩ ነገር ብዙ የስለላ ልብ - ወለድ መጻሕፍት አንብቧል። እሱን መቀራረብና መከታተል ከድርጅት ተግባርዋ አንዱ ይሆን? ግን ምኗም ምኗም የዚህ ሰው ስለማትመስል ማመን አስቸገረው። ከስለላ ልብ - ወለድ መጻሕፍት እንዳነበበው ለዚህ ዐይነት ተግባር የሚመረጡት ሴቶች ሌላው ቢቀር መልከ መልካሞች ናቸው። በቀላሉ ለማጥመድ እንዲመቻቸው። ነገሩ አላስችለው አለና በመጨረሻ ጠየቃት። «የተዋወቅነው በቅርቡ ነው። እንዲያውም እስከዚህም አንተዋወቅም ማለት ይቻላል። ግን ተሳስቸም እንደ ሆነ እንጃ ከሌሎቹ ይልቅ በእኔ ላይ የተለየ አስተያየት ያሳደርሽ ይመስለኛል። ለምን? »

«በአጭሩ ለመመለስ ስለምታሳዝነኝ! » የማስረሻ ጥያቄ ያሳፈራት አልመሰለኝም።

«አማኑኤል ደርሶ መልስ በመሆኔ? »

«አይደለም። በርግጥ ስለ እርሱም ሰምቻለሁ። »

«ታዲያ ምኔ ነው የሚያሳዝንሽ? ከዚህ ከማላውቀው ጣጣችሁ ውስጥ ከመግባቴ በስተቀር። » ‹የድርጅት ተግባርዋን እየሠራችም ከሆነ ስሜቴን ትንገራቸው› አለ በሆዱ።

«እውነቱን ለመናገር እኔም በትትክል አላውቀውም። እንዴት ብዬ ላስረዳህ። ብቻ አስተያየትህ፥ ሁናቴህ ሁሉ ይህ ነው ተብሎ የማይነገር ሥቃይና ጭንቀት ያሳለፈ፥ ይህ ነው ተብሎ የማይገለጽ ግፍና መከራ የተፈጸመበት ሕይወት ይነበብበታል። ምን ልበልህ፥ በገሃነም በኩል አልፈህ አሁንም በትዝታው የምትሸማቀቅ ትመስላለህ። »

«ልክ አንብበሻል። » አለ ማስረሻ በሰፊው ተንፍሶ።

«ግን ለምን እንዲህ ትሆናለህ? አንድ ሰው በትናንት ሠቀቀን ብቻ ከታሠረኮ ዛሬና ነገን መኖር አይችልም። »

«ለኔ ዛሬ የለም። ነገንም አላውቅም። ትናንትን ነው የምኖረው። »

«ስሕተት ነው። ሕይወት ጽልመት ፊቷን ያሳየችው ለአንተ ብቻ አይደለም። በእልፍ እምአእላፍ የሚቆጠር ሰው ሁሉ የሚደርስበት ነው። » የታፈሱ አነጋገር የማጽናናትም የመገሠጽም ዓይነት ነው።

«ስለሌለው አላውቅም። እኔ የመጣሁበትን የሕይወት ድቅድቅ ጽልመት የማውቀው እኔው ብቻ ነኝ። »

«እውነትም በጣም አስመርሮሃል። ምን ነገር ቢደርስብህ ነው? » ወዲያው ለጠቅ አድርጋ ድንገት ሳታውቀው «እስቲ በፈጠረህ አውራልኝ። ምን አገባሽ ባትለኝ » ስትል ጠየቀችው።

«ምን ዋጋ አለው ሰቆቃውን ቢተርኩ። »

«ለሰው ሲያዋዩት ይቀላል ይባላል። »

«የእኔው የሚቀልል ዓይነት አይደለም። » አለና እነዚያ ልም ዐይኖቿ መላ ሰውነቱን ሲዳብሱት በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከፈተ ንጹሕ ልብ ያገኘ መሰለው። እሱም ድንገት ሳይታወቀው «የእኔው ጉድ ተተርኮም የሚያልቅ አይደለም » ሲል ጀመረ። ከዚያም የሠቀቀን ሳግ የሚተናነቀው ይመስል ለስለስ ያለው ድምፁ እየተሰባበረ አፈር ሲፈጭ ውሀ ሲራጭ ከነበረበት ከልጅነት ጊዜው አንሥቶ የሕይወት ውጣ ውረዱን የደስታና የኃዘን የጭንቀትና የተስፋ የፍቀና የጥላቻ ፍርቅርቆሹን ይተርክላት ገባ። እሱ በትረካው ተጠምዶ እርሷ

በማዳመጥ ተመስጣ ስለ ነበር፥ እናትየዋ ቀስ ብለው ገብተው ገበታውን ሲያነሡ አልታወቃቸውም ነበር።

«አሁን ምን ይሰማሃል? » ብላ ታፈሱ ጠየቀችው፥ ዘለቃ ስለ ሠራችው ነግሮዋት ሲጨርስ።

«ስለ ምኑ? »

«ስለ ሚስትህ ማለቴ ስለ እርሷ ፍቅር ቅናት ጥላታች ወይም - » አንጠልጥላ ተወችው።

«ፖህ! ሚስት! ሚስትነቱን እንተወውና እወነቱን ለመናገር ምን እንደሚሰማኝ አላውቅም። »

«አሁን ድንገት ብታገኛት ምን ታደርጋለህ? »

«አላውቅም። ይህ ሁሉ የሚያሳየው የእኔን ደካማ ተፈጥሮ ይመስለኛል። በአጠቃላይ። »

«አይመስለኝም » አለች ታፈሱ በማፅናናት አኳኋን። «የአንተ ችግር ሕሊናህ በጣም ለስላሣ መሆኑ ይሰማኛል። ስለዚህም እንዳይቧጨርብህ አትጋጭም። አትፋጠጥም። ራስክን ትቀብራለህ ወይም ትሸፈናለህ »

«የአማኑኤል ሆስፒታል ዶክተሩም ያለኝ እንዳቺው ዓይነት ነው። በሽታህ፥ ራስዋን አሸዋ ውስጥ እንደ ቀበረችው ሰጐን ሁሉም ነገር እንዳልሆነ ከራስህ ለማምለጥ መሞከርህ ነው ያለኝ። እሺ እኔንስ እስኪበቃሽ አስለፈለፍሽኝ በተራዬ አንቺን መጠየቅ ይፈቀድልኛል።

እኔ ምን ቸገረኝ በሚል አኳኋን ያንን ትከሻዋን ነቅነቅ አደረገችለት። ልም ዐይኗ ደግሞ እንዲጠይቅ ጋበዘው።

«ለመሆኑ በነገሩ ታምኝበታለሽ? »

«ምኑን? ፖለቲካውን ማለትህ ነው? የእምነት ጉዳይኮ ሰፊና ውስብስብ ነው። ያለ ምክንያት በስሜት ብቻ ማመን አለ። ሰበብ ፈልገህም ታምናለህ። ለማማረጫ ብለህ የምታምንበት ነገርም አለ። ስለዚህ » ንግግርዋን አንጠልጥላ ተወችው።

«ስለዚህ ፍልስፍናውን ወደ ጐን አቆይውና » አለ ማስረሻ «ለመሆኑ ከዚህ ውስጥ ምን አስገባሽ። እኔስ መንገድ ላይ ተጠልፌ ነው ልበል። ከዚያም በኋላ ድፍረቱ እያጠረኝ። »

«እንደ ሌላው ሁሉ ነዋ! »

«መልስ አይደለም። ሌላው ሁሉ የተለያየ ምክንያት ሊኖረው ይችላል። »

«እሱማ እኔም አለኝ። »

«ታዲያስ! »

»ተስፋም ጥላቻም ነው በለው። አየህ እኔም እንዳንተው ብዙ ችግርና ፈተና የደአሰብኝ፥ ጭቁን ዘረ - ጭቁን ነኝ። አባቴ በጣሊያን ወራራ ጊዜ አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በጫካ ከተንከራተተ በኋላ አብሮአቸው የተዋጋው አጣምረው ራስና ጄኔራል ሲባሉ የእርሳቸው የግል ዘበኛ የመሆን ዕድል ብቻ ገጥሞት ሲያበሳጩትና ሲያሰናዱት ብስጭቱና ንዴቱን የተወጣው እየመሰለው ከካቲና ከቢጫ ጋር ሲጋተር በመጨረሻ ጉበቱን ተፍቶ የተሰናበተው ገና ሕፃን ሳለሁ ነው። እናቴ በዕድሜ ከእርሱ በጣም አነሰ ያለች ስለ ነበረች በመጀመሪያ ግርድና ገብታ እኔን ለማሳደግ ሞከረች። ግን ስላልቻለችው እንደ ሌላው ሁሉ አንዷት ቤት ተከራይታ ጥቂት ጠርሙሶች ደርድራ መተዳደር ጀመረች። ለእኔው ስትል ነው። በሰው ቤት ስለ ተንገላታሁባት። ከዚያም ትምህርት ቤት አስገባችኝ። በተቻለ መተንም ከወራዳ ኑሮዋ እኔን ለመከለል ትጥር ነበር። ግን የማላውቀው ሰው ሁልጊዜ ሰለሚመጣ መገንዘቤ አልቀረም። አንድ ሰው ብቻ እያዘወተረ ይመጣ ነበር። በመጣ ቁጥር ጭቅጭቅ ንትርክ ነው። እማየ ማልቀስ ስትጀምር እኔ ወደ ውጭ እወጣለሁ። በኋላ እንደ ነገረችኝ ማን ወንድ በቤት ዘር ብሎ ባይ ነው። ስለሚያፈራርቅ ቀንቶ እንዳይባል አምስት ሳንቲም ረድቷት አያውቅም። ታዲያ አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ውዬ ስመለስ ይኸው ሰውየ እማዬን ወለል ላይ ጥሎ በአፏና በፍንጫዋ ደም እስኪፈስ ድረስ ባልተወለደ አንጀቱ ሲረግጣት ደረስኩ «ውይ! » ብዬ ከላይዋ ላይ ስደፋ እኔንም ረጋገጠኝና ለጆሮ የሚቀፍ ባለጌ ስድቡን እያነበነበ እኔንም ረጋገጠኝ እማዬ ደሙና ሳትጠርግ እኔን እቅፍ አድርጋ የኔው አንሶ ለአንቺም ተረፍኩሽ ስትል ምርር ብላ አለቀሰች። እኔም ደግሞ ነገሩ እንዴት እንደ መጣልኝ አላውቅም በዚህ ዓይነት ኑሮሽ የምትኖሪ ከሆነ በርሬ እጠፋለሁ ወይም ራሴን እገላለሁ ብዬ ስቅስቅ አልኩባት። ‹እሺ እሺ! የኔ አንጀት እተወዋለሁ እርግፍ አድርጌ!› እያለች እንደ ሕፃን በእሹሩሩ አቆላመጠችኝ። ገና አምስተኛ ነው ስድስተኛ ክፍል ነው

የነበርኩትና እንጀራ ቆሎ፥ ሸንኩርት ሽሮ ዘርግታ የጉልቱን ሥራ ተያያዘችው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው ለሱና ለመሰሎቹ ጥላቻ ያደረብኝ። »

«ለምሆኑ ደረጃው ምን ነበር? » ሲል ማስረሻ ጠየቃት።

«ከደረጃው ምን አለኝ! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሚታየኝ እማዬ ከወለል ላይ ተዘርራ የሚረግጣት ጫማና ከእሱ በላይ የደንብ ልብሱ ነው። እውነቱን ለመናገር አሁን መልኩም ትዝ አይለኝም። »

«ግን ልክ አይደለሽም! ጭካኔኮ የግለሰብ ጠባይ እንጂ የሙያ ጉዳይ አይደለም። ሲቪልም ሊሆን ይችል ነበር። ደግሞ ብዙው ለእናት አገር ዳር ድንበር እንዲዋደቅ አትሪ። ስለዚህ በአንዱ ምክንያት በሌላው ላይ ሁሉ መፍረድ አትችይም። »

«ዐውቃለሁ » ልም ዐይንዋን ከደን አድርጋ የምታሰላስል መሰለች። «ግን እንዳልኩህ አንተም ተቆራኝቶህ የመጣ ስሜት አለ። እኔም እንደዚሁ። በዚህ ላይ ደግሞ ፖለቲካው አያገባቸውም የሚለው አለ። »

«የጥላቻሽ ጉዳይ ገባኝ። ተስፋ ያልሽውስ ምኑን ነው? » ማስረሻ አሁን የስሜት ውጥረት እየጠፋ እየተዝናና ሂዶ ነበር።

«ተስፋ? አንተም ዝምተኛ ትመስላለህ እንጂ ተከራካሪ ነህ። በደረቁ ተዳረቅን፤ የሚጠጣ ነገር ላምጣ? ትንሽ? » ስትል እንደ መነሳት ቃጣች።

«በፍጹም! » አለ ጠንከር አድርጐ «እኔ እንደ ገና ሆስፒታል መግባት አልፈልግም። አንቺ ግን መጠጣት ትችያለች። »

«እንግዲያው ድካምህን ተወጥተኸዋል። እኔኮ እስከዚህም ድረስ አልኮል አይስማማኝም። እና፥ የት ነበር ነገሬን የተውኩት? » የጠየቅሁሽ።

«አዎ! ከዚያ አብዮት ፈነዳ። አገር ተደበላለቀ። የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ ሲባል ለመሥሪያ ቤቴ ተመረጥኩ። እንግዲህ ፍጥሕ፥ እኩልነት ነጻነት መምጣት አለበት ነው የተባለው። በተለይ ሴቶችን በሚመለከት ደግሞ፥ እኔ በእናቴ የደረሰው በእናቶች ሁሉ፣ በማንም ሴት ሁሉ ወደ ፊት እንዳይቀጥል የራሴን የትግል ድርሻ ለማበርከት በመሥሪያ ቤቱ የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ሆኜ ተመረጥኩ። ከዚያም ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮቱን በአቋራጭ ተነጠቀ። ፋሽዝም ነገሠ ሲባል በነገሩ ተስቦና ተመልምሎ መግባቱ በጣም ቀላል መሰለኝ። »

«አሁንስ? »

«እርግጥ የሚያስደስቱኝ አንዳንድ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ግን ውጤቱ ስላልታየ አሁን ለመገመት አይቻልም » አለች ታፈሱ።

ማስረሻ ራሱን ነቀነቀ፤ «እኔ ግን እውነቱን ልንገርሽ ጠቅላላው ነገር ደስ አይለኝም። እኔ ፋሺዝም ሲያቆጠቁጥ የሚታየኝ ከዚሁ ከእኛው ዘንድ ነው። የተለየ ሐሳብ ማቅረብ የለ፤ መከራከር የለ፤ እንደ ጋሪ ፈረስ ከአንድ አግጣጫ የሚመጣ መመሪያ ይዞ መንጐድ ብቻ። ይኸኛው ወገን ሲመታ ሲገደል ያኛውም ወገን መልሶ እንደዚሁ ሲያደርግ ስንተላለቅ በእኩልነትና በነጻነት ፈንታ ጥላቻ ሥጋት፥ ፍርሃት፥ ጭንቀት ሲነግሥ ነው የሚታየኝ። ሌላው ቀርቶ ሁለት ሦስት እየሆኑ አላፊ አግዳሚው እየገረመሙ እየገላመጡ፣ ዓለምን የገዙ መስለው በአደባባዩ የሚጐላመሙት ጐፈሬዎች ያስፈሩኛል። ማለቴ ፋሽዝም አንድ የተወሰነ የልብስ ዓይነት የለውም። ማንኛውም ዓይነት ልብስ አጥልቆ ሊመጣ ይችላል። »

«እሱስ እውነትህን ነው። ግን ሁሉም በእነ ደረበ ዓይነት አትገምተው። ከመንገድ ላይ ሲጐማለሉ የምታያቸው ኮስታራ ጐፈሬዎች አብዛኞቹ ቅን ሐሳብ ያላቸው ናቸው። ለሀገሪቱ የሚበጅ እውነተኛ ለውጥ የሚያመጡ መስሎ ይሰማቸዋል። »

«ግንኮ ቅን ሐሳብ በተሳሳተ ጐዳና ወደ ጥፋት እንጂ ወደ ታሰበው ግብ ሊያደርስ አይችልም። ስለ አለፉት ዓመታት የፖለቲካ ሂደት ብዙም አልተከታተልኩም። መሠረታዊ ልዩነትም ምን እንደ ሆነ በትክክል ሊገባኝ አልቻለም። እኛ አብዮት አብዮት እንላለን። እነርሱም እንደዚሁ ነው የሚሉት። የእኛና የእነርሱ ሶሻሊዝም በምን እንደሚለይም አላውቅም። ሌላው ቀርቶ በታክቲክ በኩል ስንኳ ሳየው ከእኛ በኩል ስሕተቱ ግልጽ ነው። ሰፊው ሕዝብ እንላለን። ሰፊው ሕዝብ ደግሞ በአብዛኛው ገበሬ ነው። አብዛኛው ገበሬ ደግሞ ጭሰኛ የነበረ ነው። ታዲያ፥ ጭሰኝነት ያስቀረ ዐዋጅ ከአወጣለት ደርግ ጋር ቢወዳጅ እንጂ የሚጣላበት ምክንያት አይታየኝም። ተጣላ በለን ልናስገድደው ነው? እምቢ ቢልስ ልንነሣበት ነው? ሁለቱንስ ልናሸንፍ እንችለለን? ብንችልስ እምቢ ብሎ ስላስቸገረን ረግጠን መግዛት ካለብን ምን ሊባል ነው? ያው ፋሺዝም አይደለም? እኔ እንጃ። » ማስረሻ በሰፊው ተነፈሰ ከሆዱ ውስጥ አንድ ነገር ወደ ላይ የገፋው ይመስል። እንደ ዋዛ ሰዓቱን ተመለከተና እንደ መገረም አለ። «ሳይታወቀን ጊዜው ሂዶ የለም እንዴ! »

ሊነሣ ሲቃጣ ታፈሱም ሰዓቷን ተመለከተችና «ሰዓት እላፊው ተቃርቧል። ለምን ከዚሁ አታድርም? » አለችው።

«ምን? » ሲል በመገረም ጠየቃት።

«አ! አ! አ! መጥፎ ነገር በሐሳብህ እንዳይመጣ! » አለችው በቀልድ ቁጣ። «እኔ ከእማዬ ጋር እተኛለሁ። አንተ ከኔ መኝታ ክፍል መተኛት ትችላላችሁ። አይ፥ ተረኑን አልፈልግም አክልክ ደግሞ፣ ከዚሁ ከፎቴው ላይ ብርድ ልብስ ቢጤ እዘረጋለሁ። ለአንድ ቀን ይበቃሃል። »

አዲስ ታጥቦ የተተኰሰ አንሶላና ብርድ ልብስ ከትልቁ ፎቴ ላይ አነጣጥፋለት ወደ ራስዋ መኝታ ክፍል ከማምራቷ በፊት «የዛሬውን የመናፍቅ ጭውውታችንን ግን የሰይጣን ጆሮ አይስማው። በተረፈ መልካም እንቅልፍ » ብላ ተሰናበተችው።

ጭውውታቸውን የሰማ ጆሮ ባይኖር በሩቁ የተጠባበቃቸው ግን ነበር።

ደረበ፥ በመኪናው ሲያልፍ ሁለት ወደ ታፈሱ ቤት መግቢያ ሲታጠፉ በጨረፍታ እንደ ተመለከታቸው ነገሩ ከነከነውና የጥያቄ ምልክት የምትመስለውን ዳገት እንደ ወጣ እንደ ገና አዞሮ ተመለሰና ትንሽ ራቅ አድርጐ በማቆም ይጠብቅ ገባ። ሲጋራውን በላይ በላዩ እያቀጣጠለ መኪናው በጢስ ሲታፈን መስታወቱን እየከፈተ ደግሞ ደጋግሞ ለራሱ የሚያቀርበው ጥያቄ «ምን ጊዜ እንዲህ ተሻረኩ? » የሚል ነበር። በዚህ አድራጎታቸው የድርጅት ዲስፒሊን አልጣሱም። ግን ምክንያት ነበረው።

ለሰዓት እላፊ እሩብ ጉዳይ ሲሆን ሄደ።

በዚህ ጊዜ ማስረሻ ለመጀመሪያ ጊዜ ጸጥ ወደ አለ የእንቅልፍ ዓለም ውስጥ በመግባት ላይ ነበር......

# ምዕራፍ አራት

በታኅሣሥ ወር መጨረሻ ገደማ ላይ በቆሬና በሌሎችም አካባቢ የገጠር ቀበሌዎች የክረምቱ አየር ቦታውን ለበጋው አየር ለቋል። ዳመና የለም። እርጥበት የለም። ሰማዩ የጠራ ነው። ሰማያዊ። ትንሽ ሲለወጥ የግራጫ ድብዝዝ

የተበተነበት የጠራ ሰማይ። አዝመራ በሙሉ ከማሳ ተከናውኗል። በአብዛኛው ተወቅቶ ተሰብስቧል። አልፎ አልፎ ብቻ ከድርቆሽ ክምር ጋር የሚያሳስቱ አንዳንድ የእህል ክምሮች ቀርተዋል፤ የሰነፍ ገበሬ። ቢወቃ ቶሎ የሚያልቅበት የሚመስለው ስለታም ገበሬ። በልዩ ልዩ ምክንያት መውቃት ያልቻለ ገበሬም ትንንሽ ቁልል ቀርቶታል።

ነፋሻው ቀላል አየር የሚያስራጨው የቃርሚያ የአውድማ የደረቅ ሣር የገለባ ጠረን ነው። የክረምትና ፀደይ ወዝ ፍሬ ጠረን። ከላይ አእዋፍ በጠራው ሰማይ ላይ እንደልባቸው ይንሳፈፋሉ። ምግብ ፍለጋ። አንዳንዶቹ ወደ ታች እየተወረወሩ ባልተወቃ ክምርና ገለባው ብቻ ዙሪያውን ተበታትኖ በቀረ አውድማ ላይ ያርፋሉ። እህል ለመለቃቀም። ግን እንደ እሸቱ ጊዜ በብዛት ያገኙም። ስለዚህም በአየር ላይ ብዙ ይበራሉ። ይዘዋወራሉ። በመሬት ላይ የተቸገረው ሰው እንደሚንከራተት የራሳቸውንም ፈልግ ያደርሳሉ። የታኅሣሥ ወር እንደ ሌሎቹ ገጠሮች ሁሉ በቆሬም ሰማይ አእዋፍ በብዛት ሲዘዋወሩ የሚታይበት ጊዜ ነው። በእንቅስቃሴያቸውም ሰማዩን ያደምቁታል። ያስውቡታል።

በአንጻሩ ደግሞ፥ ምድሩ ጸጥታና እርጋታ የሰፈነበት ይሆናል። በተለይም ቀኑ ከገፋ በኋላ ከብቶች የማሳውን ከየውድማው የተራረፈ ገለባውን ገና ጨርሶ ያልደረቀ ሣርና አገዳው ሲለቃቅሙ ውለው ገና ከአደልረቀው ምንጭና ወራጅ ውሀ ተጐንጭተው በየዛፉ በየጥላው ሥር ያርፋሉ። ግማሹ ቁም ግማሹ ተጋድሞ እንደ ማንጐላጀት ይቃጣዋል። አንዳንዱ ገና ከአሁኑ ያመንዥካል።

የሰውም እንቅስቃሴ እንደዚሁ በጣም የረጋ ነው። በየማሳው በየመስኩ የአዝመራ ሥራ በአብዛኛው ተጠናቅቋል። የመስኩ ሥራ ባዶ ነው። ወንዱ በየፊናው ተበታትኗል። ዘመድ ለመጠየቅ ወደ ሩቅ መንደር የሄደ አለ። እህል ለመሸጥ ወይም ወሬ ለመጠያየቅ እህሉን ሸጦ በዚያው መሸታ ቤት ለመግባት ወደ ከተማ የተጓዘ አለ። የቀረው ደግሞ ግማሹ፥ አጥሩን ቤቱን የእርሻ መሣሪያውን እየጠጋገነ ሌላው በየታዛው ተቀምጦ እያሰበ በየቤቱ ተከትቷል።

ሴቱም እንዲሁ ነው። ምንጩም ወራጁም ጨርሶ ስላልደረቀ ውሀ ቅጅው ሩቅ አያስኬድም። ሰነፉም ልባሙም የሚፈልገውን ያህል ጧቱን ሊጨርስ ይችላል። ከዚህ በተረፈ ድግስ ያለው ሠርግ ያለው (መቼም መጪው ጥር የድግስ ወር ነውና) በየቤቱ ብቅሉም በርበሬውም ሙዳዩን ይሰፋል። ሌላው ደግሞ መጭው ገናን እንደየ አቅሙ ለመቀበል በየጓዳው ደፋ ቀና ይላል።

ለሆነለት የደስታ ጊዜ ነው። ላልሆነለትም የተስፋ ጊዜ ነው። አብዛኛው ገጠሬ ግን የታኅሣሥ መጨረሻ የእርጋታ ጊዜ ነው።

በዚህ የታኅሣሥ ወር መጨረሻ ላይ ካሣሁን ስለ ግብር አሰባሰብ ለመጣለት መመሪያ የበለጠ ለመረዳት ወደ ወረዳ አስተዳደሩ ሄዶ፥ ጠይቆና ተረድቶ ወደ ቆሬ ይመለሳል። የአራት ሰዓት መንገዱን የተጓዘው በእግሩ ነው። ለመኪና ኪራይ ከማኅበሩ ገንዘብ መክፈል ይችል ነበር። የወረዳ አስተዳደሩም ቢሆን በመንግሥት ጉዳይ የመጣ ስለሆነ አላፊ መኪና እንዲያሳፍረው ሊጠይቅለት ይችል ነበር። ሁለቱም አላሰኘውም።

ነፋሻውና ቀላሉ የታኅሣሥ ወር አየር እያባበለውና እያታለለው፥ ከአራት ሰዓት በላይ በእግሩ ተጉዞ፣ ጀንበር በቆሬ ተራራ ላይ ስታዘነብል ከዋናው አውራ ጐዳና መታጠፊያ ላይ ደረሰ። ቆም አለና፣ አሻቅቦ ተመለከተ። ጀንበር በምዕራብ አድማስ ማዘቅዘቅ ጀምራ በቆሬ ጋር ሰርጓዳ ወገብ ላይ ያለው የእነ ካሣሁን መንደር ጥላ ዐርፎበታል። ከአንዳንዶቹ ጐጆዎች ጣሪያ የሚተነው ጢስ መንገደኛን ለመክሰስ የሚጋብዝ ይመስላል። ከዋናው መንገድ ትንሽ ገባ ብሎ በዳገቱ ግርጌ፣ ከረባዳነቷ የተነሣ በበጋ ወራትም ልምላሜ የማይለያት የአጋም የቀጋ የክትክታና ቀንጠፋ ቁጥቋጦ የበዛበት ትንሽ መስክ አለች። ብዙ ጊዜ ከብቶችና እረኞች ይሰባሰቡባታል። ሩቅ መንገድ የተጓዙ ሰዎችም ወደ ቆሬ መንደር የሚያወጣውን ዳገት ከመያያዛቸው በፊት ዐረፍ ይሉባታል። ካሣሁንም እስከዚህም ደክሞት ሳይሆን ነፋሻው የአየርና ከብትም ሰውም ስለልነበረ ጸጥታው ስላስደሰተው ጥቂት ለመዝናናት ያህል ችምችም ባሉ ቁጥቋጦች ሥር ተጠልሎ ዐረፍ አለ። ወዲያው ሳይታወቀው ክንዱን ተደግፎ ጋደም እንዳለ በዚያው እንቅልፍ ይዞት ሄደ።

ሲነቃ ጀንበር ጠልቃ ጨለማው ለዐይን ያዝ አድርጐ በጠራው ሰማይ ላይ ከዋክብት መቁለጭለጭ ይዘው ነበር። ዙሪያውን እንቁራሪቶች ጓጉንቸሮች ይንጫጫሉ። አልፎ አልፎ የአህያ ጬኸትና የከብት እምቧይታ ከሩቅ ይሰማል።

ካሣሁን በድንገተኛ እንቅልፉ እየተገረመ ከተጋደመበት ለመነሣት ሲቃጣ፥ ከአውራ ጐዳናው በኩል የእረኛ ዘፈን ድምፅ ተሰማው። ጆሮውን አንቅቶ ጠበቀ። ካሣሁን ልጅ ሆኖ ቀኑን ሙሉ ሲዘፍን ቢውል የማይሰለቸው ስለ ነበረ አሁንም የእረኛ ዘፈን መስማት ደስ ይለዋል።

አሁን አሁን እረኛው ሳይቀር እየተወው የሄደው፤ «አው - አው - አህያ መጣች አው - አው - አህያ መጣች ተጭና ምንትስ » ሲል የሚጀምረው የእረኛ

ዘፈን ግጥሙ ግርድፍ ዜማውን ሸካራ ይሁን እንጂ ቀድሞ አዛውንት ሁሉ በጥሞና የሚያዳምጡትና የሚከታተሉት ወግ ነበር። ጒበዝ ይሞገስበታል። በቤተ መንግሥት በቤተ ክህነት፥ ሹማምንት ከታች እስከ ላይ ደጉ ይወደስበታል። መጥፎው ይነቀፍበታል። ይወገዝበታል። የአካቢው ሐሜት ይወጣበታል። ትንቢትም ይነገርለታል፣ ይባላል። ለዐዋቂ የተደበቀው ለሕፃን ይገለጻል በሚል የሃይማኖት መጽሐፍ መሠረት «እሱ በጥበቡ ለሕፃናት እረኞችም ምሥጢሩን ይገልጽላቸዋል » ተብሎ ይታመንበታል።

ካሣሁን ልጅ ሆኖ ያንጐራጐራቸውን የእረኛ ዘፈኖች ግጥም ከየት እንዳገኛቸው ከሌሎች እረኞች እንዴት እንደ ገለበጣቸው ወይም ራሱ እንዴት እንደ ገጠማቸው አያስታውስም። ግን አሁንም መስማቱ ደስ ይለዋል። አሁንም አንዳንድ ጠቃሚ ነገር የሚያገኝበት ይመስለዋል። ከመድረሱ በፊት አገር ምድሩ የሚቀባበለው የእረኛ ዘፈን፥

«አህያ መጣች ተጭና ዶቃ፣

ንጉሥ ተፈሪ ግፍህ አበቃ » የሚል ነበር።

የእረኛ ዘፈን እየቀረበ መጣ። «አው! አው! አህያ መጣች ተጭና ምስር ከበርቴ ቀረ በየድንጋይ ሥር »።

ካሣሁን ይህንን ግጥም ከአንድ ዓመት በፊት አንሥቶ የሰማው ቢሆንም አሁንም ፈገግ አለበት።

« አው! አው! አህያ መጣች ተጭና ፊኛ

የደሀው ጠላት ቀረ መሆነኛ! »

ይህንንም ሰምቶታል። የመሆኛን ጦርነት ትዛታ እንደ ክቡር ዕቃ በልቡ ቋጥሮ መቃብር የወረደው፥ አይዋ ሙሔ ይህንን ቢሰማ ምንኛ ደስ ባለው ነበር አለ በሐሳቡ።

«አው! አው! አህያ መጣች ተጭና ቁንጣ

ከበቡሽ ወሌ.....መላጣ » የሚለው ግጥም ደግሞ ካሣሁንን አሣቀው። ከበቡሽ ከአውራ ጐዳናው ካለችው ከተማ ጠጅ የምትነግድ ሴት ናት። የዚህ ግጥም ምንጭ አንድ ነገረኛ ጐረምሳ ወይም የተጣለችው ወዳጅዋ ሊሆን ይችላል!

ከዚያም የእረኛው ድምፅ እሱ ከነበረበት አግጣጫ እልፍ እንዳለ ያላሰበው ነገር ድንገት በጆሮው ላይ ፈነዳበት!

«አው! አው! አህያ መጣች ተጭና አክርማ

ስልቡ ካሣሁን ሚስቱን ተቀማ! »

እንደ ሎጥ ድንጋይ ሰውነቱ ባለበት የደረቀ መሰለው። ሰማይና ምድሩ ዞረበት። ነገር ዓለሙ ተደበላለቀበት። በሌላ በኩል ጆሮውን ማመን አቃተው። ካሣሁን ነው ያለው? ጥላሁን? ወይስ ዋሲሁን? ሌላ ካሣሁን ይሆን? ለጥርጣሬ መልሱ ወዲያው በዚያ ዘፈን መጣለት።

«አህያ መጣች ተጭና ቅርጫት

ከበደ ጣሹ ዘይኑን ነጠቃት! »

ምንም ቢሆን ጆሮው ሁለት ጊዜ ሊያሳስተው አይችልም። የሚሰማው ነገር እንደ ቀን ብርሃን እንደ ቆሬ ጋራ ገሐድና እውን ነው። ወዲያው ድንገት የመጣበት ስሜት እየተንደረደረ ሄዶ ያን ድምፅ የሚወታበትን ጉሮሮ ፈጥሮቅ ጸት ማድረግ ነበር። ግን ሰውነቱ እንደ ችካል ከተተከለበት ከመነቃነቁ በፊት ድምፁ እየራቀ ሄደ። የመጀመሪያ ንዝረቱ ትንሽ ጋብ ሲል ልጁን መተናኰል ምንም ዋጋ እንደ ሌለው ተሰማው። በልጁ ላይ ጉዳት ቢያደርስ በወንጀል ከመጠየቁ በስተቀር ዘፈኑ በሌሎች እረኞች መቀጠሉ የማይቀር ነው። የአገሩን እረኛ አፍ በሙሉ መዝጋት ደግሞ አይችልም። ጋራው ሽንተረሩ ዛፉ ቅጠሉ «አህያ መጣች ተጭና..... » እያለ የእርሱን ስም በመጥራት የተሣለቀበት መሰለውና በሁለት እጁ ጆሮውን ከደነ። በጭንቅላቱ ውስጥ ግን የእረኛውን ድምፅ መስማቱ አልቀረም ፡

ረዘም ላለ ጊዜ በውጥረት ድርቅ ብሎ እንደ ቆየ ድንገት ተወራጨና ዳገቱን በሩጫ ተያያዘው። የሚሠራው ልክ እንዳልሆነ ይታወቀዋል። ግን ራሱን መቆጣጠር አልቻለም።

ከጐጆው በር ሲደርስ ጫን ጫን እየተነፈሰ መላ አካላቱ በቀዝቃዛ ላብ ተዘፍቆ ነበር። ገርበብ ባለው የጭራሮ መዝጊያ በኩል ከምድጃ ላይ ዘይኔ ምግብ ስታበስል አየ። ወዲያውም ዘወር ብሎ ወደ ከበደ ጐጆ ተመለከተ። ከዚያም በግድግዳው በኩል የእሳት ጭላንጭል ይታያል። ይህ ነው የማይባል የጥፋት ኃይል መላ ሰውነቱን ወረረው። ዘለህ ፍጥርቅ ተንደርድረህ በፋስ እንክት አድርጋቸው የሚያሰኝ የጥፋት ኃይል ሰፈረበት። ከአእምሮው ጠባብ ማዕዘን

ዘንድ ደግሞ «የቸኰለ አፍስሶ ለቀመ ለጥፋት ከመጣደፍ ትዕግሥት » የምትል ረቂቅ ምክር እንደ ጭላንጭል ታየችው። የወጠረውን የጥፋት ኃይል ለመግታት ይመስል ጥርሱን ነክሶ መዳፋን የከረረ ቡጢ አድርጐ ጡንቻውን ሁሉ አኮማትሮ ቆመ።

ዘይኔ የሰው ኮቴ ሰምታ ቤት ሳይገባ በመቆየቱ «ካሣሁኔ ነህ? ስትል ከውስጥ ተጣራች። መልስ አልሰታትም። የቁልምጫ አጠራርዋ የባሰ አበገነው። ፊዝነቱ እንደ ጦር ወጋው።

ዘይኔ ምግብ አሰናድታ እንደ ጨረሰች ትንሽ ከጠበቀችው በኋላ ወጣ ስትል ከጐጆዋ ታዛ ሥር ተኮማትሮ ተቀምጦ አገኘው።

«አትገባም እንዴ? »

«ከዚህ ይሻለኛል » ሲል መለሰላት አንገቱን ከጉልበቱ ላይ እንደ ደፋ በጐረነነ ድምፅ።

«ምን አገኘህ? »

«ምንም አላገኘኝም። »

«ታዲያ ራትኮ ቀርቧል። »

«አላሰኘኝም። »

«መንገድ እንደ ዋልክ በባዶ ሆድህ? »

«የሆዴን ነገር የማውቀው ራሴው ነኝ! »

«እሺ ወንድሜ » ብላ ወደ ቤት ገባች ሁናቴው አደናግሮዋት። ስትጠብቀው ከቆየች በኋላ አላስችል አላትና ተመልሳ ወጣች። ከቦታው አልተነቃነቀም።

«ወይ ከዚሁ ላምጣልህ » አለችው።

«ሴትዮ! አትተይኝም! » ሲል ጮኸባት። በጥፊ እንደ ተመታች ያህል ክው ብላ ገባች።

በየጐጆው ግድግዳ ይታይ የነበረው የሳት ጭላንጭል ሁሉ አንድ ባንድ እየጠፋ ሄደ። እንስሳትም ጩኸታቸውንና ጥሪያቸውን አቆሙ። ጨለማና ጸጥታ በነገሡበት ሌሊት ካሣሁን ከታዛው ብቻውን እንደ ተቀመጠ የራሱን ሕማማት ቀጠለ። ቀስ በቀስ በመጀመሪያው ድንገት ንዝረቱ ፈንታ አንጀት የሚጨምቅ

ሥቀቀን እየተካበት ሄደ። እንደ እሳተ ገሞራ የፈነዳ ንዴቱን ጸጸትና ሐሳብ እየሸፈነው ሄደ። በሐሳቡ የሚነሡትን ጥያቄዎች ለማገናዘብና ለማመዛዘን ሞከረ። አንደ ሐሳቡ በመኰላሸቱ ምክንያት ከመሰደቡ በስተቀር፥ የዘይኔንና የከበደን ግንኙነት ለመካድ ይፈልጋል - ከበደ ይህንን በእርሱ ላይ ከቶ አይሠራውም። የሥጋም ባይሆን ልክ እንደ ወንድሙ ነው። እርግጥ ቀድሞ ዐመል ነበረበት። ግን በሰማይ ነፍሱን ይማርና ሙሒ ከገሠጸውና ያይኔ አበባን አግብቶ ኋላ በሕፃንነቱ ቢቀጭም አንድ ልጅ ከወለደ ወዲህ ከበደ ሌላ ሰው ሆኗል። አንድ ቤት ሙሉ ሴት መካከል ቢያስቀምጡት ስንኳ የሚከጀለው አይመስልም።

ከዘይኔ በኩል ከመሠረቱ ስሕተቱ የራሱ ሆኖ ተሰማው። ገና በመጀመሪያው ሳይሆንለት ሲቀር መለያየት መፍታት ነበረበት። ባልና ሚስት ሆኖ እንደ ወንድምና እኅት እንኑር አፍላ ስሜቷን ያልጨረሰች ልጅ እግር ሴት አግብቶ እንደ መነኩሴ ኑሪ ማለት አስቸጋሪ መሆኑ በፊትም ታውቆበት ነበር። ግዴለም ያለችው እሷ ነበረች። እንዳለችውም ሁናቴው አልተለወጠበትም። ሌላው ቀርቶ ጤነኛ ባል ያላቸውን ሴቶች ያህል ስንኳ መቀባበጥ አይከጅላትም። ፈተና ቢሰማትም ዕርቅ አድርጋ የቻለውችውና የእርሱንም ክብር የጠበቀችለት መስሎ ነበር የሚታየው።

ግን፥ የሰውን ነገር ማን ያውቃል? ሌላው ቢቀር የእርሱ ጉድለት እንዴት ሊታወቅ ቻለ? አዲስ አበባ በፖሊስ ጣቢያ ታሥሮ ሲመረመር ብልቱ መጐዳቱን የሚያውቁ አብረውት ታሥረው የነበሩት ተማሪዎች ናቸው። አንደኛው በወንበዴዎች ተገድሏል። ኋደኛው ታፍኖ ተወስዶ የደረሰበት አልታወቀም። ሦስተኛው አልዘምትም ብሎ ከአዲስ አበባ አልተንቀሳቀሰም ነበር። ሌላ ጉዱን የምታውቅ ራስዋ ዘይኔ ናት። እረኛው እንዳለው ንክኪ ካላቸው ደግሞ ከበደም ከእርስዋ ሊሰማ ይችላል። ሰው ናትና የራስዋን ፍላጎት በድብቅ መፈጸምዋ መቸም ይሁን ይባል። ግን የእርሱን ጉድለት የእሱን ጉድ ለምን ይፋ አውጥታ ታዋርደዋለች? ዐውቆ አልበደላትም። እንደሚያውቃት የቂም በቀልና የክፋት ተፈጥሮም አልነበረባትም።

ካሣሁን የሠቀቀን ግደማ መስቀሉን ተሸክሞ በሐሳብ እየተበጠበጠ ሌሊቱን ገፋው።

በጐጆው ዘይኔም ሌሊቱን ያጋመሰችው በሐሳብ እየተንከራተተች ነው። የእርሷ የሐሳብ ጉዞ ግን ከካሣሁን በጣም ይለያል። «ምን አግኝቶት ይሆን ደግሞ

ፈጣሪዬ » አለች በሆድዋ እሷም ራት ሳትቀምስ ከነቀሚሷ የሌሊት ጨርቃ ጨርቋን ደርባ እንደ ተጋደመች.....

ሁናቴውን ግን ከሁለቱ የጋራ ሕይወት ጋር አዛምዳ አላሰበችውም። ፈጽሞ አልታሰባትም። ምክንያቱም በእርሷ አመለካከት የሁለቱ ኑሮ ይህንን ከመሰለው ስሜት አልፎ ከሄደ ቆይቷል። እርግጥ ከረጅም ጊዜ መለያየት በኋላ ተገናኝተው እንደ ተቻላት አምራ ተዘጋጅታለት ሳይሆን ቀርቶ በተሸማቀቀ ሁናቴ የደረሰበትን ሲነግራት «እሱ ምን ዋጋ አለው » ያለችው ሥቃዩን ከመስማትና ከናፍቆትም የተነሣ ይሁን እንጂ እያደር ከሐሳቧ ጋር ተማክራበታለች። ተሟግታበታለች። ፈተናው ከብዶ የታያት ጊዜ ነበር። ውሸቱን ነው ብላ የተጠራጠረችበት ጊዜም ነበር። ለዚህ ጥርጣሬዋ ግን ከአዲስ አበባ ቆሬ ከተመለሱ በኋላ ምንም የውስልትና ፍንጭ ልታገኝበት አልቻለችም። ለእርሷም ለቤቱም አሳቢ ነው። በተረፈ ከተፈጥሮዋ ደመ በራድ ስለ ሆነች ድንገት የተጣለባትን የሕይወት ዕጣ ፈንታ በትዕግሥት በመቀበል ከውጭ እንደ ባልና ሚስት በጓዳቸው ሁለት መደብ ለየብቻቸው እየተኙ እንደ ወንድምና እኅት ሆነው የጋራ ኑሮዋቸውን ቀጠሉ። ወንድምዋ እንደ ጠፋ ቀርቶ በተለይ አባትዋ ሙሔ ከሞተ ወዲህ ምንም ሁነኛ ሰው እንደ ሌላት እየተሰማት ከካሣሁን ተለያይታ መኖር በሐሳብዋ ውልብ ስንኳ አላለም ነበር.....

‹እሱስ ቢሆን ወደ ቢተወው ወይ በርጋታ ቢይዘው ምናለ ስትል ከጨለማው ጋር ተውያየች። የታሰባት የገበሬ ማኅበሩ ጉዳይ ነበር። የማኅበሩ ሊቀ መንበር ከሆነ ወዲህ ስለ ማኅበሩ ብዙ የማሰቡንና ውጣ ውረድ የማለቱን ያህል ብዙ ሰዎች በተንኰል እየተነሡበት ማሰቡን አልፎ አልፎም በመላጨቱ ተገንዝባለች። በተለይ የመስቀል ለት ከልካይ ከሚባለው አዲስ መጥ ጋር ሲጣላና አዲስ ምርጫ ሊደረግ ሰሞን በጣም ብስጭትጭት ብሎ ነበር። አሁንም ችግሩ ከዚያ በኩል የመጣ ሳይሆን አይቀርም ብላ ገመተች። የማኅበሩን ሹመት እንዲተወው በበነጋው በረድ ሲልለት እንዴት አድርጋ እንደምትመክረው እያሰላሰለች፥ ዶሮ ሊጮህ አቅራቢያ እንቅልፍ ሸልብ አደረጋት።

ካሣሁን በበነጋው ቀርቶ በሣልሱም አልበረደላትም። ምን ማድረግ እንዳለበት ለመወሰን ሦስት ቀን ሙሉ አንጐሉን በሐሳብ ሲበጠብጥ ሰነበተ። ከሐሳቡ ጋር ሰውነቱም አብሮ ይታወካል። ይቅበጠበጣል። አንድ ጊዘ ከዛፍ ጥላ ሥር ኩርምት ብሎ ያሳባል። በሐሳብ ይተከዛል። ሌላ ጊዜ ሐሳቡ በላብና በድካም ይወጣለት ይመስል ያለ አንዳች ምክንያት የቆሬን ዳገት ይያያዘዋል። ከዚያም በነፋሻማው አናት ላይ ዝም ብሎ ከወዲያ ወዲህ ይጓዛል። አሁንም ጥግ

ጥጉን ይዞ ወደ ሩቅ ቦታ ይሄዳል። ይህ ሁሉ አላረካው ሲል ደግሞ ማሳ ወርዶ ጉቶ ይፈነቅላል። ግንድ ይቆርጣል። እንጨት ተሸክሞ መጥቶ የጓሮ አጥር ይሠራል። ውሎ - ውሎ ወደ ቤት ሲገባ «ኧረ እባክህ ነገርም እንዳለብህ በባዶ ሆድ አትወጣም » ስትለው በመጠኑ ይቀማምሳል። ይህ ሁሉ ሲሆን አእምሮው በሐሳብ መንከራተቱን አያቆምም ነበር። ዘይኔን መፍታት ራሱ አገር ጥሎ መጥፋት ሌሎችም አማራጭ ነገሮች ይመጡበታል።

በሦስተኛው ቀን ምክር ለመጠየቅ ይመስል ከሙሐ መቃብር ዘንድ ሄዶ ለረጅም ጊዜ ተከዘ። ከዚያም በሚገባ ሳይገነዘበው ከውሳኔ ላይ ደርሶ እየተንደረደረ ወደ መንደር ተመለሰ። ከበደን ከጐጆው በር ጠረፍ በሞራ ሲያሽ አገኘው።

ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ «በየህ ሰሞን አልተያየንም እኮ » አለ ካሣሁን አነጋገሩን እንደ ምንም እያረጋጋ። እውነትም ከበደ ኃጢአቱን ዐውቆ የሸሸው ይመስል ሦስቱን ቀን አልተገኞኙም ነበር።

«እኔ የትም አልሄድኩም አንተ ነህ እንጂ ያልታየኸው » ሲል ከበደ መለሰለት።

ካሣሁን ቆም ብሎ ትንሽ ከቆየ በኋላ «የማነጋግርህ አንድ ጉዳይ ነበረኝ » አለው።

«ዐረፍ በላ። »

«ወደዚያ ትንሽ ፈቀቅ እንበል እስቲ » ነገራቸውን ያይኔ አበባ እንድትሰማ ካሣሁን አልፈለገም።

ከአንድ ብሳና ዛፍ ሥር ድንጋይ አመቻችተው እንደ ገበጣ ተጫዋች ፊት ለፊት ተቀመጡ። ካሣሁን ነገሩን እንዴት እንደሚጀምር ተደናግሮት ጥቂት አመነታ። ከበደ ዝም ብሎ ጠበቀው።

«ሳትሰማው አልቀረህም! » አለ ካሣሁን በመጨረሻ።

«ምኑን? »

«የእረኞቹን ዘፈን። »

«ስንት የእረኛ ዘፈን ሞልቷል። የሰማሁት ያልሰማሁት ብዬ ምኑን አስታውሰዋለሁ። » ከበደ እንዳልገባው ሁሉ ነገሩን ያቃለለው መሰለ።

«ሰምተኸው ከሆነ ስንኳ የትኛውን ማለቴ እንደ ሆነ ታውቃዋለህ። »

ከበደ መለስ አልሰጠውም።

«ስለ እኔ ስለ አንተም የሚዘፈነው ሰምተሃል አይደል? ሲል እንደገና ጠየቀው።

ከበደ ሳያምንም ሳያስተባብልም መሬቱን በሣር ይጠቅስ ገባ።

«ምነው ዝም አልክ? »

«አዎ! መስማቱን ሰምቻለሁ። »

«እሳት ከሌለ ጭስ አይኖርምና ታዲያ ይህንን ነገር ምን አመጣው? » ካሣሁን አሁን ደሙ ከውስጥ በእሳት የሚፈነዳ መስሎ ተሰማው።

«እኔንም ገርሞኛል » ሲል ከበደ መለሰለት።

ካሣሁን ነገሩን በእርጋታ ለመጠየቅ አስቦት የነበረው ቀርቶ የሚያቃጥል ንዴት ብልጭ አለበት። «ከዘይኑ ጋር አልወሳለትክም ማለት ነው! » ሲል ጮኸ። በአዎንታ ቢመልስለት ካሣሁን ምን እንደሚያደርግ አልወሰነም ነበር።

«ምን? እኔ! » ከበደ በበኩሉ ሳይታወቀው ጮሆ ተናገረና ተፈናጥሮ ተነሣ።

«አዎ! አንተ! »

«አብደሃል ካሣሁን! »

ካሣሁን በበኩሉ ተነሣና ፊት ለፊት ተፋጠጡ።

«እረኞች በዘፈን የሚሉት ነው። »

«ግን ታምናለህ? እኔ ባንተ በወንድሜ ላይ? ዘይኔን እኅቴን? ምነው ካሣሁን! » ከበደ ከጭንቀቱ የተነሣ ድምፁ ቀጠነበት።

«የማምነውም የማላምነውም ግራ ገብቶኝማ ነው የጠየቅሁህ! »

«እርግጥ እረኛ ካላንድ ምህኛት ዘፈን አያወጣምና ብትጠረጥረኝ እውነት አለህ። ግና - ግና - » ከበደ እንደሚጸልይ ካህን ሁለት እጁን ዘርግቶ አንጋጠጠ። ድምፁ ከአንጀቱ እየተፋቀ የሚወጣ ይመስል ልዩ የጭንቀት ቃና ነበረው። «እሱ ፈጣሪ ነው ምስክሬ። በውን ቀርቶ በሕልሜ ስንኳ አስቤው ከሆነ ከይህች ምድር

ተከፍታ ትዋጠኝ። የእውነት አምላክ በእሳት ባሕር ይቀቅለኝ የሙሔ አጥንትስ አስቁሞ ያኬደኛል? ሌላ በምን ልማልልህ ካሣሁን? »

«ተወው » አለ ካሣሁን። አመነው። ከበደን እንደሚያውቀው ሌላ የጠባይ ጉድለት ቢኖርበትም በውሸት በኩል አይታማም። ያበጠው ይፈንዳ ብሎ እቅጩን መናገር ልማዱ ነው። ነገር መደበቅ ቢፈልግ እንኳ በቀልድና በተረብ ነው አድበስብሶ የሚያልፈው። አሁን ግን የሐቅ ሠቀቀኑ ከልቡ ፈንቅሎ ሲወጣ በግልጽ ያስታውቅ ነበር።

«አንተ ካልሆንክ ስም አሳስተው ነው፤ ሌላ ሰው አለ ማለት ነው » አለ ካሣሁን።

«ምንም ሰው የለም። ስለ ዘይኔ በከንቱ ኃጢአት አትግባ። ሰው ቀና ብላ ለማየት የምትፈራ ልጅ! » ከበደ በማስተባበል እንደ መወራጨት አለ።

‹አንተ ምህኛቱን ሳታውቅ ነው› አለ ካሣሁን በሆዱ

«ታዲያ ወሬውን ምን አመጣው? »

«ሆን ተብሎ የተሠራ ተንኮል ይሆናል። ሰውን ለማጣላት » አለና ከበደ መለሰለት።

«እኔ እስከዚህ ጠላት የለኝ - የግሌ። »

«ለሁሉስ እንደርስበት ይሆን የለ! መቼም የተሠረ መግለጡ አይቀር። »

አንድ ጊዜ የተነዛው የእረኛ ዘፈን ውርደቱንና ሐፍረቱን ለረጅም ጊዜ ማስተጋባቱ እንደማይቀር ካሣሁን ቢያውቀውም ከከበደ ጋር ባደረገው ጭውውት ናላውን ሲበጠብጠው የሰነበተው ጥርጣሬ ስለ ተነሣለት መንፈሱን ቅልል አለው......

ዘይኔ ከቤት ውጭ እያነጣጠሰች በርበሬ ስትቀነጥስ ካሣሁን ከከበደ ሠፈር በኩል ሲመጣ አየችው። ውቃቢዋ ነግሮዋት ሳይሆን ከሁናቴው ብቻ ከስሞኑ የተለወጠ መሆኑ ታወቃት። እንደ ስሞኑ ወደ ቤት ሲመጣ እግሩን አይጐትም። ፈጠን ባይልም ደክሞትም ቢሆን ከእርሻ ከሩቅ መንገድ ወደ ቤቱ እንደሚመለሰው ለመድረስ ሳብ ሳብ የሚል ዓይነት ነው። አንገቱም ቀና ብሎ ከቤቱ ላይ ያተኰረ ይመስላል። ሰሞኑን ያላየችበት ሁናቴ ነበር። መጀመሪያ ከንፈርዋን ምጥጥ በማድረግ ፈገግ አለችና ተነሥታ ወደ ቤት ገባች። ደህና ምግብ ልታዘጋጅለት......

# ፬

በጥር ወር መጀመሪያ ላይ፥ በቆሬና በመላውም ወሎ፥ እንደ ተቀባዩ ስሜት አዲስ የመርዶና የሥራት ወሬ ይነፍስ ገባ።

-የአሲምባ ጦረኞች ትግሬንና ወሎን ገጠሩን በቁጥጥራቸው ሥር እያዋሉ በቅርቡ ደሴ ከተማ ሊገቡ ነው። አዲስ አበባም በቅርብ ትልቅ ለውጥ ይደረጋል ይባላል። - ለውጡ ምን ያመጣል? እያንዳንዱ ከየራሱ ጥቅም ከየራሱ ስሜት አንጻር ይተረጒመዋል። ያስተጋባዋል። ተቃራኒዎቹ ኃይሎችም የየበኩላቸውን ወሬ ያሰራጫሉ። እንደተቀባዩ፣ አንዱ ተስፋው እያበበ፥ እየፈካ ይሄዳል። ሌላው ከቀን ሥጋቱ ያድጋል። ከዚህም ከዚያም ያልሆነው እንደ ዶሮ ወደሚያድነው መሸጐጫ ለመፈትለክ ጆሮውን አቆብቁቦ ያዳምጣል።

በዚሁ ሰሞን ከልካይና ሦስት ደጋፊዎቹ፣ ተከታትሎም እንደዚሁ ከበደ፣ ከቆሬ መንደር ጠፍተው ሰነበቱ።

የደጋው፣ የወይናደጋው የቆላ ቀመሱ የኢትዮጵያ ገጠሬ በጥር ወር ከመንደሩ ከሠፈሩ መዘዋወሩ የተለመደ ነው። ከዚህም ከዚያም የዘመድ አዝማድ ሠርግ ይኖራል። አዝመራ ተሰብስቦ ከአበቃ፥ ሁነኛ ዘመድና ወዳጅ የሚጠየቅበት ወራት ነው። በአምናው ፋሲካ ተድራ አሁን የተቃረበች ነፍሰ ጡር ሚስት ከእናት አባቷ ቤት እንድትታረስ ባል ይዟት የሚሄድበት ጊዜ ነው።

ለስንት ዘመናት የመሳፍንትና የመኳንንት ጦር መተላለፊያና መራኰቻ ለስንት ዘመናት የገባርነትና የመሬት ሥሪት ዓይነት መታያ፣ የብዙ ብሔረሰቦች መገናኛ መፋተጊያና መቀላቀያ በሰሜን ከትግሬ በምዕራብ ከጐንደር በደቡብ ከጐጃም የጋብቻ መጣቀሻ ለስንት ዘመናት የንግድ መናኸሪያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የኮንትሮባንድ መሿለኪያ ሆኖ በኖረው በወሎ አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ በበጋው ወራት፥ ይህ የገጠሬው ሕዝብ እንቅስቃሴ ከሌሎች አካባቢዎች የበለጠ ነው። ለወደብ ሽቀላ ወደ አሰብ ይወርዳል። ወደ አሳይታ ወደ ዱብቲ፣ ሥራ ወደ በራህሌ ይሄዳል። ሌላው ወደ ምዕራብ አምርቶ ወደ ሁመራና ወደ አብዱራፊ ይሸጋገራል። ለቡና ለቀማ እስከ ከፋ የሚዘልቅም ሞልቷል።

ለዘመናት እየታረሰ፥ ለዘመናት በውሀ እየተሸረሸረ ወዙ ካለቀ መሬት ጋር ለዘመናት እየተሸነሸነ የበሬ ግንባር ሊያካክል ምንም ካልቀረው ማሳ ጋር የሚታገለው አብዛኛው የወሎ ገበሬ ኑሮን የሚገፋው በዚህ ዓይነት አቻችሎ ነው።

የመረራቸውና ትንሽ የተሻለ ዕድል የገጠማቸው በዚያው ቀልጠው ይቀራሉ። ብዙዎቹ ለበልግና ለመከር እርሻ ተመልሰው ይመጣሉ።

ካሣሁን ይህንን ያውቃል። ግን፥ በእሱ ላይ የውጣው የእረኛ ዘፈን በቅርቡ፥ ከሚነፍሰው ወሬ ጋር ተጨማምሮ አሁን በርከት ያሉ የእርሱ ተቀናቃኞች በድንገት ከቆሬ መጥፋት መጠነኛ ሥጋት አሳደረበት። በተለይም ከበደ ሳይነግረው ወደ ሄደበት መሄዱ ከነከነው።

«የት እንደ ሄደ ታውቂያለሽ? » ሲል የከበደን ሚስት ያይኔ አበባን ጠየቃት።

«ኧረ አልነገሩኝም። »

«ለምን ብሎ ሄደ፤ ገበያ የሚያመጣው ምናምን እህል ጭኗል እንዴ? »

«ኧረ የለም! በደፈናው ብርቱ ጉዳይ አለብኝ ነው ያሉት? ስትል ያይኔ አበባ መለሰች። እሷም በብኩልዋ ግራ የተጋባች በመምሰል።

«መቸ እንደሚመለስም አልተናገረም? »

ያይኔ አበባ በአሉታ ራሷን ነቀነቀች።

ካሣሁን አንድ ዓይነት ጥርጣሬ አቆጠቆጠበትና ለወረዳው የገበሬ ማኅበር ማሳወቅ ያለበት መሆኑ ተሰማው።

ካሣሁን ወደዚያ ሲሄድ ከበደ ወደ ቆሬ ሲመለስ ሳይገናኙ በመንገድ ተላለፉ። ከበደ ቆሬ እንደ ደረሰ ወደ ካሣሁን ቤት ሄዶ አለ መኖሩን ዘይኔ ስትነግረው እየተበሳጨ ወደ ቤቱ ሄደ።

ከበደ፣ ያገኘው ነገር ያጠገበው ይመስል ያይኔ አበባ ያቀረበችለትን ራት በመጠኑ ቀማመሰ። አላሰኘውም ነበር።

«የሚጠጣ ነገር አለ? » ሲል ጠየቃት። የቤት አረቂ ማለቱ ነበር።

«ከተማ እየሄዱ የሚጠጡት አይበቃዎትም? » ስትል እንደ ቀልድ ተቆጣችው።

«ሙች አልቀመስኩም። » ደስታውም ይሁን ንዴቱ አሁን አሰኝቶት ነበር።

«ምን ነገር ደሞ ተፈጠረ? » በሥጋት ጠየቀች።

«የእነ ከልካይን ጉድ ደረስኩበታ! ለካስ ነገሩ ሁሉ የሚዶለትው ጦሳ ተራራ ሥር ነው። ደሞ በነሱ ቤት አልታየንም አልታወቅንም ብለዋል። አንጠርጥሬ ነው ነገራቸውንም እነሱንም ያወኳቸው። »

«አብደዋል? ምንስ ቢሆን አገባሁ? እህኔ አያለሁ ሲሉ ታይተው ይሆናል። ሰው ዐርፎ አይቀመጥም? ያይኔ አበባ በማኅበሩ ውስጥ የተፈጠረውን ጭቅጭቅ የምታውቅና የሰሞኑንም ወሬ የሰማች ቢሆንም፥ እንዲያው በደፈናው ፈራ ተባ እያለች ምክር ማቅረብ እንጂ ግልጽ አድርጋ መናገር አልደፈረችም።

«እህኔ አያለሁ ሲሉ ራስሁን አይተውዎት ይሆናል። የምን ጠላት መግዛት ነው? »

«ጠላት መግዛት አይደለም። ጠላት ማጥፋት ነው » ሲል ተቆጣት። «አሆሆ! ደሞ እኮ አለቃቢጤ ነው። ምረት ያረገለትን መንግሥት የሚጐዳ የአጐረሰውን እጅ ነካሽ ማለት ነው። አይዋ ሙሔ ይህንን ጉድ ሳያይ እንኳን አለፈው። ኧረ አጥንቱ እሾህ ሆኖ ይውጋው! ያም ሆነ ይህ ካሣሁን እንደ መጣ ለመንግሥት ስናስታውቅ አንዴ እፍስ አድርጎ ለላም ይሰጠን የለ! አንቺው ራስሽ ትዝ አይልሽም እነዚያ ከአዲስ ኧብባ የመጡት ዘማች ተማሪዎች? ታረቀኝ የሚባለው ለለውጡ ሲል ከዚሁ ከእኛው ፈፋ ተደፍቶ ቀረ። ማርቆስ የሚባለው ጓደኛው ጠፍቶ አደጋ ደርሶበት ነው ስንል ለካስ፣ ከነዚያ በኩል ሆኗል። ስብሰባው ላይ ለየሁት። በካሣሁን ላይ መጥፎ ስም ያዘፈነው እሱ ሳይሆን ይቀራል? አብርው ታሥረው ነበር። ወቸው ጉድ! ከበደ ራሱን ነቀነቀ።

«ታዲያ አንቱን አልደረሱቡህ! »

«አንቺ አርፈሽ ዝም በይ! የእኔም ጉዳዩ ነው! »

ከበደ የሚስቱን ልመና ዋጋ ሳይሰጠው፣ መደቡ ላይ በመጋደም ለረጅም ጊዜ አሰበ። እርግጥ ወንጀል ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ አላጋጠመውም። ግን በደርግ ላይ የሚያድሙ ለመሆናቸው በቂ ሁናቴ አይቷል። ደርግን ሲያወግዙ ሲሰድቡ ሲረግሙ ሰምቷል። ታዲያ እነርሱ ተይዘው እንዲታሠሩ ማድረግ ነገ ወንጀል እንዳይፈጽሙ መከላከል ነው። ያየውን የሰማውን ለመንግሥት ባያሳውቅና ወደ ፊት ከቆሬና ከአካባቢው ወንጀል ቢሠራ ዕዳው ከነ ካሣሁንና ከነ ከበደ ራስ አይወርድም። ስለዚህ ካሣሁን ከሄደበት እንደ ተመለሰ ይነገረውና ወደ ወረዳው ግዛት ሂደው የፖሊስ እርዳታ ይዘው ይመጣሉ።

እንቅልፍ እንደ ወሰደው ወዲያውኑ በውሻ ጩኸት ነቃ። ጆሮውን አንቅቶ አዳመጠ። በውሻው ጩኸት መካከል የሰው ኮቴና ሹክሹክታ የሰማ መሰለው። ብቻ እርግጠኛ አይደለም። ትንሽ ቆይቶ ከውስጥ በኩል በዘነዘና የተቀረቀረው የእንጨት መዝጊያ በግፊት ሲጢጥ ሲል ተሰማ።

አብዛኛው የባላገር ጐጆ መዝጊያ ገርበብ ብሎ ማደሩ የተለመደ ቢሆንም ያይኔ አበባ ዱሮ ከአባቷ ጋር ሳለች ሌሊት ተኩላ ገብቶ ከአስደነገጣት ወዲህ በር በዘነዘና ሳትቀረቅር ጀርባዋ ጋደም አይልም ነበር። ከበደ በዚህ ብዙ ጊዜ ይቀልድባታል። ጐጆው በሞላ የተነቃነቀ እስኪመስል ድረስ አሁንም በሩ በኃይል ተገፋ። በዚህ ጊዜ ከበደ ከተጋደመበት ፈጠን ብሎ ተነሣና ሱሪውን ሲያጠልቅ መዝጊያው ከነ መቀርቀሪያው ተነቅሎ ብዙ ሰው ተንጋግቶ ሲገባ በፊቱ ላይ ባትሪ ሲያበራ አንድ ሆነ።

«አካኪ ዘራፍ - ይህን ይወዳል ከቤ! » ብሎ መወራጨት ሲጀምር የብዙ ሰው እጅ ተረባርቦ ጣለውና ከመደቡ ወለል ጋር አጣበቀው። አንዳችም ጥሪ ከመስማቱ በፊት ጉሮሮውን እንቅ አርገው ያዙት። በግርግሩ ያይኔ አበባ ነቃችና ዐይኑና እያሻሸች «ምን መጣ! » ብላ ሳትጨርስ ከባትሪው ጀርባ ሁለት እጅ መጥቶ አፍዋን እፍን አደረገው። ሌላ ሁለት እጅ ከተጋደመችበት እንዳትነቃነቅ አረቃት።

ከበሩ በኩል የተነጣጠረው ባትሪ ያጐነባበሱትን ሰዎች ትከሻና ጭንቅላት እየዳበሰ በሁለቱ ባልና ሚስት ዙሪያ ቦግ ያለ ቀለበት ሠርቷል። ከባትሪው በስተጀርባ ባለው ጨለማ ውስጥ ሁለቱ ምርኮኞች የብዙ ሰዎች ቅርጽ ለይቶ ይታያቸዋል። እነማን ለመሆናቸው ፊታቸው ግን አያስታውቅም።

«አንተ ውራዳ ባንዳ! ባንተ ቤት ሳትታይ ለደርግ መሰለልህ ነበር! የሰለልከውን ለማን ነው የነገርከው በል ተናገር! » ሲል አንደኛው ጮኸበት።

ከበደ ተፈጥርቆ በተያዘ ጉሮሮው እንደሚያጓራ እየተነፋነፈ በሚወጣ ድምፅ «ከሐዲ ውሻ ሁሉ፥ ለማንስ ብናገር! ይኸን ይወዳል ከቤ! የጐራው ኮሶ! » እያለ ዐይኑን አፍጥጦ ጥርሱን አግጥጦ ነጥቆ ለመነሣት ሞከረ። ከሕመሙ ይልቅ ድምፁ ጆሮውን ያደነቆረው እስኪመስለው ድረስ አንዱ ተንደድሮ በጥፊ አናጋው።

«የተጠየከውን መልስ! የአባጊዶ መንግሥት አያድንህም! »

ከበደ አዲስ ኃይል ከየት እንዳገኘ ሳይታወቀው እንደ ወገሸ በሬ በድንገት ተወራጭቶ አንዴ በታተናቸውና ከመደቡ ራስጌ ግድግዳ ላይ የተሻጠውን ምሳር ሊያነሣ እጁን ሲዘረጋ አንድስ የሚያህል የክትክታ ዱላ አናቱን ፈጠፈጠው።

በአዳኝ ጥይት ነፍሱን እንደ ሳተ አውሬ ከበደ መጀመሪያ እንደ መንበከክ አለና ተዝለፍልፎ ወደቀ። ያይኔ አበባ ታፍናና ተፈጥርቃ ከተያዘችበት ተንፈራፈረች።

ከበሩ በኩል አንደኛው ሰዎቹን እየገፋፋና እየከፋፈለ መጣና፣ ባትሪውን ከያዘው ሰው እጅ ተቀብሎ፣ በተለይ ከከበደ አካል ላይ አነጣጠረና የተጐዳበትን ቦታ ፈለገ። ተዘርሮ የወደቀው ጀርባው ነው። ከግራ አናቱ በኩል ወደ ውስጥ ተሰርጉዶ ደምና እዢ የመሰለ ነገር ተቀላቅሎ ይወጣል። ከአፍንጫውና ከአፉም ደም መፍለቅ ጀምሯል። ባንዳፍታ ፊቱ ያበጠ ይመስላል። በዚህ መካከል እንደሚያኮራፋ ሰው ድምፅ እየሰጠ የሚወጣ እስትንፋስ አሁንም አለው።

«የማትረባ ምንድን ነው የምትሠራው? » ሲል የክትክታ ዱላውን ባለቤት ጠየቀው።

«ምነው? »

«መሞቱ እኮ ነው! »

በዚህ ጊዜ ከበደ የተናጋሪውን ድምፅ የለየ ይመስል ለመጨረሻ ጊዜ ዐይኑን ገልጦ ባትሪ በያዘው ፊት ላይ ትክል አድርጐ ቆየና «ጐበዜ? ነፍሰ ገዳይ - » እንዳለ የመጨረሻ ስቅታውን ዋጠ።

«ይሙታ! የውሻ ሞት ይኸው ነው » ሲል ባለ ዱላው መለሰ።

«መሞቱ አይደለም እኔን ያሳሰበኝ » ሲል ጐበዜ በለሆሳስ ድምፅ ተቆጣ። «የምንፈልገውን መረጃ ሳይሰጠን መሞቱ ነው። ይገባሃል! አሁን ለእነማን እንደ ተናገረ አናውቅም! »

«እሷን እንጠይቃት! ሳይነግራት አይቀርም! » አለ ከልካይ። ከተሠወረበት ጨለማ ወጣ አለ።

የአፍዋ እፍናት ተነሣላት። በዚያው መጠን ደግሞ ትንሽም እንዳትንቀሳቀስ መላ አካላቷ ከመደቡ ጋር ታርቆ ተያዘ። ትንፋሽ አጥቶ በቆየው ሰውነቷ ዐይኗ አብጦ የወጣ ይመስል። ደም ሥሮቿ ተገታትረዋል። ግን መላ አካላቷን ፈጥርቆ ከያዘው መዓት እጅ ጋር ከአንገቷ ሥር የተደቀነውን የአዳል ጩቤ ስታይ

ትንፋሽዋን ውጣ ዝም አለች። ሕይወትን ማጣት ለይኔ አበባ ቀላል አልሆነላትም። በሕይወት ሥቃይ አለ። በሞት ዓለም ደግሞ ምን አለ? ሃይማኖት በማይታወስበት የእነ መምሬ ቃለ ቡራኬ በማያጽናናበት በዚያች የጭንቅ ጨለማ ወቅት ምንም ነገር አልታያትም። የከበደ ፍጻሜ ኣይታለች። መኖር ትፈልጋለች። «ኸረ እባካችሁ ተውኝ በፈጠራችሁ? » አለች እንዳትጮህ ታፍኖ የቆየ ትንፋሽዋ አሁንም ከላይ ከላይ እየገፋት። እሪ ብላ እንዳትጮክ እንደ ዶሮ አንገቱና ጠምዝዘው ሲጥ እንዳያደርጉዋት ፈራች።

«ከበደ ከሄደበት ከተመለሰ በሁላ ከማን ጋር ተገናኝቷል? ከካሣሁን?

«አላገኙትም። ካሣሁን አልነበረም። »

«ሌላ ከማን ጋር ተገናኝቷል ወይስ ተነጋግሯል? »

«ካሣሁንን ከቤቱ ሲያጡት እንደ መጡ ነው ከዚሁ የቆዩት። » ያይኔ አበባ በተቻለ መጠን ጥያቄያቸውን ለመመለስ ሞከረች።

«ለአንቺስ ምን ነገረሽ »

«ለእኔ ምን የሚነግሩኝ ነገር አለ ብላችሁ። » አሁን ሰዎቹን አንድ ባንድ ለመለየት ዐይኗን ከወዲያ ወዲህ ታመላልሳለች።

«የት ሄዶ እንደ ነበረ ምን እንዳጋጠመው አልነገረሽም?

«እሳቸው ለኔ ጉዳያቸውን መች ያማክሩኛል። » ይህ ሁሉ ሲሆን የተዘረረው ከበደን ላለማየት በተቻለ መጠን ፊቷን እንዳዞረች ነበር።

«ውሽታም! » ሲል አንዱ በቃሪያ ጥፊ ቀለባት።

«ኸረ እውነቴን ነው የአባዬ አጥንት እሾህ ይሁንብኝ። » ከፍርሃቷ ብዛት ወዲያው ቀጠል አደረገችና «ብቻ ‹ጉዳቸውን ደረስኩበት። ነገ ይታፈሱዋታል!› እያለ ብቻቸውን ተናግረዋል! » አለች።

«የእነማን ጉድ? »

«የእከሌ እከሌ አላሉም። »

«የምታውቀውን እውነቱን የተናገረች መሰለኝ። ስለዚህ እንሂድ ከንግዲህ! » በማለት ከልካይ ሐሳብ አቀረበ።

ጉበዜ ባትሪው ወደ ከልካይ ፊት መለስ አድርጎ ትኩር ብሎ ተመለከተው። «አዎ አሁን የምታውቀውን እውነት ተናግራ ይሆናል። ደግሞ ዛሬ ያየችውን እውነት ትናገራለች፤ ያ - ውሻ » በባትሪው ከበደን አመለከተ። «እኔን በስሜ ሲጠራኝ አሁን ሰምታ የለም ሌላው ቢቀር? »

«እና? » ሲል ከልካይ ጠየቀ።

ጉበዜ የክትክታ ዱላ የያዘውን ሰው በዐይኑ ፈለገና «ነገሩን አበላሸተህ እንደ ጀመርከው ጨርሰው » አለው።

ሁሉም ገባው። ለአንዳፍታ ጸጥታ ሰፈነ። አንዳንዶቹ አንገታቸውን ደፉ። ባለ ክትክታው ዱላው ትንሽ ቀረበ፣ የጨበጠበቱን ክንዱን ወደ ታች እንዳንጠለጠለ። ያይኔ አበባ አሁን ለየችው።

በቅርብም ባይሆን ዘመዳሞች ናቸው። በወላጆቻቸው አገር የጁ ሁለቱም ልጆች ሳሉ አልፎ አልፎ ተገናኝተዋል። በኋላም እርሱ ቆሬ መጥቶ ከሰፈረ በኋላ፥ በመንደሩ ስብሰባ አጋጣሚ በየጁ ከአንድ አካባቢ መምጣታቸውን ደርሰውበት፥ የልጅነት ጊዜያቸውን አንሥተው ተጨዋውተው ነበር። እርግጥ ከዚያ በኋላ እንደ ዘመዳሞች ብዙም አልተቀራረቡም። ከበደ እንዲህ ያለውን ነገር አይወድም። ያይኔ አበባ ግን፥ ሰውየውን በልቧ እንደ ዘመዷ አድርጋ መያዟ ልቀረም።

«አንተ ዘመዴ? ምን አረኩ! አንተም እንደ ሌሎቹ ልትጨክንብኝ? » አለች ዐይኑና በጭንቀት እያንከራተተች።

«ሴት ናት! ምን ትሠራለችና ነው » አለ ዐይኗን ለማየት የፈራ ይመስል ፊቱን ወደ እነሱ መልሶ።

«ተናግሬአለሁ! ነገ ትናገራለች! ወይስ ዋስ ትሆናለህ? በተለይ እኔ ማን መሆኔን ካወቀች » ሲል ጉበዜ አፈጠጠበት።

«ሰው በገንዘብ በሀብት እንጂ በምላስ እንዴት ይዋሳል? ግን ሴት ናት » ሲል ዱላውን እየጐተተ ወደ ጀርባ አፈገፈገ።

«ሴትም ትናገራለች » አለ ጉበዜ ፍርጥም አድርጎ።

«ስለዚህ የጀመርከውን ጨርስ። »

ዱላውን እንደ ማንሣት ቃጣውና በፍርሃት በጭንቀት የሚማጠን ዐይኗን አፍጥጦ ሲመለከተው «ግና ሴት ናት እኮ! ሴት እንዴ..... » እያለ በማጉተምተም ወደ ኋላ አፈገፈገ፡

«ተወው እሱን » ሲል ባለ አዳል ጩቤው ፈንጠር ብሎ ወጣ። «እኔ እጨርሳታለሁ! » ዐይኑ ከዐይንዋ ሲጋጠም ግን የሚጥል በሽታ እንደ ያዘው መላ ሰውነቱ ለቅጽበት ተንዘፈዘፈ። «ለምን ፊቷን አትሸፍኑትም! » ሲል ጮኸ። ይዘዋት ወደ ላይ ተስቦ ባትና ጭኗ ተጋለጠ። ውብ የሆነ ልስልስ ገላ። ሕይወት፣ ፍቅር ያልጠገበ ገላ። ዐይኑን ጭፍን አደረገና በደረቷ አግጣጫ የአዳል ጩቤውን እየደጋገመ ሰነዘረው። ከሦስት ጊዜ በኋላ አሁንም ዐይኑ ሳይገልጥ ጩቤውን በዚያው ጨርቅ ላይ አገላብጦ ከጠረገ በኋላ ሲነሣ ሁሉም ተከታትለው ከጐጆው መውጣት ጀመሩ።

# ፫

ከከበደ ጐጆ በኩል በሩቅ የሚሰማውን የውሻ ጩኸት የራሱም ውሻ እየተቀበለ የሚመልሰውን አጸፋ፣ የተለመደ ነው በማለትና የመንገደኛ ድካም በተጫጫነው መንፈስ፥ ካሣሁን ለጥቂት ጊዜ ችላ ብሎት ቆዩ። ግን ጩኸት እየበረታ በመቀጠሉ ያይኔ አበባ ብቻዋን ስለሆነች ትፈራለች ብሎ በመገመት ወጥቶ ለመፈተሽ ሲያስብ የማዶው ውሻ አየር የሚሰነጥቅ ኡኡታ - ልቅሶ - ጣዕር የተቀላቀለበት የሚመስል ድምፅ አስሙቶ ጸጥ አለ። የራሱ ውሻም የበሩን ሥር እየቧጨረ ጭንቀት በወጠረው ጩኸት ያላዝን ገባ። «ምን ነካቸው እነዚህ ውሾች! » እያለ በሩን ከፈት ሲያደርግ ውሻው ጅራቱን ቀብሮ በእግሩ ሥር ተፈትልኮ ወደ ማጀቱ ገባ። ከዚያም ጥግ ይዞ ማላዘኑን አልተወም። ካሣሁን በሁናቴው ተገረመ። ውሾቹ እንደዚህ የሚሆኑት እጅግ አስፈሪ አደጋ ሲያጋጥማቸው ብቻ የሚቀመጠውን ችቦ አቀጣጠለና ሲወጣ ዘይኔ «ምን መጣ! » በማለት ከተል አለችው።

«ዐርፈሽ ቁጭ በይ! ምን ትሠሪያለሽ? » ሲል በእጁ ውዝዋዜ መለሳት። ውሻው ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ተከትሎ አልወጣም። ካሣሁን ጆሮውን አቅንቶ ዙሪያ ገቡን አዳመጠ። ምንም ነገር የለ። ጸጥ ረጭ ያለ ሌሊት ነው። ጥቂት ሄደና ድምፁን ከፍ አድርጎ «አይዋ ከበደ! አይዋ ከበደ! » ሲል ደጋግሞ ተጣራ። ካይኔ አበባም ሆነ ከከበደ የመልስ ድምፅ አላገኘም። በተለይ ውሻ

ድምፅ መጥፋት ከነከነው። ሙሔ መሆነኛ ላይ የተዋጋበትን ፋስ በቀኝ እጁ ጨብጦ በግራ እጁ ችቦ ይዞ በጥንቃቄ ወደ ከበደ ቤት አመራ።

የጐጆው መዝጊያ እንደ ተከፈተ ስለ ነበር አሁንም እየተጣራ ችቦውን አስቀድሞ አንገቱ ገባ እንዳደረገ እሳተ ነበልባል ላይ ድንገት የወደቀ ያህል መላ አካሉን ነዝሮት ወደ ኋላ ተፈናጠረ። ለቅጽበት ሰውነቱን ስሜቱን አላወቀም። ከዚያም ወደ አውሬ በማድፈጥ የጐጆውን ዙሪያ ገባ ከተመለከተ በኋላ ወደ በሩ ተመለሰ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጥርሱን ነክሶ፥ ዐይኑን ጭፍን አድርጎ ገባና መላ ስሜቱን መላ ሰውነቱ አኮሳትሮ ተመለከተ። አሁንም ድጋሚ ሲመለከተው፥ በእውን ቀርቶ በሕልም መሆኑን ማመን አስቸገረው። በሕልሙ እንደዚህ ያለ አሠቃቂ ትርኢት ታይቶ አያውቅም። ያጋጥመኛል ብሎም አላሰበም። የፈሰሰው የከበደም ደም ብዛት በጥጋብ ዘመን በጥቅምት ባሕር ብዙ ከብቶች የታረዱበት ሜዳ ዓይነቱን ይመስላል። ወለሉ፥ የሚቾቹ ሰውነት ግድግዳው ሳይቀር ደም ብቻ ነው። ከሁለቱም የፈሰሰው ደም፥ በእበት በተለቀለቀው ወለል ላይ በአንድነት ተቀላቅሎ ቀጭን ምንጭ መስሎ ወደ በሩ ኮለል ብሎ ፈስሷል። ከበደ በአንድ ጐኑ ዘንበል እንዳለ ገዳዩን ለማመልከት ይመስል ግራ እጁን ደሙ ወደ ፈሰሰበት ወደ በሩ አግጣጫ ዘርግቷል። በደም የተለወሰ ፊቱ አይለይም። ያይኔ አበባ ከአጠገቡ በጀርባዋ ተንጋላ ወድቃለች። ካሣሁን ጥርሱን በጥርሱ ነክሶ ተመለከተ። ጐንበስ ብሎ አስተዋለ። ከበደ ምንም የሕይወት ምልክት የለበትም። ከያይኔ አባባ ግን በጣም የደከመ የጣዕር ድምፅና እስትንፋስ የሰማ መሰለው። በርከክ አለና አንገቷን በክንዱ ደግፎ ቀና አደረጋት። ከሸረሪት ድር የቀጠነች የሕይወት እስትንፋስ ቀርታለች። «ያይኔ አበባ - ያይኔ አበባ » አለ ካሣሁን በልቅሶ ይሁን በሢቃ በተሰባበረ ድምፅ። «እነማን ናቸው? » ያይኔ አበባ ዐይኑናን እንደ መግለጥ ሞከረችና ያቃታት ይመስል መልሳ ከደነችው። «ያይኔ አበባ - ያይኔ አበባ! ትሰሚኛልሽ? ትሰሚኛለሽ? ትሰሚኛለሽ! » ለመቀስቀስ ይመስል እንደ መወዝወዝ አደረጋት። «እነማን ናቸው? ታውቂያቸዋለሽ? አረመኔዎቹን! »

ያይኔ አበባ ከንፈሮች እንደ መንቀሳቀስ አሉ። «ያይኔ - ያይኔ » ሲል ጮኸ። አሁንም ከንፈሮችዋ ትንሽ ተንቀሳቀሱና «ው - ው - ጉ - ጉ - በ - ው » የሚል ድምፅ አወጡ። «ምን? ምን አልሽ? » ሲል ጠየቀ አሁንም ትከሻዋን እንደ መወዛወዝ እያደረገ። ሌላ ድምፅ እስትንፋስ አልወጣትም። ቀስ አድርጐ ከከበደ አጠገብ አጋደማትና ቁሞ ሁናቴውን ተመለከተ። ስሜቱ ከኀዘን ይልቅ በንዴት ደንዝዞ ነበር። «እሺሺ! » አለ እርስ በርሱ በተናከሰ ጥርሱ መካከል ፈንቅሎ

በወጣ ትንፋሽ እሽታው የሚቾችን ፈቃድ ለመፈጸም ቃል ኪዳን ለመግባቱ ይሁን ለሌላ ራሱም በትክክል አልታወቀውም።

ከቀብሩ በኋላ ካሣሁን እንደ ገና ወደ ወረዳው አስተዳደር ሂዶ ለፖሊስ አስታወቀ።

ቃሉን እንደ ተመርማሪ ተቀበሉት።

«አንተ ለሚቾች ምንድን ነህ? »

«የቅርብ ወዳጅም ጐረቤትም። »

«አንተ ብቻ ነህ የቅርብ ወዳጅና ጐረቤት። »

«ሌሎችም አሉ። »

«ታዲያ አንተ ብቻ ለማመልከት የመጣኸው ለምንድ ነው? »

ካሣሁን ንድድ አለው። «ከወዳጅም ወዳጅ አለ። በይህ ላይ የገበሬ ማኅበር ሊቀ መንበር ስለ ሆንኩ በማኅበሩ ክልል ውስጥ አንድ ነገር ቢደርስ ለመንግሥት ማስታወቅ አለብኝ? የለብኝም? »

ቃል ተቀባዩ በመስማማት ራሱን አወዛወዘለት።

«ታዲያ አስከሬናቸውን መቅበራችሁ ደግ አላደረጋችሁም። »

«እህ! እስኪበሰብስ ዝም ብለን እናሰምጠው እንዴ። » ካሣሁን ሬሳ ውሎ ሲያድር በሐሳቡ ታየውና ሰቀጠጠው።

«የለም አስቀድሞ መመርመር ነበረበት። »

«መሞታቸውማ ተረጋግጧል » አለ ካሣሁን ግራ ተጋብቶ።

«እሱን ማለቴ አይደለም። አሻራ እንዳለ መነሣት ነእብረበት። » ካሣሁን ስላልገባው ፖሊሱን በመደናገር አኳኋን ተመለከተው። «አዎ! የወንጀለኛው ወይም የወንጀለኞቹ የጣት ምልክት ሊገኝ ይችል ነበር ይሆናል። ስለ ትብብርህ እናመሰግናለን። ሰሞኑን መርማሪ ይላካል » ብሎ አሰናበተው።

«ግን እኮ የምንጠራጠራቸው ሰዎች አሉ። »

«እነማን ናቸው? » ቃል ተቀባዩ እንደ ገና ወረቀት ሳበና ለመጻፍ ቃጣ። ካሣሁን የእነከልካይን ስም ዘረዘረለት።

«ለጥርጣሬህ ምን ምክንያት አለህ? »

«በማኅበራችን ውስጥ በመካከላችን ጥቂት መቃቃር አለ » አለ ካሣሁን ፈርጠም አድርጎ።

«ታዲያ የማኅበሩ ሊቀ መንበር አንተ። ቢተናኰሉ አንተን ነው እንጂ ወደ እነዚያ ምን ወሰዳቸው? »

ካሣሁን ይህንን ጥያቄ መመለስ አልቻለም። የእረኞቹን ዘፈን ጉዳይና የራሱንም ምሥጢር ሊገልጽ አልፈለገም። ዝም አለ።

«ያልካቸው ሰዎች ካንተ ጋር ግን፥ ጠብ አላቸው። አይደለም? »

«ጠብ አይደለም። ብቻ ቦለቲካ በሚባለው አንስማማም። እነሱ አዲሱን መንግሥት የሚደግፉ አይመስለኝም። »

«ስለዚህ በመካከላችሁ ቂም አለ? »

ካሣሁን አሁን መልስ አልሰጠም። የነገሩ አዝማሚያ ግን ደስ አላለውም። በተጠርጣሪነት ስማቸውን በመስጠቱ የግል ቂም በቀል ስላለው አስመለሰለት። «ግን መሰለዎት ከበደ ወዳጄ ከመሆኑ በስተቀር በቦለቲካውም አብረን እንስማማ ነበር። ስለይህም አይወዱትም » አለ በመጨረሻ።

«ገባኝ » ሲል መርማሪው አሰናበተው።

## ፬

ድንገት እንደ መጣለት ከልካይን ይጠርጥር እንጂ የከበደና የሚስቱ ምሥጢራዊ ግድያ ለካሣሁን ውስብስብ እንቆቅልሽ ሆነበት። እነ ከልካይ በቀብሩ ላይ እንደ ሌሎቹ ኀዘንተኞች ሆነው ከመዋላቸው በቀር ከዚያም፥ ወዲህ ምንም ዓይነት ለውጥ አልታየባቸውም። እንዲያውም ከሰላምታ አሰጣጥ አንሥቶ ከእርሱ ጋር ያላቸው አቀራረብ ከወትሮው በጣም የተሻለ ሆነ። ለማስመሰል ይሆን? ቃል ተቀባዩ ፖሊስ እንዳለው የጠረጠራቸው፣ ቂም ስላለው በስሜት ተገፋፍቶ ይሆን? ወይንስ የከበደ አሟሟት በእረኛ ዘፈን ከእነርሱ ጋር ለማጣላት ከተሞከረው ተንኰል ከበደና እነ ከልካይ ከቆሬ ድንገት ጠፍተው ከሰነበቱበት ሁናቴ ጋር ግንኙነት አለው? ከበደ የት ደርሶ እንደ ተመለሰ የሚታወቅ ነገር የለም። እነ ከልካይ ግን አንዱ ለሕክምና ሌላው፥

ጨርቅ ለመግዛት ሦስተኛው ዘመድ ጥየቃ ደሴ ከተማ ሄደው ነበር ነው የሚነገረው። ወደ ቆሬ ተመለስን የሚሉትም ከበደ ሌሊቱን ተገድሎ በበነጋው ጧት ገደማ ነው። ከበደና ያይኔ አበባ በተገደሉበት ዕለትና ምሽት፥ በቆሬ አካባቢ ላለመታየታቸው አጠያይቆ አረጋግጧል።

ተላላፊ ወንበዴዎች ለዝርፊያ ገደሉዋቸው እንዳይባል ከጐጆው የተዘረፈ ነገር የለም። ከመሠረቱም ነፍስ እስከ ማጥፋት የሚደርስ፣ እስከዚህም የሚዘረፍ ንብረት የለም። ጥቂት የቤት እንስሶች ናቸው። ያለ አንዳች ግርግር በቀላሉ እነሱን መንዳት ይችሉ ነበር። ካሣሁን እስከሚያውቀው ድረስም ከበደ ደም የተቃባው ደመኛ አልነበረውም። ታዲያ ማን በምንስ ምህኛት ሊሆን ይችላል?

እንደ ግል ጉዳዩ ሆኖ ከአስጨነቀው ከካሣሁን በቀር ሌሎቹ ስለ ግድያው እንደ ፈለጉ የየራሳቸውን የተለያየ መላ ምት ሰጡት። አንዳንዶቹም «መቸም ነፍሱን በስማይ ይማረው እንጂ ወትሮም ዐመለኛ ነበርና ሲልከሰከስ የወንድ ሚስት ነካክቶ ይሆናል፣ ሆኖ ዐረፈው » አሉ።

ካሣሁን ይህንን መላ ምት ሊቀበለው አልቻለም። ከበደ የወትሮው ዐመሉን ያልተወ ከሆነ በእረኞች ዘፈን የተነዛው ወሬ እውነት ሊሆን ይችላል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ፈጽሞ የማይሆን ነው። ምክንያቱም በዚያው ሰሞን ከበደ ምሎ ተገዝቶ ሐሰት መሆኑን ሲነግረው አምኖታል። አሁን እንደ ገና መልሶ የሚጠራጠርበት ምክንያት አልታየውም። አጉል ሠቀቀን ውስጥ መግባት ነው።

‹የሴት ጉዳይ ቢሆን ኖሮ ያይኔ አበባን አብረው የሚገድሉበት ምንም ምህኛት የለም። እሷ ተበዳይ እንጂ በዳይ አይደለችም› አለ ከራሱ ጋር አስተሳሰቡን ድጋፍ ለመስጠት።

በአራተኛው ቀን ከወረዳው አንድ ፖሊስ መጣና ምርመራውን አካሄደ። የከበደን ጐጆ ውስጡንና ዙሪያውን ፈተሸ። መተላለፊያ መንገዶችን እየተዘዋወረ ተመለከተ። ወንጀሉ በተፈጸመበት ዕለት በአካባቢው ጠጉረ ልውጥ ሰዎች ታይተው እንደ ሆነ ጠየቀ። በትንሽ የማስታወሻ ደብተር ላይ መዘገበ። ግን ፍንጭ ያገኘ አይመስልም። ይህ ሁሉ ሲሆን፥ ካሣሁን በቀበሌው የገበሬ ማኅበር ሊቀ መንበርነቱ አብሮት ይዘዋወር ነበር። አንዳንድ ልጆችም ከኋላ - ኋላ ከተል - ከተል ይላሉ። ምርመራውን ጨርሶ ለመሄድ ሲል እንደ አጋጣሚ የከበደ ውሻ ሬሳ ከወደቀበት አጠገብ ደረሱ።

«ውሻውንምኮ አብረው ገድለውት ነው የሄዱት » አለ ካሣሁን እንደ ዋዛ።

«ምን? » ሲል ፖሊሱ ጠየቀ መራመዱን አቁሞ የውሻውን ሬሳ እየተመለከተ። ሁለቱ ውሾች እንዴት እየተቀባበሉ እንደ ጮሁ፥ ከዚያም የከበደ ውሻ የማቃሰት ድምፅ አስምቶ ጸጥ ሲል የራሱ ውሻ በፍርሃት ተሸማቆ እንዴት ቤት እንደ ገባ፥ ካሣሁን ነገረው።

ፖሊሱ በተለመደው የፖሊስ የማወቅ ጉጉት ጐንበስ ብሎ አስተዋለ። ከሰሞኑ የጅብ ቅርምት የተረፈው የከበደ ውሻ ሬሳ በአገጠጠ ጥርሱ ባጣሽ ጨርቅ እንደ ነከሰ ነው። ፖሊሱ በሥንጥር ቀስ አድርጎ አላቀቀና መረመራት። ከአንድ ፊት በኩል የደረቀ ደምና ብጫቂ የሚመስል ነገር ተጣብቆበታል ፡

«አሃሃ! » አለ ፖሊሱ በማዳነቅ።

«ምን ተገኘ? » ሲል ካሣሁን ጠየቀ።

«ይኸ የቁምጣ ሱሪ ብጣሽ ነው » አለ ፖሊሱ ጨርቋን አሁንም በሥንጥር እያገለባበጠ። «ውሻው አንድ ሰው ከታፋው ላይ ነክሷል ማለት ነው። »

»በይህ ምህኛት ነዋ የገደሉት? »

ፖሊሱ ድንገት ሳይታወቀው ያልተፈለገ ምሥጢር በማውጣቱ ካሣሁን እንደ መገላመጥ ብሎ መልስ ሳይሰጠው ዝም አለ። ግን ባገኘው ፍንጭ መሠረት ወዲያው የመመለስ ሐሳቡን ቀይሮ በእያንዳንዱ ቤት እየገባ ጒሽጒሻ በማስከፈት ስልቻ በማስፈታት ከውሻው ጥርስ ጋር የሚመስል አቀዳደድ የተቀደደ ልብስ ሲፈትሽ ከዚያም የቀበሌውን ገበሬ ሁሉ ሰብስቦ የተንከሰ ታፋ ሲመረምር ዋለ። በካሣሁን ቤት ያደረገው ፍተሻ ከሌሎቹ ረዘም ያለ መስሎ ታየው። ጨርሶ ሲሄድ ካሣሁን ላቀረበለት ጥያቄ ጉዳዩን በማቃለል ዓይነት ትከሻውን ነቅነቅ አድርጐ የሰጠው መልስ «ገና ነው። እስቲ ወደ ፊት ደግሞ እናያለን » የሚል ነበር።

ሳምንት ሞላ። ምንም አዲስ እንገር አልታየም። ካሣሁን ስንት ዓይነት መላ ምት እየሰጠ፤ ራሱም በዚህም በዚያም እያውጠነጠነ የመጠበቅ ትዕግሥቱ አለቀና በድጋሚ ለማመልከት ወደ ወረዳው ሄደ።

በአሁነኛው ጊዜ የወረዳው ጉዳይ ተቀባዩ ፖሊስ በጣም በተሰላቸው ሁናቴ ተቀበለው። «አንተ ነህ እንዴ እንደ ገና የመጣኸው! » አለው ከጠረጴዛው ቀና ብሎ። እንዴት እንዳስታወሰው ካሣሁን ራሱ ገረመው። ስንኳን በአንድ ቀን ስንት ጊዜ ተመላልሰውባቸው የማያስታውሱ ሹሞች ሞልተዋል። አያስታውሱም የረሱ የሚመስሉ አሉ።

«አዎ እኔው፣ ነኝ ጌታ » አለ ካሣሁን እንደ ቆመ።

ፖሊሱ በመታከት ሁለት ክንዱን አጣምሮ ከጠረጴዛው ላይ አስደገፈና ቀና ብሎ ተመለከተው። «ምን ጉዳይ አመጣህ ደሞ አሁን? »

«ያው ነዋ ጌታዬ። የአቶ ከበደ አሟሟት ምርመራ ከምን ደረሰ ብዬ ለማወቅ። »

«አዎ ጐረቤትህ ወዳጅህ ነበር። በዚህ ላይ የማኅበሩ ሊቀ መንበር ነህ። ስለዚህ በአንድ ቀን ምርመራው ለምን አልታወቀም ነው የምትለው » አለ ጉዳይ ተቀባዩ ፖሊስ በቀጠነ ፌዝ። «እኛ ደግሞ ባለብን ኃላፊነት በየቀኑ በወረዳው ብዙ ወንጀሎች ይፈጸማሉ። ከባድም ቀላልም። ታዲያ አንተ የምትለው የኔ ጓደኛ ጓደኛ ከሁሉ ቀድሞ ይመርመርልኝ ነው። ሌላውም እንደዚሁ ነው የሚለው። እኛ ደግሞ የራሳችን የአሠራር ደንብ አለን። ስለዚህም ማንም አሳቢና ጐትጓች ሳያስፈልገን ኃላፊነታችንን ዐውቀን ነው ማንኛውንም ጉዳይ የምንፈጽመው። »

«ሥራችሁ መዓት መሆኑንማ መች አጣሁት ብለው » አለ ካሣሁን በአክብሮት አነጋገር። «ግና መቸስ ማስቸገሬ የሰው ደም ለዚህ ለለውጡ መንግሥት የሚቆረቆር ሰው ደም ደመ - ከልብ ሆኖ እንዳይቀር ብዬ እንቅልፍ ቢያሳጣኝ ነው አንጂ። እንደ ተባለው በውሻው የተነከሰው ሰውዬ ከተገኘኮ አንድ ውል ተገኘ ማለት ነበር። »

«በውሻ የተነከሰው ሰው ፍለጋ ድፍን ወረዳ እስክናዳርስ ጊዜ ይወስድብሃል። ለሁሉም ሥራችን ነው፥ አሳሳቢ አንፈልግም ብየሃልሁኮ። ለምርመራችን የሚረዳ መረጃ አግኝተህ ከሆነ ስጠን። »

«እኔ በምን አቅሜ። »

«ወደ ፊትም ካገኘህ ናና ንገረን። ሌላ ጉዳይ ከሌለህ ይኸው ነው። » ማሰናበቱ ከቢሮው እንዲወጣ ትእዛዝ ጭምር ነበር።

ካሣሁን በሁናቴው ግራ ትጋብቶ ወደ ቆሬ ተመለሰ። የቀድሞው መንግሥት የባላገር ጠር ዘራፊና ቀማኛ የሆነ አንድ ጭቃ ሹም ምስለኔ ተገደለ ብሎ አገር ምድሩን በአፈርሳታ ያስጨንቅ ነበር። በመብላት የጉልተኛ ነገረ ፈጅ ሆኖ ድሀ በማጉላላት በአገር ምድሩ የታወቀ ፖሊስ ተገድሎ በመገኘቱ ሕዝቡ በተደጋጋሚ በአፈርሳታ ከተጉላላ እብኋላ በቲስ አምስት ብር እንዲከፍል ሲታዘዝ ከችግሩ ብዛት የተነሳ እምቢ በማለቱ ግርግር ተፈጥሮ ስንት ሰው በጥይት የተደበደበበት የዘይኔ ወንድም ማሩ የተገደለበት እርሱ ራሱም እስከ

አዲስ አባባ ለመስደድና እስር ቤትም ለመግባት የደረሰበት በዳገታማ ሚካኤል የተፈጸመው አስቃቂ ድርጊት ትዝ አለው። ያም በዝቶ ሕዝቡን አስመረረ። አሁን ደግሞ የተገላቢጦሽ ድህ ገበሬም ቢሆን ለለውጡ መንግሥት የቆመ ሰው በአሰቃቂ ችካኔ ከእነ ሚስቱ ሲገደል እንደ እርሱ አስተያየት ጉዳዩ በቸልታ መያዙ አስገረመው፤ አናደደውም።

በዚሁ ሰሞን አንድ ቀን ምሽት ራት ሲበሉ እርሷና ለሎች ሴቶች ምንጭ ወርደው ውሀ ሲቀዱ ዘርጋው የተባለው የከልካይ ወዳጅ ሚስት የተናገረችውን ዘይኔ አጫወተችው። «እግርዋን ስትታጠብ በአለንጋ የተተለተለችው ገና ጨርሶ ሳይሽር ከባትዋ እስከ ጭንዋ ድረስ እንደ ሐረግ ተጋድሞ አየንና ምን ሆነሽ ነው ስንላት ዘርጋው ገርፎኝ አለች። ምን አጥፍተሽ ነው ብንላት ከልካይ ከቤታችን መጥቶ ከከተማ የመጡት ትንሽ አረኢ ነበርና እሱን እየጠጡ ሲያወጉ ለምን ደጋግመሽ ቀና ብለሽ አየሽው ብሎ ወደ ውጭ ወጥተው ቆይተው ከተመለሱ በኋላ ገረፈኝ አለች። የባታ ለት ነው።

«ታዲያ ቀበጥባጣ የሆነች ሚስቱን ቀጣና ምን አዲስ ነገር አድርገሽ ታወሪያለሽ? » አለ ካሣሁን ሊረሳው የሚፈልገውን የቅናት ነገር ስላነሣበት እንደ መበሳጨት ቃጥቶት በማጥላላት።

«የባታ ለት እኮ ነው » አለች ዘይኔ ትልቅ ምሥጢር እንደምትገልጥ ዓይነት።

«ቢሆንስ በባታ ሆነ በአቦ በሥላሴ፣ ሴት ልጅ ጨንገር አይንካት የሚል ሕግ አለ? » በመሰላቸት ከገበታው እንደ መነሣት ከጀለ።

«ጋሼ ከበደ የተገደለው እኮ የባታ ለት ነበር። »

«እና? እና? » አንድ ቁም ነገር እንደ ያዘች ታወቀና ነቃ አለች።

«እናማ እነሱ ደሞ የዛን ለቅ ቆሬ አልነበርንም ብለው ለመርማሪው ተናግረዋል አሉ » ስትል መለሰችለት።

አገጩን በሁለት መዳፉ ደግፎ፥ በመደነቅ ራሱን ነቀነቀ።

«እንዲህ ነበር ነገሩ? »

የመጀመሪያ ሐሳቡ ወዲያውኑ ወደ ወረዳው ሄዶ አዲስ ያገኘውን መረጃ ማሳወቅ ነበር። ከበደ በተገደለበት ምሽት እነ ታፈሰ ቆሬ ከነበሩበት ለመርማሪው ፖሊስ ምን ለፖሊስ ብቻ ለሁሉም ነው ያወሩት - የሐሰት ቃል ሰጥትዋል ማለት

ነው። ሐሰት መናገር ቀድሞም አሁንም ወንጀል ነው። ከዚህም በቀር ለምን ሐሰት ተናገሩ? ምህኛት ቢኖራቸው ነው እንጂ! በሌላ በኩል ነገሩን ሲያየው ደግሞ ነገሩን አቃልሎና ተሰላችቶ ያሰናበተው የወረዳው ፖሊስ ከበደ በተገደለበት ምሽት በቆሬ መገኘታቸውን ብቻ እነርሱ ለመግደላቸው እንደ በቂ ማረጋገጫ አድርጎ እንዳማይቀበለው ተሰማው። እንደ ታዘበው የፖሊሱ ሁናቴ «አንተን ምን አገባህ? ምን አስጨነቀህ? » የሚል ዓይነት ነው። የካሣሁን ስሜት ደግሞ ወንጀለኞቹ ከእነከልካይ አካባቢ እንደማይወጣ ይነግረዋል። በዚህ ጊዜ «ከበደ እንደ እብድ ውሻ ተፈጥፍጦ ሊቀር » ሲል ብርቱ ቁጭት ያድርበትና ተበቀል - ተበቀል ያሰኘዋል። እንደሚችልም ያውቀዋል። ግሩም የሆነች ‹ሽጉጤ› ምንሽር ጠመንጃ ታስንቃለች የሚላት ከሙሔ ጋር መሆነኛ ደርሳ ለማኅበሩ ስብሰባ የሚጠራ ይመስል በያንዳንዱ ቤት እየሄደ መዝጊያ ሲከፍቱለትና ወጣ ሲሉለት አናት አናታቸውን እየፈጠፈጠ መጣል ቀላል ነው። ወይም ደግሞ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ከማኅበሩ አዳራሽ ድረስ እያስጠራ ሲመጡለት ከበሩ ጥግ እየጠበቀ በየተራ ሊቀነድባቸውም ይችላል። ከዚያ በኋላስ? በረሃ መግባት ነው። በረሃ መግባቱ ስንኳ አላስፈራውም ነበር። ሌላው ቀርቶ ገድሎ ወዲያውኑ ቢሞት ደንታ አልነበረውም። ግን የበቀል ስሜት ባወራጨው ጊዜ የሚገታው የሙሔ ምክር ነበር።

-የሰው ሕይወት የመጨረሻው ክቡር ነገር ነው። ፈሪዎች ጨካኞች ናቸው፡ ፍርሃታቸውን ያሸነፉ ወይም ያጠፉት እየመሰላቸው የሰው ሕይወት ለማጥፋት ይጣደፋሉና። እርግጥ ደጅና ይገድላል። ግን አዛኝ ነው። ርኅሩኅ ነው። መግደልም ቢኖርበት ሕይወት ማጥፋት ደስ አይለውም - ብሏቸው ነበር። ታዲያ ራሱ አሁን ማድረግ የሚከጅለው የፈሪ ነው የጀግና ሥራ? እርግጥ ወንጀል የፈጸመ በሕግ ቅጣቱን ማግኘቱ ተገቢና ትክክልም ነው። ራሱ ከሳሽ ራሱ ዳኛ ሆኖ ራሱ በራሱ ሲበቀል እንደ ጀግና መግደሉ ነው ወይስ በትምክህት ሕይወት ማጥፋቱ ነው? በዚህ ላይ በበቀል ስሜት ተነሣስቶ ከሚገድላቸው ሰዎች መካከል ምናልባት በወንጀሉ የአልነበሩበት ንጹሐን ቢኖሩስ?

ይህ የሙሔ መንፈስ ጥሪ ሐሳቡን ሲጫነው ወደ ከበደ ቤት ይሄድና ዙሪያውን ገባውን ይፈትሻል። ምን ለማግኘት እንደ ፈለገ ራሱም አያውቅም። ግን ፖሊሱ በዐይን በማይታይ የጣት ምልክት ስንኳ በቂ መረጃ ሊሰጥ ይችላል እንዳለውና በኋላም ከተገደውልው ውሻ አፍ እንደ ተገኘው ነገር ምናልባት ፖሊሱ ከመቻኮሉ የተነሣ ሳይደርስበት የቀረ ምልክት እንዳለ በማለት ነበር። ከመሠረቱ ነገሩ ለካሣሁን አዲስ አይደለም። ዱሮም ቢሆን አግጣጫ በኮቴ

መከታተል የቆየና አዲስ ኮቴ በእሕቲጉ መለየት ውሻ ጠረን እንዲያሽት ማድረግ ሰው የገደለ ቋንጃ የቆረጠ ከብት የነዳ ጕተራ የሰረሰረ ወንጀለኛ ለመያዝና ለአደንም ጊዜ ሀገሬው ሲተቀምበት የኖረ ዘዴ ነው። አሁንም ከፖሊሱ እንዳየው፤ መርፌ የሚፈልግ ያህል አተኩሮ ጥቃቅኑን ነገር ሁሉ ቢፈትሽና ቢመረምር ምንም ነገር ሳያገኝ ቀረ።

ካሣሁን አውጥቶ አውርዶ ቢያምኑትም - ባያምኑትም እንደ ማስረጃ ቢቆጥሩትም ባይቆጥሩትም ከበደ የተገደለ ሌሊት ከነከልካይ ቆሬ ያደሩ መሆናቸውን ለመንገር ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ሄደ።

በአሁነኛው ጉዞው የወረዳው መርማሪ ፖሊስ በጉጉት ተቀበለው። «መጣህ እንዴ? ጐሽ! ጐሽ!። እንፈልግህ ስለ ነበር እኛንም ከድካም አዳከን » አለው መፋቂያ ነክቶት የማያውቀውንና በሲጋራ የበለዘ ጥርሱን እያሳየ።

«ወደ መንደራችሁ ልንመጣ ስንል ነው የመጣኸው። »

ካሣሁን በመጀመሪያ እንደ መዝናናት ብሎ ነበር። ግን ከፖሊሱ አስተያየት ከፌዝ፣ ፈገግታው ከአነጋገሩ ቃና የአደጋ ጠረን ድንገት እንደሚሰማት አውሬ አንድ ዓይነት ጥርጣሬ ወዲያውኑ ውልብ አለበት፡

«ለምን ነበር የፈለጋችሁኝ ጌታው » ሲል ካሣሁን ጠየቀ መረጃ የመስጠቱን ሐሳብ ቀይሮ።

«ለዚያው በመንደራችሁ ለተፈጸመው ወንጀል ነዋ! »

«ለሱማ መችም ጥርጣሬየንም የማውቀውንም ተመላልሼ አመልክቸ ነበር። »

«አዎ! በጣም ተባብረዋል። ችግሩ ምን መሰለህ? ማስጠርጠር ብቻውን አያዋጣም። ስላንተም ደግሞ አንዳንድ ወሬና ጥቆማ ደርሶናል። »

ካሣሁን ቀደም ሲል ዳር ዳርታው አለማማሩ ቢታወቀውም እንዲህ ግልጥ ብሎ ሲመጣበት ከተቀመጠበት መፈናጠር ቃጣው። «የምን መጠቆም? አፈርሳታ ስንኳ በወፍ የሚጠቆም ወንጀለኛ ነው። ስለይህ የኔው ላይ ጥቆማ ምንድን ነው? »

«ሳታውቀው ቀርተህ ነው እንድነግርህ የምትፈልገው? » ሲል በትዝብት ተመለከተው። ካሣሁን ከመገረም ጋር ጥቂት አሰባና ነገሩ ሲገለጥለት ለምን አስቀድሞ እንዳልታየው በራሱ ተናደደ።

«ገባኝ! » አለ።

«ምኑ? » ሲል ፖሊሱ እንደማያውቅ ጠየቀው።

«የእረኞች ዘፈን! » አለ በደፈናው ንዴት እየወጠረው።

«ምን የሚል የእረኛ ዘፈን? » የፖሊስ ጥያቄ የፌዝ ነበር።

«መልሼ ራሴን አልሰድብም! » አለ ካሣሁን ጥርሱን ማፋጨት እየቃጣው። «ግን በሰማይ ነፍሱን ይማርና እኔና አይዋ ከበደ ተወያይተንበት ፍጹም ውሸት መሆኑን አምኛለሁ። በመኻላችን ፍቅር እንጂ ቅያሜ አልነበረም።

«አንተ ነህ የምትል እንጂ ምስክር የለህ! »

«ታዲያ ይህ ባይኖን ኖሮ ወንጀለኛው እንዲያዝልኝ እያልኩ ከዚህ ድረስ ምን አመላለሰኝ! » አለ ካሣሁን ፊቱን ጭፍግግ አድርጎ።

ፖሊሱ ከትከት ብሎ ሣቀበት። «ነገርህ አንድ ተረት አስታወሰኝ » አለና ከእግር እስከራሱ አስተዋለው። «በሀገራችን አነጋገር ብልጥ ለብልጥ ዐይን ብልጥጥ እባብ ለእባብ ይተያያል በካብ ይባላል። ታዲያ በዚህ መሠረት ተረቱን ልንገርህ። የአራዊት ንጉሥ የሆነው አንድ አሮጌ አንበሳ ታሞ ከቤት ይውላል። አራዊት ሁሉ እንዳመቻቸው እየተመላለሱ ይጠይቁታል። ከአራዊቱ መካከል ተኩላና ቀበሮ እርስ በርሳቸው በጣም ይቀናናሉ። ተኩላ ነጋ ጠባ እየተመላለሰ አንበሳን ሲጠይቅ ቀበሮ አለመምጣቱን ተመለከተና በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም ቀበሮን ይወነጅል ገባ፤ ‹ጌታው አንበሳ፥ ቀበሮኮ እርስዎን አይወድም። አያከብርዎትም። ስለዚህም ነው እኛ አሽከሮችም ሁሉ እንዲህ ስንጨነቅ አንድ ጊዜ ብቅ ብሎ ያልጠየቀዎ እያለ ሲናገር ቀበሮ ደረሰና የመጨረሻውን ንግግር ሰማ። አንበሳም በቁጣ በቀበሮ ላይ አጓራ። ቀበሮ ግን እንደ ሌሎቹ አሽከሮቹ በጊዜው ሊጠይቀው ያልመጣበትን ምክንያት ለማስረዳት እንዲፈቀድለት ለመነ። ‹በል ተናገር እስቲ! ግና ምን የምታስረዳው አለና ነው!› አለው አንበሳ። ቀበሮ ‹አሁን ከዚህ ከተሰበሰበው የአራዊት መንጋ ጌታውን ያገለገለ ለጌታው ሕመም የተጨነቀ እንደኔ ማን አለና ነው የሚቆጡኝ። እኔ ጌታዬ ከሕመምዎ የሚድኑበትን መድኃኒት ከሐኪም ለመፈልገ አገር ምድሩን ሳዳርስ ነው የሰነበትኩት። እና ደክሜ አልቀረሁም አገኘሁልዎ› አለው። አንበሳም መድኃኒቱ ምን እንደሆነ በጉጉት ጠየቀ። ቀበሮም ‹ትኩስ የተኩላ ጉበት መብላት ነው ጌታዬ› አለ። ተኩላም እዚያው በዚያው ዋጋውን አገኘ ይባላል። ምሳሌው ሤረኛ

በራሱም ላይ ያሤራል ማለት ነው። አንበሳን በሕግ ብትመስለው ግልጽ ይሆንልሃል። »

ካሣሁን ስለ ተጠቀሰበት ተረት ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ፖሊሱ ዘብ ጠራና «ማረፊያ አስገባው » አለ።

## ፳

ኅዳርና ታኅሣሥን ይዞ የወይዘሮ ዘርፈሽዋ ስሜት በየጊዜው ሲለዋወጥ ቆየ። እንደሚሰሙት ወሬ እንደሚወጣው መግለጫ እንደሚነገረው ዜና እንደሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ከካርቱም እስከ ዶሎ ከዚህም ከዚያም እንደሚተላለፈው መልክት ስሜታቸው አንድ ጊዜ ይሞቃል - ይግላል - እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ፤ ዛሬ ያጡት የትናንት ኑሮዋቸው ክብር ማዕረጋቸው ነገ የበለጠ አምሮ ሲደገም ይታያቸዋል። ምን እንደሚሠሩ ዕቅድ ያወጣሉ። በተወረሱት የከተማ ቦታ ላይ የሚሠሩት ሠማይ ጠቀስ ሕንፃ በቆሬ መሬታቸው ላይ የሠፈሩትን ጭሰኞች ሁሉ አስነስተው የሚያቋቁሙበት ዘመናዊ የትራክተር እርሻ ከዐይነ ልቦናቸው ፊት ድቅን ይላል። የተወረሱትን የከተማ ቦታ ሌላ ሰው ተመርቶ ቤት እንዳይሰራበት ለማረጋገጥ ሄደው ያዩበት ጊዜም አለ። እንደዚሁም አንድ ጊዜ፥ ደሴ ሄጂ ዘመዶቼን ጠይቄ በዚያው እግረ መንገዴን የቆሬ መሬቴን አያለሁ ብለው ተነሥተው ጸጥታው አያስተማምንም ተብለው በወይዘሮ ሽዋዬ ከተመከሩ በኋላ ነበር የቀሩት።

ሌላ ጊዜ ስሜታቸው ይቀዘቅዛል። ይኮማተራል። እንደ ሞኝ ሐረግ አንዴ የሚለመልመው ተስፋቸው ወዲያው ተመልሶ ይደርቃል። እንደ ጊዜው ውዥንብር እንደ ወቅቱ የነፋስ አግጣጫ የሚለዋወጠው ሁናቴአቸው ወሎ ልከውት በመሆነኛ ተራራ ላይ ሙቶ ከቀረው አማናዬ የበለጠ በኰሎኔል ደመላሽ ላይ እንዲተማመኑ ከውሀ ሙላት ነፍሱን ለማዳን እንደሚጥር ሰው እንዲንጠለጠሉለት አደረጋቸው። ሙጥኝን የማለት ያህል። ሙጥኝነታቸው ግን በፊት ከማናዬ ጋር ከነበራቸው «ወንድ የማስቀመጥ » ግንኙነት ዓይነት ሳይሆን ልዩ መልክና ደረጃ የያዘ ሥነ ልቦናዊ ግንኙነት ሆነ።

ማናዬ ታዛዥ ትሑት ቅምጣቸው ነበር። በጊዜያቸው ግቢውን ሲያተራምሱትና የሚይዙትን የሚለቁትን የሚቀጡትን የሚምሩትን በሚያጡበት ጊዜ ማናዬ እንደ ቤት አሽከሩ ሁሉ እንደ ልጁ ሁሉ አብሮ

ይችላቸዋል። በገሐድ ደብድበውት ባያውቁም የቁጣቸው ማሳረፊያ ነበር። ትእዛዛቸውን ተቀብሎ ስድባቸውን ውጦ ሲያባሩት ገለል ብሎ መልሰው ሲጠሩት በሁናቴው አይግድጐ፤ ይቅርታ በመጠየቅ አኳኋን ቀርቦ ከዚህም ሁሉ በላይ «ሂድ እንደ ወንዶቹ ግደል ወይም ሙት » ሲሉ፥ በማያውቀው በማይሰማው ጀግንነት መሆነኛ ተራራ ላይ ወድቆ የቀረ ውሽማቸው ነበር።

ደመላሽ ግን እንደዚህ ገራም ውሽማ አልሆነም። አንድ ቃል ሲናገሩት ሁለት ሦስት ይመልስላቸዋል። ልኮሳተር ቢሉ እሱው የባሰ ይሆንባቸዋል። በማናዬ እንደ ለመዱት ለማዘዝ ቢቃጡ ዐፈር ድቤ የሚያስገባ ቁጣውንና ግልምጫውን ያወርድባችዋል። ይህን ጠባዩን እስከዚህም አለጠሉበትም። «መቸም ወንድ ልጅ ኮስተርተር ማለቱ አይከፋም » የሚል ስሜት አደረባቸው። ታዲያ አንድ ጊዜ እንደ ልማድም ሆኖባቸው ለመፈታተን ለመቀናጣትም ሲሉ «ደምዬ እስቲ ማርካቶ ሂድና አንድ ነገር ገዝተህልኝ ና » አሉት።

«ምን? ከፋኝ አልተቀናጣሽም ሴትዮ! » ደመላሽ የውትድርና ስፖርትና ጥሬ ሥጋ ያዳበረውን ትከሻውን የባሰ አሳብጦ ገላመጣቸው።

«ምን ነውር አለበት? » ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በበኩላቸው የተኮሳተሩ መሰሉ። በቤት ውስጥ ሁለቱ ብቻቸውን ነበሩ።

«ድንቄም! የዛሬን አያድርገውና እኔም በጊዜው እንዳንተ ያለውን አሥር ሃያውን አንጋጋው ነበር። » ነገሩከአፋችወ የወጣው በአሽከሮቻቸው ላይ ሲያደርጉት እንደ ኖሩት ሳይታወቃቸው፥ በልማድ ነበር።

ደመላሽ መልስ ሳይሰጥ የሱሪውን ቀበቶ ብቻ በቅጽበት ላጥ አርጐ አወጣ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሚያዩት ነገር እውነት መሆኑን ለማመን ፋታ ሳያገኙ ቀበቶውን እንደ ጅራፍ አዞሮ ለመጠጣቸው። በግርፊያው ግፊት ሳይሆን በድንጋጤ እንዘፍ በለው ከትልቁ ፎቴ ላይ ወደቁ። ባለቤታቸው ደጃዝማች ገሠሠ ከሞቱ ወዲህ ለመግረፍ ቀርቶ ለመቃጣት ስንኳ ሰው እጁን ሲያነሣባቸው ይኸ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። «እ! ትመታኝ » አሉ በሰለለ ድምፅ እንዳይጮሁ ከውጭ ሰው እንዳይሰማ የሚል ግብዝነትና ድንጋጤ ባንድነት ድምፃቸውን አንቆባቸው።

«አዎ! እንዳቺ ላለው የሚበጅ መድኃኔት ይኸው ነው » እያለ ደመላሽ በቀበቶው በገላቸው ላይ ሲያርፍ እንደ እሳት የሚያቃጥል ሥቃይ እየለቀቀባቸው፤ ስሜታቸውና ሐሳባችው ደግሞ ሌላ ነገር ነበር የሚያልመው - ጀግና ወንድ ነው መዋረድ የማይወድ - ወንድ ልጅ የሚያፈቅራትን ነው

የሚደበድብ የሚቀጣ ሌላዋንማ ንቆ ተጠይፎ ዞር ብሎም አያያት። የወዳጅ በትር ቅቤ ነው ቁልምጫ ነው ተብሎ የለ! የእኔ ባይሆን በቆጨኝ! - » የሚል ሐሳብና ስሜት። ሥቃዩ ሲጠናባቸው ድምፃቸውን ውጠው እየተንሰቀሰቁ «ደምዬ የኔ ጌታ፣ የኔ ቁጡ፥ በእናትህ አጥንት በአቡዬ በቁልቢ ገብርኤል፤ በፍጡነ ረድኤቱ - ሁለተኛ አይለምደኝም! » ሲሉ ተማጠኑ።

«ከደጃዝማች ሞት ወዲያ ዐይኔ ደርቋል። አንጀቴ ቆርጧል » ይሉ ያልነበሩትን ያህል እንባቸው በገፍ ወረደ። ልቅሶዋቸው ግን የደስታ አይሉት የሀዘን የሠቀቀን አይሉት የእርካታ እንደ ሙሽራ ልቅሶ ያለየለት ነበር።

ደመላሽ ቀበቶውን ወለሉ ላይ ጣል አደረገና ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተጋድመው ከተገረፉበት ፎቴ ጫፍ ላይ ተቀመጠ። «ደምዬ እንዲህ ጫካኝ ነህ! » አሉ እየተነፋረቁ። ቆሬ ይዘውት ሂደው በዚህ ወንድነቱ ለውጥ መጣ ብሎ ትከሻው ያበጠ ጭሰኞቸውን ሁሉ በጅራፍ እየሞሸለቀ ሲያባርርላቸው ታያቸው።

«አንዳንድ ጊዜ የእርማት ቅጣት የሚያስፈልግሽ መሰለኝ » የተነፋ ኳስ በሚመስል ጉንጫቸው አሁንም የሚወርደውን ዕንባ አየና እንደ ማዘን አለላቸው። መልሶ እንደ ማባበልም እንደ ዋዛም መዳፋን በታፋቸው ላይ ጣል ሲያደርግ የሕመም ሳይሆን አንድ ዓይነት ትኩሳት መላ ሰውነታቸውን ወረራቸው።

-አዎ! ወንድ ልጅ የሚወደውን ነው የሚቀጣው የሚመታው - የሚለው ዘይቤ እንደ ገና በሐሳባቸው መጣ። «ግና ግና አላስተረከኝም እኮ! እስቲ እየው » ሲሉ ቀሚሳቸውን በባታቸው በኩል ወደ ላይ ገለጥ አደረጉት። ጥቁር ደም የተቋጠረበት የሚመስል መሥመር እየተመሰቃቀለና እየተደራረበ ተጋድሟል። «አልተረፍኩም! እህህ! » እንደማቃሰት ቃጣቸው።

«ግን የአንቺው ጥፋት ነው! » አየሽ እኔ የሚያናድድ ነገር አልችልም። አልሰሬ ይነሣብኛል። ደመላሽ ሳይታወቀው የግርፋቱን መሥመር ቀስ እያለ በጣቱና በመዳፉ ይዳሰስላቸው ጀመር።

ከጥቂት ሴኮንድ በፊት የተገረፉበት ቀበቶ ከወለሉ ላይ ተጋድሞ እንዳለ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሌላ ዓለም ውስጥ ገቡ።

# ፳

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በቀበቶ አስተናጋጅነት ከዚያ በፊት የማያውቁትን የሥነ ልቦናና የስሜት ዓለም ካዩ በኋላ እንደ ሃያ ዓመት ኮረዳ በደመላሽ ፍቅር ከነፉ። እንደ ወትሮው ከሚሽት ጋር መጋራት ፈጽሞ የማይዋጥላቸው ሆነ። ምን ጊዜም ከአጠገባቸው የማይለይ የግላቸው፥ የብቻቸው እንዲሆን እሳቸውም የብቻው እንዲሆኑ ፈለጉ። ደመላሽ ደግሞ ለዚህ ፍላጐታቸው ፈቃደኛና አመቺ ሆኖ አልተገኘላቸውም። ብዙ ጊዜ አብሮዋቸው ያመሻል። አንዳንድ ጊዜ ያድራል። ግን ተጠቃልሎ አልያዝላቸው አለ። ታዲያ በተለያቸው ቁጥር በዚያ ቀበቶው ሚስቱን ወይም ሌላ ሴት አገላብጦ ገርፎ የጐበረበውን ገላ በእጁ እያሻሸ ሲያባብል ከዚያም ደግሞ እንዲያ - እንዲያ ሲሆን በሐሳባቸው እየታያቸው ቅናት ያብገነግናቸው ጀመር።

ይህን የመሰለው ችግር የተለመደውን መላ ፈልጉ። የፍቅር መድኃኒት።

አንድ ቀን እንደ ዋዛ፥ «አንቺ ሽዋዬ ለመሆኑ የሰማሽው ጥሩ መድኃኒት ዐዋቂ ሰው አለ? » ሲሉ የምሥጢር ተካፋይ ጓደኛቸውን ጠየቁ።

«ዛሬ ምን ዐዋቂ አለ ብለሽ። ለመሆኑ የምን መድኃኒት? »

«እንዲያው ማንኛውም! » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በማድበስበስ መለሱ።

«ማንኛውም መድኃኒት ብሎም ነገር የለ። እንደየበሽታው እንደየጉዳዩ ዓይነት ነው። ምን አለፋሽ መዋሸቱን እንደሁ አታውቂበትም! » ወሬ የማያመልጣቸው ወይዘሮ ሽዋዬ ያሞራ የመሰለ አንገታቸውን አሰግገው በትዝብት አስተዋሏቸው።

«ኮረኔል አስቸገረሽ እንዴ? »

«እኔ ዘርፌ! ኤጭ ምን ባልኩሽ እቴ! »

«ንሣ! አደባባዩ ሁሉ የሚያውቀውን? ቢሆንስ ምን አሳፈረሽ! አልመነኰስሽ፤ በአንቺ አልተጀመረ። »

«ሰው ቀጣጥሎ ነው የሚያወራው ባክሽን! »

«ያም ሆነ ይህ ኮረኔል ደና አድርጐ መያዙ ለአንቺም ብቻ ሳይሆን ለጉዳያችንም ይበጃል። »

«ለሱማ ብዬ ነው ቤቴን እንደራሱ ቤት አድርጎ እንዲወጣ እንዲገባ ያደረኩት! » ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ስለ ተሰጠላቸው ወይዘሮ ዘርፈሽዋ ደፈር ዘና አሉ።

«እና ችግርሽ በሱ በኩል ከሆነ » ወይዘሮ ሸዋዬ ጥቂት አሰቡ። «አዲሳባ እዚያ ኮልፌ አንድ ጥሩ ዐዋቂ ነበር። መድኃኒቱ የሚያላውስ። አሁን አዳሪ ነው ብለው ታስሮዋል አሉ። ፍቸም አንድ ሰው ነበር። እስከዚህኳ የታወቀ አይደለም። ደሞ አውሮፕላን የለ መንገዱ ይርቅብሽ ይሆናል እንጂ፣ ከሁሉም በጣም የታወቀ ባለ ዝና የሆነው ጅማ ከተማ ያለው ሱዳን ነው። በተለይ እንዲህ ላለው ጉዳይ መድኃኒቱ ከቶ አይስትም አሉ። »

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሚፈልጉት መድኃኒት ለተባለው ጉዳይ መሆኑን ሳያምኑ ምን ማድረግ እንዳሰቡም ሳይገልጹ ጭውውቱን ወደ ሌላ ቀየሩት።

ግን ጊዜ አላጠፉም። ከችኮላቸው የተነሣ ቁልቢ ገብርኤል መሳለማቸውን በማስታጐል የፊታውራሪ ወርቃለማሁን አውቶሞቢል ከነሹፌሩ ተውሰው በሁለተኛው ቀን ወደ ጅማ ወረዱ።

ኀምሳ ብር ከፍለው መድኃኒቱን ማግኘት ቀላል ነበር። ችግሩ የመጣው መድኃኒት ለደመላሽ ከመስጠቱ ላይ ነበር። ለራሳቸው የተሰጠው መድኃኒት ባላደረ ውሀ እየበጠበጡ እስከ ሦስት ቀን ሰወታቸውን የሚቀቡት የቅጠላ ቅጠል ዱቄትና በጨርቅ ውስጥ እንደ ክታብ ተሰፍቶ እንዳመቻቸው በብታቸው ወይም በአንገታቸው የሚያደርጉት ሥራ - ሥር ወይም በአንገታቸው የሚያደርጉት ሥራ - ሥር ወይም ጽሑፍ ነገር ነበር። ለደመላሽ የሰጣቸው መድኃኒት ደግሞ ሌላ ዓይነት ነበር። በቀለሙ የቅጠል ጭማቂ የሚመስል የኪኒን ብልቃጥ መስሎ ፈሳሽ ነው። «ይኸን አንቺ በጅ - በጅ፤ በታዝማ - በጣዝማ ማር ጋር እስከ ሰባት ቀን ጧት - ጣት በጅ በጅ ትጠጫለሽ ልክ ይመጣል! » ብሏቸው ዐዋቂው። ጅማ ከዳር አገር ድረስ ይመስላል። በዚህም ምክንያት ሰውየውን በጥሞና ለማነጋገር እስከዚህም ጊዜ አላገኙም። ግን፥ እንደ ተጠራጠሩት መድኃኒት ዐዋቂውም ቢሆን በዚህ በለውጡ ምክንያት የጨዋውን ልጅ መኳንንቱን ወይዛዝርቱን በጥሞና ማነጋገር የሚፈልግ አይመስል። በዚህ ላይ በለውጡ በጥሞና ማነጋገር የሚፈልግ አይመስል። በዚህ ላይ ትብትብ ካለ አማርኛው የያዙት በጣም የተወሰነው ነው። ‹ጧት ጧት በጣዝማ ማር እያደረጉ ራሳቸው በእጃቸው ሰባት ቀን መሰጠ› እንዳለባቸው ነው የገባቸው።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከመድኃኒቱ አስጣጥ መመሪያ በጣም የነካቸው ራሳቸው በእጃቸው ማጠጣት መሆኑ ነው። ራሳቸው እንደሚቀበሉት ነገርና እንደሚያስሩት ክታብ፥ መድኃኒቱ የሚሠራው ለሚያጠጣው እጅ ብቻ ከሆነ ራሳቸው ብቻ መስጠት አለባቸው ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ሰባት ቀን ሙሉ በእርሳቸው ቤት ማደር ወይም ጧት ጧት በባዶ ሆዱ መምጣት አለበት ። መድኃኒቱ ከሥራ በኋላ የጠየቁትን ሁሉ የሚፈጽም ይሆናል። እስከዚያው ግን በዚያ ጋግርታም ጠባዩ በቀላሉ እሺ ማለቱን ተጠራጠሩ። ምናልባት ለጊዜው ፈቃደኛ ሊሆን ቢችልም ሰባት ቀን ሙሉ ያለ ማቋረጥ ይፈጽማል ማለት የማይመስል ነገር ነው። ታዲያ በምንም ዓይነት መንገድ ዐዋቂው ባዘዘውመሠረት መድኃኒቱን ከእጃቸው እንዲጠጣ ማድረግ አለባቸው።

ዘዴ ፍለጋ አንድ ቀን አእምሮዋቸውን ሲበጠብጡ ዋሉ። እንዲህ - ብለው እንዲህ ይለኛል። እንዲህ፣ ቢለኝ እንዲህ እለዋለሁ - እያሉ ከራሱ ጋር እንደሚከራከር ተሟጋች ለሚያቀርቡለት ምክንያት በእርሳቸው ግምት ደመላሽ የሚሰጠውን መልስ አብረው እያሰላሰሉ ብዙ ዓይነት ውሸት ፈጠሩ። ብዙ ዓይነት ብልሀት ቀመሩ። ደመሩ። ብዙ ዓይነት ዘዴ ቋጠሩ። ፈቱ። ሌላ ሞከሩ። በመጨረሻ ከሁሉም የተሻለ የመሰላቸውን አንድ መላ ጨብጠው ያዙ።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ነገሩን ሁሉ አሰበውና አቅደው እንዳዘጋጁት ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ወጥ ቤትና ማድ ቤት ከምትላላከው ገረድ በስተቀር ሁለቱ ብቻቸውን ሆኑ። ዘለቃ ከወዳጅዋ ጋር ቢሸፍቱ ወርዳለች። ሌሎች ሰዎች የሚመጡት አመሻሽተው ነው። በእርሳቸውና በደመላሽ መካከል ያለው ከለጋ የሸኖ ቅቤ የተዘጋጀው ክትፎ አልጫና ቀይ ዶሮ ወጥ፥ ቅንጬ፥ ለጋ የብረት ምጣድ ጥብስ አልጫ፥ ፍትፍት በኮንትሮባንድ የመጣ ብላክ ሌበል ጆኒ ወከር ውስኪ ከአምቦ ውሀና ከበረዶ ጋር የተከማቸበት ማዕድ ቤት።

ከወይዘሮ ዘርፈሽዋ፣ ከክትፎ፥ ከዶሮ ወጡ ከለጋ፣ ጥብሱ እያፈራረቁ ደመላሽን ያጉርሱት ጀመር። ለመቅዳት የዊስኪውን ጠርሙስ አነሡ። ደመላሽ ለሁቱም ሁለት መዳፉን ጋረደው። «በርበሬውም፤ አልኮሉም ከመጠኔ አልፏል። እንዲያውም አልሰሬ በዚህ ሰሞን ብሶበታል። »

«ታዲያ መድኃኒቱን መውሰድ ነዋ! » አሉ፣ በማቆላመጥ እንደ ቅጠል እየረገፉ።

«ያዲሳባ ሆስፒታልና መድኃኒት ጨርሻለሁ። ያባሰብኝም እሱ ነው። አሁንማ ጨጉራዬ ከናካቴው ሳይበጣጠስ ይቀራል ብለሽ ነው፥ በመድኃኒት። » ደመላሽ ሆዱን ዳበሰ።

«ሌላ ፍቱን መድኃኒት ተገኝቷላ! » ከወገባቸው በላይ ያንን ግዙፍ ሰውነታቸውን በገበታው ላይ ደፋ አድርገው በዐይናቸው አባበሉት። እሺ ቢለኝ ምናለበት አምላኬ - እያሉ በሆዳቸው።

«ኤዲያ ፍቱን ነው እየተባለ ያልጠጣቱት ያልዋጥኩት፤ ያልተወጋሁት መድኃኒት የለም። » ደመላሽ በመታከት አኳኋን እጁን በእጁ ጠረገ።

«አሄ እኮ ከዋልድባ ገዳም የመጣ ነው። »

«ምን? »

«አዎ! አዎ - እኔ » ሲሉ ጀመሩና - ሚስትህ የወዳጅህ እኅትህ፣ እናትህ ለእርሳቸው እንደሚጥማቸው የሁለቱን ግንኙነት የሚጠሩበት ቃል ጠፉባቸውና ላንዳፍታ ተደናግረው ቆዩ። «እና እኔ ዘርፌዋ » ሁሉ ወዲያው ቀጠል አድርገው «ይሄንን ሁሉ ጊዜ ሥራ አልፈታሁም ነበር። ይሄ አልሰር አለብኝ ካልከ ጊዜ አንሥቶ እንዲህ ስትሠቃይ ሳይ ሥራ አፍለታሁም ነበር። ይሄ እንዴትስ ብዬ። አንድ ነገር ፉት ብለህ አንድ ነገር ቀምሰህ እንዲያ ስትሆን? ታዲያ አለ የተባለውን ሰው ሁሉ ሳስጠይቅና ሳማክር ለኅዳር ጥዮን አክሱም የሄደ አንድ ዘመዴ ዋልድባ ገዳም ገብተው ከሚኖሩ ባሕታዊ መድኃኒቱን ይዞልኝ መጣ፡፡ ከብቃታቸው ብዛት የሚሠወሩ ናቸው አሉ። ከዋሻቸው የሚወጡበትም በዓመት አንድ ጊዜ አክሱም ጥዮንን ለመሳለም ብቻ ነው። »

«አልሰር አሁን የዘመኑ ሥልጣኔና ብስጭት ያመጣውን በሽታ፣ የገዳም ባሕታዊ የት ያውቀዋል ብለሽ? » አለ ደመላሽ እንደ ዋዛ።

«ለእኛ ለፍጥረቶቹ መዳኛ ሲል አንድዬ ነዋ የሚገልጥላቸው። ደሞስ መድኃኒት ዐዋቂው ሁሉ በመጀመሪያ ራሱ በሽተኛ የነበረ መሆን አለበት ይባላል? »

የደመላሽ የእሺታም የእምቢታም መልስ ሳይሰጣቸው ነገሩን በቸልታ ያለፈው በመምሰሉ እንደ መናደድ ቃጣቸው። ትዕግሥት፣ ሲሉ መልሰው ራሳቸውን ገሠጹት። አሁን የያዙት ጉዳይ በንዴት፣ በቁጣ የማይሆን ነው። አልሆንላቸውም ብሎ ነው እንጂ ወትሮውንም ቢሆን «ትዕግሥተ ግባ ወዳናቴ » የሚለው ዘፈን ጥሩ ምክር መሆኑ ይታወቃቸው ነበር። ከታኅሣሥ የእነ

መንግሥቱ ንዋይ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በኋላ በጸጸት የወጣ ነው ሲባል ሰምተዋል። የአሁኑ ሰው ሁሉ ቀን ወጣልን ብሎ ነው ቂን - ቂን ከሚል ያንን ምክር ቢያዳምጥ ምን አለበት? እያሉ ብዙ ግዜኤ ከራሳቸው ጋር ተወያይተውበታል። «እና ከነገ ጀምረህ ብትጠጣው የዛሬ ሳምንት በሽታው የነበረብህ መሆኑን ከነ ጭራሹ ትረሳዋለህ። ስንቱን የመድኃኒት ዓይነት ስትጋት ኑረህ አሁን ዋናው ሲገኝ ችላ ይባላል ማ ይሙት? ጤንነትህ እኮ ለአንተው ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ይበጃል። ጤንነት ከሌለ ያሰቡትን መፈጸም የት ይቻልና! » ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቅቤ ሳያቀልጥ የሚቆሳ ከሚመስል ማባበል ጋር ውትወታቸውን ቀጠሉ።

«እሺ ከመሰለሽ እንዳልሽ፤ እንዴት እንደሚጠጣ አሳይኝና እወስደዋለሁ » አለ ደመላሽ፤ እንደ መታከት ዓይነት።

«እህ! ከዚህ ነው እንጂ የምትጠጣው። ጧት - ጧት! »

«ለምን? »

«ነዋ! »

«አልገባኝም። ከዚህ ሆነ ከዚያ መጠጣት እንጂ ሌላው ምን ቁም ነገር አለው! »

»አለው! አሳምሮ አለው እንጂ » ሲሉ ትንሽ በተኮሳተረ አኳኋን መለሱ። መድኃኒቱን ሚስቱ ብታጠጣው የተገላቢጦሽ ለእርሷው ይበጃታልና ከናካቴው ጠቅልላ ስትነጥቃቸው ድንገት በሐሳባቸው ታያቸው። እንደ መንገሽገሽ ቃጡ። «አየህ መድኃኒቱ ብዙ ጣጣ አለው » አሉ ስሜታቸውን እንደ መግታት እየሞከሩ። «ይኸንን ዋናውን መድኃኒት ከጠጣህ በኋላ ወዲያው ደግሞ የቁብ እንቁላል ገና የመጀመሪያዋ ከሆነ የጊደር ወተት ጋር ሳይውል ሳያድር እየተመታ መጠጣት አለብህ። ስለ እንቁላሉ የሆነ እንደሆነ ከዚሁ ከቤት ተፈልፍላ ያደገች ቁብ አሁን እንቁላል መጣል ጀምራለች። ወተቱንም ሰሞኑን ወይዘሮ ሸዋዬ የወለደች ጊደር አለች። ጧት - ጧት ሰው እየላክሁ አስመጣልሃለሁ። እና የሚሻለው እንዳመቸህ ከዚሁ እያደርክ ወይም ጧት ጧት እየመጣህ ባሕታዊው ያሉትን መፈጸም ነው።

«ታዲያ ዶሮዋን ልውሰዳታ! » አለ ደመላሽ በቀልድ መልክ።

«እህ! የዶሮ ጠባይኮ በጣም ከባድ ነው። ግቢው ሲለወጥባት መጣሉን ብታቆምስ? »

«እንግዲያው! ጧት - ጧት ሰው ልላክ ወይም ያንቺ አሽከር ያምጣልም። » ደመላሽ ሐሳቡን ያቀረበው በጉዳዩ ተጨንቆ ሳይሆን እንደ ዋዛ ነው ፡

«ወቸው ጉድ! የእኔ አሽከር ጧት ጧት እንቁላልና ወተት እየያዘ ቤትህ ሲመጣ ሚስትህ አትጠይቅም? ከየት ነው ብላ? ወይስ የእርስዋ አሽከር እየመጣ የግቢዬን የውስጥና የውጭ ገበና ይንገራት? »

«ብትጠራጠርስ ሳታውቅ ቀረች ብለሽ ነው እስከ አሁን? »

«ቢሆንስ - ቢሆንም፤ በይህ በወታደሩ ሥራህ አሳምረህ እንደምታውቀው አጉል አንተን መሆንም አያስፈልግም መሰለኝ። በእኛም ባገራችን ወግ መክደን ሲቻል ዕቃ ከፍቶ ማሳደር የሰነፍ ሙያ ነው ይባላል። እና የሚሻለው የሚቀለው መድኃኒቱን ከዚህ ብትወስድ ነው። »

የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ምክንያት ያለማቋረጥ ቢደረደርም፤ ደመላሽ ጉዳዩ ከምሥጢረ ሥላሴ እንቆቅልሽ ስለ ሆነበት ቁርጥ ባለ እምቢታም ሆነ እሺታ ሳይቋጥሩት እንድ እተንጠለጠለ ቀረ። ከዚያም ሲወጣ ሲገባ ሲያርፍ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ያባባሉ የገሥጹና ያኲረፉ እየመሰለ ጧትም ማታም ነዘነዙት።

«እሺ እሺ እንዳልሽ » አለ ከሁለት ቀን በኋላ። «የሚሠራ ከሆነ ከነገ ጧት ጀምሮ ከዚሁ አንቺው ታጠጪኛለሽ። » አነጋገሩ የጥርጣሬ ቃና ነበረበት። እርግጥ የሃምሳ አለቃ ሆኖ የሙቶ እልቅና ለማግኘት በጊዜው ዝነኛ ከነበሩት ድቤ ሲመታ ከሚያድርበት ከቀኛዝማች ማሞ ቤት ሦስት ቀን ደጅ ጠንቷል። እሱ እንደ ተመኘው ባለ ውቃቢው እንደ ተነበዩለት አልሆነም። ቦረና ነገሌ ዶሎ፥ ዘምቶ ከአገልግሎቱ ጋር እንዲያው እንዳጋጣሚ ነበር የሙቶ እልቅና የተሰጠው። ከዚያም ገዳም ሠፈር አንዲት ልጅ ወዶ ገንዘብ ሲያጥረው ሻምበል ለመሆን ከዚያ በኋላ ደግሞ አሁን ሦስት ልጅ የወለደችውን ድንገት የቴጌ መነን አሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ የነበረውን ድንገት አስረግዞ ነገር ዓለሙ ሲደነጋገርበት ለቁልቢ ለደብረ ሊባኖስ ለዜና ማርቆስ በትክክል የማስታውሰው ነገር ተሥሎ ነበር። ግን ተበድሮም ተለቅቶም በዚህም በዚያም ብሎ የችግሩን ጊዜ ዐለፈው እንጂ እንዳሰበው የችግሩን ጊዜ ዐለፈው እንጂ እንዳሰበው ባንዳፍታ ሎተሪ ስላልወጣለት ሥለቱ የደረሰለት አድርጎ አልቀረውም። ሥለትም አላደረሰም ነበር። አሁንም እሺ ያለው በነገሩ እስከዚህ ከልብ ነበር የሙቶ እልቅና የተሰጠው። ከዚያም ገዳም ሠፈር አንዲት ልጅ ወዶ ገንዘብ ሲያጥረው ሻምበል ለመሆን ከዚያ በኋላ ደግሞ አሁን ሦስት ልጅ የወለደችለትንና ያን ጊዜ የቴጌ መነን አሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ የነበረችውን

ድንገት አስረግዞ ነገር አለሙ ሲደነጋገርበት ለቁልቢ ለደብረ ሊባኖስ፣ ለዜና ማርቆስ በትክክል የማያስታውሰውን ነገር ተሥሎ ነበር። ግን ተበድሮም ተለቅቶም በዚህም በዚያም ብሎ የችግሩን ጊዜ ዐልፎ እንጂ እንዳሰበው ባንዳፍታ ሎተሪ ስላልወጣለት ሥለቱ የደረሰለት አድርጎ አልቆረጠውም። ሥለትም አላደረሰም ነበር። አሁንም እሺ ያለው በነገሩ እስከዚህ ከልብ ስላመነበት ሳይሆን ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ንዝንዝ ለመገላገል ነበር። ንዝንዛቸው የከረረ ቅሬታ እንዳያስከትል የሠጋበት ምክንያት ደግሞ ነበረው።

ንጉሡ በጄኔቫ ባንክ ውስጥ አስቀምጠውት ከነበረውና ደርግ ጠይቆ ከተከለከለው በብዙ መቶ ሚሊዮን ብር የሚቆጠር ገንዘብ ከፊሉ ለአልጋ ወራሹ ተሰጠ የሚል ወሬ ሰሞኑን ጐልቶ እየነፈሰ ነው። ይህ ከሆነ አልጋ ወራሹ ወይም ልጃቸው ወደ ዙፋናቸው እንዲመለሱ፣ በመኸልም በዳር አገርም ሆነው ደርግን ለሚታገሉት ወገኖች በርከት ያለ እርዳታ መላኩ የማይቀር ነው። ካለበለዚያማ ያንን ያህል ገንዘብ ብቻቸውን በልተው አይጨርሱት።

ታዲያ ለብዙ ዓመታት ያጠራቀመው የሀብት ቅሪቱ እየሸሸ በሚሄድበት ወቅት የድለላውን ሥራ በብሔራዊ ቲአትር በአንበሳ ቡና ቤት በአራት ኪሎ ቡና ቤቶች በራስ መኰንንና በትሪያኖን ቡና ቤት በቃኘው ሻለቃ ሆቴል እየተኰለኰለ የሚሻው ጡረተኛ እየበዛ በሄደበት ወቅት አልጋ ወራሹ አይጠላም። ደግሞም በእርሱ ግምት ጦር ሜዳ ሂዶ ባይዋጋም በሐሳብም፣ በእቅድም በሌላው - በሌላም ከማንንም ያላነሰ ከደርግ ጋር እየታገለ ነው። በሕይወቱ ፈርዶ - በሕይወቱ ቆርጦ።

ችግሩ መሳፍንቱና መኳንንቱ በዝርያ ሐረግ እየተጠቃቀሱ ከፍተኛውን ጉዳይና ቁም ነገር እርስ በርሳቸው ማካሄድ አለመተዋቸው ነው። እንደሚገምተው እርሱ ምንም ያህል ቢዋጋላቸው የከፉ ቀን ታማኝ ይባላ እንጂ አሁንም ለአልጋ ወራሹ የሚቀርቡት ወህኒ ቤት ውስጥ ካሉት ጋር እነ ወይዘሮ ሸዋዬ ይሆናሉ። ለወይዘሮ ሸዋዬ ደግሞ ከእርሱ ይልቅ የምሥጢር ተካፋያቸው ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ናቸው። ከአልጋ ወራሹ የሚላከው ገንዘብ ድልድልም ከዚሁ ዓይነት አሠራር አይወጣም ይሆናል።

ደመላሽ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጋር የሚያፈልግ ቅሬታ በመፍጠር ዕድሉን መዝጋት ያም ባይሆን ማበላሸት አልፈለገም። «ከመሰለሽ እሺ ልሞክረው። ግን ሰባት ቀን ሙሉ! »..... ደመላሽ ፈቃደኝነቱን በድጋሚ ከአረጋገጠ በኋላ ስለ ጊዜው ርዝማኔ ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው።

«እንዲያው ነው እንጂ የኔ ጐበዝ! ወትሮውንምኮ ቀላሉን ነገር አክብደህ ያየኸው። » ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በደስታ ፈነደቁ። «እና ዛሬ ከዚሁ አድረህ ጧት - ጧት አጠጣሃለሁ። ከደስታቸው የተነሣ በቀልድ ቅጣት ክንዱን እንደ መቆንጠር አደረጉና ራሳቸው አምነውበትም ይሁን የመድኃኒቱን ክብር ለርሱ ለማሳመን «ታዲያ በጨዋ ደንብ ነው የምታድረው። ጥላ ሆነው መድኃኒት ማጠጣት ቀርቶ በእጅም አይነካም። አሉ። - የፍቅር ጨዋታ የሚከለክል የፍቅር መድኃኒት ምን ይሉታል - የሚል ሐሳብ ወዲያው በአእምሮዋቸው መጣና ከት - ከት ብለው ሣቁ።

«ምን ያሥቅሻል? »

«አህ? ሣቅሁ እንዴ? » ሲሉ ራሳቸውን የታዘቡ በመምሰል ጠየቁ። «አንዳንድ ጊዜ እኮ ሰው ደስ ሲለው ወይም እንዲሁ የሚያሥቀውን ሳያውቀው እንዲሁ ይሥቃል። አንድ ጊዜ እኔና ዘለቃ ፒያሳ ስንዘዋወር ሞዳ ኖቫ ከነበረበት መብራት ኃይል ፎቅ በራፍ ላይ ሰው ተሰብስቦ ይሥቃል። የሚያሥቅ በሽታ ገባ ተብሎ በራዲዮ ሲነገር እንደ ሰማነው ዓይነት። ገረመኝና ዘለቃ ጠጋ ብላ የሚሥቀውን አንዱን ‹ምንድን ነው?› ስትል ጠየቀችው። አሁንም እንደገና ሣቁን ለቀቀውና፥ ‹ኧረ እኔ እንጃ ሰው ሁሉ ሢስቅ ነው ማየት » ሲል መለሰላት። እኔም እንዲያ መሆኔ እንደሆነ። ወይም አሁን እንደ ተሣለቁብን ደሞ እኛ የምንሥቅበት ጊዜ መምጣቱን እሱ ከስቶልኝ ቢሆን ደሞ እሰዬው ነው። አይደል? »

«እንዲህ ይሄ ሁሉ ጐበዝ እየተሟሟተ ይህማ የማይቀር ነው! » ሲል ደመላሽ አከለ።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከመድኃኒቱ ውጤት ጋር ደመላሽን የሚያሥቁበት ጊዜ መምጣቱ የማይቀር ስለ መሆኑ እየታሰበባቸው ቆሬ በሚሠሩት የገጠር ማረፊያ ቤት ሁለቱ ሲደስቱ በሐሳብ እየታያቸው እንደ ወትሮው ራት ከበሉ በኋላ እንቅልፍ ሳይጫጫናቸው ከራሳቸው ጋር ፈገግ ሲሉ ሌሊቱን አጋመሱት።

ደመላሽና ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በበነጋው ጧት ዕለቱን የጀመሩት በየራሳቸው እቅድ ነበር። ደመላሽ መድኃኒቱን ጠጥቶ ወደ ጉዳዩ ለመሔድ ነበር። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ደግሞ መድኃኒቱን ያለ ማቋረጥ ስለ መጨረሱ ጥርጣሬ አድሮባቸዋል። በተለይ «ሰባት ቀን ሙሉ!..... » በማለት እንደ ዋዛ መጥቀሱ በጣም ከነከናቸውና ለክፉም ለደጉም በሦስት አራት ቀን ለማስጨረስ ሲሉ የሁለት ቀን የሚሆን መድኃኒት በአንድ ጊዜ አጠጡት።

ከመድኃኒቱ ጠባይ ይሁን በመብዛቱ ምክንያት ደመላሽ እንግሊዝ ጨው እንደ ጠጣ ሆዱ ታመሰና አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይነዳው ጀመር። አንድ ሁለት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ቀኑን ሙሉ መጸዳጃ ቤት አመላለሰው። መጸዳጃ ቤት እስኪያገኝ ፋታ የሚሰጥ ስላልመሰለው ከዚያው መዋል ግድ ሆነበት።

«አንቺ ምኑን ነው ያጠጣሽኝ? » እንደ መሥጋት ብሎ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልን ጠየቃቸው።

«ሲሠራ ነዋ! ሲሠራ! ኮሶ እንኳ የሚያሽረው አስቀምጦ ነው » ሲሉ መለሱ።

«አንጀቴ ከወጣ ምኑን ዳንኩት ብለሽ! ግን ሕመም ስላልተሰማውና ሆዱን ስለ ቀለለው እምብዛም አላሰበም። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል «ተቅማጥና ወስፋት ባዶ አይወድም » እያሉ መረቅና የአልጫ ፍትፍት ደጋግመው መገቡት። ማምሻውን ሰውነትን ዝልፍልፍ የሚያደርግ ከባድ ድካም ያዘውና ከዚያው ሰውነቱን ዝልፍልፍ የሚያደርግ ከባድ ድካም ያዘውና ከዚያው አደረ። ጧት አሁንም ለሁለት ጊዜ የሚሆነውን መድኃኒት አጠጡት። በሁለተኛው ቀን ተቅማጡ ቀለል ቢልለትም ድካሙ እየባሰበት ሄደ። እየቆየም የአካል መዛል ብቻ ሳይሆን አእምሮው እየፈዘዘ እንደ ጫት ምርቃት እጋታና ሰላም የሰፈነበት ሰመመን ይወስደው ጀመር። ወደ ቤት የመሄዱ ወይም እንዳይጨነቁ ማስታወቁ ጨርሶ ከሐሳቡ ጠፋ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግን በሁናቴው በመደናገጥ ፈንታ የበለጠ ተበረታቱ። ሰመመኑና የአእምሮው መፍዘዝ፥ መድኃኒቱ እየሠራ መንፈሱን ሲለውጠው መስሎ ተሰማቸው። መድኃኒቱን ጠጥቶ ጨርሶ ሰውነቱን መልሶ ሲጠናከር፥ ስለ እርሳቸው የሚኖረው ስሜት ታያቸው።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የወደፊት የፍቅር ዓላማቸውን ብቻ ሲያሰላስሉ የሰው ባል ሦስት ቀን ከቤታቸው ሲያስቀምጡ ምን ጥያቄ ሊያስከትል እንደሚችል በሐሳባቸው አልመጣም ነበር።

## ፲

የደመላሽ ሚስት ቆንጅት ትዕግሥቷ አለቀ። በቃት።

ደመላሽ ብዙ ጊዜ ሰዓት እላፊ ሊደርስ ጥቂት ደቂቃ ሲቀረው አንዴ ‹ክበብ ስጫወት ሰዓት እላፊ ሞላ፤ ሌላ ጊዜ ለጉዳይ ደብረ ዘይት ሄድኩ የሚል ምክንያት እየሰጠ ደጋግሞ ውጪ ሲያድር በቁጣ ሳትገነፍል በጭቅጭቅ

አትነዛነዝ ቤትክን ተረከበኝ ሳትል ለብዙ ወራት የሆድዋን በሆድዋ በትዕግሥት ይዛ ቆየች። ነጋድራስ አገኘሁ በውድቀት ሌሊት ደውለው በጥርጣሬ መርፌ ከወጋጓት ወዲህ ነገሩ ሳይሰማት ቀርቶ ምክንያቱን አምናለት ወይም ተስፋ ቆርጣም አልነበረም - ትታገሥ የነበረው። እንዲያውም ጠባይዋ ገታራ ቢጤ ነው። ግን የወታደር ሚስትነቷ ሕይወት የገራላት አስተሳሰብ ደግሞ ነበር። ለግዳጅ ከመኻል እስከ ዳር አገር እየተላከ ዓመት ሁለት ዓመት ሲቆይ ምንም ያህል ሚስቱን ቢያፈቅር እንደ ቆራቢ ተቆጥቦ ተለጉሞ ይመለሳል የነበረው የቦሎቄ እርሻ ከነትራክተሩ በአዲስ አበባ ሦስት መቶ ብር ይከራይ የነበረ ቤት በትርፍነት ሲወረሱባቸው ይህም አልበቃ ብሎ ከእርሱ በታች የነበሩት አሁን ደርግ ሆነው የተገላቢጦሽ ያለ ዕድሜው ጡረታ ሲያስወጡት እየተበሳጨ አጉል ጠባይ ቢታይበት - ለቤቱ፥ ለትዳሩ ለልጆቹ ማሰቡን እስካልተወ ድረስ - ምንም ምንም ችሎ ማሳለፉ ተገቢ መስሎ ተሰምቷት ነበር። ሁለት ቀን ሙሉ ሲጠፋ ግን የትዕግሥትዋ ወሰን ተጣሰ።

ሰዓትዋን አሥር ጊዜ እያየች እስከ አምስት ሰዓት ጠብቃ ከነጋድራስ አገኘሁ ቤት ደወለች። ጥሪው ከአራት ጊዜ በላይ አቃችሎ ልትዘጋው ስትል «ሀሎ » ሲል በእንቅልፍ የጐረነነ ድምፅ መለሰ።

«ነጋድራስ ነዎት? »

«ነኝ! ማን ልበል? አጠያየቃቸው የሥጋትም የቁጣም ዓይነት ነበር።

«እኔ ቆንጅት ነኝ። እንደምን ሰነበቱ? »

«እንዴ! ቆንጅት አንቺ ነሽ እንዴ? ድምፅሽ የሌላ መሰለኝ እኮ። ምነው ምን ሆናችሁ? ደመላሽ ደህናም አይደለህ? » ድምፃቸው መርዶ ለመስማት የጓጓ መሰለ።

«አይ! እሱስ ደህና - ነው መሰለኝ » አለች ቆንጅት ጥያቄውን እንዴት እድነምትመልስ ጥቂት ግራ ተጋብታ። «ብቻ ጠፍቶ ስለ ዋለ አግኝተውት እንደሆነ ብዬ ነው። »

«ኧረ እንዲያው ሰሞኑንም አላየሁት። አሁን - አሁንማ ብዙም የማንገናኝ ሆነ። » ቆንጅት እየተራራቁ መሄዳቸውን የገለጹበት ምክንያት ወዲያው ተሰምቷት ‹የዝንብ ጠንጋራም እናውቃለን› አለች በሐሳቧ። «ለመሆኑ የት እንደ ሄደ አልነገረሽም? »

«እናንተ ማምሻውንም ወደ ሰንዳፋ እህል ላመጣ መሄዴ ነው ብሎኝ ነበር። » አለች ቆንጅት የቤተሰብ ምሥጢር የባቄላ ወፍጮ አለመሆኑን እየታሰባት።

«ከበብ ለምን አትደውዪም? ከዚያ ነው የሚሆነው። »

«ሞክሬአለሁ። »

«ከዚያው ቤትስ? » ነጋድራስ ስም ያልጠቀሱበት በይፋ የታወቀ ለማስመሰል ሆን ብለው ነበር።

«እሱን ስለማላውቀውማ ነው የደወልኩልዎት። » የወይዘሮ ዘርፈሽዋል የቴሌፎን ቁጥር ነገሩዋት። «ለመሆኑ ሠፈሩ የትነው? » ስትል እንደ ዋዛ ጠየቀች።

ከነገሯት በኋላ «ሌላ የምረዳሽ ነገር አለ? » አሉ ነጋድራስ ቴሌፎኑን ከመዝጋታቸው በፊት።

ወዲያው ቀጥላ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት ስትደውል ከጭንቅላቱ ላይ የሰው ልጅ ተቀምጦ የሚጠባበቅ ይመስል ገና በመጀመሪያው ጥሪ መልስ አገኘች።

«የት ነው? »

«የት ብለው ደወሉ? » የሴት አይሉት የወንድ የጃንደረባ የመሰለ ድምፅ ነበር።

«ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት። »

«ነው። »

«እባክዎ ኮሎኔል ደመላሽን ነበር የፈለግሁት » አለች ቆንጅት አስቀድማ እንዳቀደችው ደመላሽ ከዚያ በፊት ለመኖሩ እርግጠኛ በመምሰል። ቢያቀርቡላት ግን ምናልባት ቴሌፎኑን ከመዝጋት በስተቀር ምን እንደምትለው አልወሰነችም ነበር።

«ማ - ነበር የሚ - የለም - ኮሎኔል ደመላሽ የሚባሉ ከዚህ የሉም » ብለው ዘጉባት።

ቆንጅት ከመናደድ ይልቅ ነገራቸው አስደነቃት። - ዛሬ አልመጣም፤ ወይም ለጊዜው የለም - ቢሉ የሚመስል ነገር ነበር። ደመላሽን ጨርሶ እንደማያውቁት ‹የሚባሉ የሉም› ሲሉ ግን ውሸታቸውን ግልጽ አረጉት። በዚህ ላይ ደግሞ ‹ማን ነበር የሚፈልጋቸው?› ብለው ለመጠየቅ የቃጡ ከመሰሉ በኋላ ነበር፥

ሐሳባቸውን የቀየሩት። ‹እንግዲህ አርጐም አወሻሽት የለ!› አለች ቆንጅት ከራስዋ ጋር.....

ነጋድራስ አገኘሁ ባመለከቷት መሠረት ቆንጅት የወይዘሮ ዘርፈሽዋልን ቤት ማግኘት ምንም ያህል አላስቸገራትም። ያስቸገራት የግቢውን በር አንኳኩታ፣ አሽከር ከፍቶላት ስትገባ ልቧ ከወትሮው በበለጠ ፍጥነት መምታቱ ነበር። ረፋዱ ላይ ነው። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የገናውን መሰናዶ ለመሰለል ወደ ጓዳ ጐራ ብለዋል። ለመጠየቅ የመጣሁ ዘመዳቸው ነኝ ስላለች እስኪመጡ ሳሎን እንድትቆይ ተነግሮዋት ፊቷን በኩታዋ ሸፈንፈን አድርጋ ቁጭ እንዳለች አንድ ሰው ከመጸዳጃ ቤት ወደ መኝታ ቤት አለፈ። ቆንጅት አንገቷን ደፋ እንዳደረገች ወደ ማድ ቤት በሚያወጣው መተላለፊያ ላይ ያተኮረችው ወይዘሮ ዘርፈሽዋልን ገና ከሩቁ ለመጠባበቅ ነበር። በስም ብቻ እንጂ በመልክ ስላማታውቃቸው ጓጉታለች። በዚህም ላይ ምንም ቢሆን የጐባን ቤት ነውና ጠንቀቅ ማለት ነበረባት። ሰውዬው አላያትም። እርሷም መልኩን አላየችውም። ከላይ የተጐናጸፈው ነጠላ ፊቱን ይጋርደው አንጂ፣ ያ የወታደር አረማመዱ ጐተት ይበል እንጂ፣ ቁመናው የደመላሽ መሆንኑን ወዲያውኑ ለየችው። ከሥር ያጠለቀው ሱሪ የምታውቀው የራሱው ነው። ደመላሽ በጤናው እንዲህ ሆኖ አያውቅም። የታመመ መምሰሉ ግልጽ ነው። ተከትላው ወደ መኝታ ቤት መግባት ቃጣት። ‹ከታመመ ቤት አይደውልም ነበር? ከኔና ከልጆቹ ማን ይቀርበዋል? ካስፈለገስ ሆስፒታል አይሄድም?›

ይህንን ሁሉ ስታሰላስል በመተላለፊያው በኩል ወደ ማድ ቤት በሚያወጣው በር እንደ ፀሐይ ግርዶሽ ሙሉ ጥላ አረፈባት። ከዚያም ጥላው ወደ ፊት እየገፋ ከኋላ የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግድንግድ አካል እየተጐማለለ ተከተለ።

«ጤና ይስጥልኝ? » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የማያውቁት ዘመድ ስለ መጣባቸው እንደ መደናገር ብለው።

ቆንጅት ተነሥተው ወደ በሩ ቆመችና ለአንድ አፍታ ከግር እስከ ራስ ተመለከተቻቸው። የመጣችው ጐባንዋ ምን ዓይነት ሴት እንደ ሆነች በመጀመሪያ ለማየት ነበር። በአእምሮዋ የቀረጸችው ሥዕልም ከ «ፋፋ« ልጃገረድ በመለስ በዕድሜ ከእርሷ ወጣቱ የሆነች፤ ይህም ቢቀር የመኳንንት ዘር እንደ መሆንዋ በማር እየታሸች አድጋ በውበት ከእርስዋ የምትልቅ ሸንቅጥ ቆንጆ ነበር። ትከሻቸው ላይ ነጠላ መሳይ አል አድርገው ሁለት እጃቸውን እቅፍ

ከማይሞላው ወገባቸው ላይ አስደግፈው ተቀርጾ ያላለቀ ድብልብል ሐውልት መስለው ቆመው ስታያቸው ራሷን መቆጣጠር አቃታት። እንደ ነጐድጓድ ያስተጋባ ሣቋን አንዴ ለቀቀችውና ተፈትልካ ከግቢው ወጣች።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከግራሜ ንዝረታቸው ሲመለሱ «አሆሆ! ምን ዕብድ አመጣብኝ እባካችሁ! ወቸው ጉድ! አለባበሷን ላየ አሁን ጤነኛ አትመስልም? ለነገሩማ በዚህ ዘመን ማበድም ሲያንስ ነው » አሉ።

# ፳

ደመላሽ መድኃኒቱን ጠጥቶ ከጨረሰ ተቅማጡ ብዙም ሳይቆይ ተሸሎት ወደ ቤቱ ሲመለስ ቆጅት «ምነው ልጄ ሰው ያስባል፣ ይጨነቃልም አትል? » ከማለት በስተቀር ምንም ነገር የማታውቅ መስላ ተቀበለችው።

«አንድ ጉዳይ አጋጠመኝና ናዝሬት ሄድኩ። ከዚያም ከምግቡ ይሁን ከመጠጡ ወይም ከመንገዱ የጨጓራ በሽታዬ ድንገት በጣም አመመኝና ሦስት ቀን ኃይለ ማርያም ማሞ ሆስፒታል ተኛሁ። የማውቀው ሐኪም አግኝቼ » ሲል መለሰላት። ውሸቱ የባሰውን አንጀቷን አሣረራት። የሆድዋን በሆድዋ ቀብራ አንጀቷን ቋጥራ ቻለችው።

ደመላሽ ሰውነቱ ሙሉ ብርታቱን እንዳገኘ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንደ ጠበቁት ልብሱን ጥሎ ባይከንፍላቸውም ሚስቱንና ቤቱን ጥሎ ጠቅልሎ ባይገባላቸውም፥ እያመሸም እያደረም የፍቅር ግንኙነቱን እንደ ወትሮው ቀጠለ።

ቆንጆትም ጥቃቷን የምትወጣበትን ዘዴ መፈለግ ቀጠለች። መጀመሪያ ደላላ ቀጥሎ ፍድ ቤት አካባቢ ማመልከቻ ጸሐፊ ከዚያም የቤተ ዘመድ ዳኛ በመሆን ወደ ጥብቅና ለተሸጋገረው ትንሽ ወንድሟ አማከረችውና በሰፊው ተወያዩበት።

«ነገሩ ቀላል ነው። በጋብቻ ላይ ጋብቻ የፈጸመ በሚለው የወንጀለኛ መቅጫ አንቀጽ በአውራጃ ፍርድ ቤት የክስ ፋይል መክፈት ይቻላል። »

«ከዚያስ? »

«ከዚያማ የአውራጃ ፍርድ ቤት የቤተ ዘመድ ዳኞች ሰይሞ ወደዚያው ይመራዋል » አለ ትንሽ ወንድሟ የበለዘ ፊቱን እያሻሸ «እና የቤተ ዘመድ ዳኛ

ከሁለቱም ወገኖች በስምምነት የሚመረጡ ስለሆነ መቸም አንዱ መሆኔ አይቀርም። »

«አንተን ዳኝነት ተወውና የሕጉን መንገድ ንገረኝ። »

ቆንጅት ትንሽ ወንድሟን ትወደዋለች። ገና ሰባተኛ ክፍል ሆኖ እርሷ ሁለተኛ ደረጃ ስንኳ ሳትጨርስ የትምህርት ዕድልዋ በደመላሽ ሲቀጭ እምነቷን የጣለችው በእርሱው ላይ ነበር። ፈረንጅ አገር ሂዶ ሐኪም ሆኖ መሐንዲስ ሆኖ ስሙ በሀገሪቱ የታወቀ እንደሚሆን ታልም ነበር። ታዲያ ይህ ሁሉ ቀርቶ አሁን - አሁን ግንበኛ እየተባለ የሚጠራው የፊያሾኮ ቪኖ ደንበኛ በመሆን መወሰኑ ያበሳጫታል። ግን በእርሱም መፍረድ እንደማይቻል ይሰማታል። የመንግሥት መሥሪያ ቤት ግምጃ ቤት የነበሩት አባታቸው ሲሞቱ ባልተወራረደ ሰነድ ለቀለብም ለቤት ዕዳ ቤታቸው በሀራጅ ሲሸጥ የጡረታ አበላቸው ለቀለብም ለቤት ልጆቻቸው አልበቃ ብሎ ቤተሰቡ መበታተን ብዙዎቹ ልጆቻቸው ትምህርታቸውን ማቋረጥ ግድ ሆነባቸው። ወንድምዋ ለጥቅብና መብቃት የቻለውም በስንት መከራ ነበር።

«ታዲያ የቤተ ዘመድ ሸንጎ አንቺ የተበደልሽ መሆንሽ ከአረጋገጠና » ሲል ወንድሟ ንግግሩን ቀጠለ፤ ሽሙጧ ከልብ አለመሆኑን ስለሚያውቅ «ከአመነበት በንብረት አከፋፈል አብዛኛውን በመውሰድ እንድትካሽ ሊወስን ይችላል። ግን በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም የሚለው አንቀጽ አንዱ ችግር ተጨባጭ ማስረጃ ከማቅረቡ ላይ ነው። ብዙ ዳኞች ሁለቱ ወንጀለኞች ክርና መርፌ ሆነው መገኘት አለባቸው ይላሉ። ይገባሽ የለ ክርና መርፌ ማለት ምን እንደሆነ? »

«ቱፍ! » አለች ቆንጅት ሳታስበው ድንገት ንዴትዋ ገንፍሎ።

«በጋብቻ ላይ ጋብቻ ወይም ምንዝርና መፈጸማቸው ቢረጋገጥ ስንኳ ሊያመልጡ የሚችሉበት መንገድ አለ። በሕግ ረገድ። በእስልምና ሃይማኖት ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ስለሚፈቀድ ለመስለሙ ከሸሪአ ፍርድ ቤት ማስረጃ ከአቀረበ በሕግ በኩል ነፃ ይሆናል። ከአሁን ቀደም እንዲህ ያደረጉ አሉ። »

«ምን! ለዚያች ግዳንግድ አሮጊት ሲል ደመላሽ ሊሰልም? አሆሆ ጆሮ የማይሰማው ጉድ የለም። » ቆንጅት ይህን የመሰለ ጉድ መስማት ያልፈለገች ይመስል ሁለት ጆሮ ግንዷን በኁልት እጅዋ ያዘች።

«ከልቡ ባይሰልምም ስለምኩሊል ይችላል። »

«ሁለቱም ያው ነው። የጠበቃ ዐመል ሆኖ አንተ ነገሩን ጥምዝምዝና ወልገድጋዳ አረከው እንጂ፥ እኔ ደመላሽን ፈትቸ ንብረት ለመውሰድ ሐሳብ የለኝም። እሱን መጉዳትም አልፈልግም። ዞሮ - ዞሮ የልጆቼ አባት ነው። እሱም ደህና መሆን የሚበጀው ለልጆቹ ነው። »

«እንደርሱ ከሆነ ታዲያ እኔን ምን አርግ ትይኛለሽ? አርፈሽ መቀመጥ ነዋ! »

»እንደሱ ማለቴ አይደለም! ያች አሮጊት አንዳች አዚም አዙራበት ነው እንጂ ያለ ምክንያት እንዲህ አይሆንም። ስለዚህ እኔ የምፈልገው አሮጊቷን ብቻ ለይቼ በዞረበት እንዳትዞር እስከ መጨረሻው እርም ለማሰኘት ነው። »

በዱርዬ ከማስደብደብ አንስቶ እስከ አንደርቢ ድረስ ብዙ ዘዴዎች እያነሡ ተማከሩ። አላረካትም። በመጨረሻ «ለምን ፀረ አብዮተኛ በለን አናስመታትም » የሚል ሐሳብ አቀረበ።

«ደመላሽ አብሮ እንዳይበከል ነዋ! እሱም ደርግን አይወድም። »

»እኛ እንደ ነገርነው ሴትዮዋን ብቻ ለይቶ የሚይዝ የቀበሌ ወይም ይሄ የሕዝብ ድርጅት የሚሉት ሰው ቀስ ብለን እንፈልጋለን። »

»እንደዚህ እንኳ ይሻላል » አለች ቆንጆት ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተጋድመው ሲለበለቡና ‹አይለመደኝም! አይለምደኝም!› እያሉ ሲጮሁ በሐሳቧ ታይቷት።

# ምዕራፍ አምስት

የአዲስ አበባ ሰማይ በተለይ በስተደቡብ በስሚንቶ ፋብሪካና በሌሎችም ኢንዱስትሪዎች በሚተፋው ጭስ ከመጨገጉ በስተቀር ከዳመና ጠርቷል። ጧት ጧት ከእንጦጦ በኩል የሚወርድ ውርጭ በየቤቱ በየሰው ገላ ውስጥ እየሰረሰረ በመግባት ከእንቅልፍ ያነቃቃዋል። ቀዝቃዛው አየር እስከ ረፋድ ሰፍኖ ከቆየ በኋላ ሙቀት እየተካበት እያየለበት፥ ይውልና ማምሻውን መልሶ ይቀዘቅዛል። እያዲስ አበባን ከተማ ነዋሪ ለሥራ የሚያተጋ ደህና የተፈጥሮ አየር የሰፈነበት ሰሞን ነበር።

አብዛኛው የአዲስ አበባ ነዋሪ ግን በተረጋጋ መንፈስ የሚሠራበት ወይም የሚዝናናበት ወቅት አልሆነም። የአዲስ አበባ ማኅበራዊ አየር ከእለት ዕለት

እየባሰበት የሚሄድ ሙቀትና ውጥረት ሰፍኖበታል። የቀበሌ ተመራጮች የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች የመንግሥት፥ ሹማምንት ግድያ በሚያስፈራ አኳኋን በመቀጠሉ አንዳንዱ በገዛ ጥላው መበርገግ ደርሷል። ጋዜጦች፥ ራዲዮው፥ ቴሌቪዥኑ፥ የሚያዘወትሩት ዜናም፥ በካዛንቺስ፥ በአራዳ፥ በማርካቶ በካፋ በደሴ በሩቅም በቅርብ የሚገደሉትን ጋታዮች የሕይወት ታሪክና በየክፍለ ሃገሩ፥ በየአውራጃው በየሥፍራው ሕዝቡ፣ ፀረ - ሕዝብና ፀረ - አብዮት ኃይሎችን በመቃወም፥ ለማጋለጥ መወሰን የሚደረጉትን ሰላማዊ ሰልፍ ሆነ። በተለይም በስልሣ ስምንት ሚያዝያ ወር ላይ በወጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕራግራም ጐን በመቆማቸው የተቃዋሚ አፈ ሙዝ የተነጣጠረባቸው፥ በተለይ ዋና መፋለሚያ የሆኑት የቀበሌ ማኅበራት መሪዎች፥ በብሔራዊ ሎተሪ ስብሰባ አድርገው፥ ፀረ - ሕዝብና ፀረ - አብዮት ኃይሎችን በማውገዝ ውሳኔ አሳለፉ። ባንድ በኩል ከቀበሌ ማኅበር እየሸሸ እንዲያም ሲል አሻፈረኝ እያለ የሄደውን ሕዝብ መልሶ ለመሳብና፥ በሌላ ኩል ምንም በኅብረት ለመቋቋም ነበር። በተከታዮቹ ቀናት እንደ ታየው ከሆነ ግን ሰዉ እንደ በረገገ ነው። ግድያው እንደ ቀጠለ ነው።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ጭንቀቱንና ውጥረቱን የሚያባብስ በደርግ በራሱ ውስጥ አዲስ ሁናቴ በዚሁ ሰሞን ተከሰተ። ይኸውም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አሠራር መለወጥ ነው። ስለዚሁ የወጣው መግለጫ ‹የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን በሥራ ለማዋል እንዲያመች የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አቋምና አሠራር ተሻሻለ› በሚል አርእስት ተነሥቶ ‹የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ፥ ታሪክ የጣለበትን አብዮቱን የመጠበቅና ሥልጣኑን ለእውነተኛው የሥልጣን ባለቤት ለሆነው ለሰፊው ሕዝብ የማስረከቡን ኃላፊነት በተቀነባበረ ኃይልና ዘዴ ለመወጣት እንዲችል ከአብዮቱ ሂደት ጋር መራመድ እንዳለበት ይታመናል› የሚል ማብራሪያ ቢሰጥም፥ ብዙዎቹ ቃል በቃል አልተቀበሉትም። ከጀርባው ብዙ ምሥጢር እንዳለበት ወዲያው በሰፊው ይወራ ጀመር። ወሬው እንዲሁ ከባዶ የተፈጠረ ሳይሆን ፍንጭ ነበረው። አዲሱ የደርግ አቋም የሊቃነ መናብርቱንና የዋን ጸሐፊውን አቋም በጣም አናግቶታል። ሥልጣን የተጨመረለት አለ፤ በጣም የተቀነሰበትም አለ። ይህም ስለ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትና በጊዜው በትግሉ ሜዳ ስለ ተሰለፉት ቡድኖች ካላቸው አመለካከትና አንጻር ሲታይ፥ በደርግ ውስጥ ከፍተኛ መሸጋሸግና መፋጠጥ ማስከተሉ የማይቀር ሆኖ ተተረጐመ።

ይህ ሁሉ ተደማምሮ በብዙዎቹ የኅብረተሰብ አባሎች ዘንድ የእዝ ሠንሠለቱን እንደ ጠፋበት ሠራዊት ሚና የመለዋወጥ ቡድን የመቀያየር ትርምስምስ አስከተለ። አንድናዱ ወደ አንዱ ሠፈር እንደ መጠጋት ብሎ ቆይቶ አሁን ሙቀቱ ሲያይልበት፥ ‹አብዮት ልጅዋን የምትበላ ከሆነ› የራስዋን ልጅ ትብላ እንጂ፥ እኔ ከዚህም ከዚያም የለሁበትም ብሎ ወደ ኋላው ያፈገፍጋል። ሌላው፥ አዲሱ የኃይል ሚዛን እንደማያዋጣ ሆኖ ያጋደለ መስሎት ከነበረበት ሚና ተፈትልኮ በመውጣት ሌላው ውስጥ ይገባል። አንዳንዱ፥ መቁጠሪያም ምስባሕም ይዞ፥ ‹ይኸ ቢስት ይኸ› እያለ ራሱን እንደሚያታልለው አማኒ በሁለቱም ሠፈር ያነፈንፋል - በቁርጠኛው ጊዜ አሸናፊው ልጥፍ ለማለት። አንዳንዱ ከተሠወረበት ጉድባ ከገባበት ጫካ እየወጣ እጁና መሣሪያውን በመስጠት ራሱን ያጋልጣል። የነበረበትን ቡድን ያወግዛል። ለአብዮቱ ንስሐ መግባቱንም ይገልጻል። ራሱን ያጋለጠው ‹እንዳያስበውላው› ከእርሱ ጋር ፖለቲካ ይሠራ የነበረው ሌላው በርግጎ ይጠፋል። አንዱ ቡድን አባሉን በባለጋራው ቡድን ውስጥ አስርጎ ያስገባል። ይኸኛውም በዚያኛው ላይ እንደዚሁ ያደርጋል።

የሁናቴው ውስብስብነት የተጐለጐለ ልቃቂት ይመስላል። ውጥረቱ፥ ባሩዱ ተለኩሶ በመቀጣጠል ላይ እንዳለ ቦምብ ያስጨንቃል።

ይህ፥ የፍጥጫ፥ የፍትጊያ የድብልቅልቆሽና የትርምስ ማዕበል፥ ዘለቃንም እንደ አዙሪት ሳባት - ሚና ሊያጫውታት።

## ፪

ዘለቃ አዲሱን መሥሪያ ቤትዋን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተላምዳው መጀመሪያ ከአስቀጠራት ሰው ሌላ ወዳጆች እያፈራች ሄደች። በሥነ - ልቦና ስሜት ተመርታ ሳይሆን፥ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ለሚኖራት ዕድል የግድ አሥፈላጊ ነበር። የተቀጠረችው በየሦስት ወር በሚታደስ ኮንትራት ሲሆን በዚሁ ዓይነት ኮንትራት ለብዙ ዓመታት በመሥራት ላይ የሚገኙ ሌሎች ጸሐፊዎች ሞልተዋል። እንዲያውም ቋሚዎቹ ከአንድ የተወሰነ የዕድገት ደረጃ የደረሱና በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ግን ኮንትራቱ ምን ጊዜም አስተማማኝ አይደለም። የወርም ሆነ ሦስት ወር ኮንትራቱንም ከውጭ አሰፍስፈው የሚጠባበቁት ባለዳትሰን፥ በለቶዮታ ባለፔጆ ቆነጃጅት ብዙዎች ናቸው። በሙያ ሳይሆን በሌላ

ያስቀጠረ አንድ ወዳጅ ወረቱ ሲያልቅለት «ሥራው አለቀ ባጀት ተቀነሰ » ብሎ የኮንትራቱ ጊዜ ሲሞላ አሰናብቶ ሌላዋን አፍለኛ ቆንጆ ይቀጥራል። አንድዋ ኮንትራተኛ ከያዘችው ወዳጅ የበለጠ ሥልጣን ያለው ወዳጅና ደጋፊ ያገኘችው ደግሞ ሳይታሰብ ፈንቅላ ትተካለች።

ዘለቃ፣ በመሥሪያ ቤቱ ጊዜያዊ አቀጣጠር መሠረት እንደ ዛፍ ቅጠል ከፊሉ ሲረግፍ ሌላ ማቆጥቆጡ በመካከሉ እንዳንድ ቅርንጫፍ ሆኖ ተተክሎ መቅረቱን የተረዳችው በተቀጠረች ሰሞን ነበር።

በሰዓት ላይ ከቢሮዋ ወጥታ ወደ አውቶሞቢሏ ስታመራ ከአጠገቡ ወገብዋ በአንድ እጅ የሚጨበጥ የመሰለች ሴትሬኖ መኪና ተደግፋ ጠበቀቻት። የአለቃዋን ስም ጠርታ «......ጸሐፊ ነሽ? » ስትል ጠየቀቻት - ዘለቃን።

«አዎ ነኝ። ለምን ነበር? » አለች ዘለቃ ቁንጅናዋን ከራስዋ ቁንጅና አለባበስዋን ከራስዋ አለባበስ በሐሳብ እያወዳደረች።

«እንዲያው ለማወቅ ያህል ነው። ምን ዓይነት እንደ ተካችኝ » አለች፥ የመኪና ቁልፏን መያዣ በጣቷ ላይ እያሽከረከረች። «በአንቺ ላይ ስንኳ ቅያሜ እንጅሩ። ማነች ደግሞ እኔን የፈነቀለች ብዬ ለማወቅ ያህል ነው። እኔ እንኳ አስቀድሜ አብስዬ ስለ ነበር እንዲያውም ከዚህ የተሻለ አግኝቻለሁ። ራሴውም ከእኔ በፊት በተቀጠረች ላይ የሠራሁት ስለሆነ የምልሽ የእጅሽን ይስጥሽ ሳይሆን መልካም ዕድል ነው » ብላት ወደ አውቶሞቢሏ ገባች።

ከዚያም ብዙ ሳትቆይ፥ መንፈቅሉ በእርሷም ላይ እንደ ተቃጣ ተሰማት። ያስቀጠራት ወዳጅዋ ወረት እስከዚህም የተለወጠ ባይመስላትም ከውጭ የሚጠባበቁ ጓደኞቻቸውን ማስቀጠር የሚፈሉት ሌሎች ጸሐፊዎች «የደርግ ሰላይ ናት » «ወዳጅዋ የመረጃ ክፍል ኃላፊ ነው » እያሉ ያስወሩባት ጀመር። ስለ ዲፕሎማቲክ መብታቸው በጣም የሚጨነቁት የውጭ አገር ሰዎች ደግሞ እንደዚህ ያለው ነገር ያስበረግጋቸዋል። ስለዚህ ዘለቃ ድጋፍዋን ለማጠናከር ብዙ ወዳጆች ማፍራት ነበረባት። ወዳጅነቱና ድጋፉ ደግሞ የተለመደ ክፍያ አለው። ፈቃድ ፈጻሚ መሆን ነው።

በዚያ አካባቢ እንደ ተገኘ በቆነጃጅቱ መገልገል እንጂ በቅናት መጋጨት ስለ ሌለ፥ ይህንንም ያንንም መሳቡ መጥለፉ ለዘለቃ ችግር አልሆነባትም። አልፎ አልፎ ችግር የፈጠረባት የማስተናገጃው ሥፍራ ሆኖባት ነበር። ብዙዎቹ ባለሚስት ስለ ሆኑ ቤታቸው መውሰድ አይችሉም። የሆቴል ክፍል በማዘውተሩ ረገድ ስምና አድራሻ ምዝገባው እየተጠናከረ ከመሄዱ በቀር የሚስቶቻቸውን

ጥርጣሬ በመፍራትም ይሁን በሆቴል ማደርን አይዳፈሩትም። ከምሽቱ አራትና አምስት ሰዓት በኋላ መዘዋወሩን እያሠጋ ሄዷል። ከእናቷ ጋር አብራ ከምትኖርበት ቤት ሁልጊዜ የውጭ አገር ሰው እየያዘች መሄዱንም አልወደደችውም። ጐረቤት ዐይኑን ይጥላል። ከዚያም ወሬና ሐሜት ሊፈጠር ይችላል። ከዚህም በላይ ከነ ደመላሽ ከእነ ፊታውራሪ ወርቃለማሁ አንሥቶ ብዙ ሰው ስለሚወጣና ስለሚገባ ለጸጥታ ለሹክሹክታ፥ ጨዋታ አያመችም። ዘለቃ ብዙ ጊዜ አውጥታ አውርዳ የተሻለው ነገር ሲሆን አፓርትማ ለብቻዋ ቤት መከራት ሆኖ አገኘችው።

ዘለቃ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴርና በቅርንጫፍ ቀጣናዎቹም ብታስጠይቅ ተመዝግባ ተራ መጠበቅ እንዳለባት ተነገራት።

«እኔስ ብመዘገብ ምን ያህል ጊዜ ያስጠብቃል? » ስትል ጠየቀች።

«ማን ያውቃል፥ ዓመት ሁለት ዓመት » ትባላለች።

ከዚህ በኋላ ነበር፤ «አንድ ነገር ብለምንህ እሺ ትለኛለህ? » ስትል ዘለቃ የመረጃ ክፍል ወዳጅዋን የጠየቀችው። በኮረብታ መናፈሻ አንድ ክፍል ውስጥ እሱ ከወገቡ በላይ ሸሚዙን እንደ ለበሰ ከወገቡ በታች አንሶላ ጣል አድርጎ በእርካታ ሲጋራ ያጨሳል። እርስዋ ከአልጋው ራስጌ በኩል ካለው ግድግዳ ላይ ከአንጠለጠለው መስትዋት ፊት፥ ጋማውን እንደሚነሰንስ ፈረስ አንዳንድ ጊዜ አንገቷን ሰበቅ እያደረገች ጸጉርዋን ታበጥራለች። በመካከላቸው ከኮሞዲኖው ላይ ጭላጭ የተራረፈባቸው ብርጭቆዎች አሉ። ከአጠገባቸው ትንሽ አውቶማቲክ መሳሪያ ተጋድሟል። እንደ ዋናተኛ በውስጥ ሱሪዋ ብቻ እንደ ሆነች ወደ እርሱ ዘወር አለችና የጡት መያዣዋን እያስተካከለች፥ ምምልለምንህ እሺ ትለኛለህ? ብዙም አስቸግሬህ አላውቅም፤ አንተም ታውቀዋለህ። »

«ምንድን ነው እሱ? » ሲል ጠየቃት ዐይኑን ሳያረግብ በመላ ቁመናዋ ላይ ተክሎ። »

«መጀመሪያ እሺ በለኛ! »

«ሳላውቀው ምን እሺ እላለሁ። የማልችለው ቢሆንስ? »

«የምችለው ቀላል ነገር ነው። ከምጠይቅህ አሥር እጅ የላቀ ማድረግ እንደምትችል ዐውቃለሁ - ኤጭ፤ ይሄ ነገር ደሞ ሲያስፈራኝ - » አለች ድንገት ከውቶማቲኩ ላይ ያረፈ ዐይኗን በመጠየፍ መለስ አድርጋ «በጨዋታ ጊዜ በመዝናኛ ጊዜ ምን ያደርግልሃል! »

«ምን ይደረግ ብለሽ! ለሁሉም ነገር ተጠንቅቆ ተዘጋጅቶ መገኘት አለ » ሲል በተኩራራ አኳኋን መለሰላት።

«እና፥ ለእኔም ጉዳይ ከተዘጋጀህ እሺ አልከኝ ማለት ነዋ! ከአልጋው ላይ ተቀመጠች። »

«በመሠረቱ አላልኩም። አስቀድመሽ አትበይኝ። ግን፥ የሚቻል ከሆነ ምን ቸገረኝ።« ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ።

«ለብቻዬ አፓርትማ መከራየት እፈልጋለሁ። ሁለታችንም እንደ ልባችን ለመሆን ይመቸናል። የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅትን ብጠይቅ፥ የተመዘገበው ተረኛ ስንት ዓመትም አይደርሰውም፣ ስላሉኝ አስጨርሰልኛ! » አለችው በዐኖቿ እያባበለች፣ እያቆላመጠች። ዘልቃ፥ ከቀረጥ ነጻ መጠጥ አንሥቶ ብዙ ጥቅም ወደ ምታገኝበት አካባቢ በማዘንበል የመረጃ ክፍል ወዳጅዋን ችላ ማለት የጀመረች ቢሆንም፥ እሱም በበኩሉ ማማረጫው በዝቶ ነው መሰል፥ እንደ በፊቱ የማያስቸግራት ቢሆንም፥ ቤት የማግኘቱን ጉዳይ ባንዳፍታ ሊጨርስላት የሚችል መሆኑን በማወቅ «ኧረ ናፍቀኸኛል እኮ » ስትል በዚህ ዕለት ሽርሽር እንዲወጡ አፍ አውጥታ የጋበዘችው እርሷ ነበረች። ከመጠየቅ በፊትም አሳምራ በምታውቅበት ሙያ ስሜቱን አሽታዋለች።

«አዎ! በጣም ችግር ነው ዛሬ ጊዜ ቤት ማግኘት » አለ እንደ ዋዛ።

«ላንተ ችግር አይሆብህም። ማዘዝ ትችላለህ። »

«ለማዘዝም እኮ በቂ ምክንያት ያስፈልጋል። ለማስለቀቅም ሆነ፥ በተለቀቁት ቅድሚያ የሚሰጠው ለታጋዮች ነው። አንቺ ታዲያ በታጋይነት አልተመዘገብሽ » ሲል በፌዝ ሣቅ ከንፈሩን አንሻፈፈ።

ዘለቃም ፈገግ አለችና «ስለ ብርቱ ታጋይነቱ ካንተ ሌላ የምጠራውም ምስክር የለኝ። ሌላው ዓይነት ትግል ግን ባፍንጫዬ ይውጣ! - ይልቅስ ከሞከርክ ምንም አያቅትህም። » ዘልቃ ወደ እርሱ ጠጋ እያለች፥ ያሳከካት በመምሰል እንደ በሰለ ብጉንጅ ሊፈነዳ ያሞለሞለ ጡቷን ከመያዣው አውጥታ በእጅዋ ደባበሰችው።

ወዳጅዋ፥ ዓይኑን በደረቷ ላይ እንደ ተከለ ዘለግ ላለ ጊዜ በሐሳብ ተመስጦ ቆየና፤ አንድ ነገር ድንገት ብልጭ እንዳለለት ጣቱን ጧ! አደረገ።

«ምነው? » እርሷም ድንገት ነቃ አለች።

«የምትስማሚ ከሆነ የፈለሽውን ቤት እንድትገኚ ለማድረግ የምችልበት አንድ መንገድ አለ። »

«ምንድን ነው እሱ? » ‹ሰላይ ሁኚ› እንዳይለኝ የሚል ሐሳብ መጣበት።

«የድርጅት አባል መሆን አለብሽ። »

«የምን ድርጅት? ይኸ የሕዝብ ድርጅት የምትሉት? ሲያልፍም አይነካኝ። ሕዝብ ሲጠላው! » ዘለቃ የቀፈፋት በመምሰል ፊቷን አኮፋተረች።

«አይደለም። እሱ በይፋና በሕግ የተቋቋመው ነው። በሥውር፥ በድብቅ የሚሠሩ ቡድኖች አሉ። እነሱ ደግሞ ሕዋስ የሚባሉ አራት አምስት አባላት ያሏቸው ክበቦች አሏቸው። ከእነርሱ በአንዱ ውስጥ መግባት ነው። »

ዘለቃ ትንሽ ግራ ተጋባች። «ኢህአፓዎችን ማለትህ ነው? »

«እነዚህ እሱን የሚቃወሙ ናቸው። »

«ያው ባንዶቹ ናችዋ! » አለች ፍርጥም አድርጋ።

«ልትያቸው ትችያለሽ። »

«አልወዳቸውም። አልፈልግም። አላደርገውም! » አለች በፈረጠመ አነጋገር።

«ቆይ እንደዚህ ድርቅ ብሎኮ አይሆንም። » አሁን የሚያባብላት እርሱ ሆነ።

«ብትገቢ ምን አለበት? »

«የማላምንበትን! »

«ብታምኚበት - ባታምኚበት አንቺ ምን አስጨነቀሽ? ቁም ነገሩ የምትፈልጊውን ቤት ከማግኘት ላይ። በሳምንት አንድ ቀን በአንድ ቦታ እየተገናኛችሁ ጥናት - ይባላ - እንደ ውይይት ክበብ ማለት ነው ትማማራላችሁ፤ ብትፈልጉ የባጥ የቆጡን ታወራላችሁ - አንቺ እንዳሰኘሽ አድምጠሽ መበተን ነው። »

«ከዚህ ሁሉ » አለች ዘለቃ፥ አሁንም መደባበስ እንደምትፈልግ ወይም እንዳሳከካት እጅዋን ከጡት መያዣው በላይና በታች እያበሰች፣ «ነገሩም አላውቅም የሚያስፈልግ ከሆነ ለምን አንተ አባል ነች ብለህ መዝግበህ ቤቱን

አታስጠኝም፤ ከዚህ ሁሉ ጣጣ። ላንተ ቀላል እኮ ነው። » ሸሚዙን የምትፈታ፤ የምትቆልፍ እየመሰለች ደባበሰችው።

«አባላቸው አይደለህም እንዴ? »

«እንዲህ ያለ ጥያቄ አይጠየቅም። ኅቡዕ ማለትም ሥውር ናቸው ብየሻለሁ፤ እነማን መሆናቸውን ከእነርሱ ውጭ የሆነ ሰው አያውቅም። እኔ ደሞ ትንሽ በድብቅ የምሠራ ብሆንም አገር ያወቀኝ የመንግሥት ሠራተኛ ነኝ። ኃላፊነት ያለኝ። እና፤ ቅድም እንዳልኩት ብሆንም ባልሆንም አንተ መዝግበኝ ከአንተ ጋር መደበኝ ብሎ ነገር የለም። ያለው የጦፈ ትግል፤ ስለዚህ እንደዚህ ስልሽም እኔ ይህን ድርጌ አታድርጊ ብዬ አልነገርኩሽም። ይሄነው አሠራሩ። »

«አሠራሩ ስንኳ ምንም - ምኑም አይገባኝም። አልፈልግም ብልስ? » አለች ዘለቃ ከአጠገቡ እየተጋደመች።

«ትችያለሽ። ግዴታ እኮ አይደለም። የፈለገ ከትግሉ መድረክ ይገባል። ያልፈለገ ከውጭ ሆኖ ሊጠብቅ ይችላል። »

«ቤት የማግኘቱ ጉዳይስ? » አለች ዘለቃ፥ በቅሬታ።

«ሌላ ምንም መንገድ የለውም። » ለአቀደው ሐሳብ ዋና የካርታ ጆከሩን እንደ ያዘ በመገመት አነጋገሩን ጠንከር አደረገው።

«ሌላ ምንም መንገድ ከሌላ አዝናለሁ። » ዘለቃ ከአልጋው ወደ ዳር ወጣ እያለች እንደ መነሳት ቃጣች።

ወደ እርሱ ሳብ አረጋት። ላቀደው ሐሳብ ይህ ዕድል እንዳያመልጠው አልፈገም። «ለአፓርታማው ብቻ ሳይሆን ለኔ ስትይ አባል እንድትሆኚ እፈልጋለሁ። » ሳይታወቀው አንደበቱ ወደ ልመና ተለወጠበት።

«ለእኔ ስትይ? » ስትል ዘለቃ በመገረም ጠየቀች።

«አዎ! ሥራዬን ታውቂው የለ? »

«እና? »

ለመናገር ትንሽ ከአመናታ በኋላ «ስለ ቡድኖቹ ሁናቴ አንዳንድ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ » አለ አፉ ፈራ ተባ እያለ።

«በሌላ አነጋገር ሰልይልኝ ነው?! » በፌዝ እንደ መሣቅ አለች፤ ዘለቃ። «ግን፥ የእናንተው ከሆኑ ምናቸው ነው የሚሰለለው። »

«እንደሱ ማለቴ አይደለም። » በማስተባበል አኳኋን እጁን አራገበ። «ስለላ ከባድ ቃል ነው። እኔ የምፈልገው ቀላል ነገር። እንዴት ውይይት እንደሚያካሂዱ ምን እንደሚያስቡ። እንዲያው ለማወቅ ያህል። »

«በአንድነት ነው ያላችሁት። ራስህ አትጠይቃቸውም? »

ወዳጅዋ የሚሰጣትን ምክንያት ሲያማርጥና ሲያመዛዝን በማቅማማት ትንሽ ቆይቶ፤ «በአንድነት ሆነን መታየታችንኮ አንድ አያደርገንም። የማይታመኑ ከመካከላችን ሊኖሩ ይችላሉ። ጠላታችን ሆነው፥ ግን እኛን መስለው ሰርገው የገቡ። ታዲያ ከውስጥ ሆኖ ከሁናቴአቸው፤ ከአነጋገራቸው ከእነሱ ለማወቅ መሞከር አንዱ ተግባራችን ነው። እኔን ግን በይፋ ለማወቅ መሞከር አንዱ ተግባራችን ነው። እኔን ግን በይፋ ስለሚያውቁኝ ይጠነቀቃሉ። » የአቀራረቡ ዘዴ፥ ዒላማውን ይምታ ይሳት እርግጠኛ ስላልሆነ፥ ትክ ብሎ እየተመለከታት መልሷን ጠበቀ።

«ደበስበስ የማደርገውን እንደ ገባኝ ከሆነ ግልጽ ላድርገውና የእናንተ ወገኖች በሚባሉት ቡድኖች ውስጥ ኢሃፓዎች ስለ ገቡ እነሱን እየሰለልሽ ንገሪኝ ነው። » ዘለቃ የሽርደዳ ይሁን የማባበል ባልለየ አመለካከት ቃኘችው።

«ስላለ የሚለውን ቃል ምነው ደጋገምሽው? » እንደ መነጫነጭ ቃጣው።

«ሥራ ወሱው ከሆነ፤ ቃሉን መጥራት ብቻውን ምን አስበረገገህ? ለሥራው የታጨሁት እኔ ስንኳ ያልፈራሁትን? » በማፌዝ ከንፈርዋን አንሻፈፈች።

«የመፍራት ጉዳይ አይደለም። የሥራው ይዘት አንድ ስላልሆነ ነው። »

«ለእኔ ልዩነት አይታየኝም። አንተ ልዩ ኤክስሬ እንዳለህ አንጃ። ያም ሆነ ይህ በመካከላችሁ የገቡትን እነሱን ለማወቅ ዐውቃችሁም ለመምታት መሣሪያ እንድሆን ነው የተፈለግኩት አይደለም? » ስትል ፍርጥም አድርጋ ጠየቀችው።

«ለመምታት አይደለም። ከባድ ጥፋት አድርሰው ከመመታታቸው በፊት ለማረም ነው። »

«የሚታረምኮ የተሳሳተ ነው። የተሳሳታችሁ እናንተ እንጂ እነሱማ ልክ ነን ነው የሚሉት። ማነው ዳኛ? »

«እኛ! » አለ በቀልድ ዓይነት።

«ከሳሽም፥ ዳኛም ምስክርም። እንዲህ አርጐም የለ! »

«እንደዚህ ተከራካሪ መሆንሽን አላውቅም ነበር። ታዲያ ለምን ከዚያው ካልኩሽ ቡድን ውስጥ ገብተሽ አትከራከሪም? አታስተምሪም? »

«በማሞካሸት መብላትህ ነው ባንተ ቤት! ቱሪስት ብላ! » ስትል ሣቀችና ለጠቅ - አድርጋ «ለመሆኑ ሳላምንበት ቡድን ውስጥ ግቢ ስትል ምን ያህል ብትጨክን ነው? ስለኔ ቅንጣት አታስብም ማለት ነው? »

«እንዴት? » ቀና ብሎ ከተጋደመበት ተነሣና፣ እንደ መደባበስ ዓይነት አንድ እጁን ወደ እርሷ ዘረጋ።

«ኢሃአፓዎች ቢቀንድቡኝስ? »

«ፓህ! »

«ምን ታቃልለዋለህ! በየመንገድ ሲከነቸሩት የት ሄዳችኋል ታዲያ? ዕረፍት? እና እኔም ያ - ዕጣ እንዲደርሰኝ ትፈልጋለህ? »

«በአንቺ ላይ አያደርጉትም! »

«ምን እርግጠኛ አረገህ? »

«በእኔ ይሁንብሽ! ሌላው ቢቀር የቀድሞ ባልሽ ሳይማጠንልሽ ይቀራል? »

«ምን? ምን ትቀባዥራለህ! » አለች ዘለቃ።

«የቀድሞ ባልሽ ማስረሻ » አለ ወዳጅዋ በፌዝ ቃላቶችን ረገጥ እያደረገ «ከማኑኤል እንደ ወጣ ወዲያውኑ ቴሌ ሥራ መያዙን ከትግሉ ውስጥ መግባቱን አታውቂም እንዴ? »

ዘለቃ በመገረም ራስዋን ነቀነቀች፤ «መውጣቱንና ሥራ መያዙን ሰምቻለሁ። በተረፈ የርሱን ጉዳይ የምከታተልበት ምክንያት ጊዜም የለኝም። ለመሆኑ - » ልትጠይቅ ያሰበችውን አንጠልጥላ ተወችው።

«ኢሃፓ ነው » አላት ወዳጅዋ ሐሳቧ የገባው ይመስል።

«ለመሆኑ ይህንን ሁሉ የምትነግረኝ ለምን ነው? » ስትል ዘለቃ በመገረም ትኩር ብላ እየተመለከተች ጠየቀችው።

«ማወቅ ትፈልጊ እንደሆነ ብዬ ነዋ! » ነገሩን በማቃለል ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ። የነገራት በቀልድ ለማግባባት እንደ ዋዛ ነበር። አሁን ሲያስበው ግን ለእቅዱ እንደሚጠቅም ጭምር ገመተ። አሁንም ማስረሻን የምትጠላው

የምትጠየፈው ከሆነ ለእልህ ስትል እርሱ ያለበትን ኢ.ህ.አ.ፓን ወደ ሚቃወሙት ቡድኖች ለመግባት ፈቃደኛ ትሆናለች። ለማስረሻ የፍቅር ወይም የዘኔታ ስሜት ካላት ደግሞ መገናኘታቸው ስለማይቀር አስቀድማ አቋሙን ማወቋ ለማንኛውም ነገር እንድትጠነቀቅ ይረዳታል።

የፖለቲካውን ጉዳይ ለጊዜው አንጠልጥለው በመተው ለማሳረጊያ ያህል ጥቂት ከተዳሩ በኋላ ልብሳቸውን ሲለባብሱ «ታዲያ ተስማምተሽ ከሆነ አስፈላጊውን ዝግጅት ላድርግ? » ሲል እንደ ዋዛ ጠየቃት።

የዘለቃ አእምሮም እንቆቅልሹን ለመፍታት፥ ሐሳብ በእቅረጽ ላይ ቆይቶ ነበርና «እስቲ ትንሽ ላስብበት » አለችው.....

ውሳኔዋን እንደ ነገረችው ጉዳዮቹ በአፋጣኝ ተከናወኑ። አንድ ሰው ቴሌፎን ደውሎ ከተዋወቃት በኋላ፥ ስለሚገናኙበት ሥፍራና ጊዜ ቀጠሮ ሰጣት።

ቀድሞ የአንድ ሚኒስትር የነበረ የግንቡ አጥር የሁለት ሰው ቁመት በሚያክል ቪላ ውስጥ እንደ ተገናኙ በቴሌፎን ቀጠሮ የሰጣት የሕዋሱ መሪ እንደ ብዙዎቹ የዓለም ተራማጅ ምህሯን፥ የኤግልስን ስም ጭምር ጠቅሶ፥ መደቧን ክዳ በአብዮቱ ሠፈር በመሰለፍዋ ሲያመሰግናት ዘለቃ «ኧረ የኔ መደብ እስከዚህም ከፍተኛም አይደል! » ስትል እንደምታውቅበት ያፈረች የተሽኮረመመች መሰለች። ቀጥሎ ስም እየጠራ ከሌሎች የሕዋሱ አባሎች ጋር አስተዋወቃት። ራሷም የምትታወቅበት የኮድ ስም ተሰጣት። የሰዎቹ ስም እውነተኛ ይሁን ውሸት እርግጠኛ አልሆነችም። እንደ ሁናቴያቸው ግን በይፋ ሹመትና ማዕረግ ባይሆን ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ባለሥልጣኖች ይመስላሉ። ዕድሜያቸው ከወጣትነት አልፎ ሙሉ ሰው ወደሚባልበት የተቃረበ ነው። አለባበሳቸው በየመንገዱ ላይ እንደሚታየው ታጋይ እንደሚባለው አፎ መላ ቅጡ የጠፋው የተጠባበቀ የተቆራረጠ ጂንስ ሳይሆን፥ ለትከሻ ከበድ ለሰውነት ደርበብ ያለ ሱፍ ነው። አውቶሞቢሎቹ ደግሞ የበለጠ ይመሰክራሉ። ማን የማን መሆኑን ባታረጋግጥም አንዱ ባለመንግሥት ታርጋ አዲስ ላንድሮቨር ሌላው አሁንም የመንግሥት ታርጋ ያለው፥ ከጐንና ከጐኑ የቤቶች አስተዳደር ድርጅት አርማ የተሳለበት ጅፕ ቮልግስ ዋገን እየተባለ የሚጠራው ባለሽራ አውቶሞቢል ሦስተኛው ዳትሰን አውቶሞቢል ናቸው። ዘለቃ «አድኃሪ መልኩን ይለውጣል፤ ተራማጅ ደግሞ አውቶሞቢል ይለዋውጣል » የሚለው የሰሞኑ አሽሙር ታወሳትና እንደ መሣቅ ሲቃጣት መልሳ ዋጠችው።

የመጀመሪያው ቀን ጥናት እስከዚህም ሊገባት አልቻለም። የሕዋሱ መሪ የቡድኑ ልሣን ከሆነው ተበታኝ ወረቀት ረጋ ብሎ አነበበ። «ድርጅትን በሚመለከት፥ የእነሱ አድኃሪ አቋም የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁናቴ በሚመለከት ደግሞ የእኛ መቋቋም ስለ ብሔረሰቦች ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ስለ መገንጠል መብት » እያለ ከሌኒን እየጠቀሰ በምታውቀው የአማርኛ ቋንቋ ተወጣው። ከዚያም አንዳንዱ አርእስተ - ጉዳይ እየተቀባበሉ ተወያዩበት። ቋንቋቸው ግልጽ አማርኛ ነው። ሐሳቡ ግን በግዕዝ የሚነበብ ፍካሬ የሱስ ሆነባት።

«ታዲያ የመሥመር ልዩነታችንን እንዴት ነው የምታይው? ማለቴ ከርዕዮተ ዓለም አንጻር? » ሲል የሕዋሱ መሪ ወደ ውይይቱ ማብቂያ ላይ ጠየቃት።

«እኔኮ በፊትም የመጣሁት የናንተው ልክ ነው ብዬ ነው። ይህ ዝርዝሩ ጉዳይ ግን ብዙም አይገባኝም። ወደ ፊት ነው የምማረው » አለች ዘለቃ ቃላቱ በጆሮዋ እየተንቆረቆረ፥ ሐሳቡን ከመረዳት ይልቅ በዚያ አንድ ክፍል ውስጥ ዙሪያ ክብ የተቀመቱት ጕረምሶች ከፖለቲካው ውጪ በመዝናናቱ በመጫወቱ - በማጫወቱ እንዴት እንደሆኑ በአእምሮዋ ስትገመግም በመቆየቷ ድንገት በጥያቄው እንደ ማፈር ብላ።

«ይሄ ምንም አይደለም » አለ አንደኛው የሕዋስ አባል እንደሚጋብዝ ሁለት እጁን ወደ ላይ በመገልበጥ ወደ እርሷ ዘርግቶ። ስለ እርሷ፤ ከፖለቲካው ከአብዮቱ ከትግሉ ተጨማሪ አስተያየት እንደ ነበረው ከዐይነ ውህው የአነበበች መሰላት። በዚህ ረገድ ከነአጣጠረ የማይስት ስጦታ እንዳላት ታምናለች። ዐይንዋን ከዐይኑ ላይ ትክል አድርጋ ተመለከተችው። «እና ዋናው ቁም ነገር እር - አንቺ ኖ - ጓድ እንዲህ ጓድ ነው የምባባለው። እና በመደብ አንጻር ከአብዮትና ከሕዝብ ወገን ለመሰለፍ መወሰንሽ ነው። ዝርዝር ዕውቀቱ ጥርት አድርጎ መለየቱ እየቆየ የሚመጣ የሚገኝ ነው። ስለዚህ ነው እኛ እነርሱንም ቢሆን አፈ ሙዝን ተውትና እንወያይ እንከራከር እንረታታ የምንለው። »

«አዎ! እኛ እናሸንፋለን የምንለው በዚሁ በንድፈ ሐሳባችን እውነትነት ነው። »

ጥናቱ አብቅቶ ዘለቃ ቀድማ ከሄደች በኋላ የቀሩት ገመገሟት።

«ምን ትመስላችኋለች? »

«እኔ እንጃ! »

«ንቃትም ባይኖራት አቋሚ አስተማማኝ ለመሆኑ ከበላይ አካል ‹ኢንፎርሜሽን› ደርሶኛል። እንደነሱ መደባቸውን የካዱትን ማሰባሰቡም ሁናቴውን ለማረጋጋት የሚረዳ ይመስለኛል። »

«ሌላም - ሌላም፤ ሌላው ቢቀር ቆንጆ ናት! » አል የጐመጀ በሚመስል ልዩ አስተያየት ሲመለከታት የቆየው ጐረምሳ።

«ዲሲፕሊን! » የሕዋሱ መሪ እንደ መቆጣት አለ። «የአብዮት ጊዜ ነው። »

«አብዮት መንኩሱ አላለም። መነኮሳትም አብዮት አያካሂዱም » ሲል በዐይኑ ሊበላት የመሰለው የሕዋስ አባል። ሁሉም ተሣሣቁ።

በሁለተኛው ቀን የሕዋስ ስብሰባ ተከታይ የመሥመር ልዩነት ውይይት ከአዳመጠች በሁሉም ነገር የተስማማች መሆንዋን በፈገግታ በአስተያየትዋ በአንገት ውዝዋዜዋ ከገለጸች በኋላ የመረጃ በኋላ የመረጃ ክፍል ወዳጅዋ እንደ መከራት የኪራይ ቤት ችግርዋን ለሕዋሱ መሪ ነገረች።

ሳምንት ባልሞላ ጊዜ እርሷ እንደ ጠየቀችው ከአፓርትማ ሰማንያ አራት ሕንፃ ውስጥ ከሳሎን ከወጥ ቤት፥ ከመታጠቢያው ቤት ጋር ባላንድ መኝታ ቤት ክፍል የሚባለውን ተረከበች። በሁለተኛው ሳምንት ጥናቱ ወይም ስብሰባው ዘለቃ በተከራየችው አፓርትማ ውስጥ እንዲሆን የሕዋሱ ሌሎች አባሎች በሙሉ ተሰማው። ዘለቃ ለጊዜው በሐሳብዋ ኢንተርናሽናል ድርጅት ስለምትሠራ ከቀረጥ ነፃ የሆነ መጠጥ ሲጋራና ምግብ እንድታቀርብላቸው ቢመስላትም ከእነሱ በኩል የሚታመን ምክንያት ነበራቸው። ከባምቢስ ጀርባ ያለው ትልቅ ግቢ ግቡና አቀማመጡ ከአደጋ ለመከላከል ደህና ቢሆንም ሠፈሩ የኢህአፓ ከመሆኑ ሌላ፣ ሰው ሲገባ በቀላሉ ይታወቃል። ኢህአፓዎች ያተኮሩበት ስለሆነም የታጠቁ ጓዶች በውስጥና በውጭ አሰማርቶ ማስጠብቅ ግድ ሆኗል። ግን ይህ በኅቡዕ አሠራር ልክ አይደለም። ኅቡዕነቱ ከታወቀ በቃው። ዋጋ የለውም። በአንጻሩ ዘለቃ አሁን የገባችበት አፓርትማ ሰምናያ አራት ግልጽና ሰፊ አካባቢ ነው። ከውጭ አገር ምሑር አንሥቶ፤ እስከ ሥልጡን «የሳሎን » ሽርሙጥና አቃጣሪ በዚያ ሰፊ ግቢ፥ ሰለሚወጣውና ስለሚገባ በሜዳው የሚገጠገጠው አውቶሞቢል የማን እንደሆነ በደረጃው ‹በአሳንሰሩ› የማይወጣው የሚወርደው ማን - ማን እንደሆነ - ማን ከማን - አይለይም። ስለዚህ ከታጠረ ከተገለለ ግቢ ይልቅ አፓርትማው የተሻለ ሽፋን ይሰጣል ተባለ።

ዘለቃ አስቀድማ እንዳሰበችው አሁንም ባታምንበትም የቡድን አባልነቱም ሆነ የሕዋሱ ስብሰባ እስከዚህም የሚያስጠላና የሚያስፈራ ሆኖ አላገኘችውም። ላይ ላዩን ከውጭ ከሚታየውና ከምትሰማው ትንቅንቅና ፍጥርቅርቅ የመረጃ ክፍሉ ወዳጅዋ አልፎ አልፎ ከሚነግራት ወሬ ሌላ ውስጥ ውስጡን ኅቡዕ በሚሉት ዓለም ስለ ሚካሄደው ፍጭትና ሽኩታ ውስብስብና ምስቅልቅል ትግል፣ ርዕዮተ ዓለምን የመሥመር ልዩነት ስለሚሉት የምትሰማው እንቆቅልሽ ነገር ሁሉ እንደ ተረት የሚስባት እየሆነ፤ እንደ ስለላ ልቦለድ መጽሐፍ የሚመስጣት እየሆነ በመገረም በመደነቅ ታዳምጥ ጀመር። ስለ ሀገር አንድነትና ስለ ብሔረሰቦች እኩልነት ስለ ዲሞክራሲ፣ ስለ ፓርቲ አመሠራረት ስለ ዓለም የኃይሎች አሰላልፍ፥ እለ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁናቴና ስለ ሌሎችም ጉዳዮች የርዕዮተ ዓለሙና የመሥመር ጸጉር ስንጠቃው ምኑም ምኑም አልገባ ሲላት ሲሰለቻት የምታዳምጥ ይመስል ዐይንዋን ከደን አድርጋ ‹ካለፖለቲካ ሌላ ሕይወት የሌላቸው ካለ ትግል ጓደኝነት ሌላ ግንኙነት የማያውቁ› የሚመስሉት በአጠገብዋ ያሉት ሥግው ጕረምሶች ሥጋዊ ሕይወታቸው የፍቅር ጨዋታና ስሜታቸው ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል በሐሳብዋ ለማየት ለመዳሰስ ትሞክራለች። ሌላ - ሌላም በጣትዋ ዙሪያ እንዳሽከረከረችው ክሌዎፓትራ ዮልየስ ቄሣርን እንዳንበረከከችው፤ ዘለቃም የጊዜው የፖለቲካ ሰዎች የጊዜውን ባለሥልጣኖች ክንድዋን በማስደገፍ ከቁጥጥርዋ ሥር አውላ የምታዛቸውን ሲያደርጉ የምትከለክላቸውን ሲተዉ በሐሳብ እየታየት ሳይታወቃት ፊትዋ ፈገግ ይላል።

በሳምንት አንድ ጊዜ በአፓርተማዋ የሕዋስ ስብሰባ እንደሚደረግ ሁሉ በሳምንት አንድ ቀን ከመረጃ ክፍል ወዳጅዋ ጋር መገናኘቷም የማይቀር ፕሮግራም ሆነ። ረቡዕ ከምሽቱ በአንድ ሰዓት የሕዋሱ ስብሰባ እንደሚካሄድ ከነገረችው በኋላ ሐሙስ ጧት ይደውልላታል-

-እና፥ ዛሬ ማምሻውን እንገናኝ እንጂ - ይላል።

-እንደፈለክ።

-እፈልጋለሁ - ይልና የአንዳቸውን አውቶሞቢል አቁመው በአንዳቸው መኪና ወደሚሄዱበት ለመሄድ በራስ በገነት በዳ'አፍሪክ በዋቢ ሸበሌ፥ በኝን ወይም አውቶሞቢሉ የተሽከረከረም ይሁን፥ ክትፎ ቤት በአውቶሞቢል ውስጥ እንደሆኑ ምግብና መጠጥ አዝዘው ወይም የአልጋ ክፍል ይዘው እየተዳሩ የነገር ውሉን አይስትም። «ታዲያ ዛሬ ውይይት እንዴት ነበር » ሲል ይጠይቃታል።

«ነገራችሁ ምንም አይገባኝ። ዝም ብሎ ይሄ እንዲህ ነው ይሄ እንዲህ አለ - እኛ እንዲህ አልን - ተባለ፤ ተለያየን። »

«ስለ ኢሃአፓ በተለይ ምን አሉ? የደገፈው ወይም ይሄ ይሄን ቢያደርግ ደህና ነበር የሚል አስተያየት ያቀረበ አልነበረም? »

«ኧረ ምንም! ሁሉም የሚያወግዙት የሚረግሙት አናርኪስቶችን ነው። አናርኪስቶች የሚባሉት ኢሃፓዎች አይደሉም? »

የመረጃ ክፍል ወዳጅዋ ከንፈሩን አሞለሞለና «አዎ ናቸው። የሚያተራምሱ! » አለ ነቀፌታ ይሁን አድናቆት ባልለየ አንደበት......

አንድ ቀን ሆቴል ስንኳ ሳይገቡ አውቶሞቢሉን በአስመራና በቦሌ መካከል እያሽከረከረ፥ ከሴት ወዳጅ ጋር ያለ መሆኑን ፈጽሞ የረሳና የፖሊስ ጣቢያ ምርመራ የሚያካሂድ በሚመስል አኳኋን «እኮ ምን ምን ተባባላችሁ? ኧ - ያ - እንትና ምን አለ ስለ አናርኪስቶች? » ሲል ደጋግሞ በመጠየቅ ለምትሰጠው መልስም «ይኸው ብቻ ነው? በደንብ አዳምጠሻል? » እያለ ቢያስቸግራት ቁጣ በመሰለ መዳራት ደረቱን በመዳፍዋ ደቅ አደረገችው።

«ምነው! » አለ ዐይኑን በሐሳብ ወደ ፊት እንደ ተከለ ሳይሰብር።

«በጣም አዘንኩ! » አለች በመከፋት የታች ከንፈርዋ ወደ ፊት ለጥጣ።

«ለምን? »

«ሐሙስ ሐሙስ ማታ ለካ የምትቀጥረኝ ልክ እንደ ፖሊስ ጣቢያ ቃሌን ለመቀበል ኖሯል። እኔ ደሞ ለፍቅራችን እስከዚህ ምናልባት እንደኔ ፍቅር ባይዝህም፥ ለደስታችን ይመስለኝ ነበር። አልገባኝም ነበር ማለት ነው። » የበለጠ የታች ከንፈርዋን ጣለችው።

«የለም! የለም! ቀድሞውኑ የተዋወቅሁሽ ለዚህ እንዳልሆነ አሳምረሽ ታውቂዋለሽ። አሁንም ስላንቺ ያለኝ ስሜት አልተወለወጠም። ያው ነው። » ግን አነጋገሩ አሁንም በሌላ ሐሳብ የተመሰጠ እንጂ ስለ እርሷ ያለውን ስሜት የሚገልጽ አልሆነም። «ግን ፋታ የማይሰጥ የትግል ወቅት ነው። ስለዚህም፥ ቁም ነገሩንና የፍቅር ጨዋታውን በአንድነት አብሮ ማስኬዱ፤ ፈረንጆች እንደሚሉት ‹ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል› ነው። አይመስልሽም? » አለ እንደ መቀለድ እየቃጣው።

«አይመስለኝም። አንዳንድ ጊዜ ከሌላ ወፍ ጋር ተደርቤ ሳይሆን ብቻዬን እንድመታ እፈልጋለሁ » አለች እርሷም በቀልድ።

አሁንም ሌላ ቀን ደግሞ «እህ? ዛሬስ ምን ታዘብሽ? የአናርኪ ፍንጭ አላሳዩም? » በማለት ሲጠይቃት፤ «እንዲያው ዝም ብለህ ነው እንጂ የምታለፋኝ እንኳን ከመሃከላቸው ኢሃፓ ሊኖርባቸው ቀርቶ ስሙ ሲነሣ ያንገሸግሻቸዋል። በጣም ገረመኝ። ግን እውነት ነው? » ስትል መልሳ ጠየቀችው።

«ምኑ? »

«እነሱ እስከ ላይ ድረስ ነው ያላቸው መሆናቸውን ልትመታቱ ተፋጠጣችሁ መገኘታችሁ? »

«በምን ዐወቅሽ? »

«በስብሰባችን ጊዜ ሲሉ ሰማኋ! »

«ምን አሉ? » አጠያየቁ የጉጉት ነበር።

«ብዙ ነው፤ ከላይ ያሉ የኢሃፓ ደጋፊዎች የሕዝብ ድርጅት ሰዎችንና የሚቃወሙዋቸውን ደርጐች እምሽክ አርገው ሙሉ ለሙሉ ሥልጣን ለመያዝ ዝግጅቱ ያለቀ መሆኑን እንደ ደረሳችሁበትና እናንተም በበኩላችሁ ሳትቀደሙ ቀድማችሁ እንደ ምትመቱዋቸውና ሌላም ሌላም። አሁንማ ከኔ ጋር የሚሰበሰቡትም እንደ አንተው አውቶማቲክ ጠመንጃ እየያዙ ነው የሚመጡት። እኔኮ ውስጥ ያለውን ይህን ሁሉ ጉድ አላውቅም ነበር! » አለች በመገረም።

ለአስተያየትዋ መልስ ሳይሰጥ «ለመሆኑ ከላይ የኢሃፓ ወገን ናቸው የሚሏቸው እነማን ነው » ሲል ጠየቃት። ዘለቃ አንዳንድ ስሞች ሲጠሩ የሰማች ቢሆንም መንገር አልፈለገችም። ከመሠረቱ ከቡድኑ ሕዋስ ውስጥ የገባችው አፓርትማ፥ ለማግኘት ሌላ መንገድ እንደ ሌለ ስለ ተነገራት እንጂ ከልብ አምናበት ለመታገል፥ ወይም ተቃዋሚዎችን እየጠቆመች ለማስያዝ አይደለም። በዚህ ላይ ዛሬ ማንም ስለ ማይታመን መጠንቀቅ ይገባል ባይ ናት። ስለ መረጃ ክፍል ወዳጅዋ አቋምም እንቆቅልሽ የሆነ ጥርጣሬ ስላደረሰባት፥ እርግጠኛውን ፍንጭ እስከታገኝ ድረስ በለዘብታ መያዙን መርጣለች። «እገሌ እገሌ አላሉም፥ በደፈናው ነው የተናገሩት » አለችው።

«ከእኛ ወገንስ የሚመቱት እነማን ናቸው አሉ?

«የእናንተን ወገን ደግሞ ከአንተ ይበልጥ አንቺ ታውቂያለሽ በለኛ! » ዘለቃ በማፌዝ ትዝብት ለቅጽበት ዐይኗን ብልጥጥ አድርጋ ተመለከተችውና ወዲያው መልሳ፣ «እንዳልኩህ እገሌ እገሌ ተብሎ ስም አልተነሣም። ግን ከዚያው ከናንተው ውስጥ ነው » አለችው። ወዳጅዋ በበኩሉ እንድትነግረው በጣም አስላስጨነቃትም። የሚፈልገውን አንድ ዋና መረጃ አግኝቷል። ይሄውም ሁለቱም ወገኖች እባብ ለእባብ ይታያይል። እብካብ መሆናቸው ነው። ‹አንደኛው ወገን ለእራት ሊያደርገው ያሰበውን ሌላው በምሳ ሊቀድመው ይሰናዳል። ያ ደግሞ ቀድሞ ለቁርስ ቢያቀላጥፈው?› የሚል ሐሳብ መጣበትና ከራሱ ጋር ፈገግ አለ። ከዚህም በቀር እርሱ ድብብቆሽ እንደሚጫወት በመጠርጠር በበኩልዋ ድብብቆሽ መጫወትን ካወቀ ውል የሌለው ጥሩ ሽፍን አሠራር መሆኑን ገመተ።

ግን ሁለቱም በጊዜው ያልተነዘቡት ይህንን የመስለው የድብብቆሽ ጨዋታ - ውስብስብ የኅቡዕ አሠራር - ያልታሰበው ውስብስብ ችግር ሊያመጣ መቻሉን ነው። ሌላው ቢቀር የሕዋስ ስብሰባው በአፓርታማዋ ሲደጋገም እንደ አላፊ አግዳሚ አውቶቡስና ሳይቸንቶ ጠባቂ ጫማ አስጠራጊ ከዚያም አልፎ በሽተኛና ለማኝ በመምሰል የእሷንና የሌሎችን እንቅስቃሴ አዘውትረው የሚከታተሉ መኖራቸውን አላስተዋለችም ነበር።

## ፫

ማስረሻ ሳያውቅና ሳይፈልግ የድርጅት አባል መሆኑ ያናደደውና ያሳረረው ሳይናስ ለእስኳድነት መመደቡ ተደምሮ ትዕግሥቱ ሞልቶ ለመፍሰስ ደረሰ።

በሕዋስ አባልነቱ በሳምት አንድ ጊዜ እንደሚሰበሰብ ሁሉ በእስኳድ ምልምልነቱ ደግሞ በሳምንት አንድ ጊዜ እሑድ እሑድ መሠልጠን ነበረበት።

በአንድ ምድብ እንዲሠለጥኑ የተደረጉት ከራሱ ጋር አራት ናቸው። አስቀድሞ በተሰጣቸው መምሪያ መሠረት በሁናቴው አንድ ጊዜ ፓራ ኮማንዶ የነበረና የተሰናበተ ወይም የከዳ የሚመስል አሠልጣኛቸው ራሱ በሚያሽከረክራት ሬኖ አውቶሞቢል ከተቃጠሩበት ቦታ እያሳፈረ እንዳመቸ አንድ ጊዜ በአስመራ መንገድ ሌላ፥ ጊዜ በገፈርሳ ወይም በጐጃም መንገድ ከከተማው ራቅ ብለው ይወጣሉ። ከዚያም ጭር ያለ አካባቢ ይመረጥና ወታደር ቀመስ ሥልጠናው ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ድረስ ይካሄዳል። የሥልጠናው

የመጀመሪያ ደረጃ ስፖርትና መጠነኛ ጁዶ ነው። ማስረሻ ከትምህርት ቤት ከወጣ፥ ስፖርት የሚባል ነገር የማያውቅ ቢሆንም ሌሎች እየሣቁበት አሠልጣኙ እያፌዘበት ደፋ ቀና እያለ ወገቡ ከሁለት የተሰበረ እየመሰለው እየወደቀ እየተነሣ፣ እንደ ምንም ችሎ ተወጣው። ሁለተኛው ደረጃ ሥልጠና በመጀመሪያ ለአሥር ደቂቃ ያህል ሰውነት ማፍታታቱና ስፖርት መሥራቱ ሳይቋርጥ ከጦር መሣሪያ መተዋወቅ ነበር።

አሠልጣኙ አንድ ኡዚ አንድ ኮልት አንድ ካርባይን ይዞ መጥቶ ከአንድ ዛፍ ሥር ኬሻ ተነጥፎ፣ ከዚያ ላይ የጦር መሣሪያዎቹ እንድ እጌጥ ዕቃ በተርታ ተቀምጠው ተራ በተራ እያነሣ፣ ሥማቸውን ጠባያቸውን አስረዳቸው። እንዴት እንደሚያዙ በምን ርቀት ጉዳት እንደሚያደርሱ ነገራቸው። እንዲዳብሷቸው አያያዛቸውን እንዲለማመዱ እያነሣ ተራ በተራ ሰጣቸው። ማስረጃ የጦር መሣሪያ ሲጨብጥ የመጀመሪያ ጊዜው ስለ ነበር፣ በደሴ ቱሪንግ ሆቴል በዘሊቃ ወዳጅ የቆሰልወው ድንገት ትዝ አለውና የሚጠላውን እባብ የነካ ይመስል ሰውነቱን ስቅጥጥ አለው።

«ግሩም ዕቃ ነች ማማርዋ! » አለ አሰልጣኙ፤ ሁናቴውን አይቶ በማደፋፈር አኳኋን።

-የጥፋት ወበት - አለ ማስረሻ በሐሳቡ።

ከዚያም መሣሪያዎቹን መፍታት መወልወልና መግጠም የመሣሪያዎቹን ልዩ ልዩ ክፍሎች ስምና ተግባር በዝርዝር አጠኑ። የማስረሻ እጅም በመጠኑ እየተላመዳቸው ሄደ። ቀጥሎ የመጨረሻው ልምምድ የኢላማ ተኩስ ሆነ። ቀጥሎ የመጨረሻው ልምምድ የኢላማ ተኩስ ሆነ። በመጀመሪያ ባዶ የሜጋ ቆርቆሮ ከጉብታ ላይ አስቀምጦ በተለይ በካርባ ይኑና በሽጉጡ ሦስት ሦስት ጥይት አስተኮሳቸው። የማስረሻ አተኳኰስ ከሌሎች የተሻለም፣ የባሰም አልነበረም። አንድ ጊዜ ከሥር መሬቱን ሲበሳ ቆርቆሮውን ፈነገለ። ሁለት ጊዜ በዙሪያው አቧራ አስነሣ። ቃታውን ስቦ የተኩስ ድምፅ በአስተጋባ ቁጥር፥ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ተሰምቶ ፖሊስ የሚመጣ መስሎ እየተሰማው ሳይታወቀው ገልመጥ ይል ነበር።

«አሁን እንግዲህ ዋናውን ኢላማ እንጀምራለን » አለ አሠልጣኙ ከሞላ ጐደል ተመጣጣኝ በሆነ ልክታ የሰው ጭንቅላት ማለት ዙሪያ ክብ ቅርጹ ዑይኖቹና አፉ በነጭ ቀለም በጉልህ የተሳለበት ካርቶን ወረቀት በሰው ቁመና ልክ ከዛፍ ላይ በማሰማር እየመታ። ከዚያም ሃያ አምስት ርምጃ ያህል ቆጥሮ

በተርታ ቆሙ። «እንግዲህ » አለ አሰልጣኙ፤ እንደገና በቀኝ እጁ ሽጉጡን ይዞ በግራ እጁ ሌባ ጣት ምስሉን እያመለከተ «ግዳችሁን የምትፈጽሙበት ዋናው ጊዜ ይመጣልና በምታነጣጥሩበት ጊዜ ያንን ምስል ልክ በሕይወት እንዳለ ጠላታችሁ ቁጠሩት። መጥፋት መወገድ ያለበት ጠላት። ምሕረት አዘኔታ ሊሰጠው የማይገባ ወንጀለኛ። ብትስቱት ቢያመልጣችሁ የራሳችሁን ሕይወት የሚያሳጣችሁ፤ ከዚህም በላይ ትልቅ ዓላማችንን የሚያደናቅፍ ባለጋራ አድርጋችሁ አስቡት። ይህ ሲሆን ወንድነት ጀግንነት ስለሚሰማችሁ አነጣጥራችሁ ይበልጥ የሰመረ ይሆናል። ተኳሽነት የአካል ጥንካሬንና ቅልጥፍናን ብቻ የሚመለከት አይደለም። የሰውነት መርበተብት ከምን የሚመጣ ይመስላችኋል? ከመንፈስና ከስሜት መረበሽ ነው። ሰውነት ሲርበተበት ደግሞ፥ ትንፋሽን ተቆጣጥሮ ክንድና ትከሻን ይመጣል። ስለዚህ ነው ወኔያችሁ ኮስተር መንፈሳችሁ ልክ እንደ ደመኛ ጠላታችሁ ቁጠሩት ያልኩት። ንግግሩን ሲጨርስ አንዳንድ ጥይት ብቻ እያጐረሰ በየተራ ሰጣቸው።

ማስረሻ ኮልት የጨበጠ ክንዱን ዘርግቶ እንደ ተነገረው በምስሉ ሁለት ዐይኖች መካከል ሲያነጣጥር «ልክ ሕይወት እንዳለው ሰው አድርገህ ቁጠረው - ልክ መጥፋት እንዳለበት ጠላትህ - » ያለው የአሠልጣኙ ምክር ገሐድ ሆኖ እንደ ገና ተሰማውና ድንገት በጥፊ እንደ ተመታ ዐይኑ ድብዝዝ አለበት። በደብዛዛው በኩልም ምስሉ ሕይወት ወደ አለው የሰው መልክ ተለወጠ። ዐይኖቹን በጭንቀትና በልመና እያንገዋለለ አንድ ጊዜ የሥርጉ ዕለት ከዳስ ውጭ ተኰልኩሎ ሲለምን ያየው የመሰለውን አሳዳጊ አባቱን ሙሔን ሌላ ጊዜ ለአማኑኤል ሆስፒታል የዳረገችውንና ሊቀበላት ተመኝቶ የነበረውን የዘለቃን ምስል እየመሰለ ቃታውን መሳብ አቅቶት ዝም ብሎ ቆየ። ቃታውን በሳበ ጊዜ ጥይቱ ከዛፉ ሥር አጠገብ መሬት ፎገረ።

«ምን ነካህ? » ሲል አሠልጣኙ ጠየቀው።

«ክንዴ ዝሎ ወደ ታች ወረደ መሰለኝ » ሲል መለሰ ማስረሻ፤ በማፈር አብሮ አንገቱን እንደ መድፋት አድርጐ።

በሁለተኛው ዙር ተራውም አልተሻለውም። እንዲያውም ወደ ሕይወት የተለወጠው ምስል ጥርሱን በጭንቀት አግጥጦ እጁን እያርገበገበ የመጣበት መሰለውና ድንገት ሐሳቡን እንደቀየረ ሁሉ ቃታውን ከመሳቡ በፊት እጁን ከዛፉ አግጣጫ ወደ ቀኝ አጠፍ አድርጐ ሲተኩስ ጥይቱ ሰማይ ለሰማይ አግድም ሄደ።

በሚቀጥሉት የልምምድ ቀኖችም ቢሆን ሌሎቹ መሐል ግንባር መምታት ሲችሉ እንዲያም ሲል «በአፉ ልልቀቅበት? » እስከ ማለት ሲደርሱ ማስረሻ ሥዕሉ ያረፈበትን ካርቶን ወረቀት ስንኳ መጭረፍ አቃተው። ሽጉጡን ጨብጦ ባነጣጠረ ቁጥር ወባው እንደ ተቀሰቀሰበት በሽተኛ እጁ እየተንዘፈዘፈ አስቸገረው።

አሠልጣኙ ምስሉን ሕይወት እንዳለው ጠላት አስቦ እንዲተኩስ አሁንም አሁንም ደጋግሞ ከመረው በኋላ ትዕግሥቱን ጨርሶ የማሠልጠን ሙያው በማስረሻ ላይ ከንቱ ሆኖ በመቅረቱ ክብሩ ተነካ ቆጥሮት «ምን ሆነሃል አንተ? » ሲል በቁጣ ጠየቀ።

«ምን ሆንኩ? ሲያቅተኝ አቃተኝ » አለ ማስረሻ።

«ከንስት ልምምድ በኋላ በመሻሻል ፈንታ እየባሰብህ ይሄዳል እንዴ! ሌላው ቀርቶ የመጀመሪያው ቀን በቆርቆሮ ላይ ስታነጣጥር ደህና አልነበርክም? »

«አንተው ነህ! » አለ ማስረሻ ዐይኑን ወደ መሬት ጣል አድርጐ።

«እኔ ምን? »

«ምስሉን ሕይወት እንዳለው ሰው አድርጋችሁ አስቡት አልክ። »

«እና? »

«ይሕወት ማጥፋት አልፈልግም! ስለዚህ እጄ በራሱ ስሜታዊ እንቅስቃሴ ሆን ብሎ ይስታል መሰለኝ! »

አሠልጣኙ ከት ብሎ ሲሥቅ በዚያው አጠገብ ቁመው የነበሩት ሲቀባበሉ ማስረሻ ለጊዜው ጭር ባለው ሰፊ ሜዳ መካከል ድምፃቸው የጥይት ተኩስ ያህል ያውካካበት መሰለው።

«ምን ያሥቃችኋል? » ሲል ጠየቀ በቅያሜ እንደ መኮሳተር ብሎ።

«የእስኳድ ምልምል ሆነህ - ያው በጊዜው እስኳድ መሆንና በተግባር መሠማራት ላይቀር - ሕይወት ማጥፋት አልፈልግም ማለትህ ሁለት አብሮ እንዴት ይሄዳል? »

«እኔ ፍልጌ አይደለም። ዕጣ ወጥቶብሃል ግዴታ ነው ተብዬ ነው።› ማስረሻ ‹ከድርጅታችሁ ውስጥም ቢሆን ፈልጌ አልገባሁም የሚለውን ሐሳብ ሊናገር ቃጥቶት ከአፉ እንደ ገና መልሶ ዋጠው።

ከመሠረቱ ማስረሻ ዕጣ ቢወጣበትም ተሞክሮ ተሞክሮ ፈጽሞ የማይሆን ከሆነ አሠልጠኙ ለበላይ አካል አመልክቶ ከእኳዱ ቡድን ሊያወጣው ወይም ወደ ሌላ ዘርፍ ማለት ወደ ቅስቀሳ ወደ መረጃ ዘርፍ እንዲዛወር ሊያደርገው ይችል ነበር። ነገር ግን አሠልጣኙ በተደጋገመ የዲስፕሊን ጉድለት ከጦሩ ከተገለለ በኋላም ቢሆን ራሱን ለጦር አዛዥነት እንደ ሚበቃ ያህል ከፍ አድርጐ ስለሚገምት አሁን በተሰጠው እስኳድ የማሠልጠን ሥራ ከሙያው ጋር እልህ የገጠመ ነው። ልፍስፍሱን እንደ ብረት አጠንክሮ ፈሪውን እንደ አንበሳ አደንድኖ ዳተኛውን እንድ ሰስ ፈጣን አርጐ እንዲያው በደፈናው እንደ ብረት አቅልጦ እንደ ወይፈን እንደ ወይፈን ቀጥቅጦ ከሚሰጡት ምልምል አስኳዶች መላ ኢትዮጵያን የሚያንቀጥቅጥ ሠራዊት መፍጠር የሚችል መስሎ ይሰማዋል። በማስረሻ የገጠመውን ችግር የተመለከተውም በዚህ ስሜት ነበር። «ለመሆኑ የሰው ሕይወት ማጥፋት የማትፈልገው ለምንድን ነው? » ሲል በእርጋታ ጠየቀው። እንደ ሰሚው አልፎ አልፎ በቅንጫቢ እንዳነበበውም ሥነ ልቦናዊ አቀራረብም ይከጅለዋል። በተለይ አማኑኤል ሆስፒታል ቆይቶ የወጣ መሆኑን ስለሚያውቅ ለችሎታው ማስመስከሪያ አንድ ሌላ ፈተና አድርጐ ቆጠረው። «እህ? ለምንድን ነው የሰው ሕይወት ማጥፋት የማትፈልገው? » ሲል እንደ ገና በማባበል ጠየቀው።

«የአንድ ጊዜው ይበቃኛል » ማስረሻ ሳያስበው ነበር መልሱ ከአፉ የወጣበት።

«ምን? ከአሁን ቀደም ሰው ገድለሃል ማለት ነው? » ሁሎችም በአዲስ ዓይነት አድናቆት ተመልከቱት። የአሉታም ሆነ የአዎንታ መልስ ሳይሰጣቸው ሲቆይ «በጥይት ነው? » ብሎ ጠየቀ አሠልጣኙ።

«በምንም አይድለእም። » ማስረሻ ራሱን ነቀነቀ። «እንዲሞት አደረግሁት እንጂ አልገደልኩትም »። የሙሔ ፊት በሐሳብ ታየው። ከአማኑኤል መውጣቱ ታስቧቸው እርስ በርሳቸው ቢተያዩም የነገሩን እንቆቅልሽ እንዲነግራቸው ወተወቱት። ማስረሽ ግን «ማንም ሊረዳው የማይችል ጉዳይ ነው » ሲል ዘጋ። የሕሊና ሠቀቀኑን ለማንም የሚዘከዝክበት ምክንያት አልታየውም።

ከዚህ በኋላም ቢሆን አሠልጣኙ በበለጠ እልህ ገፋበት እንጂ ተረታሁ ብሎ አልተወውም። አንድ ቀን እንደ ተለመደው የእንጦጦን ዳገት ወጥተው ተዳፋቱን እንደ ተያያዙት፥ ከመንገዱ ዳር አንዲት የምታምር እምቦሳ ከባሕር ዛፍ ጥላ ሥር ተከልላ አገኙና አሰልጣኙ አውቶሞቢሉን አቁሞ «ከኋላ ኰፈን አስገቡዋት

እስቲ ልጆች » አላቸው። ግራ ተጋብተው በጥያቄ ዐይን ተመለከቱት። «ሰው እንደ ሌለ አይታችሁ ከኋላው ኰፈን አስገቧት ነው የምትላችሁ! » አለ በትእዛዝ መልክ ተኮሳትሮ። አስገቧት ነው የምላችሁ! » አለ በትእዛዝ መልክ ተኮሳትሮ።

ሁለት ወርደው ከአስገቧት በኋላ «ምን ልታረጋት ነው? » ሲል አንዱ ጠየቀ።

«በኋላ ታያላችሁ! » በኋላ የሚያደርገው በሐሳቡ እየታየው ከራሱ ጋር ፈገግ ብሎ።

ካለ ወትሮው ከዋናው መንገድ ብዙ ርቀው ከገቡ በኋላ እምቦሳዋን ከአውቶሞቢሉ ኮፈን አውጥተው እንዲለቋት ነገራቸው። አሁንም ግራ እንደ ተጋቡ የታዘዙትን አደረጉ።

«እምቧ! » ስትል ተጣራች አካልዋን ለማፍታታት ትንሽ እንደ መቦረቅ ካለች በኋላ። ወዲያውም አዲሱ አካባቢ የተደናገራት ይመስል ዙሪያ ገባውን ቃኘች።

«አሁን እንግዲህ ማስረሻን ሕይወት ማጥፋት ልናስተምረው ነው » አለ አሠልጣኙ ሁለቱን መዳፉን እያፋተገ። ሁሉም ከአውቶሞቢሉ አጠገብ ስብስብ ብለው ቁመው እምቦሳዋን ይመለከታል። «ኮልቱን አምጣው ከአውቶሞቢሉ ውስጥ » ሲል አዘዘ። በእምቦሳዋ ጉዳይ ሐሳባቸው ተይዞ መሣሪያ ማውጣቱንም ረስተውት ነበር። ጥይት መጉረሱን አረጋገጠና ኮልቱን ለማስረሻ ዘረጋለት። «እንዳትስት ከሰጋህ በጣም ቀረበህ ብትፈልግ ከግንባርዋ ላይ ደነህ ተኩስ። »

«ምን? » ማስረሻ ከተዘረጋለት ሽጉጥ እንደ መሸሸ አለ።

«አዎ ተኩስና ግደላት » አለ አሠልጣኙ በፈረጠመ ትእዛዝ። ሌሎቹም ቢሆኑ ተደንቀው ዐይናቸውን በለጠጡ። «አዎ! » አለ አሠልጣኙ ድጋሚ በማረጋገጥ «እንደ ማስረሻ ያለውን ካለበት ስሜት የሚያላቅቅ ዋና መፍትሔ ነው። ከአጉል ይሉኝታ መንፈስ ነጻ ያወጣዋል። »

«አንድ በርግጥ የሆነ ታሪክ ልንገራችሁ? » ሲል ቀጠለ በነገሩ የተገረሙ መሆናቸውን የሚገልጽ አስተያየታቸውን እንዳነጣጠሩበት ተመልክቶ፤ «ከብዙ ዓመታት በፊት ነው እኔ ወታደር ሳለሁ በዳር አገር የሠፈረ አንድ ሻለቃ ጦር ነበር። ያን ጊዜ ያለሁበት። ታዲያ የሻለቃው ግዳጅና ተግባር በየጊዜው እየተንቀሳቀሰ አሰሳ እያደረገ የውጭ ጠላት ሠርጎ ገቦችን ማጥቃት የውስጥ ተባባሪዎች እንዳሏቸው ከተረጋገጠ መምታት ነበር። የውስጥ ተባባሪዎች

እንዳሏቸው ከተረጋገጠ መምታት ነበር። ታዲያ በመካከላችን አንድ ወታደር ነበር። ዲሲፕሊን አለው። ሰውነቱ ጠንካራ ነው። በግል ከሰው ጋር ሲጣላም እስኪበቃ ለመደባደብ ወደ ኋላ አይልም። ማለት ፈሪ አትለውም። እንዲያውም ደፋር ነው። ግን ከጠላት ጋር ፊት ለፊት እየተያየን በምንጋጠምበት ጊዜ ዐይኑ እያየ አነጣጥሮ መተኰስ አይሆንለትም። እንጃ በጨለማ ውጊያ በጭፍኑ ተኩሶ ገድሎ ይሆናል። እንዳልኩት ዐይኑ እያየ ግን ሊገድለው በመጣ ጠላት ላይ ስንኳ አነጣጥሮ መተኰስ አይችልም። ካሁን ቀደም እንደ ነገርኳችሁ መንፈሱ ስሜት፥ ሲረበሽ መላ ሰውነቱ እንደ ነገርኳችሁ መንፈሱ ስሜቱ፥ ሲረበሽ መላ ሰውነቱ ይርበተበታል ማለት ነው። የጨበታ ውጊያ ከሆነማ፥ ሳንጃ የተሰካበት ጠመንጃ ወደ ሰማይ አቅንቶ ከወዲያው ወዲህ ይወራጫል እንጂ ጠላት መጥቶ ቢዘከዝከው ስንኳ ከቶ አይሞክረውም። ከመሠረቱም ውትድርና እንዴት እንደ ገባ፥ ለምን እንደማይወጣ ብዙዎቻችን በጣም ይገርመን ነበር። ይህም ሁሉ ሆኖ የሚገርመው ሌላ ነገር፥ የሻለቃው ጦር ሠፈር ሰው ሁሉ ያፈቅረው ነበር። ደሞም የሚፈቀር ነበር። በሰው ላይ ከማነጣጠር ሌላ ፍርሃት የለበትም። በዚህ ላይ ለሰው ሁሉ አሳቢና ትሑት ነበር። በዚህ ጠባዩ ግን ሁሉም እያዘነ እየተጨነቀና ስንኖር ሐሳቡ ከማን እንደ መነጨ አይታወቅም የሻለቃው ጦር አዛዥ ልክ ዛሬ እኔ ለማስረሻ እንዳደረግሁት ያለ እርምጃ መውሰድ ግድ ሆነባቸው። »

«እምቦሳ አስገደሉት በለና! » ሲል አንደኛው ጠየቀ።

«አይደለም » ሲል አሠልጣኙ በጉጉት ስላዳመጡት እየተኩራራ ቀጠለ፤ «ወታደሩ ልክ እንደ ልጅ የሚወስደውና የሚንከባከበው ውሻ ነበረው። የራሱን ራሽን ሳይቀር አካፍሎ የሚያበላው። ታዲያ የሻለቃው አዛዥ አንድ ቀን ውሻውን ይዞ እንዲመጣ ወታደሩን አዘዙትና ሽጉጣቸውን አውጥተው ‹በል ግደለው› አሉት። ግራ ገባው። ሰውነቱ ሁሉ እንደ መንቀጥቀጥ አለ። ምክንያት የጠየቃቸው። ‹የጠላት መሣሪያ ሰላይ ሆኖ ተገኝቶ የሞት ቅጣት ተበይኖበታልና ግደለው› አሉት። ውሻው የተገኘው ጠላት ባደፈጠበት ሥፍራ ነበር። ሳናሳውቀው ጠላንት ከመሸገበት ከመግባታችን በፊት የውሻ ቡችላ ድምፅ ሰማንና በዚያ ድቅድቅ ጨለማ ምንም ነገር የሌለበት በሚመስለው ጭር ያለ አካባቢ ሕይወት መኖሩን ዐውቀን ወዲያው ቦታ ያዝን። ከበን አድረን በበነጋው ዶግ አመድ አደረግናቸው። ቡችላ ውሻው በጩኸት ባያነቃን ኖሮ በወገን ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስ ስለ ነበር ጦር ሠፈሩ የሚመለከተው እንደ ባለ ውለታ አድርጐ ነበር። ያ ውታደር እንደ ልጅ ተንከባክቦ ያላደገውም በዚህ

ምክንያት ነበር። ታዲያ ውሻው አንዳንድ ጊዜ ወደ በረሃ እየሄደ ይቆይ ስለ ነበር አዛዡ በስለላ ሲወነጅሉበት ወታደሩ ለማንና ላለማመን ግራ ተጋብቶ ‹ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ ራስዎ ይግደሉታ!› አለ በተሠቃየ ስሜት። አዛዡ ግን የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው የወንጀለኛው ውሻ ባለ ቤት እርሱ መሆኑን ቅጣቱን እንዲፈጸምበት ከበላይ አዛዥ ሲታዘዝ እምቢ ቢል ራሱ ጦር ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ በከፍተኛ ቁጣ ነገሩት። ወታደሩም መንፈሱ ብዙ ከተሠቃየ በኋላ ትእዛዝ ከመፈጸም በቀር ምንም ምርጫ እንደ ሌለው በመገንዘብ፤ እጁ እየተንቀጠቀጠ ሽጉጡን ከውሻው ግንባር ላይ ደግኖ ተኲሰና ገደለው። ከዚያ በኋላ ሌላ ሰው ሆነ! ጠላትን ግንባር - ግንባሩን የሚቀነድብ ተኳሽ ወጣው! »

ታሪኩን ሲጨርስ ሁሉም ተገርመው ዝም አሉ። እምቦሳዋን እንዲሁ ታሪክ የገባት ይመስል አንገቷን ቀና አድርጋ ተመለከተቻቸው።

«እና ማስረሻም ያሳደገውና የሚወደው ውሻ ባይኖረውም በዚች የምታምር እምቦሳ ከስሜት ነጻ ይወጣል » አለ አሠልጣኙ ከፈገግታ ጋር።

«የሰው ከብት መግደል ራሱ ወንጀል ነው! » አለ ማስረሻ መልሶ በመወራጨት።

»ከተጠየቅን ዋጋዋን እከፍላለሁ። ያሳሰበህ እሱ ከሆነም አስቀድሜ አሁኑኑ ሄጄ ለባለቤቱ ዋጋውን ከፍዬ ልምጣ እችላለሁ።

«እሱም ቢሆን አላደርገውም። »

«በግና ዶሮ አርደህ አታውቅም? ‹ዶሮ ሲታረድ ያለቅሳሉ ወጡ ሲቀርብ ብልት ከብልት ያማርጣሉ› የሚለውን የአንዲት ሴት አሪክ አስታወሰኝ። »

«ያ - ሌላ ነው » ሲል ማስረሻ አሁንም ፍርጥም አድርጎ መለሰ።

«እንዲያውም ለእንስሶቹ ከማረድ ይልቅ በጥይት መግደል ሥቃያቸውን ያቀልላቸዋል። »

ማስረሻ ባለ መስማማት ራሱን ነቀነቀ። «የሚሠራ ከሆነ ምናለበት - በል - ምንም አይደል! » ሲሉ ሌሎቹ አዋከቡት። በግና ፍየል ማረድ በየቀኑ የሚያደርጉት ተራ ነገር መሆኑን ሲያስቡት ቀላል ነገር መስሎ ታያቸው። አሠልጣኙ አሁንም ኮልቱን ዘርግቶለት እምቦሳዋ በዚያ ጭር ያለ ሜዳ መካከል ቁማ ፍርድ እየጠእበቀች ሌሎቹ ከሥላቅ ጋር ሲደፋፈሩት ሲገፋፉት ትንሽ እንደ ቆየ ማስረሻ ሳይታወቀው በደመ ነፍስ ሽጉጡን ቀበል አደረገና ወደ እምቦሳዋ

አግጣጫ ደገነ። ግን በሚገባ አነጣጥሮ ሳይተኩስ ዝም ብሎ እንደ ቆመ ቀረ። ያፈጠጠ ዐይኑ ከአካባቢው ውጭ ሌላ ዓለም የሚያይ መሰለ። ከሕልሙ የባነነው ነገሩ ሁሉ በቅጽበት ከተፈጸመ በኋላ ነበር። አሠልጣኙ በካራቴ ቅልጥፍና ማስረሻ ሽጉጡን በጨበጠበት እጁ ላይ ራሱን ቀኝ እጅ ደርቦ ከቃታው ቀለበት ውስጥ አስገባና የአፈሙዙን አግጣጫ መርቶ እያስተካከለ፥ አከታትለው ሁለት ጥይት ተኰሱ። እምቦሳዋ እንደ ኳስ ወደ ላይ ጉና ስትወድቅ በማስረሻ ዐይን ውልብ አለችበት።

«በቃ ሌላ ሰው ነው የምትሆነው » አለ አሠልጣኙ ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ። ነገሩን ለመርሳትና ለማስረሳት ሌሎቹ መቀላለድ ቢሞክሩም፤ ማስረሻ የታች ከንፈሩን ጥሎ ያን ያጋደለ ትከሻውን ይበልጥ አዝምሞ ምንም ነገር አልተናገረም። «በል በተለወጠ ስሜትህ እስክንገናኝ » አለው አሠልጣኙ ከፈገግታ ጋር ማስረሻን ከመድረሻው ላይ ከአውቶሞቢሉ ሲያወርደው።

የማስረሻ ስሜት በመጠኑ ተለወጠ። ግን አሠልጣኙ ባሰበው መንገድ አልነበረም። ሌሊቱን ከንዴትና ከብስጭት ጋር በሐሳብ ሲጨነቅ አደረና በበነጋው ጧት በቴሌፎን ተቃጥሮ ከደረበ ጋር ተገናኘ።

«አሃሃ! ምንድን ነው እንዲህ የሚያጣድፍ ጉዳይ የማይውል የማያድር? » ሲል ደረበ ጠየቀው ከመሥሪያ ቤቱ ጠብቆት ከተገናኙ በኋላ። በመሥሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ ብዙ የሠራተኛ እንቅስቃሴና ሁካታ አለ። ደረበም ፍንጭት ጥርሱን እየገለፈጠ፥ ከዚህም ከዚያም ጋር «አሃሃ! » በማለት ይቀላለዳል።

«ትንሽ ጸጥ - ሰወር ወዳለ ቦት ሄደን በእርጋታ ብነግርህ አይሻልም? » ሲል ማስረሻ ጠየቀው።

«በዚህ አገር የሙያ አክብሮት እንደምታውቀው ነውና የኔ ቢሮ ሌላ ደባል አለበት። ታዲያ በእንደዚህ ያለ አካባቢ ከያኒ እንዴት መፍጠር ይችላል? » ሲል የግሉን ቅሬታ በማጋነን ቅላጼ ከገለጸ በኋላ፥ ዘዴ በድንገት እንደ ተከሰተለት ጣቱን ፏጨና «ወጣ ብለን በመኪናዬ ውስጥ ቡና እየጠጣን ልትነግረኝ ትችላለህ » አለ።

«ብዙም ጊዜ የሚወስድ አይደለም። ከዚህ ወጣብ ብለን ልንጨርሰው እንችላለን። » ማስረሻ ነገሩን ሁሉ እንደ ጠላው ከደረበ ጋር ባንድ መኪና ውስጥ መቀመጡንም እንደ ጭራቅ ፈራው። ጠላው። በመሥሪያ ቤቱ ጐን ከሚያልፈው አውራ ጐዳና ማዶ ባዶ ገላጣ ሥፍራ አለ። ወደዚያ አመሩ።

ነገር የሚቀልብ ጆሮ በአጠገብ አለ መኖሩን ሁለቱም ተገላምጠው ከአረጋገጡ በኋላ «እሺ አጣዳፊ ችግርህ ምን ነበር? » ሲል ደረበ ጠየቀ መልሱን አስቀድሞ የሚያውቅ በመምሰል ሁናቴ «የእስኳድ ሥልጠና አስቸገረህ? ሰምቻለሁ። »

«ማንኛውም - » አለ ማስረሻ ርግጥ አርጐ ሰውነቱ እንደ መወራጨት እየቃጣው -

«አሃሃሃ! ምነው? » ሲል ድንገት አቋረጠው። ማስረሻን የሚያበሽቀው ይህ የደረበ በሁሉም ነገር ማሾፉ መሣለቁ ነው።

«በቃኝ! »

«ትል ምግብ አይደለም የሚበቃ፤ አሃሃሃ! »

«እንግዲያው በሌላ ቃል አልፈልግም! አውሎሞቢሌ ደግሞ እንድትመለስልኝ እፈልጋለሁ! » ከቡድናቸው ሲወጣ ከሥራም ያስወጡት እንደሆነ እሷን ሸጦ እስከ ጊዜው ስንቅ ለማድረግ አስቦ ነበር።

«ላለመፈለግ መብት አለህ። ግን ድርጅትኮ ማኅበር ወይም ሰንበቴ አይደለም። እንደ ፈለግህ የምትገባበትና የምትወጣበት። » ደረበ ለመሣቅ ይሁን ለመጋጥ በማይለይ አኳኋን ፍልጥ ጥርሱን አገጠጠበት።

«በፊትም ፈልጌ አልገባሁም። አሁን ከውስጥ ሁኘ ሳየው ደግሞ ፈጽሞ ከተፈጥሮዬ ከአስተሳሰብቤ ጋር መስማማት ቀርቶ እንዲያው - እንዲያው ምን ብዬ ልግልጸልህ? ከቆየሁ አማኑኤል መግባቴ የማይቀር ነው። ተመልሼ መግባት ደግሞ አልፈልግም። ላልጠቅማሁ፥ ይቅርታ አድርጉልኝና - » ከጭንቀቱ? ከምሬቱ የተነሣ ሳግ ተናነቀው።

«አሃሃሃ! ስሜትህ ይገባኛል። አልፈርድብህም። ለትግል የተፈጠረ አለ - ሌላም የተወለደ አለ » አለ ደረበ፥ በታበየ የአዘኔታ አነጋገር፤ «ግን መመሪያ ተላልፎልኝ ወደ እኔ ሕዋስ መጣህ እንጂ እኔ አላስገባሁህም። ስለዚህም እኔ ላስወጣህ አልችልም። ጻፍና አምጣ፤ ለበላይ አካል አስተላልፍልሃለሁ። »

«ምን ልጻፍ? »

«የሕይወት ታሪክህን ለመውጣት የፈለግህበትን ምክንያት በዝርዝር። »

«ምክንያቴን እሺ ልግለጽ፤ የሕይወት ታሪኬ ግን ምን አገባው? »

«ምክንያትህ ከሕይወት ታሪክህ የመነጨ፤ የተያያዘ ነው። ሆድና ጀርባ ማለት ናቸው። አሃሃሃሃ! »

«እሺ! » የማስረሻ ድምፅ የኮሰሰ ነበር።

«እህህ - » አለ ደረበ የተረሳውን ጉዳይ ድንገት ያስታውሰው በመምሰል፤ «መኪናዋን ግን በማንኛውም ሰዓት መውሰድ ትችላለህ። »

## ፬

እንደ ተነገረው ማስረሻ አውቶሞቢሉን ከሰዓት በኋላ ከመሥሪያ ቤቱ ድረስ መጣችለት። በበነጋው ጧት ከቢሮው ገብቶ የሚፈጽመውን ማመልከቻ በማሰላሰል ላይ እንዳለ፥ የትራፊክ ፖሊስ ከቢሮው ዘው ብሎ ገባ።

«አዎ ማስረሻ? »

«ነኝ። »

«ማስረሻ ሙሔ? »

«አዎ! »

«እንዴ ይፈለጋሉ። »

«የት? »

«ትራፊክ ጽሕፈት ቤት። »

ፍርሃትም ድንጋጤም ሳይሰማው ከመገረም የተነሣ ድንብዝ አለበትና ምንም ሳይናገር ቁልፉን በጣት ላይ እያሽከረከረ ከመኪናው አጠገብ ሲደርስ ሌላ የታጠቀ ፖሊስ ቁሞ ጠበቀው። የሰሌዳ ቁጥሩን ተናግሮ፤ «ይህች ቮልስዋገን አውቶሞቢል የርስዎ ናት? » ሲል ጠየቀው። በአወንታ መለሰላቸው።

አንደኛው ፖሊስ ከማስረሻ ጐን ተሣፍሮ ሌላ የፖሊስ ቮልስዋገን እየተከተለው እንደ ተለመደው አራዳ የትራፊክ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት ሳይሆን ከአንድ ፖሊስ ጣቢያ ገብቶ ቃሉን እንዲሰጥ ተጠየቀ።

«ምንድን ነው ወንጀሌ? » ሲል ማስረሻ በተቻለ መጠን የተኮሳተረና መብቱንም የሚያስከብር መስሎ ጠየቀ።

«የትራፊክ ወንጀል! » የሚል ደረቅ መልስ ተሰጠው።

«ታዲያ የትራፊክ ጥፋት » አለ ማስረሻ «ጥፋት » የሚለውን ቃል አስተካክሎ በመድገም «የትራፊክ ጥፋት ከሆነ ትራፊክ ጽሕፈት ቤት እንጂ ፖሊስ ጣቢያ የሚያስመጣኝ ምክንያት አልገባኝም። »

«ጥፋትኮ ያው ወንጀል ነው። ያጠፋ ወንጀለኛ ደግሞ በመጀመሪያ ቀርቦ የሚመረመረው በአመቸው ፖሊስ ጣቢያ ነው። ወይስ የተለየ አሠራር አለ? » ማስረሻ መልስ ስላልሰጠ ፖሊሱ ጥያቄውን ቀጠለ።

«ወንጀልህን ታውቀዋለህ »

ማስረሻ በአሉታ ራሱን ነቀነቀ።

«እንዴታ አታውቀውም? » ሲለው ‹ጠንቋይ አልቀልብ› ማለት ቃጣውና ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ቀልድ እንደማያዋጣ በመገንዘብ ዝም ብሎ ጠየቀው።

«ወንጀልህን ባታውቅ ነው መኪናህን የደበቅኸው አንተም የጠፋኸው? ለረጅም ጊዜ። » እንደ ተለመደው ማስረሻ ወንበር ላይ ተቀምጦ በእርጋታ ቃሉን በመስጠት ፈንታ እንደ ቆመ እከካም እጅ የፎከተው ይመስል ወለሉ በተፋፋቀው ጠረጴዛ ፊት ለፊት ተፋጠጡ።

«አልገባኝም የምትናገረው! » አለ ማስረሻ መብቱን ለማሳወቅ ያህል ከእንጨት ወንበር ላይ እየተቀመጠ።

ቃል ተቀባዩ ከጠረጴዛው ቀኝ ጠርዝ በኩል የዕለት ሁናቴ ከመመዝገቢያው ትልቅ መዝገብ ሥር አንድ ዶሴ አወጣና ማስረሻን ቀና ብሎ ሳያይ ተኮሳትሮ አነበበ። «በዚህችው አውቶሞቢልህ ሰው ገጭተህ አልጠፋህም? »

«መቸ? » ማስረሻ የተከሰሰው በየትኛው ጥፋት እንደ ሆነ ቢገምትም ከስንት ጊዜ በኋላ ድንገት መያዙ ሌላም ጥርጣሬ ስላሳደረበት ከከሳሾች ተረጋግጦ እስኪመጣ ማመን አልፈለገም።

ፖሊሱ ዓመተ ምሕረቱን ወሩን ቀኑኑንና ሰዓቱን ጠቀሰለትና «በዚህ ቀን አደጋ አድርሰህ አምልጠሃል! »

«ትዝ አይለኝም! » መልሱን ለማጠናከር ማስረሻ ራሱን ነቀነቀ።

«ትዝ አይለኝም? እርግጥ ለጊዜው በስካር ጠንብዘህ ነበር ይሆናል። በኋላ እንዳገኘነው መረጃ። ወንጀል መሥራትህን ስትገነዘብ ግን አንተም

አውቶሞቢልህም ጫካ እንደ ገባ ሽፍታ ለስንት ጊዜ ተሠውራችሁ ስትኖሩ እነሆ አሁን በሕግ እጅ ወደቃችሁ። »

አሁን የክሱን አንድ ክፍል አረጋገጠ። እንደ ቅዠት ደብዝዞ ርቆ በሚታይ ዓለም ውስጥ ከሦስት ዓመት በፊት ከድንጋይ ጋር ይሁን ከኤሌክሪክ ምሰሶ ከሰው ይሁን ከእንስሳ ጋር የተጋጩበት አደጋ ነበር። በአደጋው ስለ ደረሰው ጉዳት ፈለገ። «እናንተ እንዳላችሁት አደጋ አደረስኩ እንበል። እና የተከሰስኩበት የወንጀል አንቀጽ ምንድን ነው » ሲል ቃል ተቀባዩን መልሶ ጠየቀው።

«እኔ አንቀጽ አልጠቅስልህም፤ እሱ የዐቃቤ ሕግ ሥራ ነው » ሲል ፖሊሱ ትከሻውን ወደ ላይ ገፋ አደረገ።

«እሺ አንቀጽ ይቅር » አለ ማስረሻ ቀደም ሲል የተደናገረውን ያህል አሁን ክርክሩ እንደ ተጠናከረለት በመገመት አነጋገሩን የማባበል መልክ አስይዞ «በትክክል ወንጀሌ ምንድን ነው? »

«ከመጠን በላይ አልኮል ጠጥቶ መንዳት - አንድ። ቃል ተቀባዩ ጣቱን አንድ ባንድ ወደ ላይ እየቀሰረ ቆጠረለት። በዚህም ምክንያት ሰው ገጭቶ እምግደል ሁለት። ከገጨ በኋላ አምልጦ መጥፋት ሦስት! አይበቃም? » ሲል ቃል ተቀባዩ በማሽሟጠጥ ጠየቀው።

«እሱስ ይበቃል » አለ ማስረሻ ሁናቴው ይበልጥ ሲያስገርመው፤ ክሱ አሁን ለተቀሰቀሰበት ምክንያት አንዳንድ ፍንጭ እንደ ጧት ውጋጋን ሲታየው የበለጠ እየገረመው «ግን ለዚህ ሁሉ ወንጀሌ ቅጣቱ ምን ይሆናል? »

የጣቢያው ቃል ተቀባይ ጥያቄው የማይመለከተው መሆኑን በመግለጽ ትከሻውን ወደ ላይ ገፍቶ አወረደና «አንተ እንደ ተመርማሪ እንደ ተከሳሽ መሆንህ ቀርቶ፣ እኔን ትመረምረኛና ታስለፈልፈኝ ገባህ - አሆሆ! » ካለ በኋላ «እኔ ምናውቃለሁ። ይሄን ያህል ዓመት እስራት፤ ይሄን ያህል ሺህ ብር መቀጫ፤ ከዚህ አልፎ ደግሞ በፍትሐ ብሔር ክስ ለተጐጂ ቤተሰቦች ብዙ ሺህ ብር ካሣ እንግዲህ ዝርዝሩ የሚወሰነው እንደ ዐቃቤ ሕጉ አቀራረብ እንደ ዳኞች ስሜት ነው » ሲል መለሰለት። «ደግሞም ደግሞም » አለ የነገሩን ክብደት ለማረጋገጥ አተኩሮ እየተመለከተው «አንተ የቀድሞ ያውም የኢትዮጵያን አብዮት ለማፈን የመሳፍንቱ መንግሥት ከፍተኛ ወንጀል ይፈጽም በነበረበት ጊዜ ባለሥልጣን ስለ ነበርክ በሌላ ወንጀልም ትፈለግ ይሆናል። ከስልሳዎቹ የበለጠ ወንጀል የፈጸሙ ብዙዎቹ እኮ ገና ልቅ ናቸው።

ማስረሻ ለቀረበለት አዲስ ክስ ምንም መልስ አልሰጠም። በፍርሃት አይሉት በመገረም ስሜት ደንዝዞ ስለ ነበር የሚሰጠው መስል አልነበረውም። ከስሜት ድንዘዛ ነቃ ያለው ዕቃውን እንዲያስረክብ ሲጠየቅ ነው።

«ቀበቶ? » ሲል በመገረም ጠየቀ። ፖሊስ ጣቢያ ሲታሰር የመጀመሪያ ጊዜው ስለ ነበር ቀበቶና ሰዓት መፍታት መኖሩን አያውቅም ነበር።

«አዎ! ማረፊያ ቤት ትቆያህ! »

በዞ ፈታትሾ ማስረሻ ወደ እሥር ቤቱ ተሰደው።

እሥር ቤቱ ከፖሊስ ጣቢያው ጀርባ በዛኒጋባ መልክ ከከፍተኛ የድንጋይ ግንብ ጋር የጠጣበቀ ሁለት ማዕዘን ነው። ከፖሊስ ጣቢያው ቤት በቆርቆሮ አጥር የሚለየው የእሥር ቤቱ ክፍል ከዝቅተኛ ቦታ ላይ የሚገኝ ሲሆን የዛኒጋባው ክፍሎች አቀማመት ከፍታም እንደዚሁ የተለያየ ነው። ከአንድ ማዕዘን በኩል ያለው አራት ክፍል ትንሽ ከፍ ያለ ሁኖ በእርሱ አግዳም ያለው ስድስት ክፍል እያዘቀዘቀ ይሄዳል። የክፍሎቹ ወለል ግን የውሀ ልክ የተደለደለ ስለሆነ እንደ መሬቱ አቀማመጥ ከአንድ በኩል ከፍ ከሌላው በኩል ዝቅ እያለ የሄደ ነው።

ዘቡ ማስረሻን ወስዶ ከመጨረሻው ረባዳ ላይ ከምትገኘው የመጨረሻ ክፍል አስገባው። ከዚች ክፍል ትይዩ የፖሊስ ጣቢያውን ከሚያካልለው የቆርቆሮ አጥር ግቢ አጠገብ ጉራጅ በርሜል የሽንት ዕቃ አለ። ሌሊት ከቆርቆሮው አጥር ውጭ ወደ ሚገኘው ሽንት ቤት መሄድ ስለማይቻል ሽንት መክፈል የሚፈልጉ እሥረኞች ሁሉ የየራሳቸውን ወይም ከሌሎች የሚጋሩትን ጣሳም ይሁን ሌላ መክፈያ በአቅራቢያቸው አስቀምጠው ባስፈለጋቸው ጊዜ እየከፈሉ ወደ ሽንት ዕቃው ወስደው ሲገለብጡ ያድሩና ጧት ጉማጅ በርሜል በጅንባ ጅንቦ ወደ ሽንት ቤት ተወስዶ ይፈስሳል። ግን መክፈያቸውን እየያዙ በጨለማ ወደ ሽንት ቤት ከሚሄዱት መካከል ብዙዎቹ በላዩ ስለሚያፈሱ ስለሚያፈሱ እንዲያውም ሳይደርሱ የደረሱ መስሏቸው ወይም በግዴለሽነት ከአጠገቡ አፍስሰው ስለሚመለሱ ይህ ሁሉ እየተጠራቀመ ወርዶ ከመጨረሻዋ ክፍል በር ላይ ትንሽ ኩሬ ይሆናል። ኩሬውም እንደዚሁ ሞልቶ በመንቸርፈፍ በበሩ ሥር ኮለ እያለ ወደዚች ክፍል የሚገባበት ጊዜ አለ።

ማስረሻ በክፍልዋ ውስጥ እንደርሱው አማኑኤል መግባት ያለበት የሚመስል ብቻውን የሚያነበንብ ቡትቶ ለባሽ ብቻ አገኘ። ሌሊት አለባበሳቸው ከበረንዳ አዳሪ ዱርዬ የማይሻል ራሳቸውን የሳቱ ሁለት ሰካራሞች ተጨመሩ።

ከወለሉ አልፎ እስከ ግድግዳው አጋማሽ የተለቀለቀው ከትውከት እስከ ዐይነ ምድር ድረስ ያለው ቁሻሻ በዚያ ላይ አዲስ የገቡት ሰካራሞች ሆድ ዕቃቸው ተገልብጦ የሚወጣ እስኪመስል ድረስ ቧ! እያደረጉ የሚለቁት ሁሉ ተጨምሮ ማድረሻ ከአንድ ትልቅ የመጸዳጃ ጉድጓድ ውስጥ የተዘፈቀ መሰለው። ሽታውን ለመከላከል አፍንጫውን በጣቶቹ ፈጥርቆ ያዘ። አጸያፊውን ነገር ሁሉ ላለማየት ዐይኑን ጨፈነ። የሚፈነዳ የሚመስለውን የትውከት ድምፅ ላለመስማት ጆሮውን ከደነ። ግን ጥቂት እንደ ቆዩ የራሱንም ትውከት እንደ ግንፍለት ገፍቶ መጣበት። ለመገደብ አፉን ጥርቅም አድርጐ ለተጨማሪ ማረጋገጫ አንድ መዳፉን ከደነበት። እስኪወራጭ እስኪንፈራፈር ድረስ ታግሎ ከአቅሙ በላይ በሆነ ኃይል ፈነዳበት። እሱም እንደ ሌሎቹ ለቀቀው። ለመጀመሪያ ጊዜ ትንሽ ቀለለው። መልሶ እየተጠራቀመ እየገፋ መጣበት። ተሸንፎ አሁንም ለክፍሉ ሁናቴ ተጨማሪ ድርሻውን አበእከተ። ትውከት የቆመለት ሆድ እቃው እንደ ወተት አንጀት ታልቦ ሆዱ ከጀርባው የተጣበቀ ከመሰለው በኋላ ነበር። ከዚህም በኋላ ቢሆን በደረቁ እየተናነቀው ጉሮሮው በሞረድ የተፋቀ እስኪመስለው ድረስ ቋቅ እያለው ሌሊቱን አጋመሰ። ከዚያም ከሰውነቱ መዳከም የተነሣ እንቅልፍ ሸለብ ሸለብ ሲያደርገው የሚያየው ቅዠት ከእውኑ የተሻለ አልነበረም። አማኑኤል ሆስፒስታል ከመጨረሻው ሰብአዊነታቸውን ከሳቱት ሦስተኛ ደረጃ ገብቶ አድኑ ሲያንቀው ሌላው ሲያፍነው ሦስተኛው በእውን የማይመስል ነገር ሲፈጸምበት እየታየው ከሰካራሞቹ ባላነሰ ጩኸት ይባንናል።

ማስረሻ ስለ ተመደበበት የእሥረኞች ክፍል በመጠኑ ያውቀው በበነጋው ጧት ነበር። ጧት ወደ መጸዳጃ ክፍል ለመሄድ ሁሉም በየክፍላቸው እየወጡ ሲከለኮሉ ከላይኛው ማዕዘን የመጣ አንድ እሥረኛ ማስረሻ አለባበሱ ደህና መሆኑን ተመለከተና «ምን አጥፍተህ ነው ሽቶ ቤት ያስገቡህ? » ሲል ጠየቀው።

«እ - እ? » ሲል ማስረሻ መልኩን አጨፍጐ በአስተያየቱ ጠየቀ።

«ማጠንቷ እንዴት እንደሚያውድ አይተሃል የለ? በዚህም ምክንያት ሽቶ ቤት ወይም የአርሻቤ እልፍኝ ትባላለች » አለ ሌላው እሥረኛ በመጠየፍ አኳኋን ክፍሏን እየተመለከተ። ስለዚህም ከዚያች እንዲገቡ የሚደረግ ዘቡና ሌሎቹ የጣቢያው ሰዎች የሚጠሉዋቸው ሌሎችን እሥረኞች እያወኩ የሚያስቸግሩት ወይም ልማደኛ ሰካራሞች ናቸው። አንተ ግን አትመስልም። በምን ታሥረህ ነው? »

«በትራፊክ አደጋ። »

«ታዲያ በአርሻቤ እልፍኝ ለም አስገቡህ? በስሕተት ከሆነ እንዲያዛውሩህ ጠይቅ » ሲል ማስረሻን መከረው።

እንደ ተመከረው ሲጠይቅ ግን የተሰተው መልስ «የትኛው ክፍል መታሠር እንዳለብህ መራጩና ወሳኙ አንተ አይደለህም » የሚል ነበር።

በሁለተኛው ቀን ታፈሱ ምግብ ይዛለት መጣችና ላንዳፍታ እንድታነጋግረው ዘነቡ ለምና ፈቀደላት። «ምን አለፋሽ? ለመሆኑ ማን ነገረሽ? » አለ ማስረሻ - ልትጠየቀ በመምጣቷ ባንድ በኩል ደስ እያለው በሌላ በኩል ተጐሳቁሎ በሴት ፊት መታየቱን እንደ ውርደት ቆጥሮት ቅር አየለው። እንደ አጋጣሚ ቢሮው ደውላ ተላላኪው በትራፊክ ፖሊስ መወሰዱን እንደ ገለጸላትና ሁለት ፖሊስ ጣቢያ ጠይቃ በሦስተኛው እንዳገኘችው ነገረችው። «በቃ - በቃ! » እያለ ዘቡ ሲያጣድፋቸው «እንዲረዳህ ደረበን እጠይቀዋለሁ » አለችው።

«ማን ሆነና - » ሲል ጀመረና ጥርጣሬ እንጂ እርግጠኛ ስላልነበረ ንግግሩን ሳይጨርስ ተወው። ዘቡም አቋረጣቸው።

በሦስተኛው ቀን ቃሉን ከተቀበለው መርማሪ ፊት ቀርቦ የመኪናዋ ቁልፍ ተሰጥቶ «መሄድ ትችላለህ! » ተባለ።

«መጀመሪያ ለምን ታሠርኩ? አሁንስ እንዴት ተፈታሁ? » ማስረሻ ድንገት የመለቀቁ እንቆቅልሽ የመታሠሩን ያህል አበሸቀው።

«መፈታት አልፈልግም ነው የምትለው? » ሲል መርማሪው አጨንቁሮ እየተመለከተ ጠየቀው።

«ነገሩ ስላልገባኝ ነው እንጂ። »

«ምንም ግራ የሚያጋባ ነገር የለበትም። በትራፊክ አደጋ ጥፋት ተያዝክ። ፍርድ ቤት እስክትቀርብ ጓደኞችህ የአሥር ሺህ ብር ዋስ ሆኑልህ። »

«ጓደኞቸ? » አለ ማሰረሻ ከምጸት ሣቅ ጋር።

## ፳

ከአርሻቤ እልፍኝ የሸመተው ብርቱ ጉንፋንና ብስጭት ሁለት ቀን እንዳስተኛው ምን ማድረግ እንዳለበት ማስረሻ በእርጋታ ያውጠነጥን ገባ። ችኮላ

እልህና የንዴት እርምጃ እንደማያዋጣው አይቷል። ራሱ እንደ ትንሽ ተባይ ኖኖ በግዙፍ ጭራቅ መዳፍ ውስጥ እንደ ተጨበጠ ሆኖ ተሰማው።

አውጥቶ አውርዶ ውሎ ቢጠፋው በቁጥጥሩ ሥር ስለ አዋለው ኃይል ከእርሱ የተሻለ ዕውቀት ካላት ከታፈሱ ጋር በጥሞና ተወያዩበት። በጊዜው ስለ እርሱ ደግ የሚያስብ ከእርሷ የቀረበ ጓደኛ አልታየውም።

«እኮ ምን ትመክሪኛለሽ? አሁንም እምቢ ብዬ እንደ ገና አርሻቤ እልፍኝ ወይም ከዚያ ወደ ባሰ ምናልባትም ዓለም በቃኝ መግባት ነው። ወይም ከዚሁ ውስጥ ቆይቼ እንደ ገና ቀውሼ አማኑኤል መመለስ ነው » አለ ማስረሻ ብሽቀቱን ለመሸፈን ከአንገት በላይ ፈገግታ እያሳየ። ታፈሱ «የገቢ » ወይም «ይወጪ » በሚል የቀልድ ሰበብ የዶሮ ወጥ ምሳ ከቤትዋ ኃብዛው ማዕድ ተነሥቶ የዶሮ ዐይን የመሰለ ጠላ ይጐነጯሉ።

«እስቲ ትንሽ ታገሥና ቻለው » አለች ታፈሱ በሚያባብሉ ልም ዐኖቿ አተኩራ እየተመለከተችው። «አየህ፤ ድርጅቱ ሲገቡበት እንደ ሠረገላ በር ሰፊ፤ ሲወጡ ደግሞ እንደ መርፌ ቀዳዳ ጠባብ ነው ተብሏል። ስለዚህ በትዕግሥት መቻል ነው። ዘዴ እስኪገኝ ድረስ። »

«ምኑን ታገሥኩት። አሁንማ ከመቸውም ጊዜ የባሰ አስጠላኝ። እንደዚህ ያለ አሠራር ‹የማፍያ› እንጂ የፖለቲካ ድርጅት ነው? አንቺስ ቢሆን ታምኝባታለሽ? ትቀበይዋለሽ? » ማስረሻ ሳይታወቀው አፈጠጠባት።

«ልክ አለመሆኑ ይገባኛል። የእኔን እምነት በሚመለከት ረገድ ካሁን ቀደም ነግሬሃለሁ። ግን አሁን እኮ ድርጅቱ ያረገው ለመሆኑ ምንም ማስረጃ የለም። »

«ሌላ ማን ሊሆን ይችላል? መውጣት እፈልጋለሁ ካልኩ ሃያ አራት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ስንት ዓመት የቆየ የትራፊክ ጥፋት ድንገት ተቀስቅሶ አድራሻዬ ድንገት ታውቆ መያዝ ሆን ተብሎ ከመጨረሻዋ አሰቃቂ ክፍል ውስጥ እንድታሰር መደረገ። ድንገት እንደ ታሰርኩ ጓደኞችህ ተሰውሃል ተብዬ ድንገት መለቀቅ። ይሄን ሁሉ ማድረግ የሚችል ማነው? ግልጽ ነው። ፖሊሱ ሳይቀር የተዋሱኝን ጓደኞቼን ስም ሊገልጽልኝ ለምን አልፈለገም? ምክንያት ቢኖረው ነው። አንድ ሰው፣ ገባስ ወጣስ ምን ያህል ይጠቅማቸዋል? ወይም ምን ይጐዳቸዋል? በሰላም ይተውኝ እንጂ አልጠቁምባቸው አላጋልጣቸው። » ንግግሩ ያደከመው ይመስል ማስረጃ በከባዱ ተነፈሰ።

«ታፈሱ መልሱን እንድ ዕንባ ጨምቃ የምታወጣው ይመስል ዐይንዋን ጨፍና በጣቷ ጭቁን ጭቁን አረገችው። ግን'ኮ በአንዱ ጥፋት ሁሉም መወንጀልና መፍረድ አትችልም። »

«ምን ማለትሽ ነው? » ሳይሰበው የጠላ ብርጭቆውን ከአነሣ በኋላ ያላዘወተረው መጠጥ ከራሱ ላይ እንዳይወጣ ሠግቶ መልሶ አስቀመጠው። እሱማ አላደፋፈረችውም።

«ጥርጣሬ እውነትም ቢሆን ደረበ ብቻውን የሠራው ነገር እንደሆነስ? »

ማስረሻ ራሱን ግራና ቀኝ አወዛወዘ። «ለምን? እሱን መድረክ ላይ ሲጫወት ከማናውቀውና ከማልወደው በስተቀር እዚህ ከመግባቴ በፊት ሁለታችን በግል የት እንተዋወቃለን። አሁንም የግል ቂም በቀል በሁለታችን መካከል የለ። እንዲያው በሀገራችን ልማድ እንደሚባለው ኮከባችን እሳትና ውሀ ሆኖ አልገጣጠም አልጣጣም ካላለ በስተቀር። እኔ በበኩሌ ይህንን አላምንበትም። ሊሆን ቢችልም ገና ራሱን አወዛወዘ። «ስለዚህ - ስለዚህ - » ንግግሩን አንጠጥሎ ተወው።

ታፈሱ ንግግሩን እንዲጨርስ ሳትጠይቀው ወይም የራስዋን አስተያየት ሳትሰጥበት ድንገተኛ ጉዳይ እንዳለባት ተነሥታ ወደ ማድቤት ሄደችና ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ስትመለስ ቀደም ሲል ከፊት ለፊቱ የነበረችበትን ፎቴ ትታ ከትልቁ ፎቴ ላይ ከጐኑ ተቀመጠችና ዝም አለች - ዐይኗን ከግድግዳው ላይ ተክላ።

«ምን ሆንሽ? መልስ ጠፋሽ? ስለ ድርጅትስ የምትከራከሪበት? ራሳችንንኮ ነው የምናታልለው ታፈሱ! »

«መልስ የመጥፋት ጉዳይ አይደለም። »

«እህስ? »

አሁንም ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ቆየች - በሐሳብ ተውጣ። «ደረበ በግሉ የሠራው ይሆናል ብዬ የምገምትበት ብዙ ምክንያቶች አሉኝ። አንደኛ በተፈጥሮው እኩይ ነው። ሰውን እያስጨነቀ እያሠቃዬ ሥልጣኑን ማሳየት ደስ ይለዋል። በኦቴሎ ቲአትር ውስጥ ኢያጐን ሆኖ ሲጫወት አይተኸው የለም? በቲአትሩ ውስጥ የተጫወተው ባሕርይ ልክ የራሱ ተፈጥሮ ነው። ሌላም ጥርጣሬ አለኝ። የባዶች ሰርጐ ገብ ሊሆን ይችላል የሚል። »

«ምን? አይገባኝም። ጨርሶ አይገባኝም! » ማስረሻ እንደ መጮህ ቃጣው። ሳይሳበው የጠላውን ብርጭቆ አጋመሰው።

«አየህ እኛ በእነሱ ላይ እንደምናደርገው ሁሉ የእኛን ድርጅት በሰው ዘንድ እንዲጠላ አባሎቹም እንዲበሳጩና እንዲበታተኑ ለማድረግ አንዱ መንገድ እንደርሱ ያለውን እኩይ አስርጎ በማስገባት እንዲያተራምስ ማድረግ ሊሆን ይችላል » አለች።

«ለምን በተለይ በእኔ ላይ? በአንቺም በሌሎችም የሕዋስ አባሎች ላይ እንደዚህ አልከፋም። »

«እንዳልኩህ ግምት ነው፤ ግን በአንተ ላይ እንዲህ የሆነው የትራፊክ አደጋህን የማሽነፊያ መሣሪያ ሆኖ ስለ አገኘው ሊሆን ሲችል ከኛ ግን ከአንተ የበለጠ ጊዜ የቆየን ስለሆነ ከሌሎች አባሎች ጋር እውቂያ ወይም ግንኙነት ስላለን እንደ ፈለገ ሊጫወትብን አይችልም። አትርሳ በአንተ ላይ ቂም፥ በቀል እዳለው ደሞ። »

«የምን ቂም በቀል? »

«አንተ በስልሳ ስድስት ሹም በነበርክ ጊዜ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች በአንተ ላይ አድመዋል ተብሎ የጸጥታ አስከባሪዎች መጥተው በተከፈተው ተኩስ ከሞቱት መካከል አንዱ የእርሱ ወንድም እንደ ነበር አታውቅም? »

ማስረሻ በመገረምና በማስተባበል ነቀነቀ።

«አዎ! ስለዚህ ወንድሙ አንተ ያስገደልክበት መስሎ ሊሰማው ይችላል። ታዲያ እኩይ ተፈጥሮው ደግሞ ካልተበቀለ እረፍት አያገኝም። »

ማስረሻ ፊቱን በሁለት መዳፉ ሸፍኖ ተመሰጠ። በስልሳ ስድስት በመሥሪያ ቤቱ ግቢ የተፈጸመው ድርጊት በሐሳቡ ታየው። የተኩስ ድብልቅልቅ ተሰማው። ሰው ከአለፈ ሕይወቱ ሠቀቀን ነጻ ላይሆን ነው? በቅሬታ ራሱን አወዛወዘ። ታፈሱ ጭንቀቱ ተሰማት። ወደ እርሱ ጠጋ አለችና እንደ ዋዛ ራስዋን ከትከሻው ላይ አስደገፈች። እንደዚህ ሲቀራረቡ የመጀመሪያ ጊዜ ስለ ነበር እንደ ማፈር አለች። ማስረሻ ክንዱን አዞሮ ትከሻዋን በማቀፍ ራስዋን ከደረቱ ላይ አሳረፈው። «ሌላው የበቀል ምክንያቱም እኛው እንሆን ይሆናል። »

«እነማን? » ሲል ጠየቃት ፊቷን በእጁ እያባበሰ።

«እኔና አንተ » አለችና አንገቷን ቀና ድርጋ፤ ልም ዐይኖቿን ከዐይኑ ላይ ተከለች።

«እንዴት? » ሲል ጠየቃት መደባበሱን እንደ ቀጠለ።

«እንዴት እንዳወቀ አላውቅም አንድ ቀን መሽቶብህ ከዚህ ካደርክ ቀን ጀምሮ በአሽሙር እንደነካካኝ ነው።

«አልሆነም እንጂ ታዲያ ቢሆን ምን አገባው! » ደረበን ፊት ለፊት አግኝቶ የሚቆጣው ይመስል ፊቱን ኮስተር አድርጐ።

«እኔ የሱን ፍላጐት ስላልፈጸምኩለት እንደ ውርደት ቆጥሮት ሲበሽቅ አሁን ደሞ እንደ መሰለው ሲጠረጥር የባሰ ቂም በቀል ተሰምቶት ይሆናላ። »

«ለምኖሽ ነበር ማለት ነው? ታዲያ ለእኔ ያለሽ ስሜት የአዘኔታና የርኅራኄ እንደ ሆነ ይገባኛል። ለምን እምቢ አልሽው? » ሲል በቀልድ ፌዝ ጠየቃት። የአንደኛው ሙቀት ወደ ሌላው እየተላለፈ ሰውነታቸው ሲሟሟቅ እየተሰማቸው ሂዶ ነበር።

«አክ እንትፍ! » ታፈሱ እንደ መወራጨት አለች። ሚስት ያለው ወንድ በአጠገቤ ሲያልፍም አይነካኝ! »

«ለምን? »

«ራሴን በሚስቱ ቦታ አድርጌ አየዋለኋ! አንተምኮ ሚስት አለህ! » በቀልድ አኳኋን ፈቀቅ ለማለት ራስዋን ከደረቱ ላይ አነሣች።

ማስረሻ በበኩሉ እቅፉን ወደ ደረቱ ጥብቅ እያደረገ «እንዳንቺው አባባል አክ እንትፍ! » አለ ትከሻውን በማንቀጥቀጥ።

«ስሟን አትጥሪብኝ! »

«ብትገናኙ ምን ታረጋለህ? » ስትል ጠየቀችው አንገቷን መልሳ ከብብቱ ሥር አስደግፋ።

«ምንም። »

«ጉዳት ቢደርስባትስ፤ አታዝንም? »

«ሥራም አላጣሁ! »

«ጉዳት የሚደርስባት ቢሆንስ? ወይም ደግሞ አንተ ርሷ ላይ አንድ እርምጃ እንድትወስድ ብትደረግስ? »

«ሁሉም በራሱ እንደ ሥራው ዋጋውን ያግኝ እንጂ እኔ በርሷም ላይ ሆነ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ አልፈልግም አሁን ይኸ ሁሉ ችግርስ የተፈጠረብኝ በዚህ ምክንያት አይደለም? »

«እና እጅህ አታነሣባትም ማለት ነው? »

«ዛሬ ምን ነክቶሻል? ሲል ጨዋታ አታመጪም? » በቀልድ ቅጣት ትከሻዋን በመዳፉ ቸብ አደረገ።

«ለመሆኑ የአባቷ ስም ማነው? »

«የተጋበዝኩትን ምሳ መልሰሽ በነገር ለማስተፋት እንደ ሆነ ሁለተኛ አይለምደኝም። » እንዳኮረፈ ሕፃን ከንፈሩን ላፍታ ጣል አደረገ።

«ግን ለምን ጠየቅሽኝ? » ሲል ጠየቃት ለጥቆ።

«እንዲሁ። »

ግን በማይመለከታት ነገር እንዲሁ መጠየቅ ጠባይዋ እንዳልሆነ ያውቃል። «አንድ የደበቅሽኝ ነገር አለ። »

ዝም አለች።

«በሞቴ ንገሪኝ » አለና በማባበል ደባበሳት።

«መጀመሪያ ንገሪኝና እነግርሃለሁ። »

ነገራት።

«በግምቴ አልተሳሳትኩም » አለች አብዛኛው ከራስዋ ጋር።

«ምን? »

«ኢንፎርሜሽን በመሰብሰብ ከተመደበች አንዲት ጓደኛዬ ዝርዝር ውስጥ ስምዋን አይቸ ነው። በባንዳነት ከሚጠረጠሩት ስም ዝርዝር። »

«አላምንም! » ማስረሻ በመገረም እንደ መፈናጠር አለ ፡

«አዎ! እንዲያውም ጥናት የምታካሂደው ከቀንደኞቹ ጋር ነው አሉ። »

«አሁን ገና ጥሩ ምሳዬን የሚያበላሽ ነገር አመጣሽ! »

«ይቅርታ እከሳለሁ » አለችና ፈቷን ወደ ከፍነሩ ቀና አረገች።

ማስረሻና ታፈሱ ለጊዜው ፖለቲካውንም ዘለቃንም ረስተው ወደ ራሳቸው ዓለም ሲሰምጡ ዘለቃ አዲሱን የፖለቲካ ሚናዋን በመፈተን ላይ ነበረች።

## ፺

የቀበሌ ሊቀ መንበር ጓደኛው ለደረበ ቴሌፎን ደወለና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ «.....ዛሬ ተበልቼ ነበር ለጥቂት አመለጥኩ! » አለው ትንሽ ድንጋጤ በሰባበረው ድምፅ።

«ማን ሊበላህ? » ሲል ጠየቀ - ደረበ።

«እነሱ ናቸው! አንዲት የቋጥኝ ስባሪ የሚያክሉ ሴት ለምን አሰርክ አለው። »

«አሃሃ - ዋጋህን ነው። አንተ እንደሆነ ሙታንቲ ያደርገ - ማለቴ የጡት መያዣ ያደረገ ካየህ ልጓም አይመልስህ። ለመሆኑ የቋጥኝ ስብሪ ካካሉ የጡት መያዣ ከየት አገኙ! አሃሃሃ! ሃሃ! »

«አትቀልድ የምሬን ነው። »

«እሺ የምርህን ነው። አሃሃሃ! አንዲት አሮጊት ይዘህ ቤተ ክርስቲያን ስታደርስ...... »

«ቴሌፎኑን ልዘጋው ነው ደረበ! አንተ ቁም ነገር የለህም! » ሊቀ መንበሩ ያመረረ መሆኑ በግልጽ ያስታውስ ነበር።

«እሺ! እሺ! ንገረኝ » አለ ደረበ ራሱን ገታ አድርጎ በእጁ ደግሞ የቲአትር መጽሐፍ አቅርቦ እያገላበጠ።

ታሪኩን በቴሌፎን ነገረው......

«በእኛ ቀበሌ ሞሰብ ቤት ያላቸው አንድ ቀብራራ ፊውዳል አሉ። በፊት መኖሪያ ቤትም ነበራቸው፤ አሁን ያንን ትተው ወደዚሁ ተጠቃልለዋል። ታዲያ በሌላ ቀበሌ ያለች አንዲት ሴት ወንድሟን ነው በቅርብ የማውቀው ባሌን

ነጠቁኝ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ፈጸሙ በማለት በጣም ተከሰከሰችብኝና አሳዘነችኝ። አለ አይደል ደስ የምትል ሴትዮ! »

«አሃሃሃ! እና አጽናናት! ደረትህን አስደግፊህ! አሃሃሃ! »

«ደረበ ሙት! አሁንም እዘጋዋለሁ! » አለ ሊቀ መንበር በመረረ አነጋገር።

«አሃሃሃ! እኔ መቸም በቀሚስ እንዴት ጨከንክ ብዬ ነው እንጂ መቀለዴ አይደለም። ይቅርታ! » አለ ደረበ ጠባይ ለጠባይ በቅርብ ስለሚተዋወቁ።

ሊቀ መንበሩ በዝርዝር ተረከለት «.......እና እንዳልኩህ ወንድሟን እንጂ ተበደልኩ ያለችውን ሴት በፊት አላውቃትም ነበር። ከወንድሟ ጋር መጣች። ዕንባዋን እያፈሰሰች አዋየችኝ። ረጋ ያለች ነች። የሚገርምህ ጡረታ የወጣ ፖሊስ ኮሎኔል ሚስት ነች።

«እና አቅፈህ አጽናናት? አሃሃሃ! ይቅርታ! ስሜትህ ስለሚሰማኝ ድንገት ስሜቴ በሐሳብ ወስዶኝ ሙቀት ስለ ተሰማኝ ነው! አሁን በጥሞና አዳምጣለሁ » ስለ ደረበ በግማሽ ልቡ ብዙ ጊዜ ያነበበውን መጽሐፉን እያገላበጠ።

«አሁን ቴሌፎኑን እንዳልዘጋው! ታዳምጠኛለህ? »

«በጥሞና » አለ ደረበ።

«እና ሴትዬዋ አሳዘነችኝና እኒያን አንድስ የሚያከሉ ሴትዮ ትንሽ ለማረም የህል - ትንሽ ለማስደንገጥ ያህል - ትንሽ ለመቅጣት ያህል ቀበሌያችን፥ አስመጣናቸውና ቃላቸውን እየተቀበልን ትንሽ አቆየናቸው። አለ አይደል? እንደምታውቀው። ከዚያ ጠባያቸው አሳምረ ትንሽ ከቆዩ፥ በኋላ ቤት ቴሌፎን ልደውል፥ ‹ቆየሽ ብለው እንዳይጨነቁ› ሲሉ ጠየቁ። እምቢ ማለት አይቻል፤ በሠፈሩ የታወቁ ናቸው። ታዲያ በቴሌፎኑ ብዙም አልተጋነኑም ነበር። ‹እንዳትደነግጡ ቀበሌ ነው ያለሁት› ነበር ያሉት። ማይጨው እንደሚዘምቱ ያህል የኮልትና የአውቶማቲክ ትጥቃቸውን ደቅድቀው እኩል ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ባላንድሮቨር ከተፍ አሉልሃ! በምን ምክንያት እንዳሰርኳቸው ጠየቁኝ። በቀላሉ በሚበረግግ ሰው ቢያገኙ አስተያየታቸውን መሬት የሚያስገባ አስመሰለው። ‹በሞሰብ ቤታቸው ፊውዳሎች የሚዶልቱበት ለመሆኑ ቀበሌው ጥቆማ ስለ ደረሰው ለጥያቄ ነው› አልኳቸው። እንደመጣልኝ። ምናሉኝ መሰልህ? ‹የዲማዎችና የአናርኪስቶች ተንኮ ነው እንጂ ሴትዬዋ አንድ ልጃቸውን ለአብዮቱ ያበረከቱ የታጋይ እናት ናቸውና ይቅርታ!› ተባልኩ። ከይቅርታ ጋር

ወደ ቤታቸው ሸኘኋቸው! አይገርምህም? » ሲል የቀበሌው ሊቀ መንበር ደረበን ጠየቀው።

«ምኑ? » ሲል ደረበ መልሶ ጠየቀ።

«ታጋይነት የሚሉት በዘር፥ ከልጅ ወደ እናት መተላለፉ ነዋ! » የቀበሌው ሊቀ መንበር በፌዝ ትክ ብሎ ሣቀ። ንግግሩን በመቀጠል «ሴትዬዋን ሳታውቃቸው አትቀርም። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ይባላሉ። በከተማው የታወቀች ሽቅርቅር ልጃቸው....በስልሳ ስድስት ተሹሞ በነበረ ጊዜ......ወንድምህንና ሌሎችንም ታጋዮች ያስገደለው......ማነው ስሙ?.....የሱ ሚስት ነበረች። »

«እ - እ ዘለቃ? » የደረበ አነጋገር የጥየቃ ሳይሆን የማረጋገጥ ዓይነት ነበር።

«እና የሄውልህ ሲደነፉብኝ ዋሉ እልሃለሁ » አለ የቀበሌው ሊቀ መንበር።

«ግዴለህም ተዋቸው፤ በቅርብ ጊዜ እስኪለይላቸው ድረስ ነው » ሲል ደረበ መለሰለት።

# ምዕራፍ ስድስት

ውስጥ ለውስጥ መፋጨቱ መፋተጉ መሰጋሰጉ፣ መጠላለፉ መሻኮቱ መፋጠጡ እየተፋፋመ ሄደ። የሚና አሰላለፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለየ። በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ቀበሌ ሹማምንት «አስታጥቁን! አታስጨርሱን » በሚል መፈክር ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ሄደው በደርግ ውስጥ ከነበረው አሰላለፍ የአንዱ ክፍል መሪ ተቀብለው በማነጋገር በትጥቅ በኩል የተቻለውን ያህል እንደሚደረግ ቃል ገቡላቸው። ነገር ግን በዚህ ጊዜ የተደረገው ንግግር የተካሄደው ውይይት በአብዛኛው ታርሞና ተሰርዞ፣ በዜና ማሰራጫዎች የተላለፈው ቅንጫቢው ብቻ መሆኑ በከተማው በሰፊው ተወራና አሰላለፉ ተለይቶ አሁን የሚጠበቀው ማን እንደሚያሸንፍ ሆነ። ወዲያው ተከታትሎ እየገፋ የመጣው የውጭ ከበባና የውስጥ ፀረ - አብዮተኞችን በመቃወም የአዲስ አበባ ከተማ ሰፊ ሕዝብ ከፍተኛ ትዕይንት ሕዝብ ለማድረግ መነሣቱ ተወራ። ይህ ከመሆኑ አንድ ቀን በፊት በደርግ ላይ ክንፍ ዋና መሪ በዜና ማሰራጫዎች አማካይነት ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ መልእክት ተላለፈ። ከዚያ በፊት በዜና ማሠራጫዎች ያለማቋረጥ እንደሚደረገው በዚህኛው መልእክት ውስጥ የኢ.ህ.አ.ፓ ቀልባሽነት ሳይወሳ በመታለፍሁ፥ ሁናቴው ወደ ይፋ ፍልሚያ

መቃረቡን የሚያስገነዝብ ነበር። ከዚሁም ጋር መግለጫው ባበቃ ከአንድ ሰዓት ባለበለጠ ጊዜ ውስጥ ደግሞ ከአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ መልእክቱን በመደገፍ ትዕይንተ ሕዝብ ለማድረግ ጠይቆ የተፈቀደ መሆኑ በዜና ማሰራጫዎች ተነገረ። በአሰላለፉ ውስጥ ገብተው እምብዛም በቂ መረጃ ለሌላቸው፤ የኃይል ሚዛኑ ወደ የትኛው ወገን ነው? ማነው የሚያሸንፈው? ተራው ተፋላሚ በሥጋትና በተስፋ በየሚናው ተሰለፈ።

የሰሌዳ መፈክር ጨብጦ መፈክር እያሰማ የወጣው በጅምላ ታድሞ የወጣው፣ ሳይታወቀው ሕዝብ በሚሰበሰብበት ለመገኘት ልማዱ የሳበው ይህ ሁሉ የአብዮት አደባባይ ከዳር እስከ ዳር ጢቅ አድርጐ ሞልቶ ዐይኑንና አቅሉን በመናገሪያው መድረክ ላይ ተከለ። ንግግሮቹ ሲጀመሩ ትግሉ ይፋ መውጣቱ በግልጽ ታወቀ። የአዲስ አበባን ነዋሪዎች የወከለው ሰው ባደረገው ንግግር አብዮቱን ለማራመድና የኢትዮጵያን አንድነት ለአስከበር ሰፊው ሕዝብ ቆርጦ መነሣቱን ከአረጋገጠ በኋላ ሆኖም፥ ከብዙ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ሚገኘው ጠላት ከመዝመት በፊት ከኅምሳና ከመቶ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ጠላትን አስቀድሞ ማስወገድ እንደሚያስፈልግ አስታወቀ። ከአንድ ቀናት በፊት የአመራሩ አንድ ክንፍ መሪ ካስተላለፉት መልእክት ፈጽሞ ተቃራኒ ነበር። ግልጽ የሆነ ፍልሚያ ጥሪ ወይም ክተት ነበር። ለዚያ የፍልሚያ መልክ ተስማሚ በማይመስል የሲቪል ልብስና ባርኔጣ የቀረቡት የፊተኛውን መልእክት ያስተላለፉት ባለሥልጣን የመልሱን ንግግር ማድረግ ሲጀምሩ ደግሞ ብዙ ሕዝብ በተቃውሞ ሁካታ እየተመመ ሳያስጨርሳቸው አቋርጦ ወጣ። ከዚያ በፊት ታይቶ ያልታወቀ ነበር። ንግግሮቹና በመካከሉም የሚሰነዘሩት መፈክሮች በቀጥታ በሬዲዮ እንዲተላለፉ ተደርጐ ስለ ነበር፥ ለመመታታት መቀጣጣቱ በአብዮት አደባባይ ከተገኘው ሕዝብ አልፎ በከተማም በገጠርም ሆን ብሎ ለተከታተለው ሁሉ ይፋ ወጣ። የተቀጣጣው ፍልሚያ የሚሰነዘርበትን ዕለት መጠበቅ ብቻ ነው።

ዕለቱ ጥር መጨረሻ ላይ ደረሰ። ወደ ቀትሩ ገደማ ላይ በታላቁ ቤተ መንግሥት የመትረየስ፥ የአውቶማቲክ ሌላም ብርቱ የተኩስ ድምጽ ለብዙ ደቂቃዎች ያህል ያለ ማቋረጥ ተሰም ። የሽጉጥ፥ ወይም የጠመንጃ ነጠላ ተኩስ በየመንደሩ አልፎ አልፎ መሰማቱ የተለመደ ቢሆንም ያንን፥ የመሰለ ከባድ ተኩስ፥ ያውም በታላቁ ቤተ መንግሥት ሲሰማ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ድንጉጥ ወላጆች ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤት ለማውጣት ተሯሯጡ። በመኻል ከተማ መጠነኛ የትራፊክ ትርምስ ተፈጠረ። አንዳንድ መደብሮች ተዘጉ። በዙው ሰው

ደግሞ። «ለይቶለት ይሆን? » በሚል ዕሳቤ ብቻ የዕለት ኑሮውን ቀጠለ። ማታ ቁርጡ ታወቀ።

የአማርኛው ፕሮግራም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ሲከፈት የዐዋጅ የከፍተኛ ውሳኔ የደርግ መግለጫ ሌላም ክብደት የሚሰጠው ሐተታ ማብሰሪያ የሆነ ማርሽ ከአስተጋባ በኋላ ከአብዮቱ ጋር ባለው ግንኙነት ሰው ሁሉ ከፊሉ ‹መርዶ ነጋሪ› ብዙው ‹አንደበተ ርቱዕ› እያለ የሚጠራው የራዲዮ ተናጋሪ ድምፅ ተከተለ።

«.....ለብዙ ዘመናት ታግለህ፥ ፍዳህን አይተህ፥ በታጋይ ልጆችህ ንጹሕ ደም እየኮተኮትክና እያንከበከብህ ከዚህ ያደረስከውን፥ የኑሮህ ተስፋህ የሆነውን አብዮትህን ቀልብሶ እናት አገርህን ለመቆራረስና ለአድኃሪ የዓረብ መንግሥት አሳልፎ ሰጥቶ እንዳልነበረች ለማድረግ በውስጥና በውጭ አድኃሪ ኃይሎች ረቂቅ በሆነ ከፍተኛ ደረጃ የተቀነባበረብህ ሤራ ቁንጮው ላይ ስለተመታ በመፍረክረክና በመክሸፍ ላይ ይገኛል...... » ሲል ጀመረና ወደ መጨረሻው ገደማ «......በመለዮ ለባሹ መሐል መከፋፈል፤ በመለዮ ለባሹና በሰፊው ሕዝብ መካከል መቃቃርን እያስፋፉ በሄዱት የኢ.ህ.አ.ፓ፤ የኢ.ዲ.ዩ. የውስጥ አርበኞች ላይ አብዮቱ ከመጠቃት ወደ አጥቂነት በመሸጋገር ዛሬ የማያዳግም አብዮታዊ እርምጃ ወስዶባቸዋል። በዚህም መሠረት በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ውስጥ ለኢ.ህ.አ.ፓ.ና ለኢ.ዲ.ዩ. በውስጥ አርበኝነት፤ አብዮቱን ለመቀልበስ ተራማጅ የደርግ አባላትንና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ታጋዮችን ለማፈን ሲያሤሩ በተያዙት እርምጃ ተወስዶባቸዋል..... » እርምጃ የተወሰደባቸው የደርግ አባሎች ስም በዚሁ መግለጫ ተዘረዘረ። ከዚያ በታች የነበሩና በዚሁ ፍልሚያ ውስጥ እርምጃ የተወሰደባቸው ሰዎች እያደር በይፋ በወሬ - ወሬም ወጣ።

## ፪

ዘለቃ ቡድን ውስጥ ያስገባት የመረጃ ክፍል ወዳጅዋ በጥር ወር ፍልሚያው መገደሉን ስትሰማ እምብዛም አልተደነቀችም። እንድትገባ ከጠይቃት ጊዜ ጀምሮ ጥርጣሬ ነበራት። ‹ከዚህኛው ሆኖ ያኛውን መምሰሉ ኖሯል? የዚያኛው ሆኖ ወደዚህኛው ሠርጐ የገባ ነበር? ወይም ሁለቱም ወገኖች ዐወቀው እንዳላወቁ በመምሰል ሁለቱም እንደሚተዋወቁበት በማወቅ ኃይላቸውን የሚፈታተኑበት

ወይም የሚስማሙበት ነገር ቢኖር ፍንች የሚቀባበሉበት ቀዳዳ? ከዚህም በላይ የሐሰት መረጃ እንደ ኳስ የሚወራወሩበት የጋራ መሣሪያቸው ነበር? የእሱስ ዓላማ ምንድን ነበር? ዘለቃ ይህ ሁሉ ጥያቄ እንደ ገና በሐሳብዋ ያልፍ ጀመር። እንዲያውም ቀደም ሲል እንደ አሁኑ በደርግ ውስጥ መከፋፈሉ መኖሩን ሳታውቁ ‹ኢሃፓ› የሚባለውንም ሳይታወቅ ገና ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የሚባለው እንደ ታወጀ ሲያሽሟጥጥ ሰምታ «እኔን ለመምሰል ነው፤ ወይስ አንደኛውን የእኛው ነው » ስትል ተጠራጥራ ነበር። አፓርትማ በቀላሉ ለማግኘት ፖለቲካ ድርጅት ውስጥ እምግባት እንዳለባት ሲነግራትም እንደዚሁ ድርጅት ውስጥ መግባት እንዳለበት ሲነግርትም እንደዚሁ ይህንን በመሰለው አሠራር የማያምን በመምሰል ነበር። አፓርትማ የማግኘቱ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ይህ እንቆቅልሽ ይህ የድብብቆሽ ጨዋታ ጭምር ነበር ቡድን ውስጥ እንድትገባ ስሜትዋ የገፋፋው። ልጆች በቤተ መቅደስ ውስጥ ምን አለ ይሆን? ብለው ዐይነ ልቦናቸው ከመንጦላዕቱ ጀርባ እንደሚያተኩር ሁሉ ውስጥ ውስጡን የሚካሄደው ትግል ምን ዓይነት እንደሆነ ከውስጥ ሆና ለማየት ጓጓች። በዚህም ላይ ካወቀችበት በጥንቃቄ ከተጫወተች ለክፉም፥ ለደጉም እንደ አመጣው አንዱን ለመውጋት ሌላውን ለማሳለም እንደሚያገለግለው መስቀል ከሰላጢን እንደ መጨበጥ ዓይነት ሆኖ ታያት። ኢሃፓዎች አሸንፈው ሥልጣን ከያዙ ከመሠረቱ ከልቧ ‹ኢሃፓ› እንደ ነበረችና ከዚያኛው ቡድን የገባችም፥ ወዳጅዋ እንደ መከራት በመረጃ ለመርዳት እንደ ሆነ ትናገራለች። ደርግን እንደማትወድ ስለሚያውቁ እሱም ቢሆን ይመሰክርታላ። ደርግ በሥልጣን ከቆየ ደግሞ፥ በዚያው ሥርዓት ውስጥ እነርሱን መስላ መኖር አያቅታትም። እርስዋ ራስዋ ባትሾም ባትሸለምም፥ ሥልጣን በያዙት መካከል መገኘትዋን አሳምራ ልትጠቀምበት ትችላለች። ይህንን ሁሉ አውጥታ አውርዳ ነበር የመረጃ ክፍል ወዳጅዋ እንደ ጠየቃት ቡድን ውስጥ የገባችው።

አሁን ግን በጥር ወር ፍልሚያ የወዳጅዋ ድንገት መገደል መስቀል ከሰላጢን ባንድነት ለመያዝ የነበራትን ዕቅድ አቃወሰባት። በአብዮት አደባባይ ድብልቅልቅ ያለ ሰልፍ ይደረግ እንጂ «ሽብር ወደ አናርኪስቶች ሠፈር » የሚል ጩኸት ያስተጋባ እንጂ የቀበሌ ተመራጮች መሣሪያ መታጠቅ ይጀምሩ እንጂ ለዘለቃ አሁንም ቢሆን ፍልሚያው ጨርሶ ያበቃ አልመሰላትም። ወረቀት መበተኑ በየግድግዳው ላይ መፈክር መጻፉ የደርግ ደጋፊ የቀበሌ ተመራጮች በየመንገዱ መገደላቸው አሁንም እንደ ቀጠለ ነው። እንዲያውም ብሶበታል። ታዲያ ነገ አስፈላጊ ቢሆን በኢሃፓ በኩል ብላ እንዳትወጣ የለም። ከገባችበት ቡድን አልፈልግም ብላ እንድትወጣ ጥርጣሬ ያስነሣባታል። እርስዋ የታወቀች

መሥሪያ ቤቷና መኖሪያ ቤትዋ የታወቀ ስለሆነ ተሸሽጋ ልታመልጥ አትችልም። በግላጭ ወደ ኢሃፓ መግባቱም ቢሆን የዚያኑ ያህል አደገኛ ሊሆን ይችላል። ከደርግ በኩል ከተሰለፉት ቡድን ውስጥ የቆየች መሆንዋን ከዐወቁ እርሱም ቢሆን በሥርጐ ገብነት ሊጠርጥርዋት ይችላሉ። እንዴት እንደ ገባች ብትነግራቸውም አያምኑዋት ይሆናል። የሞተ ሰው ደግሞ ዋቢ አይቀርብም።

ዘለቃ አስቀድማ ያልገመተችውና ሳትዘጋጅ እንደ ዱብ ዕዳ የተፈጠረባት አዲስ ሁኔታ ከረጅም ዕቅድዋ ከፊሉን የሚያጨናግፍ ብቻ ሳይሆን በአስጊነቱ የሚያሳስብም ሆኖ ተሰማት። ምክንያቱም ከጠባይዋ ዋናው ለኑሮዋ ለሕይወትዋ የምትፈልገውን ዓላማ ይዞ፥ ለዚህ ዓላማ መንገዱን ቀይሳ በዚያው መጓዝ ነው። የቀሰችው ጐዳና በየመናኸሪያው ቢቋረጥ ሌላ መንገድ መቀየስ ነው። መስቀለኛው መናኸሪያው ከታወቀ አዲስ የሕይወት ጐዳና መቀየስ አያስቸግራትም። ከወትሮው ሹም ጓንጉልን በቤተሰብ በዘመድ አዝማድ ቅርበት ወዳጅ ስትሆን በጊዜው በነበረው ሥልጣን ደህና ሥራ እንደሚያስገባት በማወቅ ነበር። ከማስረሻም ጋር የተጫጨችው በኋላም የተጋባችው የትምህርት ችሎታው የሚያሳድግ ዕድል እንዳለው ስለ ገመተች ነበር። ሁለቱም በየደረጃው ከየመናኸሪያው እየደረሱ አበቁ። ሹም ጓንጉል በለውጡ መንግሥት እንደ ሥልጣን ባልደረቦቹ አብዮታዊ እርምጃ ተወሰደበት ተባለ። ማስረሻን በዘር በወገን ሐረጓ እንዲሾም አደረገች። ደካማ ሆኖ አገኘችው። ተወችው። ከዚያም የቀየሰቻቸው ዕቅዶች ሁሉ ከአንዳንድ የዓላማ ምዕራፍ አድርሰዋት ቢጨናገፉም ከአዲስ ምዕራፍ ጀምራለች። የአሁን ግን አፓርትማ ከማግኘት በቀር፥ ውጤቱ ወዳልታወቀ ጨለማ አስገብቶ ያበቃ ጉዞ መሆኑ ቀፈፋት። በብልጥነቷ የምትተመን በመሆንዋም ‹እንዴት እንዲህ እበለጣለሁ› ስትል በራስዋ በሸቀች። እንዲያውም ሆን ብሎ ለመሞት ከዚህ ሐሳብ ውስጥ ያስገባት ይመስል በቀድሞው የመረጃ ክፍል ወዳጅዋ ላይ ተከፋች።

ዘለቃ ነገሩን አውጥታ አውርዳ ለጊዜው ምንም መፍትሔ ስላጣችለት አጋጣሚ የቋጠረውን ሌላ አጋጣሚ እስከሚፈታው የቡድን አባልነቷና በአፓርታማዋ ውስጥ የሚካሄደውን ሳምንታዊ የሕዋስ ጥናት እንደ ወትሮው ቀጥላ ሰነበተች። እያደርም መፈለጉዋን ሳትተው ሐሳቧ በመጠኑ እየተረጋጋ ሄደ።

ግን ብዙ ሳይቆይ አንድ ቀን የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ደረሳት። ከሥራ እንደ ዋለች ወደ ፍልዋ ስትገባ በመዝጊያ ሥር የተከተተ ፖስታ ከወለሉ ላይ አገኘች። አዲስ ነገር ስለሆነባት በመገረም አነሣችና አየችው። ተራ ፖስታ ነው።

የበለጠ ያስገረማት ደግሞ የእሷም ሆነ የሌላ ሰው አድራሻ ያልተጻፈበት መሆኑ ነው። የአፓርታማው መተላለፊያ ሲጠረግ የገባ ቆሻሻ ወረቀት ነው እንዳትል ታሽጓል። ከውስጡም ወረቀት እንዳለበት ያስታውቃል። ‹ምን ሊሆን ይችላል?› ስትል እየከነከናት ቀደደችኛ ከሁለት የታጠፈውን ወረቀት አውጥታ ዘረጋችው። ዐይንዋ በመጀመሪያ ከጽፍሑፉ በታች ካለው የማጭድና መዶሻ ቀይ ዓርማ ላይ ዐረፈ። ከየት እንደ መጣ ወዲያው ዐወቀች። ወረቀቱን የያዘው እጅዋ ትንሽ እንደ መንቀጥቀጥ እየቃጣው አነበበችው። አምስቱ መሥመር የታይፕ ጽሑፍ ስሟን ሳይጠቅስ ከባንዶችና ከደርግ ጋር መሰለፍዋ ተደርሶበት እንድትታረም ይህ የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ የተላከለት መሆኑን ይገልጽና «ኢህአፓ ያሸንፋል » ብሎ ይደመድማል። ይህም ጽሑፍ እየበዛ የሚላክ በመሆኑ በተባዕታይ ጾታ ነው የሚጠቅሳት።

ዘለቃ በመጀመሪያ ጊዜ ከፍርሃት ይልቅ ንዴት ተሰማት። ‹ለምን የልቤን ዝንባሌ አያውቁልኝም› በማለት፤ ወዲያው ደግሞ ራስዋን የምታጽናናበት የምታታልልበት ሐሳብ መጣላት። ‹ምናልባት እንደዚህ ያለ ደብዳቤ የሚስፉትኮ ላልቆረጡበት ጨክነው ለማይጨክኑበት ባንዳንድ ምክንያት ከባላጋራቸው ቡድን በኩል ይገኝ እንጂ ከመሠረቱ አዝማሚያው ደህና ለሚመስላቸው መሆን አለበት። ሌላውንማ እንዲሁ በየአደባባዩ ይቀነድቡት የለ?› አለች በሐሳብዋ።

ይህም ሆኖ ማስጠንቀቂያቸውን መቀበል እንዳለባት በማመን ጉዳዩን ማውጠንጠንዋ አልቀረም ፡ ከቡድኑ ለመውጣትና በአፓርትማ የሚካሄደውም የሕዋስ ስብሰባ እንዲቀር ብትጠይቅ በቂ ምክንያት ካላቀረበች ትርፉ መጠርጠር ነው። ከዚህም ጥርጣሬ በመነሣት በተለይ ከተገደለው ወዳጅዋ ጋር የነበራትን ግንኙነት ተከታትለው ከደረሱበት በቀላሉ አይለቋትም። እንዲያውም የሰሞኑ ውይይት ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እንዲያውም የሰሞኑ ውይይት ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በተቀበሉት ልዩ ቡድኖች መካከል ስለሚፈጠረው ኅብረት እንደዚሁም በኢሃፓና በሌሎች ፀረ - አብዮትና ፀረ - ሕዝቦች ላይ ስለሚካሄደው የማጥቃት ዘመቻ ነው። ዝንባሌዋ ለኢሃፓ ቢሆንም መታሠርም መሠቃየትም መሞትም አትፈልግም። የደረሳትን ማስጠንቀቂያ ወረቀት አሳይታ ለሕይወቷ የፈራች መሆኗን ብትገልጽላቸው ደግሞ ምናልባት በሌላ ባይጠረጥሩዋትም «ሞት ተፈርቶ ከግትል አይሸሽም » በሚል ፈሊጣቸው እንደርሷ ፍላጐት መገለልዋን ከመፍቀድ ይልቅ እንደነርሱው እንድትታጠቅ ወይም በታጠቁ ሰዎች እንድትጠበቅ ያደርጉ ይሆናል። ይህ ደግሞ በታጠቁ ሰዎች እንድትጠበቅ ያደርጉ ይሆናል። ይህ ደግሞ በአካልም በስሜትም፥

ከእነርሱ ጋር የበለጠ እንድትጣበቅ ያደርጋታል። ማስጠንቀቂያ የሰጣትን ቡድን ቁጣም ያባብሳታል። በዚህ ዓይነት ሐሳቧ የሰጣትን ቡድን ቁጣም ያባብስበታል። በዚህ ዓይነት ሐሳቧ ሌሊትም ብዙ ጊዜ እንቅልፍ እምቢ እያላት ሲወስዳትም መጥፎ ቅዠት እየመጣባት፥ አንድ ሳምንት ያህል ከአለፈ በኋላ የመራራ ኀዘን ቁስሉን ጊዘ እየሻረው እንደሚሄድ ቁጣና ንዴት ቀስ በቀስ እንደሚበርድ የፍቅር ትዝታ በዘመናት ጭጋግ እንደሚደበዝዝ ነገር ሁሉ፥ የዘለቃም ሥጋት ወደ መቃለሉ እያዘነበለ መሄድ ጀመረ እንዲያውም እንደገና እንደ እንቁጣጣሽ ካርድ ለማንም የሚያድሉት ይሆናል። ሰው ሁሉ ከመሥመራቸው እንዳይወጣ። አዎ፣ ታዲያ የእኔ፥ ስም የለበት - የሚል አስተሳሰብ እየተተካበት ሄደ።

ይህ አስተሳሰቧ ግን ብዙ ጊዜ አልቆየም።

ሁለተኛው ፖስታ አሁንም በበሩ ሥር ገብቶ የተገኘው ዘለቃ በክፍልዋ ውስጥ እንዳለች ነበር።

በአሥራ ሁለት ሰዓት ከሥራ እንደ ወጣች ከሰሞኑ፥ የመሥሪያ ቤት ወዳጅዋ ጋር አስቀድማ በተቃጠሩት መሠረት አውቶሞቢሏን ከአፓርትማው ግቢ አቁማ በእርሱ አውቶሞቢል ግዮን ሆቴል ሄደው፥ ሲባሉ ሲጠጡ እስከ ሦስት ዓመት አመሹ። ይህ የሰውየው ግብዣ ነበር። በመጨረሻ እርሷ ለምትሰጠው ግብዣ ደግሞ ወደ አፓርትማው ክፍል ሲገቡ ከመጀመሪያው ፖስታ ወዲህ እንድ ልማድ ሆኖባት ወለሉን በዐይንዋ ስትቃኝ ምንም ብጣሽ ወረቀት አላየችም ነበር። እስከ አምስት ሰዓት ከመኝታ ክፍሏ ቆይተው እንግዳዋን ለመሸኘት ወደ በሩ ስታመራ በኤሌክትሪኩ መብራት ነጸብራቅ ቦግ ብሎ ከሚታየው ነጭ ፖስታ ላይ የሁለቱም ዐይን ዐረፈ።

«አ! ደብዳቤ ወድቋል፤ የማን ነው » ሲል ሰውየው ጠየቀ። ዘለቃ አካላቷ ደርቆ እንደ ቀረ ፖስታውን አፍጥጣ ብቻ ተመለከተች። ሰውየው በተለመደው የሴት አክብሮት ተጐንብሶ አነሣውና እንደ ዋዛ ገልበጥበጥ አድርጐ አስተዋለው።

«አድራሻ የለውም! » አለ እንደ ዋዛ።

«ገና አድራሻ ያልጻፍኩበት ራሴ ለሰው የምልከው ነው፤ በክፍሉ የሚነፍስ የመተላለፊያው ነፋስ አንሥቶ ጥሎት መሆን አለበት። » ዘለቃ የሚንቀጠቀጥ ከንፈርዋን በመዳፍዋ ጋረድ አደረገች። በመጠጥና በሌላውም ሞቅታ ተሳክሮ

ሰውዬው በሚገባ አላስተዋላትም እንጂ መላ ሰውነቷ መለዋወጡ በግልጽ ያስታውቅ ነበር.......

ዘለቃ በድንጋጤ የሚረግብ ሰውነቷን ለማስረፍ ፖስታውን ከመክፈትዋ በፊት ቀስ ብላ ፎቴ ላይ ተቀመጠች። ላንዳፍታ ያህልም የታሸገውን ፖስታ እያገላበጠች አየችው። ከዚያም ከፈተችው። የወረቀቱ መጠን ያው ነው። አርማውና መዝጊያው ያው ነው። አጻጻፉና ዐረፍተ ነገሩ ያው ነው። ልዩነቱ ወደ መጨረሻው ገደማ ያለ አንድ ቃል ብቻ ነበር። «የመጀመሪያ » በሚለው ፈንታ «የመጨረሻ » የሚል ተተክቶበታል። ‹ከመጨረሻ ማስጠንቀቂያ በኋላ ምንድን ነው? የፍርድ ቅጣት! ምን ዓይነት ቅጣት? በየመንገዱ በየመንደሩ በየቤቱ በራፍ በሽጉጥ አፈ ሙዝ የሚፈጸመው ፍርድ!› ዘለቃ ፊትዋን በመዳፍዋ ደግፋና ሸፍና - አሁንም ስም የለውም በጅምላ የሚበተን ቢሆንስ? - የሚል አስተሳሰብ ሊመጣባት ሲቃጣ ወዲያው አንድ ነገር አብሮ ትዝ አላት ‹ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኋላ የአፓርትማውን መግቢያ በሮች የሚጠብቁ ዘቦች አሉ። እንደ ልብ መውጣት መግባት የሚችሉት ከሞላ ጐደል በሚገባ የሚታወቁት የአፓርትማው ነዋሪዎች የአፓርትማው ሠራተኞች የኪራይ ቤቶች፥ አስተዳደር ድርጅት የመደባቸው የጽዳት የዘበኝነት፥ የኤሌክትሪክ የሌላም ሌላም ሠራተኞች ናቸው። ጠያቂ እንግዳ ማንን እንደሚፈልግ ከዋናው በር ላይ በተረኛው ዘበኛ ይጠየቃል። እርግጥ ለመጠየቅ፥ የሚፈልገውን የአፓርትማውን ነዋሪ ስም ጠርቶ አንድ ሰው መግባት ይፈቀድለታል። በዚያም ወረቀቱን ማስገባት ይችላል። ግን ለሁሉም ክፍል ጥሏል ማለት ነው? በየተዘጋው ቤት ሥር ሲሸጉጥ ከዚያ ሁሉ ሠራተኛ የሚያየው ሰው የለም? ወይስ ማን ማን መሆኑን የሚያውቅ ክፍል ለይቶ ወረቀት ወይስ ማን ማን መሆኑን የሚያውቅ ክፍል ከሠራተኛውም ዋና ኢሃፓ ሰው አለ ማለት ነው? ማስጠንቀቂያውን እንደዚህ በቀላሉ ማድረስ ከቻለ ቅጣቱን ለመፈጸምስ ምን ያቅተዋል? » ዘለቃ ይህንን ስታስብ በሩ በቀስታ ተፈርቅቆ የሽጉጥ አፈ ሙዝ ብቅ ሲል በዓይነ ልቦናዋ ታያት። በሕይወት ለመጀመሪያ ጊዜ ብርቱ የፍርሐት ብቸኝነትና የብቸኝነት ፍርሐት ተሰማት። ወዳጆች የምታስተናግድበትን ዊስኪ ከዕቃ መደርደሪያው ውስጣ አወጣችና በውሀ ብርጭቆ ከግማሽ በላይ ቀዳችና እንደ ቆመች በደረቁ ጨለጠችው። እንደዚህ ስትጠጣ የመጀመሪ ጊዜዋ ነበር። ለደረሰባት አስጨናቂ ፈተና ትርጉም ብታጣለት ማስረሻ ትዝ አላትና «የሱ ግፍ ነው መሰለኝ » አለች - ከራስዋ ጋር ባዶውን ብርጭቆ እንደ መስተዋት ከፊትዋ ላይ ደቅና እያስተዋለች። ኢሃፓ ስለ መሆኑ የመረጃ የነበረው ሟቹ ወዳጅዋ የነገራት ታወሳትና «ወይስ ሊበቀለኝ

ፈልጐ እርሱ የሚሠራውን ይሆን? እስከዚህ ጭካኔ ያለበት አይመስለኝ » ስትል ራሷን ነቀነቀች።

ድጋሜ ዊስኪውን ለመቅዳት እጅዋን ስትዘረጋ የማስረሻ የመጨረሻ ትርኢት ድቅን አለባት። የፈዘዘ ዐይን የተንጨረረ ጸጉር የተሣሠረ አንደበት ራሱን የሳተ ሰውነት የአረቄ ብርጭቆና በሲጋራ የተሞላ መተርኮሻ ከራስጌ ኮሞ ላይ። «ኖ! እንደዚያስ አልሆነም! » አለችና ከጨኸት ብርጭቆውን ከወለሉ ላይ ከስክሳ ወደ መኝታዋ ተፈናጥራ ሄደች።

# ፫

የጥር ወሩ የማስረሻን የመንፈስ ጭንቀት አባባሰበት መፈፋፈሉ እስከ ላይ ድረስ መኖሩን የወሬ ወሬ የሰማ ቢሆንም እንደዚህ ሥር ሰድዶ ይፋ ይወጣል ብሎ አልገመተም ነበር። በመካከላቸው ልዩነት ቢኖር እንደ ዘመድ ጥል ተሸፋፍኖ ተድበስብሶ ይቀራል የሚል አስተሳሰብ ነበረው። አሁን ግን ከላይ የተጀመረው ፍልሚያ ወደ ታች ወርዶ ከዚያ በፊት እንደ ነበረው የተናጠል ግድያ ሳይሆን በአዲስ አበባ አደባባይ ግልጽ ጦርነት ሲካሄድና በነገሩ የሌሉበት ሕፃናትና አሮጊቶች በተባራሪ ጥይት ሲወድቁ በሐሳብ ታየው። ‹ግን ለምን?› እያለ በመደጋገም ራሱን ጠየቀ። መልስ ሊያገኝለት አልቻለም። መልስ ያላገኘለት ራሱን የሚመለከት ሌላ ሁናቴ ደረሰ።

ለበላይ አካል የሚቀርበውን ማመልከቻውን ከሰጠ ከሳምንት በኋላ ጉዳዩ እስኪያገኝ ድረስ በሕዋስ ስብሰባም ሆነ፥ በእስኳድ ሥልጠና መገኘት እንደማይኖርበት ደረበ ቴሌፎን ደውሎ ነገረው። ለጊዜው ‹ልላቀቅ ልገላገል ነው መሰለኝ!› የሚል እፎይታ ተሰምቶት ነበር። ውሳኔው ቢዘገይበትና ደረበንም ቢጠይቀው «ቆይ ውሳኔህን ትገኛለህ! » እያለ በቁጣ ሲያመናጭቀው ሥጋትና ጥርጣሬ እያደረበት ሄደ። «ደረበ ስለኔ ምንም ነገር አላለም? » በማለት ከየሳምንቱ የሕዋስ ስብሰባ በኋላ ታፈሱን ደጋግሞ ጠየቃት። በሦስተኛው ጊዜ «አዎ! »

«ምን አለ? »

ለመናገር ያልፈለገች ይመስል ትንሽ አቅማማችና አንገቷን ደፋ አድርጋ «ከስብሰባው በኋላ ለብቻዬ፥ ‹ሁናቴው እስኪጣራ ከእርሱ ጋር ባትገኚ መልካም ነው› አለኝ » ስትል መሰለችለት።

«ምን! በማለት ጮኸና መለስ አድርጐ » «ግን የምንገናኝ መሆናችንን በምን ዐወቀ? » ሲል ጠየቃት

«አንድ የፖለቲካ ድርጅትኮ የአባሎቹን፣ የዲስፕሊንና ሌላም ሁናቴ የሚከታተል የመረጃ ዘርፍ ይኖረዋል። »

«ግን በምን ጠረጠሩኝ? ወይስ አንቺ እንዳልሽው ያው የራሱን በቀል ለመወጣት ነው? »

«እኔ ምን ዐውቃለሁ ብለኸኝ ማስረሻ! » አለች ታፈሱ በአዘኔታ አንደበት።

«በአንቺ በኩልስ? »

«በእኔ በኩል ምን? »

«እንድንገናኝ አትፈልጊም ማለት ነው? »

«የኔ መፈለግና አለመፈለግኮ አይደለም ጉዳዩ። ሁናቴው እስኪታወቅ ድረስ ለሁለታችንም አደገኛ ነው የሚሆነው። »

«ሁለታችንም ከዛሬ ጀምሮ እምቢ ብንልስ? »

«በምን አቅማችን? ደሞ አትርሳ የምጦራት አሮጊት እናት እንዳለችኝ። »

ሁለቱም በሐሳብና በትካዜ ተውጠው ለብዙ ደቂቃዎች ዝም ብለው ቆዩ። «እውነትሽን ነው። የራሴን ሕይወት ያበላሸሁት የራሴ ጭንቀት አንሶ፥ አንቺን ጭምር ጣጣ ውስጥ መክተት አለብኝ? አሆሆ! » አለ ማስረሻ ቀዘዝ ባለ አንደበት።

ማስረሻ ለማመልከቻው የሚመጣለትን ውሳኔም ሆነ ከታፈሱ ጋር መገናኘቱን ለጥቂት ቀኖች ያህል እንደ ምንም በትዕግሥት ችሎ ይሰንብት እንጂ እያደር ትዕግሥቱን የሚፈታተን ከባድ ጭንቀት አደረበት። ዳኛ ፊት ቀርቦ ቀንጀሉ ተዘርዝሮበት ፍርዱ ሳይነገረው ተንጠልጥሎ እንደ ቀረ ተከሳሽ ቀልቡ በጭንቀት ተንጠለጠለ። የቢሮው በር በተንኳኳ ቴሌፎን በተደወለ ቁጥር ልቡ ስንጥቅ ትርትር ይልበታል። በሚጠብቀው ውሳኔ ፈንታ ሌላ ነገር፥ ሌላ ጉዳይ፥ ሆኖ ሲያገኘው መንፈሱ ሙሽሽ ይላል። በዚህ ጊዜ የሚያጽናና የሚያወያይ

የሚያጨዋውት የሚያበረታታ፥ አንድ የቅርብ ወዳጅ መንፈሱ ይሻል። ሁልጊዜ በሐሳቡ የምትመጣውም ታፈሱ ናት። ስለ እርሷ ያለውን ስሜት በተለመደው የፍቅር ትርጉም አያስበውም። ብቻ ግን የእነዚያ ልም ዐይኖች አመለካከት በእነዚያ ግርድፍ ከንፈሮች ብቅ የሚል ፈገግታ ለስለስ ያለ ድምፅዋ ይናፍቀዋል። ከሕይወቱ አንድ ነገር የጐደለ መስሎ ይሰማዋል።

አንድ ቀን በዚህ ሁናቴ ከቢሮው ተቀምጦ ዐይኑን ከበሩ ወደ ቴሌፎኑ ከቴሌፎኑ፥ ወደ በሩ እያንከራተተ ሲያስብ፥ ሲያሰላስል፥ ሲጨነቅ ከቆየ በኋላ ድንገት ትዕግሥት አበቃ። ቴሌፎኑን አነሣና ደወለ። የመለሰለት የሌላ ሴት ድምፅ ነበር። «እባክዎ ታፈስኑ? » አለ ድምፁ እንደ መቆራረጥ እየቃጣው።

«በምን ዐወቅሽ እኔ መሆኔን? »

«እንዲሁ ልቤ ነገረኝ፣ እንዳጋጣሚ ሳስብህ ነበር። ደህና አይደለህም? »

«ደህና ነኝ። ምነው? »

«ለምን ደወልክ ታዲያ? » አጠያየቋ በቅሬታ አልነበረም።

«ላገኝሽ እፈልጋለሁ። »

ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ቆየች። «አደገኛ መሆኑን እያወቅህ? »

«የመጣው ይምጣ! » አለ በቁጣ ዓይነት።

«ተው ይቅርብን ማስረሻ! » አለች በልመና፡

«ተመልሼ ሆስፒታል እንድገባ ትፈልጊያለሽ? »

አሁንም ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ቆየችና በከባዱ ተነፈሰች።

«ምን በወጣህ! »

«እንግዲያው አሁን መጣሁ! »

«እውነትም መግባት ነው የቀረህ። የሥራ ሰዓት እኮ ነው! »

«ሥራ ገደል ይግባ » አለ ማስረሻ ረገጥ ባለ አነጋገር።

«የኔው ሥራ ገደል የሚገባ ዓይነት አይደለም። የማዞሪያ ተረኛ ነኝ። ቀደም ብዬ ዐውቄ ቢሆን ኖሮ ተተኪ እለምን ነበር። ለምን ማታ ገደማ አይሆንም? »

«ጨለማ አልፈልግም! » አለ ማስረሻ ረገጥ ያእል አነጋገሩን ሳይለውጥ።

«እሺ እንግዲያው በዘጠኝ ሰዓት ፈረቃዬ እንዳለቀ። »

ማስረሻ ወሎ ደርሶ ለማደር ቀጠሮ እንዳለበት ሁሉ ኮስተር ብሎ እየነዳ በአሥመራ መንገድ ሾላ እንደ ደረሱ «የት ነው የምትሄደው? » ስትል ታፈሱ ጠየቀችው።

«ልጠልፍሽ ነው! » አላት ከልቡ ባልመጣ ቀልድ።

«ምን አስጠለፈህ? እናቴ እንደሆነ ወጥታ የማትፈልገኝ አሮጊት ናት » አለች ታፈሱ ቀልድ ያልሆነ ቀልዱን በቀልድ እየመለሰች።

አሁንም ሳይመለስ ዝም ብሎ እየነዳ ቀየና፥ በኮተቤው ድልድይ ሲደርስ «ከዚህ እብደቴ በመጨረሻ በገሐድ የወጣ! » አለ ባንድ እጁ መሪውን መደብደብ እየቃጣው። እሱ እየነዳ እርሷ በዚያች የዘማኔ ጉድጓድ በምትባል ሾልስ ዋገን ውስጥ ከጐኑ ተቀምጣ በተለይ ፊቱን ከማስተዋል በስተቀር አልጠየቀችውም። እሱ ግን ዝምትዋን ላንዳፍታ ጠብቆ የገዛውን እንቁላል እንዴት እያወጣ ታች ካለው ከአለቱ ላይ እንደ ፈጠፈጠው ተረከላት። ካሁን ቀደም ያልነገራት ስለ ነበር ስለ አእምሮው ጤንነታ ጥቂት ሥጋት አደረባት።

ኮተቤን አልፈው የመናፈሻ ሆቴል ሲደርሱ «እስክስታው የነካካኝ ግን ከዚህ ነው። ጠጣሁ። ያችን አረመኔ ከወንድ ጋር ያውም ከራሴ አለቃ ጋር ከክፍል ስትወጣ ያየሁ መሰለኝ የበለጠ ጠጣሁ። እንቁላል እያወጣሁ ስፈጠፍጥ የምጠላውን ሁሉ የፈጠፈጥሁ ይመስለኝ ነበር። »

«በምን ትዝ አላችሁ አሁን? አሁንም ታፈቅራታለህ ልበል? » ስትል ፊትዋን ጨፍገግ አድርጋ ጠየቀችው፡

«ፓህ! አፈር ድቤ ፍቅር! አንቺ ትቀልጃለሽ። ከዚህ ያደረሰኝ ያለፈ ሕይወቴን ማሰቤ ይቀራል? »

«እርሷም የሕይወትህ ክፍል ነበረች። አሁንስ? »

መስል ሳይሰጣት በደሴ መንገድ መንዳቱን ቀጠለ።

«ኧረ የት ነው ከከተማው እኮ ጨርሰን ወጥተናል። »

«እየነገርኩሽ። ወደ ሀገሬ ወደ ወሎ ልጠልፍሽ ነው። »

ለገዳዲ ሲደርሱ ከአውራ ጐዳናው ወጣና ወደ ሜዳው ገብቶ አውቶሞቢሉን አቆመ። ከአራት ዓመት በፊት ከወሎ የመጡት ስደተኞች

ሰፍረውበት የነበረው ስፍራ ነው። ከአቶሞቢሉ ወጥተው ከመስኩ ላይ ተዝናንተው ተቀመጡ። ማስረሻ ዙሪያ ገባውን በትካዜ አስተዋለና «ውብ አይደለም? ሰላም ጸጥታ፥ እርጋታ። የከተማው ትንቅንቅ የከተማው፥ ሤራ፥ የከተማው ክፋት ሁሉ ከዚህ ከዚህ የለም። ለምን ሕይወታችን እንደዚህ ሰላምና የእርጋታ ውበት የሰፈነበት አይሆንም? » አላት።

«ስለ ተፈጥሮ ውበት ለመስፈላሰፍ ኖሯል አስቸኳይ ካላገኘሁሽ ሙቼ እገኛለሁ ያልከው? ታስገርማለህ? አለች ታፈሱ። ግን ቅር አልተሰኘችም። እንዲያውም ውስጥ ውስጡን ደስ ብሏታል። አብረው ሽርሽር ሲወጡ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር።

«ጸጥ ባለ መስክ ላይ፣ በጠራ ሰማይ ሥር እንደዚህ ከአንቺ ጋር መሆን ሲያሰኘኝስ? ይሄ የሕይወት ጉዳይ አይደለም ትያለሽ? » ክንዷን ተደግፋ ጋደም ወደ አለችበት ተጠጋ። ደሞም ይህንን ሥፍራ ላሳይሽ የፈለግሁበት ምክንያት አለኝ። የበሽታዬ አንዱ ምንጭም ከዚህ ያየሁት ትርኢት ነበር። ከዚህ ሥፍራ ረሃብና፥ ችግር ምን ዓይነት እንደ ሆነ አይቻለሁ። ከዚህ ሥፍራ፤ የሕፃን ሕይወት በችጋር ሲቀጠፍ ደርሻለሁ። ከዚህ ሥፍራ በጸጋዬ ገብረ መድኅን ቃል ለመጠቀም በጣዕሩ ድረስልኝ ያለኝን የአባቴን ‹ጣዕረ ሞት› በዐይነ ልቦናዬ አይቸዋለሁ። በየሄድኩበት እየተከተለም፥ የሕሊና ወቀሳ ጅራፍ አስቃይቶኛል። እንደገና አማኑኤል ላለመግባት የመንፈስ ሰላም የሕሊና ዕረፍት እፈልጋለሁ። ስለዚህ የሰው ሕይወት መጥፋት የሕይወት ሥቃይ ያሠቃየኛል። ጸጋዬ እንደ ሚለው ይገባሻል ‹ሠቀቀኔ›? » ታፈሱ የሕሊና ሠቀቀኑን ለማዳመጥ ይመስል ጭንቅላቷን ከደረቱ ላይ ጣል አደረገች። «ስለዚህ ነው መወሰን ግድ የሆነብኝ። ስለዚህም ነው አንቺን ማግኘት የፈለግሁት። »

«የምን ውሳኔ? » በማለት ታፈሱ ጠየቀች። በሆድዋ ግን ‹ልጠልፍሽ ነው› ካላት ቀልድ በመነሣት ስለ ውሳኔው የራስዋን ግምት አድርጋ ከአፉ እስክትሰማው ብቻ ብጉጉት ጠበቀች።

ትንሽ ተዝናንቶ የቆየው ፊቱ ጭፍግግ አለ። «በሰላም የማይለቀኝ ከሆነ ራሴን ለመንግሥት አጋልጬ እሱንና መሰሎቹን ጭምር አጋልጣለሁ። ከሆስፒታል እንደ ወጣሁ የቀለቡኝን ሰይችንቶ ነጅዎች ጭምር ታዲያ እኔን ያሳሰበኝ፤ በአንቺ ላይ እኔ ባልጠቁምም እሱ ተይዞ ሲመረመር እኛን የጐዳን መስሎት አንቺን ጭምር እንዳይበክልሽ ነው። »

«የእኔኑ ተወውና አንተ ራስህኮ በሕይወትህ መፍረድህ ነው። ድርጅት ወይም የድርጅት አባል አጋልጠህ እንዲሁ አትተውም፤ በቅድሚያ እንዲሞቱ የሚያደርገው የሚያጋልጡት ናቸው። ከሐዲ ተብለው። ታዲያ ብረት ካዝና ውስጥ ተደብቀህ አትዘልቀው? »

«ከዚህ ሕይወት ሞት - ዕረፍት ነው። ሰላም! » አለ ማስረሻ ምርር ባለ አነጋገር።

«ሕይወትህን ከራስ አንጻር ብቻ አትየው። ስላንተ ሕይወት የሚያስብ መኖሩንም አትርሳ። » ታፈሱ ያለችውን በተግባር ለመተርጐም የፈለገች ይመስል በመሽኮመም ራስዋን ከብብቱ ሥር ሽጉጥ አደረገች። ማስረሻ የአንድ ሰው ዕድሜ ብቻ ሳይሆን ዘለዓለም የመኖር ፍላጐት ተሰማው።

«ሌላ ያሰብኩት፣ እንደዚህ ጠምዶ የያዘኝ በግል ጥላቻውና ቂም በቀሉ ከሆነ ለበላይ አካል በቀጥታ ለመንገር ነው። »

«ማንን ብለህ? »

«እንዴ በቡድኑ ውስጥ ቆይተሻል! አንዳንዶቹን መሪዎች ማወቅ አለብሽ። »

ታፈሱ ራስዋን በማስተባበል አወዛወዘች። «እገሌ - እነገሌ መሪዎቹ ሊሆኑ ይቻላሉ » ሲባል እንሰማለን። ግን ማንም እርግጠኛ መሆን አይችልም። በዚህ ላይ የዲሲፐሊን ጉዳይ አለ። ዘለህ ከመሪዎቹ ወይም ‹ሴንትራል› ኮሚቴ ከሚባሉት አንዱን ብታነገር ማወቅ የማይገባህን በማወቅ ድርጅቱን ከአደጋ ላይ ጣልክ ትባላለህ። ደረበ የቆየ አባልና ምናልባት ብዙዎቹን በግል ሊያውቅ የሚችል የታወቀ ተዋናይ ስለሆነ የሚሰሙትም የእርሱን ቃል እንጂ የአንተን አይሆንም። እንዲያውም እርሱ ራሱኮ ‹ሲሲ› ሊሆን ይችላል። »

«እንዴት አርጐ? የሕዋስ መሪ ብቻ አይደለም እንዴ? » አለ ማስረሻ በመገረምና ግራ በመጋባት። አስረዳችው። በአመራር ላይ የሚገኙ አልፎ አልፎ የተጋለጡ መሆናቸውን ወይም መጠርጠራቸውን በጠረጠሩ ጊዜ፥ ወደ ታች ወርደው በዝቅተኛ የሕዋስ ደረጃ ተራ አባል ይሆናሉ። ድንገት ቢያዙ በዝቅተኛው ሕዋስ ውስጥ የሚገኙትን ሌሎቹ ተራ አባሎችን በማጋለጥና እነርሱን በማስመስከር ከዚህ ውጭ ምንም የሚያውቁት ነገር እንደ ሌለ በማስመሰል በአመራር ደረጃ ግንኙነት የነበራቸውን ሁሉ ያድናሉ። ይህ ሽፋንን ማጠናከር ወይም ‹ድርብ ጎቡዕ› መግባት ይባላል። ታስታውስ እንደሆን በእነ

መንግሥቱ ነዋይ ጊዜ ስንኳ መሪዎቹ እንጂ የተፈረደባቸው ተራው የክብር ዘበኛ ወታደር ምሕረት ተደርጐለታል። እነ መንግሥቱ ነዋይም የሚታወቁት በወታደራዊ አሠራርም ዝርዝር መዝገብ በግልጽ ስላለ ነው እንጂ እንደ ተራ ወታደር ሆነው ቢቀርቡ ኖሮ ያመልጡ ነበር። ድርጅታችን ግን በሥውር ስለሚሠራ መሪዎቹ እነማን እንደ ሆኑ በግልጽ ስለማይታወቁ እንዲህ ያለው ዘዴ ይጠቅማል » አለች በመጨረሻ።

ማስረሻ እርሱን የሚያስጨንቀውንና ጭራቅ መስሎ የሚታየውን «ድጅርታችን » በማለታኡአ የተከፋ ለመምሰል ፊቱን ኮሶ አስመስሎ «ፆህ! ድንቄም ድርጅታችን » ካለ በኋላ መለስ አድርጐ «ለመሆኑ በተራ አባልነት፥ በሕዋስ ደረጃ ሆነሽ ይህንን ሁሉ እንዴት ዐወቅሽ? ወይስ አንቺም በድርብ ሽፋን ነው ያለሽው? ከአመራር ደረጃ አዘቅዝቀሽ የወረድሽ ነሽ? » ሲል ቀለደ።

እርሷም በቀልድ ጭኑን ቆንጠጥ አደረገችው። «እኔ በተፈጥሮዬ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ። በዚህ ላይ ደግሞ የቴሌ ማዞሪያ ሱፐርቫይዘር መሆኔን አትርሳ። ብዙ ጊዜ እጄም ጆሮዬም ስለማያርፍ አንዳንድ ነገሮች ሲወረወሩ እቀልባለሁ። ይህ ሁሉ እኮ በመሠረቱ የድርጅቱ ምሥጢር ነው። አንተ ደግሞ ድርጅቱን እየከዳህ ነው። ለምን ነው የምለፈልፍልህ? » አለች ፊቷን በቁጣ ያኮሳተረች በመምሰል።

«አሁንም የነፍሴን ሰቆቃ የመንፈሴን ጭንቀት አላወቅሽልኝም ማለት ነው። እኔም በከንቱ ለፈለፍኩ፤ ልቤን ተርትሬ ያሳየሁ መሰለኝ። »

«ይገባኛል። ስቀልድ ነው። » በመዳራት ሳይሆን በመተሳሰብ በመንፈስ በመፈላለግ ተጣበቁ። የሰላም ዕልም ለማለም።

«ለመሆኑ አንቺ ምን ትመክሪያለሽ? » ሲል ጠየቃት፤ ከረጅም ጊዜ ጸጥታና እርጋታ በኋላ።

«ትንሽ ቆይ። ከአሁን ቀደምም ታገሥ ብየሃለሁ። አሁንም ታገሥ » ቅዝቃዜ መምጣት ጀምሮ ስለ ነበር ከተጋደመችበት ቀና ብላ ከላይ የደረበችውን ሹራብ መቆለፍ ጀመረች። ለማስረሻም ትራስ አድርጐት የነበረውን ኮቱን እየሰጠችው «ስላንተ ምን እንዳሰቡ በተለይም ደረበ ምን እቅድ እንዳለው በመጀመሪያ እንወቅ። ከዚያ በኋላ - » አለች ታፈሱ።

«እቅዳቸው እንዴት ማወቅ እንችላለን። ነገራቸው እንዲሁ ሰውን ማስጨነቅና ሽፍንፍን ነው። »

«ቴሌ ማዞሪያ ሱፐርቫይዘር መሆኔን አትርሳ። ሥራዬ ብዬ ከተከታተልኩ አንዳንድ ነገር ማግኘት እችላለሁ። »

«ዕቅዳቸውን ተመካከረው ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ሲነሡ፥ ጊዜው መሽቶ ሙሉ ጨረቃ ብርማ ብርሃንዋን በምድሩ ላይ አንጥፋለች። ከመስኩ ወጥተው፣ ወደ አውራ ጐዳናው ሲገቡ ማስረሻ በሰፊው ተነፈሰና «ታውቂያለሽ፥ በእንደዚህ ያለ ጭር ባለ ጊዜ ትዝ የሚለኝና ቁጭ ብዬ ኮከብ መቁጠር የምፈልግበት ቦታ ሕፃን ሆኜ ያደግሁበት ትውልድ አገሬ ወሎ በተለይም ዳገታማ ሚካኤል ነው። እንደገና ነፃ ሕሊና ለማግኘት እንደገና የመንፈስ ብሩሕ ተስፋ ለማለም » አለ።

«ታዲያ ለምን አትሄዱም? ሁናቴውን እስክናጣራ ድረስ ገለል ማያ - በዚያው ላንተ እረፍት - ይሆንሃል » አለችው።

«እረፍት አልሽኝ? እረፍት » አለ ቀዝቀዝ ባለ ድምፅ። «እረፍቴንማ ገድያታለሁ። ፈረንጆች እንደሚሉት ወደ እረፍት የሚመልሰኝን ድልድይ ራሴው አቃጥየዋለሁ። ዳገታማ አሁን ጠፍ ሆኗል አሉ። በሕፃንነቴ ያሳደገኝ ሙሔ በመጨረሻ ይኖር የነበረው ቆሬ በሚባል ሥፍራ ነበር። ግን በጭንቁ ጊዜ አልደረስኩለትም » ማስረሻ በአዘኔታ ራሱን ነቀነቀ.....

ትካዜ አፋቸውን የሸበበው ይመስል ብዙም ሳይነጋገሩ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

## ፬

በጥር ወር መጨረሻ በአዲስ አበባ በከፍተኛው የአመራር ደረጃ የደረሰው የፍልሚያ ነውጥ እንደ ባሕር አዙሪት እንደ መሬት መንቀጥቀጥ ከመነሻው እየራቀ በሄደ መጠን ኃይሉ እየቀነሰ ይሂድ እንጂ ከጊዜ ጊዜ እየሰሩ ማስተጋባቱ ስለማይቀር ቆሮ ቀበሌም ደረሰ።

ካሣሁንና ሌሎችም የፖሊስ ጣቢያው እስረኞች በአዲስ አበባ ስለ ተፈጸመው ድርጊት ወሬው ደረሳቸው። ነገር ግን አመጣጡ ከሰው ሰው ሲቀባበለው እየተጨመረበት እየተቀነሰበት እየተለወጠለት እየተፈጠረለት ጭምር ስለ ሆነ የተምታታ ነበር። ከዕለት ዕለት የሚሰሙትም ፈጽሞ የተለያየ ነበር። ነገሩ የምሥራች ይሁን መርዶ ካሣሁን መወሰን አልቻለችም። የራሱን

በግፍ መታሰር በአዲስ አበባ ከደረሰው ሁናቴ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ አድርጐ ባይመለከተውም ሹም ሽር ሲደረግ፥ ዘመን ሲለወጥ ገዢ ሲቀየር በተራው ሕዝብ ኑሮ ላይም አዲስ ሁናቴ ጊዜ በኋላ የጣቢያው አዛዥ አንድ ቀን ከሥራው እንደ ወጣ ሳይመለስ ቀረ። ስለ ጣቢያው አዛዥ መጥፋት ከዚህም ከዚያም የሚመጣው ተባራሪ ወሬ ዝብርቅርቅ ነበር። አንዱ፥ ለሹመት ወይም ለመኰንንነት ኮርስ በአስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ ተጠራ ይላል። ሌላው በአዲስ አበባ የተወገዱት ባለሥልጣኖች ወገን ስለሆነ አመለጠ ይላል።

ጣቢያው ለጊዜው አዛዥ ሲያጣ ኮንትራተኛው ነጋዴ «የብዙ ዓመት ውዝፍ አልተከፈለኝም » በማለት ለእሥረኞች ቀለብ ማቅረቡን አቋርጦ የከተማው ሰው በተቻለ መጠን እየረዳቸው በችግር እንደ ቆዩ ተተኪው አዛዥ መጣ።

የጣቢያው አዛዥ የእሥረኞችን ማረፊያ ሲጐበኝ ብዙዎች እሥረኞችን ስለ ደረሰባቸው ግፍና በደል አቤቱታቸውን ሲያሰሙ ካሣሁንም የበኩሉን ምርር ብሎ አመለከተ። «እኔኮ የሚገርመኝ በዱሮው መንግሥት ‹የኢትዮጵያ አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ ብላ› ይባል እንደ ነበረው ለደርጉ መንግሥት በመቆርቆሬ፣ ‹የደሀ ደም ለምን በከንቱ ፈስሶ ይቀራል? በማለቴ የተገላቢጦሽ ግፍና መከራ መቀበሌ። ልመስገን ውለታዬ ይከፈለኝ አላልኩ። የዱሮው አንሶ አሁንም? » ሲል የምሬት ጥያቄ አቀረበ። አዲስ አለቃ ሲሺምና አዲስ ዳኛ ሲሰየም የአቤቱታ አቅራቢና ተበደልኩ ባይ መብዛቱ የተለመደ መሆኑን አዲሱ የጣቢያ አዛዥ ቢያውቅም፤ የካሣሁን አነጋገር የተለየ ስለ ሆነበት በግንባር ፊት ባይሰጠውም ወደ ቢሮው ሲመለስ ፋይሉ እንዲመጣለት አዘዘ። ግን፣ ካሣሁን ፋይል አልተከፈተለትም፤ ቃሉንም አልሰጠም ነበር። የጣቢያው አዛዥ ይህ ያልተለመደ አሠራር አስገርሞት ካሣሁን አስጠርቶ የታሰረበትን ምክንያት በዝርዝር እንዲያስረዳ ጠየቀው። ካሣሁንም በገበሬ ማኅበር ውስጥ የተፈጠረውን ጭቅጭቅ የከበደን ከእነ ሚስቱ ተገድሎ መገኘት ራሱም የገበሬው ማኅበር ሊቀ መንበር በመሆኑ ካለበት ኃላፊነት ጋር የቅርብ ወዳጁ ስለ ነበር ገዳዮቹ ተፈልገው እንዲያዝ ደጋግሞ ማመልከቱንና የሚጠራጠራቸውንም ሰዎች ለዱሮው የጣቢያ አዛዥ መጠቀሙን ስሜት እየተናነቀው ተናገረ።

የጣቢያው አዛዥ ወደ ቆሬ መንደር መርማሪ ልኮ ካሣሁን በጥርጣሬ የጠቆማቸው ሰዎች በሙሉ መጥፋታቸውን ከአረጋገጠ በኋላ፥ በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርብ ዋስ አስጠርቶ ለቀቀው።

ካሣሁን ከእሥር ቤት ወጥቶ ቆሬ መንደር መርማሪ ልኮ ካሣሁን በጥርጣሬ የጠቆማቸው ሰዎች በሙሉ መጥፋታቸውን ከአረጋገጠ በኋላ፣ በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርብ ዋስ አስጠርቶ ለቀቀው።

ካሣሁን ከእሥር ቤት ወጥቶ ቆሬ መንደር ሲመለስ ሰፈሩ እንደ መካነ መቃብር ጭር ብሎ አገኘው። የገበሬ ማኅበር መሰብሰቢያ የነበረው ዛኒጋባ ተቃጥሎ ነፋስ በተቀንቀሳቀሰ ቁጥር ከምር እንደዚሁ አመድ ሆኗል። የከበደ ጉተራ ተመዝብሯል። በአራቢያ የተገኙ ብዙ የቀበሌው ከብቶች ተነድተው ተወስደዋል። ገበሬው ማኅበር ውስጥ ይቃወሙት የነበሩት ሰዎች፣ የመጡበት ሳይታወቅ በቆሬ እንደ ተሰበሰቡ ሁሉ የደረሱበት ሳይታወቅ ድንገት የውሀ ሽታ የሆኑት ይህንን ሁሉ ጥፋት ከአደረሱ በኋላ ነበር። ካሣሁን እሥር ቤት ሳለ በቆሬ ስለ ደረሰው ጥፋት በመጠኑ ሰምቶ የነበረ ቢሆንም በዐይኑ ሲያይ በጣም ዘገነነው። ‹ሰው እንደዚህ እንዴት ጨካኝ አረመኔ ይሆናል?› ሲል አዘነ። ግን በደረሰው ጥፋት እምብዛም ሳታዝን ዘይኔን በደህና ስላገኛት ፈጣሪውን አመሰገነ።

እህል ውሀ ከቀመሰ በኋላ፥ ከቤቱ ታዛ ሥር ተቀምጦ ጠፍ እንደሆነ አጸደ ቤተ ክርስቲያን ጸጥታ የዋጠውን የቆሬን ቀዬ ሲማትር «ወንድም አለምኮ በሕይወት አለ። መጥቶ ነበር » አለችው ዘይኔ ከጉጆው በር ላይ ቆማ። በሐሳብና በትካዜ ተመስጦ ስለ ነበር አላዳመጣትም። ደግማ ነገረችው።

«ምን? ጉበዜ » አለ ድንገት እንደ ባነነ ሰው አንገቱን ሰበቅ አድርጎ።

«አዎ » አለች ዘይኔ በማረጋገጥ።

«በደርጉ መንግሥት ምሕረት ገብቷል ሲባል ከሰማንማ ቆይቷል። እንዲያውም ብቅ ሳይል ጊዜ ውሸት ይሆን? አልን እንጂ። ለመሆኑ ደህና ነው? »

«ሽበት ወርሮበታል እንጂ ደህናስ ነው » አለች ዘይኔ አንድ ዓይነት ሐሳብ የገባት ይመስል ዐይኗን ጭንቁር አድርጋ።

«የታላቅሽ ታላቅ አይደል እንዴ! እኔንምኮ ይኸው ጀማምሮኛል። የበረሃ ኑሮ እንኳን መሸበት ሌላም ያደርጋል። ለመሆኑ ታዲያ ምነው እስከ ዛሬ ሳይመለስ ቆየ? » ሲል በመገረም ጠየቃት።

«እሱስ እኔንም ገርሞኛል። ሌት ከቀን የሚያኳትን ሥራ ይዞኝ ነው አለ። »

«ምን ሥራ? »

«ዓይነቱን አልነገረኝም። »

ጐበዜ እስከ አሁን ሳይመለስ ስለቀረበት የሰጠውን ምክንያት ካሣሁን ማመንም መረዳትም አስቸገረው።

አንድ ጊዜ ማይጨው ሌላ ጊዜ አሰብ ታየ ተብሏል። እንዲያውም አንድ ጊዜ ደሴ ከተማ ታይቷል፣ ተብሎ ነበር። ታዲያ እንደዚህ ሲዘዋወር፤ ደሴ ድረስ ሲመጣ እግረ መንገዱን ቆሬ ብቅ ማለት እንዴት አቃተው? የእናቱን ልጅ አንድ እኅቱን ለማየት እንዴት አልናፈቀም? አሁን ከዚህ ከደረሰ በኋላስ እሱን እሥር ቤት ሳይጠይቀው እንዴት ተመለሰ? ጐበዜን ዱሮ ሲያውቀው እንደዚህ ድንጋይ ልብና ጨካኝ ሆድ አልነበረውም። ግን ደግሞ ሽፍቶ በረሃ የገባ ሰው በፊት ምንም ደግ ቢሆን እያደር አረመኔ ይሆናል ይባላል። «ለመሆኑ የአባባ ሙሔን ሞት ሰምቶ ነበር? » ሲል ዘይኔን ጠየቃት።

«ከሰማ ቆይቷል » አለችው በትካዜ አንደበት።

«ዛዲያ በስንት ጊዜው ከመጣ በኋላስ ለምን ጥቂት ቀን እዚህ አይሰነብትም ነበር? » ሲል እየከነከነው ጠየቀ።

«እኔንጃ! ለመሰንበት ሐሳብም ኑሮት ቢሆን ውሻው ሲነክሰው ነው ተናዶ ድንገት ለመሄድ የተነሣ። »

«ምን? » ሲል ካሣሁን በመደነቅ ጠየቀ፡

«ውሻውን ከቤት አላስቀርብ ብሎ ቢያስቸግር መትቶ አባርሬው በኋላ አዘናግቶ ወደ ጓሮ ወታ ሲል ባቱን አልቦጨቀው መሰለህ? ታዲያ በሦስተኛው ቀን የጠፋ እስከ አሁን አልመጣም። ሳምንት መሆኑ ነው እንግዲህ። »

«እንደ ገና? » የካሣሁን አነጋገር በጥያቄ ሳይሆን የመገረም ነበር።

«፣ም እንደ ገና? » ዘይኔ በበኩልዋ በመገረም ጠየቀች።

«የለም! ሌላ ነገር እያሰብኩ ነው » ሲል ካሣሁን አስተባበለ። ‹እንደገና› የሚለው ቃል ከአፉ የወጣው ሳይታወቀው ነበር። «ው - ው - ጐ - ጐ - በ » ስትል ያይኔ አበባ መጨረሻ ያወጣችው እስትንፋስ ድንገት እንደ መብረቅ በአእምሮው ውስጥ ብልጭ አለበትና ሆን ብሎ ላያሰስለው «ው - » የሚለው ቃል ውሻ፤ ጐ - በ - ጐበዝ ከሚል ቃል ጋር ተያያዘበት። ‹ጠረን አስታውሶ

ውሻው ጓደኛውን መበቀሉ እንደ ሆነስ?› የሚል ጥያቄ ቀጥሎ በሐሳቡ መጣ። «ወቸው ጉድ ይገርማል! » ካሣሁን ራሱን ነቀነቀ። ‹ይህ ሰውን ከሰው የሚያቆራርጠው የለውጥ ጠንቅ የእኛንም ቤተሰብ ከኍልት ስነጥቆ ይሆን?› የሚል ጥርጣሬም በአእምሮው ውስጥ ተፀነሰ።

ውሻውም እንደ ጠፋ ቀረ።

## ፳

ከብቶች ተነድተው በመወሰዳቸው የእህል ክምር በመቃጠሉና በመበላሸቱ መጠነኛ ችግር ይድረስ እንጂ በጥባጮቹና አዋኪዎቹ በመጥፋታቸው የቆሬ ሰፈር ሰላምና ዕረፍት አግኝቶ ነበር። ካሣሁን ብቻ የመንፈስ ሰላምና ዕረፍት ሊያገኝ አልቻለም። እንደ ግንደ ቆርቁሩ ያለ ማቋረጥ መንፍሱን ጠቅ ጠቅ የሚያደርጉ ሦስት ነገሮች ነበሩ። አንደኛ የወንጀለኞቹ አለ መያዝና ቅጣታቸውን አለ ማግኘት። ሕሊናውን የሚቆጠቁጠው እነርሱ አምልጠው የእርሱ በግፍ መታሠር የክምሩ መቃጠል የከብቱ መወሰድ አይደለም። እንደ ታሠረ አልቀረም ተፈትቷል። ነገሩ ቢቆጭም የትናንት መከራ ዛሬ ትዝታ እንጂ አያምም። እህሉ ታርሶ እንደገና ይመረታል። ከብቱም ጥሮ ግሮ እንደ ገና ይተካል። እንደገና የማይተካው በከንቱ የጠፋው የሰው ልጅ ሕይወት ብቻ ነው። እንደ ገና ያገኘው የከበደን ወዳጅነት ነው። ተዘርሮ የተገኘው ሬሣው ዘወትር በዓይነ ልቦናው ይመላስለስበታል። ከአፈሩ ወለል ላይ የፈሰሰ ንጹሕ ደሙ አፍ አውጥቶ የሚጮህና የሚጣና ይመስለዋል። አንጥን ሥርሥሮ የሚገባ ረቂቅ ድምፅ።

ሁለተኛ የሚከነክነው ነገር፣ የጐበዜ ሁናቴ ነበር። መቸም እንደ ጐበዜ የመሰለ አንድ ሰው ያላንዳች ምክንያት ይወደው ከነበረው ቤተሰብና ቤተ ዘመድ አይርቅም። አይሸሽም። ጐበዜ በሥራ ብዛት መመካኘቱ ጨርሶ የማይመስል ሆነበት። ሌላ ምክንያት መኖር አለበት። ‹ያይኔ አበባ «ጐ - በ » ስትል የጐበዜን ስም መጥራቷ ነበር? እርሷ አታውቀውም። ከበደ ሲል ሰምታ ይሆን? ይኼ ጐበዜ ወይስ ሌላ ጐበዜ? ፖሊሱ እንዳለው ታፋው ላይ የተነከሰው ጐበዜ ይሆን? ወይስ አጉል ጥርጣሬ ብቻ ነው ያደረበት?› ነገሩን ካላረጋገጠ፥ ሌላው ቢቀር ጐበዜ እንዲህ የሆነበት ምክንያት በትክክል ካላወቀ በጥፋት ጐዳና ላይ ከሆነም እንዲመለስ ሳይመከረም ቢቀር እንደ ዛሬው ሳይሆን፥ ቤተሰቦቻቸው የተማማሉባት በፍቅር በወዳጅነት አንተ ትብስ አንተ ትብስ ተባብለው የኖሩባት

የዳገታማ አድባር፥ በመጨረሻም ሌላ አብሮ አደግ ወንድማቸውን ያጡበት የዳገታማ ገበያ አፈርሳታ ቀውጢ ቀን የምትፋረደው ሆኖ ተሰማው።

ሐሳቡን የሚያስጨንቀው ሳይወድ መጥፎ መጥፎ ነገር የሚያሳስበው ሌላው፥ ጉዳይ የእርሱና የዘይኔ ግንኙነት ነው። ባልና ሚስትነት ወይም ምንኩስና በማይሉት በዚህ አኳኋን ሊቀጥል አይችልም። አንድ መልክ መያዝ ይኖርበታል።

ካሣሁን መንፈሱ እርጋታ ሊያገኝ የሚችለው እነዚህ ነገሮች ፍቺ ሲያገኙ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ ምን ምን ማድረግ እንደሚሻለው በማሰላሰል ላይ እንዳለ ደህና የበልግ ዝናም መጣል ጀመረ። አሁን ሥራውን ትቶ፥ ጐበዜን ወይም ወንጀለኛ ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ማለት እንደማይቻል ተሰማው። አንድ ሰው ያሰበውን ለመፈጸም የተመኘውን ለማድረግ መጀመሪያ ነገር በሕይወት መኖር አለበት። ካለ ምግብ ካለ እህል ደግሞ ሕይወት መኖር አይችልም። የራሱም የዘይኔም ሕይወት። በጉሽጉሽ የተቀመጠው እህል ደግሞ ለበልግ ዘር ተብቃቅቶ እስከ ጐመን መቀንጠሻ እስከ እሸት መቅመሻ ሲያወላዳ ተመስገን ነው። ካሣሁን ሌላውን ሐሳቡን ለጊዜው አዘግይቶ በበልጉ እርሻ ላይ ማተኰር ግድ ሆነበት። ይህም ደግሞ የመንፈሱን ዕረፍት ማጣት ለማቃለል ረዳው። ከጧት ጀምሮ እግሩን ጣመን ክንዱን ዝለት እስኪይዘው ድረስ በሥራ ተጠምዶ ሲውል፥ መንፈሱ ዕረፍት ማጣቱ ስንኳ አይታሰበውም። ሐሳብና ጉልበት ነገ ሕይወት ሰጪ እህል ከሚያበረክተው ጥቁር አፈር ጋር ይቆራኛሉ። ስሜት በሥራ ውስጥ ይሰምጣል። ምሽት ቤት ገብቶ እህል ቀምሶ ጥቂት በሥራ የደቀቀ ሰውነቱን እንዳሳረፈ የድካም እንቅልፍ ጭልጥ አድርጐ ይወስደዋል። በበነጋው ጧት ካሣሁንና ሥራ እንደ ገና ይጣመዳሉ። በዚህ ዓይነት ብዙም ሳይቆይ የራሱን ዕረፍት ነሺ ሐሳቦች ኢምንት የሚያደርግ ከፍተኛ ተግባር መጣ - የእናት አገር ጥሪ!!

«.......በዓለም አቀፋዊው ኢምፔሪያሊዝም አቀነባባሪነት የአካባቢው አድኃሪ የገዢ መደቦች ላለፉት ሁለት ዓመታት ተኩል ሲፈጽሙብህ የነበረው ፀረ - ሕዝብና ፀረ - አብዮት ጥቃትና ደባ ዛሬ ከማንኛቸውም ጊዜ አድጐና ተጠናክሮ ወደ ግልጽ ጣልቃ ገብነት ወረራ ተሸጋግሯል......በየዘመኑ የተፈራረቁ ኮሎኒያሊስቶችና ኢምፔሪያሊስቶች የቃጡበትን ወረራ በሀገራ ወዳድነቱና በቆራጥ ታጋይነቱ እያሳፈረ በመመለስ ተከብሮ የኖረ ታጋይ ከዚህ የበለጠ ምን ዓይነት ድፍረትና ጥቃት ሊደርስበት ይቻላል? በጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ታፍሮ ተከብሮና ተጠብቆ የኖረው ዳር ድንበራችን ዛሬ በዚህ

አብዮታዊ አዲስ ትውልድ መዳፍ ውስጥ ሆኖ መደፈር የለበትም። ለብዙ ሺህ ዘመናት አስከብሮን የኖረው አኩሪ ታሪካችን በዚህ አብዮታዊ አዲስ ትውልድ ጊዜ መጉደፍ የለበትም። ኢትዮጵያ ቀድሞም ዛሬ የጐረቤቶቿን ጥቅምና መብት ለመንካት የማትፈልግ፤ የራሷን ቅንጣት የማታስነካ መሆንዋን ደግማ ደጋግማ ገልጻለች። በተግባርም አስመስክራለች። ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ! ክብርህንና ነፃነትህን ለመድፈር፤ ሀገርህን ለመቁረስ ከጭቆናና ምዝበራ ቀንበር ያላቀቀህን ለጋ አብዮትህን ለመቀልበስ የተጀመረውን ጣልቃ ገብነትና ወረራ ከመለዮ ለባሹ ጋር ተሰልፈህ ለመደምሰስ የምትዘጋጅበት ጊዜ አሁን ነው...... ታጠቅ!..... »

ካሣሁን ከሆዳቸው ቆጥቦ በገዛትና ባትሪዋ እንዳያልቅ በየምሽቱ ለአንድ ሰዓት ያህል ከሚከፍታት ትራንሲስተር ራዲዮ ይህንን ጥሪ ሲሰማ ይህ ነው የማይባል እንዴትና ቁጭት ነዘረው። መላ ሰውነቱ እንደ መንቀጥቀጥ አለ። ጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪካዊት ኢትዮጵያ ማርና ወተት የምታፈስ ተብላ በመጽሐፍ የተጠቀሰችው ባለሙያ ኢትዮጵያ ጠላት ገብቶ ሊመዘብራት ካሣሁን፥ ሐር ቀሚስ የለበሰችው ውብ ወይዘሮ፥ መልካቸው ከሰይጣን የከፉ አረመኔዎች ከበው በሰይፍ ሲዘለዝሏት ታየው። ማመን እንደሚያስቸግር አሰቃቂ ሕልም ዘገነነው። ኢትዮጵያ ደራጎን ሊውጣት አፉን ከፍቶ እንዳሰፈሰፈባት ቢሩታዊት ሆና ራሱ በነጭ ማስላሰልና ማሰብ አላስፈለገውም። እንዳራዳው ጊዮርጊስ ነጭ ፈረስ ባይኖረውም ኢትዮጵያን ብቻውን ለማዳን እንደማይችል ቢያውቀውም እንደ አቅሙ እንደ ችሎታው፥ ከወገኖቹ ጐን ተሰልፎ ሀገሩን ማዳን ምንም የማያጠያይቅና ይዋል ይደር የማያሰኝ ተግባር ሆኖ ተሰማው።

በሣልስቱ በአውራ ጐዳናው ላይ ከምትገኘው ትንሽ ከተማ ውሎ ሲመለስ አርባ ብር አወጣና ለዘይኔ ሰጣት። «ምንድን ነው » ሲትል ግራ በመጋባት ጠየቀችው።

«ብር ነዋ! » አለ ነገሩን በማቃለል አኳኋን።

«እሱንማ እያየሁት፤ መቸ አጣሁት? » በሐሳብዋ የመጣው ጥርጣሬና ሥጋት በፊቷ ላይ ውልብ አለ። ‹ይህንን ይዘሽ ወደ ምትሄጂበት ሒጂ ማለቱ ነው?› የሚል ጥርጣሬ።

ካሣሁን የፊቷን ሰሌዳ እንድ ተመለከተ ስሜቷን አነበበ። ግልጽ ነበር። ከተፈጥሮዋ ክፋት እንደሌለባት ያውቃል። ስለዚህ እንደ ሌላው ስሜቷ ግንፍል

ብሎ ሌላውን ባይወጋም በዝምታም በቅሬታም ያስታውቅባታል። ሳይሻክርም ሳይደበዝዝም ተለሳልሶ እንደ ተቀባ ሥዕል በገሐድ ይወጣል። «ምን መሰለሽ? » አለ በማባበል ክንዷን ዳበስ ዳበስ እያደረገ «ሰው ከቤቱ ሲወጣ መቸም - መቸም እመለሳልሁ ባይ ነው። ግን አይታወቅም መንገድ - በተለይም ሩቅ መንገድ የወጣ ሰው ብዙ ነገር ሊደርስበት እንደሚችል አስቀድሞ ማወቅ፣ ለኢዝያም መዘጋጀት አለበት። እና እኔም እንግዲህ መንገደኛ ስለሆንኩ መቸም አይታወቅምና ለማንኛውም የቤት መጠባበቂያ አንዲሆንሽ ብዬ ነው። » ካሣሁን ዐይኑን ከደን አድርጐ በከባዱ ተነፈሰ።

«የት ልትሄድ ነው? »

«በቀልድም አልሰማሽም? አገራችንን ጠላት ወርሯት ተነሥ ታጠቅ!! ሲባል? እና እኔም መዝመት እፈልጋለሁ። »

ዘይኔ የጓዳ ሥራዋን እያከናወነች በራዲዮ የታወጀው አልፎ አልፎ ከጆሮዋ ገብቷል። ካሣሁንማ ጆሮውን ከዚያች ሬዲዮ ለጥፎ ሲያዳምጥ አይታዋለች። ግን ሊገባት አልቻለም። እንደ ሰማችው እንዳየችው ከሆነ ለአፈርሳታም ለዘመቻም፥ ጥሩንባ እየተነፋ በቃል እየተነገረ ያገሩ ወንድ ሁሉ እንዲ ወጣ ያለፈፋል። ምክንያት ካለው እምቢዮ ከሚለው በስተቀር ሁሉም እየተጠራራ እየተሰበሰበ ይነጉዳል። አሁን ግን፥ በቆሬ ሰፈር እዘምታለሁ ብሎ የተነሣው ካሣሁን ብቻ ነው። «ታዲያ ምን አቻኮለህ! እንደ ሌሎቹ ስትጠራ ስትታደም አትሄድም? » አለች ረጋ ባለ አንደበት።

«በራዲዮን ከመጥራት ሌላ ምን ይምጣ? »

«ታዲያ ሌላው ሲነሣ ትደርስ የለ? »

«አንዱ ሌላው እስኪነሣ የሚጠባበቅ ከሆነማ የሚሄድም አይኖር። እኔ የራሴውን እዘምታለሁ እንጂ ሌላውን ምን አስጠበቀኝ ሌላውም እንደዚሁ። »

«እንደፈቀደህ » አለች በታከተ ድምፅ። ወንድም የላት። አባት እናት የላት። ባል አይኖራት። በቆሬ ቀዬ ብቻዋን ስትቀር ታያት። ከምድጃው አጠገብ አንገቷን ደፍታ ተቀምጣ ታለቅስ ጀመር። ካሣሁን የዘይኔ ስሜት ተሰምቶት አሳዘነች ታለቅስ ጀመር። ካሣሁን የዘይኔ ስሜት ተሰምቶት አሳዘንችውና በማስተዛዘን አኳኋን ከአጠገብዋ ቁርጢጥ አለ። «ምን ያስለቅስሻል? » መዝመት በእኔ አልተጀመረ። እንዲያውም ለአንቺም ቢሆን በዚህ ዕድሜሽ አጓጉል እንደ

መነኩሲት ከመኖር እንዲያውን ‹ባልዋ ጦር ሜዳ ሄዶ ሞተ› ተብለሽ የምትሆኝውን ብትሆኚ ይሻልሻል። »

ዘይኔ የባሰውን አንሰቀሰቃት። «እ - እ - እ- አንተ ሁሌ አስተሳሰብህ የሴጣን ነው » አለች የተነፋረቀች። «ከዚህ ሁሉ ‹አልፈልግሽም ሂጂልኝ ከቤት ውጪልኝ› አትልም በኔ አሳበህ ቤት ንብረትህን ጥለህ ወደ ሞት ከምትሄድ? »

«እንደሱ ማለቴ አይደለም » ካሣሁን የተሳሳተ አነጋገሩን ለማረም ሞከረ። «ቤትም ንብረትምኮ በሀገር ነው። ሀገር ሲኖር ነው። ‹ወላጅ የሞተ እንደሁ ባገር ይለቀሳል፤ ወንድም የሞተ እንደሁ ባገር ይለቀሳል፤ ዘመድ የሞተ እንደሁ ባገር ይለቀሳል፤ ሀገር የሞተ እንደሁ ወየት ይደረሳል› የሚባለው ስለዚህ አይደለም!? እና አገራችን ስትሞት ዝም ብለህ ተቀምጠህ እይ ነው የምትይኚ? »

«ኧረ እንደ ፈቀደህ! » አለች በእንስቅስቋ መካከል።

«እኔ እንዳፈቀደኝ ብቻ አይደለም፤ አንቺም አምነሽበት መስማማት አለብሽ። ትዝ ይልሻል? በሰማይ ነፍሱን ይማርና አባባ ሙሔ እንደኔው እንደ አሁን ለመዝመት ሲነሣ ብታለቅሽበት ምን እንዳለ? ‹ወንድ ልጅ ዘመቻ ሲሄድ በልልታ እንጂ በልቅሶ አይሸኝም። ነውር ነው› ነው ያለው። ያን ጊዜ ስንኳ ሕዝቡን ያስቸገሩ የእኛው አገር ወንበዴዎች ነበሩ። አሁን ግን አገራችንን የተነሣባት ወራሪ ጠላት ነው የተባለው። በመጨረሻስ ሕይወቱ ከማለፍዋ በፊት ምን ነበር ያለን? ‹ለግፈኛ አትንበርከኩ። አገራችሁን ከጠላት ጠብቋት። ሕይወታችሁ ናትና በተደፈረች ጊዜ ሕይወታችሁን ስጧት - ወዛችሁ ከለም ዓፈርዋ ጋር ተአሕዶ እንደሚመግባችሁ - ደማሽሁን አትንፈጉዋት› አልነበረም ያለው? ታዲያ አሁን ተደፈርኩ በደማችሁ - በሕይወታችሁ አድኑኝ እያለች አይደለም? እምቢ ብል የአባባ ሙሔ መንፈስ አይረግመኝም? አጥንቱ እሾህ ሆኖ አይወጋኝም? » ሲል ትኩር ብሎ እየተመለከተ ጠየቃት።

ካሣሁን እንዳሰበው የአባቷ የመጨረሻ ቃል መወሳት መለስ አደረጋት። «ለመሆኑ ገንዘቡን ከየት አመጣኸው » ስትል ጠየቀችው ዕንባዋን በእጅጌዋ እየጠራረገች።

«ራዲዮንዋን ሸጥኳት - ሃምሳ ብር። የመጣል ያህል ነው፤ ግና ምን ይደረግ። እና አሥር ብር ለራሴ ስንቅ ቢጤ አስቀርቻለሁ። »

«ራዲዮኑን!? » በመገረም አተኩራ ተመለከተችው።

«አዎ! ከብት ከመሸጥ አይሻልም? » ሲል ‹የራዲዮዋን› ግምት በማቃለል አኳኋን መለሰ። ዘይኔ ግን ከራዲዮን ጋር በቀላሉ እንዳልተለየ ታውቃለች። ያለ የሌለ ጥራቱን አማጥጦ አሰብ የሚመላለስ ሰው ለምኖ ከአስገዛት ጊዜ ጀምሮ አቧራ እንዳይገባባት በጨርቅ ሸፍኖ በጥንቃቄ የሚይዛት ውድ ንብረቱ ነበረች። የሸጣት በመዝመቱ ቢቆርጥ መሆኑን አመነች።

«ለመሆኑ መቸ ለመነሣት ነው ሐሳብህ? » ስትል ጠየቀችው።

«እኔማ ነገ ብያለሁ። ቅሌን ጨርቄን ማለት ምን ያስፈልጋል! »

«እንግዲያው አንቺማ ተስማሚበት ካልከኝ፤ ሁለት ሦስት ቀን ታገሡኝ » አለችው።

«ለምን? »

«እህ? ትንሽ በሶ ብጤ ይዘጋጅልሃ! »

ካሣሁን ከሦስት ቀን በኋላ ለእናት አገር ጥሪ ራሱን ለማቅረብ ከቤቱ ሲነሣ ልትሸኘው አብራ ወጣችና ድንገት «ቆይ እስቲ » ብላ ወደ ቤት ተመልሳ ገባች። ወዲይው ሙሔ መሆነኛ የዘመተበትንና፤ ቆስሎ ሲወድቅ እንደ ጨበጣት የተገኘችውን ፋስ መጥረቢያ ይዛ መጣች። «የአባዬን ቃል እፈጽማለሁ ካልክ መሣሪያውንም አብረህ ተረከብ እንጂ » ስትል ሰጠችው።

«መሣሪያማ መንግሥት መስጠቱ የት ይቀራል? »

«ለማንኛውም ባዶ እጅ አይወጣም! ለቁጥቋጦ መመንጠሪያ ስንኳ ይሆናል። »

ካሁን ቀደም ሙሔ ሲዘምት ባልና ሚስቱ አብረው እንዳደረጉት አሁን ደግሞ ዘይኔ ከግራሩ ዛፍ ሥር ብቻዋን ቁማ ካሣሁን ቁልቁለቱን ሲወርድ በዐይንዋ ተከተለችው። በራቀ መጠን ቅርጹ እያነሰ እያነሰ ሄደና፣ ከዋናው አውራ ጐዳና ገብቶ ወደ ደሴ አግጣጫ ሲታጠፍ ትንሽ ነጥብ አከለ። ይህንንም ነጥብ ድንገት ሳይታወቃት በዐይንዋ ችፍፍ ያለው ዕንባ ደነበዘዘው.......

# ምዕራፍ ሰባት

ዘለቃ በገባች በወጣች ቁጥር በአፓርታማዋ ወለል ላይ ያገን አስፈሪ ወረቀት ስትፈልግ ሦስተኛው ደብዳቤ ፈጽሞ ባላሰበችው በመሥሪያ ቤትዋ ፖስታ ሣጥን በኩል ደረሳት። በመጀመሪያ ከወዳጅ ከዘመድ ከጓደኛ የሚላክ ማንኛውም ዓይነት ተራ ደብዳቤ መሰላት። ልብዋ በድንጋጤ ትር ያለው የተለጠፈበት ቴምብር ከአዲስ አበባ ለአዲስ አበባ ብቻ የሚያገለግል የአሥር ሣንቲም ቴምብር ብቻ መሆኑን ስታይ ገና ነው። በጣቷ ጨቆን ጨቆን አድርጋ መረመረችው። ከአዲስ አበባ ከተማ ፖስታ የሚደርሳት ቢሆን አብረው ውለው አብረው አምሽተው ለቅንጦት ለቀልድ ያህል የሚላላኩት የበዓል ‹ፖስት ካርድ› ነው። ይህ ግን ወረቀት እንጂ ‹ፖስት ካርድ› አይመስልም። ከአዲስ አበባ ደብዳቤ የሚጽፍላት ሌላ ሰው ደሞ አልነበረም። የምትተዋወቃቸው ሁሉ በቴሌፎን ሊያነጋግርዋት የሚችሉ ናቸው። ዘለቃ እጅዋ ትንሽ እየተንቀጠቀጠ የሻምላ ቅርጽ ባለው የፖስታ መቅደጃ ሸረከተችና ደብዳቤውን አወጣችው። ያው ከአሁን ቀደም የደረሳት ከሁለት የታጠፈ መሥመር የሌለው ብጣሽ ወረቀት ዓይነት ነው። በአንድ ክፍል ውስጥ አብራት የምትሠራው ሌላ ጸሐፊ እስክትታዘባት ድረስ እጅዋ እየተንቀጠቀጠባት አነበበችው። «ሊሆን አይችልም » አለች አንብባ ስትጨርስ ድንገት ሳይታወቃት በመጮህ። ደብዳቤው ካሁን ቀደም ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ የተሰጣት መሆኑን አስታውሶ ነገር ግን ለመታረም ፈቃደኛ ባለመሆንዋ የሞት ቅጣት እንደተወሰነባት ይገልጻል። ቅጣቱ የሚፈጸምበትንም ቀን ይጠቅሳል።

«ምን ሆንሽ? » ስትል የሥራ ባልደረባዋ ጠየቀቻት። ዘለቃ መልስ አልሰጠችም። ሳትሞት እንደ ሞተች ሆና በሞት ዓለም ውስጥ ገባች። ራስዋን ዘለዓለም እንደሚኖር አድርጋ ቆጥራው ባታውቅም ሞት እንደዚህ ዐይኑን አፍጥጦ እንደሚመጣበት ደግሞ አንድም ቀን አልታሰባትም ነበር። በድንጋጤ የተበጠበጠው አእምሮዋ የሞትን ዓለም ለመዳሰስ ሞከረ። ‹ሞት ምን ይመስላል? ከመኖር ወደ አለመኖር ሲለወጡ ምን ይሰማል? ባዶነት ነው? ባዶነት ጨለማ መዋጥ ነው? እንደ እንቅልፍ በሰመመን መውሰድ ነው? ከሞትኩ በኋላ በሕይወት የኖርኩ መሆኔ ይታወቀኛል? ወይስ ጨርሶ መሆንዋን አእምሮዋ ሊቀበል አልቻለም። «ሊሆን አይችልም! » እኔ ዘለቃ! «ነበርኩ! አለሁ! » አለች ሳይታወቃት ከፍ ባለ ድምፅ።

«በፖስታው ውስጥ ምን መዐት መጣብሽ እቴ? » አለች ዘለቃ እንዲህ ስትሆን አይታት የማታውቀው የሥራ ጓደኛዋ።

«ውጭ አገር የነበረች አንዲት ጓደኛዬ በመኪና አደጋ ሞተች! » ስትል ዘለቃ እየተንገደገደች ወደ መጸዳጃው ክፍል ሄደች። ከዚያም በመጸዳጃው ክፍል መስትዋት ውስጥ ከራስዋ አምሳያ ጋር ተፋጠጠች። በሌላው ጊዜ ከመስትዋት ፊት ቁማ ከምሳያዋ ጋር ስትተያይ መዋል አይሰለቻትም ነበር። ትወደዋለች። ትመካበታለች። ጀግኖችን ያንበረከከ፥ ዓለምን ያስገዛ የክሌዎፓትራ መልክ መስሎ ይታያታል። ትኮራበታለች። አሁን ግን ቅርጹ ያው የድሮው ቢሆንም የምትወደው ላህይዋ ጨርሶ የለም። ያለው የሞት ጥላ ያረፈበት የሚመስል ጨፈገግ ያለ ፊት ሆነባት። ሳይታወቃት ከዐይኖቿ ዙሪያ የደም ሥሮች ወጥተዋል። ተስተካክሎ ተበጥሮ የነበረው ጸጉርዋ በእጅዋ እየነካችው መሆኑ ሳይታወቃት ተንጨፍሯል። ይህንንም መልክ ቢሆን የማይታይበት ጊዜ ሊመጣ ነው። ሞት የመስትዋት አምሳያዋንም ጭምር ይወስዳል። ከፊት የመታጠቢያ ገንዳው ላይ በእጅዋ ተደግፋ ትንሽ ከተመለከተች በኋላ ከቦርሳዋ ሁለት ሦስት የቫሊየም ታብሌቶች አውጥታ በመዳፍዋ ውሀ እየገደበች ዋጠች። እንደ ማስረሻ ሰካራም አልሆንም ስትል የመጠጥ ብርጭቆ ከሰበረች ጊዜ ጀምሮ የመንፈስ ጭንቀቷን መሸከም ሲያቅታት ወይም እንቅልፍ እሚቢ ሲላት ከምታውቀው የፋርማሲ ደንበኛዋ ቫልየም ስትወስድ ግን የአሁኑ የመጀመሪይ ጊዜዋ ነው። ከዚያም ፊቷን በተለመደው ማሣመሪያ አባብሳ ወደ ቢሮዋ ተመለሰችና ትንሽ እንዳመማት በመግለጽ ወደ ቤት ለመሄድ አለቃዋን ፈቃድ ጠየቀች።

የቢሮ ጓደኛዋ፤ የሁለቱንም ሥራ ስታጠናቅቅ ውላ በአሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ትንሽ ደቂቃዎች ዘግት ብትወጣ ጭር እያለ በሄደው ግቢ ውስጥ የዘለቃን አውቶሞቢል ቆማ አየቻት። ዘለቃ ፈቃድ የወሰደችው ከምሳ በፊት አንድ ሰዓት ያህል ቀደም ብሎ ነበር። ከሰዓት በኋላ ተመልሳ አልመጣችም። የዘለቃ ሰውነት ተለዋውጦ እንደ ነበር ጓደኛዋ የተገነዘበች ቢሆንም መኪና መንዳት አቅቷት ትታ እስከ መሄድ የሚያደርስ አልመሰላትም ነበር። ለማረጋገጥ ያህል ጠጋ ብላ እንደ ተመለከተች ጨኸቷን ለቀቀችው። ዘለቃ ግራ እጅዋን ከመሪው ላይ እንዳሳረፈች ከሁለት የፊት ወንበሮች ላይ ተዝለፍልፋ ተጋድማለች። ዐይኖቿ ተከድነዋል። ከንፈርዋ ገርበብ ብሎ በሁለት ጠርዝ የደረቀ ምራቅ ነጫጭ ነጥብ ይታይበታል። የሞተች ትመስላለች። ከዘበኞቹ ጋር ሆነው አውቶሞቢሏን ከፍተው በቅርብ ሲያስተውሏት ግን ትተነፍሳለች። ሊቀስቅሷት ሞከሩ። ስንኳን

የሰው ድምፅና የእጅ ንቅናቄ፥ የመድፍ ጩኸት የምትሰማ አልሆነችም። የጤና እንቅልፍ አለ መሆኑ ገባቸውና የሰርቪስ መኪና ተለምኖ ሆስፒታል ወሰዱዋት።

« ‹ትራንኮላይዘር› ማለት የአእምሮ ጭንቀት ማስታገሻ ክኒን ከሚገባው በላይ ነው እንጂ በመሠረቱ ሌላ በሽታ ለጊዜው አላገኘሁባትም። ይህም ቢሆን በጣም ከበዛ አደገኛ ሊሆን ይችል ነበር። አሁን የክኒኑን ኃይል የሚያደክም መርፌ ወግቻታለሁ። ግን የክኒኑ ጠንቅ ከሰውነቷ ጨርሶ እስኪጠፋ ድረስ አንድ ሁለት ቀን ከዚሁ አርፋ ብትቆይ አይከፋም። ለወደፊቱም ቢሆን ይምከርዋት። ለጭንቀት ዘዴ መፈለግ ነው እንጂ እንደዚህ ያለውን መድኃኒት ማዘውተሩ ወይም መልመዱ አይበጅም። ፈረንጅ አገር ሰውን ሁሉ ያበላሸው እርሱ ነው » አላቸው ዶክተሩ፥ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልን።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቴሌፎን ተደውሎላቸው መጥተው በምርመራ ክፍሉ መተላለፊያ ላይ አሥር ጊዜ እየተቀመጡ እየተነሡ፣ ያንን ሰውነታቸውን እያንከባለሉ፥ ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉ ነበር የቆዩት። «ራሷን እኮ አሟት የማያውቀውን ልጄን ዛሬ ምን ቡዳ ለከፈብኝ? ደህና ሰው በጤና ባገር አይኑር ነው? » ሲሉ፥ ስለ ዘለቃ ሥነ ምግባር ሁሉም ሰው የሚያውቅና የሚመሰክር ይመስል አላፊ አግዳሚውን ተረኛ ታካሚውን ይጠይቃሉ። ዶክተሩም ሥራዬ ብሎ ሊያነጋግራቸው የወጣው ከውስጥ ሆኖ ድምፃቸውን ስለ ሰማ ነበር።

«እና ደህና ናት፤ ምንም አትሆንም ነው የሚሉኝ ዶክተር » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጠየቁ።

«እንዳልኩዎት ነገ ከነገ ወዲያ ወደ ቤት መሄድ ትችላለች። የዕረፍት ፈቃድ እጽፍላታለሁ። አንድ ሳምንት ያህል ዕረፍት ከአደረገች ይበቃታል። »

«አሁንስ አፓርትማ ከምትይው ከዚያ ባዶ ቤት አትሄጂም። ሰውነትሽ መለስ እስኪል፥ ውኃ ቀድቶ እህል ቁርሶ የሚያቀርብልሽ ስንኳ የለ። እኔው ራሴ ከዚያ ካልሆንኩ በስተቀር። ሰውነትሽ እኮ የለም። አልቋል ዘለቄ። ምናምኗን እየቀማመስሽ ጥቂት ቀን ባይሆን ከእኔው ጋር ሰንብቺ » አሏት ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ ዘለቃ ከሁለት ቀን በኋላ ከሆስፒታል ስትወጣ። እንደ ጠበቁት ብዙም አላንገራገረችም። ደክሟት ታክቷት ነበር። ከዚህም በቀር በዚያ ባዶ ክፍል ውስጥ ብቻዋን መሆንዋም የባሰ አስፈርቷት ነበር። ሌላው ቀርቶ ሆስፒታል በቆየችበት ጊዜ ስንኳ ሠራተኞች ሲገቡ፥ በነጩ የሕክምና ባለሙያ ልብስ ሥር የሽጉጥ አፈ ሙዝ ብቅ ሲል በሐሳብዋ እየታያት ብዙ ጊዜ

በአስደንጋጭ ፍርሃት ባንናለች። የእናቷ ቤት አጥርም ዝበኛም ስላለው የተሻለ መስሎ ተሰማት።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ ቅንጩውን ገንፎውን፥ ቆጮውን፥ ጭኮውን ፍትፍቱን እንዲያው አለ የተባለውን ምግብ ሁሉ በሰዓቱ እያፈራረቁ እየመገቡዋት፥ አካልዋ መለስ ቢልም፥ መንፈስዋ ሊያገግም አልቻለም። እንደ ወትሮው ስቆ አሳስቆ መጫወት ቀርቶ ሰው ሲያናግራት ከልብ መልስ አትሰጥም። ዐይንዋ ከፊት ለፊትዋ ላይ ከተጋረጠ አንድ ነገር ላይ ትክል ብሎ ዐይንዋ ያረፈበትን ነገር የምትመለከት ግን አትመስልም። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፥ በመጨነቅ ደግመው ደጋግመው ጠየቋት። «የእኔ አንጀት፤ አንድይዬ፣፤ ምን አግኝቶሽ ነው እንዲህ የሆንሽው? ከአንጀቴ ወጥተሽ ለኔ ያልነገርሽ ለማን ልትነግሪ ነው? »

ግን የእሳቸው ምክንያት ማወቅ ድንጋጤ ከመጨመር በስተቀር ምንም ለውጥ እንደማያጣ ስለምታውቅ ልትነግራቸው አልፈለገችም። የምትሰጣቸው መልስ «ምንም አልሆንኩ እማዬ፤ እንዲሁ ነው » የሚል ብቻ ነው።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቢቸግራቸው እንደዚህ ለመሆኗ የራሳቸውን ፍች ፈልገው አገኙ። «ግዴለሽም የዚያ መዘዘኛ ጠንቅ ነው። » ማስረሻን ማለታቸው ነበር። «ባከበርነው በሾምነው፣ ክብር ማዕረግ አልወለደልት ብሎ ባይሆንለት፤ የተገላቢጦሽ ተበደልኩ ባይ ነኝ ሳይል ይቀራል ብለሽ ነው? አሁን ደሞ በሥራ እንደፍ እንደፍ እንደሚል ሰምተናል። እንዲያውስ ለዚህ መንግሥት ሳያድር ቀረ ብለሽ ነው? እንደዚህ ያለ ሰው ለሰው አይተኛም፤ ቂመኛ፣ በቀለኛ፣ ነው። እና ግዴለሽም ነገር ጥሎብሻል። የተከላትን ባልነቅላት ደሞ እኔ ዘርፈሽዋል አይደለሁም! ጠበሉስ ምኑስ? » ይሏታል።

«እኔ እንጃ ይሆናል። ምናʼቃለሁ ትላለች » ዘለቃ እንዲተዋት ብቻ ነገራቸውን የተቀበለችው በመምሰል።

«ነው እንጂ ምን ጥርጥር አለበት! » አሉ አነጋገራቸውን እርግጥ በማድረግ።

ዘለቃ የእናቷ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያስገርማታል፤ ያሳዝናታልም። በእርሳቸው ቤት የቀረባቸው ሰው ሁሉ ጥሩ ሰው ነው። የደርግ መንግሥት ባልደረባም ቢሆን አይጠላም ባይናቸው። «መቸስ ምን ይደረግ፥ በአራዊት መካከል እንደ አራዊት ሁኑ ብሏል መጣፉ። » የሚጠሉት፤ የማይቀርባቸው ሰው ከሆነ ደግሞ «ኧረ ተይኝ! እሱ ሰው ነው ትላላችሁ? ያው ከጊዜው አረመኔዎች ጋር ቢገጥም እንጂ እንዲህ ያደረገው! ኧረ ስሙን አታንሡት! »

ብለው ይዘጋሉ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል አንድን ነገር በመጥፎነት ወይም በበጐነት አንድ ጊዜ ወስነው የሚመለከቱት በሁለት ቀለም ብቻ ነው። ጥቁር ወይም ነጭ። ግራጫ የለበትም። ማስረሻ ዘለቃን እንደ በደለ አድርገው ስለ ጠሉት (እርሷ የወሬ ወሬ እንደ ሰማችው) የደርግ ተቃዋሚ ወይም የኢሃፓ አባል መሆኑ ሊገባቸው አይችልም። ወይም ደግሞ ወዳጅዋ የነበረው የመረጃ ክፍል ሠራተኛ ስለ ቀረበችው ሳይወድ በግድ የደርግ ሠራተኛ እንደሆነ ጥሩ ሰው አድርገው ያዩታል እንጂ በደርግ ሥር እየሠራ ሌላ ዓላማ ያለው መሆኑን ማመን ያቅታቸዋል። ስለዚህም ዘለቃ ስለ ሁለቱ በመጠኑ የምትገምተውን ወይም የሰማችውን አልነገረቻቸውም ነበር።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ስለ ማስረሻ ጠንቀኝነትና መዘዘኛነት ሲነግሩዋት ዘለቃ በበኩሏ አልፎ አልፎ በእርሱ በኩል ማየት የጀመረችው የመወጣጫ ጭላንጭል ታያትና የሰው ስሜትና አስተያየት እንዴት እንደሚለያይ ገረማት።

የዘለቃ ስሜት ፍርሃትና፥ ጭንቀት ብቻ አልነበረም። አንዳንድ ጊዜ የቅጣትዋ ቀን የማይደርስ ይመስላታል። አንዳንድ ጊዜ የቅጣት ጊዜ ከመድረሱ በፊት ነበር ዓለሙ ሁሉ ተለውጦ ፍርሃትና ጭንቀቷ አንድ አስደንጋጭ ሕልም ብቻ ሆኖ የሚቀር ይመስላታል። ምኑም ነገር ሳይለወጥ ጊዜው እየተቃረበ በሄደ ቁጥር ግን - ሌላ - ሌላ ምኞቶችና ተስፋዋ እየተቀነሰ ጭንቀቷ እየከበደ ሲመጣ የሕይወት ጉዳይ ነውና፥ መሞትዋን ፈጽሞ አትፈልግምና ወጥመድ ውስጥ እንደ ተያዘች ዓይጥ ከወጥመድ ብቻ ሳይሆን ከውጭ አድፍጦ ከሚጠብቅ ድምት ጭምር የምታመልጥበትን መንገድ መፈልግ ቀጠለች። በጭንቀቷ መካከል የሚታያት እምዳኛ መንገድ አሁንም ሁለት ነው። ከዚህ ወይም ከዚያኛው ለጥቆ መግባት ነው። ቋ ቋ ቋ እንደሚል የሰዓት ደቂቃ እያንዳንዱ ቀን የሕይወቷን ፍጻሜ በሚቆጠርበት አጣዳፊ ወቅት ለዘለቃ ምርጫው ቀላል አልሆነም። በመጨረሻ ለአስተሳሰቧ ቀላል በሆነው በሁለት ወንዶች ውሽሞች አምሳል ተከሰተላት። ሁለቱ ወንዶች በባለጋራነት ፊት ለፊት ተፋጥጠዋል። እርሷ ከአንዱ ጐን ቆማለች። ፊት ለፊት ያለው ሊገድላት ሽጉጥ አነጣጥሮባታል። ለእርሱ ያላትን ታማኝነት ለማሳመን ወደ እርሱ ሩጣ ከመድረስዋ በፊት መንገድ ላይ ቀንድቦ ሊጥላት ይችላል። ከዚህም በቀር ለጊዜው የሚያሸንፍ መስሎ ሊጥላት ይችላላ። ከዚህም በቀር ለጊዜው የሚያሸንፍ መስሎ የታየው የጐኑ የቆመችው ወንድ ነው። እንግዲህ ምርጫው ግልጽ ነው። ለጊዜው ከጐንዋ ከቆመው ወንድ ጀርባ ተጋርዳ ከተነጣጠረባት ሽጉጥ መዳን። ከዚያ ቀስ ሹልክ ብሎ ወደዚያኛው መሸጋገርና መጠጋት።

ዘለቃ የመውጫዋን ዘዴ ቀደም ተከተል ከመረጠች በኋላም በሥራ ላይ ለማዋል ሁለት ቀን ያህል ስታመናታ ቆየች።

ጥናት ለምትካሂድበት ሕዋስ መሪ ቴሌፎን ስትደውል ደግሞ፥ እርሷ የማታውቀው አዲስ ምሥጢር በመገለጥ ላይ ነበር።

## ፱

የመረጃ ክፍል ሠራተኛ የነበረው ወዳጅዋ የቅርብ ዘመድ የሆነ የኢ.ህ.አ.ፓ መሪ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ መደበቁ ይደረስበትና ተወርዋሪ ጓዶች ሊይዙት ይሄዳሉ። ከክፍሉ ውጭ ሆነው እጁን እንዲሰጥ ይጠይቁታል። አሻፈረኝ ብሎ ተኩስ ይከፍታል። ተኩስ ሲቆም ጥይት እንዳለቀበት ይገምቱና በሩን በርግደው ሲገቡ እርሱ ከአምስተኛው ፎቅ በመስኮት ተወርውሮ ይፈጠፈጣል። ክፍሉና ዕቃው በመርፌ እየተነቀሰ ሲፈተሽ ከተገኙ አንዳንድ መረጃዎች መካከል አንድዋ፣ አንዲት ብጣሽ ወረቀት ነበረች። ወረቀትዋ የተገኘችው አንድዋ የውስጥ ከፈፍ ሥር ተቀብራ ሲሆን «ትክክለኞች - ሀ. ከጥላው ፀ. ኮድ ዝንቄ፤ ለ. ዘለቃ ገ. ኮድ ንብ » የሚል ጽሑፍ አለበት። የመረጃ ተንታኞቹ ፍችውን መገመት ባያቅታቸውም አጥላው ፀ. በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት አካባቢ በጣም የታወቀና በአንድ ቁልፍ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የመምሪያ ኃላፊ ስለሆነ ተጠራጠሩ። ለማረጋገጥ ወደ መሥሪያ ቤቱ ሄዱ። ከሥራ ከቀረ ሦስት ቀን አልፎት ነበር። ወደ ቤቱ ሄዱ። ተዘግቷል። የጐረቤት ልጅ እንደ ነገራቸው አጥላው አሽከርም ገረድም የለውም። ራሱ ግን ሁለቱን ቀን ሲወጣ ሲገባ አልታየም። ስሕተት ቢሠሩ በኋላ የሚያስጠይቃቸው መሆኑ ቢሰማቸውም፣ ነገሩን ለማረጋገጥ ለጊዜው ምርጫ ስላጡ በሩን በተመሳሳይ ቁልፍ ከፍተው ገቡ። ከአንዳንድ አሮጌ ቁሳቁሶች በቀር በቤቱ ውስጥ የረባ ዕቃ የለም። ክፍሎቹ ወና ይመስላሉ። ሌላው ቀርቶ በሳሎኑ ክፍል ውስጥ በአራት ማዕዘን ነጣ ብሎ የሚታየው የሳንቃ ወለል ተነጥፎበት የነበረው ምንጣፍ መነሳቱን ያረጋግጣል። በዚህ ዕለት ከሰዓት በኋላ ሌላ መረጃ ከትግራይ ክፍለ ሀገር በስልክ ተላለፈ። ይኸውም፥ አጉልዕ ከተማን አልፎ፥ ውቅሮ ከተማ ሳይገባ በሚገኘው የንንፍሌ ወንዝ አጠገብ አንድ የመንግሥት ላንድሮቨር መኪና መገኘቱ ነው። ይህ ላንድሮቨር አጥላው ለመስክ ሥራ ከአዲስ አበባ ሲወጣ የሚይዘው ነበር።

ነገሩ በማያሻማ አኳኋን ከተረጋገጠ በኋላ፥ ያኛው ቢያመልጥ የሚቀረው እርምጃ ዘለቃን መያዝ ነበር። የሕዋስዋ መሪ ግን ዐይኑን ከደን አድርጐ ከአሰላሰለ በኋላ እርምጃውን ተቃወመ። «አንቸኩል! »

«እስከታመልጥ? » የሚል ጥያቄ ቀረበለት።

«አታመልጥም። » ራሱን ነቀነቀ።

«ምን እርግጠኛ አረገህ? »

«ራስዋ አረጋገጠላት ይሆናላ! እንዳጠናከርነው መረጃ ከሆነ ባልዋን አማኑኤል ያስገባች መዓተኛ አዚማም ነውች አሉ። እሱንስ አዙራበት እንደ ሆነ ምን ይታወቃል » አለ ሌላው በዘለቃ ሕዋስ መሪ ላይ ዐይኑን አጨንቁሮ።

«ቀልዱን ተዉትና ሐሳብ አለኝ »። እንዲያዳምጣት ለማስገንዘብ እጁን ዘረጋ። «እንደምናውቅባት ካላወቀች ወይም ካልጠረጠረች ልንጠቀምባት እንችላለን። የምትገናኘው ሰው እንዳለ ረጋ ብለን በቅርብ ከተከታተልናት የምታነጋግረው ሰው ካላት ቴሌፎንዋን እንዲያ እንዲያ ካደረግነው እሷም ትልቅ ዐሣ ከሆነች ሰፌ አውታራቸውን እጃችን ማስገባት እንችላለን ማለት ነው። »

«እሱን በምርመራም ቢሆን ልናስወጣት እንችላለን። »

«ከሌሎቹ እንደምናየው ምርመራ ሁልጊዜ አይሠራም። ልታወጣም ላታወጣም ትችላለች። ያ - ለምን ራስኑ ገደለ? መረጃ ለመደበቅ አይደለም? ግን ቀላሉ መንገድ እያለ? ከዚህም በቀር እኛ የውሸት መረጃ ለእርሷ እያጐረሰን እየወሰደች ስትተፋላቸው ግራ ልናጋባቸው እንችላለን። »

«በመካከሉ ብትጠፋስ? »

«በወጥመዳችን የገባች አይጥ መጠበቅ ካቃተን የትግሉን መድረክ ብንለቅ ይሻላል » አለ የሕዋሱ መሪ። አንዳንዶቹ እየተጠራጠሩ ተስማሙ።

በዐይነ ቁራኛ ለማስጠበቅ አስፈላጊውን እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ግን በመካከሉ ከአፓርታ ክፍልዋ ሲያጣት እንደ አጥላው ያመለጠች መስሏቸው ታማ በሆስፒታል ቆይታ ከእናቷ ቤት መሆንዋን እስኪያውቁ ድረስ ተናደው ነበር።

ዘለቃ ለሕዋስ መሪዋ ቴሌፎን የደወለችው ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ነበር።

በአዘኔታ መልክ ከንፈሩን እየመጠጠ በጥሞና አዳመጣት። ሦስቱ ደብዳቤዎች እንዴት እንደ ደረሱዋት፥ ያደረባትን ፍርሃትና ጭንቀት፥ ባንድ በኩል በሚያባብል ቃና፥ በሌላ በኩል በሚያሳዝን ሲቃ ከነገረችው በኋላ፥ «ታዲያ ምን ተሻለ? » አላት እሱም አዘኔታውን በሚገልጽ ቃና መልሶ ከርሷ ምክር የሚጠይቅ በመምሰል።

«የሚሻለውን እራሴ ባውቀው ኖሮማ መች እጠይቅ ነበር! » የለቅሶ ድምፅ ለማስማት አፍንጫዋን በመሐረቧ ጠራረገች።

«እህ! እንደዚህ ሆኖ እኮ አይሆንም » አለ የሕዋሱ መሪ በማጽናናት አኳኋን፤ «ከትግል መድረክ ከገቡ ይሄ የማይቀር ነው። በመንጋ አናርኪስት ሁላችንም የሞት ቅጣት ከተፈረደብን ውሎ አድሮዋል። ታጋይ ይሞታል እንጂ ታዲያ ትግል አይሞትም። »

«እኔ መታገል እንጂ መሞት አልፈልግም። » ዘለቃ በእውነትም በማስመሰልም ተነፋረቀች። የሕዋሱ መሪ ስላላመናት በሽቀ። አስመሳይነቷ አስገረመው። ‹ምን ዓይነት ተዋናይ ይወጣሽ ነበር?› አለ በሆዱ።

«ተይ - ተይ እንዲህ ሆደ ባሻ መሆን አያሻም› አለ፣ በማባበልና በማበረታታት።

«መሆንም ሲያንሰኝ ነው! ከሕይወት የበለጠ አለ? » የባሰውን ተንሰቀሰቀች።

የሕዋሱ መሪ ስልኩን ከጆሮው እንደ ደቀነ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆየ። እውነት በአደጋ ላይ መሆንዋን ቢያምን ኖሮ አስፈላጊውን ጥበቃ ያስደርግላት ነበር። ስትወጣ ስትገባ የታጠቁ ሰዎች በመኪና ሆነው እንዲከተሉዋት፥ የምትኖርበትም ቤት ጠባቂ እንዲቆምበት ማድረግ ይችላል። የማያቁባት መሆናቸውን ለማሳመንም ይህ አንዱ ዘዴ ነበር። ግን ይህንን የመሰለው ጠንካራ ጥበቃ ደግሞ ከሌሎች የኢሃፓ ሰዎች ጋር እንዳትገናኝ ስለሚያዳግት ዋናውን ዕቅዱን ያከሽፍበታል። «የተቻለውን ያህል በዐይነ ቁራኛ እንድትጠበቂ ይደረጋል። አንቺም ደግሞ በተቻለ መጠን ጠንቀቅ ማለት ነው » አላት የሚያስብና የሚቆረቆር በሚመስል አንደበት።

ዘለቃ ቴሌፎኑን ዘግታ ቀና ስትል ተማሪ የነበረች የምትመስለው በቅርቡ የተቀጠረች ልጅ እግር የቤት ሠራተኛ ከኮሞዲኖው አጠገብ ዕቃ የምታወጣ ይመስል ጉንበስ ብላ አየቻት። ቴሌፎን መደወል ስትጀምር በክፍሉ ውስጥ

አልነበረችም። ከዚያም ወዲህ ስትገባ ኮቴዋ አልተሰማም ነበር። ጆሮዋን ቀና አድርጋ ስታዳምጥ መቆየቷ ያስታውቃል።

«ምን ትሠሪያለሽ? » ስትል ዘለቃ ተቆጣች።

«እሜቴ ሰዓቱን ጠብቀሽ አጥሚቱን ስጫት ስላሉኝ ላቀርብልዎት ነዋ » አለች ሲኒ እያወጣች።

ዘለቃ ሰዓቷን አየች። «ገና አንድ ሰዓት ይቀር የለም? ቀጣፊ! ጥፊ ከፊቴ! »

የቤት ሠራተኛዋ የዘለቃ ድንገተኛ ቁጣ ሳያስገርማትና ሳይስደነግጣት «እኔ ምን ቸገረኝ! » አለች በዐይንዋ ቂጥ እያየቻት ስትወጣ።

የሕዋሱ መሪ ቴሌፎኑ ከተዘጋ በኋላ እንደ ዕንባ ጨምቆ የሚያወጣው ይመስል ዐይኑን ጭፍን አድርጎ አሰበ። ‹ምናልባት እውነቷን ይሆን? መረጃው በአብዛኛው የሚያዘነብለው ኢ.ህ.አ.ፓ. ልትሆን መቻሏን ወደ ማረጋገጡ ነው። በቤተ መንግሥቱ ፍልሚያ ብዙ ምርጥ ጓዶችን የገደለውና ሲታኰስ የተገደለው የመረጃ ክፍል ኃላፊ የረጅም ዘመን ወዳጅዋ ነው። እንዴት ሳይመለምላት ይቀራል? ሞክሯት ስለማታምንበት እምቢ ብላው እንደ ሆነስ ለምን ሳትነግረን ቀረች? በአደባባይ የማይገለጽ ምሥጢር በአልጋ ላይ ሳት ብሎ ሳያመልጥ አይቀርም። ግን ስለ እርሱ ምንም ነገር አንሥታልኝ አታውቅም። ልብዋ ከወደዚያ ቢሆን አይደል? በዚህ ላይ ደግሞ ከቀንደኛው ኢ.ህ.አ.ፓ አባል ዘንድ የተገኘው ያለ ጥርጥር ስሙና የሚጠቅሰው ማስረጃ አለ።› ኢ.ህ.አ.ፓ. አለ መሆንዋን ማመን አቃተውና ራሱን ነቀነቀ።

ከሌሎቹ ጋር ደግሞ ተወያየበት፤ ተመካከረበት። የአብዛኞቹ አስተያየት እንደ እርሱው ዓይነት ሆነ። ‹ለምን አደጋ የተቃጣባት መምሰል ፈለገች?› ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ትንታኔዎች ቀረቡ። ዋናው ላለመጠርጠርና በዚህኛው በኩል የበለጠ ለመታመን የበለጠም ሠርጎ ለመግባት ነው፤ ኃይል ለመበታተንና ለማደናገርም ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው አጠናክሮ ለመጠበቅ ቢያንስ ቢያንስ አንድ ላንድሮቨር ሙሉ የታጠቀ ኃይል፣ ያስፈልጋል። ሠርገው የገቡ ሌሎችም መኖራቸው ሲታመን፤ እንደርሷው ከኢ.ህ.አ.ፓ አደጋ ሊጣልብን ነው እያሉ ጠንካራ ጥበቃ የሚጠይቁ ቢሆንና ጥያቄያቸው ቢፈጸም ለእውነተኛ ታጋዮች የሚደረገው ጥበቃ መሳሳት ይኖርበታል። ይህ ደግሞ ለኢ.ህ.አ.ፓ ታጋዮችን ለመግደል የቀለለ ያደርግለታል ማለት ነው። ስም ለማጥፋትም ይረዳል። ሴቶቻቸውን ወይም ውሽሞቻቸውን በታጠቀ ኃይል ያሳጅባሉ ብለው ፕሮፓጋንዳ ይነዙበታል።

በመጨረሻ፥ ‹ምናልባት እውነቷን ቢሆንስ?› ለሚለው ቅንጣት ጥርጣሬ፥ አንድ ሁለት ጓዶች ተሠውረው በዐይነ ቁራኛ እንዲጠባበቋት ተወሰነ። ከሌሎች የኢ.ህ.አ.ፓ አባሎች ጋር ግንኙነት እንድታደርግ ስለሚፈልግ። ይህ ግን ለዘለቃ አልተነገራትም።

ቅጣቱ ይፈጸማል የተባለው እስከ ገባው ወር መጨረሻ ድረስ ነው። የወሩ ማለቂያ እየተቃረበ በሄደ ቁጥር፥ የዘለቃ ጭንቀት የምትይዘው የምትጨብጠውን አሳጣት። ሐኪሙ የጻፈላት የዕረፍት ጊዜ ቢያልቅም ሥራ መሄዱን ተወችው። በአላፊ አግዳሚው ሰው ሁሉ ጉያ የሽጉጥ አፈ ሙዝ እየታያት፥ ሌላው ቀርቶ ከእናቷ ግቢ መውጣቱን አቆመች። ለሕዋስ መሪዋ ሁለት ጊዜ ስልክ ደወለች። ልታገኘው አልቻለችም። ቢሮው ውስጥ እንደ ሌለ በጸሐፊው ተነገራት። ግን አላመነችም። «የውስጥ ዝንባሌዬን ተገንዝበው፥ እነሱም ሊያስበሉኝ ነው የሚፈልጉት? » አለች ከራስዋ ጋር፥ ከንፈርዋን እየነከሰች። ሁለተኛውን እርምጃ ከመውሰድ በቀር አሁን ሌላ ምንም ምርጫ የላትም።

የማስታወሻ ደብተርዋን ከፊቷ ዘርግታ ቁጥር እያነበበች ሁለት ጊዜ የቴሌፎኑን ጭንቅላት አንሥታ መልሳ አስቀመጠችው። ‹ኩራት እራት ነው› የሚለው አነጋገር በጆሮዋ እያቃጨለ አስቸገራት። ሕይወት ደግሞ አሳሳቻት። ‹ሕይወት ከሌለ ኩራት ብቻውን እንዴት ሊኖር ይችላል?› ስትል ስሜቷን ረታችና በሦስተኛው ደወለች።

«ማስረሻ? » ስትል ጠየቀች፤ ቀድሞ የምታቆላምጥበትን አንደበት ከተቀበረበት ለማውጣት እየሞከረች። ዘለቃ በጭንቀቷና በፍርሃቷ መካከልም፣ ያ ስለታም አእምሮዋ፥ እንደ ግሩም ሠንጠረዥ ተጫዋች መረማመጃውን ማስላት አልሳተም ነበር። ኢ.ህ.አ.ፓዎችን በማስረሻ በኩል ለመቅረብ የወሰነችውም ከብዙ ማሰላሰልና ማመዛዘን በኋላ ነበር። አድነኛ ነገር የኢ.ሃ.ፓ. አባል መሆኑን - እንደ ጊዜው የጋዜጣ አባባል ከሚታመን ምንጭ - ማለትም መረጃ ሠራተኛ ከነበረው ከሚቹ ወዳጅዋ የሰማችው ማስረሻ ብቻ ነው። ስለ ሌሎች የወሬ ወሬ ሰምታለች ወይም መስልዋታል። ግን እርግጠኛ መሆን አትችልም። ሁለተኛ ነገር፥ ከልቡ እውነተኛ ኢ.ሃ.ፓ. ባይሆን ወይም የደርግ ሠርጐ ገብ ቢሆን እንኳ አሳልፎ የሚሰጣት አይመስላትም። እርግጥ ቂም ይዛበት ሊሆን ይችላል። ግን ቂሙ ወደ ከፍተኛ በቀል የሚሸጋገር ዓይነት አይደለም። የምታውቀው ማስረሻ ቆራጥ አይደለም። ሕሊናው በጣም ስስ፥ መንፈሱ ደካማ ነው። ለማኑኤል ሆስፒታል ያበቃውም ይህ ተፈጥሮው ነው። ከቅርብ ጊዜ

ወዲህ አንድ ዓይነት ነገር ይሰማት ጀምሯል። ይኸውም ‹ከዚህ ሁሉ ጣጣ ውስጥ የከተተኝ የማስረሻ ግፍ ይሆን?› የሚል ነው። ይህ ከሆነ ይቅር ለእግዚአብሔር መባባሉን በተቻለም መልሶ መወዳጀቱ የሚበጅ መስሎ ተሰምቷታል። ሕይወት በጣም አሳስቷታልና ከጭንቀቷ የተነሣ፥ ከተቆፈረባት መቃብር ወጥታ ሰላምና ሕይወት ታግኝ እንጂ ማስረሻ ከፈልገ አብራው ለመኖር እስከ መሳል የከጀለችበት ጊዜ ነበር። ራስዋን እንደምትወድ ሁሉ በውበቷ እንደምትተማመን ሁሉ ሌላ ሰው እንዴት ሊጠላት እንደሚችል ስለማይገባት፥ ማስረሻ አሁንም የሚያፈቅራት ይመስላታል።

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ፥ እሷ ያለችበት ቡድን ወገኖች ግንኙነት ማድረጓን ቢደርሱበት «ባሌ ስለ ነበር ለመፋታት ወይም ለመታረቅ እንድንነጋገር እንጂ ስለ ፖለቲካ ጉዳይ አይደለም » የሚል ምክንያት ልትሰጥ ትችላለች።

ማስረሻ ድምፅዋን አውቆ ያደፈጠ ይመስል ስልኩን አንሥቶ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆየ። «ማስረሻ? » አለች ዘለቃ እንደ ገና።

«ነኝ » አለ በጥርጣሬ አነጋገር።

«ዘለቃ ነኝ፣ እንደ ምን አለህ? ደህና ነህ? » ሰላምታውን ቀደም ብላ እንዳሰበችው አለመጣላትም። ያ ቀልጣፋ ምላሷ የተጣበቀ መሰላት። የማስረሻ አመላለስም ቢሆን አላቃለለላትም። ለጆሮዋቸውም ለአፋቸውም ጣዕም የማይሰጥ ምንችክ የተለምደ ሰላምታ ቃላት ከተቀባበሉ በኋላ «ለከባድና ለአስቸኳይ ጉዳይ እፈልግህ ነበር » አለችው።

«ለምን ነበር? »

«በቴሌፎን አይሆንም። ፈቃድህ ከሆነ ምናለ ብንገናኝ? ቤት ነው የምውለው። በማንኛውም ሰዓት ብትመጣ ታገኘኛለህ። እና ዛሬ መምጣት ትችላለህ? »

«ዛሬ አልችልም » አለ ንዴቱን ከአንደበቱ ላለማሳወቅ እየታገለ።

«ነገስ? »

«ሥራ ይበዛብኛልና እንዳመቸኝ ለመምጣት እሞክራለሁ » አለ ጭውውቱን በአጭሩ ለመቅጨት። ሦስት ሰዓት ሙሉ ይሙት ይዳን እንደ ደረሰ ፈጽሞ ረስታው የራሷን ዓለም ስትቀጭ ቆየች። ያን ጊዜም የባለሥልጣን ሚስት ለመባል፥ ከእናትዋ ጋር አሾሙት - አሁንም ያው የወትሮዋ ዘለቃ ናት።

‹አብዮትም ዕድሜም ሰውን አይለውጠውም?› ሲል ከራሱ ጋር በመጠያየቅ ራሱን ነቀነቀ።

«መቸ? »

«እንዳመቸኝ ራሴ እመጣለሁ። አልኩሽ! » ብሎ ስልኩን ሊዘጋው ሲል በአስተሳሰብ ቀድማ «እሺ እንዳልክ፤ ግን ቤቱን ታውቀዋለህ? » ስትል ያላሰበውን ጥያቄ ሰነዘረችበት።

በሽቀ። ‹ምናለ ይህንን ብልጠቷን ለደግ ነገር ብታውለው?› አለና በሐሳቡ እርሱም እንዳይበለጥ «ያው ከቀድሞው ቤት አይደላችሁም? » ሲል ጠየቀ።

«ከየጠቅኸማ ምኑን አወቅኸው። ካላወቅኸው እንዴት መምጣት ትችል ነበር? አይ የአንተ ነገር » አለች ቀድሞ ራሷን አልቃ እሱን እንደ ልጅ በምታስተምርበት ቃና። ከዚያም አዲሱን የቤት አድራሻና የቴሌፎን ቁጥር ሰጠችው። «እስከ ሁለት ቀን ካመጣህ ዋጋ የለውም። »

«እሺ » አለ በታከተ አንደበት።

ዘለቃ ቴሌፎኑን ዘግታ ከአልጋው ላይ ስትጋደም ከአለፉት ጥቂት ቀናት ለመጀመሪያ ጊዜ ዐይንዋን ከደን አድርጋ ስታስብ፥ ከንፈርዋ በተስፋ ፈገግታ ከፈት አለ። ስሟን ስትነግረው ስልኩን ከጆሮዋ ላይ አልዘጋውም። ወይም መሳደብ ቀርቶ አልወቀሳትም። ስለዚህ አሁንም ስለ እርሷ የፍቅር ስሜት እንዳለው የፍቅር ስሜትም ስላለው እንደሚመጣ ተሰማት። በአነጋገሩ ትንሽ ቆጠብ ቢልም እረፍት ነው። ለአንድ ሁለት ቀን የተኳረፉ ሰዎች ስንኳ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ልብ መጫወት ያስቸግራቸው የለ? አለች ከራስዋ ጋር።

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ስንኳ ጠበልና መድኃኒት ፍለጋ ውለው ሲመለሱ እንቅልፍ እንደ ወሰዳት የነበረው የፊትዋ ላይ ፈገግታ አስገረማቸው። «አንድዬ ተማለድከኝ? » አሉ ወደ ጣሪያው አንጋጠው።

የዘለቃ ጥሪ ማስረሻን በጭንቀት ሠቀቀኑ ላይ ተጨማሪ የሐሳብ ሸክም ጫነበት። ለምን ፈለገችው? እንደ ገና በጣቷ ዙሪያ ለማሽከርከርና መልሳ አዘቅት ውስጥ ለመጣል? ወይስ ችግር አጋጥሟት? እንደ ወትሮዋ ለማባባል ትሞክር እንጂ ድምፅዋ በመጠኑ የጭንቀት ቃና ያለበት ይመስላል። ምን ችግር ገጥሟት ይሆን? ታፈሱ እንደገረችው ቡድን ውስጥ ገብታ ከኢ.ሃ.ፓ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ተመዘግባለች። ቡድንዋ ውስጥ እንዲገባ ወይም በኢ.ሃ.ፓ ላይ እንዲሰልልላት

ልትጠይቀው ይሆን? ለምን እንደምትፈልገው ምክንያቱን ሲያውቅ መሄዱንም ሆነ መቅረቱን ለመወሰን ይቀለው ነበር። አሁን ግን በሐሳብ ተጨነቀ።

እርግጥ ከዚህ በፊትም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ ዘለቃን ለማየት እየከጀለ ተናድዷል፤ ተበሳጭቷል። - እንደ ውሻ ወደ ትፋቴ አልመለስም፥ ተፍታኛለች፥ ተፍቻታለሁ - እያለም ፈተናውን ለመወጣት ሞክሯል። እንደዚሁም እጁን ሰጥቶ ወይም በአዲሱ አነጋገር ‹ራሱን አጋልጦ› ከዚህ የፖለቲካ ወጥመድ ለመወጣትና ከናካቴው እርም ብሎ ለመተው ሲያስብ ሳይፈልግ ዘለቃን አብሮ ማሰቡ አልቀረም። ታፈሱ እንደ ነገረችው ከሆነ አደገኛ ተብላ በኢ.ሃ.ፓ ጥቁር መዝገብ የሠፈረች ዋና «ደርጊስት » ናት፤ ዋና ዋናዎቹን ታውቃለች ማለት ነው። በፈጸመችበት በደል ከተጸጸተችም ልትረዳው ትችላለች። ርዳታውን የሚፈልግ ራሱን ማጋለጥ አይደለም። ይህን ማንም - የትም ቦታ የኢ.ሃ.ፓ. አባል ሁሉ የሚያደርገው ነው። ግን በተለይ ታፈሱ በእርሱ ምክንያት እንዳትነካበት ሌሎቹን ከመጠቆም እንዲድን ይፈልጋል። በዚህም ነገሩ ሸፋፍነውለት ከጊዜ በኋላ ወደ ውጭ አገር እንዲሄድ ቢፈቅዱለት ጀርመን አገር ሥራ ሊያሲዘው የሚችል አንድ የበጎ አድራጎት ሥራ አስኪያጅ ወዳጅ አለው። ሲደለደል ታፈሱንም እንድትመጣ ያደርጋል። ይህንን ያልምና መልሶ፣ «ከዚህ መዓት አድኝኝ ከዚህ ጣጣ አውጭኝ » ብሎ ዘለቃን መለመኑ የመጨረሻ ውርደት ይመስለውና ራሱን ይታዘበዋል። በታፈሱ ላይም ክህደት የሚፈጽም ሆኖ ይሰማዋል! » ብላ ስትማጠነው የመኩራራት ስሜት ቢጤ ቢያድርበትም ምክንያቱን እስከ አላወቀ ድረስ ሌላ ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ ተጠራጠረ።

በዚህ ዓይነት የማስረሻ ሐሳብ በመዋለል ላይ እንዳለ ታፈሱ ስልክ ደውላ በአስቸኳይ እንደምትፈልገው ነገረችው።

«ፍርዴን እንደ ሆነ በስልክም ልሰማው እችላለሁ። እንዲያውም ጊዜ ከማጥፋት ይሻላል » አለ ማስረሻ።

«እሱ አይደለም። ሌላ ጉዳይ ነው። »

«በስልክ የማይነገር? »

«አዎ! »

«በምሥጢር ማዞሪያሽም? »

«አዎ ብየሃለሁ » አለች ታፈሱ እርግጥ አድርጋ። እግጥ በስልክ ልትነግረው ትችል ነበር። ግን የማስረሻ ቴሌፎን ተጠልፎ እንዳይሆን በመጠኑ ትሠጋለች።

ይበልጡን ግን በፊት ለፊት ለመንገር የፈለገችው ሲሰማ የሁናቴውን መለዋወጥ ለመገንዘብ ስትል ነበር።

«ግን አያሠጋንም? » ሲል ጠየቃት። ታፈሱ ከማስረሻ ጋር እንድትገናኝ ደረበ ካስጠነቀቃት ወዲህ እንደ ልብ ወይም እንደ ፈለጉ አይገናኙም ነበር። በጣም ይጠነቀቃሉ።

«ደረበና ሌሎች ብዙዎቹ ዛሬ ፊልም ገቢ ስለ ሆኑ ደህና ነው » አለችው።

«የምን ፊልም? »

«አሲምባን ነዋ! » አለች ባለማወቁ የተገረመች በመምሰል። የኢ.ሃ.ፓዎች «አሲምባ » እያሉ የሚጠሩት ‹ቆዩ ስንደቅ ዓላማ› የተባለው የቻይና ፊልም ነበር። የኢ.ሃ.ፓ. ሠራዊት ከአሲምባ በድል አድራጊነት ለመግባቱ እንደ ምሳሌ ሆኖ ስለ ተወሰደ አባላት ሁሉ እንዲመለከቱት መመሪያ ተላልፎ ነበር።

«ከመሰለሽ እሺ - ለአንቺ እንደ እኔ እንደ ሆነ ደንታ የለንም። » ለአስቸኳይ ጉዳይ በሁለት ሴቶች መፈለጉ ግጥጥሞሽ አስገረመው። የሚገናኙበትን ሥፍራና ጊዜ ተቃጠሩ።

ታፈሱ፥ የቤት ሠራተኛ የሚያስመስል ነጠላ ተከናንባ ማስረሻ ከኢ.ህ.ፓ እንደ ተማረው አንዲት ኮፍያ እስከ ቅንድቡ ድረስ ደፍቶ፥ አውቶሞቢሉን በመስፍነ ሐረር መንገድ ወደ ጐጃም መሥመር እየነዳ ቀለመ ወርቅ ትምህርት ቤትን እንዳለፉ «እንግዲህ አያሠጋንም ካልሽ በዚያውም እግረ መንገዳችንን የምንዝናናበት ሥፍራ አለ። ካሁን ቀደም የማታውቂው ከሆነ! » አለ በቀልድ አሽሙር። ካለወትሮዋ የመቅበጥበጥና የመጨነቅ ሁናቴ ስላየባት ለምን እንደ ፈለገችው በጥያቄ ሊያጣድፋት አልፈለገም። ታፈሱም ዝም አለች። በሐሳብ ተውጣ። መሪ ይዞ አውቶሞቢል እያሽከረከረ ብትነግረው ስሜቱ ምን እንደሚሆን እርግጠኛ አይደለችም። አማኑኤል ያስገባው ስለ ስሜት እንዳለው ታውቃለች። የት ላይ ሲነኩት እንደሚበሳ ግን አታውቅም። ሠጋች። ፈራች። ለእርሱ። ስለ እርሱ ባደረባት ስሜት ለእርሷም። ከመጀመሪያው ልትነግረው ፈልጋ ስልክ መደወሏ እንደ ስሕተት ይሰማት ጀመር። የጐድን ሥርቅ አርጋ ስታየው ለስላሳ ተፈጥሮው ያንሰባርቅባትና «ታዲያ እኔን ምን አገባኝና ነው? » ትላለች።

ድል በር መታሰቢያ ቡና ቤት ግቢ፣ ችምችም ባለ የዛፍ ጥላ ሥር አውቶሞቢሏን አቁመው ጥብስ ታዞ፥ ቢራ ቀድሞ መጥቶ የባጥ የቋጡን እያወጉ

እንደ ተጐነጨ ማስረሻ ሳያስበው ዘለቃ ትዝ አለችው። ተዋውቀው ፍቅራቸው የጦፈ በመሰለበት ወቅት እንደ አሁኑ አውቶሞቢል ውስጥ ሆኖ የበግ ጥብስ ለመብላት ቢራ ለመጠጣት፥ ለመሽኮረማመም፣ ከአስፈልገም የመኝታ ክፍሉ ቅርብ መሆኑን በማወቅ አንድ ሦስት ጊዜ አብረው መጥተው ነበር። ታዲያ አሁን ይኸን ትዝታ ምን አመጣው? ዘለቃ ስለ ደወለችለት ነው ትዝታው የተቀሰቀሰበት? ወይስ ከታፈሱ ጋር የዚህን ዓይነት ሕይወት መጀመር ፈልጎ? ሲያስበው ራሱም ግራ ገባው።

ማስረሻ በአእምሮው የመጣውን ሐሳብም ሆነ የታፈሱን ጉዳይ አቃሎ ለማየት ሞከረ። «እሺ፤ እንደ ሥለት ቀጠሮ የማያልፍ አድርገሽ የፈለግሽኝ ጉዳይ ምንድን ነው? » ሲል ማስረሻ ጠየቃት ጉንጮቿን በጣቱ ቀንጠብ ቀንጠብ እያደረገ። ነጠላዋን ተከናንባ እንዳቀረቀረች ዝም አለች። «በይ እንጂ በአስቸኳይ የፈለግሽኝ ለምንድ ነው? » እንደ ገና ጉንጯን ቆንጠጥ አደረገ።

«ልትገደል ነው! » አለች ታፈሱ ታምቆ የወጣ በሚመስል ድምፅ።

«ማን? »

ስሚን መጥራት አልሆነላትም። «ተመዝግባለች ብዬ ነግሬህ የለም! » አለች አንገቷን እንዳቀረቀረች።

«ለካስ ለሱ ነው! » አለ ማስረሻ ነገሩ ድንገት ቦግ ብሎለት በቡጢው መሪውን ለመምታት እየቃጣው።

«ምን ለካስ? » ቀና ኮስተር ብላ ጠየቀችው።

በበኩሉ አንገቱን ደፋ አድርጎ ለማድበስበስ ሞከረ።

«ለካስ! ያልከው ስለ ምንድን ነው? » ታፈሱ መልሳ አፋጠጠችው።

ማስረሻ የተናገረው ሳይታወቀው ነበር። አሁን የታፈሱን ጥያቄ መመለስ አለበት። «ለአስቸኳይ ጉዳይ እፈልግሃለሁ ስትል ስልክ ደውላልኝ ነበር። ለመሆኑ እንዴት አወቅሽ? » ሲል መልሶ ጠየቃት።

«ካሁን ቀደም እንደ ነገርኩህ በተለይ ስላንተ ጉዳይ የሚተላለፈውን ነገር ለማወቅ የደረበን ቴሌፎን ስከታተል ዛሬ ትእዛዙ ሲተላለፍለት ሰማሁ። የደወለው ደረበ ነው። እኔ በተለይ የያዝኩት የደረበን ስልክ ቁጥር ስለ ሆነ መላሹ ማን እንደ ሆነ ለማወቅ አልቻልኩም። ግን ‹የዲፌንስ ስኳድ የረጅን ወይም ወይም የዞን› ኃላፊ መሆን አለበት። ደረበ ‹የሚሸኑ› የመጨረሻ ውሳኔ

ከምን እንደ ደረሰ ጠየቀው። ያኛው የበላይ አካልም ‹ስለ ዘለቃ ነው?› ብሎ ከጠየቀ በኋላ ደረበ አዎ ብሎ ሲመልስለት በመታረም ፈንታ እንዲያውም ፕሮቴክሽን መጠየቋን ከአጠገቧ የተሰጠ መረጃ ስለ ጠቆመ በማንኛውም ጊዜ ደርግ ሊሠውራት ስለሚችል ሚሽኑ መፈጸም እንዳለበት ነገረው። እኔ ግን መፈጸም እችላለሁ ሲል መለሰ። የበላይ አካሉም ዝግጅቱ ከተሟላልህ ትችላለህ አለው። ይኸው ነው እና፥ የደወለችልህ ማስጠንቀቂያ ደርሷት ለዚሁ ይሆናል። ግን ኢ.ሃ.ፓ መሆንህንና አድራሻህን በም ዐወቀች? » ስትል በጥርጣሬ ትዝብት እየተመለከተች ጠየቀችው።

«ምን አውቃለሁ! ጠንቋይ ትቀልብ እንደሆነ! እኔ እንደሁ ካለ አሁን የት እንዳለችም አላውቅም ነበር። » ማስረሻ ትከሻውን ነቅነቅ አደረገ፥ ያቃለለ በመምሰል። ግን በሐሳቡ ውስጥ አንድ ነገር ቅርጽ እየያዘ መጥቶ ነበር። «እና፥ በአስቸኳይ የፈለግሽኝ ይህንን ልትነግሪኝ ነው? » በቁልምጫ ዐይን ተመለከታት።

በዝምታ አወንታ መለሰችለት።

«ለምን? » ሲል እንደ ገና ጠየቃት።

በቀጥታ ወዲያውኑ ልትመልስለት አልቻለችም። መልሱን የምታነብበት ይመስል ዐይንዋን ከቢራው ብርጭቆ ላይ ተክላ በሐሳብዋ ወደ ኋላ ተመለሰች። በጠለፋ ስልክ ውሳኔውን እንደ ሰማች መጀመሪያ ያደረባት ስሜ - ታዲያ ምን አገባኝ? - የሚል ነበር። እየቆየች ሕይወቷን ከማስረሻ ሕይወት ጋር አያይዛ ስታስበው ግን ሕሊና የሚቆጠቁጥ ሆነባት። በፖለቲካ ፍልሚያ የሰው ሕይወት እንደሚጠፋ ታውቃለች። አንድ የምታዋቀው ግለሰብ ሕይወት እንደሚጠፋ አስቀድማ ስትሰማ ግን የመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር። ይህ ሕይወት ደግሞ፥ አሁን - አሁን ለስላሳ ተፈጥሮው ስቧት፥ ሠቀቀኑ ማርኳት፥ በራስዋ ሕይወት ውስጥ ወሳኝ ሥፍራ የያዘ ሆኖ ከሚሰማት እሱም የሚያፈቅራት ከሚመስላት፥ ከማስረሻ ሕይወት ጋር አንድ ጊዜ የተቆራኘ ነበር። ነገሩን ደብቃ ብታስቀረው ነገ በነገ ወዲያ ምናልባት ከማስረሻ ጋር ሕይወታቸው በሚቆራኝበት ጊዜ፤ በቅናት በበቀል፥ የፈጸመችው የዝምታ ግድያ ሆኖ ሕሊናዋን እንደሚቧጭረው ተሰማት። ማስረሻ እንደምታስበው የሚያፈቅራት ከሆነ፥ የዘለቃ ሕይወት ቢተርፍም የሚቆራኘው ከእርሷ ሕይወት ጋር ነው። እንደምታስበው የማያፈቅራት ከሆነና አሁንም ከዘለቃ ፍቅር ያልተፈታ ከሆነ ደግሞ ስትገደል ስስ ተፈጥሮው ይፈናዳና እንደ ገና ወደ አማኑኤል ሊመለስ ይችላል። በጣም

ስለምታስብለት ይህ እንዲደርስበት አልፈለገችም። ስለዚህም - ልንገረውና ቢፈልግ ያስጠንቅቃት፥ ባይፈልግ እኔ ከሕሊና ወቀሳ ነጻ እሆናለሁ - ብላ ነበር የወሰነችው። የድርጅት ክህደቷን ከሚመለከት ረገድም ‹አንድ ሴት ሞተች፤ ተረፈች ምን ልዩነት ታመጣለች?› ስትል ራሷን አጽናንታ ነበር።

አሁን ግን፥ ነገሩ ካሰበችው ትንሽ የተለየ ሆነባት። አሁን ማስረሻ ስልክ ደውሎ ማስጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን ዘለቃ እንደ ፈለገችው ሂዶ መገናኘት አለበት። ግንኙነታቸው ምን ውጤት እንደሚያስከትል አታውቅም። በመጠኑ ቆጫት። ጸጸታት።

«ለማወቅ ትፈልግ እንደሆነ ብዬ ነዋ! » አለች ከረጅም ዝምታ በኋላ፥ ከሐሳብ ጉዞዋ በመመለስ።

«እና ዐወቅሁ አላወቅሁ ምን ፋይዳ አለው። እኔ ራሴ ያለሁት ጣጣ ውስጥ። የአህያ ባል ጅብ አያስጥልም ተብሏል » እንዳለ ትኩር ብላ ስትመለከተው፥ «ማለቴ ምሳሌነቱን ጠቀስኩት እንጂ፥ ባልና ሚስትነታችን ካበቃ ቆይቷል » ሲል እንገሩን ለማስተካከል ሞከረ።

«ለመሆኑ ምንን አልካት? » ስትል ታፈሱ ጠየቀችው፤ ጉዳዩን ጋብ አድርግው ጥብሱን ሲመጋገቡና ሲቀባበሉ ከቆዩ በኋላ።

«እንዳመቸኝ እመጣለሁ ነዋ! »

«እንዳመቸኝ ዘለዓለም ሊሆን ይችላል » አስተሳሰቡን ማወቅ ፈለገች።

«እና ሂድ ነው የምትዪኝ! » ስሜቷን ማወቅ ፈለገ።

ሁለቱም መልስ ሳይሰጣጡ ለአጭር ጊዜ አጥንት ሲጋግጡ ቆዩ።

«አልመለስሽልኝምኮ » ሲል በማባበል ጐንተል አደረጋት። ከእርሷ እንዲመጣላት ፈልጎ ነው እንጂ የማስረሻ አስተሳሰብ ቅርጽና ውሳኔ መያዝ ጀምሮ ነበር።

አሁን ወደ ዘለቃ ዘንድ የሚሄደው ከማጥ እንድታወጣው ለመለመን ወይም ስሜቷ እንደ ገፋፋት እጅ ለማስነሣት ስለ ጠራችው አይሆንም። የእርሷ ሕይወት በአደጋ ላይ ነው። የእርሱም ሕይወት በጭንቀት ላይ ነው። አልሰማች እንደሆነ ሂዶ ያስጠነቅቃታል። ማስጠንቀቂያ ደርሷት ለርዳታ ከፈለገችውም ሰንጢ እንኳ ሳይኖረው እንዴት እንደሚከላከልላት ለጊዜው ባይታየው፣ ህይ አጋጣሚ እንዲመጣ ያደረገው ዕድል በጭንቅ ጊዜዋ ከአጠገብዋ መገኘቱ

አደጋው የሚደናቀፍበትን አንድ ዓይነት መንገድ ይከፍትለታል። ከዚያ ብድር በምድር ነውና፣ እርሱም በበኩሉ፥ ችግሩን ነግሮ እንድትረዳው ይጠቻጣል። ልመና ሳይሆን የውለታ መመለስ ይሆናል። ነገሩ መልካም ፍጻሜ ከአገኘ በኋላ ለታፈሱ ይነግራታል። ከዚያም - ሐሳቡ ገና ቅርጽ አውጥቶ አልጨረሰምና - ብሎ ቆመ።

«የአንተ ውሳኔ ነው » ስትል ታፈሱ መለሰችለት፥ እሷም በበኩልዋ ጥቂት አስባ።

«የአንቺም ፈቃድ ነው። »

«ምን አግብቶኝ? »

«ነገሩን ያመጣሽው አንቺው ነሽ። ደግሞም ያገባሻ። »

«እንዴት? »

«አንቺ እንድሄድ ካልፈለገሽ እንዲያውም ‹ሂድ› ካላልሽኝ አልሄድም » ሲል ማስረሻ መለሰላት። የእርሷን ፈቃድ ለምን እንደ ፈለገ ራሱን በሚገባ አልተረዳውም። ግን፥ ያለ ፈቃድቃ ቢሄድ በእርሷ ላይ አንድ ዓይነት ክህደት የሚፈጽም መስሎ ተሰማው።

«ሂድ እንጂ » አለችው ታፈሱ ደከም ባለ ድምፅ።

«አብረን ነው የምንሄደው » አላት።

«ምን? ብለህ - ብለህ የእናንተ የትዝታ ሙሾ ሲወርድ ምስክርነት አቁመኝ! ይኸው ነው የቀረህ! » ሰውነቷ ትንሽ እንደ መወራጨት ቃጣው። ማስረሻ ባቀረበው ሐሳብ ግን ከልብዋ እምብዛም አልተከፋችም።‹ስለኔ ስሜት ቢኖረው ነው› ብላ አሰበች። በዚህ ላይ ደሞ ጉዳዩን ስትነግረው የሁናቴውን መለዋወጥ ማወቅ እንደ ፈለገች ሁሉ ከዘለእቃ ጋር እንደሚገናኝ የሚያድርበትን ስሜት መገንዘብ ትሻለች። ‹ለምን?› ለሚለው ጥያቄ መልሱን መተንተን አትችልም። በመልከም፤ በሀብትም በፖለቲካም የወደፊት ዕድልም የተሻሉ የሚመስሉ ብዙ ወንዶች ስታወቅ ድንገት ስለ ማስረሻ ልብዋን ለምን እንደ ሰነፈ ራስዋም በትክክል አይገባትም። የሚሰማት ሳይታወቃት ሕይወቷን ከሕይወቱ ጋር መቋጠር ነው። ስለዚህም እንድትከተለው ልብዋ ይገፋፋታል። ይሉኝታዋ ደግሞ ወደ ኋላ ይጐትታታል።

«የእርሷና የኔ ጉዳይ ያለቀ የደቀቀ መሆኑን አታምኝም ማለት ነው? ምንም የትዝታ ጠብታ የለበትም። አብረን እንድንሄድ የፈለግሁትም ይህንኑ ለማረጋገጥ ነው። »

«የምትለው እውነት ከሆነ ለማመን ከእርሷ ቤት ድረስ መሄድ የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም » አለች ታፈሱ እጅግም ባልከረረ አነጋገር።

«ያስፈልጋል። ካልሄድሽ እኔም አልሄድም። » ታፈሱ አብራው እንድትሄድ ማስረሻ የፈለገው ግን፥ ያለቀ የደቀቀ መሆኑን ለማሳወቅ ሳይሆን፥ ራሱን ጥንካሬ ስለ ተጠራጠረ ነበር። ዘለቃ ድንገት ከአንገቱ ላይ ብጠመጠምበት፤ ደረቱን ተደግፋ ብታለቅስበት ምን እንደሚሰማው እርግጠኛ አልሆነም። ታፈሱ ከአጠገቡ ተገኝታ ተጨማሪ ጥንካሬ እንድትሰጠው ፈለገ።

የደጋገሙት ቢራ ሞቅታ እየሰጣቸው፥ በጉዳዩ ረእም ላለ ጊዜ ተጨቃጨቁበት። ተከራከሩበት። በመጨረሻ አብራው ሂዳ ከውጭ አውቶሞቢል ውስጥ ሆና ልትጠብቀው ታፈሱ ተስማማች። «ለመሆኑ ሠፈራቸው የት ነው? ታውቀዋለህ? » ስትል በትዝብት መልክ ጠየቀችው። ዘለቃ ያመለከተችውን ነገራት። «ከዚያም አንዷት የቅርብ ዘመድ - አክስት አለችኝ - እግረ መንገዴን እጠይቃለሁ » አለች።

«እንዲህ ነው የኔ ሸጋ። ቀላሉ ነገር ከባድ መስሎ ታይቶሽ ነበር » ሲል ማስረሻ ትከሻዋን እቅፍ አድርጎ ወደርሱ አስጠጋት። ለድከመት ጥርጣሬ ከእርሷ ኃይል ለመሳብ።

## ፫

ማስረሻ ሌሊቱን ሲያስብበት እንደ ቆየ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሠፈር ደርሰው ግቢውን እንደ ተመለከተ ሐሳቡን ቀየረ። ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ትንሽ ፈቀቅ ብሎ አውቶሞቢሉን አቆመና «ከዚሁ ሆነን እንጠብቃለን » አላት ታፈሱን። ስላልገባት በአስተያየት ጠየቀችው። «እኒያ ግንድስ የሚያክሉ እናቷን አልፈግልም። ሌሎችም መሰሎቻቸውም ሊኖሩ ይችላሉ። »

«እና የምትፈልገው ብቻዋን ልትገናኛት ነው! » አለች ታፈሱ፣ ቅናት ቆንጠጥ ያደረገው በሚመስል አሽሙር።

አስተሳሰቧ ገባው። «አይደለም። እስክትወጣ ጠብቄ አንቺው እያየሽ አነጋግራታለሁ። ወይስ እኒያ ጋንዲያ እናቷ እስኪወጡ እጠብቃለን። አንቺ ሰውኮ አይደሉም » አለ በማዳነቅ።

ማስረሻና ታፈሱ በአውቶሞቢል ተቀምጠው የባጥ የቆጡን እያወጉ አሁንም - አሁንም የወይዘሮ ዘርፈሽዋልን ግቢ በዐይናቸው እየሰለሉ አንድ ሰዓት ያህል ጠበቁ። የወጣም የገባም ሰው የለም።

«እንደማየው ከሆነ ከዚህ ሙሉ ቀን ተቀምጠን ልንውል ነው። ስለዚህ አንተ እንዳልከው ነው። ስለዚህ አንተ እንዳልከው ጠብቅ፤ እኔ ደሞ አክስቴን ጠየቅ አድርጌ ልምጣ » ብላ ከአውቶሞቢሉ ወጣች።

ሁለቱም ያላስተዋሉት በሩቅ ሆኖ በዐይነ ሥጋ የሚመለከታቸው በዐይነ ልቦና የሚከታተላቸው መኖሩን ነው። ዘለቃን በዐይነ ቁራኛ እንዲጠብቁ ከድርጅት የተመደቡት ሁለት ወጣቶች ማስረሻ አውቶሞቢሉን ከአቆመ አንሥቶ በሩቅ ሲጠባበቁ ቆይተዋል። ታፈሱ ከአውቶሞቢል ስትወጣ እርስ በርሳቸው ተያዩና፤ «እሱ ማሳሳቻ ሆኖ ዋናዋ እሱዋ ሳትሆን አትቀርም » አለ አንደኛው። ከዚያም የምትገባበትን ለማየት ራቅ ብለው ተከተሉዋት።

ታፈሱ እንደ ተለየችው ትንሽ ቆይቶ ልዋጭ አዟሪዎች ወደ ሠፈሩ መጡ። አድነኛው እስከ ቅንድቡ ድረስ አሮጌ ጨርቅ ጠምጥሞ፣ በሳጠራ ቅርጫት ጓዙን በራሱ ተሸክሙላ። ሁለተኛው ዐይኑን ሳይቀር በኮፍያ ጋርዶ ዕቃውን በዘንቢል አንጠልጥሏል። - ልዋጭ ልዋጭ - ጫማ ያለው - በሳፋ በብርጭቆ፤ በሳህን - ልዋጭ አሮጌ ልብስ ያለው ልዋጭ ልዋጭ፤ ጥሩ ዕቃ አዲስ ዕቃ በአሮጌ ልዋጭ! - እያሉ በመቀባበል ይጮሃሉ።

ማስረሻ እንደ ዋዛ ተመለከታቸው። ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ሲደርሱ ቆም ብለው በመጋደም «ልዋጭ! ልዋጭ! ልዋጭ! » አሉ። አንዲት ልጅ በሩን ከፈተችና የተሸከሙትን ዕቃ በዐይንዋ ቃኘት አደረገችና «እስቲ ያላችሁን ዕቃ እንየው! » ስትል ጋበዘቻቸው። ተከታትለው ገቡ።

ወዲያው ሁለት ጥይት ተከታትሎ ሲተኮስ ማስረሻ ከሐሳቡ ብንን አለ። ከመኪናው ተስፈንጥሮ ወጣና ወደ ግቢው ተወረወረ። ሁለቱ ሰዎች፥ ከቤቱ በር ላይ ያስቀመጡትን ዕቃ በእግራቸው እየተራመሱ ሲወጡ ማስረሻ ከበረንዳው የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ሲደርስ ፊት ለፊት ተጋጠሙ። ራሱን በጨርቅ የጠመጠመው ደረበ መሆኑን መለየት አላቃተውም። ግን አንዳች ቃል ከአፉ

ከመውጣቱ በፊት፣ «ለካ አንተም የእነርሱ ነህና! » ሲለውና የሽጉጥ አፈ ሙዝ ሲደቀን አንድ ሆነ።

ዘለቃን በዐይነ ቁራኛ እንዲጠብቁ የተመደቡት ወጣቶች የመጀመሪያን ተኩስ እንደሰሙ ሽጉጣቸውን በእጃቸው እየጨበጡ ወደ ድምፁ አግጣጫ በሩጫ ሲመለሱ፥ ደረበና ጓደኛው እየተፋጠኑ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ሲወጡ አዩዋ ቸው። «ቁም! እጅ ወደ ላይ! » አለ አንዱ ለማረጋገጥ ያህል። ደረበ ግን ዞሮ እየተኰሰ ሩጫቸውን ቀጠሉ። እነሱም እየተኰሱ እነ ደረበን ተከተሏቸው። መሣሪያ የያዘው ደረበ ብቻ ነበር። ጓደኛው ነፍስ አውጭኝ ተፈተለከ። ደረበ ዞር አለና የሽጉጡን ቃታ ሳበ። ቀጭ! የሚል ድምፅ ብቻ ተሰማ። ያጐረሰውን ጥይት ጨርሶ ነበር። ዞሮ ሲሮጥ ታፋው የተነቀለ መስሎ ሲነዝር ተሰማው። ወደ ፊቱ ተደፋ።

ታፈሱ የመጀመሪያውን ተኩስ ስትሰማ ባለችበት ላንዳፍታ ድርቅ ብላ ከቀረች በኋላ ወዲያው ብድግ ብላ ካክስቷ ቤት ወጣች። እየሮጠች ስትመጣ ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ አጠገብ በርከት ያለ ሰው ሲተራመስ ነበር። ማስረሻ ከመኪናው ውስጥ አለ መኖሩን ላንዳአፍታ ተመልክታ ወደ ግቢው ሮጠች። ማስረሻ የአማቱን አዳራሽ እጅ የሚነሣ ይመስል ከበረንዳው ደረጃ ላይ ተደፍቷል። ከግንባሩ የሚፈሰው ደም በደረጃው ላይ ኩልል ብሎ ይወርዳል። እሪታዋን ለቀቀችው።

ወዲያው ትንሽ ዘግይተው ዘለቃን በዐይነ ቁራኛ ይጠብቁ የነበሩት ወጣቶች፥ የሆነውን ነገር በትክክል ለማረጋገጥ ለመመራመር በሌሎች የቀበሌ ሰዎች እርዳታ ደረበን ጅንባ ጅንበ አንጠልጥለው መጡ። ደረበ በሁለት ብብቱ ወደ ላይ ተንጠልጥሎ ደህናውና በደም የተዘፈቀው እግሩ አንዳንድ ጊዜ ይጐተታል። ሌላ ጊዜ ይንሳፈፋል።

«አሃሃሃ! » አለ ታፈሱን ከማስረሻ በድን አጠገብ ስታለቅስ ሲያያት። «አሃሃሃ! ጠርጥሬሃለሁ! ዐውቄሃለሁ! መጀመሪያ ዋናዋን የባንዳ አገናኝ መኰንን መቅጣት ነበረብኝ! አሁንም አይቀርልሽም! አሃሃሃ! »

ታፈሱን ቲአትር ቤት ገብታ እንደ ተለመደው ስያሽካካ ቧልታይ ትርእይት ወይም ደግሞ ቅዠት የምታይ መስሎ ተሰማትና በፊዝ እንደ መሣቅ ቃጣት። በመጨረሻም የማስረሻ ሬሣ ሲነሣ ለማስረገጥ ያህል ሁሉት እጅዋን ወደ እርሱ ዘርግታ «በእርሱ ተፈጥሮ ይህንን ማዕበል እንደማያልፈው ተሰምቶት ነበር። እኔም ዐውቄዋለሁ! መስሎኝ ነው እንጂ » አለች።

«አሃሃሃ! » ብሎ ደረበ መናገር ሲጀምር ወጣቱ በሽጉጥ ጥፊ አቋረጠው።

## ፬

ካሣሁን ደሴ ከተማ ሲደርስ ያጋጠመው ሁናቴ ከአሰበው የተለየ ነበር። ነጋሪት እየተጐሸመ ጥሩምባ እየተነፋ ሕዝቡ ለዘመቻ በሰለፍ ወጥቶ እየተመመ የደሴ ከተማ ተጨንቃ ተጠባ፥ የሚደርስ መስሎት ነበር። ግን አልነበረም። ከሸዋ በር ጀምሮ በሙጋድ በፒያሳ፥ በዓረብ ገንዳ ሠፈር ሰው የዕለት ሥራውን እንደ ተለመደው ያከናውናል። የበረንዳ ልብስ ሰፊው፥ የጉሊት መደቡ የእህል በረንዳው እንደ ሁሉ ጊዜው ተዘርግቷል። ቡና ቤቶች ሱቆች፥ ተከፍተው ደንበኛ ያስተናግዳሉ። ተንቀሳቃሽ ነጋዴ ተሸካሚ ተላላፊው በየመንገዱ ይተራመሳል። እያንዳንዱ ሰው ምናልባት ስለ ዘመቻው የሚያስብም ቢሆን ከፊቱ ላይ አይታወቅም። ‹አገር ተወርራ አገር ሰላም ይሆናል?› ካሣሁን ተገረመ። ግራ ገባውም ሰው መጠእይቅ ከጀለ። ግን በእርሱ ቀበሌ ውስጥ የደረሰውን ነገር ሲአይስታውስ፣ ‹ማን መሆኑ ይታወቃል? ማንስ ይታመናል?› የሚል ሐሳብ መጣበትና መልሶ ተወው። ቀስ ብሎ ለመጠያየቅ፥ ሰኞ ገበያ ወደ ምትኖረው የአክስቱ ልጅ ዘንድ ሄደ።

«ወይ! ካሡ ከየት አገር መጣህ? » አለችው በመደነቅ። ብዙ ጊዜ የማይጠያየቁ ቤተ ዘመዶች ናቸው። ባልዋን ፈትታ ደሴ ከተማ ገብታ ጠላ መሸታ ከጀመረች አንሥቶ እንደ አጋጣሚ ወይም ጠላዋን ለመጠጣት ካልሆነ በስተቀር ካሣሁንም ሆነ ሌሎቹ ዘመዶቿ ሆን ብለው፥ ጠይቀዋት አያውቁም። ካሣሁን ከዳገታማ በመሸሽ አዲስ አበባ ቆይቶ እንደ ገና ቆሬ ከተመለሰ ወዲህ ደጃፏን ሲረግጥ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነበር።

«ለመሆኑ በሕይወት እያላችሁ ነው? » አለች በቅሬታ መልክ። ከስንት ዓመታት በፊት ከባልዋ ጋር ተፋትታ፥ ደሴ ከተማ ገብታ ለአጭር ጊዜ በግርድና፥ በኋላ በመሻችነት፥ ስትኖር ዘመዶችዋ እምብዛም ጠይቀዋት ስለማያውቁ እንደ ታዘበቻቸው ነው። «ለነገሩማ ድሃን ማን ይጠጋዋል? » እያለች በሆድዋ ትታዘባቸዋለች። መሸታ ከጀመረች ጊዜ አንሥቶ አግኝታም አጥታም አታውቅም። የወስፋቷን ጩኸት አስታግሣ እርቃንዋን ሸፍና እንደ ምንም ኑሮን ትገፋለች።

ካሣሁን ያችን የማትለወጥ አኗኗርዋን በአርምሞ ተመለከተ። የሰኞ ገበያ ቤቶች ደረጃ አላቸው። የገበያውን መስክ ዙሪያውንና ወደ ገራዶ የሚያዘልቀውን ዋናውን መንገድ ይዞ ያሉት ቤቶች፥ የልብስ ሰፊዎች የእህል ባለ በረንዳዎች፥ የአልቤርጎ የሻይና፥ የቡና ቤቶች ናቸው። አልፎ አልፎ የታወቁት ጠጅ ቤቶች በዚሁ ረድፍ ይገኛሉ። መሥመር ሳይዙ እንደ ደረጃቸው ከጀመሪያዎቹ ዝቅ ያሉ ጠጅ ቤቶች መኖሪያ ቤቶች ሉካንዳ ቤቶች፥ ትኪ ምርኪ የሚሸጥባቸው ሱቅ ቢጤዎች ናቸው።

የካሣሁን ዘመድ ጠላ ቤት ከዚህ ሁሉ ጀርባ ናት። አንድዋ ክፍል ቤት ዱሮ ሲያውቃት ያዘመመች ነበረች። አሁንም እንዳዘመመች ናት። አትወድቅ፥ አትቀና፥ በጠባብዋ ክፍል ውስጥ የቤት ዕቃውና የቤቱ አቀማመጥ እንደ ዱሮው ነው። ከአንደኛው ግማሽ በኩል የእንጨት አልጋው፥ የጠላ መጥመቂያ እንስራው፥ ቁናው ሰፌዱ፥ የጠላ ማንቆርቆሪያው የምግብ ማቅረቢያው እርስ በርሱ ተደራርቦና ታጅቦ ይገኛል። ከዚሁ ሥር ምድጃው አለ። ሌላው ቁሳቁስ ሁሉ በዙሪያው ተከማችቷል። ከወንበሩ በኩል ሁለቱን ግድግዳ ጥግ ይዞ አንዱ ሰሌን ምንጣፍ ሌላው የበግ አጐዛ የተነጠፈባቸው ሁለት የእንግዳ መቀመጫ መደቦች አሉ። ባለቤቷ፥ እህል ስትለቅም ወይም መሸተኛ ደንበኛ ስትጠባበቅ የምትቀመጥበት በሰው ወዝ ያወለወለ የሚመስለው ደልዳላ የባሕር ድንጋይ አሁንም ከበሩ አፍ ላይ እንደ ተተከለ አለ። ሌላው ቀርቶ መሸተኛ ከውጭ ለመጥቀስ በእንጨት ላይ የተደፋችው ጣሳ ስንኳ፥ ያችው የወትሮዋ መሰለችው። የሰው ሕይወት የሰው፥ አኗኗር ይለወጣል። የዚች የዘመዱ ግን፥ ውሀ ስንኳ እንደማይቦረቡረው አለት ባለበት ቁሞ ደርቆ መቅረቱ ካሣሁንን አስገረመው።

«እንዲያው ይህችን ሠፈር ሙጥናን ብለሻት ቀረሽ? ምን አለ ወደ መንገድ ሠፈር ወጣ ብትይ ነፋሻነቱምኮ ይሻላል » አላት ሰላምታ፥ ከተሰጣጡ በኋላ ጠላ በብርጭቆ ስታቀርብለት።

« ‹የዴላው ገንፎ ያኻሃል› አለ ያገሬ ሰው። አዬ፥ የኔ ዘመዶች ነገር። ይልቅስ ነፍስሽ አለ ወይ ማለቱ አይሻልም ነበር? » ስትል በምፀት ጠየቀች።

ካሣሁን የማማረር ንግግር ከጀመረች እንደ ሐምሌ ዝናም እንደማታባራ ስለሚያውቅ ነገሩን ወዲያው ቀየረ። «ለመሆኑ ስለ ዘመቻው ምን ይወራል? የደሴ ሰው ግን ምንም ነገር እንደ ሌለ ነው ዝም ብሎ የሚንጋጋው » ሲል ስለ መጣበት ዋና ጉዳይ ጠየቃት።

«የምኑ ዘመቻ? »

«ሀገራችን ወራሪ ገብቷልና ተነሡ ተብሎ በራዲዮ የነገረው » አላት ካሣሁን።

«እኔ ምናውቄ ብለኸኝ። ከዚች ከጓዳዬ አልወጣ ይኸ ቴሌፎን የምትሉት አይገባኝ። ብቻ ጨረፍታ ጨረፍታውን ሰምቻለሁ። » ጥቂት እንደ ማሰብ ቃጣትና ወዲያው ለጠቅ አድርጋ «ግና ጐበዜ ደሞ የሚለው ሌላ ነው፤ እቴ! »

«ለመሆኑ ከጐበዜ ጋር ትጠያየቃላችሁ? አኗኗሩስ እንዴት ነው? » ካሣሁን ስለ ጐበዜ እንደገና ሲሰማ ያ ጥርጣሬው እንደገና ብልጭ ብሎበት በመደነቅ ጠየቀ።

«ደህና ነው። በአዲሱ መንግሥት ምረት ከገባ ቆይቷል፤ እንዲያውም የጐበዝ አለቃ ሁን ብለውት እምቢ ብሎ ነው ከእንናተ ከሥጋ ዘመዶቼስ የዚያ ቅዱስ ነው፤ የአይዋ ሙሔ ዘር ተሻለኝ። » ለሙሔ ሞት አዘኔታ ከንፈርዋን መጠጠች። «አልፎ አልፎ ከጓደኞቹ ጋር እየመጣ ይጠይቀኛል። እናንተ ዘንዳ መጥቶ ኢያቅም እንዴ! »

«እኔ አላገኘሁትም እንጂ እርሙን አንደዩ መጥቶ ነበር አሉ » ካሣሁን ራሱን ነቀነቀ።

«የአባቱ ሞት ቀየውን አስጠልቶ ይሆናላ? »

«ይሆናል » አለ ካሣሁን በሆዱ የሚያስበውን እያሰበ «ለመሆኑ እንዴት ይኖራል? የትስ ይኖራል? »

«የሚኖርበትንማ የት ዐውቄ። እንጃ ከጓደኞቹ ጋር እንደሆነ ከርሱ ጋር አብረው የሚሄዱት ጉደኞች አሉት። የሚሠራው ግን ከድርቅ ርዳታ መሰለኝ። መቸም ከዚህ ከሰነበትክ ትገናኙ ይሆናል። »

«አዎ መገናኘታችንስ የማይቀር ነው » አለ ካሣሁን።

ካሣሁን ለመዝመትም ሆነ ጐበዜን ለማግኘጥ እንደተጣደፈው ያህል በቶሎ አልቀናውም። ልክ በሙሔ ላይ እንደደረሰበት ሁሉ «እኔማ አመጣጤ ላገሬ ለመዝመት ነው! » እያለ በየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ሲጠይቅ አንዳንዱ እንደ ጅል እንደ ወፈፌ ይመለከተዋል። ሌላዉ ‹መመሪያ አልመጣልንም። ወደ ሠፈርህ ተመለስ እስክትጠራ ጠብቅ› ይለዋል። አንድ ሁለት መሥሪያ ቤቶች ደግሞ ስሙን መዝግበው ስለ ፈቃደኛነቱ አመስግነው ሸኙት። «እና መቸ

ልምጣ? » ለሚለው ጥያቄ ግን መልስ አልሰጡትም። በመጨረሻ ሂዶ ማመልከት ያለበት በራሱ ወረዳ መሆኑን አንድ ሰው ነገረው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ጐበዜን ከመፈለግ አልቦዘነም ነበር። በእርዳታ ማስተባበሪያ የወሎ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ዕይተመላለሰ ጠየቀ። ከዚያ እንደሚሠራ ተነገረው። ግን እርዳታ ከሚያጓጉዙ ካሚዎኖች ጋር እንደ ዘበኛ ሆኖ ስለሚዘዋወር ሊያገኘው አልቻለም። ከወረዳ አስተዳደሩ ተመዝግቦ ቤቱም ሳይደርስ ወደ ደሴ በመመለስ ጐበዜን ፍለጋ ቀጠለ። ጐበዜ ስለ ደርግና ስለ እናት አገር ጥሪው ያለውን አስተያየት የአክስቱ ልጅ ከነገረችው ወዲህ ጥርጣሬው አይሎበት ነበር።

ለንስቅ የያዛት ገንዘብ ጨርሳ ከመሚጠጧ በፊት በፒያሳ፥ በአረብ ገንዳ በሸዋ፥ በር በረንዳ በቅዳሜ ገበያ፥ በሰኞ ገበያ እየተዘዋወረ «ሻለቃ - ሻለቃ! » ተብሎ ሲጠራ በማቅረብ ለቀን ጉርሱ የምትበቃውን ከአገኘ በኋላ ወደ እርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት እየሄደ ብዙ ቀን ሲጠብቅ አንድ ቀን አጋጠመው። ያለ በቂ ምክንያት የግቢውን በር አዘውትሮ ለማለፍ ዘበኞች ስለማይፈቅዱለት፥ በዐይኑ እየሰለለ የሚጠባበቅ ከውጭ ሆኖ ነበር። ለዚሁም «ከዚህ ምን ትሠራለህ አንተ ሰው? » እያሉ ሊያባርሩት ይሞክራሉ። «ኧረ ወንድሜ እዚህ ነው የሚሠራ። ታዲያ ብዙ ጊዜ ወደ ውጭ ይሄዳል ስለ ተባለ እሱን ለማግኘት ነው » እያለ ሲለምን አይተውታል። አንድ ቀን በዚህ ዓይነት ከግቢው ውጭ ቆሞ ሲያስተውል አንድ ካሚዎን ገባና ተሳፋሪዎቹ መውረድ ጀመሩ። ፊቱን አላየውም። ግን ጐበዜ እንደ ሆነ ተሰማው። እየሮጠ በሩን ለመግባት ሲል ዘበኛው አገደው። «ያው ወንድሜን ለመገናኘት ነው » አለ። የተናገረው ጮህ ብሎ ስለ ነበር እንደ ሊሎቹ የሰማው ጐበዜ ድምፁን የለየ ይመስል ላመል ያህል ገልመጥ አለና መንገዱን ቀጠለ። «ማነው ወንድምህ » ሲል ዘበኛው ጠየቀው በጠመንጃ አፈ ሙዝ እንዳገደው።

«ያው - ያው! » ካሣሁን በጣቱ አመለከተና ሆን ብሎ «ጐበዜ! ጐበዜ! ጐበዜ! » ሲል ተጣራ።

ከአጠገቡ ላሉት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ድምፁ በግቢው ሙሉ ስላስተጋባ ጐበዜ እንዳልሰማ ለመምሰል አልቻለም። ስሙ ስለ ተጠራ እንደ ዋዛ በመገረም አኳኋን ዘወር አለ። ጐበዜ እንዳላዬ፣ እንዳልሰማ ለመምሰል መሞከሩን ካሣሁን ተገነዘበ። ጥርጣሬው የባሰ እየለበትና በበኩሉ ብልጥነት ተሰማው። «ጐበዜ ምን ነካህ? እኔ ካሣሁን ነኝ እኮ » አለ አሁንም ድምፁን ከፍ እንዳደረገ። ጐበዜ በዚያ

ታዛቢ ሁሉ መካከል እንደ መንጠቅ ወደ ያዘው ጥሪ መዞር ግድ ሆነበት። በመጀመሪያ ግራ እንደ ተጋባ ሰው ዐይንቹን አጨንቁሮ እየተለመለከተ በዝግታ ከተራመደ በኋላ «ኧረ! ኧረ! ካሤ ካሤ! » ሲል ተንደረደረ። ትከሻ ለትከሻ ተያይዘው ተሳሳሙ።

በጉበዜ መሪነት በአቅራቢያው ወደ ምትገኝ አንድ ሻይ ቤት ገብተው እንደ ተቀመጡ፥ በካሣሁን ወትዋችነትና ጥይይቅ ጭውውታቸውን ቀጠሉ። «ለመሆኑ ጤና ነህ? እኛም በጭምጭምታ ስንሰማ ቆይተን ቆሬ መምጣትህን ዘይኔ እስክትነግረኝ ድረስ በሕየት ተርፈህ በደህና መግባትህንስ በውል አላወቅሁም ነበር። ለመሆኑ እንዴት ሁነህ ኖርከው ወንድሜ? »

ጉበዜ በበረሃ የሽፍታ አለቃ እየቀያየረ እንደ ቆየ ከዚያም ራሱ የሽፍታ አለቃ እንደ ሆነ፤ በኋላም የደርግ መንግሥት ባወጣው የምሕረት ዐዋጅ እንዴት እንደ ገባ ባጭሩ ተረከለት።

«ታዲያ የጉበዝ እልቅናውን ለምን ጠላኸው? ከዚህ ከአሁኑ ሥራህ ይሻል ነበር መሰለኝ » ሲል ከሣሁን ጠየቀ።

ጉበዜ ለመመለስ የታከተ ይመስል፥ በአንድ እጁ የሻይ ብርጭቆውን ይዞ ፉት እያለ፥ በሌላ እጁ ጸጉሩን አካከከ፤

«ከዚህ ሁሉ ጣጣ ምን አገባኝ? ደም መቃባት አያስፈልግም። ለዚህ መንግሥት ጠበቃ ሆኖ አባባም ሳይቸግረው በከንቱ ነው የሞተው። በመሞቱ አዝኛለሁ። በአሟሟቱም አዝኘበታለሁ። »

ካሣሁን፥ በጉበዜ አነጋገር ቢገረምም እንዲታወቅበት አላደረገም። ላንዳፍታ ያህል ዝብ ብሎ በትዝብት ተመለከተው። ጉበዜ ሳይወድ ዐይኑን ሰበር አደረገ። «ለመሆኑ ዘይኔ እንደ ምን ሰንብታለች? » ሲል ጠየቀ።

«አዬ ጉበዜ! የእናት አባት ልጅ ወንድምኮ ነህ። አገር ከገባህ ስንት ጊዜ ሲሆንህ አሁን ሰሞኑን ነው አንድ ቀን ብቅ ብለህ አይተሃት፥ ሳታጫውታት የተመለስከው። » አነጋገሩን ሆን ብሎ ከወቀሳ ይልቅ ወደ አሽሙር አዘነበለው።

«ሥራዬ አላደርስኝ እያለ ነዋ! » ሲል ጉበዜ ፍርጥም አርጎ ተናገረ።

«የአባታችሁን እርም አብራችሁ ለማውጣት ስንኳ? » ሲል ካሣሁን በመገረም አኳኋን ጠየቀ። «እኔም ብሆን ተቀይሜሃለሁ። ታሥሬ አልጠየቅኸኝም። »

«መቸስ ምን ይደረግ! አብረን እርም አወጣን አላወጣን እንግዲህ አይመለስ! የአንተን መታሠር እንኳ ዘይኔ ነች የነገረችኝ። ጊዜ አጣሁ።

ካሣሁን ለአስተያየቱ መልስ መስጠት ከጀለና ማወቅ የሚፈልገውን እስኪያውቅ ድረስ አለስልሶ መያዙ የተሻለ ስለ መሰለው መልሶ ተወው። ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ሻያቸውን ፉት እያሉ ቆዩ።

«ለመሆኑ ደሴ ምን እግር ጣለህ? » ሲል ጒበዜ ጠየቀው።

«ለመዝመት ብዬ ነበራ! ራዲዮው ተናገረ እንጂ ከዚህ ሰው ብዙም የሚያውቀው አልመሰለም። »

ጒበዜ በፌዝ እንደ መሣቅ ቃጣው፤ «አንተም የእኛ አባት አዚም ይዞሃል ማለት ነው። ወደ ሞት የሚጠራ! »

«ሲሞት የተናገረውን ብትሰማ ኖሮ እንዲህ አትልም ነበር። »

«ሰምቻለሁ! »

ካሣሁን በጥያቄ አስተያእይት ተመለከተው።

«አዎ! ዘይኔ ሁሉንም ነግራኛለች » አለ ጒበዜ በሁሉም የተከፋ ይመስል በቅሬታ አኳኋን። በጒበዜ አነጋገር ካሣሁን እርሱን ፍለጋ፥ የመጣበትን መርማሪው ፖሊስ የነገረውን የውሻ ንክሻና የጨርቅ ቅዳጅ በማስታወስ ሱሪውን ተመለከተ። ጒበዜ የታጠቀው ሱሪ ሽሮማ ቀለም ቦላሌ ነበር። ግን ይህ ምንም ነገር አያረጋግጥም። የመንግሥት ሠራተኛ ከሆነና ደሞዝ ካለው ከአንድ የበለጠ ሱሪ ሊኖረው ይችላል። ውቃቢ የነገርወ ይመስል ድንገት ከባድ ጥርጣሬ ላይ ወድቋል። በከበደ ውሻ የተቦጨቀውን ሱሪና የተነከሰውን ታፋ፥ ሰው ማን እንደሆነ እስካላረጋጠ ድረስ፤ እንደበሰበሰ ጥርስ መላ ሰውነቱን ከሚሰቀስቀው ሠቀቀን እንደማይገላገል ያውቀዋል። ይችን እውነት ለማግኘት፤ ያች ሱሪ አለች ብሎ ከሚጠረጥረው ሥፍራ ሥርቆት እስከ መሄድ ድረስ ደስ የማይለውን ብዙ ነገር ከማድርግ እንደማይመለስ ተሰማው።

ጒበዜ ራሱ መንገዱን ከፈተለት። «ከመሥሪያ ቤቱ እየተመላለስክ እኔን መጠየቅህን ስለ ነገሩኝ ከመጣህ ሰንብተሃል ማለት ነው። ለመሆኑ የት አረፍክ? ሰኞ ገበያ ከአክስትህ ልጅ ዘንዳ? » ሲል ጠየቀው፣ ባንድ በኩል ከአምቻ፣ የሥጋ ዝምድና እንደሚስብ በሥጋት እርሱም ጥርጣሬ እያደረበት።

«አሄሄሄ ጒበዜ ዕርሷ ማንን ታስጠጋለች ብለህ? አልፈርድባትም። ጒጆዋ ገብቶ ለሚቆምና ለሚቀመጥ አትበቃም። እኔ የማድረው እንደዚያ እንደ ለማኙ በየመንገዱ ዳር አጥሩን ይዤ ከውሻ - ከውሻ ጋር » የመጨረሻውን ቃል ሆን ብሎ ረገጥ አደረገውና፥ «ስጣላ » ነው። እና፥ አሁን ካሣሁን በማባበል ዓይነት ለዘብ ረጋ አደረገው። «አንተን አፈላልጌም ለጊዜው እንድታስጠጋኝ ብዬ ነበር። ሥጋስ ሆነ ምንስ ሆነ ከአንተ ማን ይቀርበኛል። »

ጒበዜ ፊቱን በሁለት መዳፉ ላይ አስደግፎ እያሰበ ተመለከተው። ያሰበም፥ የተጨነቀም መስለ። «እሱማ ነው። ግን እኔም ከሰው ተጠግቸ ነው ያለሁት። ሰው ማስቸገር ይሆንብኛል። »

«ላንተ ከተቸገሩ፥ ለእኔም ለወንድምህ አብረው ይቸገሩ። ያው ነው » አለ ካሣሁን ቀበል አድርጐ።

ጒበዜ ከንፈሩን ምጥጥ አድርጐ «ኧረ እንዲያው የሚሆን አይመስለኝም ካሡ » ሲል በለዘብታ መለሰለት። ሁለቱም ሻያቸውን ፉት እያሉ፥ በታከተ ፈገግታ እየተያዩ በየልባቸውም እየተፈታተኑ ዝም ብለው ቆዩ። ካሣሁን ዱሮ በአዲስ አበባ በቅርቡም በቆሬ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ እሥር ቤት በቆየበት ጊዜ ከማስፈራራትና ከመመርመር ሌላ በማባበል፥ በማስተዛዘን ነገር እንዴት እንደሚወጣጣ በመጠኑ ቀስሞ ነበርና እንደ መሰለው ሞከረ። «እንደምታውቀው በደሴ ቀርቶ በድፍን ወሎ ከአንተ የሚቀርብ ወንድም የለኝ። እምቢ፥ አላስጠጋህም ካልከኝማ፥ መቸስ ዓረብ ገንዳ ጥግ ይዤ ማደር አያቅተኝ » ሲል እንደ መነሣት ቃጣው። የካሣሁን ዘዴ ቀላል ነበር። ጒበዜ ከሚኖርበት ቤት እንዳይደርስ ከፈለገ እንዳይታወቅበት የሚፈልገው ነገር አለ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ካሣሁን ለሚጠራጠረው ነገር ተጨማሪ መጠራጠሪያ ነው። ከዚህ የሚቀጥለው ጥርጣሬውን የሚያደርግበት ማስረጃ በምንም መንገድ ማግኘት ይሆናል።

የጒበዜም ጭንቅላት ሥራ አልፈታም። ካሥሁን መጠጊያ የፈለገው የደርግ፣ ደጋፊ ነውና የተላከው እርሱን እንዲሰልል ከሆነ እምቢ ቢለው ጥርጣሬውን ለማጠናከር ይረዳዋል። የሚረዳው መመጠራጠሩን ምንም እንደማያውቅ መስሎ፥ መልሶ መከታተሉ ነው። ማን ያውቃል? አስተሳሰቡንም እንዲቀይር ማድረግ ይቻል ይሆናል። የካሣሁንን አመጣጥ ከከበደ ግድያ ጋር ግን ፈጽሞ አላገናዘበውም። «መቸስ ሌላ መጠጊያ ከሌለህማ እስቲ ባልተቤትዋን ልለምናቸው! » አለው።

ጐበዜ የሚኖረው በማመዶ ሠፈር፥ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ሲወረስ ባላቸው በልብ ድካም ከሞቱባቸው ሴት ቅጥር ግቢ ከአንዷት ማድ ቤት ውስጥ ነው። በጥገኝነት ሳይሆን ከዐዋጅ በፊትም ትከራ ስለ ነበር፥ ከሌሎች ሁለት የፖለቲካ ጓደኞቹ ጋር ተከራይቶት ነበር። ካሣሁንን ከማስገባቱ በፊት ለጥንቃቄ ያህል ጓደኞቹ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወሩ ማድረግ ነበረበት።

ካሣሁን ልቡ እንደ ተሠቀለበት የሚፈልገውን ማረጋገጫ በቀላሉ ሊያገኝ አልቻለም። ማግኘት የሚፈልገው ሁለት ነገሮች ብቻ ነበር። አንድ ቀዳዳ ያለበት ቁምጣና የታፋ ላይ ጠባሳ። አንድ የእንጨት ሣጥን አለ። የልብሱ ማስቀመጫ መሆኑን ዐውቋል። ግን ውስጡን ለመመርመር ዕድል አጣ። ካሣሁን በደሴ አደባባይ ነገር በሆዱ እየበላ ለመንገዋለል ጐበዜ ወደ ሥራው ለመግባት ጧት ክፍሏን ከውጭ ዘግተው የሚወጡት አብረው ነው፡ ምሽት ጐበዜ ቀድሞ ከመጣ ከፍቶ ይቆየዋል። ካሣሁን ከቀደመ ከውጭ ይጠብቀዋል። ጐበዜ ወደ ጓሮ ሲወጣ ካሣሁን ብቻውን ከክፍል የሚቆይበት ጊዘ ቢኖርም ሣጥኑ ሁልጊዜ በጓጉንቸር ቁልፍ እንደ ተቆለፈ ነው። መክፈቻውም ከጐበዜ አይለይም። ካሣሁን በጣም ከመብሸቁ የተነሣ ጠብ ፈጥሮ የጐበዜን ሱሪ ከላዩ ላይ በመቅደድ ጠባሳውን ለማየት ወይም በጉልበት ሣጥኑን አስከፍቶ ውስጡን ለመፈተሽ የቃጣበት ጊዜ ነበር። ግን በድንገት አደጋ ካልጣለበት በስተቀር በቀላሉ እንደማይወጣው ያውቃል። ዱሮ፣ ትግልና ድብድብ ሲገጥሙ አዘውትሮ የሚያሸንፍ ጐበዜ ነበር። ዱሮ ደልዳላ ሙሉ የነበረው አካላቱ በበረሃው ኑሮ ሊሆን ይችላል አሁን ደግሞ ተለብልቦ እንደወጣለት የክትክታ ዱላ ስብስብ ፍርጥም ጥጥር ብሎ የበለጠ ጥንካሬ ያለው ያስመስለዋል። ከዚህም በቀር ጥርጣሬው በከንቱ ሆኖ የተገኘ እንደ ሆነ ትፉ ትዝብትና አጉል ቂም በቀል ማትረፍ ብቻ መሆኑ ተሰማው። ይህን ደግሞ አልፈለገውም። በዚህ ዓይነት እስቲ የዛሬውን እስቲ የንገን እያለ ሲያመነታ ሲጨነቅ ብዙ ቀኖች አለፉ።

በመኻሉ በአጋጣሚ አንድ ሐሳብ መጣለት። አንድ ቀን ሽቀላ ፍለጋ በአረብ ገንዳ ሲዘዋወር አንድ ሰው በድምፅ ማጉያ ነዋሪውን ሕዝብ ሲለፍፍ ሰማና፥ ሰው ዘመቻው ጥሪ መስሎት ለማዳመጥ ቀረብ አለ። ልፈፋው ግን ስለ ውሾች አያያዝ ከደሴ ማዘጋጃ ቤት የተሰጠ ምክር ነበር። «በደሴ ከተማ አልፎ - አልፎ የውሻ በሽታ መግባቱ ታውቋል። እንደሚታወቀው የውሻ በሽታ በሰው ላይ እጅግ አሠቃቂ ጉዳት የሚያደርስ ስለሆነ ውሾቻችሁን እንድታስከትቡና፣ ከግቢያችሁ እያሠራችሁ እንድትጠብቁ፥ በሽታው የለከፈው ውሻ ስታገኙም

ወዲያውኑ እንድስታውቁ » ብሎ ሰውዬው ሲናገር ካሣሁን ሐሳቡ ምን ጊዜም ከውሻ ንክሻ ላይ እንዳተኰረ ነበርና ድንገት አንድ ሐሳብ ብልጭ አለለት።

የራሱ ውሻ ጒበዜን የነከሰውና በኋላም የጠፋው ምናልባት ታሞ እንደ ሆነስ ወንጀልና ወንጀለኛ ሲያሰላስል ይህንን ጉዳይ አዙሮ አለ ማየቱ ለጊዜው ጸጸት አሳደረበት። ግን አሁን ምንም ማድረግ እንደማይችል ታወቀው። ጒበዜ ቆሬ መጥጦ ከተመለሰ አንድ ወር ገደማ ሆኖታል። በበሽታው ተለክፎ ከሆነም ሦስት ሳንምት አልፎታልና አገር እንደሚያውቀው መድኃኒቱ አይሠራለትም። ‹አይ እንግዲህ እርሱ ያለው እርሱ የወሰነው ነው የሚሆነው› ሲል በሐሳቡ ራሱን አባበለ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ጒበዜ በሥራ ምክንያት ወደ ተንታ ሄደ። ካሣሁን ዐይንና ልቡ አትኩሮበት የሰነበተውን ያንን ሣጥን አሁን ብቻ ለብቻ ቢያገኘውም ጓጉንቸር ቁልፉ፥ ቢሰበው ቢጠመዝዘው በምስማር ቢጐረጉረው፥ ፍንክች የማይል ሆነበት። ከግቢዋ ሴትዮ ሞረድ ለምኖ ግማሽ ቀን ያህል ገዝግዞ እንደ ምንም ሰበረው። ከዚያም፤ ራሱን መልሶ እስኪታዘብ ድረስ እጁ በጉጉት እየተንቀጠቀጠበት ፍተሻውን ቀጠለ። እንደ ተሸፈነ ጽላት እንደዚያ በቃላቅ አንክሮ ይመለከተው በነበረው ሣጥን ውስጥ እስከዚህም የሚያስደንቅ ልዩ ነገር አላገኘም። በመጀመሪያ በደፈናው በሁለት እጁ ገልበጥበጥ አደረገውና ጨርቆቹን አንድ በአንድ እየነቀሰ ምርመራውን ቀጠለ። መርማሪው ፖሊሱ እንደ ነገረው በውሻው ንክሻ የተቀደደው ብጫቂ የቁምጣ ሱሪ ቢሆንም፣ ኮቱንና ሸሚዙንም እጀ ጠባቡንም በጥንቃቄ ማስተዋሉ አልቀረም። ጨርቆቹ በአብዛኛው ብዙ ቀዳዳ ያለባቸው የተጣፉ ስለ ነበሩ ምናልባት ስለሚያገኘው መረጃ እርግጠኛነት ጥርጣሪ አደረበት። ግን ፍለጋውን ቀጠለ።

በመጨረሻ ከታፋው ላይ የተጣፈ ቁምጣ ሱሪ አገኘ። የጨርቁ ዘር ለማስረጃ ከያዛት ብጫቂ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ግን በርጥበትም በእድፍም ቀለሙ ለየት ብላኡል። በዚህ ላይ ደረቱ በጣም ሰፊ ስለሆነ ውሻው ንክሻ ይሁን በሌላ ምንም ግምት ባያደርግም ለጥርጣሬው በቂ ማስረጃ እንዳገኘ ተሰማው። አብሮም የከበደ አሟሟት በሐሳቡ ታየውና ንዴት ድንገት ውርር አደረገው። ጒበዜን ተጠያቂ የሚያደርግበት የወንጀል ክብደት ታሰበውና፣ ‹ጒበዜ ምን መጥፎ ዕፅ ቢቀምስ ነው እንደዚህ አረመኔ ሊሆን የሚችለው?› ሲል ለስንተኛ ጊዜ ራሱን በመጠየቅ ስላገኘው ማስረጃ ትንሽ ጥርጣሬ ገባው። አዳኝ መቃረቡን በስሜቱ እንደሚያውቅ አውሬ፣ ካሣሁንም ጥርጣሬው ትክክለኛ መሆኑን ስሜቱ ይነገረዋል። አእምሮው ደግሞ ሌላ ጥርጣሬ ይጠቁመዋል። ማስረጃው ልክ

ይመስላል። ግን የሱሪው ጨርቅ ተመሳሳይ መሆንና ከታፋ ላይ መቀደዱ አጋጣሚ ቢሆንስ? ፍጹም እርግጠኛ መሆን የሚችለው ተጨማሪ ማስረጃ ሲያገኝ ብቻ ነው። ‹ፍጹም እርግጠኛ ባልሆንም አሁን ለጥርጣሬዬ በቂ ማስረጃ ስለለኝ አፍ አውጥቼ እጠይቀዋለሁ። ከካደኝም ታፋህን አሳየኝ እለዋለሁ፤ እብሚ ካለም ያው ነው ይዋጣልናል› ሲል ወሰነ።

## ፳

ካሣሁን የፈራው በጉልበት የመዋጣቱ ጉዳይ አስፈላጊ አልሆነም።

ጉበዜ ካለወትሮው በጣም ጠውልጐና ፈዞ ከቀትር ላይ ከሄደበት ተመለሰ። እንደ ገባ ከአልጋው ላይ ዝልፍልፍ ብሎ ተቀመጠና፥ ጫማውን በእግሩ እርስ በርሱ እየፈለቀቀ አወለቀው። ከዚያም አልጋው ከተጠጋበት ግድግዳ ላይ ደገፍ ብሎ በመዳፉ ፊቱን ያሻሽ ጀመር።

ካሣሁን ከአጠገቡ ቁሞ በጥሞና ከአስተዋለው በኋላ፤ «ምን ሆነሃል ጉበዜ? » ሲል ጠየቀው።

«እኔ እንጃ » አለ ጉበዜ በመታከት አኳኋን ትከሻውን ነቅነቅ አድርጐ «መላ አካላቴን ጤና አይሰማኝም። »

ካሣሁን ሥጋት ቆንጠጥ አደረገው። ኀዘኔታም ተሰማው። አንድ እጁን ከጉበዜ ትከሻ ላይ ጣል አደረገና ትኩሳት እንዳለው ለማወቅ በሌላ እጁ ግንባሩን ዳበሰ። የጉበዜ ሰውነት በረድ ያለ ነው። ካሣሁን መልሶ ተረጋጋ። መታመሙ ግን በግልጽ ያስታውቅ ነበር። ዐይኖቹ ወደ ውስጥ ተሰርጉደው ገብተዋል። አተነፋፈሱ ልክ አይደለም። እንቅልፍ እንደ ያዘው ሰው አሁንም አሁንም ስልምልም ይላል። ካሣሁን ሰሞኑን በሐሳብ እንደ ወሰነው እርግጡን ማወቅ እንዳለበት ቢሰማውም ዝም ብሎ ሲያመነታ ቆየ። ከፊት ለፊቱ ተቀምጦ በሣር ወለሉን እየጫረ ለረዥም ጊዜ ከአስተዋለው በኋላ፤ «አንድ ነገር ብጠይቅህ እውነቱን ትነግረኛለህ? » ሲል በመጨረሻ ጠየቀ።

«ምን? » ጉበዜ ከአልጋው ላይ እንደ ተጋደመ የደከመ ድምፅ አወጣ።

ካሣሁን ጥያቄውን እንዴት እንደሚጀምር አሁንም ጥቂት አመናታ። «አንተ ኢሃፓ የሚባለው የደርግ ጠላት ነህ፥ አይዴል? »

ጐበዜ ከተጋደመበት ትንሽ ቀና አለ። «ምን ጥፋት አለበት? »

«ደግ አላደረከም » አለ ካሣሁን።

ጐበዜ መልስ አስልሰጠውም።

«አይዋ ከበደ መሞቱን ሰምተሃል አይዴል? »

«ነፍሱን ይማረው » አለ ጐበዜ ይበልጥ እየደከመና እየታከተ በሄደ ድምፅ።

ካሣሁን ዐይኑን በጐበዜ ላይ እንደ ተከለ አሰላሰለ። ጐበዜ የሱሪውን አንድ እግር ወደ ላይ እንፎ የሕመሙን ምንጭ ያገኘው ይመስል ቅርፊቱ ጨርሶ ያልተነሣ ከባቱ ላይ ያለውን ጠባሳ ያሻሽ ጀመር። ሁለተኛ ጊዜ የተነከሰው መሆን አለበት ሲል ካሣሁን አሰበና ምርምሩን ለማወዛዛት ያህል «ምን አግኝቶህ ነው? » ሲል ጠየቀው።

«ውሻ ነከሶኝ » የትና የማን ውሻ እንደ ሆነ አልተናገረም።

«ምነው የውሻ እላት አብዛብህ? » አለ ካሣሁን ድንገት ሳይታወቀው። ጐበዜ ግን ያልሰማ መሰለ።

ሁለቱም ረዘም ላለ ጊዜ ሳይነጋገሩ ቆዩ። አጠገብ ላጠገብ ናቸው። ግን በሐሳብ፥ በስሜት እንደ ሰማይና ምድር ተራርቀዋል። አብረው አድገው፥ እንደ ወንድማማች የሆኑበት ጊዜ ነበር። ያም ቢቀር አማችና ምራት ናቸው። አሁን ግን እንደማይተዋወቁ ባዳዎች ሆነዋል። ይህ የቅርበት መራራቅ ይህ የአብሮ አደግ ባዕድነት ሁለቱንም ተሰማቸው።

ስሜቱን በመጀመሪያ የገለጸው ጐበዜ ነበር። ከተጋደመበት ትንሽ ቀና በማለት በሥቃይ ላይ ፈገግታ ለማሳየት ሞከረ። «እስቲ ቦለቲካውን ለጊዜው እንተወውና ስለ ዱሮው እንጨዋወት። ጨዋታ ሕመምንም ነገርንም፥ ያስረዳል ይባላል ልጅነት ተመልሶ አይመጣም የሚባለው እኮ እውነት ነው። ትዝ ይልሃል የዳገታማ ፍጅት? » ጐበዜ መከንፈሩን መጥጦ ራሱን እንደ መነቅነቅ አደረገ። «እኔማ ሞተህ መስሎኝ ነበር። ለመሆኑ እንዴት አመለጥክና በአዲስ አበባ ዙረህ መጣህ? »

ከጐበዜ ሕመም ይልቅ የጠባዩ ድንገት መለወጥ ካሣሁን አሳሰበው። ከጥቂት ቀናት በፊት የሚያውቀው ጐበዜ ከልጅነት ጠባዩ ኮስተርተር ያለ ሊቀርቡት ሲፈልጉ የሚርቅ እንደ ዱሮው ሊያቁት ሲሞከሩ፣ የሚደበቅ ዓይነት ነበር። አሁን ደግሞ የጥንት ቅርበታቸውን እንደ ገና ለመመለስ የሚሻ ሌላ ሰው

ሆነ። ካሣሁን በመገረም ሲመለከተው ፊቱ ሳይቀር የልጅነቱ መሰለው። ጐበዜን ፍለጋ የመጣበትን ዋና ጉዳይ ለጊዜው ረሳውና ሳይታወቀው ከፈርሳታው እልቂት ጀምሮ የደረሰበትን ሁሉ በዝርዝር ይተርክለት ገባ።

ካሣሁን በአተራረኩ ተመስጦ ስለ ነበር የጐበዜን ሁኔታ መለወጥ በመጀመሪያ አላስተዋለም ነበር። «በጣም አመመህ እንዴ? » ሲል ጠየቀ። ከሥቃይ የተነሣ ፊቱን አጨፍጐ ጥርሱን አግጥጦ በሁለት እጁ እራሱን ይዞ ሲያየው፡

«ራሴ ራሴ፣ ሥፍር ቁጥር በሌለው መርፌ የሚጠቀጠቅ ይመስለኛል » ሲል በማቃሰት መለሰለት።

ካሣሁን ጥርጣሬ ብቻ ሳይሆን ሥጋት ጭንቀት፥ ፍራቻም ጭምር ተሰማው። ጐበዜ በእርግጥ በጣም ታሟል። በሽታው ያው ከሆነ በሀገር ሲነገር፥ የሰማው አንድ የማወቂያ ምልክት አለ። «አይዞህ የጉዞው ድካም ሊሆን ይችላል። ትሬንታ ኳትሮ እኮ ሲያንገጫግጭ ከእግር ጉዞ የበለጠ ነው ሰውነት የሚያወላልቀው። እና እግርህንም፣ ራስክንም ብትተጣጠብ ይቀልሃል፤ ውሀ ላምጣልህ? » ሲል ጠየቀው በክፍሉ ውስጥ ከሚገኙት ጥቂት የቤት ዕቃዎች አንዱ የሆነውን ሳፋ እያነሣ።

ጐበዜ በአሉታ ራሱን አወዛወዘ።

«እኔም እግሬን ብለቃለቅ አልጠላም » አለና ካሣሁን በሳፋው ውሀ ሞልቶ ተመለሰ። ጐበዜ ፊቱን ዘወር አደረገ። ውሀውን ለማየት አለ መፈለጉ ያስታውቅ ነበር። ካሣሁን ውሀውን እያንቦጫረቀ መታጠብ እንደ ቀጠለ «ውጣ ከዚህ » ሲል ጐበዜ በሚያቃስት ድምፅ ጮኸበት። ካሣሁን ከነሳፍው ተንደርድሮ ወጣ።

ካሣሁን ከጐበዜ በአንድ ክፍል መቆየቱ እጅግ ቀፈፈውና «እስቲ ትንሽ የሚሸቀል ነገር ባገኝ » በሚል ሰበብ ጥሎት ሄደ። ወደ ማታ ገደማ፤ መጨረሻውን ለማወቅ ፈራ ተባ እያለ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ዓይኑን ማመን አቃተው። ጐበዜ ከወለሉ ላይ እንደ ዝንጀሮ ቁርጢጥ ብሎ ተቀምጧል። እብደቱ ከዐይኑ ላይ እንደ እሳት የሚንቀለቀል ይመስላል። ዐይኖቹን ጉንጮቹ እንደ መንቀጥቀጥ ይላሉ። ጥርሱን የሸፈነው ብጫ ለሐጭ በከንፈሩ ላይ መሥመር አበጅቷል።

«ጐበዜ! » አለ ካሣሁን በሚተናነቅ ድምፅ። ጐበዜ፤ ጥርሱን አግጥጦ ሁለት እጁን ወደ ፊት አንጨፍርሮ አውሬ መስሎ አውሬ፤ ሆኖ ተወርውሮ መጣበት።

ከጉሮሮው የሚወጣው ድምፅ የአውሬ አይሉት የሰው፥ ልዩ ዓይነት ነበር። ድምፁ ማስታወክ እስኪ.ቃጣው ድረስ አንጀቱን አመሰበት። ለመሮጥ ሞከረ። እግሩ ለቅጽበት የማይንቀሳቀስ ሽባ ሆነበት። «ተው! » ብሎ ጮኸና ጕበዜ ዘሎ በጥርሱና በጁ ሲይዘው አንድ ሆነበት። አንድ ጀሮው የተበጠሰ ሲመስለው ፊቱ ሲተለተል አካሉ፥ ከየቦታው ሲቢጨቅ ተሰማው። የጕበዜ ጥርስ የካሣሁንን ሰርስሮ በሚገባበት ጊዜ ስንኳ ከጉሮሮው የሚወጣው አስፈሪ ድምፅ አያቋርጥም ነበር። በሥጋው በኩል አልፎ ልቡን የሚሰነጥቅ ድምፅ ነበር።

ተያይዘው ወደቁ። ተገለባበጡ። ካሣሁን፥ የነፍስ ነፍስ በደመ ነፍስ፥ በአንድ እጁ የጕበዜን ጉሮሮ ፈጥርቆ በሌላ፥ እጁ መንጋውን እጁ መንጋጋውን ፈልቆ፣ ንክሻውን በማላላት ተራግጦ ተወራጭቶ በመላቀቅ ተስፈናጥሮ ሮጠ። እስሩ ዙሮ በዋናው በር እስኪወጣ ጕበዜ ወግሽቶ በረት እንደሚሰብር በሬ በአጠናና በትራኮራታ (ባለ እሾህ የአጥር ሺቦ) የታጠረውን ግቢ ጥሶ አቋረጠው። አጥሩ ልብሱንና አካሉን፥ በአብዛኛው ዘነጣጥሎ አስቀርቷል። ሸሚዙ ግማሹ የለም። የቀረው በትከሻው ላይ የተንጠለጠለ ብጭቅጫቂ ነው። ሱሪውም ግማሽ አካሉን አይሸፍንም። በዚህ ላይ ከጭንቅላቱ አንሥቶ እስከ እግሩ ድረስ መላ አካላቱ ደም በደም ሆኗል። አንድ ዐይኑ ተጕልጕሎ የወጣ ይመስል ነጭና ሌላም ቀለም ከደሙ ጋር በጉንጩ ላይ ይወርዳል። አገጩ በአረፋ ተሸፍኗል።

ካሣሁን ይህንን አሠቃቂ፥ ይህንን በሕልሙ ስንኳ አይቶት የማያውቀውን ትርኢት ለቅጽበት አየ። አንድ ጊዜ ከተነከሰ የአሁኑ ሽሽት በሽታው ከመለከፍ እንደማያድነው ያውቃል። በሽተኛ ስለሆነ ፊት ለፊት ቢጋጠሙም እስከዚህ ድረስ ከባድ ጉዳት እንደማያደርስበት ይታወቀዋል። ግን ይህ ፊት ማየት ሰው አይሉት አውሬ፥ ያንን አዲስ ፍጡር መቋቋም አልቻለም። እግሬ አውጪኝ ሮጠ። የውሻ በሽታ በሰው ላይ ሲጋባ ስለሚያስከትለው አሠቃቂ ሁናቴ ሰምቶ ነበር። እንደዚህ ዓይነት ይሆናል ብሎ ግን ጭራሽ አላሰበም። ልቡ ደረቱን በርግዶ የሚወጣ እስኪመስል ድረስ፥ ሳምባው ትንፋሽ መስጠት ያቃተው እስኪመስል ድረስ፥ ቋንጃው መንቀሳቀስ እስከቻለ ድረስ ሮጠ። የፍርሃት ሩጫ አይደለም። ሽሽቱ ከፍርሃት በላይ ነበር። አንዱ አባራሪ ሌላው ሸሺ ሆነው ሁለቱ እየተከታተሉ ሲሮጡ አላፊ አግዳሚው ሰው እየተጯጯኸ ስብስብ ብትን እያለ ያጅባቸዋል። በመካከላቸው ለመግባት የሞከረ ግን አልነበረም ካሣሁን የእግሩ እንቅስቃሴ እንደ መሪው እንጂ ወደየት እንደሚሮጥ አያይም ነበር። አረብ ገንዳ ዋናው መንገድ መግባቱንም አያውቅም ነበር። ያንን ነገር ሳያይ ነው። በዚህ ጊዜ

ሁሉ ግን «ያዙት! ያዙት! የውሻ በሽታ አለበት! የውሻ በሽታ! » እያለ ይጮህ ነበር። ይህ ደግሞ ተራ አምባጓሮ መስሎት ለማዳነቅ ማጀብ ጀመረው ከፊሉን አስበረገገው።

ካሣሁን ድምፁ ከጭንቅላቱ ውስጥ እንደ ፈነዳ ፊኛ ሲጮህና፤ ግንባሩ በፋስ ለሁለት እንደ ተከፈለ መስሎ ሲሰማው የኋሊት ተፈንግሎ ወደቀ። ምቱ፣ ከእንቅልፍ እንደሚያስነሣ ጥፊ ዐይኑና አስተሳሰቡን ለቅጽበት ከፈተው። ከፊት ለፊት ሰማይ የነካ የሚመስል ትልቅ ምሰሶ ተገትሯል። ወዲያው ሙሉ እርቃኑን ለመሆን ምንም ያልቀረው ያ አውሬ ከላዩ ላይ እንዣበበ። ላንዳፍታም፥ መዳፍ እይሚያክል ጠባሳ ከጭኑ ላይ ታየው። ግን ምንም ስሜት አልሰጠውም። ትርጉሙ እንደ ተረሣ አንድ ዓይነት የሩቅ ጊዜ ሕልም መስሎ ታየው። ከዚያም ከፊት እንደ እሾህ የተንጨፈረረ ሁለት እጅ፣ ከእርሱ ኋላ እስከ አገጩ በቢጫ አረፋ ያደፈቀ ጥርስ ማነቆው ላይ ተተከለና እፍን ስልም አደረገው። ራሱን የሳተው ከዚህ ምስል ነበር።

## ፺

የደመላሽ ሚስት ወይዘሮ ዘርፈሽዋን ለማስደንገጥ መጀመሪያ ባደረገችው ሙከራ ለአጭር ጊዜ ብቻ በቀበሌ ጽሕፈት ቤት ቆይተው በመለቀቃቸው እንደ በሽቀች ሳለች ደመላሽም ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት መመላለሱን እንደ ቀጠለ ሳለ፤ የዘለቃ መገደል ላፍታ «እሰዬ » ቢያሰኛትም ቂሟን አላበደላትም። የበቀል ስሜቷን አላረካላትም። እንዲያውም ይባስ ብሎ ለዘለቃ ሞት ደመላሽ ራሱ ኀዘን እንደ ተቀመጠ ያህል ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት አዘውትሮ ማምሸቱ እርር ድብን አደረጋት። ከደመላሽ ጋር ትዳር «እሳት የወለደች ላም እንዳትልሰው ፈጃት እድናትተወው ልጅ ሆነባት » እንደሚለው ዓይነት ሆነባት። እንዳፈታው ጋንዲላ በሚያክሉ አሮጊት መሸነፍዋን ማመን ሆኖ ተሰማት። ተፋትታስ ምን ትሆናለች? ንግዱን እንደሆነ ዘርፈሽዋል ያሉት «መሶብ ቤት » እያሉ ተሻምተውታል። የኪራይ ስም ቤቱም እንደ ልብ አይገኝ።

ጭዳ ከመጣልና መርዝ ከመስጠት አንሥቶ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልን እንዴት መበቀል እንደሚቻል ከወንድሟ ጋር በሰፊው ተመካከሩበት። ግን አሁንም የተሻለ ሆኖ ያገኙት በቀበሌ አንድ ነገር ማስደረግን ነው። ለዚሁም ከበፊቱ አሁን

ያመቻል። ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር አጸፋ እየተመታ ነው። በአገር ወዳጆች ጠቋሚነት ብዙ ሰዎች እየተለቀሙ ነው።

እንዳለፈው ጊዜ እንዳይከሽፍባቸው በዘዴና በጥንቃቄ ተያያዙት። መጀመሪያ ኃይለኛ የተባለውን ቀበሌና ከፍተኛ አጠኑ። ቀጥሎ ወንድምዬው በሰው ሰው ከቀበሌውና ከከፍተኛው አንዳንድ ሹማምንት ጋር ተዋወቀ። «የፖለቲካ ወጪውን » ከእኅቱ የተቀበለውን ሁለት ሦስት ጊዜ ያህል ጋበዛቸው። አንድ ቀን ምሽት በቢራ ሞቅታ ጨዋታው ሲደራ «በየቤቱ እንዴት ዓይነት ፀረ - አብዮተኛ አለ መሰላችሁ » ሲል ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሚባሉ የለየላቸው አድኃሪ ኢ.ዲ.ዩ፤ ብዙ የጦር መሣሪያ የደበቁና በመቶ ኩንታል የሚቆጠር በርበሬ ያከማቹ መሆናቸውን ነገራቸው። የወይዘሮ ዘርፈሽዋል አድራሻ በማስታወሻ ደብተር ላይ ተመዘገበ።

የወንድምና የኅት ግምት ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ብቻቸውን ቀበሌ ወይም ጸጥታ ተወስደው ይታሠራሉ የሚል ነበር። ግን እንደ ፈለጉት ወዲያው ባይሆንም ቆይቶ ያልጠበቁት ሁናቴ ደረሰ.......

# ፲

የተውሶ ፔጆ አውቶሞቢል በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግቢ ውስጥ ፊቷን ወደ በሩ አድርጋ ቆማለች። ከኋላ የተቀመጡት ወይዘሮ ሸዋዬ ሰዓታቸውን አሁንም አሁንም ይመለከታሉ። ሹፌሩ ከመሪው ላይ ደገፍ ብሎ ይጠብቃል። እሑድ ስለ ሆነ ከአውቶሞቢሉ የኋላ ኮፈን ሻንጣዎች መጫናቸውን ላላየ ሰው ቅዳሴ ሳያልቅ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ የተጣደፉ ይመስላሉ። የተፈለገው ይኸውም ነበር።

ወይዘሮ ሸዋዬ ከሠራተኛ ፊት ወይዘሮ ዘርፈሽዋልን አንቺ ማለቱ ማዋረድ ሆነባቸው አንቱ ማለቱም ቀፍፎዋቸው ማንን መሆኑን ሳይጠቅሱ በደፈናው «እስቲ ሂድና ሰዓት ያልፋል በል » ሲሉ ሹፌሩን አዘዙት። አሁንም ጥቂት ደቂቃ ከጠበቁ በኋላ ራሳቸውን ከመኪናው ወርደው ወደ ቤት ሲገቡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ከፎቴው ላይ ፈዘው ተቀምጠው አገኙዋቸው። «ምን ነክቶሻል -

አትነሽም እንዴ? » አሉ ወይዘሮ ሽዋዬ በግሣጼ አንገታቸውን እንደ ዶሮ ሰገግ አድርገው።

«ለመሆኑ የሚሳካልን ይመስልሻል ሽዋዬ? » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በጭንቀት ጠየቁ፣ «እኔ - እኔማ - ሆዴ » አልቆርጥ አለ ለማለት ፈልገው ንግግራቸውን አቋርጠው ተውት።

«ምነው ሽዋ! እየፈጩ ጥሬ መከርንበት ዘከርንበት ያለቀለት ነገር አሁን እንደ አዲስ ትጠይቂኛለሽ? » ወይዘሮ ሽዋዬ አንገታቸውን እንዳሰገጉ ዐይናቸውን አጉረጠረጡ።

«እሱማ ነው » ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ግንዲላ የሚያክል እጃቸውን እርስ - በርሱ እያፍተለተሉ ወደ ላይ አንጋጠው በጭንቀት ወይዘሮ ሽዋዬን ተመለከቱ፤ «ግናስ - እንዲያው አሁንም አሁንም ሳስበው፤ ከማያውቁት መላክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል እንደሚባለው የማናውቀው አገር » አሁንም ንግግራቸውን መጨረስ አቅታቸው።

«እጭ እቴ! የምታውቂው የጭዋ ልጅ ሰው መሆንሽ ቀርቶ ከከብት ከትቢያ በታች ሲያውልሽ አይተሽዋል። አልበቃሽም? እኔ ሽዋዬ እንደሆን በቅቶኛል። መዋረዱ መረገጡን እንደ አህያ እይምትችይው ከሆነ የራስሽ ጉዳይ ነው። እኔ ግን » ብለው ወይዘሮ ሽዋዬ ፊታቸውን ወደ በሩ መልሰው እንደ መራመድ አሉ።

«ኧረ እንደሱ ማለቴ አይደለም። በስማም ወልደ መንፈስ ቅዱስ! ምን አልኩሽ እቴ! » ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ፊታቸውን በእጃቸው ሸፍነው እንደ መወራጨት አሉ። የደረሰው ሁሉ በሐሳባቸው መጣባቸው......

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አልፏል። በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቤት የራት ገበታ ተነሥቶ ለዘለቃ አርባ መሰናዶ በሥራም በሐሳብም ሲረዱ፥ የዋሉት ጥቂት ሰዎች መጠጥ ይዘው ይጨዋወታሉ። ለሌሎች የቀረበው ቢራ ጠላና፣ ጠጅ ሲሆን ዊስኪ የተቀዳው፤ የተቀመጡበት ሶፋ እንደ ዙፋን ፈቀቅ ብሎ ለተሰጣቸው ለወይዘሮ ሽዋዬ ብዬ ነው። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል፣ የገንዘብ አቅማቸው እንደ ልብ የማያዝናና እየሆነ በመሄዱ በገበያ ላይም በቀላሉ ስለማይገኝ ለእንግዳ ሁሉ ዊስኪ መጋበዙን ቆጠብ አድርገውታል። ለወይዘሮ ሽዋዬ ግን ሌላ መጋበዝ አይችሉም ነበር። ወይዘሮ ሽዋዬ ምሣ ወይም ራት በልተው አንድ መለኪያ ዊስኪ ካልቀመሱ አይሆንላቸውም። ወትሮ በራሳቸውና በመሰሎቻቸው ቤት ዊስኪና ሻምፓኝ እንደ ውሀ ይቀዳ የነበረበት ጊዜ ትዝ እያላቸው ፉት ባሉ ቁጥር «ይሁና - መቼስ » ይላሉ በሆዳቸው።

ደመላሽ ሌሎቹ ከወጡ በኋላ ለሰውነት ማሞቂያ ተብሎ ከሚቀመጥለት ኩርቫዞር እስኪሰጠው ድረስ በጠጅ ያዘግማል። ከመካከላቸው ወንድ እርሱ ብቻ ስለ ነበር በኤሌክትሪኩ መብራትና ሁሉም በለበሱት ጥቁር ልብስ አንጻር እጅግ የደመቀና የፈካ የሚመስለውን ያልተሸፈነ አካላታቸውን ተራ በተራ በዐይኑ ሲዳብስ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በጨዋታው መካከል በትዝብት አመለካከት ይከተሉታል።

በዚህ ሁናቴ እንዳሉ እስከነታጣፊው የተገነጠለ እስኪመስል ድረስ የቤቱ ዋና በር በኃይል ተበረገደ። የመሬት መንቀጥቀጥም መብረቅም፥ መስሎዋቸው ሁሉም በድንጋጤ ለአንዳፍታ ድርቅ አሉ። ወዲያው ሰዎች ተንጋግተው ሲገቡ «እጅ ወደ ላይ » የሚል ጩኸት አስተጋባ። አምስት ናቸው። ሁሉም የጦር መሣሪያ ይዘዋል። ሦስቱ ዲሞፍተር ጠመንጃ አንዱ አውቶማቲክ ካርባይኑን ወደ መሰላቸው ኢላማ ደገኑ። ከመካከላቸው እንደ መሪ የሆነው አምስተኛ ክንድ የማትሞላ አውቶማቲክ መሣሪያውን ከደረቱ ላይ እንዳንጠለጠለ በጨበጠው ኮልት ሽጉጥ አፈ ሙዝ ክፍሉን በሙሉ ቃኘ። ደመላሽ በውትድርና እንደ ተማረው መሣሪያ ያልጨበጠ መሆኑን ለማሳየት ያህል ሁለት እጁን ፊት ለፊት ትንሽ ብድግ አደረገ። ከሴቶቹ መካከል፥ አንዳንዶቹ ምሕላ እንደያዙ እጃቸውን ወደ ጣሪያው ዘረጉ። አንዳንዶቹ እንደ ክፍል ተማሪ አንድ እጃቸውን አነሡ። እጃቸውን አንሥተው ከመ ቅጽበት ያወረዱ ሁለት እጃቸውን ከደረታቸው ላይ የለጠፉም ነበሩ። ወይዘሮ ሸዋዬ ብቻ እጃቸውን ከሁለት ጭናቸው ላይ እንዳስቀመጡ ቀና ቀጥ ብለው ቀሩ። ተኰፍሰው እየተመለከቱ።

የውሻ ምላስ የመሰለች ኮፍያውን እስከ አፍንጫው ጫፍ ድረስ የደፋው ወጣት ኮልቱን እያወዛወዘ ክፍሉን በዐይኑ ከፈተሸ በኋላ ከአንዱ በስተቀር ሁሉም ሴቶች መሆናቸውን ተመልክቶ እንደ መዝናናት አለ። «የልዕልቶች ስብሰባ ነው? ዘርፈሽዋል ማንኛዋ ናት? » ሲል በቁጣ ጠየቀ።

«እኔ ነኝ፤ ምን ነበር? » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ድምፃቸው የተዘጋ ይመስል በሰለለ አንደበት።

«ተነሽ! »

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ትእዛዙን ከመፈጸማቸው በፊት «ምንድን ነው ምክንያቱ በር ተሰባብሮ የሚገባበት! ሕግ የለም እንዴ ባገሩ! » ሲሉ ወይዘሮ ሸዋዬ ጮህ ብለው ተናገሩ።

«አብዮት ከሁሉም በላይ ነው! » ኮልት የጨበጠው ወጣት ወደ እርሳቸው ተንደርድሮ ሄደ።

«ውንብድና ነው! » አሉ ወይዘሮ ሸዋዬ ድርቅ ባለ አነጋገር። የሚያስፈሩ የሚያስበረግጉ መስሏቸው ነበር። ግን ቃሉ ገና ከፊታቸው ሲወጣ «ምን? » ብሎ ጮኸና በኮልት ጥፊ ሲለጋቸው ከሶፋው ላይ ክንብል ብለው ከወለሉ ላይ ወደቁ። በክፍሉ ውስጥ የድንጋጤና የሲቃ ድምፅ አስተጋባ። ወይዘሮ ዘርፌሸዋል «ውይ! » ብለው ጮሁና ወይዘሮ ሸዋዬን ለማንሣት እመር ሲሉ መኻል መንገድ ላይ በኮልት ጥፊ ተቀበላቸው። እርሳቸውም ተዘረሩ። ሌሎቹ በያሉበት ኩርምትምት ብለው ቀሩ። ደመላሽ ብቻ ከተቀመጠበት እንደ መነሣት ቃጣውና መልሶ ተወው። ወዲያው የወይዘሮ ዘርፌሸዋል የሲቃ ጥሪ መጣበት። «አልተረፍኩም! አልተረፍኩም - ደመላሽ ዝም ትላለህ! » የሴቶቹ ሁሉ ዐይን በእርሱ ላይ አረፈ። ሁሉም ወንድነቱን የሚፈታተኑ ወንድነቱን የሚማጠኑ መሰለው። ምንም ማድረግ እንደማይችል ቢያውቅም ይህንን ጥሪ ባይቀበል ደግሞ ነገር በእነዚህ ታዛቢ ዐይኖች ፊት አንገቱን ቀና አድርጎ መቀመጥ እንዳማይችል ተሰማው። ሲነሣ እንደ መፈከር ቃጣው።

ትርምሱ ረጅም ጊዜ አልወሰደም። ደመላሽ ከአንድ ሁለት ላይ ቡጢ እንዳሳረፈ፥ በሰደፍ አዳፍተው ወዲያው በቁጥጥር ሥር አዋሉት። ደመላሽ በአራት አጃቢ ተይዞ ወይዘሮ ዘርፌሸዋል በአንድ አጃቢ እየተነዱ ተወሰዱ። በበነጋው ኮርኒሱ ሳይቀር እየተነቀለ ቤታቸውና ግቢያቸው ሲበረበር ዋለ።

ወይዘሮ ዘርፌሸዋል በስንት አማላጅ ዋስ ጠርተው ከጉንጫቸው ላይ ያልሻረ ትልቅ ጠባሳ ለመታሰቢያ ተይዘው ከሳምንት በኋላ ተፈቱ። ታሥረው የሰነበቱ በፖሊስ ጣቢያ ነበር። ወይዘሮ ሸዋዬም ሁለት ጥርስ አጥተው ከሆስፒታል ወጡ። ደመላሽ ግን ከዚያን ቀን ምሽት ወዲያ ጀምሮ የደረሰበት አልታወቀም። አልተረጋገጠም እንጂ የእርሱን የሚመስል ሬሣ ከውስኪ ጠርሙስና ከኃይል ሥላሴ ፎቶ ግራፍ ጋር በሰንጋ ተራ ሠፈር ተጥሎ ታይቷል ተብሏል።

ወይዘሮ ዘርፌሸዋል በዘለቃ ሞት በደመላሽ መጥፋት በራሳቸውም ላይ በደረሰው ከባድ ኀዘንና ምሬት ይህ ነው የማይባል ብቸኝነትና ሠቀቀን ይሰማቸው እንጂ ወደ ፊት እንደ ሰው ተኩራርተው መኖራቸው ያከተመ መሆኑ ይታወቃቸው እንጂ የስደት ነገር የመነጨው ከወይዘሮ ሸዋዬ ነበር።

«ከእንግዲህ ወዲያ በሰው አገር እንዴት ተደርጎ ይኖራል ብለሽ ነው ሽዋዬ? » አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሐሳቡ መጀመሪያ ሲቀርብላቸው።

«የእኛ ሰው ሁሉ እንደሚኖረው ነዋ! ከዚህ የቀርነው ተጎዳን እንጂ እነሱማ ዝንባቸውን ስንኳ እሺ የሚልባቸው ሳይኖር ተዘባነው ነው ያሉት። ሩቅ ሳንሄድ ከዚህ ከአጠግባችን በጅቡቲ ያሉት ስንኳ ስንቶች ከብረዋል። የበረደድ ሚሽት ዓመት ሳይሞላት ነው ምን የመሰለ ትልቅ ቡና ቤት የከፈተችው። ሰው ሲተሳሰብና ሲረዳዳ እንዲህ አይደለም አሉ። »

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል «እሱማ ገና ሽንቅጥ ቆንጆ ናት » አሉና በሆዳቸው «ታዲያ ሁሉ ይሆንለታል ብለሽ ነው? ጥሪቴ እንደሆነ እየተሟጠጠ ሄዷል » ሲሉ መለሱ።

«ታዲያ ከዚህ ተቀምጠሽ አዲስ ጥሪት ከሰማይ ይወርድልሻል መሰለሽ? የተረፈሽ ይወስዱልሻል እንጂ » አሉ ወይዘሮ ሽዋዬ ኮስተር ባለ አነጋገር። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እሽታም እምቢታም፣ ሳይመልሱ በማቅማማት ዝም አሉ። «አንቺ እንዳፈቀደ፤ እኔ ግን ከልቦናዬ ጋር አውጥቼ አውርጄ በቃኝ! ቆርጫለሁ! »

«የእነርሱ መምጫቸው ደርሷል የሚባለውስ? » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጠየቁ - ሕይወት ተደናግሮባቸው።

«ታዲያ እሲመጡ ማንም ውርጋጥ ይርገጠኝ! »

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የባዕድ አገር ኑሮ ፈክቶ ባይታያቸውም ወይዘሮ ሽዋዬ ከሄዱ የባሰውን የብቸነት ጨለማ እንደሚውጣቸው ተሰማቸው። ሲቸገሩ የሚሄዱበት ሌላ ሁነኛ ሰው አይኖራቸውም።

«የዘለቅዬስ አርባስ? » አሉ በማሳዘን አንደበት።

«እሱማ ይወጣል። »

የዘለቃ አርባ እስኪወጣ ከአውቶሞቢል አንሥቶ ደህና ደህናው ዕቃ ሁሉ በሥውር ሲሸጥ ሰነበተ። የአሜሪካን ብር ቀስ እየተባለ ተመነዘረ። ወይዘሮ ሽዋዬ በሚያውቁት መሥመርም በድሬዳዋ አስፈላጊው ግንኙነት ተደረገ። ለኬንያና ለጅቡቲ በአምስት ሺህ ብር ለአውሮፓ በአሥር ሺህ ብር ለአሜሪካ በአሥመራ አምስት ሺህ ብር ቪዛ ማግኘት የሚቻልበት መንገድ መኖሩን ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሰምተው ነበር። መሆኑ ካልቀረ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሚመርጡትም

ከዚሁ ከአዲስ አበባ ብርር ብሎ መውጣቱን ነበር። ወይዘሮ ሸዋዬ ግን የአዲስ አበባው ጨልሌ ሙሉ በሙሉ የሚታመን መሆኑን ተጠራጠሩ። ገንዘባቸውን በልቶ በጐን ለደርግ ነግሮ አውሮፕላን ጣቢያ ለቀም ቢያስደርጋቸውስ? ከዚህም በቀር ይበልጥ አስተማማኝ የሆነው የየብስ መሪ ሁለቱም በአምስት መቶ ብር ጅቡቲ ጠረፍ ሊያሻግራቸው ሲችል አሥር ሺህ ብር መክፈል፥ ገንዘብ በከንቱ እንደ መበተን ሆኖ ተሰማቸው።

ወይዘሮ ዘርፈሸዋል ብቻቸውን ለመሄድም ሆነ ብቻቸውን መቅረት ስለማይችሉ በወይዘሮ ሸዋዬ እቅድ መስማማት ግድ ሆነባቸው።

ከአንድ ሁለት የምሥጢር ሰዎችና ዝግጅቱ ከሚመለከታቸው በስተቀር ሌላ ማንም ሰው ሳይሰማ የዘለቃ አርባ በወጣ በሳምንቱ ሁሉም ነገር ተጠናቆ አበቃ። መቸም አብሮ የበላ ሆድ አይቀርጥምና ወይዘሮ፥ ሸዋዬ ለጥቂቶቹ ቀራቢዎቻቸው «ዘርፉ እኮ ከስወንት ወጣች። የልጅዋ ኀዘን ትንሽ ቢቀላት በልነ ድሬዳዋ ለጥቂት ቀን ዕረፍት መሄዳችን ነው። እዚያውም ቁልቢን ተሳልመን ተስለን እንመጣለን። እናንተ ቁልቢን የምታውቁት ከማርካቶ የባሰ ግርግር ያለበት የታኅሣሡን ብቻ ነው። ስለት የሚሰማው ታቦቱ ግን ምን ጊዜም ከመንበሩ አለ። እርጋታው፤ ጸጥታው አይሻልም? » የሚል ምክንያት እየሰጡ ተሰናበቱ።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ነበር፥ ወይዘሮ ዘርፈሸዋል ለመጨውረሻው ከቤታቸው መውጣት ጭንቅ ሆኖባቸው ሲያመናቱ የወይዘሮ ሸዋዬ ትዕግሥት ያለቀው፤ የአውሮፕላን ጣቢያ መድረሻ ጊዜውም የተቃረበው።

ወይዘሮ ዘርፈሸዋል ሳይሳቡት በዐይናቸው ዕንባ ችፍፍ አለባቸውና በመሐረም ቢጠርጉት እንዳይታወቅባቸው በቅንድባቸው ጭምቅ ጭምቅ እያደረጉ ወይዘሮ ሸዋዬን ተከትለው ወደ አውቶሞቢሉ ገቡ።

## ፳

ወይዘሮ ሸዋዬ የጥንቱን የላሊበላ ተሳላሚዎች ዘፈን ቀይረው «አልጋ አልጋ ነው መንገዱ፤ አልጋ አልጋ ነው መንገዱ ሰው ዘር ሥፈር፤ ከጨዋ ወገስ ሲሄዱ » እያሉ ለማባባል በወይዘሮ ዘርፈሸዋል ጆሮ እንዳንጐራጐሩት ሁሉ ጉዞዋቸው አስቀድሞ በተደረገው ዝግጅት መሠረት ተሳክቶ ቀጠለ። በድሬዳዋ ራስ ሆቴል

ደርጐችና የደርግ ሰዎች ያዘወትሩታል ስለ ተባለ የተመረጠው ጨረቃ ሆቴል ነበር። ነጋዴውም፥ ደላላውም ኮንትሮባንዲስቱም አቃጣሪና ተቃጣሪውም ስለሚገጣጠምበት አሳሳች ነው። ማን ከማን ለምን እንደሚገናኝ ለማወቅ ያስቸግራል።

በዚህ ሆቴል ውስጥ እስከ ጅቡቲ የሚደርሱት የጉዞ ዝግጅት ተጠናቀቀ። ጉዳዩን በኃላፊነት የያዘው አብዮቱ በፈዲስ ምን የመሰለ አሥር ጋሻ የሸንኩርት የጫትና፥ የእህል መሬት ያሳጣው፥ በፖለቲካ ታማኝነቱ የእነወይዘሮ ሽዋዬ ወገኖች አገናኝና ጉዳይ ፈጻሚ ሆኖ የሚሠራ የኮንትሮባንድ ነጋዴ ነበር።

በዚህ ወቅት ድሬዳዋ ወሬና ሥጋ ሰፍኖባት ነበር። ከዋርዴር ከወልወል፣ ከቆራሄ፥ ከቀብሪደሃር ከደገሀቡር ከጐዴ፣ የሚመጡ ሰዎች ስለ ሶማሊያ ወራሪዎች ብዙ አሠቃቂ ታሪክ ይናገራሉ። ብዙዎቹ ጓዛቸውን እየያዙ ሸሽተው የመጡ ናቸው። አዝማሚያው ያላማራቸው በርከት ያሉ የድሬዳዋ ነዋሪዎችና ወደ አዲስ አባባና ወደ አሰበ ተፈሪ መሄድ ጀምረዋል። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ሥጋት ገባቸው፤ «የሚወራው መጥፎ መጥፎ ነው። ለመሆኑ የመንገዱ ጸጥታ ያስተማምናል? » ሲሉ ጠየቁ።

«ታች ታቹን እንጂ በዚህ በኩል ምንም ነገር የለም። ቢሆንስ እኛን በነሱ ጦርነት መካከል ምን አገባንና ይተናኰሉናል? ሲሆን አጅበው ያሳልፉናል እንጂ » ሲል መለሰላቸው።

«ከዚህ ከደረስን በኋላ፥ እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ ማለት ምንድን ነው እቴ! » በማለት ወይዘሮ ሽዋዬም ገሠጹዋቸው።

ዱካቸውን ለማሳሳትና ለማጥፋት አንድ ቀን ቁልቢ ሌላ ቀን ዓለማያ እየሄዱ ተመለሱ። በሦስተኛው ጊዜ ዘመድ ጥየቃ ሐረር መሄዳቸውን አስወርተው ጉዳይ ፈጻሚያቸው ባቀረበላቸው ቶዮታ ‹ክሩዘር› መኪና ከነጓዛቸው ተሳፈሩ። እይደንጎን ዳገት እንዳጋመሱ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ወደ ኋላ መለስ ብለው ድሬዳዋን ከተማ ለመጨረሻ ጊዜ ሲመለከቱ ሆዳቸው ባር ባር አለባቸው። ‹ጨክን ሆዴ› አሉ በሆዳቸው።

ጉዞዋቸው አልቤህን የጋዴን፣ የአዲጋላን ከተሞችና የባቡሩን ሐዲድ በስተግራ እየተወ ወደ አይሻ በሚወስደው የጠጠር መንገድ ነበር። እየራቁ በሄዱ መጠን የመሬቱ ልምላሜ እየገረጣ ዛፍና ቁጥቋጦ እየሳሳ አሸዋው እየበዛ ሐሩሩ እያየለ፣ የመንገዱ አባጣ ጐርባጣነት እየከፋ ሄደ። ወደ አሥር ሰዓት ላይ አይሻ ከተማ ለመድረስ አንድ አሥር ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው ከመንገድ ወጡና

ዙሪያውን በበረሃ ቁጥቋጦ ተከቦ መኻሉ እንደ አውድማ ገላጣ በሆነ ቦታ ሠፈሩ። የከብትና የመኪናው ኮቴ፥ አመድና የእንጨት ትርኳሹ የወዳደቀው ቁሳቁስ የኮንትሮባንድ መናኸሪያ መሆኑን ያስታውቃል። «እንግዲህ አዳር ከዚህ ነው » አለ ሰውዬው ለዚሁ ተብሎ ተጠቅልሎ የተያዘውን የመንገድ ‹እስፖንጅ› ፍራሽ አውጥቶ እየዘረጋ ኬላውን በመኪና ማለፍ ስለማይቻል ከዚህ በኋላ እስከ ጅቡቲ ጠረፍ ያለው ጉዞ በከብት መሆኑን ነግሮዋቸው ነበር።

ሰውዬው ከቤት አሠርቶ ያመጣው የአገልግል እንጀራ በቢራና በባቢሌ ውሀ እየተወራወረደ ተበልቶ እንደ ኮንትሮባንድ ዕቃ ጨዋታም ሲነግድ የኖረ ይመስል እይማይልቅበትን አስደናቂ ታሪክ ሲያወጋቸው አምሽቶ ድካም ተሰምቷቸው ስለ ነበር የሰላም እንቅልፍ ተኝተው አደሩ። አልፎ - አልፎ የሚሰማው የአራዊት ጩኸት ስንኳ አላወካቸውም።

ጧት ሰርዲንና የቆርቆሮ፣ አትክልት ቆርሰው ፀሐይ በምሥራቅ አድማስ ገና ብቅ እንዳለች አንድ ሰው ሦስት ግመሎች እየነዳ ከሰፈሩበት መጣ። ከሰዬው ጋር ሰላምታ ተሰጣጡና ሴቶቹ በማይገባቸው ቋንቋ ተነጋገሩ። ሰውዬው መልሶ ሁኔታውን ለሁለቱ ሴቶች አስረዳቸው። በአንዱ ግመል ዕቃቸውን ጭኖ በሁለቱ ግን እነርሱን አሳፍሮ በሚያውቀው መንገድ ጅቡቲ ግዛት ውስጥ ያስገባቸዋል። ከዚያ መኪና ይዞ የሚጠብቃቸው ሰው ተደርጓል። ባለ ግመሉ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር አስቀድሞ የወሰደ ሲሆን ቀሪውን ሁለት መቶ ሃምሳ ብር ደግሞ ለነርሱ አድርሶ በደህና ለመድረሳቸው መተማመኛ ማስታወሻ ወረቀት ይዞ ሲመለስ ለመቀበል ተስማምቷል። ከዚያ በፊት ግን ባለ ግመል በዚህ ዓይነት ብዙ ሰዎች ያስወጣ ስለሆነ ምንም ችግር የለበትም ተባሉ፤ ወይዘሮ ሽዋዬ በመስማማት ራሳቸውን ሲነቀንቁ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቀፈፋቸው። አማርኛ ስንኳ የማያውቅ አንድ ባንዳ ሰው አምኖ እንዴት በበረሃ ይጉዋዙዋል? ግን በግልጽ አፍ አውጥተው መቃወም አልቻሉም። ወይዘሮ ሽዋዬ ያመናጭቋቸዋል። ባለ ግመሉስ ቢሆን አማርኛ የሚሰማ ከሆነ ቂም ይዞ በኋላ ቢተናኮላቸውስ? ስሜታቸውን በሆዳቸው ውስጥ አምቀው ዝም አሉ።

በግመል ላይ መሥፈሩ መጀመሪያ ለሁለቱም ሴቶች በጣም ችግር ሆኖባቸው ነበር። ቀርቶ ከግመል አጠገብ ሲቀርቡ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር። እንስሶቹ የረጉ ገራሞች ቢመስሉም አንገታቸውን አስግገው፥ ለምቦጫቸውን ጥለው የሚያንጐላቹ አስቀያሚ ፍጥረቶች ሆነው ታዩዋቸው። ይህ የሁለቱም ሴቶች ስሜት ነበር። ባለ ግመሉ እያሳያቸውና እየረዳቸው በትእዛዝ ከተንበረከኩት ግመሎች ጀርባ ላይ እንደ ምንም ወጡ። ‹ሃይ!› ተብለው

ግመሎቹ ወደ ላይ ብድግ ሲሉ ሰማይ የወጡ መሰላቸው። መሬቱ በጣም ወደ ታች ራቀባቸው። አንዴ ጉዞውን ከጀመሩ በኋላ ግን ቀለላቸው። እንዲያውም ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በስንት ዘመናቸው ከብት ጀርባ ላይ ተቀምጠው ግመሉ እሹሩሩ እንደሚልና በቀስታ ወተት እንደሚንጥ ወለም ዘለም ሳብ ረገብ፥ እያደረገ ሲያወዛውዛቸውና የጭናቸው መጋጠሚያ ሲተሻሽ እንደ ተኮረኮረች ኮረዳ ወሲብ ብጤ ተሰማቸው።

ቶዮታው አውቶሞቢል ወደ ዋናው የጠጠር መንገድ ገብቶ ፊቱን ወደ ድሬዳዋ ሲመለስ፥ ሰውዬው እጁን በማወዛወዝ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበታቸው። ሁለቱ ሴቶችም በአንዳንዱ እጃቸው ኮርቻውን ጥርቅም አድርገው እንደ ጨበጡ በሌላ እጃቸው አጻፋቸውን ለመመለስ ሞከሩ። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተወልደው ካደጉበት ወልደው ከብደው ከኖሩበት አገር ጋር የሚያገናኛቸው እትብት ሲበጠስ አንጀታቸው አሁንም በፍርሃትና በጭንቀት እንደ መላወስ አለ። እንደ ግመሉ አንገታቸውን አስግገውና ኮስተር ብለው የሚጓዙትን ወይዘሮ ሸዋዬን ተመልከቱና ላለመሸነፍ ጥርሳቸውን ነከስ አደረጉ።

ከፊት ለፊታቸው የምታንጸባርቀው ፀሐይ ከቡናማ የአቧራ ጭጋግ በቀር ደመና በሌለው አድማስ ላይ ገና ብዙም ከፍ ሳትል ሐሩሩ፣ እንደ ነበልባል ይወርድ ጀመር። የሚያበርደው ነፋስ የለም። የሚገታውና አግጣጫውን የሚያስቀይር ተራራ ጉብታ፥ ዛፍና ቁጥቋጦ የለም። በተንጣለለ ሜዳ ላይ፣ ግሎ ግለቱን መልሶ ይመልሳል። በዚህ መካከል እስከ ቀትር ድረስ ከተጓዙ በኋላ መቀጠል አልቻሉም።

የቀትሩ ሐሩር በረድ እስኪል፥ ብዚያ ገላጣ በረሃ ውስጥ እንደ ብቸኛ ዘብ ሆኖ በተገኘ የግራር ዛፍ ሥር አረፍ አሉ። ዛፉ በቀጥታ ከላይ ከሚወርደው የፀሐይ ጨረር በመጠኑ ይከልላቸው እንጂ ከመሬት የሚፈላው ሙቀት ገላ ይለበልባል። እሳት ውስጥ ተወልዶ ያደገ ይመስል ሐሩሩ እምብዛም የማያስጨንቀው ባለ ግመል ከሁለቱ ሴቶች ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ተቀምጦ ጫት ያኝካል። ግመሎቹ ተጠጋግተው ቆመዋል። ማምሻውን ጅቡቲ ጠረፍ እንደሚደርሱ ባለ ግመሉ በተኮላተፈ አማርኛና በእጅ ምልክት ስለ ነገራቸው ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ወይዘሮ ሸዋዬ እንደ መዝናናት ብለው ድካሙም ወበቁም እንደ ሰመመን ወሰድ መለስ ያደርጋቸዋል።

መጀመሪያ የጣሪያ ቆርቆሮ በድንጋይ ሲደበደብ እንደሚያሰማው የሚመስል ድምፅ አልፎ አልፎ፥ በሩቁ ተሰማ። ባእል ግመሉም ግመሎቹም

አንገታቸውን ቀና አደረጉ። ለአጭር ጊዜ ተቋረጠና ሲቀጥል እየቀረበ እየበረከተ መጣ። ጧጧጧ! ዱ - ዱዋ ጧ! ጧ! ጧጧጧ!› የተኩስ ድምፅ ነበር።

«ምንድን ነው እሱ? » ሲሉ ወይዘሮ ሸዋዬ በጭንቀት ጠየቁ።

«ወያ የሶማል ቶር - ወያ የጉምሩክ! » አለና የጐረሰውን ጫት ቱፍ ብሎ ከተቀመጠበት ተነሣ። ግመሎቹ እንደ መቁነጥነጥ አሉ።

ለማሰላልሰም፥ ዘዴም ለመፈለግ ፋታ አልሰጣቸውም። የጠመንጃ የመትረየስ የአዳፍኔ፥ ተኩስ ዙሪያውን ያስተጋባ ጀመር። ከሩቅ አቧራ ሲነሣ እንጂ የሰው እንቅስቃሴ አይታይም ነበር። ተኩሱም እየቀረበ መጥጦ አንድ አዳፍኔ ድንገት እንደ ፈነዳ እሳተ ጐመራ መሬቱን ገልብጦ ወደ ሰማይ ሲያስነሣውና ድምፁ አካባቢውን ሲያደባልቀው ግመሎቹ ሽምጥ ጋለቡ። ባለ ግመሉም ተከትሎዋቸው ሮጠ። ይህ ሲሆን ሁለቱ ሴቶች በሚገባ አላስተዋሉም ነበር። ከድንጋጤና ከፍርሃታቸው የተነሣ የማያስቡ በድን ሆነው ነበር። እርስ በርሳቸው ተቃቅፈውና የግራርን ግንድ አቅፈው እየተንቀጠቀጡ ኩርምት አሉ። ተኩሱ አንድ ሰዓት ያህል እንደ ቆየ ቀስ እያለ እየቀነሰና እየራቀ ሄደ። በመጨረሻም ከናካቴው ቆመ። ባለ ግመሉና ግመሎቹ ግን አልተመለሱም።

ሁለቱ ሴቶች መናገር አቅቷቸው፥ የሚነጋገሩት ጠፍቷቸው ኩርምት እንዳሉ ለረጅም ጊዘ ዝም ብለው ቆዩ። «ሰውዬው መጥፋቱ አንቺ? » የዘርፈሽዋል አነጋገር ጣዕር የሚመስል ነበር።

«ወይ ጉዳት ደርሶበታል - ወይ? » አሉ ወይዘሮ ሸዋዬ የመልሱ አጨራረስ ጠፍቷቸው።

«ታዲያ ከዚህ ቁጭ ብለን የአውሬ ራት እንሁን እንዴ? እንሂድ እንጂ » አሉ ወይዘሮ ሸዋዬ ሁለቱም በዝምታ ተውጠው ለረጅም ጊዜ ከቆዩ በኋላ።

«የት አባታችን ብለን ሸዋዬ? »

«በዚሁ ፊት - ለፊታችን » ወይዘሮ ሸዋዬ በጃቸው አመለከቱ። «ጥቂት ነው የቀረን ብሎን ነበር። »

ለመለያየት የፈሩ ይመስል ተደጋግፈው ተነሡና የእግሩን መንገድ ተያያዙት። ግን ብዙም ሳይገፉ ሰውነታቸው በሐሩሩና በድካሙ እየዛለ ሄደ። በተለይ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ያን ግዙፍ ገላቸውን እንደሚንከባለል ቋጥኝ ወደ ፊት መግፋት ሲሳናቸው እግራችው ከአሸዋው ውስጥ ዝፍቅ - ዝፍቅ እያለባቸው

ወደ ኋላ መጐተት አመጡ። አንድ አራት ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ምንም እንደ ተጓዙ እግራቸውን ማንሣት አቃታቸው።

«ጭንና ጭኔ ተላልጦ አላንቀሳቅስ አለኝ አሉ እግራቸውን አምቡዋትረው ጫን ጫን እየተነፈሱ። ሳይታወቃቸውም እንደ ሕፃን ልጅ ከአሸዋው ላይ ዘርፈጥ ብለው ተቀመጡና ከግንባራቸው የሚወርደውን ላብ በጨርቃቸው እየጠረጉ፣ ዐይናቸውን ከማዶው አድማስ ላይ ተከሉ። «አንቺ ሸዋዬ! ባሕር ይታይሻል? » ሲሉ በመደነቅ ጠየቁ።

«ገና ጅቡቲ ሳንገባ ባሕር ከየት አርጎ መጣ? » አሉ ወይዘሮ ሸዋዬም የሚያይትን ማመን አቅቷቸው።

«ከዚያ ወስዶ ማን በነከረኝ! » ሲሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ዐይናቸውን ከማዶው ላይ በጉጉት እንደ ተከሉ ቁጭ ብለው ቆዩ። ባሕር የመሰለው ሰማያዊ ነገር የበረሃ ሐሩር ነጸብራቅ ኅብረ - ማይ (ሚራዥ) መሆኑን አላወቁም።

ወዲያው ባሕር ከመሰለው ኅብረ - ማይ አግጣጫ በርከት ያሉ አሞሮች ጨረሩን እየሰጠነቁ መጡና ሁለቱ ሴቶች በተቀመጡበት አካባቢ አየር ላይ እክፍና ዝቅ እያሉ ያንዣብቡ ጀመር። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ይህ ነው የማይባል የፍርሃት ሠቀቀን ድንገት ወረራቸው። በሕይወት እንዳሉ አሞሮቹ ዐይናቸውን የሚያወጡባቸው ይመስል ጭፍን አደረጉት።

## ፱

የደሴው ሆስፒታል ሐኪም ካሣሁንን የመጨረሻ ማጣሪያ ምርመራ ካደረገለት በኋላ «ከዚህ እንግዲህ አልጋ ማጣበብ እንጂ የሚጨምርልህ ነገር የለም። መውጣት ትችላለህ » አለው።

ካሣሁን ስለ ተደረገለት እርዳታ አመስግኖ ከመሰናበቱ በፊት «እንዲያው - እንዲያው አንድ አንድ ነገር » ሲል መናገር ጀመርና አቋርጦ ተወው።

«የሚቸግርህ ነገር አለ? » አለ ሐኪሙ ካሣሁንን የመጓጓዛ ገንዘብ የጠየቀ መስሎት እጁን ወደ ኪሱ እየከተተ።

«ኧረ ምንም ችግር የለብኝም! » በማእልት ካሣሁን አስተባበለ። ግን አሁንም በመሄድና በመናገር መካከል ዋለለ።

«ጉዳይ ካለህ ንገረኝ » አለ ሐኪሙ ቦርሳውን አውጥቶ በእጁ እንደ ጨበጠ። ካሣሁን የሐኪሙን ሐሳብ ገባውና «ገንዘብ መጠየቁ አልነበረም » ሲል አስታወቀ።

«ሌላ ጉዳይም ቢሆን ንገረኝ። »

ካሣሁን ማመንታቱና በሐፍረት መጨነቁ ከፊቱ ላይ ይነበብ ነበር። «እስቲ ቁጭ በል። መናገር የምትፈልገው ጉዳይ እንዳለ ይሰማኛል። ግን ታቅማማለህ። ለምን? አየህ ከንሰሐ አባትና ከሐኪም የሚደበቅ ነገር የለም ይባላል። ስለዚህ አትፍራ ንገረኝ » ሲል አባበለው።

ካሣሁን አንገቱን ደፋ አድርጎ ጥቂት አሰበ። በፊትም ቢሆን ችግሩን ለሐኪሙ ማዋየት ፈልጎ ከራሱ ጋር ብዙ ተሟግቶ ነበር። ‹ገበናን ማውጣት እንጂ ምን ዋጋ አለው? ግን ማን ያውቃል መድኃኒት ይኖር ይሆናል። ከስንት በሽታ ይዳን የለ? በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም ተብሏል። ግን፤ እንዲህ ያለውን ጉድ እንዴት ብለው ለሰው ይነግሩታል? › ሲል ሐሳቡን ከሁለት ከፍሎ ይከራከርበታል። ሐኪሙ በመንግሥት ተቀጥሮ እንደሚሠራ ሳይሆን እንደ ቅርብ ዘመድ እንደ ጥኑ ወዳጅ ከልቡ ያከመውና ያስታመመው መሆኑን ሲያስብ ደግሞ ለመናገር ይቃጣዋል። በሰው ልጆች ሥቃይ አብሮ የሚሠቃይ የሚመስለው የአዘኔታ አስተያየት ሳይቀር ምሥጢር እንዲያካፍለው የሚገፋፋ ነው። ይህም ሆኖ መድፈር አቅቶት ነገር ሳልስት ሲል የመሰናበቻ ሰዓቱ ድንገት ደረሰ። ከዚህ በኋላ ሌላ ዕድል እንደማያገኝ ተሰማው። ግን፥ አሁንም ቢሆን ደፍሮ መንገር ተቸገረ። ጥፍሩን በጥፍሩ እየቀነጣጠበ አንድ ዓይነት ጉድፍ እንደሚፈልግ እጆቹን ሲያስተውል ቆየና «ኧረ እንዲያው ዝም ብዬ ነው እንጂ ለመንገርም የሚያመች አይደለም » አለ በመጨረሻም።

«እንዳልኩህ ሐኪም የሰውን ሰውነት ሙሉ እርቃኑን ከዚያም አልፎ በመሣሪያ አማካይነት ውስጥ እቃውን ሁሉ የሚመረምር በሽታን ሕመምን በሚመለከት ከእርሱ የሚደበቅ ነገር የለም። ሊኖርም አይገባም። ሌላ ሰው እንዲያውቅበህ የማትፈልገው ነገር ከሆነ ግዴለህም ምሥጢርከን ከሆዴ ውስጥ ቀብሬ ነው ራሴው መቃብር የምወርደው። » ሐኪሙ በእነዚያ አጽናኝና አስተዛዛኝ ዐይኖቹ ትክ ብሎ እየተመለከተ ጠበቀው።

«እንዲያው ታሪኩን እንዴት ጀምሬ እንዴት እንደምጨርሰምኮ ግራ ሆነብኝ! » ሲል ካሣሁን እጁን አራገበ።

«እንደ መስለህ ጀምርና ጨርሰው። ቅድም እንዳልኩህ ከንስሐ አባትና ከሐኪም የሚደበቅ ነገር የለም። እና እስቲ ለአንድ ለልብ ጓደኛህ ወዳጅህ እንደምታዋየው እንደ መጣልህ አውጋው » ሲል ሐኪሙ አሁንም በአስተያየቱ አቆላመጠው።

ካሣሁን እንደ ምንም ዐረፍተ ነገሩ ከአፉ ከወጣለት በኋላ ሳይታወቀው ከአንደበቱ ይወርድ ጀመር። የሚናገረው እንደ መጣለት እንጂ በማሰላሰል ባይሆንም፥ ለሐኪሙ የታሪኩ ሂደት የተያያዘና ግልጽ ነበር። ካሣሁን፥ ከዳገታማ አፈርሳታ እልቂት አንሥቶ፥ በእሥር ቤት የደረሰበትን የምርመራ ጉዳት ከረጅም ጊዜ መለያየት በኋላ ከዘይኔ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻቸውን በአንድ ቤት አድረው በመካከላቸው የተፈጠረውን ሁናቴ፣ በቆሬ ያሳለፈውን የውርደት የፈተናና የጭንቀት ጊዜ ተርኮ ሲጨርስ በሐፍረት አንገቱን አቀረቀረ።

«እና ከዚያ የመጀመሪያ ጊዜ በኋላ እንደ ገና አልሞከርከም? ወይም አልተቀራረባችሁም? » ሲል ሐኪሙ ጠየቀ። ካሣሁን በአሉታ ራሱን ነቀነቀ።

«ይገባኛል » አለው ሐኪሙ ራሱን ላይና ታች በማወዛወዝ «አዎ፥ ያው የሚደርስ እየመሰለህ ድጋሚ እንዳትዋረድ ትፈራለህ። ግን የመጀመሪያ ጊዜ ገመምተኛ ስለነአብርክ ድካም ተሰምቶህ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ምርመራው ባደረሰብህ ጉዳት ጥርጣሬ አድሮብህ ስለ ነበር ሰውነትህ ተሸማቅቆ ሊሆን ይችላል። ታዲያ ይህ ሁሉ የአካል ጉዳት ነው ማለት ይችላል። ታዲያ ይህ ሁሉ የአካል ጉዳት ነው ማለት አይደለም። እስቲ ለሁሉም ዛሬን ዋልና ምርመራ ላድርግልህ።

ሐኪሙ ምርመራውን ከጨረሰ በኋላ ካሣሁንን ወደ ቢሮው ጠራውና እንዲቀመጥ ጋበዘው። ከዚያም ልዩ ልዩ የቪታሚን መድኃኒት ቢልቃጦች ከጠረጴዛው ላይ እያስቀመጠ ለአጭር ጊዜ በዝምታ አስተዋለው። ካሣሁን ለመስማት ተቻኮለ። «እህስ? » ብሎ ለመጠየቅም ከጀለውና ‹ሰባት ዓመት የታወረ ሰው አንድ ቀን እደር ቢሉት እንዴት ብዬ አለ ይባላል› የሚባለው ምሳሌ ትዝ ብሎት ራሱን ታዘበ።

«የምርመራው ውጤት እንደሚያሳየው በአካልህ ላይ ምንም ጉዳት የለብህም። የአካላትህ ሕዋሳቶች በደንብ ይሠራሉ። የተዛባ ወይም የተቃወሰ ነገር የለም » ሲል ሐኪሙ ምክሩንና አስተያየቱን ቀጠለ። «ግን እንዳተ ያለው ችግር በአካል ጉዳትና ሕመም ብቻ የሚመጣ አይደለም። ብዙ ጊዜ ከአስተሳሰብና ከጭንቀት - ከፍርሃት የሚመጣ ነው። ማንም ሰው አንድ ጊዜ

ላይሆንለት ይችላል። ግን ለሚቀጥለው ጊዜ እንደዚያ እሆናለሁ ብሎ ያለማቋረጥ ካሰበ ሰውነቱ እየተሸማቀቀ ይብስበታል እንጂ አይሻለውም። በኃይል እንተን ማድረግ አይቻልም። ወይም ደግሞ አንድ ሰው መልካም ፈቃዱ ስለሆነ ብቻ አይሆንለትም » ሐኪሙ እንደ መሣቅ አለ። «ወንድ በተፈጥሮው ስሜቱ ሲነሣ ብቻ የሚሆን ነው። አንድ ወንድ ደግሞ አንዲት የሚያፈቅራት ሴት ስትስመው ስትነካው ስታሻሽው ስትዳራው ተፈጥሮው ነውና፥ ስሜቱ እንደሚነሣሣ ራስህንም የምታውቀው ነው። ነገር ግን ከዚያ የመጀመሪያ ቀን በኋላ ያው የሚደገም እየመሰለህ ራስህን ተፈጥሮህን ሌላ ዕድል ሳትሰጠው ብዙ ዓመት ቆየህ። ሳትረሳውስ ትቀራለህ » ሲል ሐኪሙ በቀልድ ሣቀ። «እና መድኃኒቱ የተዝናና ከፍርሃት ነጻ የሆነ አቀራረብ ነው። ከዚህም በቀር የሚፋቀሩ ባልና ሚስት በጋራ ሊደሰቱ የሚችሉባቸው ብዙ ዓይነት የፍቅር ጨዋታዎች አሉ። »

ካሣሁን ባንድ በኩል ተስፋ ሲያድርበት በሌላ በኩል ስለ ሥነ ልቦና ትንተና ሐኪሙ የሚነግረው እንቆቅልሽ ስለሆነበት አገጩን በመዳፉ ላይ አስደግፎ በጥያቄ መልክ ግንባሩን ሸብሽብ ዐይኑን ጨንቁሮ አደረገ።

«ምን ይቀባዥራል እንደምትል ይገባኛል » አለ ሐኪሙ በማዳነቅ፤ «አዎ መስበክ መምከር ቀላል ነው። ሕይወት ግን በጣም ውስብስብ ነው። ተፈጥሮ ገና ቅንጣት ያህል ኣያልታወቀ ምሥጢር ነው። ስለዚህ አሁን እኔ ለምሳሌ ተዝናና፣ ተዝናና፤ አትፍራ አትፍራ፤ እያልኩ ብጮህ እንድትዝናና ማድረግ አልችልም። አንተም ብቻህን አልፈራህ እያልክ ብትፎክርም አትችልም። የሁለት ጾታዎችን ትብብር ይጠይቃል ማለት ነው »። ሐኪሙ ካሣሁን የበለጠ ጋራ መጋባቱን ተገንዝቦ አነጋገሩን ለወጠ። «የእኛ የሐኪሞች ቋንቋ አስቸጋሪ ነው። የአልኩት ሁሉ ለጊዜው ተወውና እስቲ ሂደህ ሚስትህን ይዘሃት ና። እሷንም ልምከራት። መቸም ነገሩ ለእርሷ ምሥሪር አይደለም። በሀገራችን አነጋገር ዐይነ ጥላ መግፈፍ ሊሆን ይችላል። የአንተ ሐፍረት ዓይነ ጥላ የእርሷ የማፈር ዓይነ ጥላ። የእናት አገር ጥሪ እዘምታለህ ብለሃል። እንግዲያው ከዚያ በፊት አብራችሁ ብትመጡ መልካም ነበር። ወንድ ልጅ ጦርነት ሲሄድ ዘር ትቶ እንዲሄድ አባቶቻችን ይመከራሉ። ትውልድ እንዲተካ ሲሉ። ከእነዚህ መድኃኒቶች ከእያንዳንዱ ብልቃት በቀን አንዳንድ ዋጥ። ለገመምተኛ ብርታ የሚሰጡ ናቸው። »

በእጅ ሰላምታ ተሰነባበተው ካሣሁን ሊወጣ ሲል «ለመሆኑ አደጋ ያደረሰብህን በሽተኛ ታውቀው ነበር? » ሲል ጠየቀው።

ካሣሁን እንደ መወራጨት ያህል በአሉታ ራሱን በኃይል ነቀነቀ። ለምን እንደ ካደ ለራሱም አልገባውም። ብቻ በእውን እንዳልደረሰ ቅዠት ለመቁጠርና ለመርሳት ፈለገ። አሁን ማሰብ የፈለገው ሐኪም ስላሳደረበት አዲስ ተስፋ ነበር። ይህንን ተስፋ ቋጥሮም ወደ ቆሬ ተመለሰ። ሥቀቀኑን በእናት አገር ጥሪ ዘመቻ ሊከላ።

ካሣሁን ቆሬ ሠፈሩ ሲደርስ ራሷን ተላጭታ ወይባ ለብሳ ከቤቱ ታዛ ቁማ እንዳያት ወዲያው ገባው። ስለ ጐበዝ መጨረሻ ጠይቆ አላረጋገጠም። መጨረሻውም ምን እንደሚሆን ማመቅም አልፈለገም። ግን መርዶው ከእርሱ ቀድሞ ይደርሳታል ብሎ አላሰበም ነበር። መርዶውን ለመጋራት አንድ እጁን፥ እያራገበ ሌላ እጁን ወደ ፊት ዘርግቶ፥ «ወይኔ ወንድሜ! ወይኔ ወንድሜ! »እያለ በመጮህ ወደ ዘይኔ ሲያመራ እርሷም «ወንድም ዓለም! ወንድም ዓለሜ! » በማለት ለቅሶዋን እያቀለጠች ከአንገቱ ላይ ተጠመተመች። ስለ ራሱ ስለ ዘይኔ፥ ስለ ጐበዜ ሞት ይሁን ኀዘኑ ለይቶ ሳይታወቀው ጉንጭ ለጉንጭ እንደ ተጋጠሙ ዕንባቸው አብሮ ይወርድ ጀመር። ሌላ አልቃሽ ሳይኖራቸው ብቻቸውን ነበሩ። የዶክተሩ ተስፋ ሊሆን ይችላል። ዘይኔ ራሷን ተላጭታ ወይባ ለብሳ በወንድም ሞት ሥቀቀን ተመትታ ሲያይት በሁናቴዋ ልዩ ውበት የተጐናጸፈች የሚመስል ስሜት አሳድሮበትም ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በሀገሬው ባሕል አንገት ለአንገት ተናንቀው ሲጠጋጋ እንደዚህ ገላቸው ሲተሻሽ የመጀመሪያ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ብቻ ከወገቡ በታች ሕይወት ሲዘራ ተሰማው። «ወይ ፈጣሪ ይህንን አሁን ምን ይሉታል? » ሲል ራሱን ታዘበው - በለቅሶ መካከል።

«ወንድም ዓለሜ ተቀጨ እኮ፤ ካሡ ብቻችንን ቀረን እኮ! » እያለች ከአንገቱ ላይ ተጠምጥማ ልቅሶዋን ቀጠለች። ካሣሁንም የሕይወት ዝራቱ ይበልጥ እየተሰማው ሄደ። ፍሬ ትቶ የመዝመት ተስፋ እንዳለው ታወቀው። ትከሻ ለትከሻ እንደ ተደጋገፉ ወደ ቤት ገቡ።

**ተፈጸመ።**



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ብርሃኑ ዘርይሁን በ1925 ዓ.ም በጎንደር ከተማ ተወለዱ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቤተክርስትያን ትምህርት ተምረዋል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጎንደር ይገኝ በነበረው በቀድሞው ቀዳማዊ ሃይለሥላሴ ትምህርትቤት አጠናቀቁ፡፡ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በተግባረ እድ ትምህርት ቤት በሬዲዮ ቴክኒሺያንነት ሙያ ተመረቁ።

ሥራ የጀመሩትም በመምህርነት ነው። በወቅቱ በካርታ ሥራ ድርጅት ቴክኒሺያንነት ሙያ ሠርተዋል። ከዚያም የጦር ሚኒስቴር እየተባለ ይጠራ በነበረው የአሁኑ መከላከያ ሚኒስትር በአስተርጓሚነት አገልግሏል። ማስታወቂያ ሚኒስትር እንዲዛወሩ ከተደረገ በኋላ የኢትጵያ ድምጽ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነዋል። ከሶስት አመት በኋላ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው የማይረሳ ተግባር አከናውነዋል።

ብርሃኑ ዘርይሁን የደረሱት ‹ሞረሽ› በ1972 ዓ.ም፤ ‹ጣጠኛው ተዋናይ›በ1975 ዓ.ም እና ‹አባደፋር› በ1977 ዓ.ም፤ የተባሉት ቴያትሮቻቸው ተወዳጅ ነበሩ።

ከጻፏቸው መጻሕፍት ውስጥም ‹የቴዎድሮሥ እንባ › በ1958 ዓ.ም፤ ‹የእንባ ደብዳቤዎች› በ1961 ዓ.ም እና የታንጉት ምሥጢር› በ1978 ዓ.ም፤ እንዲሁም ለረጅም ተከታታይ ጊዜያት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ሲተረኩ የነበሩት ‹የአብዮት ዋዜማ፤የአብት መባቻና የአብዮት ማግስት› የተሰኙት ማጸሐፍት ይገኙበታለል።

ብርሃኑ ዘርይሁን ለሐገራቸው የስነ ጽሁፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አበርክተዋል። በቀዳሚዎቹ ዘመናት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበርን በሥራ አመራር አባልነት ካገለገሉት መካከል አንዱ ብርሃኑ ናቸው።

**ምንጭ:** የኢትዮድያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ማእበል የአብዮቱ ዋዜማ(**ልብወለድ**)
2. የአብዮቱ መባቻ(**ልብወለድ**)
3. የእንባ ደብዳቤዎች(**ልብወለድ**)
4. የቴዎድሮስ ዕንባ(**ልብወለድ**)
5. ድል ከሞት በኋላ(**ልብወለድ**)
6. የበደል ፍጻሜ(**ልብወለድ**)
7. ጨረቃ ስትወጣ(**ልብወለድ**)
8. የአብዮት ማግስት(**ልብወለድ**)
9. የታንጉት ምስጢር(**ልብወለድ**)
10. ሞረሽ(**ተውኔት**)
11. ባልቻ አባነፍሶ(**ተውኔት**)
12. ጣጠኛው ተዋናይ(**ተውኔት**)
13. ብር አምባር ሰበረልዎ(**ልብወለድ**)
14. አማኑኤል ደርሶ መልስ(**ልብወለድ**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY